

አጋጣሚ አይደለህም፡፡ ዓለማት ሳይፈጠሩ እግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ስለነበርክ፣ ለዓላማዎቹ አቀድህ፡፡ እነዚህ ዓላማዎች ጥቂት ከሆነው ዕድሜህ እጅግ እርቀው የሚሄዱ ናቸው፡፡ ለዘላለም ነው የተፈጠርከው!

የግል ጥረትን የሚያበረታቱ መጻሕፍት፣ የሕይወትህን ትርጉምና ዓላማዎች ከውስጥህ ፈትሸህ እንድታገኝ ያሳስቡሃል፡፡ የዓላማ መር መጽሐፍ ደራሲ ግን ይህ ከተሣሣተ ሥፍራ መጀመር ነው ይላሉ፡፡ ፈጣሪህ ከሆነው እግዚአብ ሔር፣ እና አንተን ከፈጠረበት ምክንያት ነው መጀመር ያለብህ፡፡ በእግዚአ ብሔርና ለእግዚአብሔር ነው የተፈጠርከው፤ ይህን እስካልተገነዘብክ ድረስ ሕይወት ትርጉም የለሽ ትሆንብሃለች፡፡ ይህ መጽሐፍ፣ በሕይወት የምትኖረው ለምን እንደሆነና እግዚአብሔር እዚህና አሁን፣ እንዲሁም ለዘላለም ለአንተ ያለውን አስደናቂ እቅድ እንድትገነዘብ ይረዳሃል፡፡

ለምንድነው የተፈጠርኩት? ለሚለው የሕይወት ዋና ጥያቄ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ትችል ዘንድ ይህ መጽሐፍ በቀጣዮቹ 40 የግል የንባብ ቀናት ወቅት ይመራሃል፡፡ እግዚአብሔር ለምን እንደፈጠረህ ማወቁ ሥጋትን ይቀንስልሃል፣ ኃይልህን እንዳታባክን ያደርግሃል፣ ውሳኔዎችህን ዘና ያደርጋቸዋል፣ ለሕይወትህ ትርጉም ይሰጠዋል፣ እና ከሁሉም ይልቅ ለዘላለም ሕይወት ያዘጋጅሃል፡፡

ሪክ ዋረን

# ዓላማ መር ሕይወት

ኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ
Evangelical Theological College
Addis Ababa (Ethiopia)
1997/2005

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
"The Purpose Driven Life"
By Dr. Rick Warren
Copyright@2002 by Rick Warren,
Zondervan, Grand Rapids, Michigan 49530
ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን፣ የታተመውም
በደራሲው ፈቃድ ነው::

በኢቫንጀሊካል ቴዎሎጂካል ኮሌጅ ተተርጉሞና ተዘጋጅቶ ታተመ::
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ::

**Publisher**

Evangelical Theological College

Addis Ababa, Ethiopia

1997/2005

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው::

ሦስተኛ እትም
3rd Edition

ይህ መጽሐፍ ለአንተ አክብሮት የዋለ ነው፡፡
ከመወለድህ በፊት እግዚአብሔር *ይህን ጊዜ* በሕይወትህ ወስነው፡፡ ይህ መጽሐፍ እጅህ የገባው በአጋጣሚ አይደለም፡፡ የተፈጠርክበትን ዓላማ ትገነዘብ ዘንድ እግዚአብሔር *በጥብቅ ይፈልጋል*፤ በምድር ላይ፣ በዘላለም ውስጥም፡፡

*ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፡፡*

ኤፌሶን 1፥11

ሕይወቴን የቀረፁትና እነዚህን እውነቶች እንድማር የረዱኝ፣ በመቶ የሚቆጠሩ ቀደምትና የዘመናችን ጸሐፍት እንዲሁም መምህራን ባለውለታ ዎቼ ናቸው፡፡ እነዚህን እውነቶች ለአንተ ለማካፈል ዕድል በማግኘቴ እግዚአብሔርን፣ እንዲሁም አንተን አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫዎች




ዓላማ ያለው ጉዞ 9

ቃልኪዳኔ 13

ለምንድነው የተፈጠርኩት 15

1ኛ ቀን የሁሉም ጀማሪ እግዚአብሔር ነው 17

2ኛ ቀን አጋጣሚ አይደለህም 23

3ኛ ቀን ሕይወትህ የሚመራው በምንድነው 28

4ኛ ቀን ለዘላለም ሕይወት ተፈጥረሃል 38

5ኛ ቀን ሕይወትን ከእግዚአብሔር እይታ አንፃር መመልከት 44

6ኛ ቀን ሕይወት ጊዜያዊ ሥራ ነው 51

7ኛ ቀን የሁሉም ነገር ምክንያት 57

ዓላማ ቁጥር 1፣ ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ነህ 65

8ኛ ቀን ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ነህ 67

9ኛ ቀን እግዚአብሔርን ፈገግ የሚያሰኘው ምንድነው? 73

10ኛ ቀን የአምልኮ ልብ 82

11ኛ ቀን የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጆች መሆን 91

12ኛ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነትህን ማሳደግ 99

13ኛ ቀን እግዚአብሔርን የሚያስደስት አምልኮ 107

14ኛ ቀን እግዚአብሔር የራቀ ሲመስል 115

ዓላማ ቁጥር 2፣ የተበጀኸው ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ነው 123

15ኛ ቀን ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተበጅተሃል 125

16ኛ ቀን ዋናው ነገር 131
17ኛ ቀን የመገኛ ሥፍራ 138
18ኛ ቀን ሕይወትን በጋራ መኖር 147
19ኛው ቀን ህብረትን ማሳደግ 154
20ኛው ቀን የፈረሰ ህብረትን ማደስ 162
21ኛው ቀን ቤተክርስቲያንህን መጠበቅ 170
ዓላማ ቁጥር 3 ክርስቶስን ለመምሰል ነው የተፈጠርከው 180
22ኛው ቀን ክርስቶስን ለመምሰል ተፈጥረሃል 182
23ኛው ቀን እድገታችን 190
24ኛው ቀን በእውነት መለወጥ 196
25ኛው ቀን በችግር መለወጥ 205
26ኛው ቀን በፈተና ውስጥ ማደግ 213
27ኛው ቀን ፈተናን ማሸነፍ 220
28ኛው ቀን ጊዜ ይወስዳል 229
ዓላማ ቁጥር 4፣ የተበጀኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው 237
29ኛው ቀን የተሰጠህን ሥራ መቀበል 239
30ኛ ቀን የተበጀኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው 247
31ኛ ቀን መልክስልህን (ቅርጽህን )መረዳት 254
32ኛ ቀን እግዚአብሔር በሰጠህ መጠቀም 263
3ኛ ቀን የእውነተኛ አገልጋዮች ፍሬ 271
34ኛ ቀን እንደአገልጋይ ማሰብ 279
35ኛ ቀን የእግዚአብሔር ኃይል በድካምህ ውስጥ 286
ዓላማ ቁጥር 5 የተሠራኸው ለተልዕኮ ነው 294
36ኛ ቀን የተሠራኸው ለተልዕኮ ነው 396
37ኛ ቀን የሕይወት መልእክትህን ማካፈል 304
38ኛ ቀን ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን መሆን 312
39ኛ ቀን የሕይወትህን ሚዛን መጠበቅ 321
40ኛ ቀን በዓላማ መኖር 328
ተቀጥላ 338

# ዓላማ ያለው ጉዞ



## በዚህ መጽሐፍ በሚገባ ለመጠቀም

ይህ መጽሐፍ «ለምንድነው የተፈጠርኩት? » ለሚለው የሕይወት ዋና ጥያቄ መልስ ታገኝ ዘንድ ወደሚረዳህ የ40 ቀን መንፈሳዊ ጉዞ ይመራሃል:: በመሆኑም፣ ከሌሎቹ መጻሕፍት የላቀ ተልዕኮ አለው:: መጽሐፉ ውስጥ በምታደርገው ጉዞ ፍጻሜ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ትገነዘባለህ:: የተለያዩት የሕይወትህ ክፍሎች ሁሉ እንዴት እንደሚያያዙ ስለምትገነዘብ የሕይወት ሙሉ ስዕል ይኖርሃል:: ይህ ግንዛቤ፣ ጭንቀትህን ይቀንሳል፣ ለሁኔታዎች የምትሰጠውን ውሳኔ ቀላል ያደርገዋል፣ እርካታን ይጨምርልሃል፤ ከሁሉም ይልቅ ለዘላለም ሕይወት ያዘጋጅሃል::

## ቀጣዮቹ 40 ቀኖችህ

ዛሬ በበለፀጉ አገሮች ያለው ዓማካይ የሰው ዕድሜ 25550 ቀን ይሆናል:: ጤንነቱ የተሟላ ሰው የሚኖረው ዕድሜ ይህ ነው:: ታዲያ ከነዚህ ቀናት ውስጥ በ40ዎቹ፣ እግዚአብሔር ምን እንድታደርግባቸው እንደሚፈልግ ለማወቂያነት ብትገለገልባቸው ብልህነት አይደለምን?

እግዚአብሔር 40 ቀናትን ጠቃሚ የመንፈሳዊ ወቅት አድርጎ የሚመለከታቸው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያስገነዝባል:: እግዚአብሔር አንድን ሰው ለዓላማው ሲያዘጋጅ 40 ቀናትን ይወስድ ነበር::

- የኖህ ሕይወት፣ በ40 ቀናት የዝናብ ወቅት ተለውጧል::
- ሙሴ የተለወጠው፣ ሲና ተራራ ላይ ለ40 ቀናት በቆየበት ወቅት ነው::
- ሰላዮች የተለወጡት፣ ተስፋይቱ ምድር ውስጥ ለ40 ቀናት በመቆየታቸው ነበር::
- የዳዊትን ሕይወት የለወጠው፣ 40 ቀናት የቆየው የጐልያድ ተግዳሮት

ነው።

* ኤልያስ የተለወጠው፣ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ምግብ ለ40 ቀናት የሚሆን ብርታትን በሰጠው ጊዜ ነበር።
* የነነዌ ከተማ የተለወጠችው፣ ሕዝቦቿ ንስሐ ይገቡ ዘንድ እግዚአብሔር 40 የለውጥ ቀናትን ስለሰጣቸው ነው።
* ኢየሱስ ክርስቶስ፣ 40 ቀናት ምድረበዳ ውስጥ በመቆየት ኃይልን ተሞላ።
* ደቀ መዛሙርት የተለወጡት፣ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ 40 ቀናት አብሯቸው በመቆየቱ ነው።

ቀጣዮቹ 40 ቀናት *ሕይወትህን* ይለውጡታል።

ይህ መጽሐፍ በ40 አጫጭር ምዕራፎች ተከፋፍሏል። በቀን አንድ ምዕራፍ ብቻ እንድታነብ ነው የማሳስብህ። ይህን ስታደርግ፣ የምታነበው ነገር ለሕይወትህ የሚኖረውን እንደምታ *ታሰላስል* ዘንድ በቂ ጊዜ ይኖርሃል። «*መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍፁም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም ስትምሰሉት*» ሮሜ 12፥2፣ ይላል መጽሐፍ ቅዱስ።

የምናነባቸው ብዙ መጻሕፍት ሕይወታችንን ሊለውጡት ከማይችሉባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ የመጽሐፉን ቀጣይ ምዕራፍ ለማንበብ ከሚኖረን ጉጉት የተነሣ፣ ለጥቂት ጊዜ ቆም አድርገን ያነበብነውን ክፍል በሚገባ ስለማናሰላስል ነው። ያን ከማድረግ ይልቅ ቀጣዩን እውነት ለማወቅ እንቸኩላለን።

ይህን መጽሐፍ እንደዋዛ *አታንብበው*። በጥንቃቄ *አንብበው፣ አሰላስለው*፣ ከሥሩም አስምርበት። አሳቦችህን ህዳጉቹ ላይ ጻፍ፤ በአጠቃላይ መጽሐፉን የራስህ፣ የግልህ አድርገው። በጣም የጠቀሙኝ መጻሕፍት ያነበብኳቸው ሁሉ ሳይሆኑ፣ ከላይ በተገለጠው አካኋን በትኩረት ያጠናኋቸውና ያሰላሰልኳቸው ናቸው።

## የሚረዱህ አራት አሳቦች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ፣ «ስለ ዓላማዬ ሳስብ» የሚል ክፍል አለ። ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አራት አሳቦች እዚያ ታገኛቸዋለህ፤

* ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:- ይህ ዓላማ ያለው ሕይወት አኗኗርህን በአጭሩ የሚገልጥ ጠቃሚ እውነት ስለሆነ፣ ቀኑን ሙሉ ልታሳላስለው

ትችላለህ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲህ ብሎታል፡- «እኔ *የምለውን ልብ በል፤ ጌታም በሁሉም ነገር ማስተዋልን ይሰጥሃል»* 2ጢሞ. 2÷7።

- **ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** ይህ፣ ከምዕራፉ ውስጥ አንድን እውነት የሚያስተምርህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው። በእርግጥ ሕይወትህን ለማሻሻል ከፈለግህ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ከሁሉ የላቀና ልትጀምረው የሚገባ ልማድ ነው። የምታጠናቸውን ጥቅሶች በሚገባ ለማስታወስ፣ ካርዶች ላይ መዝግበህ በመያዝ ወይም በሌላ ዘዴ ለመጠቀም ትችላለህ።
- **ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** እነዚህ ጥያቄዎች፣ ያነበብካቸው ክፍሎች ያላቸውን መልእክትና፣ መልእክቱ ከግል ሕይወትህ ጋር የሚዛመድበትን ሁኔታ እንድታሰላስል ይረዱሃል። ለጥያቄዎቹ ያሉህን መልሶች፣ በዚህ መጽሐፍ ህዳጎች ላይ፣ በማስታወሻ ወይም ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ መመዝገቢያ ላይ ታሠፍራቸው ዘንድ አበረታታሃለሁ። አሳብህን በማስታወሻ ማስፈሩ፣ ስለዚያ ጉዳይ ጥርት ያለ መረዳት እንዲኖርህ በማድረጉ ሂደት ብቸኛው ተመራጭ ነው።

ተቀጥላ 1 ውስጥ፡-

- *የመወያያ ጥያቄዎችን ታገኛለህ።* ይህን መጽሐፍ በምታነብባቸው በሚቀጥሉት 40 ቀናት፣ አብሮህ የሚያነብ አንድ ወይም ሁለት ጓደኞች ይኖሩህ ዘንድ ከልቤ መክርሃለሁ። በጉዞ ወቅት አብሮ ተጓዥ ሲኖር መልካም ነው። ያነበብከውን ከአንድ ጓደኛ ወይም ቡድን ጋር በምትወያይበት ጊዜ፣ ከእያንዳንዱ ሰው ጠቃሚ አሳቦች ይፈልቁ ይሆናል። ይህ አሠራር መንፈሳዊ ሕይወትህ በጥልቀትና በጥንካሬ እንዲያድግ ይረዳሃል። እውነተኛው መንፈሳዊ ዕድገት፣ የተናጠልና የግል ተግባር አይደለም። ዕድገት የግንኙነትና በጋራ የመሥራት ውጤት ነው።

እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ የመገንዘቢያው ተመራጭ መንገድ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ እንዲናገር መፍቀድ ነው። በመሆኑም፣ እዚህ መጽሐፍ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በብዛት ተጠቅሷል። ከአሥራ አምስት የተለያዩ እንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች በተወሰዱና ከሺህ በበለጡ ጥቅሶች፣ እንዲሁም ማብራሪያዎች ተጠቅሜያለሁ።

## እየፀለይኩልህ ነኝ።

ይህን መጽሐፍ በምጽፍበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ፈጥሮ በዚህች ምድር ላይ ያኖረህ ለምን መሆኑን ከመረዳት የተነሣ የሚገኘውን አስደናቂ ተስፋ፣ ብርታ

ትና ደስታ ትለማመድ ዘንድ ደጋግሜ እጸልይ ነበር:: ይህን የመሰለ መልካም ልምምድ የለም:: በሕይወትህ ሊከናወኑ የሚችሉ ብዙ ታላላቅ ነገሮችን ስለ ማውቅ ደስታ ይሰማኛል:: እነዚህ ታላላቅ ነገሮች ለኔ ሆነውልኝ የሕይወትን ዓላማ ከተረዳሁ ወዲህ ተለውጫለሁ::

የሕይወትን ዓላማ የመረዳትን ጥቅም ለማወቅ ትችል ዘንድ የ40 ቀን ጉዞ ህን በሚገባ እንድታከናውነው አበረታታሃለሁ፤ የየዕለት ንባብህን ፈፅሞ አትዝ ለለው:: ሕይወት ጊዜ ወስደን ልናስብበት የሚገባ ታላቅ ነገር ነው:: በዕለታ ዊው እቅድህ ውስጥ ጊዜ መድብለት:: በዚህ ጉዳይ ቁርጠኛ ውሳኔ ካደረግህ፣ አንድ ቃል ኪዳን እንፈራረም:: ስምና ፊርማህን የምታሥፍርበት ቃል ኪዳን ታላቅ ቁም ነገር አለው:: ይህን መጽሐፍ አብሮህ የሚያነብ ጓደኛ ካለህ እሱንም ቃል ኪዳኑ ላይ አስፈርመው:: አብረን እንጀምር እንግዲህ::



# ቃል ኪዳኔ

በእግዚአብሔር እርዳታ ቀጣዮቹን የሕይወቴን 40 ቀናት እርሱ
ለሕይወቴ ያለውን ዓላማ ለማወቂያነት አውላቸዋለሁ።

______________________________

ስም

______________________________

የጓደኛህ ስም

______________________________

ሪክ ዋረን

*«ለሥራቸው መልካም ውጤት ስለሚያገኙ*
*ከአንድ ሁለት መሆን ይሻላል፤*
*አንዱ ቢወድቅ ባልንጀራው ደግፎ ያነሣዋል።»*

*መክ. 4፥9-10*



# ለምንድነው የተፈጠርኩት?

*በሀብቱ የሚታመን ሁሉ ይወድቃል፤*

*ጻድቃን ግን እንደ ለረንጓዴ ቅጠል ይለመልማሉ።*

ምሳሌ 11÷28

*ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፣ መታመኛውም*

*እግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው። በውሃ ዳር እንደተተከለ*

*ሥሩንም ወደ ወንዝ እንደሰደደ ዛፍ ነው፣ ሙቀትም ሲመጣ*

*አይፈራም፤ ቅጠሉም ዘወትር እንደለመለመ ነው፤ በድርቅ*

*ዘመን አይሰጋም፤ ፍሬ ማፍራቱንም አያቋርጥም።*

ኤር 17÷7-8

# የሁሉም ጀማሪ እግዚአብሔር ነው

*ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኃይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ ሁሉ ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል።*

*ቆላ. 1፥16*

*በእግዚአብሔር መኖር ካላመንህ፣ የሕይወቴ ዓላማ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ትርጉም የለሽ ነው።*

*በርትራንድ ራሰል፣ (እግዚአብሔር የለም የሚል)*

ስለአንተ አይደለም።

የሕይወትህ ዓላማ፣ ከግል እርካታ፣ ከአእምሮ ሰላምና ከደስታህም ሁሉ የላቀ ነው። ከቤተሰብህ፣ ከሥራህ፣ ከማይጨበጥ ሕልምና ምኞትህ ይበል ጣል። ለምን እንደተፈጠርህ ለመገንዘብ ከፈለግህ፣ እግዘአብሔርን በማወቅ ጀምር። የተፈጠርከው፣ በእግዚአብሔር ዓላማና ለእርሱ ዓላማ ነው።

የሕይወትን ዓላማ የመፈለጉ ነገር፣ ሰዎችን ለብዙ ሺህ ዓመታት ግራ ሲያጋባቸው ኖሯል። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ በአብዛኛው መነሻችን ከተሳሳተ ሥፍራ፣ ማለትም ከራሳችን በመሆኑ ነው። ምን ለመሆን ነው የምፈልገው? በሕይወቴ ምን ላድርግ? ዓላማዬና የወደፊት ምኞቴ ምንድነው? እያልን እራስ ተኮር ጥያቄዎችን እናነሳለን። በራሳችን ላይ ማተኮር የሕይወታችንን ዓላማ በፍጹም አይገልጥም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«የፍጥረት ሁሉ ሕይወት፣ የሰውም ሁሉ መንፈስ በእጁ ናትና»* ኢዮብ 12፥10።

ታዋቂ መጻሕፍት፣ ሲኒማዎችና ሴሚናሮች እንደሚገልጡት አይደለም ነገሩ፤ ወደ ውስጥህ በመመልከት ለሕይወትህ ትርጉም ለማግኘት አትችልም። ይህን ነገር ከዚህ ቀደም ሞክረኸው ይሆናል። የራስህ ፈጣሪ ስላልሆንክ፣ ለምን እንደተፈጠርክ ልትገልጥ አትችልም።

*በራሳችን ላይ ማትኮር በፍጹም የሕይወታችንን ዓላማ አይገልጥም::*

ከዚህ ቀደም ያላየኸውን አንድ የፈጠራ ሥራ ብሰጥህ፣ ያ ዕቃ የተፈጠረበትን ዓላማ ልታውቅ አትችልም:: ሥራው እራሱም ቢሆን የተፈጠረበትን ዓላማ አይገልጥልህም:: ሥራውን የፈጠረው ሰው ወይም አጠቃቀሙን ሚያስረዳ ጽሑፍ ብቻ ነው የተፈጠረውን ነገር ዓላማ ሊገልጡት የሚችሉት::

አንድ ጊዜ በተራራዎች ላይ በመንዝ ላይ ሳለሁ መንገድ ጠፋኝ:: አንድ ሰው አግኝቼ የምሄድበት ቦታ ያለበትን አቅጣጫ ይነግረኝ ዘንድ ስጠይቀው፣ «*ከዚህ ተነስተህ እዚያ ልትደርስ አትችልም::* ከተራራው ሌላ አቅጣጫ በመነሳት ተጓዝ» አለኝ:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ራስህ ላይ በማትኮር ተነስተህ ወደ ሕይ ወትህ ዓላማ አትደርስም:: በመሆኑም መነሻህ፣ ከፈጣሪህ ከእግዚአብሔር ይሁን:: የምትኖረው እግዚአብሔር እንድትኖር ከመፍቀዱ የተነሣ ነው:: የተ ፈጠርከውም በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ነው:: ይህን ካልተገነዘብህ ሕይወት ትርጉም ያለው አይሆንልህም:: ከእግዚአብሔር ብቻ ነው መነሻች ንን፣ ማንነታችንን፣ የሕይወታችንን ትርጉም፣ ዓላማችንን፣ ጠቃሚ ወይም አስፈላጊነታችንን እና የመጨረሻ መድረሻችንን ልናገኝ የምንችለው:: ሌላው አቅጣጫ ሁሉ ወደ ሞት ነው የሚመራው::

ብዙ ሰዎች፣ እግዚአብሔርን እነሱ ለሚፈልጉት ሁኔታ ሊገለገሉበት ይሻሉ:: ይህ ድርጊት የተፈጥሮ ተገላቢጦሽ ሲሆን፣ ፍፃሜውም ውድቀት ነው:: አንተ ለእግዚአብሔር ተፈጠርህ እንጂ፣ ተገላቢጦሹ አይደለም የሆ ነው:: የሕይወት ትርጉም፣ እግዚአብሔር ለዓላማው እንዲጠቀምብህ መፍቀድ እንጂ፣ ለራስህ ዓላማ እርሱን መጠቀሚያ ማድረግ አይደለም:: «*የሥጋን ነገር ማሰብ ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው*» ሮሜ 8÷6:: ይላል መጽሐፍ ቅዱስ::

የሕይወቴን ዓላማ ለማግኘት የምችልባቸውን ዘዴዎች የሚጠቁሙ ብዙ መጻሕፍት እንብቤአለሁ:: ሁሉም ጉዳዩን ራስ ተኮር ከሆነ አቅጣጫ ስለሚመለ ከቱ የ«እራስህን እርዳ» መጻሕፍት በመባል ይመደባሉ:: «እራስህን እርዳ» መጻሕፍት፣ ክርስቲያናዊዎቹም ቢሆኑ እንኳን፣ በአብዛኛው የተለመዱትን የሕይወት ዓላማ ማግኛ መንገዶች ነው የሚጠቁሙን:: ምኞትህን አስብ፤ ዋጋ የምትሰጣቸውን ነገሮች በግልጥ ለይ፤ ጠንካራ ጐንህን ለይተህ እወቅ:: ለት ልቅ ግብ አልም:: ባለ ኃይልህ ግባበት:: ራስህን ለሥርዓት አስገዛ:: ካቀድክበት ግብ እንደምትደርስ እመን፣ ከሌሎች ጋር ሥራ፣ በፍጹም ተስፋ አትቁረጥ::

እነዚህ ምክሮች ብዙ ጊዜ ወደ ከፍተኛ ስኬታማነት ይመራሉ:: ለጉዳዩ በእርግጥ ትኩረት ከሰጠኸው፣ ካቀድከው ግብ ትደርሳለህ:: ይሁን እንጂ፣ ስኬታማ መሆንና የሕይወትህን ዓላማ ከግብ ማድረስ፣ በፍፁም ተመሳሳይ ነገሮች አይደሉም:: ግላዊ ግብህን ሁሉ አሳክተህና በዓለም መሥፈርት አድናቆትን ያተረፈ ክንውን ባለቤት ሆነህ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር የተፈጠርክበትን ዓላማ የሳትህ ትሆን ይሆናል:: በመሆኑም «እራስህን እርዳ» ከሚለው የላቀ ምክር ያስፈልግሃል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፣ ነገር ግን ነፍሱን ስለ እኔ የሚያጠፋት ያድናታል»* ማቴ. 16÷25::

ይህ መጽሐፍ እራስን ስለመርዳት የሚገልጥ አይደለም:: ትክክለኛ ሞያዊ ተግባር ስለማግኘት፣ ህልምህ እውን ስለሚሆንበት ወይም ለሕይወትህ ስለማቀድህ አይደለም የሚገልጠው:: በጣም በተጣበበ ጊዜ ውስጥ ብዙ ሥራ ስለማጨቅም አይደለም የሚያስረዳው:: እንደውም አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ በማትኮር፣ በሕይወትህ የምታከናውናቸውን ነገሮች የምትቀንስበትን መንገድ ነው የሚያስተምርህ:: *እግዚአብሔር* ሲፈጥርህ እንድትሆንለት የፈለገውን ሆነህ ስለመገኘትህ የሚያስረዳ ነው::

እንዴት ነው ታዲያ የተፈጠርክበትን ዓላማ ልትገነዘብ የምትችለው? ሁለት ምርጫዎች ብቻ ናቸው ያሉህ:: የመጀመሪያው ምርጫ፣ *መላምት* ነው:: ብዙ ሰዎች ይህን ይመርጣሉ:: መላ ይፈልጋሉ፣ ይገምታሉ፣ በምርምር ያሰላስላሉ:: ሰዎች፣ «ሕይወት ... ናት ብዬ ሁል ጊዜ አስባለሁ» ሲሉ፣ «ላቀርበው የሚቻለኝና ከሁሉ የላቀ ግምቴ ይህ ነው» ማለታቸው ነው::

ባለብሩህ አእምሮ ፋላስፋዎች የሕይወትን ትርጉም በተመለከተ ለብዙ ሺህ ዓመታት ተወያይተዋል፣ መላምቶችንም አቅርበዋል:: ፍልስፍና ጠቃሚ ትምህርት ነው፤ የራሱ ፋይዳም አለው:: የሕይወትን ዓላማ ለመረዳት ግን፣ እጅግ ብልሆቹ ፈላስፋዎች እንኳን ከመገመት አያልፉም::

*የተፈጠርከው በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ነው:: ይህን እስካልተገነዘብህ፣ ሕይወት ትርጉም ያለው አይሆንልህም::*

ዶክተር ኸግ ሙርሄድ የተባሉ የአንድ የሰሜን አሜሪካ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ኘሮፌሰር፣ ለ250 እውቅ ፈላስፋዎች፣ ሳይንቲስቶችና የዓለም ምሁራን «የሕይወት ትርጉሙ ምንድነው?»፣ በማለት የጽሑፍ ጥያቄ አቀረቡላቸውና የመጡላቸውን መልሶች በአንድ መጽሐፍ አሳተሟቸው:: ለጥያቄው መልስ ከሰጡት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ፣ አሉን የሚሏቸውን ግምታዊ አስተያየቶች ሰጡ:: ሌሎቹ የሕይወት ዓላማቸውን

ለራሳቸው መቀየሳቸውን ገለጡ:: የቀሩት ደግሞ ምንም የሚታያቸው ነገር ወይም ፍንጭ የሌለ መሆኑን በታማኝነት ተናገሩ:: አንዳንዶቹ ስመጥር ምሁራን እንደውም፣ ጥያቄውን ያነሱት ፕሮፌሰር ሙርሄድ እራሳቸው የሕይወትን ዓላማ አግኝተውት እንደሆን በደብዳቤ ይገልፁላቸው ዘንድ ጠየቋቸው::

ደግነቱ ግን፣ የሕይወትን ትርጉምና ዓላማ በተመለከተ መላምታዊና ግምታዊ አመለካከቶችን የሚተካ *መገለጥ* አለ:: እግዚአብሔር ስለ ሕይወት ምንነት በቃሉ የገለጠውን ልንመለከት እንችላለን:: የአንድን የፈጠራ *ሥራ* ዓላማ ለመረዳት የሚመረጠው ቀላል ዘዴ፣ ፈጣሪውን ወይም ሠሪውን መጠየቅ ነው:: የሕይወትህን ዓላማ የመገንዘቢያ ዘዴም ይሄው ነው፤ እግዚአብሔርን ጠይቀው::


የሕይወትን ዓላማ በመላምትና በግምት በመፈለግ እንባዝን ዘንድ እግዚአብሔር ጭለማ ውስጥ አልተወንም:: ለሕይወታችን ያዘጋጃቸውን አምስት ዓላማዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጧቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ከፈጠረን አምላክ የተሰጠን *መመሪያ* ነው:: በሕይወት የምንኖረው ለምን መሆኑን፣ እንዴት መኖር እንደሚገባን፣ ልናስወግዳቸው ስለሚገቡ ነገሮችና ልንጠብቀው ስለሚገባ ተስፋ ይገልጥልናል:: የራስህን እርዳ መርህ ወይም የፍልስፍና መጻሕፍት ሊገልጧቸው የማይቻላቸውን ነገሮችም ያስረዳናል:: ይህንኑ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ነገር ግን ተሠውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ምስጢር ጥበብ ነው፤ ይህም ጥበብ እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ለክብራችን አስቀድሞ የወሰነው ነው»* 1ቆሮ. 2፥7::

እንደኛ ቀን
የሁሉም
ጀማሪ
እግዚአብሔር
ነው

እግዚአብሔር የሕይወትህ መነሻ ብቻ ሳይሆን፣ የሕይወትህ ምንጭም ነው:: በመሆኑም የሕይወትህን ዓላማ ለመገንዘብ ትኩረትህን ወደ እግዚአብሔር ቃል አድርግ፤ ወደ ዓለም ጥበብ አይደለም:: ሕይወትህን ዘላለማዊ እውነት ላይ እንጂ፣ በሳይኮሎጂ፣ በሥጋዊ ስኬት መነሣሣት ወይም መገፋፋት ላይ አትመሥርት:: *«ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ እቅድ፣ አስቀድሞ የተወሰንን፣ እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል»* ኤፌ. 1፥11 ይላል መጽሐፍ ቅዱስ::

1. ማንነትህንና የሕይወትህን ዓላማ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሚኖርህ ግንኙነት ዓማካይነት ታገኛለህ:: እንዲህ ያለው ግንኙነት ከሌለህ፣ እንዴት መጀመር እንደሚገባህ ዘግየት ብዬ እገልጥልሃለሁ::

2. ስለእርሱ ማሰብ ከመጀመርህ እጅግ አስቀድሞ፣ እግዚአብሔር ስለ አንተ ያስብ ነበር፡፡ ለሕይወትህ ያለው ዓላማ፣ በእናትህ ማህፀን ከመፀነስህ በፊት እጅግ የቀደመ ነው፡፡ በሕይወት ከመኖርህ በፊትና *የአንተ እርዳታ ሳያስፈልገው ነው* እግዚአብሔር የሕይወት ዓላማህን ያቀደው፡፡ ሥራህን፣ የትዳር ጓደኛህን፣ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያህንና ሌሎች የሕይወት ጉዳዮችህን ልትመርጥ ትችላለህ፤ ዓላማህን ግን ልትመርጥ አትችልም፡፡



3. የሕይወትህ ዓላማ፣ እግዚአብሔር ለዘላለም ባቀደውና እጅግ በገዘፈው ፈለካዊ (Cosmic) ዓላማ ውስጥ የሚገጥም ወይም የሚወሀድ ነው፡፡ ይህንን ነው ይህ መጽሐፍ የሚያወሳው፡፡

አንድሬይ ቢቶቭ የተባለ ሩሲያዊ ደራሲ፣ ያደገው እግዚአብሔር የለም በሚል ኮሙኒስታዊ መንግሥት ውስጥ ነበር፡፡ ደስተኛ ባልነበረበት አንድ ቀን እግዚአብሔር አሳቡን ወደራሱ ሳበው፡፡ የዚያን ዕለት ትዝታውን እንደሚቀጥለው ገልጦታል፡- «በሀያ ሰባተኛው ዓመት ዕድሜዬ፣ አንድ ቀን፣ በሌኒን ግራድ (አሁን ሴንት ፒተርስበርግ ተብሏል)፣ የምድር ውስጥ ባቡር እንጓዝ ነበር፡፡ ሕይወት እንቅስቃሴዋን ያቆመች እስኪመስለኝ ድረስ በድንገት ተስፋ የመቁረጥ ስሜት አደረብኝ፡፡ እንኪን የሕይወት ትርጉም፣ የወደፊት ተስፋዬ ሁሉ ጨለመብኝ፡፡ ወዲያውኑ፡- *ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ትርጉም የላትም* የሚል ዐረፍተ ነገር በዓይነ ህሊናዬ ታየኝ፡፡ ዐረፍተ ነገሩን ደጋግሜ እያነበብኩ ከባቡሩና ከምድሩ ውስጥ መንገድ በመውጣት፣ ወደ እግዚአብሔር ብርሃን ገባሁ»፡፡

ስለ ሕይወትህ ዓላማ በምታስብበት ጊዜ፣ ጭለማ ውስጥ ያለህ ያህል ይሰማህ ይሆናል፡፡ እንኪን ደስ ያለህ፣ በብርሃን ልትመላለስ ነው፡፡

አንደኛ ቀን

ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ** :- ስለ እኔ አይደለም

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ**:- *«ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአልና፣ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኃይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል» ቆላ. 1፥16 ::*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ**:- በዙሪያዬ ብዙ የሚባል ነገር አለ:: ታዲያ እንዴት ነው፣ የምኖረው ሕይወት ለእኔ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መሆኑን የማስታውሰው?

# አጋጣሚ አይደለህም

*የፈጠረህ፣ ከማህፀንም የሠራህ፣*
*የሚረዳህም እግዚአብሔር ... ::*
ኢሳ. 44÷2

*እግዚአብሔር ቁማር አይጫወትም::*
አልበርት አንስታይን

አጋጣሚ አይደለህም::

በአጋጣሚ ወይም በድንገት አልተወለድክም:: ሕይወትህም ተፈጥሮ ያደለችህ አይደለም:: ወላጆችህ በተለይ አንተን ለመውለድ ብለው አላቀዱ ይሆናል፣ እግዚአብሔር ግን አቅዶሃል:: የአንተ መወለድ እግዚአብሔርን አላስደነቀውም፤ እንደውም ይጠብቀው የነበረ ጉዳይ ነው::

ገና ድሮ በወላጆችህ ከመፀነስህ በፊት እግዚአብሔር አሳብ ውስጥ ተፀንሰህ ነበር:: ስለ አንተ መጀመሪያ ያሰበ እርሱ ነው:: በዚህች ቅጽበት በሕይወት ያለኸው፣ እግዚአብሔር በፍላጎቱ ስለፈጠረህ ነው፤ በዕድል ወይም በአጋጣሚ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ :- *«እግዚአብሔር በእኔ ላይ ያለውን ዓላማ ይፈጽማል»* መዝ. 138÷8፣ ይላል::

እያንዳንዱን የአካልህን ክፍሎች ይሁኑ ብሎ ያገጣጠማቸው እግዚአብ ሔር ነው:: ዘርህን፣ የቆዳህን ቀለም፣ ፀጉርህንና ሌላውን መልክህን የመ ረጠው ሆነ ብሎ ነው:: አካልህን እርሱ በፈለገው ሁኔታ ወስኖ ሠራው:: ደግሞም የተፈጥሮ ችሎታህንና ማንነትህ ወሰነ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣ ዓጥንቶቼ ከአንተ አልተደበቁም»* መዝ. 139÷15::

እግዚአብሔር የፈጠረህ በምክንያት ስለሆነ፣ የምትወለድበትን ጊዜና ምን ያህል ዘመን እንደምትኖርም ወስኗል:: የመወለጃና የመሞቻህን እቅጯን

ሰዓት በመምረጥ አስቀድሞ የሕይወትህን ቀናት አቅዷቸዋል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይገልጠዋል፡- *«ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን አዩ፤ ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት፣ ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ፣ በመጽሐፍ ተመዘገቡ»* መዝ. 139÷16፡፡

እግዚአብሔር ለዓላማው የት እንደምትወለድና የት እንደምትኖር አቅዷል፡፡ ጎሳህና ዜግነትህ እንኳን አጋጣሚ አይደለም፡፡ አንድንም ነገር ለዕድል ወይም ለአጋጣሚ አልተወም፡፡ ሁሉንም ለዓላማው አቅዶታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውን ልክና የመኖሪያ ሥፍራቸውንም ዳርቻ ወሰነላቸው፡፡»* ሐዋ. 17÷26፡፡ በሕይወትህ በዘፈቀደ የሆነ ነገር የለም፤ ሁሉም በዓላማ ነው የተፈጠረው፡፡

ከሁሉም የሚያስደንቀው፣ የምትወለድበትን ሁኔታ እንኳን እግዚአብሔር የወሰነ መሆኑ ነው፡፡ የተወለድክበት ሁኔታና የወላጆችህ ማንነት ምንም ይሁን ምን፣ እግዚአብሔር ሲፈጥርህ ግን ዓላማ ነበረው፡፡ ወላጆችህ ጥሩ ይሁኑ መጥፎ፣ ወይም ግድ የለሾች ምንም አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ግን፣ እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በእርሱ አሳብ ውስጥ የነበርከውን፣ አንተን *በቀጥታ* ሊያስገኝ የሚችል ትክክለኛ የዘር ቅንብር እንዳላቸው ያውቅ ነበር፡፡ አንተን ሊሠራበት የፈለገውና DNA የተባለው ዘር ነበራቸው፡፡

ህጋዊ ያልሆኑ ወላጆች ሊኖሩ ቢችሉም፣ ህጋዊ ያልሆኑ ልጆች ግን የሉም፡፡ በወላጆቻቸው ሳይታቀዱ የተወለዱ ብዙ ልጆች አሉ፡፡ ያለ እግዚአብሔር እቅድ ግን አልተወለዱም፡፡ እግዚአብሔር የሰብዓውያንን ስህተትና፣ ኃጢአት እንኳ ሳይቀር ይጠቀምበታል፡፡

> *ገና በወላጆችህ ከመፀነስህ በፊት እግዚአብሔር አሳብ ውስጥ ተፀንሰህ ነበር፡፡*


እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር በድንገት አያደርግም፤ በሥራውም በፍጹም አይሳሳትም፡፡ ማንኛውንም ነገር የሚፈጥርበት ምክንያት አለው፡፡ እፅዋትና እንስሳት ሁሉ በእግዚአብሔር የታቀዱ ናቸው፡፡ እንዲሁም ማንኛውም ሰው ለዓላማ በእግዚአብሔር ታቅዶ ነው የተፈጠረው፡፡

አንተን እንዲፈጥር እግዚአብሔርን ያነሳሳው፣ ፍቅሩ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጥ እንዲህ ይላል፡- *« በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናል፡፡»* ኤፌ. 1÷4፡፡

እግዚአብሔር ገና ዓለምን ሳይፈጥር ስለ አንተ ያስብ ነበር፡፡ ዓለምን የፈጠረውም ለዚሁ ነው፡፡ ይህችን ምድርና አካባቢዋን ሁሉ የፈጠረው ለእኛ ኑሮ እንድትመች አድርጎ ነው፡፡ እኛ እኮ የእግዚአብሔር የፍቅሩ ትኩረትና፣ ከፍጥረቱም ሁሉ የከበርን ነን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«የፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን»* ያዕ. 1፥18፡፡ ይህን ያህል ነው እግዚአብሔር የሚወድህና ከፍ ያለ ሥፍራ የሚሰጥህ!

ግብታዊ አይደለም፤ ማንኛውንም ነገር የፈጠረው በፍፁም ትክክለኛነት ነው፡፡ የፊዚክስ፣ የሥነ - ሕይወት ተመራማሪዎችና ሌሎች ሳይንቲስቶች ስለ ዓለማት ይበልጥ በተረዱ ቁጥር፣ እኛም የተፈጠረው ዓለም ለሰው ልጅ ህልውና ተስማሚ ይሆን ዘንድ ሳይዛባ ተደራጅቶ መፈጠሩን እንገነዘባለን፡፡

ዶክተር ሚካኤል ደንተን የተባሉ አንጋፋ የሥነ-ሕይወት ተመራማሪ እንዲህ ብለዋል፤ «በሥነ ፍጥረት ሳይንስ ዓማካይነት የተሰበሰቡ ማስረጃዎች ሁሉ የሚያረጋግጡት ፈለክ (Cosmos)፣ ሕይወትንና ሰብዓዊ ፍጡራንን መሠረታዊ ዓላማና ግቡ አድርጎ በተለየ ሁኔታ የተደራጀ ምልዓት መሆኑን ነው፡፡ ሁሉም፣ የተፈጠረው ዓለም ገጽታዎች ትርጉምና መገለጫ የሚያገኙት በዚህ ማዕከላዊ እውነት ነው፡፡»



መጽሐፍ ቅዱስም ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ይህንኑ እንዲህ በማለት ገልጦታል፡- *«ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው፣ ምድርን ያበጃት፣ የሠራት የመሠረታት፣ የሰው መኖሪያ እንጂ ባዶ እንድትሆን ያልፈጠራት...»* ኢሳ. 45፥18፡፡

እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ለምን አደረገ? ዓለማትን ስለእኛ ለመፍጠር እዚህ ሁሉ ግዴታ ውስጥ ያገባው ምንድነው? የፍቅር አምላክ መሆኑ ነው፡፡ ይህን ዓይነቱን ፍቅር፣ መረዳቱ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በመሠረቱ ግን አስተማማኝ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልዩ የፍቅር ማረፊያ ሆነህ ተፈጥረሃል፡፡ ይወድህ ዘንድ ፈጥሮሃል፤ ይህ ሕይወትህን ትመሠርትበት ዘንድ የሚገባ እውነት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«እግዚአብሔር ፍቅር ነው»* ይለናል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር *ስለው* አይደለም የሚለው፡፡ እርሱ ፍቅር *ነው፡፡* ፍቅር የማንነቱ መሠረታዊ ባሕርይ ነው፡፡ በሥላሴነቱ ውስጥ ፍፁም ፍቅር ስላለ፣ ፍቅር ፍለጋ አንተን መፍጠር *አያስፈልገውም* ነበር፡፡ ብቸኛም አልነበረም፡፡ ነገር ግን ፍቅሩን ይገልጥብህ ዘንድ አንተን መፍጠር አስፈለገው፡፡ በቃሉ እንዲህ

ይላል :- *«ከተፀነሳችሁበት ጊዜ ጀምሮ የያዝኋችሁ፣ ከተ ወለዳችሁበት ጊዜ ጀምሮ የተሸከምኋችሁ ... እኔ ነኝ። ሠርቻች ኋለሁ፣ እሸከማችኋለሁ፤ እደግፋችኋለሁ፤ አድናችኋለሁ»*

ኢሳ. 46÷3-4።

## ሁለተኛ ቀን
## አጋጣሚ አይደለህም

እግዚአብሔር የለም ቢባል፣ እኛ በአጥናፈ ዓለሙ በድንገት የተከሰትን አጋጣሚዎች እንሆን ነበር። እንዲያ ከሆነ ደግሞ ሕይ ወት ዓላማና ትርጉም የላትምና ይህን መጽሐፍ ማንበብህን ለማቆም ትች ላለህ። በዚህች ምድር ላይ ካለችህ አጭር የሕይወት ዘመንህ ያለፈ ተስፋ ስለማይኖርህም ልክ የሚባሉና ስህተት የሚባሉ ነገሮች አይኖሩም።

ነገር ግን ለዓላማ የፈጠረህ አምላክ *አለ*፤ ሕይወትህም *ታላቅ ዓላማ* አለው! የእንዲህ ዓይነቱን የሕይወት ዓላማና ትርጉም የምናገኘው፣ እግዚ አብሔርን የሕይወታችን መነሻ መሠረት ስናደርገው *ብቻ* ነው ።

ሮሜ 12÷3 ውስጥ የተጠቀሰው ምንባብ በአጭር አፈታት ሲነበብ እንደ ሚከተለው ይሆናል፣ *«እራሳችንን የምንገነዘብበት ብቸኛና ትክክለኛ መንገድ፣ የእግዚአብሔርን ምንነት፣ እንዲሁም ሥራውን መረዳት ነው»*።

የሚከተለው የሩሴዌል ግጥም እስካሁን ያየነውን አሳብ በአጭሩ እንዲህ ይገልጠዋል፡-

ሥፍራ አለህ አወሳሰቦ ባረቀቀው
ምክንያት አለ አሁን አንተ ለሆንከው።
ሴት ወይም ወንድ ተብለህ ብትጠራ፣
ነህ እኮ ክቡር የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ።
አምላካችን መቼም አይሳሳት፣
የመሰልከውን ለመምሰልህ አለው ምክንያት።
አበጃጀህ፣ አስቀመጠህ፣ በማህፀን፣
ድሮ ገና ያሰበህን አንተነትህን፣
የአሁኑን ማንነትህን፣
ቢመስልህም ባይመስልህም ባይመቸውም ስሜትህን፣
መርጧቸዋል ለዚህ ዓላማ እናትና አባትህን።
በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተሠሩ፣ በአሳቡ በትልሙ፣
ናቸውና በመለኮት የታተሙ።
በሕይወት ጎዳና በስቃይ ብታልፍም፣
ልብህ እንዲቃና ይህንን ቢፈቅድም፣

እርሱን ወደመምሰል ታድግ ዘንድ ቢወድም
በስቃይህ እኮ እርሱ አይደሰትም።
ምክንያት አለው አሁን አንተ ለሆንከው፣
አንተን አንተ ያደረጉህ እጆቹ ናቸው፣
ወዳጄ ሆይ ይህ ሁሉ የሚሆነው
ፈጣሪ አምላክ ስላለ ነው!

ሁለተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** በአጋጣሚ የተፈጠርኩ አይደለሁም።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«የፈጠረህ፣ ከማሕፀን የሠራህ፣ የሚረዳህ፣ እግዚአብሔር ...።» ኢሳ. 44፥2።*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** እግዚአብሔር ድንቅ አድርጎ እንደፈጠረኝ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ከጆርባ እኔነቴ፣ ከአካሌና በአጠቃላይ ከሰብእናዬ አልቀበል ያልኩት የትኛውን ነው?

# 3

# ሕይወትህ የሚመራው በምንድነው?

*እንዲሁም ጥረትና የሥራ መከናወን ሁሉ ሰው*
*በባልንጀራው ላይካለው ቅናት*
*እንደሚመነጭ ተመለከትሁ።*
*መክ. ፬፥4*

*ዓላማ የለሽ ሰው የአቅጣጫ መቆጣጠሪያ እንደሌለው*
*መርከብ ነው - ተንከራታችና ምናምንቴ፣ አረ*
*እንዲያውም ሰው አይደለም ።*
ተማስ ከርሊል

የማንኛውም ሰው ሕይወት በአንድ ነገር ግፊት ይመራል። ብዙ መዝገበ *ቃላት አንቀሳቀሰ* ለሚለው *ግሥ* :- «መራ፣ ተቆጣጠረ ወይም አቅጣጫን ወሰነ» የሚል ፍቺ ይሰጡታል። መኪናም ነዳህ፣ ምስማር በመ ዶሻ መታህ ወይም ኳስ አንከባለልህ፣ በዚያን ወቅት ያንን ነገር እየመራህ፣ እየተቆጣጠርክና አቅጣጫውን እየወሰንክ ነው። ታዲያ ልክ እንዲሁ ሕይ ወትህን የሚመራው ኃይል ምንድነው?

በአሁኑ ጊዜ በአንድ በሆነ ችግር፣ በሆነ ጫና፣ ወይም ማለቅ ያለበትን ሥራ ለመጨረስ በጥድፊያ በመራመድና በመንቀሳቀስ ላይ ትገኝ ይሆናል። በክፉ ትዝታ፣ በአስበርጋጊ ፍርሃት ወይም በቅጡ ባልገባህ አንድ ኅሊናዊ እምነት ትመራ ይሆናል። ሕይወትህን ሊያንቀሳቅሱና ሊመሩ የሚችሉ ብዙ ሁኔታዎች፣ የሕይወት ፋይዳዎችና ስሜቶች አሉ። ቀጥሎ የተዘረዘሩት አምስቱ በጣም የተለመዱና የታወቁ ናቸው:-

ብዙ ሰዎች በበደለኛነት ስሜት ይመራሉ:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ዘመናቸ ውን ሁሉ ጸጸትና ቁጭት ከወለደው ሃፍረታቸው ለመሸሸግ ሲሸሹ ይኖራሉ:: ቁጭትና ጸጸት የሚመራቸው ሰዎች፣ የትዝታ ተጠቂዎች ናቸው:: ያለፈው ሕይወታቸው መጪውን ሕይወታቸውን እንዲቆጣጠረው ይፈቅዱለታል:: ብዙውን ጊዜ ሳያውቁት የሕይወት ስኬታቸውን እያበላሹ እራሳቸውን ይቀ ጣሉ:: ቃየል ኃጢአትን በሠራ ጊዜ በደሉ ከእግዘአብሔር ህልውና ለየው፤ እግዚአብሔርም እንዲህ አለው:- *«በምድር ላይ ኮብላይና ተንከራታች ትሆናለህ»* ዘፍጥ. 4÷12:: ይህ ቃል በዘመናችን ያለ ዓላማ በሕይወት ጎዳና የሚንከራተቱ ብዙ ሰዎችን ይገልጣል::

ምንም እንኳን የዛሬ ኑሯችን የትናንት ውጤት ቢሆንም፣ የትናንት ኑሯችን ግን የዛሬ እስረኞች ሊያደርገን አይገባም:: ምክንያቱም፣ የእግዚአብሔር ዓላማ ባለፈው ሕይወትህ የሚወሰን አይደለም:: እግዚአብሔር ሙሴ የተባለውን ነፍሰ ገዳይ ወደ ሕዝብ መሪነት፣ ጌዴዎን የተባለውን ፈሪ ደግሞ ወደ ደፋር ጀግናነት ለውጧቸዋል:: በአንተ ቀሪ ሕይወትም እንዲሁ አስደናቂ ነገሮችን ሊያደርግ ይችላል:: እግዚአብሔር ለሰዎች አዲስ የሕይወት ጅማሬ በመስጠት የተካነ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኃጢ አቱም የተሸፈነችለት እንዴት ብሩክ ነው» *መዝ. 32÷1::*

ብዙ ሰዎች በቂምና በቁጣ ይመራሉ:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ደረሰብን የሚሉትን ጉዳት ከማስወገድ ይልቅ አቅፈውት ይኖራሉ:: የጉዳታቸውን ስቃይ በይቅርታ ከማስወገድ ይልቅ፣ በመደጋገም ያብሰለስሉታል:: አንዳንዶቹ ደግሞ፤ ዝም በማለት ንዴታቸውን ውስጣቸው *«ስምቀው»* ይይዙታል! የቀ ሩት ደግሞ የታመቀ ቁጣቸውን *«በማፈንዳት»* በሌሎች ላይ ያምባርቃሉ:: እነዚህ ሁሉ አጸፋዎች ጤናማ ያልሆኑና የማይጠቅሙ ናቸው::

የአንተ ቂም መያዝ፣ ቂም በያዝክበት ሰው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት ይበ ልጥ የሚጎዳው አንተን ነው:: የጎዳህ ወይም ያስቀየመህ ሰው ድርጊቱን ረስ ቶት የራሱን ኑሮ እየመራ ይሆናል፤ አንተ ግን ያለፈውን ቂም አምቀህ በመ ያዝ በብስጭት ትብለሰለሳለህ::

ልብ በል! ከዚህ በፊት የጎዱህ ሰዎች አልጥል ባልከው የገዛ ቂምህ ካልሆነ *በቀር* እየጎዱህ ሊኖሩ አይችሉም:: ያለፈው ነገርህ አልፏል! ምንም ሊቀይረው አይችልም:: በመራርነትህ ራስህን ብቻ ነው የምትጎዳው:: በቃ ለራስህ ስትል ካለፈው ተማርና ተወው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ሞኙን ሰው ብስ ጭት ይገድለዋል፣ ቂሉንም ቅናት ያጠፋዋል» ኢዮብ 5÷2::*

ብዙ ሰዎች በፍርሃት ይመራሉ:: እንዲህ ላሉ ሰዎች የሥጋታቸው

ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች፣ በሕይወታቸው ያሳለፉት አስፈሪ ጉዳት፣ በእውነት ላይ ያልተመሠረተ ምኞትና ጉጉት፣ ጥብቅ ቁጥጥር ባለበት ቤተሰብ ውስጥ ማደግ፣ ወይም በተፈጥሮ የመጣ ፍርሃት ያለባቸው ይሆኑ ይሆናል:: ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን፣ በፍርሃት የሚኖሩ ሰዎች ድፍረት ከማጣታቸው የተነሣ፣ ሁኔታዎችን ስለማይጋፈጡ ብዙ ዕድሎች ያመልጧቸዋል:: ፍርሃትን በድፍረት ከማሸነፍ ይልቅ፣ ችግር ካለበት ሁኔታ መሸሽንና ባሉበት ሁኔታ ውስጥ መቆየትን ይመርጣሉ::

ፍርሃት፣ እግዚአብሔር ያቀደልህን እንዳትሆን የሚያግድህና እራስህን ያስገ ባህበት እሥር ቤት ነው:: በፍቅርና በእምነት መሣሪያነት ልትጋፈጠው ይገ ባል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍፁም ፍቅር ግን ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል፤ ፍርሃት ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍፁም አይደለም»* 1ዮሐ. 4÷18::

**ብዙ ሰዎች ለመበልፀግ ባላቸው ምኞት ይመራሉ**:: እንዲህ ያሉት ሰዎች የሕይወታቸው ዋና ግብ፣ ሀብት ማግኘት ነው:: እንዲህ ያለው ሁልጊዜ ይበ ልጥ ሀብት የመፈለግ ግፊት የሚመነጨው፣ ብዙ ሀብት ሲኖረኝ ይበልጥ ደስ ተኛ፣ ይበልጥ ታዋቂና ዋስትና ያለኝ እሆናለሁ ከሚል የተሳሳተ አመለካከት ነው:: እነዚህ ሦስቱም አስተሳሰቦች ስህተት ናቸው:: ሀብት ሊያስገኝ የሚች ለው ጊዜያዊ ደስታን ነው :: ምክንያቱም ቁሳዊ ነገሮች ስለማይለወጡ ያሰለ ቹናል:: በመሆኑም አዳዲስ፣ ትልልቅና የተሻሉ ነገሮችን እንደገና እንፈል ጋለን::

ብዙ ሀብት ካለኝ ይበልጥ የተከበርኩና ተፈላጊ ሰው እሆናለሁ የሚልና የማይጨበጥ እምነትም አለ:: እኛ እራሳችንን የተመነንበት ዋጋ ከትክክለኛ ዋጋችን ጋር ተመሳሳይ አይደሉም:: ዋጋህ አንተ አሉኝ በምትላቸው ውድ ነገሮች አይወሰንም:: በሕይወት እጅግ ዋጋ ያላቸው፣ *ቁሳዊ ነገሮች* እንዳል ሆኑ እግዚአብሔርም ይነግረናል::

ስለ ገንዘብ በጣም የተለመደው የማይጨበጥ እምነት፣ ብዙ ገንዘብ ካለኝ፣ በሁሉ ነገር ዋስትናዬ በጣም የተጠበቀ ይሆናል የሚለው ነው:: አይሆንም! በተ ለያዩና ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሀብት ወይም ገንዘብ በቅጽበት ይጠ ፋል:: እውነተኛ ድነት ወይም ዋስትና የምታገኘው፣ ፈጽሞ ማንም ሊወስድብህ ከማይቻለው ማለት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ካለህ ግንኙነት ነው::

**ብዙ ሰዎች በሌሎች ዘንድ ተቀባይነትን በመፈለግ ማንነት ይመራሉ**:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ወላጆቻቸው ወይ ልጆቻቸው ወይ ደግሞ አስተማሪዎቻ ቸው አለዚያም ሌሎች ወዳጆቻቸው ከእነርሱ የሚጠብቁትን ነገር ለማሟላት የሚያደርጉት ጥረት ሕይወታቸውን እንዲቆጣጠር ይፈቅዳሉ:: አንዳንድ ሰዎች

ከኀለመሱ በኋላም እንኳን ለማስ ደሰት አስቸጋሪ በሆኑ ወላጆቻ ቸው ተቀባይነትን ለማግኘት ይፈ ልጋሉ። ሌሎች ደግሞ፣ ሰዎች ስለ እነርሱ የሚያስቡት ነገር እያስ ጨነቃቸው በእኩዮቻቸው ተጽዕኖ ይመራሉ። የሚያሳዝነው ግን ብዙ ዎችን ለማስደሰት የሚሞክሩ ሰዎች በሂደቱ ራሳቸውን ያጣሉ።

*እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ከማወቅህ የሚበልጥ ግድ ልትሰጥበት የሚገባ ነገር የለም፤ ይህ ዕውቀት ቢጎድልህ ግን በምንም ልታካክሰው አትችልም።*

ለስኬት የሚያበቁ ቁልፍ ነገሮችን በሙሉ ባላውቅም፣ ለውድቀት የሚያ በቃው ዋነኛ ነገር ግን፣ ሁሉንም ለማስደሰት መሞከር ነው። በሌሎች አስተ ሳሰብ መመራት፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ እንድትስት የሚ ያደርግህ መንገድ ነው። ኢየሱስ፦ *«ሰንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል ስይችልም»* ብሏል ማቴ. 6÷24 ።

አላስፈላጊ ጭንቀት፣ እርካታ ያጣ ሕይወት፣ ጥቅም ላይ ያላዋልከው ችሎ ታና ሌሎች ብዙ ነገሮች ሕይወትህን ሊያሽከረክሩት ይችላሉ፤ ሁሉም ግን የትም የማያደርሱ ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምታደርገው የአርባ ቀን ጉዞ *በዓላማ የሚመራ ሕይ ወትን* እንዴት ለመኖር እንደምትችል ያሳይሃል። እንዲህ ዓይነቱም ሕይወት በእግዚአብሔር ዓላማ ቁጥጥር ሥር ሆኖ የሚመራና የሚቃኝ ነው። እግዚአ ብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ከማወቅ ይበልጥ ግድ ልትሰኝበት የሚገባ ነገር የለም፤ ይህ ዕውቀት ቢጎድልህ ግን በምንም ልታካክሰው አትችልም። የኑሮ ስኬት፣ ባለጠግነት፣ ባለዝና መሆንና ሌሎች ደስታ ሰጪ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ለአንተ ያሰበውን የሕይወት ዓላማ ሊተኩት አይችሉም። ሕይ ወት ያለ ዓላማ ትርጉም የሌለው መንከላወስ፣ አቅጣጫ የሌለው ተግባርና ምክንያት የሌላቸው ድርጊቶች የሞሉበት ነው። ሕይወት ያለ ዓላማ የማይ ረባ፣ የማይጠቅምና ትርጉም አልባ ነው።

## በዓላማ የሚመራ ሕይወት ጥቅሞች

ሕይወትን በዓላማ በመኖር የሚገኙ አምስት ጥቅሞች አሉ፦

**የሕይወትን ዓላማ ማወቅ፣ ትርጉም ያለው ሕይወትን ለመኖር ይጠቅማል**። የተፈጠርነው ትርጉም ያለው ነገር ይኖረን ዘንድ ነው። ለዚህ ነው ሰዎች የሕይወትን ትርጉም ፍለጋ የማይታመኑ ዘዴዎችን፣ ኮከብ

ቆጠራ፣ ጥንቆላና የመሳሰሉ አሠራሮችን የሚሞክሩት። ሕይወትህ ትርጉም ሲኖረው፣ ሁሉንም ነገር ትችለዋለህ። ካልሆነ ግን ምኑንም አትችለውም።


ዕድሜው በሃያዎቹ ዓመታት ውስጥ የሆነ አንድ ወጣት እንዲህ በማለት ጻፈ፦ « ልሆን የምፈልገውን አንድ ነገር ለማግኘት በትግል ላይ ነኝ። ያ ነገር ምን መሆኑን እንኳን አላውቅም። በመሆኑም ምንም ነገር ያልተሳካለት ሰው እንደሆንኩ ይሰማኛል። እንግዲህ አሁን የማውቀውና የማደርገው ነገር ቢኖር ዝም ብሎ ኑሮን መቀጠል ነው። አንድ ቀን ይህን የሕይወቴን ዓላማ ስገነዘብ ኑሮን እንደ አዲስ የምጀምር መሆኔ ይሰማኛል»።

## ሦስተኛ ቀን

## ሕይወትህ የሚመራው በምንድነው?

ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ዓላማ የላትም። ያለ ዓላማ ደግሞ ትርጉም አልባ ናት። ያለ ትርጉም ደግሞ ጥቅምና ተስፋም የላትም። እንዲህ ያለውን ባዶነት ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሁኔታ ገልጠውታል። ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ነበር፦ *«እኔ ግን፣ ዓላማ ሳይኖረኝ እንዲሁ ደከምሁ፣ ምንም ጥቅም ለሌለውና ለከንቱ ጉልበቴን ጨረስሁ፤. ..»* ኢሳ. 49÷4። ኢዮብ ደግሞ እንዲህ አለ፦ *«ዘመኔ ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ ይፈጥናል፤ ያለ ተስፋም ያልቃል።»* ኢዮብ 7÷6፤ እና *«ሕይወቴን እጸየፋለሁ፤ ዘላለም መኖር አልፈልግም፣ ዘመኔም እንደ እስትንፋስ ነውና ተወኝ »* ኢዮብ 7÷16። አሳዛኙ ነገር ሞት ሳይሆን፣ ዓላማ የሌላት ሕይወት ናት።

ተስፋ የአየርና የውሃን ያህል ለሕይወትህ አስፈላጊ ነገር ነው። የሕይወትን ተግዳሮት ለመቋቋም ተስፋ ያሻል። ዶክተር በርኒ ሲይግል የተባሉ ሐኪም ከነቀርሳ በሽታ ህመምተኞቻቸው የትኛው እንደሚያገግም የሚያውቁበት ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር፦ «ዕድሜዎ መቶ ዓመት እስኪሞላ ለመኖር ይፈልጋሉ?»። ለጥያቄው የአዎንታ መልስ የሰጡትና በሕይወት የመቆየት አዝማሚያ ያሳዩት፣ ጥልቅ የሕይወት ዓላማ ያላቸው ህመምተኞች ነበሩ። ተስፋ የሚመጣው ዓላማ ካለው ሕይወት ነው።



ተስፋ የመቁረጥ ስሜት የሚሰማህ ከሆንህ፣ ቆም በልና አስብ! ሕይወትህን በዓላማ መምራት ስትጀምር፣ አስደናቂ ለውጦች ይፈጸማሉ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ *«ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ አውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር። <ዕቅዱም ፍጻሜው ያማረና ተስፋም የሚሰጥ፣ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም>»* ኤር. 29÷11። በጣም አስቸጋሪ በሆነና

በማይቻል ሁኔታ ውስጥ እንዳለህ ይሰማህ ይሆናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «... *ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው...*» ኤፌ. 3÷20።

**የሕይወትህን ዓላማ ማወቅህ ኑሮን ቀላል ያደርግልሃል።** ሕይወትህን በዓላማ መምራት፣ ማድረግ የሚገባህንና የማይገባህን ነገሮች እንድትለይ ይጠቅምሃል። በዚህ መሠረት ዓላማ አስፈላጊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጊቶችን የምትመዝንበት ነው። በአጭሩ «ይህ ድርጊቴ እግዚአብሔር ለሕይወቴ ካለው ዓላማዎች አንዱን እንዳከናውን ይረዳኛልን?» ብለህ ትጠይቃለህ።

ግልጥ የሕይወት ዓላማ ከሌለህ፣ የውሳኔዎችህ መነሻ የሚሆን፣ ጊዜህን እንዲሁም አለኝ የምትለውን ንብረት የምታውልበት መሠረት አይኖርህም። የውሳኔ ምርጫዎችህ በሁኔታዎች፣ በጊዜው ባለህበት ስሜትና በሌሎች ተጽዕኖዎች ላይ ይመሠረታሉ። ዓላማቸውን የማያውቁ ሰዎች በአንድ ጊዜ ብዙ ነገር ለማድረግ ይጥራሉ። *ይህም* ጭንቀትን፣ ድካምንና ከሌሎችም ጋር ግጭትን ይፈጥርባቸዋል።

ሰዎች እንድታደርግላቸው የሚፈልጓቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረጉ አይቻልህም። ያለህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማከናወን ብቻ የሚበቃ ነው። ያሰብከውን በሙሉ ለመሥራት ካልቻልክ፣ ምናልባት እግዚአብሔር ላንተ ከመደበልህ በላይ ለመፈፀም በመሞከር ላይ ትሆናለህ። (ምናልባት ጊዜህን በማይረባ ነገር ለማሳለፍ በመሞከር ላይ ነህ)። በዓላማ የሚመራ ሕይወት፣ ቀላል የኑሮ ዘዴና ጤነኛ የጊዜ አጠቃቀም አለው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «*ምንም ሳይኖረው ባለጠጋ መስሎ የሚታይ ሰው አለ፤ ሌላው ደኻ መስሎ ይታያል፤ ግን ብዙ ሀብት አለው*» ምሳሌ 13÷7። ሕይወትን በዓላማ መምራት፣ የአእምሮ ሰላምንም ያመጣል፦ «*በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ የምትደገፈውን ነፍስ ፈፅመህ በሰላም ትጠብቃታለህ*» ኢሳ. 26÷3።

**የሕይወትህን ዓላማ ማወቁ፣ ኑሮን በትኩረት ለመምራት ይጠቅምሃል።** ዓላማ፣ ጥረትና ኃይልህን ጠቃሚ ነገር ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ይረዳሃል። የምትሠራውን መርጠህ ስለምትሠራ ውጤታማነትህ ይጨምራል።

መቼም በጥቃቅን ነገሮች ከዋነኛው የሕይወት አቅጣጫ መዛባት ሰብዓዊ ተፈጥሮ ነው። ከንቱ የሆኑ ብዙ የሕይወት ፍለጋዎች ያንከራትቱናል። ለዚህ ነው ሄነሪ ዴቪድ ቶሩ የተባለ ምሁር፣ ሰዎች፣ «*እርካታን ፍለጋ ይንከራተታሉ*» ያለው። በዛሬው ሁኔታ ግን፣ *በዓላማ ቢስነት ኑር ይመላለሳሉ* የሚለው አባባል ይበልጥ ይገልጠዋል። ብዙ ሰዎች ስፍራውን ሳይለቅ እንደ ሚሾር እንዝርት መሰል ሞተር ይሽከረከራሉ። ሕይወታቸው ግን ካለበት አልፍ

አይልም።

ግልፕ የሕይወት ዓላማ ከሌለህ፣ ግራ ለመጋባትህና ለልብህ ባዶነት መልስ ይሆነኛል በማለት ከቤተክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን፣ ካንዱ ወዳጅ ወደ ሌላው፣ ከሥራ፣ ሥራ እየቀያየርክ ትኖራለህ። የሚቀጥለው ምርጫህ የተለየና *የተሻለ ይሆናል ብለህ ታስባለህ።* ችግርህ ግን የሕይወት ዓላማና ትኩረት ማጣት ስለሆነ፣ ይህ ድርጊትህ ፈጽሞ አይረዳህም።

*መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ»* ኤፌ. 5፥17።

የትኩረት አቅጣጫ ያለውን ሕይወት ከብርሃን ጋር አነጻጽረን ለማየት እን ችላለን። የተበታተነ ብርሃን የሚኖረው ኃይል፣ ወይም የሚሰጠው ጥቅም እም ብዛም ነው። ይህንኑ ብርሃን በአንድ ትኩረት እንዲሰበሰብ በማድረግ ኃይሉን ለማጠናከር ግን ይቻላል። የፀሐይ ጨረርን በአጉልቶ ማሳያ (ሌንስ) እንዲሰበ ሰብ በማድረግ፣ ሳርና ቅጠል የመሳሰሉ ነገሮችን በእሳት ለማቀጣጠል ይቻላል። የብርሃን ኃይል ታምቆ እንደሚወረወር ጨረር (ሌዘር ቢም) በከፍተኛ ክምችት ሲሰባሰብ፣ ጠንካራ ብረትን ሊቆራርጥ ይችላል።

*ሕይወትህ ተጽእኖ ያለው እንዲሆን ከፈለገህ፣ ሰብስበው።*

በአቅጣጫ ትኩረትና በዓላማ የሚመራ ሕይወትን ያህል ብርቱ ነገር የለም። በታሪክ ውስጥ፣ ታላላቅ ሥራዎችን ያከናወኑ ሰዎች፣ የሕይወት ትኩረት የነበራቸው ናቸው። ለም ሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስትናን በሮማው ያን ግዛት ሁሉ ያሰራጨው ብቻውን ነው። የውጤታማነቱ ምስጢር፣ ሕይወቱ የትኩ ረት አቅጣጫ የነበረው መሆኑ ነው። ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- *«አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ፣ በፊቴ ወዳለው እዘ ረጋለሁ»* ፊል. 3፥13።

ሕይወትህ ተጽዕኖ ያለው እንዲሆን ከፈለህ፣ ሰብስበው! ሁሉን ለማድረግ ከመባከን ይልቅ፣ የተወሰነ ነገር ሥራ። መልካም ናቸው ብለህ የምታስባቸ ውን ነገሮች እንኳ በመቀነስ፣ ከሁሉ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ብቻ አድርግ። ውጤታማ የሆነ ሥራ መሥራትንና ጥድፊያን አንድ አድርገህ አትመልከታቸው። ዓላማ ሳይኖርህ እንዲያው ጥድፊያ ብቻ የበዛብህ ልትሆን ትችላለህ፤ ታዲያ ይህ ምን ይጠቅምሃል? ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡- *«... ሁላችን ነገሮችን በዚህ ሁኔታ ማየት ይኖርብናል፤ በአንዳንድ ነገር የተለየ አስተ ሳሰብ ቢኖራችሁ እግዚአብሔር እርሱንም ይገልጥላችኋል»* ፊል. 3፥15።

**ዓላማህን ማወቁ ሕይወትህን ያነሣሣዋል።** ዓላማ ሁልጊዜ መልካም ስሜት ይፈጥራል። ግልጥ ዓላማን ያህል ኃይል የሚሰጥ ነገር የለም። በሌላ በኩል ዓላማ ከሌለ የሕይወት ግለት ይባክናል፤ ጠዋት ከአልጋችን መውረዱ እንኳን ከባድ ሥራ ይሆንብናል። ብዙውን ጊዜ ትርጉም የለሽ ሥራ በመሥራት ነው ጉልበታችን ሚባክነው፤ እንደከማለን ደስታችንም ይጠፋል።

*በምድር ላይ የተፈጠርከው ሌሎች እንዲያስታውሱህ ሳይሆን፣ ለዘላለም እንድትዘጋጅ ነው።*

ጆርጅ በርናርድ ሾው የተባለ ደራሲ እንዲህ በማለት ጽፏል፡- «ሁል ጊዜ አጉረምራሚ፣ ራስ ወዳድ፣ ሰው ሁሉ እሹሩሩ ይበለኝ የምትል አትሁን፤ በዓላማ ከመመራትህ የተነሳ ለራስህ ያለህ ግምት ከፍ ይበል። ይህ ነው የሕይወት እወነተኛ ደስታ።»

**ዓላማህን ማወቁ ለዘላለም ሕይወት ያዘጋጅሃል።** ብዙ ሰዎች የሕይወት ዘመናቸውን የሚጨርሱት፣ ምድር ላይ ትተውት የሚያልፉትን ዘላቂ ቅርስ በማዘጋጀት ነው። ሲሞቱ፣ ትተውት በሄዱት ቅርስ አማካይነት እንዲታወሱ ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ፣ የመጨረሻው ቁም ነገር ሰዎች ስለ አንተ የሚሉት ሳይሆን፣ *እግዚአብሔር* የሚለው ነው። ሰዎች የሚዘነጉት ነገር፣ መልካም ግኝቶች ሁሉ ከነሱ በላቀ ግኝት የሚሻሩ፣ ክብረ ወሰኖች ደጋግመው የሚሰበሩ፣ ዝና የሚደበዝዝና መታሰቢያዎች የሚረሱ መሆናቸውን ነው። ጀምስ ዶብሰን የተባሉ ስመ ጥር ሰው፣ በኮሌጅ ትምህርት ዘመናቸው የነበራቸው ግብ፣ የትምህርት ቤቱ የቴኒስ እስፖርት ሻምፒዮን መሆን ነበር። በዚሁ መሠረት የተሸለሙት የአሸናፊነት ዋንጫ ትምህርት ቤቱ ሽልማቶች ማከማቻ ውስጥ በቋሚነት ሲቀመጥላቸው ኩራት ተሰማቸው። ከዓመታት በኋላ ግን፣ አንድ ሰው ዋንጫውን ለጀምስ ላከላቸው። የትምህርት ቤቱ ህንፃ ተሻሽሎ በሚታደስበት ጊዜ ዋንጫው የተገኘው ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ተወርውሮ ነበር። ጀምስ ዋንጫውን ከተቀበሉ በኋላ እንዲህ አሉ፡- «*ይዋል ይደር እንጂ፣ ዋንጫዎችህ ሁሉ በሌላ ሰው ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ይወረወራሉ።*»


ምድራዊ ቅርስ ለማከማቸት መኖር፣ ዘላቂ ያልሆነ ግብ ነው። ብልህ የጊዜ አጠቃቀም ግን *ዘላለማዊ ቅርስ* ማከማቸት ነው። በምድር ላይ የተፈጠርከው ሌሎች እንዲያስታውሱህ ሳይሆን፣ ለዘላለም እንድትዘጋጅ ነው።

አንድ ቀን እፊቱ ስትቆም እግዚአብሔር ሕይወትህን ይመረምረዋል፤ ወደ ዘላለም ሕይወት ከመግባትህ በፊትም የመጨረሻ ፈተና ያቀርብልሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*ሁላችን በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንቆር ባለንና። ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን*» ሮሜ

14÷10-12:: እድለኞች ስለሆንን፣ እና እግዚአብሔር ፈተናውን እንድናልፍ ስለፈለገ ጥያቄዎቹን በቅድሚያ ሰጥቶናል:: እግዚአብሔር ሁለት ወሳኝ ጥያቄ ዎችን የሚያቀርብልን መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ ካነበብነው ቃል ልንገምት እንችላለን::

መጀመሪያው፣ *«ልጄን ኢየሱስ ክርስቶስን ምን አደረግከው?»* የሚል ነው:: እግዚአብሔር ሃይማኖት ነክ ታሪክህን ወይም አስተምህሯዊ አመለካከትህን አይጠይቅህም:: ዋናው ነገር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ ያደረገውን በእምነት ተቀብለሃልን? እርሱን መውደድንና ማመንን ተምረሃልን? እንዲህ ብሏል ኢየሱስ:- *«መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም»* ዮሐ. 14÷6::

ሁለተኛው *«በሰጠሁህ ማንኛውም ነገር ምን አደረክበት?* በሕይወትህ፣ በስጦታ ዎች፣ በችሎታዎች፣ በመልካም አጋጣሚዎች፣ በብርታትህ፣ ከሌሎች ጋር



ባሉህ ግንኙነቶችና በሰጠሁህ ሀብት ምን አደረክባቸው? ለራስህ ተጠቀምክባቸው፣ ወይስ አንተን ለፈጠርኩበት ዓላማ አዋልካቸው?» እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች ለመመለስ ትችል ዘንድ አንተን ማዘጋጀት የዚህ መጽሐፍ ግብ ነው:: የመጀመሪያው ጥያቄ ዘላለምን *የምታሳልፍበትን ሥፍራ* ይወስናል:: ሁለተኛው ደግሞ ዘላለም ውስጥ *የምታከናውነውን ሥራ* የሚወስን ይሆናል:: ይህን መጽሐፍ አንብበህ ስትጨርስ ሁለቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ትሆናለህ::

## ሦስተኛ ቀን
## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** በዓላማ መኖር ወደ ሰላም የሚያደርስ መንገድ ነው፡፡

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ የምትደገፈውን ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ»* ኢሳ. 26+ 3 ፡፡

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ሕይወቴን የሚያንቀሳቅሰው ኃይል ምንድነው ይላሉ? እኔስ ምን እንድሆን ነው የምፈልገው?

# ለዘላለም ሕይወት ተፈጥረሃል

*እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ዘላለማዊነትን አኖረ።*

*መክብብ 3፥11*

*በእርግጥ እግዚአብሔር ሰውን ያህል ፍጡር ለአንድ ቀን ሕይወት አልፈጠረውም! በጭራሽ ሰው የተፈጠረው ለዘላለማዊነት ነው።*

አብርሃም ሊንከን

ሕይወት ይህ የምናየው ብቻ አይደለም።

ምድራዊ ሕይወት አንድ የልብስ ፋብሪካ ውስጥ ሙሉው የማምረት ተግባር ከመጀመሩ በፊት የሚደረግ ዝግጅት ወይም ልምምድን ይመ ስላል። በምድር ላይ ከሚኖርህ ይልቅ ከሞት ባሻገር ባለው *ዘላለማዊ* ሕይወት እጅግ ብዙ ጊዜ ታሳልፋለህ። ዓለም የመለማመጃ፣ እንደ ትምህርት መጀመሪያ የምትቆጠርና ለዘላለማዊው ሕይወትህ የሙከራ ሥፍራ ናት፤ እውነተኛው ግጥሚያ ከመጀመሩ በፊት የመለማመጃና የመሟሟቂያ ሥፍራ። በእርግጥ ይህ ሕይወታችን ለሚቀጥለው ሕይወት መዘጋጃ ነው።

በምድር ላይ የምትኖረው ቢበዛ አንድ መቶ ዓመት ነው፤ በዘላለም ውስጥ ግን ፍጻሜ የሌለው ሕይወት ትኖራለህ። ሰር ቶማስ ብራውን የተባሉ ምሁር በምድር ያለውን ሕይወት «በዘላለም ውስጥ በቅንፍ ያለች ጥቂት ወቅት ናት» ብለው ገልጸውታል። የተፈጠርከው ለዘላለም ሕይ ወት ነው።

*መጽሐፍ ቅዱስ፦ «... በሰዎች ልብ ዘላለማዊነትን አኖረ»* መክ. 3፥11

ይላል:: ዘላለማዊነትን የሚናፍቅ ተፈጥሮ ውስጥህ አለ:: ይህ የሆነው ለዘላለም ትኖር ዘንድ እግዚአብሔር በአምሳሉ ስለ ፈጠረህ ነው:: ሰው ሁሉ በጊዜው የሚሞት መሆኑን ብናውቅም፣ ሞት ሁል ጊዜ ተፈጥሯዊና ተገቢ ያልሆነ ይመስለናል:: ለዘላለም መኖር አለብን የሚለው ስሜት ያደረብን፣ እግዚአብ ሔር ያን የመፈለግ ስሜት አእምሯችን ውስጥ ስላኖረው ነው !

አንድ ቀን ልብህ ምቷን ታቆማለች:: ያ ወቅት የአካልህና የምድራዊው ጊዜህ ማብቂያ ይሆናል፤ የአንተ ፍፃሜ ግን አይደለም:: ምድራዊ አካልህ የመ ንፈስህ ጊዜያዊ መኖሪያ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ምድራዊ አካልህን «ድንኳን» ይለዋል:: የወደፊት አካልህን ግን «ቤት» ነው የሚለው:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *«መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስም፣ በሰው እጅ ያልተሠራ፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰማይ እንዳለን እናውቃለን» 2ቆሮ. 5÷1* ይላል ::

ምድራዊ ሕይወት በምድር ላይ ብዙ ምርጫዎች የሚያቀርብልን ሲሆን፤ ዘላለም ግን ሁለት ምርጫዎች ብቻ ያቀርብልናል፤ እነርሱም መንግሥተ ሰማያትና ገሃነመ እሳት ናቸው:: በምድራዊ ሕይወትህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት፣ በዘላለማዊ ሕይወትህ ከእርሱ ጋር የሚኖርህን ግንኙነት ይወስነዋል:: የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ከወደድህና በእርሱ ካመንህ፣ ዘላለምን ከርሱ ጋር ታሳልፍ ዘንድ ትጋበዛለህ:: ፍቅሩን፣ ይቅርታውንና አዳኝነቱን አልቀበልም ካልክ ግን፣ ዘላለምን እግዚአብሔር በሌለበት ነው የምታሳልፈው::

ሲ ኤስ ሌዊስ የተባሉ ሰው እንዲህ ብለዋል:- «ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ፤ እግዚአብሔርን:- <*ፈቃድህ ትፈጸም* >፤ የሚሉና በሌላ ወገን ደግሞ እግዚአብሔ ር እራሱ:- <*በሉ እንግዲህ እንደመረጣችሁ ይሁንላችሁ*> የሚላቸው ናቸው::» የሚያሳዝነው ግን፣ ብዙ ሰዎች ምድራዊ ሕይወታቸውን ያለ እግዚአብሔር ለማሳለፍ በመምረጣቸው፣ ዘላለምን ያለ እርሱ ለመኖር መገደዳቸው ነው::

*ይህ ሕይወት ለሚቀጥለው ሕይወት መዘጋጃ ነው*

አሁንና እዚህ ካለው የበለጠ ሕይወት መኖሩን በደንብ ስትረዳ፣ እንዲሁም ምድራዊው ሕይወት ለዘላለም የዝግጅት ጊዜ መሆኑን ስትገነዘብ፣ ኑሮን በተለየ አካኋን እና *ከዘላለም አንፃር መኖር* ትጀም ራለህ:: ይህን የመሰለ አኗኗርህ፣ ከሌሎች ጋር የሚኖርህን ግንኙነት፣ ሥራህንና ሁኔታዎችህን ይቀርጻቸዋል:: የምታከናውናቸው ብዙ ተግባራት፣ ግቦችህ እና ከባድ የሚመስሉ ችግሮች እንኳን ሳይቀሩ ወዲያውኑ ቀላል፣ ትንሽ

እና ከቁምነገር የማትቆጥራቸው ይሆናሉ:: ወደ እግዚአብሔር በቀረብህ ቁጥር ሁሉም ነገር እያነሰ ይሄዳል::

ከዘላለም አንፃር ስትኖር፣ ለሕይወት የምትሰጠው ፋይዳ ይቀየራል:: በጊዜና በገንዘብህ በጥበብ መጠቀምንም ትጀምራለህ:: ከዝና፣ ከሀብት፣ ከስኬት ወይም ጨዋታ ይልቅ፣ ከሰዎች ጋር ለሚኖርህ ግንኙነትና መልካም ባህርይ ከፍተኛ ሥፍራ ትሰጣለህ:: ነገሮችህ ተገቢ ቅደም ተከተላቸውን ይይዛሉ:: ከዚያ በኋላ የአለባበስ ፋሽንና ሕዝብ የሚወዳቸው ጊዜያዊ ፋይዳዎች በአንተ ዘንድ እምብዛም እንደቀድሞው ሥፍራ አይኖራቸውም:: ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *«ነገር ግን ይጠቅመኝ የነበረውን ሁሉ አሁን ለክርስቶስ ስል እንደ ጉድለት ቆጥሬዋለሁ»* ፊል. 3÷7::

ለአንተ ሕይወት ማለት በምድር ላይ የምትኖረው ብቻ ከሆነ፣ ኑሮን ቶሎ ትጀምረው ዘንድ አሳስብሃለሁ:: ጥሩና የሥነ ምግባር ሰው የመሆንህንም ነገር እርሳው፤ ባደረግከው ነገር ሳቢያ ስለሚመጣብህ ነገርም መጨነቅ አይኖርብህም:: ድርጊትህ የረጅም ጊዜ መዘዝ ስለማይኖረው በፍጹም ለራስህ ብቻ እያሰብህ እንዳሻህ ኑር:: *ዋናው ልዩነት ግን*፣ ሞት ፍፃሜህ አለመሆኑ ነው:: ሞት ወደ ዘላለም መሸጋገሪያህ እንጂ፣ የሕይወትህ ማብቂያ አይደለም::

*ከዘላለም አንፃር ስትኖር፣ ለሕይወት የምትሰጠው ፋይዳ ይቀየራል::*

ስለዚህ በምድር ላይ የምታደርገው ማንኛውም ነገር የሚያስከትለው ዘላለማዊ ውጤት ይኖራል:: በሕይወታችን የምናከናውነው ማንኛውም ድርጊት፣ ከዘላለም ጋር ንክኪ አለው::

የዚህ ዘመን ኑሯችን እጅግ ጎጂ ጎን፣ አስተሳሰባችን ለአጭር ጊዜ ብቻ መሆኑ ነው:: በሕይወትህ ታላቅ ሥራ ለማከናወን፣ የዘላለምን ራዕይ ያለማቋረጥ በአእምሮህ መመልከት አለብህ፤ የዚያን ፋይዳ ደግሞ በልብህ ማኖር:: ሕይወት፣ አሁንና እዚህ ካለው እጅግ የላቀ ነገር አላት:: ዛሬ የግዙፉ ሕይወት የጫፍ ዕይታ ነው:: ከዚያ ቀጥሎ በሰፊው ያለውና አሁን የማናየው ዘላለም ነው::

ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለምን መኖር ምን ይመስል ይሆን? እርግጡን ለመናገር፣ አእምሯችን የመንግሥተ ሰማያትን አስደናቂነትና ታላቅነት የመረዳት አቅም የለውም:: ውስብስቡን የመረጃ መረብ (ኢንተርኔት)፣ ለጉንዳን ለመግለጥ የመሞከር ያህል ነው፤ ከንቱ ሙከራ:: ዘላለማዊውን ሕይወት በሚገባ ሊገልጡት የሚችሉ ቃላት አልተፈጠሩም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ዐይን ያላየችውን ጆሮ ያልሰማውን፣ በሰውም ልብ ያልታሰበውን፣ እግዚአ*

*ብሔር ለሚወዱት ለዘጋጀተለቻ ...* » 1ቆሮ. 2+9::

ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በቃሉ የዘላለምን ጭላንጭል አሳይቶናል:: በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መኖሪያ እያዘጋጀልን መሆኑን እናውቃለን:: ወደ መንግሥተ ሰማያት ስንሄድ አማኞች ከሆኑት ወዳጆቻችን ጋር እንገናኛለን፤ ከሕመምና ከስቃይ እንላቀቃለን:: በምድር ላይ ሳለን ስላሳየነው ታማኝነት እንሸለማለን፤ ደስ የምንሰኝበት ሥራ ይሰጠናል:: በማይጨበጥና በከንቱ ነገር ጊዜ ያችንን አናባክንም:: ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ አንድነት ይኖረናል:: እሱም ፍጻሜና ገደብ በሌለው ሁኔታ ከእኛ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ደስ ይለ ዋል:: አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ይላል:-

**አራተኛ ቀን ለዘላለም ሕይወት ተፈጥረሃል**

*«እናንተ ለባቱ የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዘ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ»* ማቴ. 25+34::


ሲ. ኤስ ሌዊስ ለሕጻናት ከጻፏቸው ሰባት የተረት መጻሕፍት በአንደኛው የመጨረሻ ገጽ የዘላለምን እሳቤ እንዲህ በማለት ገልጠውታል:- «ለእኛ ይህ ያነበብነው የታሪክ ፍጻሜ ሲሆን ... ለነሱ ግን የእውነተኛው ታሪክ መጀመሪያ ነው:: በዓለም ያለው ሕይወታቸው ሁሉ ... የመጽሐፍ ሽፋንና የአርእስት ገጽ ነበር:: አሁን በመጨረሻ ማንም ምድራዊ ሰው ያላነበበው፣ ለዘላለም የሚቀ ጥልና የታላቁን ታሪክ የመጀመሪያ ምዕራፍ ንባብ በመጀመር ላይ ናቸው:: ይህ ታላቅ ታሪክ ለዘላለም የሚቀጥል ሲሆን፣ ከአንዱ ምዕራፍ ወደሚቀጥለው ሲታለፍ ይበልጥ እየተሻለ የሚሄድ ነው::»

እግዚአብሔር ለምድራዊው ሕይወታችን ዓላማ አለው:: ዓላማው ግን እዚሁ የሚያበቃ አይደለም:: በምድር ላይ ከምታሳልፋቸው ጥቂት አሥርት ዓመታት እጅግ ይልቃል:: «ከዚህ ዓለም ሙሉ የሕይወት ዕድል» ይበልጣል:: እግዚአብሔር ከሕይወት ዘመንህ *ባሻገር የሆነ ዕድል* ይሰጥሃል:: መጽሐፍ ቅዱስ :- *«የእግዚአብሔር ለሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል፤ የልቡም ለሳብ ለተውልድ ሁሉ ነው»* መዝ. 33+11 ይላል::

ብዙ ሰዎች ስለ ዘላለም የሚያስቡበት ብቸኛ ጊዜ፣ በቀብር ሥርዓት ላይ ሲሆን፣ ያም ጥልቀት በሌለው ስሜትና ባለማወቅ ላይ የተመሰረተ ነው:: ስለ ሞት ማሰብ አያስደስትም ብለህ ትገምት ይሆናል:: በመሠረቱ፣ ሞትን መካ ድና አይቀሬ የሆነውን ነገር ችላ ማለት፣ ጤነኛነት አይደለም:: መምጣቱ የማ ይቀር መሆኑን ሁላችን ለምናውቀው ነገር ዝግጅት ሳያደርግ የሚኖር ሞኝ ብቻ

ነው:: ስለ ዘላለም ማሰብ ያለብህ በትንሹ ሳይሆን በብዛት ነው::

እናትህ ማህፀን ውስጥ ያሳለፍካቸው ዘጠኝ ወራት፣ የሕይወት የዝግጅት ጊዜ እንጂ፣ የነገር ሁሉ ፍጻሜ እንዳልሆኑ ሁሉ ይህ ሕይወትም ለሚቀጥለው ሂደት የዝግጅት ጊዜ ነው:: በኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ካለህ፣ ሞትን መፍራት የለብህም:: ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የመግቢያ በር ነው:: በምድር ላይ የመጨረሻ ሰዓት ይሆናል! እንጂ የአንተ መጨረሻ ግን አይሆንም:: ይልቁንም ወደዘላለም ሕይወት የምትወለድበት ዕለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ምክንያቱም በዚህ ቋሚ ከተማ የለንም፤ ነገር ግን ወደ ፊት የምትመጣዋን ከተማ እንጠብቃለን»* ዕብ. 13+14::



በምድር የምናሳልፈው ሕይወት፤ ከዘላለም ጋር ሲነፃፀር፣ ዓይንን ከድኖ የመክፈት ያህል ቅፅበታዊ ነው:: አኗኗራችን የሚያስከትለው ውጤት ግን ዘላለማዊ ይሆናል:: የአሁን ሕይወታችንና ድርጊቶቻችን ቀጣይ ዕጣችንን ይወስኑታል:: *«... በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደምንገኝ እናውቃለን ...»* 2ቆሮ. 5÷6:: «እያንዳንዷን ቀን፣ በምድር ለሚቀርህ ዘመን የመጀመሪያ ቀን እንደሆነች እየቆጠርክ ኑር» የሚለው አባባል ከዓመታት በፊት ብዙ ሰዎችን አበረታቷቸው ነበር:: ከዚህ የሚሻለው ጥበባዊ ኑሮ ግን፣ እያንዳንዷን ቀን የሕይወታችን የመጨረሻ ዕለት እንደሆነች በመቁጠር መኖሩ ነው:: ማቲው ሄነሪ የተባሉ ሰው ይህንኑ አስመልክተው ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል:- «የእያንዳንዱ ቀን ጉዳያችን ሊሆን የሚገባው ነገር፣ ለመጨረሻው ዕለታችን መዘጋጀት ነው::»

## አራተኛ ቀን
## ስለ ዓለማዊ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** ሕይወት አሁንና እዚህ ካለው የላቀ ነገር አላት።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** «*ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል*» 1ዮሐ. 2፥17።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** ዘላለም እንድኖር የተፈጠርኩ እንደመሆኔ መጠን፣ ልተወው የሚገባ ድርጊት የቱ ነው? ዛሬ ልጀምረው የሚገባኝስ ነገር ምንድነው?

# ሕይወትን ከእግዚአብሔር እይታ አንፃር መመልከት

*ሕይወታችሁ ምንድናት?*

*ያዕ. 4፥14*

*እኛ ነገሮችን እንደራሳችን እንጂ እንደራሳቸው ስናያቸውም፡፡*

*አናይስ ኒን (ሰመፐር ምሁር)*

*ለሕይወትህ ያለህ ስተያይ ሕይወትህን ይቀርፀዋል፡፡*

ለሕይወት የምትሰጠው ትርጉም፣ ፍጻሜ ዕጣህን ይወስነዋል፡፡ የሕይወት እይታህ በጊዜ፣ በገንዘብ፣ ባለህ ተሰጥኦ አጠቃቀም እና ከሌሎች ጋር ላለህ ግንኙነት በምትሠጠው ዋጋ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡

ሰዎችን መገንዘቢያ ከሆኑት ተመራጭ መንገዶች አንዱ «*ሕይወትህን እንዴት ትመለከተዋለህ?*» ብሎ መጠየቅ ነው፡፡ እንዲያ ብታደርግ፣ እንደምትጠይቃቸው ሰዎች የበዙና የተለያዩ መልሶችን እንደምታገኝ ትረዳለህ፡፡ ሕይወት፣ እንደ ሰርከስ ትርዒት፣ የማዕድን ሥፍራ፣ ፈጣን የመጫወቻ ተሽከርካሪ፣ እንቆቅልሽ፣ የሙዚቃ ትርዒት፣ ጉዞ፣ እንዲሁም ጭፈራ ናት ተብሎ ተነግሮኛል፡፡ ሰዎች «ሕይወት ሽክርክሪት ናት፤ አንዳንዴ ከፍ፣ ሌላ ጊዜ ዝቅ ትላለህ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ዝም ብለህ ትሽከረከራለህ » ወይም «ሕይወት እጅግ ፈጣንና ኃይሉን ሁሉ ልንጠቀምበት እንደማይቻለን አስር ማርሽ እንዳለው ቢስክሌት ናት» ወይም «ሕይወት በካርታ ጨዋታ ትመሰላለች፤ በእጅህ ላይ ባሉት ካርዶች መጫወት ይኖርብሃል» ይላሉ፡፡

የሕይወትን ምስል እንዴት ትገልጠዋለህ? ብዬ ብጠይቅህ፣ ምን ዓይነት ስዕል ነው በአእምሮህ የሚከሰተው? ያ ምስል የሕይወትህ ተምሳሌት፣ በመረዳትም ሆነ ባለመረዳት በአእምሮህ የያዝከው *የሕይወት ምስል ነው::* ሕይወት እንዴት እንደምትሠራና ከሷ የምትጠብቀው ምን መሆኑን የምትገልጥበትም ነው:: ሰዎች ብዙ ጊዜ የሕይወታቸውን ምስል የሚገልጡት፣ በልብስ፣ በጌጣጌጥ፣ በፀጉራቸው አሠራር፣ በመኪናቸውና ሌሎች ነገሮቻቸው ላይ በሚለጥፏቸው ጽሑፎች፣ እንዲሁም ምልክቶች፤ በንቅሣት እንኳን ሳይቀር ነው::

በንግግር የማይገለጠው የሕይወትህ ተምሳሌት፣ ከምትገነዘበው በላይ በሕይወትህ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፤ ከሕይወት የምትጠብቃቸውን ነገሮች፣ ፍላጐትህን፣ ፋይዳህን፣ ከሰዎች ጋር ያለህን ግንኙነት፣ ግብህንና ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ነገሮች ይወስናል:: ለምሳሌ ሕይወት ጭፈራ ነው ብለህ ካሰብህ፣ የሕይወትህ ዋና ፋይዳ፣ *መዝናናትና መደሰት* ይሆናል:: ሕይወትን እንደ ውድድር ከቆጠርከው፣ ፋይዳህ *ፍጥነት* ይሆንና ብዙውን ጊዜ በጥድፊያ ላይ ትሆናለህ:: ሕይወትን እንደረጅም እሩጫ ከቆጠርከው ደግሞ፣ *ትልቅ ሥፍራ ለመድረስ ትሮጣለህ::* ሕይወትን እንደ እስፖርት ፍልሚያ ወይም ጦርነት ከቆጠርከው *ማሸነፍ* ዋና ነገርህ ይሆናል::

ሕይወትን እንዴት ነው የምታየው? የመሠረትከው በተሳሳተ ምስል ላይ ይሆናል:: እግዚአብሔር ለአንተ የፈጠረልህን ዓላማ ለማከናወን፣ ልማዳዊውን ተራ ጥበብ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የሕይወት ምስል ልትተካው ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-*«መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍፁም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ፣ ይህን ዓለም አትምሰሉ »* ሮሜ 12፥2::

## አምስተኛ ቀን
## ሕይወትን ከእግዚአብሔር እይታ አንፃር መመልከት

መጽሐፍ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔርን የሕይወት እይታ የሚያመለክቱ ሦስት ተምሳሌቶችን ያቀርባል:: እነሱም *ሕይወት ፈተና ነው*፣ ሕይወት *ባለአደራነት ነው*፣ ሕይወት *ሥራ ነው* የሚሉ ናቸው:: እነዚህ አሳቦች ዓላማ መር ለሆነ ሕይወት መሠረቶች ናቸው:: የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን በዚህ ምዕራፍ፣ ሦስተኛውን ደግሞ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታቸዋለን::

**ሕይወት በምድር ላይ ፈተና ነው::** ይህ የሕይወት ተምሳሌት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት ታሪኮች ታይቷል:: እግዚአብሔር የሰዎችን ባሕርይ፣ እምነት፣ ታዛዥነት፣ ፍቅር፣ ቅንነትና ታማኝነት ያለማቋረጥ ይፈትናል::

*መከራ*፣ *ፈተና*፣ *ማጥራት*፣ እና *መመርመር* የመሳሰሉት ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ200 ጊዜ በላይ ተጠቅሰዋል:: እግዚአብሔር፣ ልጁን ይስሐቅን ይሰዋ ለት ዘንድ በመጠየቅ አብርሃምን ፈትኖታል:: ራሔልን ለማግባት ለተጨማሪ ዓመታት ያገለግል ዘንድ ያዕቆብን ፈትኖታል::

አዳምና ሔዋን በገነት የአትክልት ስፍራ ተፈትነው ወድቀዋል:: ዳዊት በተ ለያዩ አጋጣሚዎች ከእግዚአብሔር የቀረቡለትን ፈተና ሳያልፍ ቀርቷል:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዮሴፍን፣ ሩትን፣ አስቴርንና ዳንኤልን የመሳሰሉና ግዙፍ ፈተና ያለፉ ሰዎችን በተመለከተ ብዙ ምሳሌዎችን ይገልጥልናል::

ባሕርይ በፈተና አማካይነት ያድጋል፣ ይገለጣልም:: ሕይወት ባጠቃላይ ፈተና ነው:: *ሁልጊዜ* በመፈተን ላይ ነህ:: እግዚአብሔር ለሰዎች፣ ለችግሮች፣ ለስኬቶች፣ ላለመግባባቶች፣ ለበሽታ፣ ለብስጭት፣ ለአየር ሁኔታ እንኳን ሳይ ቀር ያለህን መልስ ይመለከታል:: ለሌሎች በር ስትከፍት፣ የወደቀ ቆሻሻን ስታነሳና ለሚያስተናግዱህም ትህትናን ስታሳይ፣ ጥቃቅን ነገሮችንም ስትፈጽም እግዚአብሔር ያይሃል::

*ባሕርይ በፈተና አማካይነት ያድጋል፣ ይገለጣል:: ሕይወት ባጠቃላይ ፈተና ነው::*


እርሱ የሚያቀርብልንን ፈተናዎች አናውቅም:: አንዳንዶቹን ግን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ልንተነብ ያቸው እንችላለን:: በታላላቅ ለውጦች፣ በዘገዩ ተስፋዎች፣ በማይቻሉ ችግሮች፣ ባልተመለሱ ጸሎቶች፣ ባልተገቡ ነቀፋ ዎች እና ሰቆቃዎች ትፈተናለህ:: እግዚአብሔር *እምነቱን* በችግሮች፣ *ተስፋዬን* የኔ በምላቸው ነገሮች፣ *ፍቅሬን* ደግሞ በሰዎች አማካይነት የሚፈትን መሆኑን ተረድቻለሁ::

በጣም ጠቃሚው ፈተና፣ የእግዚአብሔር ሕልውና በማይሰማህ ጊዜ የምት ኖረው ሕይወት ነው:: አንዳንድ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሆን ብሎ ወደኋላ ስለ ሚያፈገፍግ ቅርብ መሆኑ *አይሰማንም*:: ሕዝቅያስ የተባለው ንጉሥ እንዲህ ያለው ፈተና ደርሶበታል:: እንዲህ ይላል፣ መጽሐፍ ቅዱስ:- *«እግዚአብሔር ሊፈትነውና በልቡ ያለውን ሁሉ ሊያውቅ ስለፈለገ ተወው»* 2ዜና. 32+31:: ሕዝቅያስ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረው:: ነገር ግን በሕይወቱ ወሳኝ በሆነ ጊዜ ባሕርይውን ሊፈትን፣ አንድ ድካምን ለመግለጥ እና ለበለጠ ኃላፊነት ይፈትነው ዘንድ ተወው::

ሕይወት ፈተና መሆኑን ስትረዳ፣ በሕይወትህ የማይጠቅም ነገር *ያለመኖሩን* ትገነዘባለህ:: በጣም ትንሹ ሁኔታ እንኳን ለባሕርይህ እድገት ትልቅ ሥፍራ አለው:: *እያንዳንዱ* ቀን ጠቃሚ ዕለት ነው! እያንዳንዱ ሰከንድ ደግሞ ባሕር

ይህ ሥር የሰደደ እንዲሆን፣ ፍቅርን እንድትገልጥ፣ ወይም በእግዚአብሔር ላይ እንድትደገፍ የሚያደርግ እድል ነው። አንዳንድ ፈተናዎች ከባድ ሲመስሉ፣ አንዳንዳቹ ደግሞ ልብ የማትላቸው ናቸው። ሁሉም ግን ዘላለማዊ እንደምታ አላቸው።

የምሥራቹ ግን የሕይወትን ፈተና ታልፍ ዘንድ እግዚአብሔር የሚፈልግ መሆኑ ነው። ፈተናዎችህ፣ ትቋቋማቸው ዘንድ እሱ ከሚሰጥህ ፀጋ የበለጡ ይሆሁ ዘንድ ፍጹም አይፈቅድም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው *የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ፣ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል*» 1ቆሮ. 10+13።



ፈተናህን ባለፍክ ቁጥር እግዚአብሔር ይመለከታል፤ በዘላለም ሕይወት ጊዜ ሊሸልምህም ዕቅድ ይይዛል። ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡- «*በፈተና የሚፀና ሰው የተባረከ ነው። ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል*» ያዕ. 1+12።

ምድራዊው ኑሮ የባለዐደራነት ሕይወት ነው። ይህ፣ ሁለተኛው የሕይወት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌት ነው። ምድራዊው ጊዜያችን፣ ኃይላችን፣ እውቀታችን፣ መልካም ስጦታዎቻችን፣ ከሰዎች ጋር የሚኖሩን ግንኙነቶችና ብልጽግናዎቻችን ሁሉ፣ እንጠብቃቸውና እናስተናግዳቸው ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰገሱን ስጦታዎች ናቸው። እኛ እግዚአብሔር የሚሰጠንን ነገሮች ሁሉ የምናስተዳድር ነን። ይህ ማስተዳደር የሚለው ጽንሰ አሳብ የሚጀምረው፣ በምድር ላይ ያለ የማንኛውም ነገርና ሰው ባለቤት፣ እግዚአብሔር ነው ከሚለው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣ ዓለምና በወስጧ የሚኖር ሁሉ የእግዘብሔር ነው*» መዝ 24+1።

በምድር ላይ በምንኖርበት አጭር ጊዜ፣ በእርግጥ የኛ ነው የምንለው ምንም ነገር የለም። በሕይወት በምንኖርበት ጊዜ እንገለገልባት ዘንድ እግዚአብሔር ምድርን ያውሰናል። ምድር እኛ ከመፈጠራችን በፊትም የእግዚአብሔር ሀብት ናት። በመሆኑም አንተ ስትሞት ለሌላ ሰው ደግሞ ያውሳታል። ለአንተ የተሰጠችህ ለጊዜው ትደሰትባት ዘንድ ብቻ ነው ።

እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን ከፈጠሯ በኋላ፣ ምድርንና የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ ይንከባከቧቸው ዘንድ አዘዛቸው፤ የንብረቱ ባለዐደራ አደረጋቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*እግዚአብሐርም ብዙ፣ ተባዙ ምድርንም ሙሉ*

*ለት፣ ገዙአትም፤ ... ብሎ ባረካቸው* » ዘፍ. 1÷28::

እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸው የመጀመሪያ ሥራ፣ በምድር ላይ ያለ ንብረቱን መጠበቅና ማስተዳደር ነው:: ይህ ሥራ ወይም ኃላፊነት አልተሻረም:: ዛሬም ቢሆን ከዓላማዎቻችን አንዱ ነው:: የምንገለገልበት ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር በዐደራ እንደተሰጠን ሊቆጠርና በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «... *ያልተቀበልኸው የራስህ የሆነ ነገር ምን አለ? ከተቀበልህ ታዲያ እንዳልተቀበልህ ለምን ትመካለህ?»* 1ቆሮ. 4÷7::

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ባልና ሚስት፣ ሀዋይ በምትባል ደሴት ባህር ዳርቻ ባለው ቤታቸው ውስጥ እኔና ሚስቴ ጥቂት የእረፍት ቀናችንን እንድናሳልፍ ፈቀዱልን:: ልንከፍል የማንችለው ዕድል ስለነበር፣ በሚገባ ተገለገልንበት:: «የራሳችሁ እንደሆነ ቆጥራችሁ ተገልገሉበት» ተብለን ነበር:: እንደተነገረን አደረግን:: በመዋኛው ሥፍራ ተንቦጫረቅንበት፣ ማቀዝቀዣው ውስጥ የነበረውን ምግብ ተመገብን፣ በፎጣዎችና በዕቃዎቹ ሁሉ ተጠቀምንባቸው፤ አልጋዎቹ ላይ ተዝናናን! ያን ሁሉ ስናደርግ ግን፣ ንብረቶቹ የኛ እንዳልሆኑ ስለምናውቅ፣ በጥንቃቄ ነበር የምንገለገልባቸው:: የኛ ባልሆነው ቤት ለመገልገል ባገኘነው ዕድል ተጠቀምንበት::

ባህላችን:- «ያንተ ካልሆነ፣ እንደፈለገህ አድርገው » ይላል:: ክርስቲያን ግን «ንብረቱ *የእግዚአብሔር* ስለሆነ፣ በተቻለኝ መጠን እጠነቀቅለታለሁ» በሚል ከፍተኛ ሥነ ምግባር ነው የሚኖረው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-

«*ባለ አደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው*» 1ቆሮ. 4÷2:: ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ሕይወት በአደራ የተሰጠን መሆኑን በመግለጥ፣ ስለ አደራው በእግዚአብሔር ዘንድ የሚኖርብንን ተጠያቂነት በብዙ ምሳሌዎች አብራርቷል:: ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተጠቀሰው የመክሊቶች ታሪክ፣ አንድ ጌታ ወደ ሌላ አገር ሲሄድ፣ ሀብቱን ለአገልጋዮቹ አደራ መስጠቱ ተገልጧል:: በተመለሰ ጊዜ እያንዳንዱ አገልጋይ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ያከናወነውን ተግባር መዝኖ የሚገባቸውን ሽልማት ይሰጣቸዋል:: አደራ ሰጪው ጌታ እንዲህ አለ:

«*አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤*
*በትንሽ ነገር ላይ ታማኝ ስለሆንህ*
*በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ወደ*
*ጌታህ ደስታ ግባ*» ማቴ. 25÷21::

በምድራዊው ሕይወትህ ፍጻሜ፣ እግዚአብሔር በአደራ በሰጠህ ነገር የተጠቀምህበት ሁኔታ ተመዝኖ

*እግዚአብሔር ደበልጥ በሰጠህ መጠን፣ ደበልጥ ኃላፊነት የሚሰማህ እንድትሆን ይፈልጋል::*

ተገቢውን ሽልማት ታገኛለህ:: ይህ ማለት የምታደርገው ሁሉ፣ ዕለታዊዎቹን ጥቃቅን ነገሮች እንኳን ጨምሮ፣ ዘላለማዊ እንደምታ አላቸው ማለት ነው:: ማንኛውንም ነገር *በአደራ* እንደተሰጠህ ቆጥረህ በጥንቃቄ የምትይዘው ከሆንህ፣ እግዚአብሔር በዘላለም ሕይወት ወቅት እውን የሚሆኑ ሦስት ተስፋዎችን ሰጥቶሃል:: *መጀመሪያ፣ ማረጋገጫን ወይም ተቀባይነትን* ከእግዚአብሔር ታገኛ ለህ:: «*አንተ መልካም ታማኝ* ባሪያ » ይልሃል:: ሁለተኛ ፣ *ሹመት ታገኛለህ፣* በዘላለም ሕይወትም የበለጠ ኀላፊነት ይሰጥሃል:: «በብዙ ነገሮች እሾምሃለሁ» *ይልሃል::* ከዚያም በከፍተኛ *የደስታ ዝግጅት:-* «ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» የሚለውን ክብር ታገኛለህ::

ገንዘብ ከእግዚአብሔር የሚመጣ ፈተና እና ዐደራ መሆኑን ብዙ ሰዎች ይዘነጋሉ:: እግዚአብሔር ገንዘብን በርሱ እንድንታመን ለማስተማሪያነት ይጠቀምበታል:: ገንዘብ ለብዙ ሰዎች፣ ትልቁ ፈተና ነው:: እግዚአብሔር ታማኝነታችንን ለመፈተን ሲል የገንዘብ አጠቃቀማችንን ይመለከታል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እንግዲህ በዚህ ዓለም ሀብት ካልታመናችሁ፣ እውነተኛውንማ ሀብት ማን ዐደራ ብሎ ይሰጣችኋል?»* ሉቃስ 16÷11::

ይህ እጅግ ጠቃሚ እውነት ነው:: በገንዘብ አጠቃቀሜና በመንፈሳዊ ሕይወቴ መካከል ቀጥታ ግንኙነት ያለ መሆኑን እግዚአብሔር ይገልጥልኛል:: ገንዘቤን *(«ዓለማዊ ብልፅግና»)*፣ የማስተዳድርበት ሁኔታ፣ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ በረከት *(«እውነተኛ ሀብት»)*፣ ምን ያህል ሊያምነኝ የሚችል መሆኑን ይወስናል:: ቁስቲ ልጠይቅህ ፤ የገንዘብ አያያዝህ እግዚአብሔር በሕይወትህ ከሁሉ ሁኑ ይበልጥ እንዳይሠራ እያደረገው ነው? ለመንፈሳዊ በረከት የምትታመን ሰው ነህ?

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- «*ብዙ ከተሰጠው ሁሉ፣ ብዙ ይፈለግበታል፣ ብዙ አደራም ከተቀበለም ብዙ ይጠበቅበታል*» ሉቃስ 12÷48:: ሕይወት ፈተናና አደራ ነው፣ እግዚአብሔር አብዝቶ በሰጠህ መጠን፣ ይበልጥ ታማኝ እንድትሆን ይፈልጋል::

## አምስተኛ ቀን
## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** ሕይወት ፈተናና አደራ ነው፡፡

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ ፡-** *«በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ፣ በትልቅም ይታመናል»* ሉቃስ 16፥10 ፡፡

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ ፡-** ከእግዚአብሔር የሆነ ፈተና መሆኑን አሁን የምረዳውና በቅርቡ የደረሰብኝ ነገር ምንድነው? እግዚአብሔር በዐደራ የሰጠኝ ታላላቅ ነገሮች ምንድናቸው?

# 6

# ሕይወት ጊዜያዊ ሥራ ነው

*እግዚአብሔር ሆይ፣ የሕይወቴን ፍጻሜ፣ የዘመኔንም ቍጥር አስታውቀኝ፤ አላፊ ጠፊ መሆኑንም ልረዳ።*

*መዝ. 39÷4*

*እኔ በምድር መጻተኛ ነኝ።*

*መዝ. 119÷19*

ምድራዊው ሕይወት ጊዜያዊ ሥራ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምድራዊው ሕይወት አጭር፣ ጊዜያዊና አላፊ መሆኑን በሚያስተምሩ ተምሳሌታዊ ወይም ዘይቤያዊ ገለጣዎች የተሞላ ነው። ሕይወት *በጭጋግ፣ በፈጣን ሯጭ፣ በእስትንፋስና በጭስነት እየተመሰለ* ተገልጧል። መጽሐፍ ቅዱስ፦ «*ዘመናችን በምድር ላይ እንደጥላ ነውና፤ እኛ የትናንት ብቻ ነን*» ይላል ኢዮብ 8÷9 ።

እጅግ ውጤታማ ሕይወት ለመኖር ትችል ዘንድ፣ ሁለት እውነቶችን በፍፁም መዘንጋት የለብህም። አንደኛ፣ ከዘላለም ጋር ሲነጻጸር ምድራዊው ሕይወት እጅግ አጭር መሆኑን። እና ሁለተኛ፣ ይህች ምድር ጊዜያዊ መኖሪያ መሆኗን። በምድር ላይ ብዙ ስለማትኖር፣ ከዓለም ጋር አትቆራኝ። ሕይወትን እሱ እንደሚያየው ለመመልከት እንድትችል እግዚአብሔር ይረዳህ ዘንድ ለምነው። ዳዊት እንዲህ በማለት ጸልዮአል፦ «*እግዚአብሔር ሆይ፣ የሕይወቴን ፍጻሜ፣ የዘመኔንም ቍጥር አስታውቀኝ፣ አላፊ ጠፊ መሆኑንም ልረዳ*» መዝ. 39÷4።

መጽሐፍ ቅዱስ በመደጋገም ምድራዊ ሕይወትን በባዕድ አገር ለጊዜው ከመኖር ጋር ያነጻጽረዋል። ምድር ቋሚ መኖሪያህ፣ ወይም የመጨረሻ መድረሻህ አይደለችም። የምትጎበኛት አላፊ መንገደኛ ነህ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ በምድር ላይ የምንቆይበትን አጭር ጊዜ ለመግለጥ *ስደተኛ፣ ወደ አንድ ቅዱስ ሥፍራ ተጓዥ፣ እንግዳ*፣ የሚሉ ቃላትን ተጠቅሟል። ዳዊት፦ «*እኔ በምድር*

*እንግዳ ነኝ»* መዝ. 118÷19 ብሏል:: ሐዋሪያው ጴጥሮስ ደግሞ እንዲህ ብሏል:- *«ለሰው ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደየሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ የምትጠሩት ከሆነ፣ በዚህ ምድር በእንግድነት ስትኖሩ በፍርሀት ኑሩ»* 1ጴጥ. 1÷17::

ብዙ ሰዎች ሥራ ፍለጋ ከሌላው የዓለም ክፍል እኔ ወደ ምኖርበት ግዛት፣ ካሊፎርኒያ መጥተዋል:: ዜግነታቸውን ግን በትውልድ አገራቸው እንዳጸኑ ናቸው:: ካሊፎርኒያ ውስጥ ሲቆዩ፣ ነዋሪነታቸው የሚረጋገጥበት ካርድ፣ ወይም ግሪን ካርድ የሚባለው እንዲኖራቸው ይጠየቃሉ:: ምንም እንኳን የአገሪቱ ዜጎች ባይሆኑ፣ ሥራ እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው መሆኑን ካርዱ ያረጋግጥላቸዋል:: ክርስቲያኖችም፣ ሰማያዊ ዜጎች መሆናችንን የሚያስታውሰን መንፈሳዊ «ግሪን ካርድ» ሊኖረን ይገባል:: እግዚአብሔር ፣ ልጆቹ የሆኑት ክርስቲያኖች፣ ስለ ሕይወት ዓለማውያን ከሚያስቡት በተለየ ሁኔታ ሊያስቡ ይገባል ይላል:: *« ... ልባቸው ያረፈው፣ በምድራዊ ነገር ላይ ነው:: እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ... ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠብቃለን»* ፊልጵ. 3÷19-20:: እውነተኛ አማኞች፣ በምድር በሚኖሩበት ጥቂት ዓመታት ከሚኖራቸው ይልቅ እጅግ የከበረ ነገር በዘላለም ሕይወት ያለ መሆኑን ይረዳሉ::

ማንነትህ ዘላለማዊ፣ አገርህ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ነው:: ይህን እውነት ስትጨብጥ፣ በምድር ላይ «ሁሉንም ነገር» ካልያዝኩ እያልክ መጨነቅን ታቆማለህ:: እዚህና አሁን በሆነ ኑሮ መኖርና በዙሪያችን ያለውን ዓለም ፋይዳ፣ ቀዳሚ ነገሮች፣ እንዲሁም የሕይወት ዘይቤ፣ ተቀብሎ መኖር አደጋ ያለው መሆኑን እግዚአብሔር በግልጥ ተናግሯል:: ከዓለም ፈተናዎች ጋር ስንዳራ፣ ያን ድርጊታችንን እግዚአብሔር መንፈሳዊ ማመንዘር ይለዋል::

> *ማንነትህ ዘላለማዊ፣*
> *አገርህ ደግሞ መንግሥተ*
> *ሰማያት ነው::*

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ከዓለም ጋር ወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ አታውቁምን? ስለዚህ የዓለም ወዳጅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆናል»* ያዕ. 4÷4::

ጠላት በሆነ አንድ አገር ውስጥ የአገርህ አምባሳደር ሆነህ እንድትሠራ እንደተጠየቅህ አድርገህ አስብ:: በዚሁ መሠረት ለአንተ አዲስ የሆነውን የአገሩን ቋንቋ መማር፣ ትሁት በመሆን ተልእኮን ለማከናወን ይረዳህ ዘንድ፣ የሕዝቡን ባህልና የባህል ልዩነቶችን መማር ይኖርብህ ይሆናል:: አምባሳደር ከሆንክ፣ እራስህን ከጠላት ለማግለል አትችልም:: ተልእኮህን ለመፈፀም፣

ከጠላቶችህ ጋር ግንኙነት መፍጠር ይኖርብሃል።

ነገር ግን በአምባሳደርነት የተላከበትን ባዕድ አገር ከአገርህ ይበልጥ ብትመርጥ፣ የጠበቀ ፍቅር ብትመሠርትና ተዝናንተህ ብትቀመጥስ? ታማኝነትና ቃል ኪዳንህ ይቀየራል። የአምባሳ ደርነት ተልዕኮህን መወጣት ያዳግትሃል። አገርህን በመወከል ፈንታ፣ እንደ ጠላት መሆን ትጀምራለህ፤ ከሀዲ ትሆናለህ።

**ስድስተኛ ቀን**

**ሕይወት ጊዜያዊ ሥራ ነው**

መጽሐፍ ቅዱስ *«እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን »* ይላል 2ቆሮ. 5+20። የሚያሳዝነው ነገር ግን፣ ብዙ ክርስቲያኖች ንጉሣቸውንና መንግሥቱን ከደዋል። አሁንም በምድር ላይ ነዋሪዎች በመሆናቸው ምድርን ዘላለማዊ
ቤታቸው እንደ ሆነ አድርገው በመቁጠር ሞኝነት ከተፀናወተው ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። ምድር ቤታቸው አይደለችም። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ እንዲህ ይላል:- *«ወዳጆች ሆይ፣ በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ እለምናችኋለሁ»* 1ጴጥ. 2+11። በዙሪያችን ካለው ነገር ጋር፣ በጣም እንዳንጣበቅ እግዚአብሔር ያስጠነቅቀናል፤ ጊዜያዊና አላፊ ነውና። *«በዚህ ዓለም ነገር የሚጠቀሙም እንደማይጠቀሙበት ይሁኑ፤ የዚህ ዓለም መልክ አላፊ ነውና»* 1ጴጥ. 2+11።

ከሌሎች ምዕተ ዓአታት ጋር ሲነፃፀር፣ በብዙዎቹ የምዕራቡ ዓለም አገሮች ውስጥ ኑሮ እንደዚህ ዘመን ቀላል የሆነበት ጊዜ የለም። ያለማቋረጥ የሚያ ዝናኑንና የሚያስደንቁን መስተንግዶዎች ይቀርቡልናል። አስደናቂ መስህቦች፣ ቀልብ ሳቢ መገናኛ ብዙሃን እና አስደሳች ልምምዶች ባሉበት በአሁኑ ጊዜ፣ የሕይወት ሁለንተና ግብ ደስታን ማሳደድ አለመሆኑን በቀላሉ መርሳት ይቻ ላል። ሕይወት ፈተና፣ አደራ እና ጊዜያዊ ሥራ መሆኑን ስናስታውስ ብቻ ነው፣ እነዚህ ነገሮች በሕይወታችን ላይ የሚያሳድሩብን ተፅዕኖ የላላ የሚሆነው። እኛ እኮ በመዘጋጀት ላይ ያለነው ለበለጠና ለተሻለ ሕይወት ነው ። *«የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፣ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው»* 2ቆሮ. 4+18።

እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በዓለም ሳለን፣ ሐዘን፣ መከራና ስደት ይደርስብናል። ይህ የሚያስረዳን፣ ይህች ምድር የመጨረሻ ቤታችን ያለመሆኗን እውነት ነው፣ ዮሐ. 16+33፤ 16+20፤ 15+18-19። አንዳንድ የእግዚአብሔር ተስፋዎች ያልተፈፀሙ፣ አንዳንድ ጸሎቶች ያልተመለሱ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎችም ፍትሕ የተጓደለ መምሰላቸውም የነገሮች ማብቂያ እዚህ አለመሆኑን ያስረዳናል።

ከዓለም ጋር እጅግ እንዳንጣበቅ ለማድረግ እግዚአብሔር በተወሰነ ደረጃም

ቢሆን፣ በኑሯችን ደስተኛ ያለመሆንና ያለመርካት ስሜት እንዲያድረብን ይፈቅዳል። በመሆኑም በአሁኑ ሕይወት ፍፁም ሊሆን የማይችለውንና በዘላለም ሕይወት ብቻ የሚሆነውን ነገር እንመኛለን። አሁንና እዚህ ሙሉ በሙሉ ደስተኞች አይደለንም፣ ልንሆንም አንችልም! መሬት የመጨረሻዋ መኖሪያችን አይደለችም። የተፈጠርነውም እጅግ ለተሻለ ነገር ነው።

ዓሣ የተፈጠረው ውሃ ውስጥ እንዲኖር ስለሆነ፣ የብስ ወይም መሬት ላይ ቢኖር በፍፁም ደስተኛ አይደለም። ንሥር በክንፉ እንዳይበር ቢደርግ በፍፁም ደስተኛ አይሆንም። የተፈጠርከው ለበለጠ ነገር ነው፤ በመሆኑም በምድር ላይ በፍፁም ሙሉ ደስተኛ አትሆንም። እዚህ ሳለህ አስደሳች ጊዜዎች ይኖሩሃል፤ ነገር ግን ይህ ደስታ እግዚአብሔር ካቀደልህ ነገር ጋር ሲነጻጸር ምንም አይደለም።

*መሬት የመጨረሻ መኖሪያችን አይደለችም፤ የተፈጠርነው እጅግ ለተሻለ ነገር ነው።*


ምድራዊው ሕይወት ጊዜያዊ ሥራ መሆኑን ተገንዝበህ፣ ፋይዳህን በሥር ነቀል ለውጥ መቀየር አለብህ። ጊዜያዊ ዎቹ ሳይሆኑ፣ ዘላለማዊ እሴቶችህ ናቸው የውሳኔዎችህ ሁሉ መሠረቶች መሆን ያለባቸው። ሲ. ኤስ. ሉዊስ:- «ዘላለማዊ ያልሆነ ነገር ሁሉ ለዘላለም ከንቱ ነው» ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስም:- *«ስለዚህ ዓይናችን የሚያተኩረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፣ የማይታየው ግን የዘላለም ነው»* 2ቆሮ. 4÷18 ይላል።

እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለው ዓላማ፣ ዓለም እንደሚለው ቁሳዊ ብልጽግና ወይም በዓለማዊ ቋንቋ ሕዝብ ያደነቀው ክንውን ነው ብለህ ካመንህ፣ ከባድ ስህተት ትፈጽማለህ። የተትረፈረፈ ሕይወት፣ ከተትረፈረፈ ቁሳዊ ብልጽግና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆንም በሥራ ወይም፣ በአገልግሎትም ስኬታማ ለመሆን ዋስትና አይደለም። በጊዜያዊ ሽልማት ላይ ትኩረትህን አታድርግ 1ጴጥ. 2÷11።

ጳውሎስ ታማኝ አገልጋይ ነበር፤ ግን ወህኒ ውስጥ ተጣለ። መጥምቁ ዮሐንስ ታማኝ ነበር፤ ነገር ግን እራሱን ተቀላ (ተሰዋ)። በሚልዮን የሚቆጠሩ ታማኝ ሰዎች፣ ለማዕት ሆነዋል፣ ሁሉን አጥተዋል ወይም ይህ ነው የሚባል ነገር ሳይኖራቸው የምድራዊው ሕይወታቸው ፍፃሜ ሆኗል። የምድራዊው *ሕይወት ማብቃት ግን የመጨረሻ ነገር አይደለም!*

በእግዚአብሔር አተያይ፣ ታላላቅ የእምነት ጀግኖች የሚባሉ ሰዎች ብልፅግና፣ የኑሮ ስኬት፣ እና በምድራዊ ሕይወታቸው ሥልጣንና ኃይል

ያላቸው ሳይሆኑ፣ የአሁን ሕይወታቸው ጊዜያዊ ሥራ እንደሆነ ቆጥረውና ቃል የተገባላቸውን ሽልማት በዘላለም ወቅት እንደሚያገኙ አምነው በታማኝነት የሚያገለግሉ ናቸው:: ስለ እግዚአብሔር የጀግንነት መስፈርት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እነዚህ ሁሉ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ሳያገኙ እምነታቸውን እንደጠበቁ ሞቱ:: ሆኖም ከሩቅ አይተው ሰላም አሉት፤ በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና እንግዶች መሆናቸውን ተገንዝበው ነበርና:: እንደዚህ የሚሉት ሰዎች የራሳቸው የሆነውን አገር እንደሚጠብቁ ያሳያሉ ... ::ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሲጠራ አላፈረም፤ ከተማን አዘጋጅቶ ላቸዋልና »* ዕብ. 11+13-16:: በምድር የምትኖርበት ጊዜ የሕይወትህ ሙሉ ታሪክ አይደለም:: ለቀጣዮቹ የሕይወትህ ምዕራፎች እስከ መንግሥተ ሰማያት ድረስ መጠበቅ አለብህ:: በምድር ላይ እንደመፃተኛ ለመ ኖር እምነትን ይጠይቃል::



ጡረታ ወጥቶ አገሩ ወደሆነችው አሜሪካ ይመለስ ስለ ነበረ አንድ ሚስዮ ናዊ የሚነገር የቆየ ታሪክ አለ:: ሰውየው ይጓዝ የነበረው በጊዜው የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ይጓዙበት በነበረ መርከብ ነበር:: ፕሬዝዳንቱ ወደሚሄዱበት ሲደርሱ፣ የሚያጨበጭብ ሕዝብ፣ ወታደራዊ ሙዚቃ፣ ቀይ ምንጣፍ፣ ባንዲራ፣ የመገናኛ ብዙሀን ሰዎች ተዘጋጅተውና ተሰብስበው ተቀበሏቸው:: ሚሲዮናዊው ግን ማንም ልብ ሳይለው ሹልክ ብሎ ከመርከቡ ወረደ:: ከዚያም በሀዘንና በቅሬታ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመርም ጀመር:: ይሄኔ እግዚአብሔርም በዝግታ:- «ልጄ ሆይ አንተ እኮ *ወደ እውነተኛው አገርህ ገና አልደረስክም»* ብሎ አስታወሰው::

*መንግሥተ ሰማያት እንደገባህ ገና ሁለት ሰከንድ ሳይሞላህ እንዲህ ትላለህ:- «ለምንድነው እንዲያ ጊዜያዊ በሆኑ ነገሮች ላይ በጣም አትኩሬ የነበረው?»*፤ ምን ሳስብ ነበር? ለምንድነው ዘላለማዊነት በሌለው ነገር ላይ ይህን ያህል ብዙ ጊዜና ጉልበት ያባከንኩት? የመጨነቅ ጊዜስ ያሳለፍኩት?»

ሕይወት ስትበረታብህ፣ ጥርጣሬ ሲጫንህ፣ ወይም ለክርስቶስ መኖር ያን ያህል ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል ወይ? የሚል ጥያቄ ወደ አእምሮህ በሚመጣብህ ጊዜ፣ ዘላለማዊው ቤትህ ገና እንዳልደረስክ እወቅ፣ የምትሞትበት ወቅት፣ ከቤ ትህ የምትለይበት ሳይሆን ወደ ቤትህ *የምትሄድበት* ነው::

## ስድስተኛ ቀን
## ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ይህ ዓለም ቤቴ አይደለም።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«ዐይናችን የሚያተኩረው በሚታየው ሳይ ሳይሆን፣ በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፣ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው»* 2ቆሮ. 4+18።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** ምድራዊው ሕይወት ጊዜያዊ ሥራ የመሆኑ እውነት የአሁኑን አኗኗሬን ሊለውጠው የሚገባው እንዴት ነው ?

# 7

# የሁሉም ነገር ምክንያት

*ሁሉ ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና ።*

*ሮሜ 11፥36*

*እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለራሱ ዓላማ ሠርቷል፡፡*

*ምሳሌ 16፥4*

ሁሉም ለእርሱ ነው፡፡

የዓለማት የመጨረሻ ግብ የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ ነው፡፡ አን ተን ጨምሮ የማንኛውም ነገር ህልውና ምክንያቱ ይኸው ነው፡፡ እግዚአ ብሔር ሁሉን ለክብሩ ፈጠረ፡፡ ከእርሱ ክብር ውጭ ምንም ሊኖር አይ ችልም፡፡

የእግዚአብሔር ክብር ምንድነው? ክብሩ እራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ክብሩ፣ ባሕርይው፣ የታላቅነቱ ክብደት፣ የግርማው ነፀብራቅ፣ የኃይሉ መገለጥ፣ እና የእርሱ መገኘት የሚፈጥረው ሁኔታ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ክብር፣ የመልካምነቱ መገለጥና የእሱነቱ መገለጫ ዘላለማዊ ባሕርያቱ ናቸው፡፡

የእግዚአብሔር ክብር ያለው የት ነው? እስቲ ዙሪያህን ተመልከት፡፡ በእግዚአብሔር የተፈጠረ *ነገር ሁሉ* በአንድም ሆነ በሌላ ሁኔታ ክብሩን ያንጸባርቃል፡፡ ክብሩን በሁሉም ሥፍራ፣ በዓይን ከማይታዩ ጥቃቅን ፍጥ ረታት አንስቶ እስከ ግዙፎቹ የከዋክብት ክምችቶች፣ በፀሐይ መጥለቅና በከዋክብት፣ በማዕበሎችና በሚለዋወጡ ወቅቶች ሁሉ ውስጥ እናየዋለን፡፡ ተፈጥሮ የፈጣሪያችንን ክብር ትገልጣለች፡፡ እግዚአብሔር ሀያል መሆኑን፣ በተፈጥሮ ልዩ ልዩ ነገሮች ደስ መሰኘቱን፣ የተፈጥሮን ውበት መውደዱን፣ ዓላማውን የማከናወኛ ሥርዓት ያለው መሆኑን፣ ጥበበኛና ፈጣሪ መሆኑን

ከተፈጥሮ እንማራለን:: መጽሐፍ ቅዱስ:- «*ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ*» መዝ. 19÷1 ይላል ::

እግዚአብሔር በታሪክ ሂደት ሁሉ ክብሩን በተለያየ መንገድ ለሰዎች ገልጧል:: መጀመሪያ ኤደን ገነት ውስጥ፣ ቀጥሎ ለሙሴ፣ ከዚያም በመገና

*ለእግዚአብሔር ክብር መኖር፣ በሕይወታችን ልንፈመው ከሚቻለን ከነውን ሁሉ ትልቁ ነው::*

ኛው ድንኳንና በቤተመቅደስ፣ ቀጥሎ በኢየሱስ፣ እና በቤተ ክርስቲያን በኩል ራሱን ገልጧል፤ ዘፍ. 3÷8፤ ዘፀ. 33÷18-23፤ 40÷33-38፤ 1ነገ. 7÷51፤8÷10-13፤ ዮሐ. 1÷14፤ ኤፌ. 2÷21-22፤ 2ቆሮ. 4÷6-7:: የተ ገለጠውም እንደሚባላ እሳት፣ እንደ ደመና፣ መብረቅ፣ ጭስ እና በሚያንፀባ ርቅ ብርሃን ነው፤ ዘፀ. 24÷17፤40÷34፤ መዝ. 21÷1፤ ኢሳ. 6÷3-4፤6÷1፤ ሉቃስ 2÷9:: በመንግሥተ ሰማያት፣ አስፈላጊው ብርሃን ሁሉ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ክብር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን ስለሚሰጣትና፣ በጉም መብራቷ ስለሆነ፣ ከተማዋ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጋትም* » ራእይ 21÷23::

የእግዚአብሔር ክብር ከሁሉም ይልቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ነው የተገ ለጠው:: የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔርን ባህርይ ያንጸባ ርቃል:: ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ፣ እግዚአብሔር ምን ይመስላል? ከሚለው የጥያቄ ጭለማ ወጥተናል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*እርሱ የእግዚአ ብሔር ክብር ነፀብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ...* » ዕብ. 1÷3:: ኢየሱስ ክርስ ቶስ ወደ ምድር የመጣው፣ እግዚአብሔርን በሙላት ለመረዳት ይቻለን ዘንድ ነው:- «*ቃልም ሥጋ ሆነ በመካከላችንም አደረ፣ ... ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን* » ዮሐ. 1÷14::

ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር ስለሆነ፣ የእግዚአብሔር የክብር *ባህርይ* አለው፤ ይህ እርሱነቱ ነው :: ፀሐይ ይበልጥ እንድታበራ ለማድረግ ችሎታው እንደሌ ለን ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ክብር ላይም ምንም ልናክልበት አንችልም:: ነገር ግን ክብሩን *እንድናውቅ*፣ ክብሩን *እንድንገነዘብ*፣ *እንድናወድስ*፣ *እንድናመ ሰግን*፣ ክብሩን *እንድናንጸባርቅ* እና ለክብሩ *እንድንኖር* ታዝዘናል 1ዜና 16÷24፤ መዝ.29÷1፤ 66÷2፤96÷7:: ለምን? ምክንያቱም ይህ ሁሉ ለእግዚአብሔር ይገባዋልና ነው:: የተቻለንን ያህል ክብርን ለእርሱ መስጠት አለብን:: ሁሉን የፈጠረ እርሱ እንደመሆኑ፣ ክብር ሁሉ ሊሰጠው ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ጌታችንና አምላካችን ሆይ፣ ክብርና ሞገሥ፣ ኃይልም ልትቀበል*

*ይገባሃል»* ራዕይ 4÷11::

በዓለማት ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍጡራን ሁለቱ ብቻ ናቸው ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት የሚያቅታቸው:: እነሱም፣ የወደቁት መላእክት (አጋንንት) እና እኛ (ሰዎች) ነን:: የኃጢአት ሁሉ ሥር ለእግዚአብሔር ክብርን አለመስ ጠትና ከእርሱ ይልቅ ሌላ ነገርን መውደድ ነው:: ለእርሱ ክብርን አለመስ ጠት እብሪትና አመጽ ሲሆን፣ ሰይጣንን ለውድቀት የዳረገውም ይሄው ኃጢአ ት ነው:: የእኛም ውድቀት ከዚሁ ኃጢአት ነው የመጣው :: ሁላችን ለእግ ዚአብሔር ሳይሆን፣ በተለያዩ መንገዶች ለራሳችን ክብር ነው የኖርነው:: *«ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር ጐድሎአቸዋል»* ሮሜ 3÷23 ይላል መጽሐፍ ቅዱስ ::

እግዚአብሔር ከሕይወታችን ሊቀበል የሚገባውን ሙሉ አክብሮት ማንኛ ችንም አልሰጠነውም:: ይህ ከምንሠራው ኃጢአት ሁሉ አስከፊውና ትልቁ ስህተት ነው:: በሌላ በኩል ግን፣ ለእግዚአብሔር ክብር መኖር፣ በሕይወታችን ልንፈጽመው ከሚቻለን ክንውን ሁሉ ትልቁ ነው:: እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል:- *«ለክብሬም የፈጠርሁትን፣ ያበጀሁትንና የሠራሁትን ስምጡ»* ኢሳ. 43÷7:: የሕይወታችን ትልቁ ግብ ወይም ዓላማ ይህ መሆን አለበት::

## ለእግዚአብሔር ክብርን ልሰጠው የምችለው እንዴት ነው?

ኢየሱስ ለአብ እንዲህ ብሏል:- *«የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበር ሁህ»* ዮሐ. 17÷4:: ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ዓላማ በምድር ላይ በማከና ወን አከበረው:: እኛም እግዚአብሔርን በተመሳሳይ ሁኔታ እናከብረዋለን:: በተ ፈጥሮ ውስጥ፣ ማንኛውም ነገር ዓላማውን በሚያከናውንበት ጊዜ እግዚአብሔ ርን ያከብረዋል:: አእዋፍ በመብረር፣ በማዜም፣ ጎጆ በመሥራት እና እግዚአ ብሔር ለእነርሱ የወሰነላቸውን ሌሎች ሥራዎች በማከናወን እግዚአብሔርን ያከብሩታል:: ኢምንቱ ፍጡር ጉንዳን እንኳን የተፈጠረበትን ዓላማ ባከናወነ ጊዜ እግዚአብሔርን ያከብረዋል:: እግዚአብሔር ጉንዳኖችን የፈጠራቸው፣ ጉን ዳኖች ይሆኑ ዘንድ ነው:: አንተ ንም አንተ እንድትሆን ነው የፈጠ ረህ:: ቅዱስ ኤሬኔዎስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን አባት እንዲህ ብሎ ነበር :- «የእግዚአብሔር ክብር ሰው ሕይወትን በሙላት ሲኖር ይገለጣል::»

> *ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር ዓላማውን በሚያከናውንበት ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ያከብረዋል::*

እግዚአብሔር የሚከበርባቸው ብዙ መንገዶች ቢኖሩም፣ እርሱ ለሕይወትህ

ባለው አምስት ዓላማዎች ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ የዚህን መጽሐፍ ቀሪ ክፍል እነዚህኑ ዓላማዎች በመመልከት እንፈጽመዋለን፡፡ አስቀድመን ግን ቅኝት እናድርግ፡፡

**ስናመልከው እግዚአብሔርን እናከብረዋለን፡፡** አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት የመጀመሪያው ኃላፊነታችን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ደስ በመሰኘት እናመልከዋለን፡፡ ሲ.ኤስ. ሌዊስ ፡- «እግዚአብሔር እንድናከብረው ሲያዘን፣ በእርሱ ደስ እንድንሰኝ መጋበዙ ነው» ይላል፡፡ እግዚአብሔር አምልኳችን በግዴታ የሚነሣሣ ሳይሆን ከፍቅር፣ ከምሥጋና እና ከደስታ የተነሣሣ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

ጆን ፓይፐር የተባሉ ሰው፡- «እኛ በእግዚአብሔር ይበልጥ ስንረካ፣ እርሱ ይበልጥ ይከብራል» ብለዋል፡፡

አምልኮ ከምሥጋና፣ ከዝማሬና ጸሎት ያለፈ ነው፡፡ በእግዚአብሔር *ደስ የመሰኘት አኗኗር*፣ እሱን *መውደድ*፣ ለዓላማው *መገልገያ ለመሆን* እራሳችንን *መስጠት* ነው፡፡ ሕይወትህን ለእግዚአብሔር ክብር ስትገለገልበት፣ ድርጊትህ ሁሉ አምልኮ ይሆናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ»* ሮሜ 6÷13፡፡

**ሌሎች አማኞችን በመውደድ እግዚአብሔርን እናከብረዋለን፡፡** ዳግም በመንፈስ በተወለድህ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ሆነሃል፡፡ ኢየሱስን መከተል የማመን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱ ቤተሰብ መሆንንና የእግዚአብሔር *በተሰብ* አባላትን መውደድንም ይጨምራል፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ብሏል፡- *«ወንድሞቻችንን ስለምንወድ፣ ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን»* 1ዮሐ. 3÷14፡፡ ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ ብሏል፡- *«እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሆን ዘንድ ክርስቶስ እንደተቀበላችሁ እርስ በርሳችሁ ተቀበሉ»* ሮሜ 15÷7፡፡

ሰባተኛ ቀን
የሁሉም
ነገር
ምክንያት

እግዚአብሔር እንደሚያፈቅር፣ ማፍቀርን መማር የአንተ ኃላፊነት ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፣ ማፍቀር እርሱን ያከብረዋል፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል ፡- *«አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እንግዲህ እኔ እንደወደድኳችሁ፣ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡፡ እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ»* ዮሐ. 13÷34-35፡፡

**ክርስቶስን በመምሰል እግዚአብሔርን እናከብረዋለን፡፡** ከመንፈስ ዳግም በመወለድ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ከሆንን፣ ወደ መንፈሳዊ ጉልምስና (ብስለት) እናድግ ዘንድ እርሱ ይፈልጋል፡፡ መንፈሳዊ ጉልምስና ወይም እድገት

ምን ይመስላል? መንፈሳዊ ጉልምስና፣ በአስተሳሰብ፣ በስሜትና ድርጊታችን ኢየሱስን መምሰል ነው፡፡ የክርስቶስን ባሕርይ በሕይወትህ ባዳበርክ ቁጥር፣ እግዚአብሔርን ይበልጥ ታከብረዋለህ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስታወት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንደንመስል ከክብር ወደክብር እንለወጣለን»* 2ቆሮ. 3÷18፡፡

ክርስቶስን በተቀበልክ ጊዜ እግዚአብሔር አዲስ ሕይወትና አዲስ ተፈጥሮ ሰጥቶሃል፡፡ በመሆኑም፣ በቀሪው ምድራዊ ሕይወትህ፣ ባህርይህን የመለወጡን ሂደት ሊቀጥል ይፈልጋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሚገኘው የጽድቅ ፍሬ እንድትሞሉ ነው»* ፊልጵ. 1÷11፤ ዮሐ. 15÷8 ይላል፡፡

**በስጦታዎቻችን ሌሎችን በማገልገል፣ እግዚአብሔርን እናከብረዋለን፡፡** ሁላችንም ከተሰጥኦዎች፣ ስጦታዎች፣ ሞያዎችና ችሎታዎች ጋር በልዩ ሁኔታ በእግዚአብሔር ተፈጥረናል፡፡ እንዲህ የተሠራኸው በአጋጣሚ አይደለም፡፡ ለግላዊ ዓላማም አይደለም እግዚአብሔር ችሎታዎችን የሰጠህ፡፡ ሌሎች ሰዎች ለአንተ ጥቅም ያውሏቸው ዘንድ ችሎታዎች እንደተሰጧቸው ሁሉ፣ ለአንተ የተሰጡህም ለሌሎች ጥቅም ይሆኑ ዘንድ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል፤ ... ይሄውም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንዲከብር ነው »* 1ጴጥ. 4÷10-11፤ 2ቆሮ. 8÷19፡፡


**ስለ እርሱ ለሌሎች በመንገር እግዚአብሔርን እናከብረዋለን፡፡** እግዚአብሔር ዓላማውና ፍቅሩ ምስጢር እንዲሆን አይፈልግም፡፡ እውነትን ከተረዳን በኋላ፣ ያንን ለሌሎች እንድናካፍል ይፈልጋል፡፡ ሰዎችን ከኢየሱስ ጋር ማስተዋወቅ፣ ዓላማቸውን ያውቁ ዘንድ መርዳትና ለዘላለማዊ ግባቸውም ማዘጋጀት ታላቅ ዕድል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«ለብዙ ሰዎች እየደረሰ ያለው ጸጋ፣ ለእግዚአብሔር ክብር በምሥጋና ላይ ምስጋናን እንድንጨምር ይህ ሁሉ ለእናንተ ጥቅም ሆኗል፡፡»* 2ቆሮ. 4÷15 ይላል፡፡

## ለምን ዓላማ ነው የምትኖረው?

ቀሪ ሕይወትህን ለእግዚአብሔር ክብር መኖር፣ የጉዳዮችህን ቅደም ተከተል፣ የጊዜ አጠቃቀምህን፣ ከሰዎች ጋር የሚኖሩህን ግንኙነቶችና ሌሎችንም ጉዳዮች እንድትቀይር ይጠይቅሃል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ከቀላሉ ይልቅ፣ አስቸጋሪ አቅጣጫን የመምረጥ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ እንኳን እንዲህ ካለው ሁኔታ ጋር ታግሏል፡፡ ወደ መስቀል ሞት መሄጃው እንደ ደረሰ ባወቀ

ጊዜ እንዲህ በማለት ጮኋል፡- «*አሁንስ ነፍሴ ተጨነቀች፤ ምን ልበል? አባት ሆይ፤ ከዚህች ሰዓት ታድነኝ? የለም፤ ይሁን የመጣሁት ለዚህች ሰዓት ነውና። አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው*» ዮሐ. 12÷27-28።

ኢየሱስ መስቀለኛ መንገድ ላይ መቆምን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ ነበር። የእግዚአብሔርን ዓላማ በመፈጸም እርሱን ያስከብር፣ ወይስ ወደኋላ አፈግፍጎ



ምቹና ራስ ወዳድ በሆነ ሕይወት ይኑር? አንተም ተመሳሳይ ምርጫ ይገጥምሃል። ለራስህ ግቦች፣ ምቾትና ደስታ መኖር፣ ወይስ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሽልማት እንዳዘጋጀልህ በማወቅ፣ ቀሪ ሕይወትህን ለእርሱ ክብር ትኖራለህ? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*ሕይወቱን የሚወድ ያጣታል፤ በዚህ ዓለም ሕይወቱን የሚጠላ ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል*» ዮሐ. 12÷25።

ለዚህ ጉዳይ ውሳኔ የመስጫው ጊዜ አሁን ነው። ለማን ልትኖር አስበሃል? ለራስህ ወይስ ለእግዚአብሔር? ለእግዚአብሔር ለመኖር ብርታቱ ያለህ ወይም የሌለህ መሆኑን በማሰላሰል ታመነታ ይሆናል፤ አትጨነቅ። ለእግዚአብሔር መኖርን ከመረጥህ፣ የሚያስፈልግህን እርሱ ይሰጥሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል*» 2ጴጥ. 1÷3።

አሁን በዚህ ጊዜ፣ በእርሱ የተፈጠርክበትን ዓላማ በማከናወን ለክብሩ ትኖር ዘንድ እግዚአብሔር ይጋብዝሃል። ብቸኛው የኑሮ አቅጣጫ በእርግጥ ይኸው ነው። ከዚህ የተለየው ሁሉ ዝም ብሎ ኑሮ ይሆናል። እውነተኛው ኑሮ የሚጀምረው፣ ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመስጠት ነው። ይህን ላለማድረግህ እርግጠኛ ካልሆንክ፣ ማድረግ የሚኖርብህ፣ ክርስቶስን መቀበልና ማመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ቃል ይገባል፡- «*ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው*» ዮሐ. 1÷12። የእግዚአብሔርን ስጦታ ትቀበላለህን?

በመጀመሪያ እመን። እግዚአብሔር እንደሚወድህና ለዓላማው እንደፈጠረህ፣ አጋጣሚ አለመሆንህን፣ ዘላለም ለመኖር መፈጠርህንም እመን። እግዚአብሔር፣ ለአንተ ሲል በመስቀል ላይ ከሞተው ኢየሱስ ጋር ግንኙነት እንዲኖርህ የመረጠህ መሆኑን እመን። ያደረግኸው ምንም ይሁን ምን፣ እግዚአብሔር በደልህን ይቅር ሊል እንደሚፈልግ እመን።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ተቀበል። ኢየሱስን እንደ ጌታህና አዳኝህ አድርግና ወደ ሕይወትህ ጋብዘው። ለኃጢአትህ የሚሰጥህን ይቅርታ ተቀበል። የሕይወትህን

*ለእርሱ ትኖር ዘንድ የሚያስ ፈልግህን ሁሉ ኢየሱስ ይሰጥሃል።*

ዓላማ ታከናውን ዘንድ ኃይል የሚሰጥህን የኢየሱስን መንፈስ ተቀበል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው*» ዮሐ. 3፥36። ይህን ጽሑፍ የምታነበው የትም ይሁን የት፤ አንገትህን አቀርቅረህ ዘላለምህን የሚቀይረውን ይህን ፀሎት በለሆሳስ ትጸልይ ዘንድ እጋብዝሃለሁ፡- «*ኢየሱስ ሆይ! በአንተ አምናለሁ፣ እቀበልሃማለሁ*» በል፣ አሁን አድርገው።

ጸሎቱን ከልብህ ከጸለይህ፣ እንኳን ደስ አለህ! ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብነት እንኳን በደህና መጣህ! አሁን እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ልታውቅና ልትኖረው ዝግጁ ነህ። ይህንኑ ቁም ነገር ለሌሎች እንድት ነግር አበረታታሃለሁ።

ሰባተኛ ቀን

ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡** ሁሉ ለእርሱ ነው።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** «*ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና*» *ሮሜ 11፥36።*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** በተለመደው ዕለታዊ ተግባሬ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ክብር ይበልጥ ልብ ላደርገው የምችለው በየትኛው ነው?

# ዓላማ ቁጥር 1



# ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ነህ

*እነርሱ የክብሩ መገለጫ እንዲሆኑ፣ እግዚአብሔር የተከላቸው፣ የጽድቅ ዛፎች ተብለው ይጠራሉ።*

ኢሳ. 61÷3

# ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ነህ

*አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፣ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፣ ሆነዋልምና፡*

ራእይ 4÷11

*እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይለዋልና ::*

መዝ. 149÷4

ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ነህ::

ወደዚህ ዓለም በተወለድህ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የማይታይ ምስክር ሆኖ መወለጃህ *ሥፍራ* ነበር:: ህያው ትሆን ዘንድ ይፈልግ ስለ ነበር፣ በመወለድህ ታላቅ ደስታ ሆኖለታል:: አንተን መፍጠሩ *አሳስፈለገውም* ነበር፤ ለራሱ ደስታ ሲል ግን ሊፈጥርህ *መረጠ*: የምትኖረው፣ ለጥቅሙ፣ ለክብሩ፣ ለዓላማውና ለደስታው ነው::

እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት መኖር የሕይወትህ የመጀመሪያ ዓላማ ነው:: ይህን እውነት በሙላት ስትረዳ ፣ የማልጠቅም ነኝ በሚል ስሜት ዳግመኛ አትቸገርም:: የምትረዳው ነገር ጠቃሚ ሰው መሆንህን ያረጋግጥልሃል:: ለእግዚአብሔር ያን ያህል ጠቃሚ ከሆንክና ከእርሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር የተገባህ አድርጎ ከቆጠረህ፣ ከዚህ የላቀ ምን ጠቃሚነት ይኖርሃል? የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ ከፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ይበልጥ ደስ ታሰኘዋለህ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን*» ኤፌ. 1÷5::

እግዚአብሔር ከሰጠህ ታላላቅ ነገሮች አንዱ፣ ደስተኛ መሆን ነው::

ደስታን ትለማመደው ዘንድ እግዚአብሔር በአምስት የስሜት ሕዋሳት አቀና ብሮሃል:: ሕይወትን እንድትኖረው ብቻ ሳይሆን፣ እንድትደሰትበትም ይፈል ጋል:: ደስተኛ ለመሆን የቻልከው፣ እግዚአብሔር *በአምሳሉ* ስለ ፈጠረህ ነው::

እግዚአብሔር እንደ እኛ ስሜት ያለው መሆኑን ሁልጊዜ እንዘነጋለን:: ስለ ነገሮች በጥልቀት ይሰማዋል:: የሚያዝን፣ የሚቀና፣ የሚቆጣ፣ የሚራራ፣ እንዲሁም የሚደሰትና የሚረካ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ይወዳል፣ ሀሴት ያደርጋል፣ ደስታ ይሰማዋል፣ ከዚያም አልፎ ይስቃል፣ ዘፍ. 6÷6፤ ዘፀ. 20÷5፤ ዘዳ. 32÷36፤ መሳ. 2÷19፤ 1ነገ. 10÷9፤ 1ዜና 16÷27፤ መዝ. 2÷4፤5÷5፤ 18÷19፤35÷27፤ 37÷23፤ 103÷13፤104÷31፤ ሕዝ. 5÷13፤1ዮሐ. 4÷16::

**እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት «አምልኮ» ይባላል::** መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ነገር ግን እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል»* መዝ. 147÷11::

የምታደርገው ማንኛውም ነገር፣ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ከሆነ፣ ድርጊቱ አምልኮ ነው:: አምልኮ እንደ እንቁ *ብዙ ገፅታ* አለው:: ስለ አምልኮ መገንዘብ ያለብንን ነገር *ሁሉ* ለመዘርዘር ቢፈለግ፣ አያሌ መጻሕፍት ይወጣ ዋል:: በመሆኑም በዚህ ክፍል የምንመለከተው፣ የአምልኮን መሠረታዊ ነገሮች ብቻ ይሆናል::

*ሥነ-ሰብዓውያን* (Anthropologists) አምልኮ፣ ውስጣዊ ሕልውናችን ውስጥ በእግዚአብሔር ሰርጾ የተሠራ እና በዓለም ደረጃ በሰዎች ሁሉ ዘንድ የሚገኝ መነሣሣት ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ውስጣችን የተሠራ ፍላጎት ነው ይላሉ:: አምልኮ እንደ መመገብና መተንፈስ ተፈጥሯዊ ነው:: እግዚአ ብሔርን ባናመልክ፣ በምትኩ ሌላ የምናመልከው ነገር ይኖረናል፤ እራሳችንን እንኳን ቢሆን:: እግዚአ ብሔር ከአምልኮ ፍላጎት ጋር የፈጠ ረን፣ አምልኮን ስለሚፈልግ ነው:: ኢየሱስ:- *«አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰ ግዱትን ይፈልጋል»* ዮሐ. 4÷23 ብሏል::

> *የምታደርገው ማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን የሚያስደስት ከሆነ ድርጊቱ አምልኮ ነው::*

በሃይማኖታዊ ልምምድህ መሠረት ስለ አምልኮ ያለህን ግንዛቤ ለማስፋት ትፈልግ ይሆናል:: ስለ አምልኮ ስታስብ የዝማሬ፣ የጸሎትና የስብከት አገል ግሎት ስላለባት ቤተ ክርስቲያን ታስብም ይሆናል:: ወይም ስለ ዝግጅቶች፣ የሻማ መብራቶችና ስለ ጌታ እራት ታስባለህ:: ወይም ስለ ፈውስ፣ ስለ ተዓም

ራትና ስለሚያስፈነድቁ ልምምዶች ታስብ ይሆናል፡፡ አምልኮ እነዚህን ሁሉ የሚያካትት ሊሆን ቢችልም፣ ከነዚህ ሁሉ *እጅግ የላቀ* ድርጊትና ሁለንተ ናዊ አኗኗር ነው፡፡

**አምልኮ ከመዝሙርም በላይ ነው፡፡** ለብዙ ሰዎች ማምለክ ማለት መዘመር ማለት ነው፡፡ «በቤተ ክርስቲያናችን መጀመሪያ አምልኮ ይካሄድና ትምህርት ይቀጥላል» ይላሉ፡፡ ይህ ትልቅ የግንዛቤ ስህተት ነው፡፡ *እያንዳንዱ* የቤተ ክርስ ቲያን አገልግሎት ጸሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ ዝማሬው፣ ንስሐ፣ ጥሞና፣ ስብከት ማድመጥ፣የሚማሩትን ማስታወሻ ላይ መጻፍ፣ መባ መስጠት፣ ጥምቀት፣ የጌታ እራትና ከሌሎች አማኞች ጋር ሰላምታ መለዋወጡ እንኳን ሳይቀር፣ አምልኮአዊ ድርጊት ነው፡፡

*አምልኮ፣ ከመዝሙርም በላይ ነው፡፡*

አምልኮ ከዝማሬ እጅግ ይቀድማል፡፡ አዳም በዔደን ገነት የአትክልት ሥፍራ አምልኳል፡፡ ከዘፍጥረት 4፥21 ከዩባል መወለድ በፊት ሙዚቃ አልተ ጠቀሰም፡፡ አምልኮዎች ዝማሬ ብቻ ቢሆኑ ኖሮ፣ ዝማሬ የማይሆንላቸው ሁሉ ፍፁም አያመልኩም ነበር፡፡ አምልኮ ከዝማሬ የበለጠ ነገር ነው፡፡

ይበልጥ አሳዛኙ ነገር ደግሞ፣ ብዙ ጊዜ «አምልኮ» ከዝማሬም የተለየ ዓይነት ዝማሬ ሆኖ ለአጠቃቀም መጠቀሱ ነው፡፡ «መጀመሪያ አንድ መዝሙር ዘመርን፤ ቀጥሎ ደግሞ *የምስጋናና አምልኮ* መዝሙር ዘመርን» ወይም «ፈጣኖ ቹን የምስጋና መዝሙሮች እወዳቸዋለሁ፤ ለስላሳዎቹን የአምልኮ ዝማሬዎች ግን ከሁሉም ይበልጥ እወዳቸዋለሁ» የሚሉ ሰዎች አሉ፡፡ በዚህ አባባል መሠ ረት አንድ መዝሙር ከፍ ያለ ድምፅ ያለውና ፈጣን ከሆነ፣ ወይም ለየት ባለ የሙዚቃ መሣሪያ ከታጀበ፣ «የምሥጋና ዝማሬ » ይባላል፡፡ ዝግ እና ረጋ፣ ደግሞም ረቀቅ ያለ ከሆነና ምናልባትም በጊታር ከታጀበ ግን አምልኮ ነው፡፡ ይህ «አምልኮ» ለሚለው ቃል የተሰጠ የተሳሳተ ትርጉም ነው፡፡

አምልኮ ከዝማሬ ዘይቤ፣ ከድምፁ ብዛት ወይም ፍጥነት ጋር ምንም ግን ኙነት የለውም፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ዓይነት ሙዚቃ ፣ ፈጣንና ዝግ ያለውን፣ የጎላውንና ለስላሳውን፣ አዲስና አሮጌውን ይወዳል፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም የፈጠራቸው እርሱ ነው፡፡ ምናልባት አንተ ሁሉንም አትወድ ይሆናል፤ እግዚአብሔር ግን ይወዳቸዋል፡፡ በመንፈስና በእውነት ለእግዚአብ ሔር የሚቀርብ እስከሆነ ድረስ አምልኮ ነው፡፡

ብዙ ጊዜ በአምልኮ የሚቀርቡ መዝሙሮችን በተመለከተ፣ ክርስቲያኖች አይስማሙም፡፡ የሚወዱት የአዘማመር ዘይቤ ከሁሉ ይልቅ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊና እግዚአብሔርን የሚያከብር መሆኑን እየገለጡ አጥብቀው ይከራ

ከራሱ:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የዝማሬ ዓይነት የሚባል ነገር የለም:: የሙዚቃ ኖታዎች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሉም፤ መጽሐፉ በተጻፈበት ዘመን የነበሩት የሙዚቃ መሣሪያዎችም አሁን የሉንም::

በግልጥ ለመናገር፣ ከሁሉ አስበልጠህ የምትወደው የዝማሬ ሁኔታ እግዚአብሔርን ከማስከበር ይልቅ፣ ስለ አንተ የጀርባ ታሪክና ማንነት ነው የሚናገረው:: የአንዱ ብሔረሰብ ሙዚቃ ለሌላው ሁከት ወይም ጫጫታ መስሎ ይሰማው ይሆናል:: እግዚአብሔር ግን ልዩነታቸውን ይወዳል፣ በሁሉም ደስ ይሰኝባቸዋል::

ክርስቲያናዊ ሥነ-ግጥም እንጂ «ክርስቲያናዊ» ሙዚቃ የሚባል ነገር የለም:: መዝሙርን የተቀደሰ የሚያደርጉት ቃላቱ እንጂ ዜማው አይደለም:: መንፈሳዊ ዜማዎች የሉም:: አንድ ዜማ ያለ ቃላቱ ብጫወትልህ፣ ዜማው ክርስቲያናዊ መሆኑን የምትለይበት መንገድ የለም::

> ስምንተኛ ቀን
> ለእግዚአብሔር
> ደስታ
> የታቀድህ
> ነህ

**አምልኮ ለአንተ ጥቅም አይደለም::** እንደ መጋቢነቴ፣ እንዲህ የሚሉ ማስታዎሻዎች ይደርሱኛል:- «የዛሬውን አምልኮ ወድጄዋለሁ፤ ብዙም ተባርኬበታለሁ»:: ይህ ስለ አምልኮ፣ ሌላው የተሳሳተ ግንዛቤ ነው:: አምልኮው ለአንተ ጥቅም አይደለም:: ለእግዚአብሔር ጥቅም ነው የምናመልከው:: በምናመልክበት ጊዜ፣ ዓላማችን እግዚአብሔርን እንጂ፣ እራሳችንን ማስደሰት አይደለም::

«በዛሬው አምልኮ ምንም አልተባረክሁም» ያልክበት ጊዜ ካለ፣ የአምልኮህ ምክንያት የተሳሳተ ነበር ማለት ነው:: አምልኮ፣ ለእግዚአብሔር እንጂ ለአንተ አይደለም:: እርግጥ ብዙ «አምልኮዎች» የአንድነት፣ የመተናነፅና የወንጌል ምስክርነት ጉዳዮችን ያካተቱ በመሆናቸው ጥቅም አላቸው:: የምናመልከው ግን እራሳችንን ለማስደሰት አይደለም:: ዓላማችን ፈጣሪያችንን ማክበርና ደስ ማሰኘት ነው::

ኢሳይያስ 29 ውስጥ እግዚአብሔር በተከፈለ ልብና በግብዝነት ስለሚቀርብ አምልኮ ያለውን ነቀፌታ ይገልጣል:: ሕዝቡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ቅድስና የራቀው ጸሎት ከልብ ያልሆነ ምስጋና፣ ባዶ ቃላትና፣ ትርጉሙን እንኳን የማያስቡበት ሥርዓት ነበር:: የእግዚአብሔር ልብ በፍቅራችንና በመስጠታችን እንጂ፣ በሥርዓታዊ አምልኮ አይነካም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፡ በከንፈሩም ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው»* ኢሳ. 29÷13::

አምልኮ የሕይወትህ አንድ ክፍል ሳይሆን፣ ሕይወትህ ነው። አምልኮ በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ አገልግሎት ብቻ አይደለም። «ፊቱን ዘወትር ፈልጉ» መዝ. 105፥4 ተብለናል። «ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያው ድረስ» እግዚአብሔርን እንድናመሰግንም መዝ. 113፥3 ውስጥ ታዝዘናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው፣ ሰዎች ሥራህ ቦታ፣ ቤታቸው ውስጥ፣ በጦርነት ጊዜ፣ እስር ቤት ውስጥ ተኝተው እንኳን እግዚአብሔርን አመስግነውታል! ምሥጋና ማለዳ ከእንቅልፍህ ነቅተህ ዓይንህን ስትከፍት የመጀመሪያ፣ መሽቶ ዓይኖችህን ስትከድን ደግሞ የመጨረሻ፣ ተግባርህ መሆን አለበት፤ መዝ. 119፥147፤ 5፥3፤63፥6፤11፥62። ዳዊት፦ «እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እባርከዋለሁ፣ ምስጋናውም ዘወትር ከአፌ አይለይም» መዝ. 34፥1 ብሏል።

ማንኛውንም ክንውን ለእግዚአብሔር ምሥጋና፣ ለእርሱ ክብርና ደስታ የምታደርገው ከሆነ፣ ወደ አምልኮነት ይለወጣል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።» 1ቆሮ. 10፥31። ማርቲን ሉተር፦ «ላሞችን የምታልብ አገልጋይ እንኳን ያን የምታደርገው፣ ለእግዚአብሔር ክብር ሊሆን ይችላል» ብሏል።

ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር ለማድረግ እንዴት ይቻላል? የምታደርገውን ሁሉ ለኢየሱስ እንደምታደርገው በመቁጠርና፣ ስታከናውነውም ከእርሱ ጋር የማያቋርጥ የጸሎት ግንኙነት በማድረግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉት ቆጥራችሁ፣ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት » ቆላ. 3፥23።

የአምልኳዊ ሕይወት ዘይቤ ምስጢር ማንኛውንም ተግባር ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደምታደርገው በመቁጠር ማድረግ ነው። ይህን ማለት በአጭሩ «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ



እለምናችኋለሁ» ሮሜ 12፥1 ማለት ነው። ሥራ፣ የእግዚአብሔር ስታደርገውና፣ እርሱ አጠገብህ እንዳለ ቆጥረህ ስትሠራው አምልኮ ይሆናል።

ሚስቴን መጀመሪያ እንዳፈቀርኳት፣ ስለ እሷ ሳላቋርጥ አስብ ነበር። ቁርሴን ስመገብ፣ መኪና እያሽከረከርኩ ወደ ትምህርት ቤቴ ስንዝ፣ በትምህርት ላይ እያለሁ፣ ዕቃ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄጄ እንደተሰለፍኩ፣ ነዳጅ ስቀዳ ... ስለ እሷ ማሰቤን ሳቋርጥ አልችልም! ስለ እሷ ከራሴ ጋር እያወራሁ፣ እንድወዳት ስላደረጉኝ

ነገሮቿ አስብ ነበር፡፡ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ተራርቀን የምንኖርና በተ ለያዩ ኮሌጆች ውስጥ የምንማር ብንሆንም፣ ይህ ሁኔታ ነበር አጠገቤ ያለች ያህል እንዲሰማኝ ያደረጋት፡፡ ያለማቋረጥ ስለ እሷ እያሰብኩ፣ *ፍቅሯ ውስጥ እኖር ነበር፡፡* እውነተኛ አምልኮም እንዲሁ ነው፤ *በኢየሱስ ፍቅር መያዝ!*

ስምንተኛ ቀን

ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድኩ ነኝ፡፡

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይሰኛልና» መዝ 149÷4፡፡*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡** ከተለመደው ሥራዬ ውስጥ፣ በቀጥታ ለኢየሱስ እንደማደርገው እየቆጠርኩ ለመሥራት የምጀምረው ሥራ ምንድነው?

# እግዚአብሔርን ፈገግ የሚያሰኘው ምንድነው?

*እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ... ::*

*ዘኁል. 6÷25*

*በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ፣ ሥርዓትህንም አስተምረኝ ::*

**መዝ. 118÷134**

የእግዚአብሔር ፈገግታ የሕይወትህ ግብ ነው::

እግዚአብሔርን ማስደሰት የሕይወትህ የመጀመሪያ ዓላማ እንደመሆኑ መጠን፣ ዋነኛው ተግባርህ ያን ማድረጊያውን መንገድ ማግኘት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *«እንዲሁም ጌታን ደስ የሚያሰኘውን ፈልጉ»* ኤፌ. 5÷10፣ ይላል:: ጥሩነቱ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አንድ ግልጥ የሕይወት ምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: በምሳሌው የተጠቀሰው ሰው ስም ኖኅ ይባላል::

በኖኅ ዘመን፣ መላው ዓለም ምግባረ ብልሹ ነበር:: እያንዳንዱ ሰው የሚኖረው ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለራሱ ደስታ ሆነ:: በመሆኑም እግዚአብሔር፣ እርሱን ሊያስደስት የሚፈልግ ሰው በምድር ላይ ስላላገኘ፣ ሰውን በመፍጠሩ አዘነ፣ ተፀፀተ:: ከምድር ሊያጠፋው እስኪያስብ ድረስ በሰው ዘር ላይ ተቆጣ:: ያም ሆኖ ግን፣ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ አንድ ሰው ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *«ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አገኘ»* ዘፍ. 6÷8 ይላል::

እግዚአብሔር እንዲህ አለ:- «ይህ ሰው ደስ ያሰኘኛል፣ ፈገግ እንድልም ያደርገኛል:: ሥራዬን ከዚህ ሰው ቤተ ሰብ ጋር እንደገና እጀምራለሁ»::

ኖኅ እግዚአብሔርን ደስ ስለ አሰኘው፣ እኔና እናንተ ዛሬ በሕይወት አለን:: እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙትን አምስት የአምልኮ እውነቶች ከኖኅ ሕይወት እንማራለን::

**ከሁሉ አስበልጠን ስንወደው እግዚአብሔር ደስ ይለዋል::** ኖኅ በዓለም ላይ እግዚአብሔርን ማንም ባልወደደው ጊዜ እንኳን በዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ ይበልጥ ወደደው:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ ኖኅ በሕይወት ዘመኑ:- *«ሰካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ»* ይላል::

እግዚአብሔር ከምንም ይበልጥ ካንተ የሚፈልገው ይህን ነው:: ፈጣሪ ከእኛ ጋር ግንኙነት ለመመሥረት መፈለጉ እጅግ አስገራሚ እውነት ነው:: እግዚአብሔር የፈጠረህ ሊወድህ ነው፤ አንተም መልሰህ እንድትወደው ይጓጓል:- «*ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአ ብሔርን ማወቅ እወድዳለሁና*» ሆሴዕ 6÷6 ይላል::

እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ፍቅር ከዚህ ጥቅስ ትረዳለህን? እጅግ ጥልቅ በሆነ ፍቅር ይወድሃል፤ አፀፋ ፍቅርንም ከአንተ *ይፈልጋል*:: ታውቀውና አብ ረኸው ጊዜ ታሳልፍ ዘንድ *ይጓጓል*:: ለዚህ ነው፣ እግዚአብሔርን መውደድንና በእርሱም መወደድን መማሩ የሕይወትህ ታላቅ ዓላማ መሆን የሚኖርበት:: ይህን የሚያክል ጠቃሚ ነገር የለም:: ይህን ጉዳይ ኢየሱስ ታላቂቱ ትእዛዝ ይለዋል:- «*ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህም ፣በፍጹም አሳብህም፣ ውደድ:: ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት*» ማቴ. 22÷37-38፣ ብሏል::

**በፍፁም ስንታመንበት እግዚአብሔር ደስ ይለዋል::** ኖኅ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘበት ሁለተኛው ምክንያት፣ ትእዛዙን ለመረዳት አዳጋች በነበረበት ጊዜ እንኳ በእርሱ ማመኑ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ፈርቶ በተሰ ዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት ሠራ፣... በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ*» ዕብ. 11÷7::

> *እግዚአብሔር ከምንም ይልቅ ከአንተ የሚፈልገው ግንኙነትን ነው*

እስቲ ይህን ትዕይንት አስብ:: አንድ ቀን እግዚአብሔር ወደኖህ መጥቶ እንዲህ አለው:- «ሰብዓዊ ፍጡራን አስቆጥተ ውኛል:: በመላው ዓለም ከአንተ በቀር ስለ እኔ የሚያስብ ሰው የለም:: አንተን ስመለከት ፈገግ እላለሁ:: በሕይወትህ ተደስቻለሁ:: ዓለምን በውሃ ላጠፋትና ሥራዬን ከአንተ ቤተ ሰብ ጋር እንደገና ልጀምር ነው:: አንተንና እንስሳትን ከጥፋት ውሃ የሚያድን ግዙፍ መርከብ እንድትሠራ እፈልጋለሁ»::

ኖኅ እንዲጠራጠር ሊያደርጉት የሚችሉ ሦስት ችግሮች ነበሩ:: የመጀመሪያው፣ ዝናብ አይቶ አያውቅም:: ምክንያቱም ከጥፋት ውሃ በፊት እግዚአብሔር ምድርን፣ ከታች ወደ ላይ ውሃን በማውጣት ዘፍ. 2፥5-6 እንደ መስኖ ነበር ውሃ የሚያጠጣት:: ሁለተኛ፣ ኖኅ የኖረው በአቅራቢያው ካለ ውቅያኖስ በመቶ ማይሎች እርቆ ነበር:: መርከብ መሥራቱን ቢያውቅበትም እንኳን፣ ከሠራው በኋላ እንዴት ነበር ውሃ ወደ አለበት የሚወስደው? ሦስተኛ፣ እንስሳቱን ሁሉ የመሰብሰቡና የመመገቡ ችግርም ነበር:: ኖኅ ግን ቅሬታ አላሰማም ወይም አልችልም አላለም:: እግዚአብሔር የነገረውን በፍጹም አመነ፤ ይህ ድርጊቱም እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው::



በምሕ

እግዚአብሔርን በፍጹም ማመን ማለት፣ ለሕይወትህ ከሁሉ የሚሻለውን መልካም ነገር ሁሉ እርሱ ያውቃል በሚል እምነት መኖር ማለት ነው:: እርሱ የሰጠህን ተስፋ እንዲፈጽም፣ በችግርህ ጊዜ እንዲረዳህና፣ አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ የማይቻል ነገር የሚመስለውን ሁሉ እንዲያደርግልህ መጠበቅ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *«እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ ረቱ በሚታመኑም ይደሰታል»* መዝ. 146፥11 ይላል::

ኖኅ መርከቡን ለመሥራት 120 ዓመታት ወስዶበታል:: መቼም ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ቀናት እንዳሳለፈ እገምታለሁ:: ከዓመት ዓመት የዝናብ ምልክት ሳያይና ሰዎች:- «እግዚአብሔር አናገረኝ የሚል እብድ» በማለት በአስከፊ ሁኔታ እየነቀፉት ኖረ:: ልጆቹ እደጃቸው ላይ የሚሠራውን ግዙፍ መርከብ እያዩ ሁልጊዜ ያፍሩና ሰው ምን ይለናል ይሉ እንደ ነበር እገምታለሁ:: ኖኅ ግን እግዚአብሔርን በማመን ፀና::

በየትኛዎቹ የሕይወትህ ጉዳዮች ነው፣ ፍጹም በእግዚአብሔር መታመን የሚገባህ? ማመን የአምልኮ ድርጊት ነው:: ወላጆች ልጆቻቸው ፍቅርና ጥበባቸውን ሲገነዘቡላቸው ደስ እንደሚላቸው፣ እንዲሁ እምነትህ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም»* ዕብ. 11፥6 ::

**እግዚአብሔር ከልባችን ስንታዘዘው ደስ ይለዋል::** ከዓለም አቀፉ የጥፋት ውሃ የእንስሳትን ዝርያ ለመታደግ፣ ለአስፈላጊና ዝርዝር ነገሮች ትልቅ ትኩረት መስጠት ያስፈልግ ነበር:: ሁሉም ነገር *እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት* መከናወን ነበረበት:: እግዚአብሔር:- «ኖኅ፣ የፈለግኸውን ዓይነት እርጌ መርከብ *ሥራ*» አላለም:: የመርከቡን መጠን፣ ቅርፅ፣ የሚሠራበትን ቁሳቁስና በተለያየ ቁጥር ወደ ውስጡ ስለሚገቡት እንስሳት ዝርዝር መመሪያ ሰጥቶ

ታል። ኖኅ በታዘዘ ጊዜ ያደረገውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይገልጠዋል፡-

*«ኖኅም ሁሉን እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ»* ዘፍ. 6፥22፤ *ዕብ. 11፥7*።

ኖኅ *በፍጹም* (እንዲንም ትእዛዝ ሳያዛንፍ)፤ እና *በትክክል* መታዘዙን (*ሥራው* እግዚአብሔር በፈለገው ሁኔታና ጊዜ መከናወኑን)፤ ልብ አድርግ። ይህ ነው ከልብ መታዘዝ ማለት። እግዚአብሔር በኖኅ ደስ መሰኘቱ አይገርምም።

ግዙፍ መርከብ እንድትሠራ እግዚአብሔር ቢያዝህ፤ ጥቂት ጥያቄዎች፤ ተቃውሞዎች ወይም ጥርጣሬ የሚኖርህ አይመስልህምን? ኖኅ ግን አልነበ ረውም። በሙሉ ልቡ ለእግዚአብሔር ታዘዘ። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሁሉ ያለ ጥርጥርና ማመንታት መታዘዝ ማለት ይህ ነው። ሰበብ ፈልገህ *«እጸልይ በታለሁ»* አትልም። በፍጥነት ትፈጽመዋለህ። የዘገየ መታዘዝ፤ እንዳለመታዘዝ የሚቆጠር መሆኑን ወላጅ ሁሉ ያውቀዋል።

እግዚአብሔር ታደርገው ዘንድ ለሚያዝህ ነገር ሁሉ፤ ማብራሪያ የመስጠት ወይም ምክንያቱን የመንገር ግዴታ የለበትም። መረዳት ሊዘገይ ይችላል፤ መታዘዝ ግን አይችልም። ዕድሜ ልክ ከሚደረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ውይይት ይልቅ፤ ፈጣን መታዘዝ ስለ እግዚአብሔር ያስተምርሃል። እንዲያውም አንዳ ንድ ትእዛዞችን መጀመሪያ በመታዘዝ ካልፈጸምካቸው፤ ልትረዳቸው አትች ልም። መታዘዝ የመረዳትን ቁልፍ ይከፍተዋል።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን *በከፊል* ልንታዘዘው እንሞክራለን። ልንፈጽም የምንፈልጋቸውን ትእዛዞች መርጠን ለመውሰድም እንፈልጋለን። የነዚያን ዝርዝር እንወስድና እንታዘዛለን። ተገቢ አይደሉም፤ ያስቸግራሉ፤ ብዙ ወጪ አላቸው ወይም በሰዎች ዘንድ አይወደዱም የምንላቸውን ትእዛዞች ግን ችላ እንላቸዋለን። በቤተክርስቲያን ሥርዓቶች እሳተፋለሁ፤ አሥራት

*እግዚአብሔርን በፍጹም ማመን ማለት፤ ለሕይወትህ ከሁሉ የሚሻለውን መልካም ነገር ሁሉ እርሱ ያውቃል በሚል እምነት መኖር ማለት ነው።*

ግን አልከፍልም። መጽሐፍ ቅዱስ አነባለሁ፤ ለሚበድለኝ ሰው ግን ይቅርታ አላደር ግለትም። ከፊል መታዘዝ እኮ አለመታዘዝ ነው። በሙሉ ልብ መታዘዝ ሲኖር፤ ትእዛዙ በደስታና በፍላጎት ይፈጸማል። መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«በደስታ ለእግዚአብሔር ተገዙ»* ይላል። ዳዊትም የታዛዥነት ስሜቱን እንዲህ በማለት ገልጧል፡- *«እግዚአብሔር ሆይ፤ የሥርዐትህን መንገድ አስተምረኝ፤ እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ»* መዝ. 119፥33።

ያዕቆብ ለክርስቲያኖች ሲናገር እንዲህ ብሏል:- *«እንግዲህ በእምነት ብቻ ሳይሆን፣ በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ»* ያዕ. 2÷24:: በራስህ ሥራ ልትጸድቅ እንደማትችል የእግዚአብሔር ቃል በግልጥ ይናገራል:: በአንተ ጥረት ሳይሆን፣ በጸጋ ነው የምትጸድቀው:: ነገር ግን፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆንህ፣ በመታዘዝ ሰማያዊ አባትህን ልታስደስተው ትችላለህ:: ማንኛውም የመታዘዝ ድርጊት፣ አምልኮም ድረጊትም ነው:: ለምንድነው መታዘዝ እግዚአብሔርን በጣም የሚያስደስተው? ምክንያቱም መታዘዝ በእርግጥ የምትወደው መሆንህን ያረጋግጣል:: ኢየሱስ እንዲህ ብሏል :- *«ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ »*
ዮሐ. 14÷15::

እግዚአብሔር ሳናቋርጥ ስናከብረውና ስናመሰግነው ደስ ይለዋል:: ልባዊ ምስጋናና አድናቆትን ከሌሎች ከመቀበል ይበልጥ የሚያስደስቱ ብዙ ነገሮች የሉም:: እግዚአብሔርም እንዲሁ ምስጋናና ሙገሳን ይወዳል:: ምስጋናችን ንና ለእርሱ ያለንን ፍቅር ስንገልጥለት ደስ ይለዋል::

ኖኅ የሙገሳና የምስጋና ልብ ስለ ነበረው፣ ሕይወቱ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኝ ነበር:: ከጥፋት ውሃ ከተረፈ በኋላ፣ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር፣ መሥዋ ዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን ማመስገን ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ከዚያም ኖኅ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፤ ...መሰዊያው ላይ ...የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ »* ዘፍ. 8÷20::

ኢየሱስ መሥዋዕት አድርጐ እራሱን ከማቅረቡ የተነሣ፣ ኖኅ እንዳደረገው የእንስሳት መሥዋዕት አናቀርብም:: በዚያ ፈንታ *«የምሥጋና መስዋዕት»* ዕብ. 13÷15፤ መዝ. 116÷17፣ እንድናቀርብ ተነግሮናል:: እግዚአብሔርን *«ስለማንነቱ እና ስለአደረገው ነገር እናመሰግነዋለን»*:: ዳዊት እንዲህ ብሏል:- *«የእግዚአብሔርን ስም እወድሰዋለሁ፤ በምሥጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ:: ... ይህ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል»* መዝ. 69÷30-31::

ለእግዚአብሔር ሙገሳና ምስጋና ስናቀርብለት፣ አስደናቂ ነገር ይሆናል፤ ደስ ስናሰኘውም፣ የራሳችን ልብ በደስታ ይሞላል!

እናቴ ለኔ ምግብ ማዘጋጀት ያስደስታታል:: ካገባሁ በኋላ እንኳን ከሚስቴ ጋር ወላጆቼን ልንጎበኝ ስንሄድ፣ ለግብዣ የሚሆን አስደናቂ ምግብ ታዘጋጅልን ነበር:: በሕይወቷ ደስ ከሚያሰኙዋት ታላላቅ ነገሮች አንዱ፣ ልጆቿ ተሰባስበን የሠራችውን ስንመገብ መመልከት ነው:: ምግቡን ደስ ብሎን በተመገብን መጠን፣ እርሷም በጣም ደስ ይላታል::

እኛም ያዘጋጀችውን ምግብ የወደድነው መሆናችንን በመግለጥ፣ ደስ መሰኘ ቷን ለማየት እንወድ ነበር:: ግሩም ምግቧን እያደነቅሁና እናቴን እያመሰገንሁ

እመገባለሁ:: ፍላጎቴ በምግቡ መርካት ብቻ ሳይሆን፣ እናቴንም ደስ ማሰኘት ነው:: ሁላችንም በዚህ ደስተኞች ነበርን::

አምልኮም እንዲሁ ሁለት አቅጣጫ አገልግሎት አለው:: እግዚአብሔር ባደረገልን ነገር ደስ ይለናል፤ ያን ደስታችንን ስንገልጥለት እርሱም ደስ ይለዋል:: ይህም እንደገና ደስታችንን እንዲጨምር ያደርገዋል:: መዝሙረ ዳዊት እንዲህ ይላል:- *«ጻድቃንም ደስ ይበላቸው፣ በእግዚአብሔርም ፊት ሐሤት ያድርጉ፣ ደስታንና ፍስሐን የተሞሉ ይሁኑ»* መዝ. 68÷3::

**እግዚአብሔር በችሎታዎቻችን ስንገለገልባቸው ሲያይ ደስ ይለዋል::** ከጥፋት ውሃ በኋላ እግዚአብሔር ቀጥሎ ያሉትን ቀላል ትእዛዛት ለኖኅ ሰጠው:- *«ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት:: ... ሕያውና ተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ»* ዘፍ. 9÷1-3::

እግዚአብሔር እንዲህ ያለ ይመስላል:- «ሕይወትህን የምትቀጥልበት ጊዜ ነው፤ ሰዎችን ስፈጥር፣ ያደርጓቸው ዘንድ ያቀድኳቸውን ነገሮች አድርግ:: ከሚስትህ ጋር ተኛ፤ ልጆችንም ውለዱ፤ ቤተ ሰብህን አስፋ፤ እህል እያመረትህ ተመገብ፤ ሰው ሁን! የፈጠርኩህ እንዲህ እንድትሆን ነውና »::

እግዚአብሔር በአንተ ደስ የሚለው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን፣ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መካፈልን፣ መጸለይን ወይም እምነትህን መመስከርን የመሳሰሉ «መንፈሳዊ» ተግባራትን በምታከናውንበት ጊዜ ብቻ ይመስልህ ይሆናል:: ስለ ሌላው የሕይወትህ ክፍል ደግሞ ግድ የለውም የሚል አሳብ ይኖርህ ይሆናል:: እግዚአብሔር ግን፣ ስትሠራ፣ ስትጫወት፣ ስታርፍም ሆነ ስትበላ እያንዳንዱን ተግባርህን ማየት ደስ ያሰኘዋል:: እንቅስቃሴዎችህ ሁሉ አያመልጡትም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይነግረናል:- *«የሰው አካሄድ በእግዚአብሔር ይጸናል፣ በመንገዱ ደስ ይለዋል::»* መዝ. 37÷23::

*እግዚአብሔር የሕይወትህን ዝርዝር ነገሮች ማየትን ይወዳል::*

ለአምልኮ ዓላማ እስካደረግኸው ድረስ፣ ከኃጢአት በቀር ማንኛውም ሰብዓዊ ድርጊት ለእግዚአብሔር ደስታ የሚከናወን ሊሆን ይችላል:: ለእግዚአብሔር ክብርን እየሰጠህ የቤት ዕቃ ልታጥብ፣ የተሰበረን ልትጠግን፣ አንድ የምርት ዓይነት ልትሸጥ፣ የኮምፒውተር ፕሮግራም ልትጽፍ፣ እህል ልታመርት ወይም ቤተ ሰብ ልታስተዳድር ትችላለህ::

እርሱ በለገሰህ ተሰጥኦና ችሎታዎች ስትጠቀምባቸው እያየ በልጁ መልካም ድርጊት እንደሚኮራ አባት ደስ ይለዋል:: ለራሱ ደስታ ሲል ሆነ ብሎ የተለ

ያዩ ስጦታዎችን ሰጠን:: አንዳንዶቹን እስፖርተኞች፣ ሌሎቹን ደግሞ የአ እምሮ ሥራ የሚሳካላቸው አድርጎ ፈጥሯቸዋል:: የመካኒክነት፣ የሂሣብ፣ የሙዚቀኛነት ወይም ሌሎች ብዙ ስጦታዎች ይኖሩህ ይሆናል:: እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት ይችላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እርሱ የሁሉንም ልብ የሠራ፣ የሚያደርጉትንም ሁሉ የሚያስተውል ነው»* መዝ. 32÷15::

ስጦታህን በመሸሸግ ወይም ሌላን ሰው ለመምሰል በመሞከር፣ እግዚአብሔርን ልታከብረው ወይም ደስ ልታሰኘው አትችልም:: ደስ ልታሰኘው የምትችለው፣ እራስህን ሆነህ በመገኘት ብቻ ነው:: የአንተነትህን አንድ ክፍል አልቀበልም ባልክ ጊዜ እግዚአብሔር አንተን የፈጠረበትን ጥበብና ልዕልና አልቀበልም ማለትህ ነው:: እግዚአብሔር እንዲህ ይላል :- *«ከሸክላ ሸክላዎች መካከል ከሠሪው ጋር ክርክር ለሚገጥም ወዮለት! ጭቃ፣ ሸክላ ሠሪውን <ምን እየሠራህ ነው?> ይለዋልን?»* ኢሳ. 45÷9::

ዘጠነኛ ቀን

እግዚአብሔርን

ፈገግ

ሚያደርገው

ምንድነው?

የእሳት ሠረገሎች በሚለው ፊልም ውስጥ ኤሪክ ሊደል የተባለ የኦሎምፒክ ሯጭ እንዲህ ብሏል :- «እግዚአብሔር ለአንድ ዓላማ እንደ ፈጠረኝ አምናለሁ:: ፈጣን ሯጭ አድርጎም ሠርቶኛል:: እናም በምሮጥበት ጊዜ የእግዚአብሔር ደስታ ይሰማኛል»:: በኋላ ደግሞ እንዲህ አለ:- «እሩጫን ማቆም ማለት እርሱን ማዋረድ ማለት ነው»:: ያለ ቦታቸው የዋሉ እንጂ፣ *መንፈሳዊ ያልሆኑ* ስጦታዎች የሉም:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ክብር በስጦታህ መጠቀም ጀምር::

እርሱ በፈጠረው ነገር ሐሤት ስታደርግ በመመልከትም እግዚአብሔር *ደስ* ይለዋል:: ውበትን አይተህ ትረካ ዘንድ ዓይን፣ ለድምጽ ጆሮ፣ አበባ አሽትተህ እንድትረካ አፍንጫ፣ ጣዕምን ታጣጥምበት ዘንድ ምላስ፣ ትዳስስ ዘንድ በቆዳህ ሥር የስሜት ሕዋሳትን ሰጠህ:: እግዚአብሔርን እስካመሰገንክበት ድረስ፣ ደስ የሚያሰኝህ እያንዳንዱ ድርጊት አምልኮ ይሆናል:: እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «... *ደስም እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰጠን* ...» 1ጢሞ. 6÷17::

ተኝተህ ሲያይህ እንኳን እግዚአብሔር ደስ ይለዋል! ልጆቼ ህፃናት በነበሩ ጊዜ ተኝተው ሳያቸው ይሰማኝ የነበረውን ጥልቅ እርካታ አስታውሳለሁ:: አንዳንዴ፣ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲያስቸግሩና አልታዘዝም ሲሉ ይሆናል የዋሉት:: ሲተኙ ግን እርካታ፣ ሰጋት አልባነትና ሰላም ይታይባቸዋል:: ያ ሁኔታቸው

ደግሞ ለነሱ ያለኝን የፍቅር ጥልቀት ያስታውሰኛል።

በእነርሱ ደስ ይለኝ ዘንድ ልጆቼ ለእኔ ምንም ማድረግ አልነበረባቸውም። በጣም ስለምወዳቸው፣ እንዲሁ ሲተነፍሱ ሳያቸው ብቻ ደስ ይለኛል። ትንንሽ ደረቶቻቸው ከፍና ዝቅ ሲሉ እያየሁ ፈገግ እል ነበር። አንዳንዴም የደስታ እንባ በዓይኖቼ ግጥም ይላል። እግዚአብሔር ስትተኛ በፍቅር ወደ አንተ ይመለከትና የእርሱ እቅድ ስለሆንክ በዓለም ላይ ያለኸው አንድ አንተ ብቻ የሆንክ ያህል ይወድሃል።

ወላጆች ለራሳቸው ደስታ ሲሉ ልጆቻቸው ፍጹማን ወይም በሳሎች እንዲሆኑ አይጠብቁም። በእያንዳንዱ የዕድገት ደረጃቸው ደስ ይሏቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር ይወድህ ዘንድ ወደ መብሰል እስክትደርስ ድረስ አይጠብቅም። በእያንዳንዱ የመንፈሳዊ ዕድገት ደረጃህ ይወድሃል፣ ደስ ይሰኝብሃልም።

በእድገትህ ወቅት ባንተ ደስተኞች ያልነበሩ መምህራን ወይም ወላጆች ገጥመውህ ይሆናል። እባክህ እግዚአብሔርም ስለ አንተ እንደእነሱ ይሰማዋል ብለህ አታስብ። ፍጹም ወይም ኃጢአት የማትሠራ ሰው ለመሆን እንደማትችል ያውቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እርሱ አፈጣጠራችንን ያውቃልና፤ ትቢያ መሆናችንንም ያስባል»* መዝ. 103÷14።

እግዚአብሔር የሚያየው የልብህን ዝንባሌ ነው። ትልቁ መሻትህ እሱን ማስደሰት ነውን? የጳውሎስ የሕይወት ግብ ይህ ነበር። *«ስለዚህ በሥጋ ብንኖርም ወይም ከሥጋ ብንለይም ዓላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት ነው።»* 2ቆሮ. 5÷9። በዘላለም ግንዛቤ ስትኖር፣ ትኩረትህ፣ «ከሕይወት የማገኘው ደስታ ምን ያህል ነው?» ከሚለው ጥያቄህ፣ «እግዚአብሔር በሕይወቴ ምን ያህል ይደሰታል?» ወደሚለው ይለወጣል።

እግዚአብሔር በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደኖኅ ያሉና ለእርሱ ደስታ ለመኖር የሚፈቅዱ ሰዎችን ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«የሚያስተውል፣ እግዚአብሔርን የሚፈልግ መኖሩን ለማየት፣ እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ።»* መዝ. 14÷2።

የሕይወትህ ግብ እግዚአብሔርን ማስደሰት እንዲሆን ታደርጋለህን? ሙሉ በሙሉ እራሱን ለዚህ ግብ ወይም ዓላማ ለሰጠ ሰው እግዚአብሔር የማያደርግለት ነገር የለም።

ዘጠንኛ ቀን

ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላስታውሰው የሚገባ ጉዳይ፡-** እግዚአብሔር ስተማመንበት ደስ ይለዋል፡፡

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል»* መዝ. 147÷11፡፡

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር ከሁሉ የሚሻለውንና መልካም የሆነውን ስለሚያውቅ፣ በርሱ ይበልጥ ልታመን የሚገባኝ በየትኛው የሕይወቴ ጉዳይ ነው?

# 10

# የአምልኮ ልብ

*ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ ... የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ ::*

ሮሜ 6÷13

የአምልኮ ልብ፤ (ዋና ነገር) መማረክ ነው ::

*መማረክ* የሚለው ቃል፣ መገዛት የሚለውን ያህል የማይፈለግና የተጠላ ነው:: *መሸነፍን ያመለክታል*:: መሸነፍን ደግሞ ማንም አይፈልገውም:: *መማረክ*፣ በውጊያ ድል ሆኖ አሜን በማለት የመቀበልን፣ በስፖርት ውድድር ወቅት በበቃኝ የመሸነፍን ወይም ለብርቱ ተቀናቃኝ እጅ የመስጠትን አስከፊ ምስል ያሳያል:: ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎት ላይ የሚውለው፣ በአሉታዊ አገባቡ ነው:: የተያዙ ወንጀለኞች ለባለሥልጣኖች እጃቸውን ይሰጣሉ::

ፉክክር የሞላበት የዘመናችን ባህል የሚያስተምረን፣ ተስፋ አለመቁረጥንና አለመሸነፍን ነው:: በመሆኑም እጅ ስለመስጠት ሲነገር ብዙም አንሰማም:: የሕይወት ዋና ነገር ማሸነፍ ከሆነ፣ እጅ መስጠት የሚለው ቃል *አይታሰብም*:: እጅ ስለ መስጠት፣ ስለ መታዘዝ፣ ስለ መሸነፍ፣ ስለ መማረክ ከመናገር ይልቅ፣ ድል ስለ ማድረግ ስለ ማሸነፍ፣ ስለ መማረክ፣ መናገርን እንመርጣለን:: ለእግዚአብሔር መማረክ የአምልኮ ዋና ነገር ሲሆን፣ ለአስደናቂው የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት የሚሰጥ ተገቢ ምላሽም ነው:: እራሳችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛው ከፍርሃት ወይም ከግዴታ ሳይሆን፣ ከፍቅር የተነሳ ነው:- *«እርሱ አስቀድሞ ወደናልና»* 1ዮሐ. 4÷9-10፣ 19::

ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን አስገራሚና አስደናቂ

ፀጋ በአሥራ አንድ የሮሜ መጽሐፍ ምዕራፎች ከገለጠልን በኋላ፣ እራሳችንን በአምልኮ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እናስገዛ ዘንድ እንዲህ በማለት ያሳስበናል:- *«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ»* ሮሜ 12÷1::

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እውነተኛ አምልኮ የሚከናወነው፣ እራስህን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስታስገዛ ነው:: ጥቅሱ ውስጥ *ታቀርቡ ዘንድ* የሚለውን ቃል ልብ አድርግ::

አምልኮ እራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ነው:: ይህ ግላዊ የመገዛት ተግባር፣ መቀደስ፣ ኢየሱስን ጌታህ ማድረግ፣ መስቀልህን መሸከም፣ ለሥጋ መሞት እና እራስን ለመንፈስ ቅዱስ ማስገዛት የመሳሰሉ ብዙ ፍቺዎች አሉት:: ቁም ነገሩ ለድርጊቱ የምትሰጠው ፍች ሳይሆን፣ ማድረግህ ነው:: እግዚአብሔር ሕይወትህን ይፈልገዋል፤ ሁሉንም:: ዘጠና አምስት በመቶው በቂ አይደለም::

*አምልኮ እራስህን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ነው::*

ሁለመናችንን ለእግዚአብሔር እንዳናስገዛ የሚያግዱን ሦስት መሰናክሎች አሉ:: እነርሱም፣ ፍርሃት፣ ትዕቢትና ግራ መጋባት ናቸው:: እግዚአብሔር የቱን ያህል እንደሚወደን አንገነዘብም፣ ሕይወታችንን እራሳችን ለመግዛት እንፈልጋለን፣ ራስን ስለማስገዛት ያለን መረዳት የተሳሳተ ነው::

**እግዚአብሔርን ላምነው እችላለሁን?** *ማመን*፣ የመገዛት አንዱ መሠረታዊ ክፍል ነው:: እግዚአብሔርን ካላመንከው ራስህን አታስገዛለትም:: በተሻለ ሁኔታ እስክታውቀው ድረስ ደግሞ ልታምነው አትችልም:: ፍርሃት ራሳችንን እንዳናስገዛ ያግደናል፤ *ፍቅር ግን ፍርሃትን ሁሉ ያስወግዳል*:: እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወድህ ይበልጥ በተረዳህ ጊዜ፣ ራስህን ለሱ የማስገዛቱ ጉዳይ ቀላል ይሆንልሃል::

እግዚአብሔር እንደሚወድህ በምን ታውቃለህ? እርሱ እራሱ ብዙ ማረጋገጫዎችን ይሰጥሃል:: እግዚአብሔር እወድሃለሁ ይላል፣ መዝ. 144÷9 ፣ ዓይኑን ከአንተ ላይ አያነሣም መዝ. 138÷3፣ ስለማንኛውም የሕይወትህ ዝርዝር ጉዳይ ይጨነቃል ማቴ. 10÷30፣ በማንኛውም ደስታ የመርካት ፍስህን ሰጠህ 1ጢሞ. 6÷17፣ ለሕይወትህ መልካም እቅዶች አሉት፣ ኤር. 29÷11 ፣ ኃጢአትህን ይቅር ይላል መዝ. 85÷5 ፣ በፍቅርም ይታገስሃል፣ መዝ. 144÷8:: ልታስበው ከሚቻልህ በላይ እግዚአብሔር ይወድሃል::

የዚህ ትልቁ መገለጫ የእግዚአብሔር ልጅ ለአንተ መስዋቱ ነው:- *«ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል»* ሮሜ 5+8:: በእግዚአብሔር ምን ያህል እንደተወደድክ ለማወቅ ከፈለግህ፣ ክርስቶስ እጆቹን በመስቀል ላይ ግራና ቀኝ ዘርግቶ፣ «ይህን ያህል እወድሃለሁ! ያለ አንተ ከምኖር መሞት ይሻለኛል» ሲልህ ተመልከተው::

እግዚአብሔር ጨካኝ ባሪያ ፈንጋይ ወይም እንገዛለት ዘንድ በኃይል የሚያስገድደን ገዢ አይደለም:: እራሳችንን በፈቃደኝነትና በነፃ እንሰጠው ዘንድ ያባብለናል እንጂ፣ ፍቃዳችንን በኃይል ሊሽር አይሞክርም:: አፍቃሪና ነፃ አውጪ ነው:: እራስን ለርሱ መስጠት ነፃነት እንጂ ባርነት አይደለም:: እራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለኢየሱስ ስንሰጥ፣ እሱ አዳኝ እንጂ ጨካኝ ገዥ፣ ወንድም እንጂ አለቃ፣ ጓደኛ እንጂ አምባገነን አለመሆኑን እንገነዘባለን::

**ውሱንነታችንን መቀበል:-** ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ያለመስጠታችን ሁለተኛው መሰናክል ኩራታችን ነው:: ፍጡራን ብቻ እና ሁሉን የማድረግ ሥልጣን የሌለን መሆናችንን ለመቀበል አንፈልግም:: *«እንደ እግዚአብሔር እንደ ምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው ... » ዘፍ. 3+5*፤ የሚለው ጥንታዊ ፈተና ነው:: ያ ሁሉን ነገር የመቆጣጠር ፍላጎት ነው በሕይወታችን ብዙ መጨነቅን የሚፈጥረው:: ሕይወት ትግል ነው:: ትግላችን እንደያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ግን ብዙ ሰዎች አይገነዘቡም! እግዚአብሔር ለመሆን እንፈልጋለን፣ ነገር ግን ትግሉን የምናሸንፍበት ምንም መንገድ የለም::

ኤ. ደብልዩ ቶዘር የተባሉ ሰው እንዲህ ብለዋል:- «ብዙ ሰዎች በመቸገር፣ በመፈለግ፣ ጥቂት ዕድገት ብቻ በማሳየት ላይ ያሉበት ምክንያት፣ ከእነርሱነታቸው ጫፍ ስላልደረሱ ነው:: አሁንም ትዕዛዛዝ ለመስጠት በመሞከር ላይ ነን፤ እግዚአብሔር በሕይወታችን በሚያከናውነው ሥራ ውስጥም ጣልቃ እንገባለን::»

እግዚአብሔር አይደለንም፤ መቼም አንሆንም:: ሰዎች ነን:: እግዚአብሔርን ለመሆን በሞከርን ጊዜ ይበልጥ ሰይጣንን ወደ መምሰል እንሄዳለን:: የሰይጣን ፍላጎትም ይኸው ነበር::

አስረኛ ቀን
የአምልኮ
ልብ

ሰብዓዊነታችንን በአእምሮ እንጂ በስሜታችን አንቀበለውም:: ከራሳችን ውሱንነት ጋር ስንፋጠጥ ደግሞ፣ ብስጭት፣ ቁጣና ቅሬታ እናሳያለን:: ካለን ቁመት ረዘም ወይም አጠር ለማለት፣ ይበልጥ ብልህ፣ ጠንካራ፣ ተሰጥዖ ያለን፣ ቆንጆ ወይም ባለጠጋ ለመሆን እንፈልጋለን:: ሁሉ እንዲኖረንና ሁሉን ለማድረግ

እንፈልግና ሳይሳካልን ሲቀር እንበሳጫለን:: እግዚአብሔር እኛ የሌሉንን ባሕርያት ለሌሎች እንደሰጣቸው ስንመለከት ደግሞ ቅናት፣ ምቀኝነትና ሀዘን ይሰማናል::

*ራስን ማስገዛት ምንድነው?* ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ማለት፣ እንዲሁ በይሁንታ የሚደረግ፣ በዕድል የሚገኝ ወይም የስንፍና ሽፋን አይደለም:: ካለው ሁኔታ ጋር የመስማማት ጉዳይም አይደለም:: ከነዚህ ነገሮች በተቃራኒ፣ ሕይወትህን መስዋዕት ማድረግ ወይም መለወጥ ያለበትን ነገር ለመለወጥና መከራን መቀበል ሊሆን ይችላል:: እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ እራሳቸውን ያስገዙለትን ሰዎች የእርሱን ውጊያ ይዋጉለት ዘንድ ይጠራቸዋል:: ራስን



ማስገዛት ፈሪዎችና ሁሉ እንደፈለገ የሚያደርጋቸው ሰዎች እንደሚሆኑት ማድረግ አይደለም:: መመርመርና ማመዛዘንን መተው ማለትም አይደለም:: እግዚአብሔር የሰጠህን አእምሮ አያባክንም! ሰው ሠራሽ ሮቦቶችን የመሰሉ አእምሮ የለሾች እንዲያገለግሉትም አይፈልግም:: ራስን ማስገዛት ማለት፣ አንተነትህን መጫን ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር የሚፈልገው፣ በተለየ ማንነትህ ለመጠቀም ነው:: ራስን ማስገዛት፣ አንተነትህን ከማጥፋት ይልቅ፣ ያሳድገዋል:: ሲ.ኤስ. ሊዊስ የተባሉ ጸሐፊ እንዲህ ብለዋል:- «እግዚአብሔር ይበልጥ የራሱ እንዲያደርገን ስንፈቅድለት፣ ይበልጥ እውነተኞቹ እኛ እንሆናለን! የፈጠረን እርሱ ነውና:: እኔና አንተ ልንሆን በታቀድነው መሠረት እግዚአብሔር የተለያዩ ሰዎች አድርጎ ፈጥሮናል ... ወደ ክርስቶስ ስመለስና እኔነቴን በእርሱነቱ ስተካ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛውን እኔነቴን ያገኘሁት»

መገዛት በጥሩ ሁኔታ የሚገለጠው፣ በመታዘዝ ውስጥ ነው:: እንድታደርግለት ለሚጠይቅህ ነገር ሁሉ *«እሺ ጌታ ሆይ »* በል:: *«አይሆንም ጌታ ሆይ »* ማለት እርስ በርስ የሚጋጭ ንግግር ነው:: ሲያዝህ እምቢ እያልክ፣ ኢየሱስን ጌታዬ ልትለው አትችልም:: ጴጥሮስ፣ ሌሊቱን በሙሉ አሣ ለማጥመድ ያደረገው ሙከራ ስኬታማ ሳይሆንለት ከቀረ በኋላ፣ እንደገና እንዲሞክር ኢየሱስ ባዘዘው ጊዜ በመታዘዝ፣ የመገዛት ሞዴል ሆኗል:- *«መምህር ሆይ፣ ሌሊቱን ሙሉ ስንደክም አድረን ምንም አልያዝንም፤ አንተ ካልህ ግን መረቦቹን እጥላለሁ »* ሉቃስ 5÷5:: የተገዙ ሰዎች፣ ነገሩ ባይገባቸውም እንኳን የእግዚአብሔርን ቃል ይታዘዛሉ::

ሙሉ በሙሉ የተገዛ ሕይወት ሌላ ገፅታው፣ እምነት ነው:: አብርሃም የት እንደሚያደርሰው ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ምሪት ተከትሏል:: ሀና መቼ እንደሚሆን ሳታውቅ የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠበቀች:: ማርያም እንዴት እንደ

ሚሆን ሳታወቅ ተዓምር ጠበቀች:: ዮሴፍ የደረሰበት ነገሮች ሁሉ ለምን እንደሆኑ ሳያውቅ፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ አመነ:: እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አስገዙ::

እራስህን ለእግዚአብሔር ማስገዛትህን የምታወቀው ሌሎችን ለመደለል ወይም ለማታለል፣ ጉዳይህን በነሱ ላይ ለመጫንና ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ከመሞከር ይልቅ፣ ለነገሮች መከናወን በእግዚአብሔር ላይ ስትታመን ነው:: አንተ ተወው እግዚአብሔር ይሥራው:: አንተ መቆጣጠርህን በመተው እግዚአብሔር እንዲሠራ ፍቀድለት:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል፤ በትዕግሥትም ጠብቀው*» መዝ. 37÷7:: በብርቱ ከመሞከር፣ ከቀድሞው ይበልጥ እመን:: በሌሎች ስትነቀፍ፣ መከፋትህንና ራስህን ለመከላከል መሯሯጥህን ስትተው፣ ለእግዚአብሔር መገዛትህን ታውቃለህ:: ለጌታ የተገዙ ልቦች ይበልጥ የሚገለጡት በግንኙነቶች ነው:: እራስህን ስታስገዛ ሌሎችን አትጋፋም፤ መብቶችህን አትጠይቅም፤ እራስህን ብቻ የምታገለግልም አትሆንም::

ብዙ ሰዎች እራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዳያስገዙ ከምንም በላይ እንቅፋት የሚሆንባቸው፣ ገንዘባቸው ነው:: «ለእግዚአብሔር ለመኖር እፈልጋለሁ ግን በምቾት ለመኖር የሚያስችለኝን በቂ ሀብት አከማችቼ ጡረታ ለመውጣት እፈልጋለሁ» ብለው ያስባሉ:: ይህ ዓይነቱ ምኞት ዋና የሕይወት ትኩረታችንን በመሳብ ረገድ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚፎካከር፣ የተገዛ ሕይወት ሊኖረው የሚገባ ግብ ወይም ፍፃሜ ሊሆን አይገባም:: ኢየሱስ እንዲህ ይላል:- «*እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም*» ማቴ. 6÷24:: «*ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያው ይሆናል*» ማቴ. 6÷21::

እራስን የማስገዛት ትልቁ ምሳሌ ኢየሱስ ነው:: በመስቀሉ ዋዜማ በነበረ ምሽት እራሱን ለእግዚአብሔር እቅድ አስገዛ:: እንዲህ በማለትም ፀለየ:- «*አባ አባት ሆይ፣ ሁሉ ይቻልሃልና ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን*» ማር. 14÷36::

*መገዛት በጥሩ ሁኔታ የሚገለጠው፣ ታዛዥነት ውስጥ ነው::*

ኢየሱስ:- «ይህን እቅድ ለማስወገድ *ከቻልክ* አባክህን አስወግደው» ብሎ አይደለም የጸለየው:: እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የሌለ መሆኑን አረጋግጧል:: በመሆኑም እንዲህ አለ:- «ይህን ስቃይ ማስወገዱ በታላቁ ፍላጐትህ ውስጥ ካለ፣አድርገው:: ዓላማህን የሚያገለግል ከሆነ ግን፣ እኔም የምፈልገው እሱን ነው»::

እውነተኛ መገዛት እንዲህ ይላል:- «አባት ሆይ፣ ይህ ችግር፣ ስቃይ፣

በሽታ፣ ወይም ሁኔታ፣ በእኔ ወይም በሌላ ሰው ዓማካይነት ዓላማህንና ክብር ህን የሚያገለግል ከሆነ፣ እባክህን *አትውሰደው*»:: እንዲህ ያለው መንፈሳዊ እድገት በቀላሉ አይመጣም:: ኢየሱስን በተመለከተ፣ የደም ጠብታ እስኪያል በው ነው የእግዚአብሔርን እቅድ ተሸክሞ ያጣጣረው:: መገዛት ከባድ ተግባር ነው:: እኛን በተመለከተም ራስ ወዳድ ከሆነው ተፈጥሯችን ጋር የሚደረግ ጠንካራ ውጊያ ነው::

**የመገዛት በረከት::** ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር በምታስገዛበት ጊዜ ስለምታገኘው በረከት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይናገራል:: *መጀመሪያ* ሰላም ይኖርሃል:: *«ለእግዚአብሔር ተገዛ፤ ከእርሱም ጋር ሰላም ይኑርህ፤ በረከትም ታገኛለህ»* ኢዮብ 22÷21:: ቀጥሎ ደግሞ ነፃነትን ትለማመዳለህ:- *«ብልቶቻችሁን የክፋት መሣሪያ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ ... እራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅ ርቡ»* ሮሜ 6÷13-14:: *ሦስተኛ*፣ የእግዚአብሔርን ኃይል በሕይወትህ ትለማ መዳለህ:: የማይበገሩ ፈተናዎችና ከባድ ችግሮች ለኢየሱስ ሲሰጡ፣ በእርሱ ድል ይሆናሉ::

ኢያሱ በሕይወቱ ትልቅ ወደሆነው ጦርነት በተቃረበ ጊዜ 5÷13-15፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኘ፤ በአምልኮ እፊቱ ወደቀና እቅዶቹን ለእርሱ ምሪት አስገዛ:: ያ ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት፣ ኢያሪኮ ላይ ወደተገኘው አስገራሚ ድል መራው:: ይህ ነው እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስል ነገር፣ በመገዛት (በመማረክ) ድል ይገኛል:: መገዛት ያበረታሃል እንጂ አያደክምህም:: ለእግዚአብሔር ከተገዛህ፣ ምንንም መፍራት ወይም ለሌላ ለምንም መገዛት አስፈልግህም:: ሳልቬሽን አርሚ የተባለው ድርጅት መሥራች፣ ዊልያም ቡዝ እንዲህ አለ:- «የአንድ ሰው ኃይል ወይም ሥልጣን ታላቅነት መለኪያ፣ ራሱን ለእግዚአብሔር ያስገዛበት ልክ ነው::»

እግዚአብሔር የሚገለገለው እራሳቸውን ባስገዙለት ሰዎች ነው:: ማርያም የኢየሱስ እናት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣት፣ ተሰጥኦ፣ ሀብት ወይም ውበት ስለነበራት ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ስለተገዛች ነው:: የሚሆን የማይመስለውን የእግዚአብሔር ዕቅድ መልአኩ ከገለጠላት በኋላ፣ በእርጋታ እንዲህ አለች:- *«እነሆ፤ እኔ የጌታ ባሪያ፤ እንደቃልህ ይሁንልኝ»* ሉቃስ 1÷38:: እንደተገዛ ሕይወት በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ብርቱ መገልገያ የሚሆን ነገር የለም:: *«እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ»* ያዕ. 4÷7::

**ተመራጩ የሕይወት መንገድ::** ማንኛውም ሰው በመጨረሻ ለአንድ ነገር ወይም ሰው ይገዛል:: ለእግዚአብሔር የማትገዛ ከሆንህ፣ ለሌሎች ሰዎች አሳቦችና ምኞቶች፣ ለገንዘብ፣ ለብስጭት፣ ለፍርሃት፣ ለገዛ ኩራትህ ወይም

ትዕቢትህ፣ ለፍትወት ምኞት ወይም ለእኔነትህ ትገዛለህ:: የተፈጠርከው፣ እግዚአብሔርን እንድታመልከው ነው:: ካላመለከው፣ ሕይወትህን የምታስገዛ ላቸው ሌሎች ጣኦታትን ትፈጥራለህ:: ራስህን ለማን ማስገዛት እንደሚኖርብህ የመምረጥ ነፃነት አለህ፤ ምርጫህ ከሚያስከትለው የመጨረሻ ውጤት ግን ነፃ አይደለህም:: ኢ. ስታንሌይ ጆንስ የተባሉ ፀሐፊ:- *«እራስህን ለክርስ ቶስ ካላስገዛህ፣ በምስቅልቅል ነገር ትገዛለህ»* ብለዋል::

ለእግዚአብሔር መገዛት፣ *ከሁሉ የተሻለ* ሳይሆን፣ ብቸኛው የሕይወት መንገድ ነው:: ሌላ መንገድ የለም:: ሌሎቹ መንገዶች ወደ ተስፋ መቁረጥ፣ ብስጭትና ራስን ማጥፋት ነው የሚያደርሱት:: መጽሐፍ ቅዱስ መገዛትን፣ *«እንደባለ ለአምሮ የምታቀርቡት አምልኳችሁ ነው»* *ሮሜ 12፥1* ይለዋል:: ሕይወትህን ለእግዚአብሔር ማስገዛት፣ ስሜታዊና የሞኝነት ውሳኔ ሳይሆን፣ የአዋቂነት ድር ጊት፣ እንዲሁም በሕይወትህ ሙሉ ከም ታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ይበልጥ፣ *ለሰተ ዋይነትና ኃላፊነት* የተሞላበት ነው:: ለዚህ ነው ጳውሎስ:- *«ዓላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት ነው» 2ቆሮ. 5፥9* ያለው:: ከምንጊዜውም ይልቅ ብልህ የሆንክበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ጥሪ አቤት ያልክበት ነው::

*ለእግዚአብሔር መገዛት ከሁሉ የተሻለ ሳይሆን፣ ብቸኛው የሕይወት መንገድ ነው:: ሌላ መንገድ የለም*

አንዳንዴ ድርጊቱ ዓመታት ሊወስድ ይችላል:: ቢፈጅም፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን በረከት የሚያግዱት፣ ሌሎች ሰዎች ሳይሆኑ፣ እራስህ ማለት የግል ፈቃድህ፤ ግትር ኩራትህና ግላዊ ፍላጎትህ መሆናቸውን ትረዳለህ:: በራስህ ዕቅድ ላይ እያተኮርክ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ልትፈፅም አትችልም::

እግዚአብሔር ጥልቅ *ሥራውን* በአንተ የሚፈፅም ከሆነ፣ እንዲህ ነው የሚጀምረው:: ስለዚህ ሁሉንም ለእግዚአብሔር ስጠው፤ ያለፈ ፀፀትህን፣ የአሁን ችግሮችህን፣ የወደፊት ምኞቶችህን፣ ፍርሃቶችህን፣ ህልሞችህን፣ ድካሞችህን፣ ልማዶችህን፣ ጉዳቶችህንና የሚያውኩህን ነገሮች ሁሉ ለእርሱ ስጠው:: የሕይወትህን አቅጣጫ መሪ ለኢየሱስ ልቀቅለት:: አትፍራ፤ በርሱ ቁጥጥር ሥር ያለ ነገር ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን አይችልም:: ኢየሱስ ጌታህ ከሆነ፣ ማንኛውንም ነገር ትችለዋለህ:: እንደ ጳውሎስም እንዲህ ትላለህ:- *«ኃይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ»* ፊልጵ. 4፥13::

የጳውሎስ መገዛት (*መማረክ*) የተከናወነው፣ በደማስቆ *መንገድ* ላይ በመንገዝ

ላይ ሳለ፣ ኃይለኛ ብርሃን እንፀባርቆበት ከወደቀ በኋላ ነው። ሌሎቻችንን በተ መለከተ እግዚአብሔር የሚገናኘን ቀለል ባለ መንገድ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ፣ መገዛት የአንድ ጊዜ ድርጊት አይደለም። ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡- *«እኔ በየቀኑ እሞታለሁ»* 1ቆሮ. 15÷31። የመስጠት ወይም የመገዛት ስንደ ወቅት አለ፤ የመገዛት ልምምድ ደግሞ አለ፤ ድርጊቱ የማያቋርጥና የዕድሜ ልክ ነው። የሕያው መስዋዕት ችግሩ፣ ከመሰዊያው ላይ ተንሸራትቶ ለመውረድ መቻሉ ነው። ስለዚህ፣ ሕይወትህን በቀን አምሳ ጊዜ መስጠት ወይም ማስገዛት ይኖርብህ ይሆናል። ዕለታዊ ልምድ ልታደርገው ይገባል። ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡- *«በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ»* ሉቃስ 9÷23።

ላስጠንቅቅህ፤ ሙሉ በሙሉ በተሰጠ ወይም በተገዛ ሕይወት ለመኖር ስትወስን፣ ውሳኔህ ይፈተናል። አንዳንዴ የማይመች፣ ሰው የማይወደው፣ ዋጋ የሚያስከፍልና የማይቻል ይመስል ይሆናል። ለማድረግ ከምትፈልገው ነገር ተቃራኒ የሆነን ነገር ማድረግ ሊሆንም ይችላል።

ከሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታላላቅ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ፣ ቢል ብራይት የተባሉና የካምፓስ ክሩሴይድ ፎር ክራይስት ድርጅት መሥራች ናቸው። በዓለም ዙሪያ ባሉ የድርጅቱ አገልጋዮች፣ በሚሠራጩ «አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች» በሚለው ትራክትና፣ የኢየሱስ ፊልም (ብዛታቸው ከአራት ቢሊዮን በላይ የሆነ ሰዎች ተመልክተውታል)፣ ዓማካይነት ከ150 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መጥተዋል፤ ዘላለም በመንግሥተ ሰማያት ይሆናሉ።

አንድ ጊዜ ቢልን እንዲህ በማለት ጠየቅኳቸው፡- *«ለምንድነው እግዚአብሔር የተጠቀመብዎትና ሕይወትዎን ይህን ያህል የባረከው?»*፤ እሳቸውም *«ወጣት ሳለሁ ከእግዚአብሔር ጋር ተዋዋልኩ። ውሉን ጽፌ ግርጌው ላይ ስሜን ፈረምኩበት። ውሉም እንዲህ ይላል <ከዛሬ ጀምሮ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነኝ >»* ብለው መለሱልኝ።

እንዲህ ያለ ውል ከእግዚአብሔር ጋር ተፈራርመህ ታውቃለህ? ወይስ በሕይወትህ የፈለገውን የማድረግ መብቱን በተመለከተ አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር በመከራከርና በመታገል ላይ ነህ? ለእግዚአብሔር ፀጋ፣ ፍቅርና ጥበብ የመገዛትህ ጊዜ አሁን ነው።

## አሥረኛ ቀን
## ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** የአምልኮ ዋናው ነገር መገዛት ነው::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«ብልቶቻችሁንም .. . ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገሩ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ»* ሮሜ 6÷13::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** ለእግዚአብሔር ያላስገዛሁት የሕይወቴ ክፍል የቱ ነው?

# 11

# የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ መሆን

*የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም !*

*ሮሜ 5፥10*

እግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅህ ሊሆን ይፈልጋል።

ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት ብዙ ገጽታዎች አሉት። እርሱ ፈጣሪህ፣ ሠሪህ፣ ጌታህ፣ ገዢህ፣ ፈራጅህ፣ ነፃ አውጪህ፣ አባትህ፣ አዳኝህና ከዚህም በላይ ነው፣ መዝ. 94፥6፤ 135፥3፤ ዮሐ. 13፥13፤ ይሁዳ 1፥4፤ 1ዮሐ. 3፥1፤ ኢሳ. 33፥22፤ 47፥4፤ መዝ. 89፥26። አስገራሚው እውነት ግን ኃያሉ እግዚአብሔር ወዳጅህ ለመሆን መጓጓቱ ነው።

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያለውን ትክክለኛ ግንኙነት ኤደን ገነት ውስጥ ከነበረው ሁኔታ እንመለከታለን። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ወዳጅነት ነበራቸው። መንፈሳዊ ወግ፣ ሥርዓቶች ወይም ሃይማኖት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔርና እርሱ በፈጠራቸው ሰዎች መካከል በፍቅር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ብቻ ነበር ያለው። አዳምና ሔዋን የበደለኝነት ስሜትና ፍርሃት ሳያግዳቸው በእግዚአብሔር ደስተኞች ሲሆኑ፣ እርሱም በእነርሱ ደስ ይለው ነበር።

ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት እንዲኖረን ሆነን ነበር የተፈጠርነው። ነገር ግን፣ በኃጢአት ምክንያት ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ተቋ

ረጠ:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ከእግዚአብሔር ጋር እንደዚህ ያለ ወዳጅነት የነበራቸው ሰዎች ጥቂት ነበሩ:: ሙሴና አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጆች ተብለው ነበር:: ዳዊት፣ በእግዚአብሔር «እንደልቤ የሆነ ሰው » ተብሏል:: ኢዮብ፣ ሄኖክና ኖህ የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጆች ነበሩ ዘፀ. 33+11፣17፤ 2ቆሮ. 20+7፤ ኢሳ. 41+8፤ ያዕ. 2+23፤ ሐዋ. 13+22፤ ዘፍ. 6+8፤5+22፤ ኢዮ. 29+4:: ይሁን እንጂ፣ በብሉይ ኪዳን በአብዛኛው የሚታየው፣ ከእግዚአ ብሔር ወዳጅነት ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት ነበር::

ከዚያም ኢየሱስ ሁኔታውን ለወጠው:: የኃጢአታችንን ዕዳ በመስቀል ላይ በከፈለ ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር የመለየታችን ተምሳሌት የሆነው የቤተመቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ተተረተረ:: ይህ የሚያመለክተው፣ እንደገና በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ለመግባት የተቻለ መሆኑን ነው::

## አሥራ አንደኛ ቀን የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጆች መሆን

ከእግዚአብሔር ለመገናኘት እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት የብዙ ሰዓታት ዝግጅት ሳያስፈልገን፣ በማንኛውም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንችላለን:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ይህ ብቻ አይደለም:: ነገር ግን አሁን ዕርቅን ባገኘ ንበት በጌታችን በኢየሱስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ ሐሴት እናደርጋለን »* ሮሜ 5+11:: ከእግዚአብሔር ፀጋና ከኢየሱስ መስዋዕትነት የተነሣ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለመወዳጀት ይቻ ላል:- *«ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን»* 2ቆሮ. 5+18:: «ኢየሱስ ክርስቶስ የእኔ ወዳጅ» ይላል አንድ የቆየ መዝሙር:: ከሥላሴ ሦስት አካላት ጋር ወዳጅነትና ግንኙነት እንድንመሠርት የሚጋብዘን ግን እግዚአብሔር ነው፤ አብ 1ዮሐ. 1+3 ፣ ወልድ 1ቆሮ. 1+9፣ መንፈስ ቅዱስ 2ቆሮ. 13+14::

ኢየሱስ እንዲህ አለ:- *«ከእንግዲህ አገልጋዮች አልላችሁም፤ አገልጋይ ጌታው የሚሠራውን አያውቅምና፤ ነገር ግን ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጽሁላችሁ ወዳጆች ብያችኋለሁ::»* ዮሐ. 15+15:: በዚህ ጥቅስ፣ *«ወዳጆች»* የሚለው ቃል የሚያመለክተው፣ ጊዜያዊ ትውውቅን ሳይሆን፣ መቀራረብና መተማመን ያለበትን ህብረት ነው:: በንጉሥ ቤተ መንግሥት፣ አገልጋዮች እንደፈለጉ ወደ ንጉሡ ለመቅረብ አይችሉም:: ቤተሰቦቹና ታማኝ ወዳጆቹ ግን፣ ቅርብ ግን ኙነት የማድረግ፣ በቀጥታ ወደ እርሱ የመግባትና ምስጢራዊ ነገሮችን የመለ ዋወጥ ዕድል ይኖራቸዋል::

እግዚአብሔር የቅርብ ወዳጁ ሊያደርገኝ መፈለጉ፣ ከአእምሮ በላይ የሆነ

ነገር ነው። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ»* ዘፀ. 34+14።

እግዚአብሔር በቅርብ እንድናውቀው ይፈልጋል። እንደውም የሕይወታችንን ዝርዝር ጉዳዮች ጨምሮ፣ ዓለማትን በእቅዱ የሠራቸውና ታሪክን ያመቻቸው ወዳጆቹ እንድንሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ፣ በምድር ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውን ልክና የመኖሪያ ሥፍራቸውንም ዳርቻ ወሰነላቸው። ይኸውም ሰዎች እግዚአብሔርን ፈልገው ተመራምረው ምናልባት ያገኙት እንደሆነ ብሎ ነው»* ሐዋ. 17+26-27።

እግዚአብሔርን ማወቅና መውደድ ትልቁ ዕድላችን ሲሆን፣ መታወቅና መወደድ ደግሞ ለእግዚአብሔር ትልቅ ደስታን ይሰጠዋል። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- *«የሚመካ ግን እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ በማወቁና በምድር ላይ ምህረትን፣ ፍትህንና ጽድቅን የማደርግ መሆኔን በመረዳቱ፣ በዚህ ይመካ፤ እኔ በነዚህ ነገሮች እደሰታለሁና»* ኤር. 9+24።

ሁሉን ቻይ፣ የማይታይ እንዲሁም ፍፁም በሆነ እግዚአብሔርና፣ ውሱንና ኃጢአተኛ በሆነ ሰብዓዊ ፍጡር መካከል ቅርብ ወዳጅነት ሊፈጠር ይቻላል ብሎ ማሰቡ ያስቸግራል። በጌታና አገልጋይ፣ ፈጣሪና ፍጡር፣ ወይም በአባትና ልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳቱ ይቀላል። እግዚአብሔር ወዳጁ ሊያደርገኝ ፈለገ ሲባል ግን ምን ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተ ጠቀሱትን የእግዚአብሔር ወዳጆች ሕይወት በመመርመር የእግዚአብሔር ወዳጅ የመሆንን ስድስት ምስጢሮች እንማራለን። በዚህ ምዕራፍ ሁለቱን ምስጢራት፣ የቀሩትን አራቱን ደግሞ በሚቀጥለው እናያቸዋለን።

## የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ መሆን

**በማያቋርጥ መነጋገር።** በሳምንት አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ወይም በየዕለቱ የፀሎና ጊዜ እንዲኖርህ በማድረግ እንኳን በፍፁም ከእግዚአ ብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት ልታሳድግ አትችልም። ከእርሱ ጋር ወዳጅነት የምት መሠርተው፣ የሕይወት ገጠመኞችህን ሁሉ ለእርሱ በማዋየት ነው።

> *እግዚአብሔርን ማወቅና መውደድ ትልቁ ዕድላችን ሲሆን፣ መታወቅና መወደድ ደግሞ ለእግዚአብሔር ትልቅ ደስታን ይሰጠዋል።*

በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛ ዕለታዊ የጽሞና ጊዜ ልምድ መመሥረቱ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በጊዜ ሰሌዳህ ከያዝከው ቀጠሮ የበለጠ ነገር ይሻል።

በእነቅስቃሴዎችህ፣ በንግግሮችህና በምታስባቸው ነገሮች ውስጥ እንኳን ሳይቀር እንድታስገባው ይፈልጋል:: በቀን ውስጥ *በማንኛውም ሰዓት* ስለምታከናውነው ወይም ስለምታስበው ነገር ገደብ በሌለውና በማያቋርጥ ሁኔታ ከእርሱ ጋር ልትወያይ ትችላለህ:: «ሳታቋርጡ ፀልዩ» 1ቆሮ. 5÷17 ሲል፣ እየተገበያየን፣ በመኪና እየተጓዝን፣ *ሥራ* እየሠራን ወይም ማንኛውንም ዕለታዊ ተግባር እያከናወንን ከእግዚአብሔር ጋር እንድንወያይ ማዘዙ ነው::

የተለመደው የተሳሳተ አመለካከት፣ «ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ» ማለት ከእርሱ ጋር *ለብቻ* መሆን የሚለው ትርጉም ነው:: እርግጥ ኢየሱስ በምሳሌነት እንዳሳየን፣ ከእግዚአብሔር ጋር የብቻ ጊዜ ያስፈልገናል:: ይህ ከአንቅልፍ ሌላ ካለህ ጊዜ እጅግ ትንሹ ነው:: እግዚአብሔር በምታከናውነው ነገር ውስጥ ድርሻ እንዲኖረው ከጠየቅኸውና፣ እዚያ መገኘቱ ከተሰማህ፣ የምታደርገው *ነገር ሁሉ* «ከርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ» ሊሆን ይችላል::

ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ውይይት ማዳበርን ለመማሪያነት የተጻፈ ዓይነተኛ መጽሐፍ፣ *የእግዘአብሔርን መገኘት መለማመድ* (Practicing The presence of God) የሚለው ነው:: መጽሐፉ የተዘጋጀው በአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአንድ የፈረንሳይ ገዳም ውስጥ ምግብ አብሳይ በሆነ ትሁት ሰው ነው:: ሰውዬው፣ ወንድም ላውረንስ ይባል ነበር:: ላውረንስ፣ ምግብ ማዘጋጀትና ዕቃ ማጠብን የመሰሉ የተለመዱና ዝቅተኛ *ሥራዎችን*፣ እግዚአብሔርን ወደማመስገኛነትና ከእርሱ ጋር ህብረት ወደ መፍጠሪያ ክንውንነት የመለወጥ ችሎታ ነበረው:: በእርሱ አገላለጥ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነት የመፍጠሪያው ቁልፍ፣ የምታደርገውን ነገር መቀየሩ ሳይሆን፣ ስለምታደርገው ነገር *ያለህን አመለካከት* መለወጥ ነው:: ብዙውን ጊዜ ለራስህ የምታደርጋቸውን፣ ማለት መመገብን፣ መታጠብን፣ መስራትን፣ መዝናናትን ወይም ማጽዳትን የመሳሰሉ ነገሮችን፣ ለእግዚአብሔር ማድረግን ጀምር::

እግዚአብሔርን ለማምለክ ይቻለን ዘንድ ዕለታዊ ተግባሮቻችንን «ወደ ጎን ማድረግ»፣ አለብን የሚል ስሜት ብዙ ጊዜ ይሰማናል:: የዚህ ምክንያቱ እርሱ ሁል ጊዜ ከኛ ጋር መሆኑን አለመለማመዳችን ብቻ ነው:: ወንድም ላውረንስ በሕይወት ተራ ተግባራት ዓማካይነት እግዚአብሔርን የማምለኩን ነገር ቀላል ሆኖ አግኝቶታል:: ለመንፈሳዊ አምልኮ የተለየ ፀጥታ ወዳለው *ሥፍራ* መሄዱ አላስፈለገውም::

ይህ ነው የእግዚአብሔር እቅድ:: ኤደን ገነት ውስጥ አምልኮ በስብሰባ መልክ የሚካሄድ ሳይሆን፣ የማያቋርጥ ድርጊት ነበር:: አዳምና ሄዋን ከእግዚአብሔር ጋር የሁል ጊዜ ግንኙነት ነበራቸው:: እግዚአብሔር ሁል ጊዜ አብሮህ

ስለሆነ፣ አሁን ካለህበት ይልቅ ለእርሱ የሚቀርበው ሥፍራ የለም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ከሁሉ በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ* » ኤፌ. 4+6::

የወንድም ሳውረንስ ሌላ ጠቃሚ አሳብ፣ ረጅም ጊዜ ከሚወስድ ውስብስብ ፀሎት ይልቅ፣ *በተከታታይነት* ቀኑን ሙሉ ውይይታዊ የሆኑ አጫጭር ጸሎቶች ሲያደርጉ መዋሉ ይመረጣል የሚል ነው:: ትኩረት ስለማድረግና የሚበታተን አሳብን ስለ መሰብሰብ ሲናገር ደግሞ እንዲህ ይላሉ:- «በጸሎት ጊዜ ብዙ መናገር ለአሳብ መበታተን ምክንያት ስለሚሆን፣ ብዙ ቃላት እንድትጠቀም አልመክርህም »:: የትኩረት እጥረት ባለበት በዚህ ዘመን፣ ጸሎትን ግልጥና አጭር ስለማድረግ ከ450 ዓመት በፊት የተሰጠ ይህ ምክር አግባብነት አለው::

መጽሐፍ ቅዱስ «*ሳታቋርጡ ጸልዩ*» 1ተሰ. 5+17 ይለናል:: ይህን ማድረጉ እንዴት ይቻላል? የሚቻልበት አንዱ መንገድ፣ ክርስቲያኖች ለዘመናት እንዳደ ረጉት፣ ቀኑን ሙሉ «የእስትንፋስ ጸሎት» መጸለይ ነው:: በአንድ ትንፋሽ ለኢ የሱስ ልትደግመው የሚቻልህ አጭር ዐረፍተ ነገር ወይም ቀላል ሀረግ ምረጥ :: «ከእኔ ጋር ነህ»፣«ፀጋህን አግኝቻ ለሁ»፣ «በአንተ እታመናለሁ»፣ «ላውቅህ እፈልጋለሁ»፣ «የአንተ ነኝ»፣ «እንድታመንብህ እርዳኝ» የሚሉትንና የመሳሰሉትን:: በተ ጨማሪም አንድ አጭር አንቀጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልትጠቀም ትችላለህ:- «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው»፣ «ፍፁም አትተወኝም»፣ «አንተ አምላኬ ነህ» የሚሉ ትንና የመሳሰሉትን:: ወደ ልብህ ጠልቀው እንዲገቡ በተቻለህ መጠን ሁል ጊዜ ጸልያቸው:: ዓላማህ እግዚአብሔርን ለመቆጣጠር ሳይሆን፣ እሱን ለማክ በር ስለመሆኑ እርግጠኛ ሁን::

> *እግዚአብሔር በምታከናውነው ነገር ውስጥ ድርሻ እንዲኖረው ከጠየቅኸውና መገኘቱ ከተሰማህ፤ የምታደርገው ነገር ሁሉ «ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ» ሊሆን ይችላል::*


የእግዚአብሔርን በአጠገብህ መኖር መለማመዱ፣ ልታሳድገው የሚቻልህ ልማድና ጥበብ ነው:: ሙዚቀኞች ዘና ብለው ሙዚቃ መጫወትን ለመልመድ በየዕለቱ ጥበቡን እንደሚያጠኑ፣ አንተም በየዕለቱ በተለያየ ጊዜ ስለ እግዚአ ብሔር ማሰብን ለመማር እራስህን ማስገደድ አለብህ:: አእምሮህ እግዚአብሔርን እንዲያስታውስ አሰልጥነው::

በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር መሆኑን በቋሚነት የሚያስታው ሱህ (አስታዋሾችን) መፍጠር ያስፈልግሃል:: የሚታዩ አስታዋሽ ነገሮችን

በዙሪያህ በማስቀመጥ ጀምር:: *«እግዚአብሔር አሁን ለእኔና ከእኔ ጋር ነው»* የሚል ትንሽ ማስታወሻ አዘጋጅተህ አጠገብህ ልታኖር ትችላለህ:: ቤኔዲክት የተባለ ውን የሥነ-መለኮት ሰው አስተምህሮ የሚከተሉ መነኮሳት *«የሰዓቱን ጸሎት»* ያስታውሳቸው ዘንድ ደወል ባለው የሰዓት ድምፅ ይጠቀማሉ:: አንተም አስ ታዋሽ ድምፅ የሚያሰማ ሰዓት ወይም ስልክ ካለህ፣ ልትጠቀምበት ትችላ ለህ:: አንዳንዴ የእግዚአብሔር አብሮህ መገኘት ይሰማሃል፤ አንዳንዴ ደግሞ አይሰማህም::

በነዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔር መገኘት *እንዲሰማህ* የምትሻ ከሆንክ፣ ቁም ነገሩን ስተሃል:: እግዚአብሔርን የምናመሰግነው መልካም ስሜት እንዲሰማን ሳይሆን መልካም ነገርን ለማድረግ ነው:: ዓላማህ ወይም ግብህ ስሜት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ አብሮህ ስለመገኘቱ *እውነት* የማያቋርጥ ግንዛቤ ያለህ መሆኑ ነው:: ይህ ነው የአምልኳዊ ሕይወት አኗኗር::

**በማያቋርጥ ጥሞና ማሰላሰል::** ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነት የመመስረ ቻው ሁለተኛ መንገድ፣ ቀኑን ሙሉ ስለ ቃሉ ማሰብ ነው:: ይህ ድርጊት ማሰ ላሰል የሚባል ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስም ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ስለ አደረጋቸውና ስለ ተናገራቸው ነገሮች እንድናሰላስል በተ ደጋጋሚ ያስገነዝበናል መዝ. 22÷24፤ 142÷5፤ 144÷5፤ ኢያሱ 1÷8፤ መዝ. 1÷2::



እግዚአብሔር *የሚናገረውን ሳንረዳ* ወዳጆቹ ልንሆን አንች ልም:: ሳታውቀው ልትወደው፣ ቃሉን ሳትረዳም ልታወ ቀው አትችልም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እግዚአብሔር በሴሎ ይገለጥ ነበር፤ በዚያም በቃሉ ዓማካይነት ራሱን ለሳሙኤል ገለጠ»* 1ሳሙ. 3÷21:: እግዚአ ብሔር ዛሬም በዚሁ መንገድ ይጠቀማል::

መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ቀኑን ሙሉ ባታሳልፍም፣ ያነበብካቸውን ወይም ያጠናሃቸውን ጥቅሶች *እያሰላሰልካቸው* ልትውል ትችላለህ::

ጥሞና በገለልተኛ ሥፍራ በሚኖሩ መነኩሴዎች ወይም መናኞች የሚከና ወን አስቸጋሪና ምስጢራዊ የአምልኮ ሥርዓት እንደሆነ ተደርጐ ብዙ ጊዜ የተ ሣሣተ ግንዛቤ ይሰጠዋል:: ጥሞና ያተኮረና የተሰባሰበ ማሰላሰል ሲሆን፣ ማንም ሊማረውና የትም ሆኖ ሊጠቀምበት ይችላል::

አንድን ችግር በመደጋገም በአእምሮህ ካሰላሰልከው፣ ያ መጨነቅ ይበላል:: ስለ እግዚአብሔር ቃል በመደጋገም ስታሰላስል ግን፣ ድርጊቱ ጥሞና ይባላል:: መጨነቅን ካወቅህ፣ ጥሞናንም ታውቀበታለህ! ማድረግ ያለብህ፣ ትኩረትህን ከችግርህ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መቀየር ነው:: በእግዚአብሔር ቃል

ላይ ይበልጥ ጥሞና ካደረግህ፣ የሚያስጨንቅህ ነገር ያነሰ ይሆናል።

እግዚአብሔር ኢዮብንና ዳዊትን እንደወዳጆቹ የቆጠራቸው፣ ቃሉን ከምንም ይልቅ በማክበራቸው ነው። ያለ ማቋረጥ፣ ቀኑን ሙሉ ስለ ቃሉ ያስቡ ነበር። ኢዮብ እንዲህ ብሏል ፡- «*ከአፉ ከወጣው ትዕዛዝ አልራቅሁም፣ የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዠአለሁ*» ኢዮብ 23፥12። ዳዊት ደግሞ እንዲህ አለ፡- «*አቤቱ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ! ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ።*» መዝ. 119፥97። «*ሥራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፣ ድንቅ ሥራህን ሁሉ አውጠነጥናለሁ*» መዝ. 77፥12።

የተወዳጁ ሰዎች ምስጢር እንደሚጋሩ፣ አንተም ቀኑን ሁሉ ስለቃሉ የማሰላሰል ልምድን ብታዳብር፣ እግዚአብሔርም ምስጢሩን ያካፍልሃል። ምስጢሩን ለአብርሃም ነግሮታል። ለዳንኤል፣ ለጳውሎስ፣ ለደቀ መዛሙርት እና ለሌሎቹም እንዲሁ አድርጓል፣ ዘፍጥ. 18፥17፤ ዳን. 2፥19፤ 1ቆሮ. 2፥7-10።

መጽሐፍ ቅዱስ ካነበብክ፣ ስብከት ከሰማህ ወይም ቴፕ ካዳመጥክ በኋላ ችላ ብለህ አትሂድ። ደጋግመህ በማሰላሰል እውነቱን በአእምሮህ ከልሰው። እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ይበልጥ በከለስከው ቁጥር ብዙ ሰዎች የሚያመልጣቸውን የሕይወት «ምስጢር» ይበልጥ ትረዳለህ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*እግዚአብሔር ምስጢሩን ከሚፈሩት ወዳጆች አይሰውርም፣ ኪዳኑንም ይገልጥላቸዋል*» መዝ. 25፥14።

በሚቀጥለው ምዕራፍ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነት ማጎልበትን በተመለከተ አራት ተጨማሪ ምስጢሮችን እንማራለን። ነገር ግን እስከ ነገ አትጠብቅ። ከእግዚአብሔር ጋር ተደጋጋሚ ውይይት ማድረግንና ቃሉን ያለ ማቋረጥ ማሰላሰልን ዛሬውኑ ጀምር። ጸሎት ለእግዚአብሔር እንድትናገር ያደርግሃል፤ ጥሞና ደግሞ እግዚአብሔር እንዲያናግርህ ያደርገዋል። ሁለቱም የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመሆን እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው።

## አሥራ አንደኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ :-** እግዚአብሔር የቅርብ ወዳጁ ለመሆን ይፈልጋል::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«እግዚአብሔር ምስጢሩን ከሚፈሩት ወዳጆቹ አይሰውርም፤ ኪዳኑንም ይገልጥላቸዋል»* መዝ. 25÷14::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** ስለ እግዚአብሔር ማሰብንና ቀኑን ሙሉ ከእርሱ ጋር መነጋገርን ለማስታወስ ምን ላድርግ?

# 12

# ከእግዚአሔር ጋር ወዳጅነትህን ማሳደግ

*ለቅን ሰው ግን ምስጢሩን ይገልጥለታል ::*

*ምሳሌ 3÷32*

***ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል ::***

***ያዕ. 4÷8***

ወደ እግዚአብሔር ያለህ ቀረቤታ ልትቀርበው በመረጥከው ልክ ነው:: እንደማንኛውም ወዳጅነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ወዳጅነት ለማሳደግ መጣር አለብህ:: በአጋጣሚ የሚሆን ነገር አይደለም:: ፍላጎት፣ ጊዜና ብርታትን ይጠይቃል:: ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅና የቀረበ ግንኙነት እንዲኖ ርህ ከፈለክ፣ ስሜትህን ለእርሱ በታማኝነት ማካፈልን ልመድ፣ አንድ ነገር ሲያዝህ በእምነት አድርገው፣ እርሱ የሚወደውን መውደድን ተማር፣ ከሁሉም ይልቅ የእርሱን ወዳጅነት ፈልግ::

**ለእግዚአብሔር እውነተኛ መሆንን መምረጥ አለብኝ::** ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖር ጥልቅ ወዳጅነት የመጀመሪያው የማዕዘን ድንጋይ፣ ስለ ድካሞችህና ስሜቶችህ ፍፁም እውነተኛና ግልጥ መሆን ነው:: ፍፁምነትን እግዚአብሔር ከአንተ አይጠብቅም፤ እውነተኛና ግልጥ መሆንህን ግን በጥብቅ ይፈልገዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር ወዳጆች አንዳቸውም እንኳን ፍፁም አልነበሩም:: የእግዚአብሔር ወዳጅ የመሆኛው መስፈርት ፍፁ ምነት ቢሆን ኑሮ፣ ወዳጆቹ ለመሆን በፍፁም አንችልም ነበር:: መልካሙ ነገር፣ ከእግዚአብሔር ፀጋ የተነሣ፣ ኢየሱስ አሁንም:- *«የኃጢአተኞች ወዳጅ»* ማቴ. 11÷19 መሆኑ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ወዳጆች፣ ስሜታቸውን

በመግለጥ፣ ቅሬታቸውን ለፈጣሪያቸው በማሳወቅ፣ ውሳኔዎቹን በመንቀፍና በመከራከር የሚሰማቸውን በእውነተኛነት የሚገልጡ ነበሩ። በዚህ ግልጥነታቸው እግዚአብሔር የተቸገረ አይመስልም፤ እንደውም ድርጊታቸውን አበረታታ።

አብርሃም የሰዶም ከተማ ጥፋትን በተመለከተ ጥያቄ እንዲያነሣና እንዲደራደረው እግዚአብሔር ፈቅዷል። ከአምሳ ጻድቃን ሰዎች እስከ አሥር ብቻ ድረስ በመደራደር፣ ከተማይቱን ከጥፋት ለማዳን በሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ተደራድሯል፣ ተሟግቷል።

ዳዊት «ረሳኸኝ»፣ «ጣልከኝ»፣«ተውከኝ»፣ በማለት ያቀረባቸውን አቤቱታዎችም እግዚአብሔር በትእግስት አድምጧል። ኤርምያስ እግዚአብሔር እንዳታለለው በተናገረ ጊዜ፣ አልቀሰፈውም። ኢዮብ በሰቆቃው ጊዜ ምሬቱን እንዲናገር ተፈቅዶለት ነበር። በመጨረሻ ግን እውነተኛና ግልጥ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር ተሟግቶለታል። ጓደኞቹን ግን እውነተኞች ባለመሆናቸው ገስጿቸዋል። እንዲህ ነው ያላቸው:- *«እንደአገልጋዬ እንደ ኢዮብ ስለ እኔ ቅን ነገር ስላልተናገራችሁ ... አገልጋዬ ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፣ እኔም ጸሎቱን እቀበላለሁ» ኢዮብ 42፥7-8።*

ግልጥ ወዳጅነት በታየበት አንድ አስገራሚ ምሳሌ ውስጥ ዘፀ. 33፥1-17፣ እግዚአብሔር በእስራኤል አለመታዘዝ ምክንያት የተሰማውን ቁጣ በግልጥ ተናግሯል። የተስፋይቱን ምድር ለእስራኤላውያን ለመስጠት የገባውን ቃል የሚያከብር መሆኑን ለሙሴ ከገለጠለት በኋላ፣ ነገር ግን በምድረበዳው ከእነርሱ ጋር አንዲት እርምጃ ወደ ፊት የማይራመድ መሆኑን አስረዳው። እንዳታከቱት በመግለጥ ስሜቱን ለሙሴ አስታወቀው።

*ፍፁም እንድትሆን እግዚአብሔር አይጠብቅም፤ ፍፁም ታማኝ መሆንህን ግን በጥብቅ ይፈልገዋል።*

ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ወዳጅነቱ በተመሳሳይ ግልጥነት እንዲህ አለ:- *«እነዚህን ሕዝብ ምራ ብለህ ነገርኸኝ ነበር፣ ከኔ ጋር የምትልከው ማን እንደሆነ ግን አላሳወቅኸኝም፤...በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ፣ አንተን አውቅህና ያለማቋረጥ በፊትህ ሞገስ አገኝ ዘንድ አስተምረኝ፤ ይህ ሕዝብ የአንተ ሕዝብ መሆኑን አስታውስ። ... እግዚአብሔር <ሀልዎቴ ከአንተ ጋር ይሄዳል እረፍትም እሰጥሃለሁ> ብሎ መለሰ ። ከዚያም ሙሴ < ሀልዎትህ ከእኔ ጋር ካልሄደ ከዚህ አትስደደን። አንተ ከእኛ ጋር ካልሄድህ፣ አንተ በእኔና በሕዝብህ መደሰትህን ሰላው እንዴት ያውቃል?>*

*ለሱ:: እግዚአብሔርም ሙሴን፣ <በአንተ ደስ ስላለኝና በስም ስለማውቅህ፣ የጠየቅ ኸውን ያንኑ አደርጋለሁ> አለው» ዘፀ. 33÷12-17::*

እንዲህ ያለውን እውነተኛነትና ብርቱ ታማኝነት እግዚአብሔር ከአንተ ይቀበላልን? እንዴታ ! እውነተኛ ወዳጅነት በግልጥነት ላይ ነው የሚመሠረ ተው:: ድፍረት የሚመስል ነገርን እግዚአብሔር እንደ *እውነተኛነት* ያየዋል:: በጥልቅ ስሜት የሚገለጡትን የወዳጆቹን ቃላት ያደምጣል:: አታካች ሃይማኖ ታዊ ድግግሞሾች ግን ያሰለቹታል:: ወዳጁ ለመሆን ትችል ዘንድ፣ ሊሰማህ ወይም ልትናገረው ስለሚገባህ ነገር ሳይ ሆን፣ እውነተኛ ስሜትህን በማካፈል ግልጥ ልትሆንለት ይገባል::

*መራራነት ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነት እንዳይመሠረት የማያግድ ትልቅ እንቅፋት ነው::*

በሕይወትህ አንዳንድ ሁኔታዎች የተታለልክ መስሎህ ወይም ቅር የተሰኘ ህበት ነገር እንዳለ ተሰምቶህ፣ በእግዚአ ብሔር ላይ በድብቅ ተቆጥተህ፣ እንዲሁም ተበሳጭተህ ከሆነ፣ ንስሐ መግባት ያስፈልግሃል:: በሕይወታችን ላይ የሚደርስን ማንኛውንም ነገር እግዚአብሔር ለበጎ የሚጠቀምበት መሆኑን ወደ መረዳት ደረጃ እስክናድግ ድረስ፣ መልካችንን፣ ያለፈ ሕይወታችንን፣ መልስ ያላገኙ ጸሎቶቻችንን፣ ያለፉ ጉዳቶቻችንና እኛ እግዚአብሔር ብንሆን ኑሮ እንገለውጣቸው የነበሩ ሌሎች ነገሮችን እናስብና በእግዚአብሔር ላይ ቅር እንሰኛ ለን:: ሰዎች ብዙ ጊዜ ከሌሎች ለሚደርስባቸው ጉዳት እግዚአብሔርን ይወቅሳሉ:: እንዲህ ያለው ነገር፣ ዊሊያም ባክስ የተባለው ጸሐፊ እንዳለው፣ «ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት መካከል ስውር ሽለቆን» ይፈጥራል::

መራርነት «እንዲህ ያለው ሁኔታ እንዲደርስብኝ እግዚአብሔር የሚፈቅድ ከሆነ፣ የእርሱ ወዳጅ መሆኑ ምን ያደርግልኛል?» የሚል ጥያቄን ስለሚፈ ጥር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖርህ ወዳጅነት ትልቅ መሰናክል ነው:: የዚህ መፍትሄው፣ የደረሰብህ ነገር ከባድና ከግንዛቤህ በላይ ቢሆን እንኳን፣ እግዚአ ብሔር ሁልጊዜ የሚሠራው ለጥቅምህ መሆኑን መረዳቱ ነው:: ይሁን እንጂ ቅሬታህን ማሳወቁና ስሜትህን መግለጡ ለፈውስ የመጀመሪያ እርምጃ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ብዙ ሰዎች እንዳደረጉት፣ የሚሰማህን ለእግዚአብሔር በትክክል ንገረው ኢዮብ 7÷17-21፤ መዝ. 83÷13፤ ኤር. 20÷7፤ ሩት 1÷20::

እግዚአብሔር ቅንነትንና፣ እውነተኛነትን ሊያስተምረን መዝሙረ ዳዊትን ሰጠን:: መዝሙረ ዳዊት፣ እሮሮን፣ አድናቆትን፣ ጥርጣሬን፣ ፍርሃትን፣

ቅሬታን ከምሥጋና ጋር የተጣመረ ጥልቅ ስሜትን፣ ውዳሴን እና የእምነት መግለጫዎችን የያዘ የአምልኮ መመሪያ ነው። እሉ የምንላቸው ስሜቶች ሁሉ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ ተመዝግበዋል። የዳዊትንና የሌሎቹን በጥልቅ ስሜት የታጀበ ንሰሐ በምታነብበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገው፣ ምንም ሳትሸሽግ በዚህ መልኩ እንድታመልከው መሆኑን ተገንዘብ። እንደ ዳዊት:- *«ብሶቴን በፊቱ እፈሳለሁ፤ ችግሬንም በፊቱ እናገራለሁ»* መዝ. 142፥2 በማለት ልትፀልይ ትችላለህ።

የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጆች ሁሉ ሙሴ፣ ዳዊት፣ አብርሃም፣ ኢዮብና ሌሎቹም ከጥርጣሬ ጋር ትግል የነበረባቸው መሆኑን ማወቁ ያበረታታል። ቅሬታቸውን በሃይማኖታዊ የአስመሳይነት ጭምብል ከመሸፈን ይልቅ፣ በቅንነትና በግልጥ በአደባባይ ገለጧቸው። ጥርጣሬን መግለጥ አንዳንድ ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ወዳጅነት ወደ ሁለተኛው ደረጃ የመሸጋገሪያ የመጀመሪያ እርምጃ ነው።

**እግዚአብሔርን በእምነት መታዘዝን መምረጥ አለብኝ።** የእግዚአብሔርን ጥበብ ባመንክና፣ ትእዛዙ የማይገባህ ቢሆን እንኳን በፈፀምከው ጊዜ ሁሉ ከእርሱ ጋር ያለህን ወዳጅነት ታሳድገዋለህ። ታዛዥነት የወዳጅነት መገለጫ ነው ብለን ብዙ ጊዜ አናስብም። ያ ከወላጅ፣ ከአለቃ ወይም ከበላይ ሹም ጋር ላለ ግንኙነት እንጂ ለወዳጅነት የተጠበቀ አይደለም እንላለን። ይሁን እንጂ፣ ታዛዥነት ከእግዚአብሔር ጋር ለመወዳጀት ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ኢየሱስ እንዲህ በማለት በግልጥ አስገንዝቧል:- *«የማዛችሁን ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ»* *ዮሐ. 15፥14።*

ኢየሱስ «ወዳጆቼ »፣ ብሎ ሲጠራን የተጠቀመበት ቃል፣ ንጉሳዊ ቤተ መንግሥት ውስጥ «የንጉሡ ወዳጆች»፣ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ሊሆን እንደሚችል ባለፈው ምዕራፍ ገልጫለሁ። የንጉሡ ወዳጆች የተለየ ዕድል ቢኖራቸውም፣ ለእርሱ መገዛትና ትእዛዛቱንም መፈፀም ነበረባቸው። የእግዚአ ብሔር ወዳጆች እንጂ፣ አቻዎቹ አይደለንም። አፍቃሪ ገዢያችን ስለሆነ እንከተለዋለን።

እግዚአብሔርን የምንታዘዘው፣ ከኃላፊነት፣ ከፍርሃት ወይም ከመገደድ የተነሣ ሳይሆን፣ *ስለምንወደውና* ለኛ የሚጠቅመንን ያውቃል ብለን ስለምናምን ነው። ኢየሱስ ካደረገልን ነገር ሁሉና ከውለታው የተነሣ ልንከተለው *እንፈል ጋለን፤* በቅርብ ስንከተለውም ወዳጅነታችን ጥብቅ ይሆናል።

አማኒያን ያልሆኑ ሰዎች፣ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር የሚታዘዙት፣ በግዴታ፣ በጥፋተኝነት ስሜትና ቅጣትን በመፍራት ነው ብለው ያስ

ባሉ። እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው። ይቅር በመባላችንና ነፃ በመውጣታችን ከፍቅር የተነሣ እንታዘዛለን፤ ታዛዥነታችንም ታላቅ ደስታን ያመጣልናል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ *«አብ እንደወደደኝ እኔም ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ፤ እኔ የአባቴን ትእዛዝ ጠብቄ፤ በፍቅሩ እንደምኖር፤ እናንተም ትእዛዜንብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። ደስታዬ በእናንተ እንዲሆን፤ ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነገሬአችኋለሁ»* ዮሐ. 15÷9-11።

አሥራ ሁለተኛ ቀን
ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ወዳጅነት ማሳደግ

ኢየሱስ ከእኛ የሚጠብቀው፣ ከአብ ጋር ባለው ግንኙነት እርሱ ያደረገውን እንድናደርግ ብቻ እንደሆነ አስተውል። እርሱ ከአባቱ ጋር ያለው ግንኙነት እኛ ከእርሱ ጋር ለሚኖረን ወዳጅነት ምሳሌ ነው። ኢየሱስ ከፍቅር የተነሣ አብ የጠየቀውን ሁሉ አደረገ።

እውነተኛ ወዳጅነት በተግባር ይገለጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን እንድንወድ፣ ችግረኞችን እንድንረዳ፣ ያለንን እንድናካፍል፣ ሕይወታችንን በንጽሕና እንድንጠብቅ፣ ይቅርታ እንድናደርግና ሌሎችን ወደ እርሱ እንድናመጣ ሲጠይቀን በፍጥነት እንድንታዘዘው ፍቅር ያነሳሳናል።

ለእግዚአብሔር *«ታላቅ ነገር»* እንድናደርግ ሁልጊዜ ይነገረናል። በመሠረቱ እግዚአብሔር ይበልጥ ደስ የሚለው፣ በፍቅር በመታዘዝ ትናንሽ ነገሮችን ስናደርግለት ነው። ሥራዎቻችን በሌሎች ሰዎች አይታወቁ ይሆናል። እግዚአ ብሔር ግን ያያቸዋል፤ እንደ አምልኮም ይቀበላቸዋል።

ታላላቅ ዕድሎች ወደ እኛ የሚመጡት በሕይወት ዘመናችን አንድ ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል። ትንንሾቹ ዕድሎች ግን ሁልጊዜ በዙሪያችን ናቸው። እውነት መናገር፣ ደግነት፣ ሌሎችን ማጽናናት በመሳሰሉት ትንንሽ ድርጊቶቻችን እንኳን እግዚአብሔርን ፈገግ እንዲል እናደርገዋለን። ከጸሎት፣ ከምሥጋና ወይም ከስጦታችን ይልቅ ለትንንሽ የመታዘዝ ድርጊቶቻችን ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጣቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *«ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል እግዚአብሔር በሚቃጠል ቁርባንና መስዋዕት ደስ ይሰኛልን? እነሆ ! መታዘዝ ከመስዋዕት፤ ማዳመጥም ከአውራ በግ ስብ ይበልጣል»* 1ሳሙ. 15÷22።

ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው፣ በሰላሳ ዓመቱ በዮሐንስ ዓማካይነት በመጠመቅ ነው። ያኔ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ፀማለት ከሰማይ ተናገረ፦ *«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው»* ማቴ. 3÷17። እግዚአብሔርን እንዲህ ደስ ያሰኘውና ኢየሱስ ለሰላሳ ዓመት ያደርገው የነበረ ሥራ ምንድነው?

ስለነዚያ ድብቅ ዓመታት ሉቃስ 2÷51 ውስጥ ከተጠቀሰው ቃል ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጠው ነገር የለም። እንዲህ ነው የሚለው ቃሉ:- *«ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደናዝሬት መጣ፣ ይታዘዝላቸውም ነበር»።* እግዚአብሔር የተደሰተባቸው ሰላሳ ዓመታት *«ይታዘዝላቸውም ነበር»* በሚሉ ሁለት ቃላት ተጠቃለዋል።

**እግዚአብሔር ዋጋ ለሚሰጣቸው ነገሮች ዋጋ መስጠት አለብኝ።** የተወዳጁ ሰዎች ይህን ነው የሚያደርጉት- ለወዳጆቻቸው ጠቃሚ ስለሆነ ነገር ያስባሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ወዳጅነት ባደገ መጠን፣ እርሱ የሚወዳ ቸውን ነገሮች ይበልጥ እየወደድካቸው ትመጣለህ። በሚያሳዝነው ነገር ታዝናለህ፣ በሚያስደስተው ትደሰታለህ።

ጳውሎስ ይህን ለመሰለው ወዳጅነት ከሁሉ የላቀ ምሳሌ ነው። የእግዚአብ ሔር አጀንዳ፣ የእርሱም አጀንዳ፣ ፍላጎቱ የእርሱም ፍላጐት ነበር። *«በእግዚአ ብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና»* 2ቆሮ. 11÷2 ብሏል*።* ዳዊትም ተመሳሳይ ስሜቱን ሲገልጥ እንዲህ አለ:- *«የቤትህ ቅንዓት በላችኝ፤ የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ አርፎአል»* መዝ. 69÷9*።*

እግዚአብሔር ከሁሉም ይልቅ የሚፈልገው ምንድነው? የሕዝቡን ነፃ መውጣት። የጠፉ ልጆቹ ሁሉ እንዲገኙ ይፈልጋል! ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት አጠቃላይ ምክንያት ይህ ነው። በእግዚአብሔር ልብ እጅግ ውዱ ነገር፣ የልጁ ሞት ነው። ሁለተኛው ውድ ነገር፣ ልጆቹ ይህን የምሥራች ለሌ ሎች ማካፈላቸው ነው። የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመሆን ከፈለግህ፣ እርሱ የሚወዳቸውንና በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች መውደድ አለብህ። የእግዚአብሔር ወዳጆች፣ ለወዳጆቻቸው ስለ እግዚአብሔር ይናገራሉ።

**ከምንም ይበልጥ ከእግዚአብሔር ጋር መወዳጀትን መፈለግ አለብኝ።** መዝሙረ ዳዊት በዚህ ዓይነቶቹ የፍላጎት ምሳሌዎች የተሞላ ነው። ዳዊት ከምንም ይልቅ እግዚአብሔርን ለማወቅ ተመኝቷል። መንገት፣ መናፈቅ፣ መጠማት፣ መራብ የሚሉ ቃላትን ተጠቅሟል። እንዲህ በማለት እግዚአብሔርን ተማጠነው:- *«እግዚአ ብሔርን አንዲት ነገር እለምነዋለሁ እርሷንም እሻለሁ፤ ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአ ብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ክብር ውበት አይ ዘንድ፣ በመቅደሱም ሆኜ አሰላስል ዘንድ ነው»* መዝ. 27÷4። በሌላ መዝሙሩ ደግሞ፣ *«ምህረትህ ከሕይወት ይበልጣልና»* መዝ. 63÷3 ብሏል።

> *ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ወዳጅነት ባደገ መጠን፣ እሱ የሚወዳቸውን ነገሮች ይበልጥ እየወደድካቸው ትመጣለህ።*

ያዕቆብ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት የነበረው ጉጉት ከፍተኛ

ስለነበር፣ ሌሊቱን በሙሉ፡- *«ካልባረከኝ አልለቅህም»* ዘፍ. 32÷26፣ እያለ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል አድሯል። የታሪኩ አስደናቂ ክፍል፣ ኃያል የሆነው እግዚአብሔር ያዕቆብ እንዲያሸንፈው መፍቀዱ ነው! *«ስንታገለው»* እግዚአብሔር አይከፋውም። ምክንያቱም ትግል መጠጋጋትን ስለሚጠይቅ፣ ወደ እርሱ በጣም ያቀርበናል! በተጨማሪም ሁኔታው የፍቅር ድርጊት ነው። የፍቅር ድርጊታችንን እግዚአብሔር ይወደዋል።

ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ወዳጅነት እንዲኖረው ይጓጓ የነበረ ሌላ ሰው ጳውሎስ ነው። ከዚህ የሚበልጥበት ነገር አልነበረም፤ ቀዳሚ ነገሩ፣ አጠቃላይ ትኩረቱ፣ እና የሕይወቱ የመጨረሻ ግብ ነበር። ለዚህ ነበር እግዚአብሔር ጳውሎስን በታላቅ ሁኔታ የተጠቀመበት። የጳውሎስ የልቡ ምኞት እንዲህ ተገልጧል፣ *«ስሙታን ትንሣኤም እንድደርስ እናፍቃለሁ»* ፊልጵ. 3÷11።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ወደ እግዚአብሔር የሚኖርህ ቅርበት፣ *አንተ በመረጥከው መጠን ነው*። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን የቅርብ ወዳጅነት በምርጫ እንጂ፣ በአጋጣሚ የሚመጣ አይደለም። ሆን ብለህ ልትፈልገው ይገባል። በእርግጥ ከምንም ይበልጥ ትፈልገዋለህን? ለእርሱ ወዳጅነት ምን ያህል ዋጋ ትሰጣለህ? ከእርሱ ጋር ላለህ ወዳጅነት ስትል ሌሎች ነገሮችን ለመተው ፈቃደኛ ነህን? ወዳጅነትታችሁን ለማጠናከር የሚያስፈልጉ ልምዶችንና ክህሎቶችን ለማዳበር ፈቃደኛ ነህን?

ባለፉት ዘመናት ለእግዚአብሔር ልዩ ፍቅር ኖሮህ፣ አሁን ግን ያ ፍቅር ጠፍቶ ይሆናል። ይህ ነበር የኤፌሶን ክርስቲያኖች ችግር፤ የቀድሞ ፍቅራቸውን ጣሉት። ተገቢ ነገሮችን ሁሉ አድርገዋል፤ ያደረጉት ግን ከፍቅር ሳይሆን፣ ከግዴታ የተነሣ ነበር። የምትኖረው በልማዳዊ መንፈሳዊነት ከሆነ፣ እግዚአብሔር በሕይወትህ (መከራ) እንዲያልፍ ቢፈቅድ አትደነቅ።

መከራ ፍቅር የሚያቀጣጥል ነዳጅ ነው። በተፈጥሮ የኛ ያልሆነውን ነገር እንድንቀይር ብርታት ይሆነናል። ሲ.ኤስ.ሉዊስ የተባሉ ሰው፣ «ሥቃይ የእግዚአብሔር ድምፅ ማጉያ ነው » ብለዋል። ከመንፈሳዊ ልፍስፍስነታችን ሊያነሣን እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ዘዴ ነው። ችግሮችህ ቅጣት ሳይሆኑ፣ አፍቃሪ ከሆነው እግዚአብሔር የተላኩ የንቃ ጥሪዎች ናቸው። እግዚአብሔር በአንተ ስለተቆጣ ሳይሆን፣ እጅግ አድርጎ ስለሚወድህ ነው። ስለሆነም ከሱ ጋር ወዳለህ አንድነት ሊመልስህ ማንኛውንም ነገር ያደርጋል። ነገር ግን ለእርሱ ያለህን ፍቅር እንደገና የምታቀጣጥልበት ቀላል መንገድ አለ። እራሱ ይህን ይሰጥህ ዘንድ መጠየቅ ጀምር፤ እስክትቀበለውም ድረስ

ጥያቄህን አታቋርጥ:: ቀኑን ሙሉ እንዲህ እያልክ ጸልይ:- «ውዱ ኢየሱስ ሆይ ከምንም ይልቅ በቅርብ ላውቅህ እፈልጋለሁ»:: ባቢሎን ውስጥ ለነበሩት ምርኮኞች እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው:- *«እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፤ በፍፁም ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ» ኤር. 29፥13::*



## በጣም አስፈላጊው ግንኙነትህ

ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነትን ከማዳበር የበለጠ አስፈላጊ ነገር በፍጹም የለም:: ይህ ወዳጅነት ዘላለማዊ ነው:: ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲህ አለው:- ***«የዚህ ዓይነት ዕውቀት አለን ሲሉ የነበሩ አንዳንዶች ይህን በማድረጋቸው ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል»*** **1ጢሞ. 6፥21::** በሕይወትህ ከሁሉ ነገር ይበልጥ አስፈላጊ የሆነውን ነገር አጥተሃልን? ከሆነ አሁኑኑ እርምጃ ለመውሰድ ትችላለህ:: ምርጫው የአንተ መሆኑን አስታውስ:: ወደ እግዚአብሔር የሚኖርህ ቅርበት አንተ በመረጥከው መጠን ነው::

አሥራ ሁለተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ወደ እግዚአብሔር የሚኖረኝ ቅርበት እኔ በመረጥኩት መጠን ነው::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተም ይቀርባል» ያዕ. 4፥8::*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ ለመቅረብ ዛሬ የማደርገው ተግባራዊ ምርጫ ምንድነው?

# 13
# እግዚአብሔርን የሚያስደስት አምልኮ

*ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ።*

*ማር. 12፥30*

እግዚአብሔር ሁለንተናህን ይፈልጋል።

የአንተነትህን አንድ ክፍል ብቻ አይደለም የሚፈልገው። ልብህን በሙሉ፣ ነፍስህን በሙሉ፣ አእምሮህን በሙሉ፣ እና ኃይልህን በሙሉ ይፈልጋል። እግዚአብሔር፣ ግማሽ ልብ የሆነ መሰጠትህን፣ ከፊል ታዛዥነትህን፣ እና ትርፍ ጊዜህን እንዲሁም ገንዘብህን አይደለም የሚፈልገው። ሙሉ ፍቅርህን ወይም ታዛዥነትህን እንጂ፣ የሕይወትህን ትንሽ ክፍል አይደለም የሚፈል ገው።

አንዲት ሳምራዊት ሴት ከሁሉ ስለሚሻል የአምልኮ ጊዜ፣ ሥፍራና ዘዴ ከኢየሱስ ጋር ለመከራከር ሞክራለች። እነዚህ ውጫዊ ጉዳዮች ዋጋ የሌላ ቸው ነገሮች መሆናቸውን ኢየሱስ ገለጸላት። የምታመልክበት ሥፍራ ከምታ መልክበት ምክንያቶችና በአምልኮም ጊዜ ለእግዚአብሔር ካለህ መሰጠት ጋር እኩል ጠቃሚነት ያለው ጉዳይ አይደለም። ትክክል የሆነና ያልሆነ የአምልኮ ሁኔታ አለ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እግዚአብሔርን እናመስግን፤ ደግ ሞም ደስ በሚያሰኘው መንገድ በአክብሮትና በፍርሃት እናምልከው» ዕብ.12፥28።* እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ፣ አራት ባህሪያት አሉት።

አምልኳችን ትክክለኛ ሲሆን እግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ሰዎች ብዙ ጊዜ ፡- «እግዚአብሔር እንደ ... ነው ብዬ ለማሰብ እፈልጋለሁ» ይላሉ።

ከዚያም ሊያመልኩት ስለሚፈልጉት የእግዚአብሔር ዓይነት ይናገራሉ። ነገር ግን የራሳችን የሆነና ለኛ የሚስማማ ወይም በሁሉም ተቀባይነት ያለው የእግ ዚአብሔር ምስል ፈጥረን ልናመልክ አንችልም። እንዲህ ያለው ድርጊት ጣኦት አምልኮ ነው።

አምልኮ ስለ እግዚአብሔር በሚኖረን አስተሳሰብ ላይ ሳይሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ መመሥረት አለበት። ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት እንዲህ አላት:- *«በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመ ጣል፣ አሁንም መጥቶአል፣ አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል»* ዮሐ. 4÷23።

በ«እውነት መስገድ (*ማምለክ*)» ማለት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተ ገለጠው እውነት መሠረት፣ እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ነው።

**በእውነት ስናመልከው እግዚአብሔር ደስ ይለዋል።** ኢየሱስ *«በመንፈስ»* ማምለክ አለባችሁ ሲል፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን፣ *ስለ አንተ* መንፈስ መናገሩ ነበር። በእግዚአብሔር አምሳል የተሠራህና በአካሉ ውስጥ በመንፈስ የምትኖር ነህ። ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ትችል ዘንድ እግዚአብሔር መንፈስህን ቀረፀው። አምልኮ፣ መንፈስህ ለእግዚአብሔር መንፈስ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው።

ኢየሱስ:- *«እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህና ነፍስህ »* ውደድ ሲል፣ አምልኮ እውነተኛና ከልብ መሆን አለበት ማለቱ ነው። ትክክለኛ ቃላትን የመናገር ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ከልብህ የምትናገር መሆንም አለብህ። ከልብ ያልሆነ ምስጋና ምስጋና አይደለም። ዋጋ የሌለውና እግዚአብሔርን መሳደብ ነው።

*እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አምልኮ፣ በጥልቅ ስሜትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ የተመሠረተ ነው። በምናመልክበት ጊዜ ልብ እና አእምሯችንን እንገለገልባቸዋለን።*

በምናመልክበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከቃላቶቻችን ባሻገር የልባችንን ዝንባሌ ነው የሚመለከተው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፣ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል»* 1ሳሙ. 16÷7።

አምልኮ በእግዚአብሔር ደስ የመሰኘት ነገር ስለሆነ፣ ስሜቶችህንም ይጨም ራል። እግዚአብሔር ስሜቶችን የሰጠህ፣ በጥልቅ ስሜት እንድታመልከው ነው። በስሜቶችህ የምትገልጣቸው ነገሮች ግን እውነተኞች እንጂ፣ ማስመ ሰል መሆን የለባቸውም። እግዚአብሔር ግብዝነትን ይጠላል። በአምልኮ ወቅት አስመሳይነትን ወይም ውሸትን አይፈልግም። ታማኝና እውነተኛ ፍቅርህን ነው

የሚፈልገው። ፍጹም ባልሆነ ሁኔታ እግዚአብሔርን ልናመልከው እንችላለን። *ከልብ ባልሆነ፣* ወይም ቅንነት በሌለበት ሁኔታ ግን አንችልም።

እርግጥ ቅንነት ብቻውን በቂ አይደለም፤ ቅን ሆነህ ትሳሳት ይሆናል። ለዚህ ነው መንፈስና እውነት ያስፈለጉት። አምልኮ ትክክልም እውነተኛም መሆን አለበት። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አምልኮ፣ በጥልቅ ስሜትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ የተመሠረተ ነው። በምናመልክበት ጊዜ ልብ እና አእምሮአችንን እንገለገልባቸዋለን።

ዛሬ ብዙ ሰዎች፣ በሙዚቃ የሚደረግን የስሜት መነሣሣት፣ በመንፈስ እንደ መነሣሣት ይቆጥሩታል። ሁለቱ የሚመሳሰሉ ነገሮች አይደሉም። እውነተኛ አምልኮ፣ በሙዚቃ ቃና የሚነሣሣ ሳይሆን፣ መንፈስህ ለእግዚአ ብሔር መንፈስ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ የሚከናወን ነው። እንደውም አንዳንድ ስሜትን የሚኮረኩሩና በራስ አሳብ ላይ ያተኮሩ ዜማዎች፣ ትኩረታችንን ከእግዚአብሔር ላይ በማንሣት ስሜታችን ላይ እንድናነጣጥር ስለሚያደርጉን፣ አምልኮን ያደናቅፋሉ። አምልኮህን ከሚያውኩ ነገሮች ዋነኛው፣ አንተው እራስህ ነህ። ፍላጎትህና ሰዎች ስለ እኔ ምን ያስባሉ የሚለው ጭንቀትህ አምልኮህን ያውካሉ።

ተገቢና እውነተኛ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚገለጥበትን መንገድ በተ መለከተ፣ ክርስቲያኖች የተለያየ አመለካከት አላቸው። ልዩነቶቹ ብዙ ጊዜ የግል ባሕርይንና የልምምድን ልዩነቶች ብቻ ነው የሚያንፀባርቁት። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ የአምልኮ ዓይነቶች ተገልጠዋል። ከነሱም ንስሐ፣ ዝማሬ፣ ጩኸት፣ በአክብሮት መቆም፣ መንበርከክ፣ ጭፈራ፣ የደስታ ድምጽ ማሰማት፣ መመስከር፣ የሙዚቃ መሣሪያ መጫወትና እጃችንን ማንሳት፣ ያዕ. 13÷15፤ መዝ. 7÷17፤ ዕዝ. 3÷11፤ መዝ. 149÷3፤150÷3 ይገኙባቸዋል። ከሁሉ የሚበልጠው አምልኮ፣ እግዚአብሔር በሰጠህ ልምድና ግለ - ባሕርይ ላይ ተመሥርተህ ለእርሱ ያለህን ፍቅር በእውነት የምትገልጥበት ነው።

> *ከሁሉ የሚበልጠው አምልኮ እግዚአብሔር በሰጠህ ግለ-ባሕርይ ላይ ተመሥርተህ ለእርሱ ያለህን ፍቅር፣ በእውነት የምትገልጥበት ነው።*

ባልንጀራዬ ጌሪ ቶማስ እንዳጤነው፣ ብዙ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ህያው ወዳጅነት ከመመሥረት ይልቅ፣ በማያረካና አሰልቺ በሆነ የአምልኮ ሁኔታ ውስጥ ተዘፍቀዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ እግዚአብሔር እነሱን በልዩ አካኋን ላዘጋጀበት ሁኔታ በማይስማማ ፅሞና ወይም አምልኮ ሁኔታ ውስጥ ለመግባት እራሳቸውን ስለሚያስገድዱት

ነው፡፡

ጌሪ ፡- *እግዚአብሔር ሆን ብሎ የተለያየን አድርጎ ከፈጠረን፣ ለምንድነው ሰዎች ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔርን እንዲወዱት የሚጠበቅባቸው?* ብሏል፡፡ ክርስቲያናዊ ሥነ- ጽሑፎችን ካነበበና ለበሳል ክርስቲያኖች ቃለ መጠይቅ ካደረገላቸው በኋላ ጌሪ የደረሰበት ነገር፣ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ግንኙነትን ለመፍጠር ላለፉት 2000 ዓመታት በተለያዩ መንገዶች የተጓዙ መሆኑን ነው፡፡ ከቤት ውጭ በመሆን፣ በማጥናት፣ በመዘመር፣ በማንበብ፣ በማሽብሸብ፣ ህብረት በመፍጠር፣ እና በሌሎች ብዙ ክንዋኔዎች ውስጥ በመሳተፍ ... ይህንኑ ፍላጎታቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ጌሪ፣ *ቅዱስ መንገዶች* በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ከሚቀርቡባቸው መንገዶች ዘጠኙን ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ገልጿቸዋል፡፡ *የተፈጥሮ አድናቂዎች፣* ከቤት ውጭ ሆነው፣ ተፈጥሮን በሚያደንቁበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለመውደድ መንፈሳቸው ይበልጥ ይነሣሣል፡፡ *ስሜተኞች፣* እግዚአብሔርን በስሜታቸው ስለሚወዱት፣ ጆሯቸውን ብቻ ሳይሆን ማየትን፣ ማጣጣምን፣ ማሽተትንና መዳሰስን የሚያካትቱ አምልኮዎችን ይወዷቸዋል፡፡ *ባሕል አጥባቂዎች* ደግሞ፣ በሃይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ አምልኮዎች፣ ስዕሎች (ምልክቶች) እና በማይለወጡ አደረጃጀቶች ዓማካይነት ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ፡፡ *ባህታውያን፣* በብቸኝነት ሕይወትና አኗኗር ፍቅራቸውን ለእግዚአብሔር ቢገልጡለት ይመርጣሉ፡፡ *ለውጥ ፈላጊዎች፣* ክፉ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን በመጋፈጥ፣ ከፍትህ አዛቢዎች ጋር መታገል፣ እና ዓለምን ምቹ የመኖሪያ ሥፍራ ለማድረግ በመሥራት ዓማካይነት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ይገልጣሉ፡፡ *በጎ አድራጊዎች፣* ሌሎችን በመውደድና የሚያስፈልጋቸውን በማድረግ ሥራቸው ዓማካይነት እግዚአብሔርን ይወዱታል፡፡ *በስሜት ተደሳቾች፣* ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር የሚገልጡት በመፈንጠዝ ነው፡፡ *የጽሞና ሰዎች፣* በማምለክ እግዚአብሔርን ያከብሩታል፡፡ *ምሁራን፣* በአእምሯቸው በማጥናት እግዚአብሔርን ይወዱታል፡፡



እግዚአብሔርን ማምለክንና ከእርሱ ጋር መወዳጀትን በተመለከተ፣ ለሁሉም ተስማሚ የሆነ አንድ ዓይነት አቀራረብ የለም፡፡ አንድ ነገር እርግጥ ነው፡- ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ባቀደህ መሠረት እንጂ፣ ሌላ ሰው ለመሆን በመሞከር እሱን ልታከብረው አትችልም፡፡ እግዚአብሔር እራስህን እንድትሆን የሚፈልግ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጥ እንዲህ ይላል፡- *«በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፣ አሁንም መጥቶ*

*ለዐ፣ ለብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል» ዮሐ. 4÷23።*

አምልኳችን ከልብ ሲሆን እግዚአብሔር ይደሰታል ። «*እግዚአብሔርን በፍ ጹም ሰሳብህ ውደድ*»፣ የሚለው የኢየሱስ ትእዛዝ አዲስ ኪዳን ውስጥ አራት ጊዜ ተደጋግሟል። ባልተሰበሰበ አሳብ የሚደረግ ዝማሬ፣ ካንገት በላይ የሆነ አሰልቺ ጸሎት ወይም በግዴለሽነት የታጀበ እና የምንለው ነገር ሲጠፋን የምንናገረው የ«ጌታ ይመስገን» ቃለ አጋኖ እግዚአብሔርን አያስደስተውም። በተሰበሰበ አእምሮ የማይከናወን አምልኮ ትርጉም አልባ ነው። በአምልኮ ጊዜ አእምሮህን መሰብሰብ አለብህ።

ባልተሰበሰበ አእምሮ የሚያመልኩትን ኢየሱስ፦ «*በከንቱ ለትድገሙ*» ማቴ. 6÷7 ይላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አነጋገሮች እንኳን ብዙ ጊዜ ከመደጋገማቸው የተነሣ አሰልቺ ይሆኑና ስለ ትርጉማቸው ማሰባችንን እንተወዋለን። በአምልኮ ጊዜ፣ እግዚአብሔርን በአዳዲስ ቃላትና ሁኔታ በማምለክ ፈንታ፣ በተደጋገሙ ድርጊቶችና ቃላት ማምለኩ በጣም ይቀላል። ለዚህ ነው የተለያዩ

**አሥራ ሶስተኛ ቀን**
**እግዚአብሔርን የሚያስደስት አምልኮ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችንና አገላለጦችን እንድታነብ የማበረታታህ። ይህን ማድረጉ፣ የአምልኮ አቀራረብህን ያሰፋልሃል።

*ሃሌሉያ፣ ለመሰግንሃለሁ* ወይም *አሜን* የሚሉ ቃላትን ሳትጠቀም እግዚአብሔርን ለማመስገን ሞክር። «ልናመሰግንህ እንፈልጋለን»። *በማለት ፈንታ፣ ልናደንቅህ፣ ልናከብርህ፣ ልንወድስህ፣ ልንፈራህ፣ የመሳሰሉና ያልተደጋገሙ* ተመሳሳይ ቃላትን መዝግብና ተጠቀምባቸው።

ደግሞም *ገልፕ* ሁን። አንድ ሰው መጥቶ አሥር ጊዜ «አመሰግንሃለሁ» ቢልህ፣ *ለምን? ብለህ ታስብ ይሆናል።* ከሀያ አጠቃላይ አነጋገር ይልቅ ሁለት ግልጥ ምስጋና ብትቀበል ይሻልሃል። እግዚአብሔርም እንዲሁ ነው።

ሌላው አሳብ፣ ልዩ ልዩዎቹን የእግዚአብሔር ስሞች በዝርዝር ይዞ በነሱ ላይ ማትኮር ነው። የእግዚአብሔር ስሞች በአንድ ነገር ላይ ብቻ ያተኮሩ አይደሉም። ስለ ባህርይው የተለያዩ ክፍሎች ይነግሩናል። እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳን ውስጥ ቀስ በቀስ አዳዲስ ስሞቹን በማሳወቅ ነው እራሱን ለእስራኤል የገለጠው። እናም ስሙን እናከብር ዘንድ ያዘናል።

የአምልኮ ስብሰባችንም በማስተዋል እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል። ጳውሎስ 1ቆሮ. 14 ውስጥ ሙሉውን ምዕራፍ ስለዚህ ጉዳይ በመስጠት በማጠቃለያው ላይ «*ነገር ግን ሁሉም በአገባብና በሥርዓት ይሁን*» 1ቆሮ. 14÷40 ብሏል።

ከዚህ ጋር በተዛመደ ሁኔታ፣ ያላመኑ ሰዎች በመካከላችን በሚኖሩበት ጊዜ፣ የአምልኮ ሥርዓታችን እነሱ የሚረዱት ሆኖ እንዲከናወን እግዚአብሔር በጥብቅ ይፈልጋል:: ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- *«እንዲህማ ካልሆነ፥ እግዚአብሔ ርን በመንፈስ በምታመሰግንበት ጊዜ፥ ስነገሩ እንግዳ የሆነ ሰው፥ አንተ የምትናገረውን ካልተረዳ፥ እንዴት አድርጎ ለምስጋናህ «አሜን» ሊል ይችላል? አንተ በሚገባ ታመሰ ግን ይሆናል፤ ሌላው ግን አይታነጽበትም»* 1ቆሮ. 14፥16-17:: በአምልኳችሁ ጊዜ የማያምኑ ሰዎች ሲጎበኙዋችሁ፣ እነርሱን በጥንቃቄ መያዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝ ነው:: ይህን ትእዛዝ ችላ ማለት፣ አለመታዘዝና ፍቅር አልባ መሆን ነው:: ለዚህ ጉዳይ ሙሉ ማብራሪያ ለማግኘት (*Purpose Driven Church*) በሚለው ሌላ መጽሐፌ ውስጥ:- «አምልኮ ምስክርነት ሊሆን ይችላል» የሚለውን ምዕ ራፍ ተመልከት::

**አምልኳችን በተግባር ሲሆን እግዚአብሔር ደስ ይለዋል::** መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋ ዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለአእምሮ የምታቀርቡት አምልኳችሁ ነው»* ሮሜ 12፥1:: ለምንድነው እግዚአብ ሔር ሰውነትህን የሚፈልገው? ለምንድነው «መንፈስህን አቅርብ» የማይለው? ምክንያቱም በዚህች ዓለም ያለ ሰውነትህ ምንም ልታደርግ አትችልም:: በዘላለም ሕይወት አዲስ፣ የተሻሻለና ከፍ ያለ አካል ትቀበላለህ:: በምድር ባለህበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር «ያለህን ስጠኝ» ይልሃል፤ አምልኮ ተግባራዊ እንዲሆንለት ይፈልጋል::

ሰዎች:- «በዛሬው ምሽት ስብሰባ ላይ ልገኝ አልችልም፤ ቢሆንም *በመንፈስ* ከእናንተ ጋር እሆናለሁ» ይላሉ:: ይህ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ? ምንም ማለት አይደለም:: ዋጋ የሌለው ንግግር ነው:: በምድር ላይ እስካለህ መንፈስህ ሊኖር የሚችለው አንተ ባለህበት ሥፍራ ነው:: ሰውነትህ እዚያ ከሌለ፣ አንተም እዚያ አይደለህም::

በአምልኮ ወቅት፣ «ሰውነታችንን ሕያው መስዋዕት አድርገን እንድናቀርብ» ይጠበቅብናል:: «መስዋዕት » የሚለውን ጽንሰ አሳብ በተለምዶ ከአንድ ከሞተ ነገር ጋር እናዛምደዋለን:: እግዚአብሔር ግን ሕያው መስዋዕት እንድትሆን ይፈልጋል:: ለእርሱ *እንድትኖርለትም* ይፈልጋል:: ይሁን እንጂ፣ ሕያው መስዋ ዕት ከመሰዊያው ላይ ተንሸራትቶ የመውረድ ችግር አለበት፤ እኛም ብዙ ጊዜ እንዲህ እናደርጋለን:: እሁድ ዕለት «ክርስቲያን ወታደር ሆይ! ወደፊት ተጓዝ» እያልን እንዘምርና፣ ሰኞ ደግሞ ኮብላዩን ወታደር ሆነን እንገኛለን::

በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ እግዚአብሔር በብዙዎቹ የአምልኮ መሥዋዕቶች

ተደስቷል። ምክንያቱም፣ መሥዋዕቶቹ ክርስ ቶስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ የሚከፍለውን መሥዋዕት ቀድመው ያመለክቱ ስለ ነበር። አሁን እግዚአብሔር በብዙዎቹ የአምልኮ መሥዋዕቶች ማለት፣ ምስጋና፣ ውዳሴ፣ ትህትና፣ ንስሃ፣ የገንዘብ ስጦታ፣ ጸሎት፣ ሌሎችን ማገልገል፣ ያለንን ለተቸገሩ ማካፈል በመሳሰሉት ደስ ይለዋል፤ መዝ. 50+14፤ ዕብ. 13+15፤ መዝ. 51+17፤ 54+6፤ ፊልጵ. 4+18፤ መዝ. 141+2፤ ዕብ. 13+16፤ ማር. 12+33፤ ሮሜ 12+1።

***እውነተኛ አምልኮ፣ መሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል ነው።***

እውነተኛ አምልኮ ዋጋ ያስከፍላል። ዳዊት ይህን ተገንዝቦ እንዲህ አለ፡- «*ለአምላኬም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ያለ ዋጋ አላቀርብም*» 2ሳሙ. 24+24።

አምልኮ ከሚያስከፍለን ዋጋ አንዱ፣ እራስ ወዳድነታችንን ነው። እራስህንና እግዚአብሔርን በአንድ ጊዜ ከፍ ከፍ ለማድረግ አትችልም። በሌሎች ለመታየት ወይም እራስህን ለማስደሰት ስትል ልታመልከው አትችልም። በመሆኑም የአምልኮ ትኩረትህን ከራስህ ላይ ማንሳት አለብህ።

ኢየሱስ፡- «*እግዚአብሔርን በፍፁም ኃይልህ ውደድ*» ባለ ጊዜ፣ አምልኮ ጥረትና ኃይል የሚያስፈልገው ነገር መሆኑን አስገንዝቧል። ድርጊቱ ሁል ጊዜ የሚሳካና ምቹ አይደለም። አምልኮ አንዳንድ ጊዜ የልብ ፈቃድ ድርጊት ነው፤ በፍቃደኝነት የሚከፈል መሥዋዕትነት።

የማመስገን ፍላጎት ባይኖርህ እንኳን እግዚአብሔርን ስታሞግሰው፣ ደክመህ ሳለ ልታመልከው ከመኝታህ ስትነሣ፣ ወይም ድክም ብሎህ ሳለ ሌሎችን ስት ረዳ፣ ለእግዚአብሔር የአምልኮ መሥዋዕት በማቅረብ ላይ ነህ።

ኢንግላንድ ውስጥ የአምልኮ መሪ የሆነውና ማት ሬድማን የተባለ ሰው፣ የቤተክርስቲያኑ መጋቢ ስለ እውነተኛ አምልኮ ለቤተክርስቲያኑ ያስተማረበትን መንገድ እንደሚከተለው ገልጦታል። መጋቢው አምልኮ ከሙዚቃ የሚበልጥ መሆኑን ለማሳየት፣ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ሌላ የአምልኮ መንገድ እንዲማሩ በማድረግ ዝማሬዎችን ሁሉ አገደ። የትምህርቱ ጊዜ ሲያበቃ መጋቢው ተወዳጅ የሆነውንና «የአምልኮ ልብ» የሚል ርዕስ ያለውን መዝሙር ጻፈ።

> ከዝማሬ የሚበልጥ መጣሁ ይገፍልህ፣
> ዝማሬን ብቻ ስላልሆነ ከኔ የጠየቅህ።
> ከሚታዩ ነገሮች ይልቅ ጠልቀህ
> ልቤን በመመርመር ላይ ነህ

አሥራ ሦስተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** እግዚአብሔር ሁለንተናዬን ይፈልጋል።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና፣ በፍጹም ኃይልህ፣ ውደድ»* *ማር. 12÷30።*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** እግዚአብሔርን አሁን ይበልጥ የሚያስደስ ተው የቱ ነው? ከሕዝብ ጋር የማደርገው ወይስ የግል አምልኮዬ? ስለዚህ ነገር ምን ላድርግ?

# እግዚአብሔር የራቀ ሲመስል

*ፊቱን ከያዕቆብ ቤት የሸሸገውን እግዚአብሔርን እጠብቃለሁ፣ እርሱንም ተስፋ አደርጋለሁ።*

*ኢሳ. 8፥7*

ምንም ይሰማህ ምን፣ እግዚአብሔር እውን ነው።

ነገሮች በመልካም ክንውን ላይ ባሉ ጊዜ፣ ማለት እግዚአብሔር ምግብ፣ ጓደኞች፣ ቤተሰብ፣ ጤና እና ደስ የሚሉ ሁኔታዎችን ሲሰጥህ እሱን ማምለኩ ቀላል ነው። ነገር ግን፣ ሁኔታዎች ሁል ጊዜ ደስ የሚሉ አይደሉም። እንዲህ ባለው ጊዜ እግዚአብሔርን የምታመልከው እንዴት ነው? አንድ ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ያህል የራቀ ሲመስልህስ ምን ታደርጋለህ?

የአምልኮ ጥልቀት መለኪያዎች፣ በህመም ጊዜ እግዚአብሔርን ማክበር፣ በመከራ ጊዜ ማመስገን፣ በፈተና ወቅት በእርሱ መታመን፣ በስቃይ ጊዜ ራስን ለእርሱ ማስረከብ፣ እና የራቀ በሚመስልበት ጊዜ እሱን መውደድ ናቸው።

ወዳጅነት ብዙ ጊዜ በመለየትና በዝምታ ይፈተናል። ሰው በአካል በመራራቅ ወይም ለመነጋገር ባለመቻል ይለያያል። ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖርህ ወዳጅነት፣ አብዛኛውን ጊዜ ወደ እርሱ የቀረብህ መስሎ አይሰማህም። ፊሊፕ ያንሲ የተባለ የሥነ-መለኮት ጸሐፊ እንዲህ ብሏል፡- «በማንኛውም ግንኙነት የመቀራረብና የመራራቅ ጊዜ አለ። ከእግዚአብ

ሔር ጋር በሚደረግ ግንኙነትም፣ የቱንም ያህል ቁርኝት ቢኖር፣ መቀራረብና መራራቁ ይፈራረቃል።» አምልኮ አስቸጋሪ የሚሆነው እንዲህ ባለ ጊዜ ነው።

እግዚአብሔር፣ ከእርሱ ጋር ያለህን ወዳጅነት ለማሳደግ ሲል፣ የተወህና የረሳህ በሚመስል ጊዜ ዓማካይነት ወዳጅነታችሁን ይፈትነዋል። አንድ ሚሊዮን ኪሎ ሜትር የራቀህ ይመስልሃል። ጆን ኦፍ ዘ ክሮስ የተባለው ሰው፣ የመንፈሳዊ ድርቀት፣ የጥርጣሬ እና የመራራቅ ስሜት የሚፈጠርባቸውን እነዚህን ቀናት፣ «ጭለማዎቹ የነፍስ ሌሊቶች» ብሏቸዋል። ሄነሪ ኖውን የተባለ ሰው ደግሞ፣ «ያለመገኘት አገልግሎት»፤ ኤ. ደብልዩ. ቶዘር የተባሉት፡- «የሌሊቱ አገልግሎት» ፣ ሌሎች ደግሞ ፡- «የልብ ክረምት» ብለውታል።

ከኢየሱስ ቀጥሎ ዳዊት ከማንም ይልቅ የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ ሳይሆን አይቀርም። እግዚአብሔር ፡- «እንደ ልቤ የሆነ ሰው » 1ሳሙ. 13÷14፤ የሐዋ. 13÷22 በማለት በደስታ ጠርቶታል። ዳዊት ግን እግዚአብሔር እንኑ ያልተገኘ በሚመስለው ጊዜ ሁሉ እንዲህ በማለት በተደጋጋሚ ቅሬታውን ገልጧል፡- *«እግዚአብሔር ሆይ ለምን እንደዚህ ርቀህ ቆምህ? በመከራ ጊዜስ ለምን ድምፅህን አጠፋህ? »* መዝ. 10÷1። *«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? እኔን ለማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ»* መዝ. 22÷1። «ለምን ተውኸኝ» መዝ. 43÷2።

እግዚአብሔር ዳዊትን አልተወውም፤ አንተንም አይተውህም። እንዲህ በማለት በተደጋጋሚ ተስፋ ሰጥቶሃል፡- *«አይለይህም አይተውህም»* ዘዳ. 31÷8።

**አሥራ አራተኛ ቀን**
**እግዚአብሔር**
**የራቀ**
**ሲመስል**

በተጨማሪም፣ መዝ. 36÷28፤ ዮሐ. 14÷16-18 ፤ ዕብ. 13÷5። ነገር ግን፡- «ሁል ጊዜ ህልውናዬ *ይሰማሃል»* በማለት እግዚአብሔር ቃል *አልገባም*። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ፊቱን ከእኛ የሚሰውር መሆኑን ያምናል ኢሳ. 45÷15። በሕይወትህ የሚያከናውነውን ሥራ አቋርጦ በድንገት የሚጠፋ የሚመስልባቸው ጊዜዎች አሉ።

ፍሎይድ ማክለንግ የተባለ ሰው እንዲህ ያለውን ጊዜ ሲገልጠው፡- «አንድ ቀን ማለዳ ከእንቅልፍህ በምትነቃበት ጊዜ፣ መንፈሳዊ ስሜቶችህ ሁሉ ትተውህ እንደጠፉ ትረዳለህ። ትጸልያለህ፣ ምንም አይሆንም። ዲያብሎስን ትገስጻለህ፣ ድርጊትህ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ነገሮችን ታከናውናለህ ... ትዝ የሚሉህን ኃጢአቶች ሁሉ ትናዘዛለህ፤ የምታውቃቸውን ሰዎች ሁሉ እየዞርክ ይቅርታ ትጠይቃቸዋለህ። ትጾማለህ ... አሁንም ምንም የሚሆን ነገር አይኖርም። ይህ መንፈሳዊ ጭጋግ እስከ መቼ ነው የሚቆየው? የሚለው ነገር ያሳስብሃል። ለቀናት? ለሳምንት? ለወራት?... ያልፍ ይሆን?

ጸሎትህ ከጣራ ጋር እየተላተመ የሚመለስ መስሎ ይሰማሃል:: ምን ነካኝ? እያልክ በተስፋ መቁረጥ ታለቅሳለህ::»

እውነቱን ለመናገር፣ አንተ ምንም አላጠፋህም! ይህ ሁኔታ የተለመደና ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ወዳጅነት መፈተኛና ማሳደጊያ ሂደት ነው:: ማንኛውም ክርስቲያን ቢያንስ አንዴ፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን በተደጋጋሚ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ያልፋል:: ሁኔታው አስቸጋሪና ግራ የሚያጋባ ቢሆንም፣ ለእምነትህ ማደግ ፍጹም አስፈላጊ ነው:: በሕይወቱ የእግዚአብሔር

> *እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ፊቱን ከእኛ የሚሰውር መሆኑን ያምናል*

ሕልውና የሌለው መሆኑ በተሰማው ጊዜ፣ ይህን ማወቁ ለኢዮብ ተስፋ ሆኖ ለታል:: ይህንኑ እንዲህ በማለት ገለጠው:- «*ዳሩ ግን ወደ ምሥራቅብሄድ በዚያ የለም፤ ወደ ምዕራብም ብሄድ እርሱን አላገኘውም፤ በሰሜን እየሠራ ሳለ አላየውም፤ ወደ ደቡብ በሚዞርበት ጊዜ ደብዛው አይገኝም*» ኢዮብ 23÷8-10::

እግዚአብሔር የራቀ በሚመስልህ ጊዜ፣ ባንተ የተቆጣ ወይም በኃጢአት ምክንያት የሚቀጣህ መስሎ ይሰማህ ይሆናል:: እርግጥ ኃጢአት ከእግዚአብ ሔር ጋር ያለንን የቅርብ ግንኙነት ያቋርጠዋል:: ባለመታዘዝ፣ ከሌሎች ጋር በምናደርገው ግጭት ወይም ፀብ፣ በሥራ ምክንያት፣ ከዓለም ጋር በመወዳ ጀትና በሌሎች ምክንያቶች የእግዚአብሔርን መንፈስ እናሳዝንና ከእርሱ ጋር ያለንን አንድነት እናጠፋው ይሆናል፣ መዝ. 51፤ ኤፌ. 4÷29-30፤ 1ተሰ. 5÷19፤ ኤር. 2÷32፤ 1ቆሮ. 8÷12፤ ያዕ. 4÷4::

ይሁን እንጂ ይህ በእግዚአብሔር የተተውን ወይም ከእርሱ የራቅን ሆኖ የመሰማት ጉዳይ ከኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: ሁላችንም የምን ጋፈጠው የእምነት መፈተኛ ነው:: የእግዚአብሔር ሕልውና በማይሰማህና በሕይወትህ በመሥራት ላይ ያለ የመሆኑ ግልጥ ማረጋገጫ በማይኖርህ ጊዜ፣ እግዚአብሔርን መውደድህን፣ ማመንህን፣ መታዘዝህንና ማምለክህን ትቀጥ ላለህ?

ክርስቲያኖች ዛሬ በአምልኮ ውስጥ የሚፈጽሙት በጣም የተለመደ ስሕ ተት፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ አንድ ዓይነት ልምምድ መፈለጋቸው ነው:: አንድ ዓይነት ስሜት ይፈልጋሉ፤ ከሆነላቸው፣ ስለ ማምለካቸው እርግጠኞች ይሆናሉ:: ይህ ስሕተት ነው! ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በእነርሱ እንዳንደገፍ ስሜቶቻችንን ያስወግዳቸዋል:: ስሜትን መሻት፣ ከክርስቶስ ጋር የመቀራረብ ስሜት ቢሆንም እንኳን፣ አምልኮ አይደለም::

አዲስ ክርስቲያን በሆንክ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ብዙ የማረጋገጫ ስሜቶችን ይሰጥሃል፤ በጣም ጩቅላና ግለ ተኮር ጸሎቶችህንም ይመልሳል። ይህን የሚያደርገው፣ ሕያውነቱን ታውቅ ዘንድ ነው። በእምነት እያደግክ ስትሄድ ግን እነዚህን ጥገኝነቶች ያቋርጣቸዋል።

*ክርስቲያኖች ዛሬ በአምልኮ ውስጥ የሚፈጽሙት በጣም የተለመደ ስሕተት፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ አንድ ዓይነት ልምምድ መፈለጋቸው ነው።*

የእግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ መገኘትና፣ የህልውናው መገለጥ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንደኛው የተረጋገጠ እውነት ሲሆን፣ ሌላው ብዙ ጊዜ ስሜት ነው። መገኘቱ በማይሰማህ ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር በቅርብህ አለ። መገኘቱ ደግሞ በስሜት ሊገለጥ የማይቻልና እጅግ ታላቅ ነው።

አዎ፣ መገኘቱ እንዲሰማህ ይፈልጋል፤ ነገር ግን በስሜት ከምታውቀው ይልቅ በእርሱ *ማመንህን* ነው ይበልጥ የሚሻው። እግዚአብሔርን የሚያስደስተው የስሜቶች ጉዳይ ሳይሆን፣ እምነትህ ነው።

እምነትህን በጣም እንዲያድግ የሚያደርጉት ሁኔታዎች፣ ሕይወትህ ሲመሰቃቀልና እግዚአብሔርን ፍፁም ልታገኘው በማትችልበት ወቅት ውስጥ ያለህ በሚመስልህ ጊዜ ያሉት ናቸው። ኢዮብ ይህን የመሰለ ሁኔታ ደርሶበታል። ቤተሰቡን፣ ሥራውን፣ ጤናውንና *ያለውን ነገር ሁሉ* በአንድ ቀን ውስጥ አጣ። ከሁሉ ተስፋ የሚያስቆርጠው ነገር ደግሞ፣ ሰላሳ ሰባት ምዕራፎች ሙሉ እግዚአብሔር ዝም ማለቱ ነው!

የማትረዳው ነገር በሕይወትህ እየተከናወነና እግዚአብሔርም ዝም እያለህ እንዴት ታመሰግነዋለህ? ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ሳትችል፣ ከእርሱ ጋር ተጣብቀህ የምትኖረው እንዴት ነው? እንዴት ነው እንባ በሞላባቸው ዓይኖችህ ኢየሱስ ላይ ለማትኮር የምትችለው? ኢዮብ ያደረገውን አድርግ፦ *«ተነሣ መጐናጸፊያውን ቀደደ፣ ራሱንም ተላጨ፣ በምድርም ላይ ተደፍቶ ሰገደ፤ እንዲህም አለ፦ ራቁቴን ከእናቴ ማህጸን ወጣሁ፣ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን»* ኢዮብ 1፥20-21።

**የሚሰማህን በትክክል ለእግዚአብሔር ንገረው።** ልብህን ለእግዚአብሔር አፍስስ። የሚሰማህን ስሜት ሁሉ አራግፍ። ኢዮብ ቀጥሎ ያለውን ቃል በተናገረ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነው፦ *«ስለዚህ ከቶ ዝም አልልም፤ በመንፈሴ ጭንቀት እናገራለሁ፤ በነፍሴም ምሬት አጕረመርማለሁ»* ኢዮብ 7፥11። እግዚአብ

ሔር የራቀው በመሰለውም ጊዜ እንዲህ በማለት ጮኸ:- «*እነ ብርቱ ነበርሁ፣ የእግዚአብሔር ወዳጅነት በቶን ይባርክ ነበር*» ኢዮብ 29+4:: እግዚአብሔር፣ ለጥርጣሬህ፣ ለቁጣህ፣ ለፍርሃትህ፣ ለሐዘንህ፣ ለግራ መጋባትህና ለጥያቄዎችህ መፍትሄ አለው::

ተስፋ የለሽ መሆንህን በእግዚአብሔር ፊት መቀበልህ የእምነትህ መገለጫ ሊሆን መቻሉን አውቀሃል? ዳዊት በእግዚአብሔር በመታመንና ተስፋ በመቁረጥ መካከል ሆኖ እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «*እጅግ ተጨንቄአለሁ ባልሁበት ጊዜ እንኳ፣ እምነቴን ጠብቄአለሁ::*» መዝ. 116÷10 :: እምነቴን ጠብቄአለሁ፤ እጅግ ተጨንቄአለሁ፣ የሚለው አነጋገር እርስ በርሱ የሚቃረን ይመስላል:: የዳዊት ግልጥነት የሚያስገነዝበው፣ ጥልቅ እምነትን ነው:: አንደኛ በእግዚአብሔር አመነ:: ሁለተኛ እግዚአብሔር ጸሎቱን እንደሚሰማለት እርግጠኛ ሆነ:: ሦስተኛ የተሰማውን እንዲናገር እግዚአብሔር እንደሚፈቅድለትና በማንኛውም ሁኔታ የሚወደው መሆኑን አመነ::

በእግዚአብሔር ማንነት- በማይለወጥ ባሕርይው ላይ አትኩር:: ሁኔታዎች ምንም ይሁኑ ምን፣ አንተም ምንም ተሰማህ ምን፣ በእግዚአብሔር የማይለወጥ ባህርይ ላይ ተጣበቅ:: እግዚአብሔር መልካም ነው፣ ይወደኛል፣ ከኔ ጋር አለ፣ ያለሁበትን ሁኔታ ያውቃል፣ ይጠነቀቅልኛል፣ ለሕይወቴ መልካም ዕቅድ አለው፤ እያልክ ስለ እግዚአብሔር የምታውቀውን ዘላለማዊ እውነት ለአንተነትህ አስታውሰው:: ቪ. ሬይመንድ ኤድማን የተባሉ ጸሐፊ እንዲህ ብለዋል:- «እግዚአብሔር በብርሃን የነገረህን ነገር በጭለማ አትጠራጠረው::»

ሕይወቱ እንዳልነበረ በሆነና እግዚአብሔርም ዝም ባለው ጊዜ፣ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንባቸው ነገሮች ነበሩት:-

- መልካምና አፍቃሪ መሆኑ ኢዮብ 10÷12::
- ኃያል መሆኑ ኢዮብ 42÷2፤ 37÷5 ፣ 23::
- የሕይወቱን ዝርዝር ነገሮች ሁሉ የሚመለከት መሆኑ ኢዮብ 23+10::
- ማንኛውንም ነገር የሚቆጣጠር መሆኑ ኢዮብ 34+13::
- ለሕይወቱ እቅድ ያለው መሆኑ ኢዮብ 23+14::
- የሚያድነው መሆኑ ኢዮብ 19÷25::

እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚጠብቅ መሆኑን እመን:: መንፈሳዊ ድርቀት በሚሰማህ ጊዜ፣ በስሜትህ ሳይሆን፣ ትዕግሥት በተሞላበት ሁኔታ



በእግዚአብሔር ተስፋ ተማመን:: ከፍ ወዳለ የእምነት ደረጃ እያሸጋገረህ መሆኑንም ተረዳ:: በስሜት ላይ የተመሠረተ ወዳጅነት ሥር የለውም::

ስለዚህ በችግር አትቸገር:: ሁኔታዎች የእግዚአብሔርን ባሕርይ አይቀይሩትም:: የእግዚአብሔር ጸጋ አሁንም በሙሉ ብርታቱ አለ:: ልብ ባትለውም እንኳን አሁንም ለአንተ ነው:: ኢዮብ፣ በማይመቹ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ እንኳን በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመጽናት እንዲህ አለ:- «*ከአፉ ከወጣው ቃል አልራቅሁም፣ የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዣለሁ*» ኢዮብ 23+12::

ሁኔታዎች ትርጉም የለሽ በሆኑ ጊዜ ኢዮብ በታማኝነት እንዲጸና ያደረገው፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለው እምነት ነው:: ስቃይ ውስጥ ቢሆንም እምነቱ ጠንካራ በመሆኑ:- «*ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ*» ኢዮብ 13+15 ብሏል::

እግዚአብሔር የተወህ መስሎ ቢሰማህም እንኳን፣ በእርሱ ማመንህን ከቀጠልክ፣ እጅግ ጥልቅ በሆነ መንገድ ታመልከዋለህ::

እግዚአብሔር ያደረገልህን አስታውስ:: እግዚአብሔር ሌላ ምንም ተጨማሪ ነገር ባያደርግልህም እንኳን፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለአንተ ከፈፀመው ሥራ የተነሣ፣ በቀሪ ሕይወትህ ሁል ጊዜ ልታመልከው ይገባል:: *የእግዚአብሔር ልጅ ስለ አንተ ሞቷል::* የአምልኮህ ትልቁ ምክንያት ይህ ነው::

የሚያሳዝነው ነገር፣ እግዚአብሔር በኛ ምትክ ያደረገውን የአስጨናቂ መስዋዕት ዝርዝሮች መርሳታችን ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ፣ ከመስቀሉ በፊት እንኳን፣ ልብሱ ተገፎ እርቃኑን ሆኗል፣ መልኩ እስኪጠፋ ድረስ ተደብድቧል፣ ተገርፏል፣ ተዋርዷል፣ ተቀልዶበታል፣ የሾህ አክሊል ደፍቷል፣ በንቀት ተተፍቶበታል::

*እግዚአብሔር የተወሀ መስሎ ቢሰማህም እንኳን፣ በእርሱ ማመንህን ከቀጠልክ፣ እጅግ ጥልቅ በሆነ መንገድ ታመልከዋለህ::*

በጨካኞች ውርደትና መሳለቂያ ደርሶበታል፤ ለእንስሳት የተገባ ያህል ክብር እንኳን አላገኘም:: ደሙ በመፍሰሱ ምክንያት ህሊናውን ለመሳት ጥቂት ሲቀረው፣ ለሸክም የማይመቸውን ግዙፍ መስቀል ተሸክሞ ተራራ እንዲወጣ ተገዷል፤ መስቀል ላይ በምስማር ተቸንክሯል፣ በዝግታና በስቃይ እንዲሞት

ተደርጓል:: ደሙ ከውስጡ በመሟጠጥ ላይ እያለ፣ በዙሪያው ያውካኩ የነበሩ ሰዎች አምላክ ነኝ ማለቱን በመገዳደር በስቃዩ አሾፉበት::

በዚህ ሁኔታ የሰዎችን ሁሉ ኃጢአትና በደል የራሱ ባደረገበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ያን አስከፊ ትእይንት ላለመመልከት ፊቱን ወደ ሌላ መለሰ:: ያኔ ኢየሱስ ከስቃዩ ክብደት የተነሣ «አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውከኝ?» አለ:: እንዲያ ካለው የስቃይ ሞት እራሱን ሊያድን ይችል ነበር:: ያን ቢያደርግ ኑሮ ግን ሊያድንህ አይችልም::

ያኔ የነበረውን አስከፊ ጭለማ ቃላት ሊገልጡት አይችሉም:: ለምንድነው እግዚአብሔር እንዲያ ያለውን በጣር የተሞላ የግፍ ሥራ የፈቀደውና በዝምታ የተመለከተው? ዘላለምን በሲዖል እንዳታሳልፍ አንተን ለማዳንና የዘላለም የክብሩ ተካፋይ እንድትሆን ነው! መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኃጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው*» 2ቆሮ. 5+21::

አንተ የሁሉም ነገር ባለቤት ትሆን ዘንድ፣ ኢየሱስ ሁሉን ነገር ተወ:: ለዘላለም ትኖር ዘንድ ሞተ:: *ይህ ብቻ* የሁል ጊዜ ምስጋናና አምልኮህ የሚገባው ነገር ነው:: ከእንግዲህ እግዚአብሔርን የማመስግንበት ነገር ምን አለ ብለህ ልትጠይቅ አይገባም::

አሥራ አራተኛ ቀን


ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገበ ጉዳይ:-** የሚሰማኝ ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔር እውን ነው::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** «*እግዚአብሔር ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም ብሉአልና*» ዕብ. 13+5::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** እግዚአብሔር የራቀኝ በሚመስለኝ ጊዜ፣ እንዴት ነው እርሱ ከኔ ጋር ያለ በመሆኑ እውነት ላይ ለማተኮር የምችለው?

# ዓላማ ቁጥር 2



# የተበጀኸው ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ነው

*እኔ የወይን ተክል ነኝ፣ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።*

ዮሐ. 15÷5

*እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እያንዳንዳችን የሌላው ብልት ነን።*

ሮሜ 12÷5

# 15

# ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተበጅተሃል

*ሁሉ ነገር ለእርሱና በእርሱ የሚኖር እግዚአብሔር ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማምጣት፣ የድነታቸውን መሥራች በመከራ ፍጹም ሊያደርገው የተገባ ነበር።*

*ዕብ. 2፥10*

*የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ ለትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ነን።*

*1ዮሐ. 3፥1*

ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተበጅተን ነበር።

እግዚአብሔር ቤተሰብ ይኖረው ዘንድ ስለሚፈልግ፣ የዚያ አባል ትሆን ዘንድ ነው የፈጠረህ። ከመወለድህ በፊት እግዚአብሔር ለሕይወትህ ካቀደልህ ዓላማዎች ይህ ሁለተኛው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ባጠቃላይ፣ እግዚአብሔር የሚወደውን፣ የሚያከብረውንና ከእርሱ ጋር ለዘላለም የሚነግሠውን ቤተሰብ በመገንባት ላይ መሆኑን ይተርካል። እንዲህ ይላል፦ «*በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደበጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን*» ኤፌ. 1፥5።

እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፣ ለግንኙነቶች ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣቸዋል። በባህርይው ግንኙነት ፈላጊ ስለሆነ፣ እራሱን ከቤተሰባዊ አጠራር ጋር ያዛምዳል - አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በማለት። ሥላሴ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ፍጹም በሆነ ግንኙነታዊ አሠራር ሀብር የተሟላ ምሳሌ ስለሆነ፣ እንደምታውን ልናጠና ይገባል።

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ከራሱ ጋር አፍቅሯዊ በሆነ ግንኙነት ስለኖረ ብቸኛ ሆኖ አያውቅም። ቤተሰብ የግድ አላስፈለገውም ነበር። ነገር ግን እኛን ለመፍጠር፣ ወደ ቤተሰቡ ሊያስገባንና ካለው ሁሉ ሊያካፍለን ወደ ደና አንድ እቅድ ነደፈ። ይህ ድርጊቱ እግዚአብሔርን በጣም ያስደስተ

ዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«የፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን»* ያዕ. 1÷18:::

በክርስቶስ ስናምን፣ እግዚአብሔር አባታችን ይሆናል፤ እኛም ልጆቹ እንሆ ናለን:: ሌሎቹ አማኞች ወንድሞችና እህቶቻችን፣ ቤተክርስቲያን ደግሞ መንፈሳዊ ቤተሰባችን ትሆናለች:: የእግዚአብሔር ቤተሰብ፣ ያለፉትን፣ አሁን ያሉትንና የወደፊቶቹን አማኞች ሁሉ ይጨምራል::

ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር በእግዚአብሔር ነው *የተፈጠረው፤* ሁሉም ግን የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም:: ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት የመቀላቀ ያው ብቸኛ መንገድ፣ ወደ ቤተሰቡ ዳግም መወለድ ነው:: በቀዳማይ ልደትህ ዓማካይነት የሰብዓዊው ቤተሰብ አባል ሆነሃል:: የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የምትሆነው ግን፣ በዳግም ልደት አማካይነት ነው:: እግዚአብሔር:- *«ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት፣ እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን»* 1ጴጥ. 1÷3-4::

ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት የሚቀርበው ጥሪ ወይም ግብዣ፣ አጠቃላይ ነው፣ ማር. 8÷34፤ የሐዋ. 2÷21፤ ሮሜ 10÷3፤ 2ጴጥ. 3÷9:: አንድ ቅድመ ሁኔታ ግን አለበት፤ በኢየሱስ ማመን:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ»* ገላ. 3÷26::

መንፈሳዊው ቤተሰብህ ዘላለማዊ ስለሆነ፣ ከሥጋዊው ቤተሰብህ ይልቃል:: ምድራዊዎቹ ቤተሰቦቻችን ከእግዚአብሔር የተለገሱን ድንቅ ስጦታዎች



ናቸው:: ነገር ግን ጊዜያዊና ተሰባሪ፣ እንዲሁም በፍቺ ምክንያት፣ በቦታ ርቀት፣ በእርጅና፣ እና በማይቀረው ሞት ሳቢያ ይበታተናሉ:: በአንጻሩ ግን፣ መንፈሳዊው ቤተሰባችን፣ ማለት ከሌሎች አማኞች ጋር ያለን ግንኙነት፣ ለዘላለም ይኖራል:: ከሥጋ ዝምድና ይልቅ፣ የጠነከረ ህብረትና ዘላለማዊ መተሳሰር ያለው ነው:: ጳውሎስ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዘላለማዊ ዓላማ ቆም ብሎ ባሰበ ቁጥር፣ ምስጋና ከውስጡ ይፈነቅለውና እንዲህ ይላል:- *«በዚህ ምክንያት በአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ ከእርሱም በሰማይና በምድር ያለ በተሰብ ሁሉ ስያሜ ያገኛል»* ገላ. 3÷14-15::

## የእግዚአብሔር ቤተሰብ የመሆን ጥቅሞች

ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት በመንፈስ በተወለድህበት ቅጽበት አስገራሚ የልደት ስጦታዎች ተለግሰውሃል:: እነሱም፣ የቤተሰብ ስም፣ ቤተሰባዊ መመ ሳሰል፣ ቤተሰባዊ መብቶችና ጥቅሞች፣ ቤተሰባዊ ቀረቤታ፣ እና የቤተሰብ

ሀብት ውርስ 1ዮሐ. 3÷1፣ ሮሜ 8÷17 ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ልጅም ስለሆንህ እግዚአብሔር ወራሽ አድርጎሃል»* ገላ. 4÷7::

አዲስ ኪዳን ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ለተትረፈረፈው «ውርሳችን» ነው:: እንዲህ በማለት ነው የሚገልጥልን:- *«አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ በክርስ ቶስ ኢየሱስ ይሞላባችኋል»* ፊልጵ. 4÷19::

*መንፈሳዊ ቤተሰብህ ዘላለማዊ ስለሆነ፣ ከሥጋዊው ቤተሰብህ ይልቃል ::*

የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን ከቤተሰቡ ሀብት እንካፈላለን:: በምድር ላይ እያለን:- *«የጸጋው ... ባለጸጋነት ... በጎነት ... ትእግስት ... ክብር ... ጥበብ ... ኃይል... እና ምህረት»* ኤፌ. 1÷7፣ ሮሜ 2÷4፣ 9÷23፣ 11÷33፣ ኤፌ. 3÷16፣ 2÷4 ተሰጥቶናል:: በዘላለም ሕይወት ግን ከዚህም የበለጠ ነገር እንወርሳለን::

ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *«በቅዱሳኑ ዘንድ ያለውን ክቡር የሆነውን የርስቱን ባለጠግነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ»* ኤፌ. 1÷18:: ውርሱ በትክክል ምንን ያካትታል? አንደኛ፣ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር ወደ እግዚአብሔር እንሄዳለን 1ተሰ. 5÷10፣ 4÷17:: ሁለተኛ፣ ክርስቶስን እንድንመስል ፍፁም እንለወጣለን 1ዮሐ. 3÷2፣ 2ቆሮ. 3÷18:: ሦስተኛ፣ ከበሽታ፣ ከሞትና ከስቃይ ሁሉ ነፃ እንሆናለን ራእይ 21÷4:: አራተኛ፣ እንሸለማለን፣ የአገልግሎት ሥልጣንም ይሰጠናል ማር. 9÷14፣ 10÷30፣ 1ቆሮ. 3÷8፣ ዕብ. 10÷35፣ ማቴ. 25÷21-22:: አምስተኛ፣ ከክርስቶስ ክብር እንካፈላለን ሮሜ 8÷17፣ ቆላ. 2÷14፣ 2ጢሞ. 2÷12፣ 1ጴጥ. 5÷1:: እንዴት ያለ አስደናቂ ውርስ ነው! ልትገምተው ከሚቻልህ በላይ ሀብታም ነህ::

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እንዲያውም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን »* 1ጴጥ. 1÷5:: ይህ የሚያስረዳው፣ ዘላለማዊው ውርስህ፣ በዋጋ ሊተመን የማይቻል፣ ንፁህ፣ ቋሚ፣ እና የተጠበቀ መሆኑን ነው:: ማንም ሊወስድብህ አይችልም፣ በጦርነት፣ በችግር፣ ወይም በተፈጥሮ አደጋ አይጠፋም:: ይህ በጡረታ ጊዜ የሚገኝ ጥቅም ሳይሆን፣ ልትጠብቀውና ልትጥርለት የሚገባ ዘላለማዊ ውርስ ነው ::
ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- *«የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታ ደርጉት ቀጥራችሁ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት:: ከጌታ ዘንድ እንደብድራት የምትቀበሉት ርስት እንዳለ ታውቃላችሁና የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነው»* ቆላ. 3÷23-24:: ጥሩ ጥሪት ይዞ ጡረታ መውጣት የአጭር እይታ ግብ ነው:: ከዘላለም አንጻር ነው መኖር ያለብህ::

# ጥምቀት፤ ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋር አንድ መሆን

የመልካም ቤተሰብ አባላት በቤተሰቦቻቸው ይኮራሉ፤ የቤተሰቡ አባላት ተብለው ቢጠሩም አያፍሩም:: የሚያሳዝነው ግን፣ ኢየሱስ እንዳዘዘው በጥምቀት ዓማካይነት እራሳቸውን ከመንፈሳዊው ቤተ ሰባቸው ጋር በግልጥ ያላመሳሰሉ ክርስቲያኖች ገጥመውኛል::

**አሥራ አምስተኛ ቀን**

**ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተበጅተሃል**

ጥምቀት፣ ሊዘገይ ወይም ሊተላለፍ የማይገባውና አማራጭ የሌለው ሥርዓት ነው:: ሥርዓቱ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት መጨመርህን ያመለክታል:: «የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል በመሆኔ አላፍርም» ማለትህን በግልጥ ለዓለም ያውጃል:: ተጠምቀሃል? ቤተሰቡ ሁሉ ይህን ውብ ሥርዓት ይፈፅሙ ዘንድ ኢየሱስ፤ «*ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው*» ማቴ. 18÷19 በማለት አዞናል::

ኢየሱስ የሰጠው ታላቅ ተልዕኮ ወንጌልን ለመስበክና ለማነጽ የሚሰጠውን ያህል፣ ለጥምቀት ታላቅ ሥፍራ መስጠቱ ለምንድነው? እያልኩ ለብዙ ዓመታት ስጠይቅ ቆይቻለሁ:: ለምንድነው ጥምቀት በጣም ጠቃሚ የሆነው? በኋላ የተገነዘብኩት ነገር፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለው ሁለተኛ ዓላማ፣ ማለት በዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የመሳተፍህ ተምሳሌት ስለሆነ መሆኑን ነው::

ጥምቀት ብዙ ትርጉም አለው:: እምነትህን እንዲሁም የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተካፋይነትህን የሚያውጅ፣ የአሮጌውን ሕይወትህን ሞት በተምሳሌ ትነት የሚገልጥና በክርስቶስ ያገኘኸውን አዲስ ሕይወት የሚያረጋግጥ ነው:: ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት የመጨመርህ ደስታ በዓልም ነው::

ጥምቀትህ የመንፈሳዊው እውነት አካላዊ ምስል ነው:: እግዚአብሔር ወደ ቤተሰቡ ባስገባህ ጊዜ የሆነውን ነገር ይወክላል:- «*አይሁድ ወይም፣ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፣ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን ፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና ፣ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል*» 1ቆሮ. 12÷13::

በክርስቶስ ማመንህ እንጂ፣ ጥምቀት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል አያደርግህም:: በልብህ ያደረግከውን ውስጣዊ ቃል ኪዳን እንደ ጋብቻ ቀለበት በገሀድ የሚያመለክት ማስታወሻ ነው:: የአዲሱ ሕይወትህ ጅማሬ መግለጫ እንጂ፣ በመንፈሳዊ ሕይወትህ እስከታድግ ድረስ የምታቆየው ጉዳይ

አይደለም።

አዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምናነበው፣ ሰዎች እንዳመኑ ወዲያው ነበር የሚጠመቁት። በጰንጠቆስጤ ዕለት 3000 ሰዎች ክርስቶስን *እንደተቀበሉ* ተጠምቀዋል። በሌላ *ሥፍራ* ደግሞ አንድ ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን በክርስ ቶስ ባመነ ጊዜ *እዚያው* ተጠምቋል። ጳውሎስና ሲላስ የፊሊጵስዩሱን የወህኒ ኃላፊና ቤተሰቡን *በእኩለ ሌሊት* አጥምቀዋቸዋል። የዘገየ ጥምቀት አዲስ ኪዳን ውስጥ አልነበረም። በክርስቶስ ላለህ እምነት እንደ መግለጫነት የሚያገለግለ ውን ጥምቀት አላከናወንህ እንደሆን፣ ኢየሱስ እንዳዘዘው በቶሎ ተጠመቅ።

## የሕይወት ትልቁ ዕድል

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ሰዎችን የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሰዎች ከአንድ ቤተሰብ ናቸው፤ ስለዚህ ኢየሱስ ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው አያፍርም»* *ዕብ. 2 ÷11*። ይህ አስደናቂ እውነት ወደ ውስጥህ ይዝለቅ፤ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አካል ነህ። ኢየሱስ ስለ ሚቀድስህም፣ እግዚአብሔር በአንተ ይኮራል! እንዲህ የሚሉት የኢየሱስ ቃላት ትክክል ናቸው፡- *«በእጁም ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ እንዲህ አለ እናቱና ወንድሞቹ እነዚህ ናቸው፤ በሰማይ ያለውን የአባቱን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፣ ወንድሜ፣ እህቱና እናቱም ነው»* ማቴ. 12÷49-50። የእግዚአ ብሔር ቤተሰብ አባል መሆን ከሁሉ የላቀ ከፍተኛ ክብርና ታላቅ ዕድል ነው። የማትጠቅም እንዲሁም የማትወደድ ሲመስልህና ዋስትና የሌለህ ሆኖ በተሰማህ ቁጥር የማን መሆንህን አስታውስ።

> *የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል መሆን ከሁሉ የላቀ ከፍተኛ ክብርና ታላቅ ዕድል ነው።*

## አሥራ አምስተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ነው የተበጀሁት::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ እንደበጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን» ኤፌ. 1÷5::*

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** ሌሎች አማኞችን እንደ ቤተሰቤ አባላት መመልከትን ልጀምር የምችለው እንዴት ነው ?

# 16

# ዋናው ነገር

*ያለኝን ሁሉ ለድሆች ብሰጥ፣ ሰውነቴም እንዲቃጠል ለእሳት ብዳርግ፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም::*

1ቆሮ. 13÷3

*ይህም ፍቅር በትእዛዛቱ መሠረት እንመላለስ ዘንድ ነው:: ትእዛዙም ከመጀመሪያ እንደሰማችሁት በፍቅር እንድትኖሩ ነው::*

2ዮሐ. 1÷6

የሕይወት ዋና ነገር ፍቅር ነው::

እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፣ በምድር ላይ እንድትማረው የሚፈልገው ከሁሉ የሚበልጥ ነገር ማፍቀርን ነው:: ይበልጥ እርሱን የምንመስለውም በማፍቀር ነው:: በመሆኑም ፍቅር፣ እሱ የሰጠን ትእዛዞች ሁሉ መሠረት ነው:: *«ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሏል፣ ይኸውም፣ <ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ > የሚል ነው»* ገላ. 5÷14::

ራስ ወዳድ ሳይሆኑ ሌላን መውደድን መማር ቀላል አይደለም:: ራስ ወዳ ድነት ባህርያችን ነው:: ለዚህ ነው ራስን አለመውደድ ዕድሜያችንን ሁሉ የምንማረው ነገር ሆኖ የተሰጠን:: እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እንድናፈቅር በተለይ ግን በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎችን ማፍቀርን እንድንማር ይፈልጋል:: ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ የሕይወትህ ሁለተኛ ዓላማ ይህ ነው:: ጴጥሮስ እንዲህ ይለናል:- *«ወንድሞችን ውደዱ»* 2ጴጥ. 2÷17:: ጳውሎ ስም እንዲህ በማለት ይህን አባባል ያጎላዋል:- *«ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ::»* ገላ. 6÷10::

ለምንድነው እግዚአብሔር ለሌሎች አማኞች የተለየ ፍቅርና ትኩረት እንድ ንሰጥ አጥብቆ የሚያዘን? ለምንድነው በቅድሚያ እነርሱ ሊወደዱ የሚገባቸው? ምክንያቱም ቤተሰብ ከሌላ ነገር ይልቅ፣ እርስ በርስ በመዋደድ ዓማካይነት

አሥራ ስድስተኛ ቀን

ዋናው ነገር

እንዲታወቅ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ለዓለም የሚታየው ትልቁ ምስክርነት፣ የእምነት አቋማችን ሳይሆን፣ እርስ በእርስ ያለን ፍቅር መሆኑን ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- *«እርስ በእርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ»* ዮሐ. 13፥35።

በእግዚአብሔር ቤተሰብነታችን፣ በመንግሥተ ሰማያት ለዘላለም ደስ እንሰኛለን። በመጀመሪያ ግን፣ ለዘላለማዊው ማፍቀር እራሳችንን እናዘጋጅ ዘንድ፣ በምድር ላይ የምናከናውነው ጥቂት ብርቱ ሥራ አለን። እግዚአብሔር የሚያሰለጥነን «የቤተሰብ ኃላፊነቶችን» በመስጠት ሲሆን፣ ከነዚህ ሁሉ የሚበልጠው፣ እርስ በእርስ መዋደድን መልመድ ነው።

የማፍቀር ጥበብን ትማር ዘንድ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር የማያቋርጥና የቀረበ አንድነት እንዲኖርህ እግዚአብሔር ይፈልጋል። በብቸኝነት ወይም በገለልተኛነት ፍቅርን ለመማር አይቻልም። አናዳጅና ተስፋ አስቆራጭ ከሆኑ፣ እንዲሁም ጉድለት ካለባቸው ሰዎች ጋር መቀላቀል አለብህ። ህብረት በማድረግ ዓማካይነት ሦስት ጠቃሚ እውነቶችን እንማራለን።

## በሕይወታችን ልናከናውን የምንችለው ከሁሉ የሚበልጥ ተግባር ፍቅር ነው።

ቀዳሚ ነገርህ፣ ዋና ዓላማህ እና ከሁሉ በላይ የሆነ ምኞትህ ፍቅር መሆን አለበት። ፍቅር የሕይወትህ ፐሪ ጎን ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉ የሚበልጥ ክፍል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«ፍቅርን ተከታተሉ»* 1ቆሮ. 14፥1 ይላል።

ከአስር ዋና ዋና ነገሮቻችን *እንደ አንዱ* በመቁጠር፣ «በሕይወቴ ከምፈልጋቸው ነገሮች አንዱ ማፍቀር ነው» ማለታችን በቂ አይደለም። ከማንኛውም ነገር ይልቅ ከሌሎች ጋር ያለህ ህብረት በሕይወትህ ቀዳሚውን ሥፍራ ሊይዝ ይገባል። ለምን?

**ሕይወት ያለ ፍቅር ፋይዳ ቢስ ነው።** ጳውሎስ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡- *«ያለኝን ሁሉ ለድሆችን ብሰጥ፣ ሰውነቴም እንዲቃጠል ለእሳት ብዳርግ፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ፣ ምንም አይጠቅመኝም»* 1ቆሮ. 13፥3።

ብዙ ጊዜ ከሌሎች ጋር ያሉን ህብረቶች በኛ የጊዜ ሰሌዳዎች ውስጥ የሚካተቱ እንደሆኑ አድርገን ነው የምንንቀሳቀሰው። ለልጆቻችን ጊዜ *ስለማግኘት*፣ ወይም ለሕይወታችን ቅርብ ለሆኑ ሰዎች ጊዜ ስለመመደብ እንናገራለን።

ይህ የሚያመለክተው ከሰዎች ጋር ያሉን ግንኙነቶች፣ ከሌሎች ሥራዎች ጋር የተዳመሩ የሕይወታችን አንድ ክፍል መሆናቸውን ነው። እግዚአብሔር ግን ግንኙነቶች የፍቅር ሁለንተና ናቸው ይላል።

ከአሥርቱ ትእዛዛት አራቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ይመለከታሉ። ስድስቱ ግን ከሰዎች ጋር የሚኖሩን ግንኙነቶች ናቸው። በዚህ ሁኔታ አሥሩም ግንኙነቶችን ነው የሚመለከቱት። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ዋና የሆነውን ነገር በሁለት ዐረፍተ ነገሮች አጠቃልሎታል፤ እግዚአብሔርን ውደድ፣ ሰዎችን ውደድ። *«ጌታ አምላክህን በፍፁም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ሐሳብህም ውደድ። ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው። ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም <ጐረቤትህን እንደራስህ ውደድ> የሚለው ነው። ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው»* ማቴ. 22÷37-40። እግዚአብሔርን ማፍቀርን ከተማርክ በኋላ (አምልኮ)፣ ሌሎችን ማፍቀርን መማሩ፣ የሕይወትህ ሁለተኛ ዓላማ ይሆናል።

በሕይወትህ ቅድሚያ ልትሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች፣ የምታገኛቸው ስኬቶች ወይም የምታከማቸው ሀብት ሳይሆኑ፣ ከሌሎች ጋር ያለህ ህብረት ወይም ግንኙነት ነው። ለምንድነው ታዲያ ግንኙነታችን በጣም ውሱን እንዲሆን የምናደርገው? የሥራ ጫና በሚበዛበን ጊዜ፣ ግንኙነታችንን ማላላት እንጀምራለን። የወዳጅነት ግንኙነቱ የሚጠይቀውን ጊዜ፣ ጉልበትና ትኩረት እናሳጥረዋለን። የእግዚአብሔር ዋና ነገር፣ አስቸኳይ በሆነ ነገር ይተካል።

የሥራ ብዛት የግንኙነቶች ዋና ጠላት ነው። ለኑሯችን የሚያስፈልገንን ነገር በማግኘት ተግባር በመያዝ፣ በሥራ፣ ዕዳዎችን በመክፈልና፣ እነዚህ የሕይወት ዋና ነገሮች የሆኑ ይመስል የእነርሱን እቅዶች በማከናወን ሂደት እንጠመዳለን። አይደሉም። የሕይወት ዋና ነገር፣ እግዚአብሔርን እና ሰውን መውደድን መማር ነው። ሕይወት ሲቀነስ ፍቅር፣ ይሆናል ባዶ (ዜሮ)።



**ፍቅር ለዘላለም ይኖራል።** ፍቅርን የመጀመሪያ ነገራችን እንድናደርገው እግዚአብሔር የሚነግረን ዘላለማዊ ስለሆነ ነው፡- *«እንግዲህ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህ የሚበልጠው ፍቅር ነው»* 1ቆሮ. 13÷13።

ፍቅር ቅርስ ያኖራል። በምድር ላይ የምትተወው ቀጣይ ተጽዕኖ፣ ሀብትህ ወይም ስኬትህ ሳይሆን፣ ለሌሎች የምታደርገው ነገር ነው። ማዘር ቴሬዛ የተባሉ ምግባረ ሰናይ ሴት እንዲህ ብለዋል፡- «ዋናው ነገር የምታደርገው ሳይሆን፣ በድርጊትህ ውስጥ የምትጨምረው የፍቅር መጠን ነው »። ፍቅር የማይጠፋ ቅርስ ምስጢር

ነው::

ብዙ ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ እመኝታቸው አጠገብ ሆኜ የሚሉትን የማዳመጥ እድል ገጥሞኛል:: ሰዎች ዘላለም መግቢያ ጫፍ ላይ ሲደርሱ፣ ቆም ብለው፣ «ዲፕሎማዎቼን አምጡ፣ አንድ ጊዜ ልመለከታቸው እፈል ጋለሁ:: ሽልማቶቼንና ሜዳሊያዎቼን፣ የተሸለምኩትን የወርቅ ሰዓት አሳዩኝ» ሲሉ አልሰማሁም:: ምድራዊ ሕይወት በሚያበቃበት ጊዜ በዙሪያቸው ቁሳቁሶ ችን አይደረድሩም:: በዙሪያችን እንዲሆኑልን የምንፈልጋቸው፣ የምናፈቅራ ቸውና ከእኛ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው::

ሕይወት እራሱ ግንኙነት ነው:: ይህን ሁላችንም የምንረዳው፣ በፍፃሜያችን ወቅት ነው:: ጥበብ የሚሆነው ግን፣ ይህን እውነት ሳይዘገይ ቶሎ መማሩ ነው:: እንደ ግንኙነት ዋና ጉዳይ የሌለ መሆኑን ለመረዳት እስከ መሞቻህ ጊዜ አትጠብቅ::

*ሕይወት እራሱ ግንኙነት ነው::*

በፍቅራችን እንመዘናለን:: ፍቅርን መማርን የሕይወታችን ግብ ልናደርግ የሚገባን ሦስተኛ ምክንያት፣ በዘላለም ሕይወት ወቅት የምንመዘንበት በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር መንፈሳዊ እድገትህን ከሚመዝንባቸው መንገዶች አንዱ፣ የግንኙነትህ ዓይነት ነው:: በመንግሥተ ሰማያት:- «ስለ ሥራህ፣ ባንክ ውስጥ ስላለህ ገንዘብና ስለ ትርፍ ጊዜ መዝናኛዎችህ ንገረኝ» አትባልም:: ይልቁንም ለሌሎች፣ በተለይም ለችግ ረኞች ስላደረግህላቸው ነገር ነው የሚጠየቀው ማቴ. 25÷34-46:: እርሱን የመውደጃው መንገድ፣ ቤተሰቦቹን መውደድና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማድ ረግ መሆኑን ኢየሱስ እንዲህ በማለት ገልጧል:- «*እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ ከነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው ይላቸ ዋል*» ማቴ. 25÷40::

ወደ ዘላለም ስትሻገር ሁሉንም ነገር ትተኸው ነው የምትሄደው:: ይዘኸው የምትሄደው ነገር ቢኖር ባሕርይህ ነው:: ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚለው:- «*የሚጠቅመውስ በፍቅር የሚገለጥ እምነት ብቻ ነው*» ገላ. 5÷6::

ይህን ካወቅህ፣ ታደርገው ዘንድ የምመክርህ ነገር ይህ ነው:: ሁል ጊዜ ጠዋት ከእንቅልፍህ ስትነቃ፣ አልጋህ ሥር ተንበርክከህ ወይም ጫፉ ላይ ተቀምጠህ እንዲህ በማለት ጸልይ:- «እግዚአብሔር ሆይ! በዛሬው ዕለት ምንም ላድርግ ምን፣ አንተን በማፍቀርና ሌሎች ሰዎችን በማፍቀር ጊዜዬን ስለማ ሳለፌ እርግጠኛ ለመሆን እፈልጋለሁ:: ምክንያቱም ሕይወት እራሱ ማፍቀር ነው:: ይህን ዕለት በከንቱ ላሳልፈው አልፈልግም»:: በከንቱ የምታሳልፈው

ከሆነ፣ ለምንድነው እግዚአብሔር ሌላ ቀን የሚሰጥህ?

## የፍቅር የላቀ መገለጫ ጊዜ ነው::

የነገሮች ጠቃሚነት የሚለካው፣ ለነገሮቹ በምንመድበው የጊዜ መጠን ነው:: ለአንድ ነገር ብዙ ጊዜህን በሰጠህ ቁጥር፣ ያ ነገር ለአንተ ያለውን ፋይዳና ጠቃሚነት ይበልጥ ትገልጣለህ:: አንድ ሰው ቅድሚያ የሚሰጠው እንዴት ላሉ ነገሮች መሆኑን ለማወቅ ከፈለክ፣ የጊዜ አጠቃቀሙን በደንብ ተመልከት::

ጊዜ ተወስኖ የተሰጠህ በመሆኑ፣ ከሁሉ የበለጠ ክቡር ስጦታ ነው:: ባለህ ገንዘብ ላይ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ትችላለህ:: ባለህ ጊዜ ላይ ግን ለመጨመር አትችልም:: ለአንድ ሰው ጊዜህን ስትሰጠው፣ እንደ ገና የማታገኘውን የሕይወትህን አንድ ክፍል መስጠትህ ነው:: ጊዜህ ሕይወትህ ነው:: ለዚህ ነው ለአንድ ሰው የምትሰጠው ትልቅ ነገር፣ ጊዜ የሚሆነው::

ግንኙነቶች ጠቃሚ ናቸው *ማለቱ* ብቻ በቂ አይደለም:: ለግንኙነቶቹ ጊዜ በመመደብ የአባባላችንን እውነትነት ማረጋገጥ አለብን:: ቃላት ብቻቸውን ፋይዳ የላቸውም:: «*ልጆች ሆይ፣ በተግባርና በእውነት እንጂ፣ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ*» 1ዮሐ. 3÷18:: ግንኙነቶች ጊዜና ጥረት ይጠይቃሉ::

> *ለአንድ ሰው የምትሰጠው ትልቅ ነገር ጊዜህ ነው::*

የፍቅር ፍሬ ነገር፣ ለሌሎች የምናስበው፣ የምናደርገው ወይም የምንለግሳቸው ነገር ሳይሆን፣ ከእኛነታችን የምንሰጣቸው መጠን ነው:: ወንዶች በተለይ ይህ ነገር አይገባቸውም:: ብዙዎቹ እንዲህ ብለዋል:- «የሚስቴና የልጆቼ ነገር አይገባኝም:: የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ:: ከዚህ ይበልጥ ምን ይፈልጋሉ?»:: ቤተሰቦችህ አንተን ይፈልጋሉ! ዓይኖችህን፣ ጆሮዎችህን፣ ጊዜ ህን፣ አስተውሎትህን፣ መገኘትህን፣ ትኩረትህን፤ ባጠቃላይ ጊዜህን ይፈል ጋሉ:: ይህን ምንም ሊተካው አይችልም::

ተወዳጁ የፍቅር ስጦታ እንቁ፣ አበባ ወይም ቸኮሌት አይደለም:: ከልብ *የሆነ* ትኩረት ነው:: ፍቅር እራስህን እስክትረሳ ድረስ በተፈቃሪው ላይ እንድ ታተኩር ያደርግሃል:: «በጣም ክቡር ንብረቴ የሆነውን ጊዜዬን እስክሰጥህ ድ ረስ አፈቅርሃለሁ» ማለት ነው፣ ትኩረት:: ጊዜህን በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉ መሥዋዕት በማድረግ ላይ ነህ፤ መሥዋዕት ደግሞ የፍቅር ዋና ነገር ነው:: የኢየሱስ ሞዴልነት እንዲህ ነው:- «*ክርስቶስም እንደወደደን ራሱንም ስለእኛ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ፣ እናንተም*

*በፍቅር ተመላለሱ»* ኤፌ. 5+2::

ፍቅር ሳይኖርህ ስጦታን ልትሰጥ ትችላለህ፤ ሳትሰጥ ግን ልታፈቅር አትችልም:- *«እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና»* ዮሐ. 3÷16:: ፍቅር ማለት ሌላን ሰው ለመጥቀም ሲባል የግል ምርጫን፣ ምቾትን፣ ግቦችን፣ ዋስትናን፣ ገንዘብን፣ ጉልበትን ወይም ጊዜን መተው ነው::

## ከሁሉ የተሻለ የማፍቀሪያ ጊዜ አሁን ነው::

የማይረባ ሥራን ዛሬ ነገ እያሉ ማስተላለፉ አንዳንድ ጊዜ ተገቢ ሊሆን ይችላል:: ፍቅር ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ዋና ጉዳይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ጉዳይ በጥብቅ ሲያስገነዝብ እንዲህ ይላል:- *«ስለዚህ እድሉ ካለን፣ ለሰው ሁሉ፣ ... መልካም እናድርግ»* ገላ. 6÷10:: *«ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ »* ኤፌ. 5÷16:: *«ማድረግ እየቻልህ ለሚገባቸው መልካም ነገር ከማድረግ አትከልክል:: «አሁን በእጅህ እያለ ገረቤትህን <ቀይተህ ተመለስ፣ ነገ እሰጥሃለሁ> አትበለው »* ምሳሌ 3÷27-28::



ፍቅርን የመግለጫ ተመራጩ ጊዜ *አሁን* የሆነበት ምክንያት ምንድነው? ይህ ዕድል ለምን ያህል ጊዜ ያንተ እንደሚሆን ስለማታውቅ ነው:: ሁኔታዎች ይለዋወጣሉ፣ ሰዎች ይሞታሉ፤ ሕፃናት ያድጋሉ:: ስለ ነገ ዋስትና የለህም:: ፍቅርን ለመግለጥ ከፈለክ፣ አሁን ብታደርገው ይሻላል::

አንድ ቀን እግዚአብሔር ፊት የምትቆም መሆንህን በማወቅ፣ ልብ ልትላቸው የሚገቡ ጥያቄዎች እነሆ! እቅዶችህ ወይም ሌሎች ነገሮች ከሰዎች ይልቅ ጠቃሚ ስሆኑብህ ጊዜያት ምን ምክንያት ነው የምትሰጠው? ብዙውን ጊዜህን ማሳለፍ የሚገባህ ከማን ጋር ነው? ይህን ለማድረግ እንድትችል፣ ከጊዜ ሰሌዳህ ውስጥ ልታስወግደው የሚገባ ነገር ምንድነው? እንዴት ያሉ መሥዋዕቶችን ለመክፈል ትፈልጋለህ?

በሕይወትህ ልታከናውነው የሚቻልህና ከሁሉ የሚልቅ ተግባር ፍቅር ነው:: ከሁሉ የሚበልጠው የፍቅር መግለጫ ጊዜ፣ ከሁሉ የሚሻለው ጊዜ ደግሞ፣ አሁን ነው::

## አሥራ ስድስተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** የሕይወት ዋናው ነገር ፍቅር ነው።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** «*ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃልሏል፤ ይኸውም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው*» ገላ. 5÷14።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** እውነቱን ብናገር፣ ግንኙነቶች ከሁሉ የማስቀድማቸው ነገሮች ናቸው? በእርግጥ እንዲሆኑም ለማድረግ የምችለው እንዴት ነው?

# 17
# የመገኛ ሥፍራ

*ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔ ርም ቤተሰብ አባል ናችሁ እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ መፃተኞችና እንግዶች አይደላችሁም፡፡*

*ኤፌ. 2÷19*

*በቱም የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ይኸውም የእውነት ዐምድና መሠረት ነው፡፡*

1ጢሞ. 3÷15

የተጠራኸው እንድታምን ብቻ ሳይሆን፣ አባል እንድትሆንም ነው፡፡ ፍጹም በሆነውና ኃጢአት አልባ በሆነው ኤደን ገነት ውስጥ እንኳን እግዚአብሔር፡- «*ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም*» ዘፍ. 2÷18 ብሏል፡፡ ህብረተሰብ ውስጥ ለመኖር የተፈጠርን፣ ለህብረት ኑሮ የተዘጋጀን፣ በቤተሰብ የተቀረፅን ነን፡፡ ማንኛችንም ብንሆን የእግዚአብሔ ርን ዓላማ ብቻችንን ልንፈጽም አንችልም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች አማኞች ስለ ተለዩና ህብረት ሳያደርጉ ስለሚ ኖሩ ቅዱሳን ወይም መንፈሳዊ ባሕታውያን የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ *የሚነግረን፣ የተሰባሰብን፣ የተያያዝን፣ በአንድነት የተሠራን፣ የጋራ አባላት የሆንን፣ አብረን ወራሾች፣ የተጣመርን፣ የተቀራኘን እና አብረን ወደ ላይ የምን ነጠቅ መሆናችንን ነው፣* 1ቆሮ. 12÷12፤ ኤፌ. 2÷21-22፤ 3÷6፤ 4÷16፤ ቆላ. 4÷17፡፡ ከእንግዲህ ብቸኛ አይደለህም፡፡

ከክርስቶስ ጋር ያለህ ግንኙነት ግላዊ ቢሆንም፣ ብቸኛ እንድትሆን በፍጹም እግዚአብሔር አላቀደም፡፡ እግዚአብሔር ቤት ውስጥ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ተያይዘሃል፤ *ለዘላለምም* እርስ በእርሳችን አንድ እንሆ ናለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «እንዲሁም እኛ *ብዙዎች ስንሆን*

*በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እያንዳንዳችንም የሌላው ብልቶች ነን»* ሮሜ 12፥5።

ክርስቶስን መከተል ማመን ብቻ አይደለም፤ አባልነትንም ይጨምራል። ቤተክርስቲያን ውስጥ የአካሉ አባላት ነን። ሲ.ኤስ. ሉዊስ የተባሉ ሰው፦ «አባልነት የሚለው ቃል የሚመነጨው ከክርስትና ነው። ዓለም ግን ወስዳ መሠረታዊ ትርጉሙን አሳጣችው» ብለዋል። መደብሮች «ለአባላት» ቅናሽ ያደርጋሉ፤ ዕቃ አስተዋዋቂዎች በፖስታ ማስታወቂያ በመላክ የአባላቶቻቸውን አድራሻ ይሰበስባሉ። ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ አባልነት ስምን በመዝገብ ላይ ከማጻፍ ያለፈ፣ አባሉ የሚጠበቅበት ወይም እርሱ የሚጠብቀው ምንም ነገር የለም።

ለጳውሎስ ግን የቤተክርስቲያን «አባል» ማለት፣ የህያው አካል ጠቃሚ ብልት፣ አስፈላጊና ከሌሎች ጋር የተጣመረ የክርስቶስ አካል ክፍል ነው፣ ሮሜ 12፥4-5፤ 1ቆሮ. 6፥15፤ 12፥12-27። የአባልነትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም እንደገና ማንሣትና በሥራ ላይ ማዋል ይኖርብናል። ቤተክርስቲያን አካል እንጂ ህንፃ፣ ዘአካል *(organism)* እንጂ፣ ድርጅት አይደለችም።

የአካልህ ክፍሎች ዓላማቸውን ያከናውኑ ዘንድ፣ ከአካልህ ጋር መያያዝ አለባቸው። የክርስቶስ አካል እንደመሆንህ፣ አንተም እንዲሁ ነህ። የተፈጠርከው ለተወሰነ ተግባር ነው። ህያው ከሆነችው አጥቢያ ቤተክርስቲያን ጋር ግንኙነት ከሌለህ ግን፣ ይህን የሕይወት ሁለተኛ ዓላማ ትስታለህ። ሕይወት ውስጥ ያለህን ሚና ምንነት የምትገነዘበው፣ ከሌሎች ጋር በሚኖርህ ግንኙነት ዓማካይነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፦ *«እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣ እነዚህም ብልቶች አንድ ዓይነት ተግባር እንደሌላቸው ሁሉ፣ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን፣ በክርስቶስ አንድ አካል ነን»* ሮሜ 12፥4-5።

*ሕይወት ውስጥ ያለንን ሚና ምንነት የምንገነዘበው፣ ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ዓማካይነት ነው።*

አንድ የአካል ብልት በአንዳች ሁኔታ ከአካሉ ቢቆረጥ ደርቆ ይሞታል። ለብቻው ሆኖ ሊኖር አይችልም፤ አንተም እንዲሁ ነህ። ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካል የደም ሥር ከተለያየህ፣ መንፈሳዊ ሕይወትህ ይጠወልግና በመጨረሻ ህልውናህ ያበቃል ኤፌ. 4፥16። ለዚህ ነው፣ የመንፈሳዊ ማሽቆልቆል የመጀመሪያ ምልክት ብዙ ጊዜ በአምልኮና ሌሎች ክርስቲያናዊ ስብሰባዎች ተሳትፎ ሄድ መጣ ማለት የሚሆነው። ለህብረት ግድ የለሾች በምንሆንበት ጊዜ፣ ሌሎች ነገሮቻችንም መንሸራተት ይጀምራሉ።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነት ፋይዳ እንደሌለው ወይም እንደ ቀላል ነገር የሚተውም አይደለም:: ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር፣ የዓለም አጀንዳው ናት:: ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ :- «*ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም* » ማቴ. 16÷18:: ቤተክርስቲያን ሳትጠፋ ለዘላለም ትኖራለች:: የዓለማት ህልውና ሲያከትም እርሷ ግን መኖሯን ትቀጥላለች፤ በእርሷ ውስጥ አንተ ያለህ ድርሻም እንዲሁ ነው:: «ቤተክርስቲያን አታስፈልገኝም» የሚለው አባባል እብሪተኛነት ወይም አለማወቅ ነው:: ቤተክርስቲያን ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተላትና ታላቅ ናት:- «*ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳትና እራሱን ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ* » ኤፌ. 5÷25::

*የዓለማት ህልውና ሲያከትም*
*ቤተ ክርስቲያን ትኖራለች፤*
*በሷ ውስጥ ያለው የአንተ*
*ሚናም እንዲሁ::*

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን «*የክርስቶስ ሙሽራ*» እና «*የክርስቶስ አካል*»፣ 2ቆሮ. 11÷2፤ ኤፌ. 6÷15፤ 12÷12- 27 ይላታል:: «አንተን እወድሃለሁ፤ ሙሽራህን ግን እጠላታለሁ» ወይም «አንተን እቀበላለሁ፣ አካልህን ግን አልፈልገውም» ብሎ ለኢየሱስ ለመናገር የሚቻል ስለመሆኑ መገመቱ ያቅተኛል:: ቤተክርስቲያንን ስንተዋት፣ ስናቃልላት ወይም ስንወቅሳት ከላይ የተጠቀሰውን ማድረጋችን ነው:: እግዚአብሔር፣ ቤተክርስቲያንን ኢየሱስ የወደዳትን ያህል እንድንወዳት ያዘናል:: መጽሐፍ ቅዱስ:- «*ወንድሞችን ውደዱ*» 1ጴጥ. 2÷17 ይላል:: የሚያሳዝነው ግን፣ ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያንን *ይጠቀሙባታል* እንጂ አይወዷትም::

## የአጥቢያ ህብረትህ

ለጥቂት አስፈላጊ ሁኔታዎች በታሪክ ውስጥ የነበሩ አማኞችን ሁሉ ለመጥቀስ ካልሆነ በቀር፣ አብዛኛውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *ቤተክርስቲያን* የሚለው ቃል የሚያመለክተው፣ አጥቢያንና የአማኞች ጉባዔን ነበር:: አማኞች ሁሉ የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆናቸው የሚጠበቅ ነገር እንደ ነበር ከአዲስ ኪዳን እንረዳለን:: የአንድ አጥቢያ ህብረት አባላት ያልነበሩ ክርስቲያኖች፣ ከባድ ኃጢአት በመፈፀማቸው ምክንያት ቤተክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ወስዳባቸው ከህብረቱ የተወገዱት ብቻ ነበሩ፣ 1ቆሮ. 5÷1-13፤ ገላ. 6÷1-5::

መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ ቤተክርስቲያን አባል ያልሆነን ክርስቲያን አካል

እንደሌለው ብልት፣ ከመንጋው እንደተለየ በግ፣ ወላጆች እንደሌሉት ህፃን ነው ይለዋል። ስለ ህብረት ሲናገርም ፦«*ከቅዱሳን ጋር ... የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ናችሁ*»፣ ኤፌ. 2÷19 ይላል።

የዘመናችን የብቸኝነት ባህል ወላጅ አልባ የሆኑ ብዙ መንፈሳዊ ህፃናትን ፈጥሯል። የትምና የማንም ሳይሆኑ፣ ምንም አገልግሎት ሳይኖራቸው፣ ከቤተክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን ይዘልላሉ። ብዙ ሰዎች አንድ ሰው የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ሳይሆን (በአምልኮዎች እንኳን ሳይካፈል)፣ «ጥሩ ክርስቲያን» ሊሆን ይችላል ብለው ያምናሉ። እግዚአብሔር ግን ይህን አሳብ በጥብቅ ይቃወማል። የአጥቢያ ህብረት አባል መሆንንና መሳተፍን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ አሳማኝ ምክንያቶችን ያቀርባል።

## ቤተክርስቲያናዊ ቤተሰብ የሚያስፈልግህ ለምንድነው?

**ቤተክርስቲያናዊ ቤተሰብ፣ የእውነተኛ አማኝነትህ መታወቂያ ነው።** የአንድ የደቀ መዝሙርነት ቡድን አባል ካልሆንኩ፣ የክርስቶስ ተከታይ ነኝ ለማለት አልችልም። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ «*እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ*» ዮሐ. 13÷35።

ከተለያየ ዘርና ማህበራዊ ደረጃ መጥተን በምንሰባሰብበት ጊዜ፣ ድርጊታችን ለዓለም ጠንካራ ምስክርነት ነው፣ ገላ. 32÷28፤ 17÷21። ብቻህን የክርስቶስ አካል አይደለህም። የአካሉ ክፍል ትሆን ዘንድ ሌሎች ሰዎች ያስፈልጉሃል። በተናጠል ሳይሆን *በሕብርነት* ነው የእርሱ አካል የምንሆነው 1ቆሮ. 12÷17።

**ቤተክርስቲያናዊ ቤተሰብ እራስ ወዳድ ከሆነ መገለል ያወጣሃል።** አጥቢያ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ አብሮ መኖርን የመማሪያ ክፍል ናት። ከራስ ወዳድነት የራቀ ፍቅር መለማመጃ መድረክም ናት። የአንዲት አጥቢያ ተሳታፊ አባል ስትሆን፣ ለሌሎች ማሰብን ትማራለህ፤ የነሱን ልምድም ትካፈላለህ። «*አንድም ብልት ቢሰቃይ፣ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከብር፣ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል*» 1ቆሮ. 12÷26። ከሌሎች ጋር እውነተኛ ግንኙነት ስለማድረግና ስለመደጋገፍ የተገለጠውን የአዲስ ኪዳን እውነት የምንማረው፣ ተራና ፍጹም የሆነ ሕይወት ከሌላቸው አማኞች ጋር የዘወትር ግንኙነት ስናደርግ ብቻ ነው፣ ኤፌ. 4÷16፤ ሮሜ 12÷4-5፤ ቆላ. 2÷19፤ 1ቆሮ. 12÷25።

***አስራ ሰባተኛ ቀን የመገኛ ሥፍራ***

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ህብረት፣ ከኢየሱስ ጋር እንዳደ

ረግነው እርስ በርሳችንም አንዳችን ለሌላችን መስጠታችን ነው። አንዳችን ለሌ ላችን ሕይወታችንን እንድንሰጥ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ዮሐንስ 3፥16ን የሚያውቁ ብዙ ክርስቲያኖች 1ዮሐንስ 3፥16ን አይገነዘቡም። እንዲህ ይላል፦ *«ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለሰጠ፤ ... እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል»* 1ዮሐ. 3፥16። እግዚአብሔር የሚፈ ልግብህ ይህን የመስለውን መሥዋዕታዊ ፍቅር ለሌሎች አማኞች እንድታሳይ ነው። ኢየሱስ አንተን በሚወድበት ሁኔታ ልትወዳቸው ፈቃደኛ እንድትሆን ይፈልጋል።

**ቤተክርስቲያናዊ ቤተሰብ መንፈሳዊ ጡንቻህን ያጠነክርልሃል።** የአምልኮ ፕሮግራሞችን በመካፈልና የሩቅ ተመልካች በመሆን ብቻ መንፈሳዊ ዕድገት አታገኝም። መንፈሳዊ ጡንቻን የሚያጠነክረው በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሙሉ እንቅስቃሴ ውስጥ መካፈል ብቻ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *«አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፤ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል»* ኤፌ. 4፥16።

*«እያንዳንዱ»* ወይም *«እርስ በርስ»* የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን ውስጥ ከአ ምሳ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። እርስ በርሳችን *እንድንዋደድ፤* አንዳችን ለሌ ላችን *እንድንጸልይ፤ እንድንበረታታ፣* እርስ በርስ *እንድንተናነጽ፤ ሰላም* እንድንባ ባል፣ አንዳችን ሌላችንን *እንድናገለግል፤ እንድንማማር፤ እንድንቀባበል፤ እንድንቻ ቻል፤* አንዳችን የሌላችንን ሸክም *እንድንሸከም፤ ይቅር እንድንባባል፤* አንዳችን ለሌላችን *እንድንሸነፍ፤ ታማኞች እንድንሆንና* በጋራ *ሥራዎች* ህብረት እንዲኖረን ታዘናል። ይህ ነው መጽሐፍ ቅዱሳዊው አባልነት ወይም ሕብረት! በአጥቢያ ህብረት በኩል እንድታከናውናቸው እግዚአብሔር የሚፈልግብህ «ቤተሰባዊ ሃላፊነቶች» እነዚህ ናቸው። *ከማን ጋር* ነው እነዚህን የምታከናውናቸው?

ምርጫህን ወይም ፍላጎትህን የሚያሰናክልብህ ሰው በአቅራቢያህ ከሌለ፣ ቅዱስ መሆኑ ቀላል ይሆን ይሆናል። ይህ ዓይነቱ ቅድስና የውሸትና ያልተ ፈተነ ነው። ገለልተኛነት መታለልን ይወልዳል፤ የሚገዳደረን ሰው በአቅራ ቢያችን በማይኖርበት ጊዜ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን አድገናል ብለን እራሳች ንን ማታለሉ ቀላል ነው። እውነተኛ ዕድገት በግንኙነት ይገለጣል።

በመንፈሳዊ ሕይወታችን እናድግ ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ሌሎች አማኞች ያስፈልጉናል። እርስ በርሳችን ስንማማርና አንዳችን ስለሌላ ችን ኃላፊነት (ተጠያቂነት) ሲሰማን፣ በፍጥነት እናድጋለን። እግዚአብሔር የሚያስተምራቸውን ሌሎች ሲያካፍሉኝ፣ እኔም እማራለሁ፤ አድጋለሁም።

**የክርስቶስ አካል ይፈልግሃል።** ቤተሰቡ ውስጥ የምትጫወተውን ድንቅ

ሚና እግዚአብሔር አዘጋጅቶልሃል፡፡ ይህ ሚና «አገልግሎት» ይባላል፡፡ ለዚህ ተልዕኮ የሚረዳህ ስጦታም ሰጥቶሃል፡- «*መንፈስ ቅዱስን መገለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው*» 1ቆሮ. 12÷7፡፡

የአጥቢያ ህብረት፣ ስጦታዎችህን እንድታውቃቸው፣ እንድታሳድጋቸው እንድትጠቀምባቸው እግዚአብሔር ያዘጋጀልህ ሥፍራ ነው፡፡ ከዚያ የሰፋ ሌላ አገልግሎት ይኖርህ ይሆናል፡፡ ያ ግን አጥቢያ ህብረትህ ውስጥ ባለህ አገልግሎት ላይ ተጨማሪ እንጂ ዋናው አይደለም፡፡ ኢየሱስ ቃል የገባው *በተ ክርስቲያኑን እንጂ*፣ የአንተን አገልግሎት ለማነፅ አይደለም፡፡

**ክርስቶስ ዓለም ውስጥ ባለው ተልእኮ ተካፋይ ትሆናለህ፡፡** ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሥጋዊ አካል ዓማካይነት ሠር ቷል፤ ዛሬ ደግሞ በመንፈሳዊ አካሉ ይገለገላል፡፡ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ የእግዚአብሔር መሣሪያ ናት፡፡ እርስ በርሳችን በመዋደድ የእግዚአብሔርን ፍቅር መግለጥ ብቻ ሳይሆን፣ ያን ፍቅር ወደ ቀረው ዓለም በጋራ መውሰድ አለብን፡፡ ይህ በጋራ የተሠጠን አስደናቂ ዕድል ነው፡፡ እንደ የክርስቶስ አካል ነታችን፣ እጆቹ፣ ዓይኖቹ እና ልቦቹ ነን፡፡ ዓለም ውስጥ በእኛ ይሠራል፡፡ እያንዳንዳችን የምናበረክተው ድርሻ አለን፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፡- «ምክን ያቱም *እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን*» ኤፌ. 2÷10፡፡

**ቤተክርስቲያናዊው ቤተሰብ ወደ ኋላ ከመመለስ ይጠብቅሃል፡፡** ማንኛችንም ብንሆን ፈተና የማይነካን አይደለንም፡፡ እኔና አንተ ለኃጢአት በሚያጋልጥ ሁኔታ ውስጥ ከሆንን፣ ኃጢአት ለመሥራት የምንችል ነን 1ቆሮ. 10÷12፤ ኤር. 17÷9፤ 1ጢሞ. 1÷19፡፡ እግዚአብሔር ይህን ያውቃል፤ በመሆኑም ነው እርስ በርሳችን እንድንጠባበቅ ለያንዳንዳችን ኃላፊነትን የሰጠን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- « *ማንም በኃጢአት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድን ... እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ*» ዕብ. 3÷13፡፡ «ምን አገባህ» የሚለው አባባል ክርስቲያናዊ ቋንቋ አይደለም፡፡

> *ኢየሱስ ቃል የገባው፣ በተ ክርስቲያኑን እንጂ፣ ያንተን አገልግሎት ለማነጽ አይደለም፡፡*

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነው የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጠቃሚነት፣ መንፈሳዊ በሆኑ መሪዎች የምናገኘው ጥበቃ ነው፡፡ የመንጋውን መንፈሳዊ ደህንነት ይጠብቁ፣ ይከላከሉና፣ ይጠነቀቁለት ዘንድ እግዚአብሔር ለመሪዎች ኃላፊነትን ሰጥቷል፣ ሐዋ. 20÷28-29፤ 1ጴጥ. 5÷1-4፤ ዕብ. 13÷7፤17፡፡ እንዲህ ተብለናል፡- «*በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር*

*ለባለባቸው፣ ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ* » ዕብ. 13÷17::

ሰይጣን፣ ከሌሎች ምዕመናን፣ ከክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያን) ጋር ያልተ ቆራኙ፣ ከእግዚአብሔር ቤተሰብ የተነጠሉ እና ለቤተክርስቲያን መሪዎች የማይታዘዙ አማኞች፣ ዘዴውን የሚቋቋሙበት መከላከያና አቅም የሌላቸው መሆናቸውን ስለሚያውቅ ይወዳቸዋል::

## ሁሉም ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው

የጤናማ ቤተክርስቲያን አባል መሆን፣ ጤናማ ሕይወት ለመኖር አስፈላጊ መሆኑን፣ *ዓላማ መር ቤተክርስቲያን* በሚለው መጽሐፌ ውስጥ ገልጫለሁ:: መጽሐፉን እንደምታነበው ተስፋ አደርጋለሁ:: እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያዘጋጃቸውን አምስት ዓላማዎች ለማከናወን እንድትችል ትረዳህ ዘንድ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተበትን ሁኔታ እንድታውቅ ይረዳሃል:: ቤተክርስቲያንን የመሠረታት አምስቱንም ጥልቅ ፍላጐቶችህን ማለት:- ልትኖርበት የሚገባ ዓለማ፣ አብረሃቸው የምትኖራቸው ሰዎች፣ የምትኖርባቸው መርሆዎች፣



በሥራ የምትገልጠው እምነት፣ እና የምትኖርበት ኃይል የሚሉትን እንድትሰጥህ ነው:: እነዚህን አምስት ጥቅሞች አንድ ቦታ የምታገኝበት ሌላ ሥፍራ በዓለም ውስጥ የለም::

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ ያሉት ዓላማዎች፣ ለአንተ ካሉት አምስት ዓለማዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው:: አምልኮ ወደ እግዚአብሔር *እንድታተኩር*፣ ህብረት ደግሞ *የሕይወትን ችግሮች እንድትጋፈጥ* ያግዝሃል፤ ደቀ መዝሙርነት *እምነትህን ያጠነክረዋል*፤ አገልግሎት *ተሰጥኦህን እንድትገነዘብ*፤ የወንጌል ሥራ ደግሞ *ተልዕኮ ህን እንድትፈጽም* ይረዱሃል:: በምድር ላይ ቤተክርስቲያንን የመሰለ ምንም የለም!

## ምርጫህ

ህፃን በሚወለድበት ጊዜ ሁሉ ወዲያውኑ የዓለም አቀፉ ሰብዓዊ ፍጡር አባል ይሆናል:: ያው ህፃን፣ ጤናማና ጠንካራ ሆኖ ለማደግ እንዲችል፣ በጥንቃቄ የሚያሳድገው የአንድ ቤተሰብ አባል መሆንም ያስፈልገዋል:: በመን ፈሳዊ ሕይወት ያለው ሁኔታም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ዳግም በተወለድህ ጊዜ ወዲያውኑ የዓለም አቀፉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ትሆናለህ:: በአ ጥቢያ ደረጃ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል መሆንም ያስፈል ግሃል::

የቤተክርስቲያን *ስብሰባዎች ተካፋይ* በመሆንና የቤተክርስቲያን *አባል በመሆን*

መካከል ያለው ልዩነት እራስን የመስጠት ጉዳይ ነው። የስብሰባ ተካፋዮች ዳር ሆነው ተመልካቾች ሲሆኑ፣ አባላት ግን በቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ናቸው። ተካፋዮች ተቀባዮች፣ አባላት ደግሞ አስተ ዋጽዖ አድራጊዎች ናቸው። የስብሰባ ተካፋዮች የሃላፊነቱ ተጋሪዎች ሳይሆኑ፣ የቤተክርስቲያኒቱ ተጠቃሚዎች ለመሆን ይፈልጋሉ። እንዲህ ያሉት ሰዎች ጋብቻ ሳይመሠርቱ አብረው ለመኖር የሚፈልጉ ጥንዶችን ይመስላሉ።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆኑ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ምንድነው? አባልነትህ በአሳብ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባራዊ ተሳትፎ ከመንፈ ሳዊያን ወንድሞችህና እህቶችህ ጋር የተቆራኘህ መሆንህን ስለሚያረጋግጥ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው፣ ሰዎችን *እንዳሉ* እንጂ *ፍፁማን* እስኪሆኑ ጠብቀህ እንድትወዳቸው አይደለም። ፍፁም የሆነች ቤተክርስቲያን ፍለጋ ዕድሜህን ልታሳልፍ ትችላለህ፤ ግን አታገኝም። እግዚአብሔር እንዳደረገው፣ ፍጹማን ያልሆኑ ኃጢአተኞችን እንድትወድ ነው የተጠራኸው።

ሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደምናነበው፣ ኢየሩሳሌም ውስጥ የነበ ሩት ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው በጥብቅ የተቆራኙና ለህብረታቸው የታ መኑ ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*በሐዋርያት ትምህርትና በህብረት፣ እንጀራንም በመቁረስ በየጸሎቱ ይተጉ ነበር*» ሐዋ. 2፥42። ዛሬም እግዚአብ ሔር ተመሣሣይ ነገር እንድታደርግ ይፈልግብሃል።

የክርስትና ሕይወት፣ እራስን ለክርስቶስ መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ ለሌሎች ክርስቲያኖች መሰጠትንም ይጨምራል። የመቄዶንያ ክርስቲያኖች ይህን ተረ ድተው ነበር። ጳውሎስ ስለ እነርሱ እንዲህ ብሏል፡- «*በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፣ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ* » 1ቆሮ. 8፥5። የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆንህ ቀጥሎ የሚከናወን ድርጊት ነው። እራስህን ለክርስቶስ በመስጠት ክርስቲያን ትሆናለህ፤ የአንድ የአማኞች ህብረት አባል በመሆን ደግሞ የቤተክርስቲያን አካል ትሆናለህ። የመጀመሪያው ውሳኔህ ድነትህ ነው፣ ሁለተኛው ደግሞ ህብ ረትን ያስገኝልሃል።

## አሥራ ሰባተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የማገባ ጉዳይ:-** እንዳምን ብቻ ሳይሆን አካል እንድሆንም ነው የተጠራሁት።

**ላስታውሰው የማገባ ጥቅስ:-** *«እንዲሁም ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤ እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን»* ሮሜ. 12÷5።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** አጥቢያ ቤተክርስቲያኔ ውስጥ ያለኝ የተሣትፎ ደረጃ፣ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ የምወድና እራሴን አሳልፌ የሰጠሁ መሆኔን ይገልጣል?

# 18

# ሕይወትን በጋራ መኖር

*እንደ አንድ አካል ሆናችሁ የተጠራችሁበት*
*የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ::*
*ቆላ. 3፥15*

*ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት ቢኖሩ፣ እንዴት መልካም ነው!*
*ምንኛስ ደስ ያሰኛል!*
*መዝ. 133፥1*

ሕይወት በጋራ የምንኖረው ነው::

የእግዚአብሔር አሳብ ሕይወትን እንድንጋራ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ እንዲህ ያለውን የጋራ ልምምድ *ህብረት* ይለዋል:: ይሁን እንጂ ቃሉ ዛሬ በአብዛኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙን አጥቷል:: «ህብረት» የሚለው ቃል በተለምዶ ዛሬ የሚገልጠው፣ ውይይትን፣ ማህበራዊነትን፣ ምግብንና ጫወታን ሆኗል:: «ህብረት የምታደርገው የት ነው?» የሚለው ጥያቄ ትርጉም፣ «የትኛው ቤተክርስቲያን ነው የምትካፈለው?»፤ «ከዚህ በኋላ ለህብረት ጊዜ ወደኋላ ቅሩ»፤ በአብዛኛው «በጋራ ለሚቀማመሰው ቀላል ምግብ ቆዩ» እንደማለት ነው::

እውነተኛ ህብረት በአምልኮ አገልግሎት ስብሰባዎች ጊዜ ብቅ ከማለት እጅግ ይበልጣል - *ሕይወትን በጋራ መለማመድ* ነው:: ይህ ደግሞ፣ ፍጹም ፍቅርን፣ በታማኝነት መጋራትን፣ ተግባራዊ አገልግሎትን፣ መስዋዕታዊ መስጠትን፣ በርህራሄ ሌላውን ማጽናናትን፣ እና አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች የ«እርስ በርሳችሁ» ትእዛዛት ያካትታል::

ስለ ህብረት በምንነጋገርበት ጊዜ መጠን ወሳኝ ስለሆነ፣ *አነስተኛ ቁጥር ይመረጣል::* ብዙ ቁጥር ካለው ሕዝብ ጋር ለማምለክ ትችላለህ፤ እንዲህ ካለው ጉባኤ ጋር ህብረት ልታደርግ ግን አትችልም:: አንድ ቡድን ወይም የሰዎች ስብስብ ከአሥር ያህል በላይ ከሆነ፣ ከመካከላቸው አንድ


ሰው ተሳትፎውን ያቆማል፡፡ ይህም በአብዛኛው ከሁሉ ዝምተኛ የሆነ ሰው ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ጥቂት ሰዎች ቡድኑን ይቆጣጠሩታል፡፡

ኢየሱስ ጥቂት ደቀ መዛሙርት ባሉበት ቡድን ውስጥ አገልግሏል፡፡ ብዙ ደቀ መዛሙርት ሊመርጥ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን አባላት ሁሉ መካፈል በሚኖርባቸው ቡድን ውስጥ፣ አሥራ ሁለት ከፍተኛ ቁጥር መሆኑን ተረድቷል፡፡

የክርስቶስ አካል፣ ልክ እንዳንተው አካል፣ የብዙ ጥቃቅን ህዋሳት ስብስብ ነው፡፡ የክርስቶስ አካል ሕይወት፣ እንዳንተው ሕይወት፣ ሕዋሳቱ ውስጥ ነው ያለው፡፡ በመሆኑም፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን፣ በቤት ለቤት ህብረት፣ በእሁድ ትምህርት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና በመሳሰሉት የቤተርስቲያኑ አነስተኛ ቡድኖች ውስጥ መሣተፍ ያስፈልገዋል፡፡ እውነተኛ ህብረት የሚኖረው በትላልቅ ስብሰባዎች ሳይሆን፣ እንዲህ ባሉት ቡድኖች ውስጥ ነው፡፡ ቤተክርስቲያንህን እንደ መርከብ ብታስባት፣ ትንንሾቹን ቡድኖች ደግሞ፣ መርከቡ ላይ እንዳሉ የአደጋ ጊዜ መንሳፈፊያ ጀልባዎች ልትቆጥራቸው ትችላለህ፡፡

ትንንሽ የአማኞች ቡድኖችን በተመለከተ፣ እግዚአብሔር የሚያስደንቅ ታላቅ ተስፋን ሰጥቶናል:- «*ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁ*» ማቴ. 18÷20፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ግን፣ በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ብትሆንም እንኳን እውነተኛውን ህብረት የማግኘት ዋስትና አይኖርህም፡፡ ብዙ የእሁድ ትምህርት ክፍሎችና አነስተኛ ቡድኖች፣ ላይ ላዩን በሆነ የማስመሰል ህብረት ተይዘው፣ እውነተኛው ህብረት ምን እንደሚመስል ፍንጩ የሌላቸው ሆነዋል፡፡ ትክክለኛ ባልሆነውና በሆነው ህብረት መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው?

**ትክክለኛ ህብረት ያላቸው ሰዎች በእውነተኛነት ላይ የተመሠረተ ህብረትን ይለማመዳሉ፡፡** እውነተኛነት ያለበት ህብረትን የይስሙላና ላይ ላዩን አይደለም፡፡ እውነተኛ፣ ልብ ለልብ እና ከአንጀት የሆነ መጋራት ነው፡፡ ህብረቱ ሊኖር የሚችለው፣ ሰዎች ስለ ማንነታቸውና በሕይወታቸው በመከናወን ላይ ስላለው ነገር ሐቀኞች ሲሆኑ ነው፡፡ እንዲህ በሚሆኑበት ጊዜ ጉዳታቸውን ይጋራሉ፣ ስሜታችውን ይገልጣሉ፣ ፍርሃታቸውን ያምናሉ፣ ደካማነታቸውን ይቀበላሉ፡፡ እንዲያ በማድረግም እርዳታና ጸሎት ይጠይቃሉ፡፡



እውነተኛነት አንዳንድ አቢያተክርስቲያን ውስጥ ከምናገኘው ነገር ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ እውነተኛና ትሁት በሆነ ህብረት ፋንታ፣ ማስመሰል፣ ግብዝነት፣ ያልተገባ ተወዳጅነትን መፈለግ፣ የይስሙላ

ትህትናና ከልብ ያልሆነ ንግግር ይታያሉ። ሰዎች ማንነታቸውን ለመሸፈን ጭምብል ያጠልቃሉ፣ ራሳቸውን ይደብቃሉ፣ ነገር ሁሉ በሕይወታቸው የተመቻቸላቸው መስለው ለመታየት ይሞክራሉ። እንዲህ ያሉት አዝማሚያዎች ለእውነተኛ ህብረት ሞት ናቸው።

እውነተኛ ህብረት የሚኖረን ሕይወታችንን ግልጥ ስናደርግ ብቻ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ፥ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በርሳችን ህብረት አለን፥ ... ኃጢአት የለብንም ብንል እራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በኛ ውስጥ የለም»* 1ዮሐ. 1+7-8። ዓለም፣ ጥልቅ ወዳጅነት የሚገለጠው በጭለማ ነው ብላ ታስባለች፤ እግዚአብሔር ግን በብርሃን የሚሆን ነው ይላል። ጭለማ መጎዳታችንን፣ ስሕተታችንን፣ ፍርሃታችንን እና ጉድለታችንን ይደብቅልናል። በብርሃን ግን ሁሉንም ግልጥ እናደርጋቸውና እውነተኛ ማንነታችንን አምነን እንቀበላለን።

*እውነተኛ ህብረት የሚኖረው፥ ሰዎች ማንነታቸውንና በሕይወታቸው በመከናወን ላይ ያለውን ነገር በታማኝነት ሲገልጡ ነው።*

እርግጥ ነው፣ እውነተኛነት ብርታትና ትህትናን ይጠይቃል። እራሳችንን የመግለጥ ፍርሃታችንን፣ ማንነታችን ቢገለጥ ሰዎች የሚያገለግሉንና እንደገና የምንጎዳ መሆናችንን ሁሉ መጋፈጥን ይጠይቃል። ለምን ብለን ነው ለዚህ ዓይነቱ አደጋ ራሳችንን የምናጋልጠው? ለመንፈሳዊ እድገትና ለጤናማ ስሜት ብቸኛው መንገድ ይህ ብቻ በመሆኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል :- *«ስለዚህ ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ጸልዩ»* ያዕ. 5+16። ችግሮችን በመጋፈጥ ብቻ ነው የምናድገው። ከሁሉ የሚጠነክረው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ፣ ለራሳችንና ለሌሎች እውነተኛና ግልጥ መሆን ነው።

ሰዎች በእውነተኛ ህብረት ዓማካይነት መደጋገፍን ይለምዳሉ። መደጋገፍ የመስጠትና የመቀበል ጥበብ፣ እንዲሁም መተጋገዝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ይህንም ያደረገው በአካል ብልቶች መካከል መለያየት ሳይኖር፥ እርስ በርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው።»* 1ቆሮ. 12+25። መደጋገፍ የህብረት ዋና ነገር ሲሆን፣ እርስ በርስ የመረዳዳት ግንኙነትንና ኃላፊነት መካፈልን ይገነባል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *« ይኸውም እናንተና እኔ በእያንዳንዳችን እምነት እርስ በርሳችን እንድንበረታታ ነው»* ሮሜ 1+12።

ሁላችንም ሌሎች አብረውን ሲጓዙና ሲያበረታቱን በእምነታችን ይበልጥ የፀናን እንሆናለን። የጋራ ተጠያቂነት፣ መበረታታት፣ አንዱ ሌላውን

ማገልገል እና መከባበር እንዲኖር መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል ሮሜ 12÷6:: «አንዳችን ለሌላችን» እና «እርስ በርሳችን» የተለያዩ ነገሮችን እንድናደርግ አዲስ ኪዳን ውስጥ ከአምሳ ጊዜ በላይ ታዞናል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትን፣ እርስ በርሳችን የምንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ»* ሮሜ 14÷19::

ክርስቶስ አካል ውስጥ ለሆነ ሰው ሁሉ ኃላፊነት የለብህም፤ ለእነርሱ ግን ተጠያቂነት አለብህ:: እነርሱን ለመርዳት የተቻለህን ሁሉ እንድታደርግ ላቸው እግዚአብሔር ይፈልጋል::

**በእውነተኛ ህብረት አንዱ የሌላውን ችግር እንደራሱ ያየዋል::** ይህ ማለት ምክር ወይም ፈጣንና የታይታ የሆነ እርዳታ ማድረግ አይደለም:: የሌሎችን ስቃይ መጋራት ነው:: የሌላው ችግር የሚሰማው ሰው :- «ያለህበትን ሁኔታ አውቃለሁ፤ የሚሰማህ ነገር ያልተለመደ ወይም እብደት አይደለም» ይላል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- « ... *የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ምርጦች እንደመሆናችሁ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ ጨዋነትንና ትዕግሥትን ልበሱ»* ቆላ. 3÷12::

አንዱ የሌላውን ችግር መረዳቱ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ሰብዓዊ ፍላጎቶችን ያገለግላል:: እነሱም ሰዎች እንዲረዱን መፈለግና፣ ስሜታችንን እንዲገነዘቡልን መሻታችን ናቸው:: የአንድን ሰው ስሜት በተረዳህለትና «የተሰማህ ስሜት አግባብ ነው» ባልከው ጊዜ ሁሉ ህብረትን ትመሠርታለህ:: አስቸጋሪው ነገር፣ አስቀድመን ለሰዎች ርህራሄያችንን ለመግለጥ ጊዜ እስከማይኖረን ድረስ ችግራቸውን ለመፍታት መጣደፋችን ነው:: ወይም በራሳችን ችግሮች አእምሮአችን ይያዛል:: ለራስ ብቻ የሚደረግ ሀዘኔታ፣ ለሌሎች ሊደረግ የሚገባ ርህራሄን ያደርቀዋል::

የተለያዩ የህብረት ደረጃዎች አሉ:: እያንዳንዱም ለተለያዩ ጊዜያት ተስ ማሚ ነው:: ቀላሎቹ የህብረት ደረጃዎች፣ *ያለንን እርስ በርስ የምንጋራባቸውና* የእግዚአብ ሔርን ቃል *የምናጠናባቸው* ናቸው:: ጠለቅ ያለው የህብረት ደረጃ፣ *በሚሲዮናዊ ተልዕኮ ወይም በበጎ አድራጎት* ፕሮጀክት አብረን በምናገለግልበት ጊዜ የሚኖረን ነው:: ከሁሉ የሚበልጠውና አስቸጋሪው የህብረት ደረጃ ደግሞ *የመከራ ህብረት፣* ፊልጵ. 3÷10፤ ዕብ. 10÷33-34 ነው :: በዚህ ጊዜ ነው በእርስ በርሳችን ስቃይና ሐዘን ውስጥ የምንገባውና ሸክማችንን የምን

> *የአንድን ሰው ስሜት በተ ረዳህለትና የተሰማህ ስሜት አግባብ ነው ባልከው ጊዜ ህብ ረትን ትገነባለህ::*

ጋራው። ይህን የህብረት ደረጃ በጣም የሚገነዘቡት፣ በዓለም ዙሪያ ተሠራጭ ተው የሚሰደዱ፣ የሚናቁና እና ብዙ ጊዜ ስለ እምነታቸው መስዋዕት የሚሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያዛል፡- *«አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፤ በዚ ህም ሁኔታ የክርስቶስን ሕግ ትፈፅማላችሁ»* ገላ. 6÷2። ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ አንዳችን ሌላችንን የምንፈልገው፣ በከባድ ችግር፣ ሐዘንና ጥርጣሬ ጊዜ ነው። ሁኔታዎች ሲጫኑንና እምነታችን በሚዋዥቅበት ደረጃ ላይ ስንደርስ ነው አማኝ የሆኑ ወዳጆች ይበልጥ የሚያስፈልጉን። ስለ እኛ በእግዚአብሔር የሚታመኑና እጃችንን ይዘው ወደ ፊት እንድንጓዝ የሚረዱን ጥቂት ወዳጆች ያሉበት አንድ ቡድን ያስፈልገናል። ጥቂት ሰዎች ባሉበት ቡድን ውስጥ ከሆንን፣ ከእግዚአብሔር የራቅን በሚመስለን ጊዜ እንኳን የክርስቶስ አካል የሆነው ህብረት እውንና የሚጨበጥ ይሆንልናል። ኢዮብ በመከራው ጊዜ በጣም ያስፈለገው ነገር ይህ ነበር። በመሆኑም እንዲህ በማለት ጮኸ፡- *«ለወዳጁ በጎነት የማያሳይ ሰው፣ ሁሉን የሚችለውን አምላክ መፍራት ትቶአል »* ኢዮብ 6÷14።

**እውነተኛ ህብረት ውስጥ ሰዎች ምህረትን ይለማመዳሉ።** ህብረት፣ ስህተ ቶች የሚስተናገዱበት ሳይሆን፣ የሚወገዱበት የፀጋ ሥፍራ ነው። ህብረት የሚኖረው፣ ምህረት ፍርድን በሚያሸንፍበት ጊዜ ነው።

ሁላችንም ምህረት ያስፈልገናል። ምክንያቱም ሁላችንም ተንገዳግደን የምን ወድቅ ነን፤ በመሆኑም ተነስተን ጉዟችንን ለመቀጠል እንድንችል እርዳታ ያስፈ ልገናል።

> አሥራ ስምንተኛ ቀን
> ሕይወትን በጋራ መኖር

አንዳችን ሌላችንን ይቅር ለማለትና ይቅርታም ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን ያስፈልገናል። እግዚአ ብሔር እንዲህ ይላል፡- *«ደግሞም ከልክ በላይ ለሐዘና ተሰፋ እንዳይቆርጥ፣ ይቅር ልትሉትና ልታጽናኑት ይገባ ችኋል»* 2ቆሮ. 2÷7።

ያለ ይቅርታ ህብረት ሊኖርህ አይችልም። እግዚ አብሔር «ቂም እንዳንይዝ» ቆላ. 3÷13 ያስጠነቅቀ ናል። ምክንያቱም መራርነትና ቁጣ ሁል ጊዜ ህብረትን ያፈርሳሉ። ፍፁማን ያልሆንን እና ኃጢአተኞች ስለሆንን፣ ለብዙ ጊዜ አብረን በምንሆንበት ጊዜ አን ዳችን ሌላችንን መጉዳታችን አይቀርም። አንዳንዴ ሆን ብለን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በስህተት እርስ በርሳችን እንጎዳዳለን። በዚያም ሆነ በዚህ፣ ህብረትን ለመፍጠ ርና ለማቆየት ብዙ ይቅርታና ፀጋ ያስፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ

ይላል:- «እርስ በርሳችሁ ተቻቻሉ፣ ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅር የተሰኘበት ነገር ቢኖር ይቅር ተባባሉ፤ ጌታ ይቅር እንዳላችሁ፣ እናንተም ለሌላው ይቅር በሉ » ቆላ. 3፥13::

ከእግዚአብሔር ያገኘነው ይቅርታ፣ ለሌሎች ይቅርታ እንድናደርግ ያነሳሳ ናል:: እግዚአብሔር ካደረገልህ ይቅርታ ይበልጥ ለሌላ ሰው እንድታደርግ በፍ ፁም የማትጠየቅ መሆንህን አስታውስ:: በአንድ ሰው ጉዳት በሚደርስብህ ጊዜ፣ ኃይልና ስሜቶቼን ለበቀል ልጠቀምባቸው ወይስ ለእርቅ? ከሚሉት አማራ ጮች አንዱን ትወስናለህ:: ሁለቱንም ልታደርግ አትችልም::

ብዙ ሰዎች ሰውን በማመንና ይቅርታ በማድረግ መካከል ያለውን ልዩነት ስለማይረዱ፣ ለበደላቸው ሰው ይቅርታ ለማድረግ አይፈልጉም:: ይቅርታ ያለፈ ነገርን መተው ነው:: ማመን ግን የወደፊት ባሕርይን ነው የሚያመለክ ተው::



ይቅርታ፣ አንድ ሰው ጠየቀም አልጠየቀ፣ ወዲያውኑ መከናወን አለበት:: በዳዩን የማመኑ ነገር ግን ከጊዜ ጋር የሚያድግ ነው:: ማመን ያለፈ ታሪክን ይፈልጋል:: አንድ ሰው በተደጋጋሚ ሲበድልህ በደሉቹን ወዲያውኑ ይቅር እንድትል በእግዚአብሔር ብትታዘዝም፣ መበደሉን እንዲቀጥል እንድትፈቅድለት ግን አይጠበቅብህም:: በዳዮችህ ከጊዜ በኋላ የተለወጡ መሆናቸውን በድርጊታቸው ማስመስከር አለባቸው:: የታጣን መታመን ለመመለስ የሚቻልበት ከሁሉ የተሻለ ሥፍራ፣ ማበረታታ ትና ተጠያቂነት ያለበት አነስተኛ የህብረት ቡድን ነው::

እውነተኛ ህብረት ያለበት አነስተኛ ቡድን አካል በመሆን የምታገኛቸው ሌሎች ጥቅሞችም አሉ:: ህብረት ችላ ልትለው የማይገባና የክርስትና ሕይወ ትህ ጠቃሚ ክፍል ነው:: ክርስቲያኖች ከ2000 ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ አነስ ተኛ ቡድኖች ውስጥ ህብረት ለማድረግ ሲሰበሰቡ ኖረዋል:: እስከ ዛሬ እንዲህ ያለው ቡድን አካል ካልሆንክ፣ የሚጎድልህን ነገር በትክክል አላወቅህም::

ከሌሎች አማኞች ጋር እንዲህ ያለውን ህብረት ለመመሥረት በሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ በሚቀጥለው ምዕራፍ፣ እንነጋገራለን:: ይህ ምዕራፍ ግን እውነ ተኛ ህብረት ያሉትን ቁም ነገሮች፣ ማለት መተማመን፣ የጋራነት ስሜት፣ ርህራሄ፣ እና ይቅርታን እንድትራብ እንዳደረገህ ተስፋ አደርጋለሁ:: የተፈጠ ርከው ለህብረት ወይም ለማህበራዊ ኑሮ ነው::

## አሥራ ስምንተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ላስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** በሕይወቴ ሌሎች ሰዎች ያስፈልጉኛል።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፤ በዚህም ሁኔታ የክርስቶስን ሕግ ትፈጽማላችሁ»* ገላ. 6÷2።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ :-** ይበልጥ እውነተኛና ልብ ለልብ በሆነ ደረጃ ከሌሎች አማኞች ጋር ህብረት ለመፍጠር ዛሬ ልሄደው የምችለው አንድ እርምጃ ምንድነው?

# 19

# ህብረትን ማሳደግ

*የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉ በሰላም ይዘራል::*

*ያዕ. 3÷18*

*እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በህብረት፣ እንጀራውንም በመቁረስና በጸሎት ይተጉ ነበር::*

**የሐዋ. 2÷42**

ህብረት መስጠትን ይጠይቃል::

በአማኞች መካከል እውነተኛ ህብረትን ለመመሥረት የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ህብረቱን የሚያሳድገው ግን ከምናሳየው ምርጫና መስጠት በመነሣት ነው:: ጳውሎስ:- «*በሰላም ማሰሪያ የመንፈ ስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ*» ኤፌ. 4÷3 ሲል፣ ይህንኑ ጣምራ ኃላፊነት ማመልከቱ ነበር:: ፍቅር ያለበትን ክርስቲያናዊ ህብረት የመመሥረቱ ጉዳይ፣ የእግዚአብሔርን ኃይልና የኛንም ጥረት ይጠይቃል::

አሳዛኙ ነገር ግን፣ ብዙ ሰዎች ጤናማ ግንኙነት በሌለበት ቤተሰብ ውስጥ በማደጋቸው ምክንያት፣ ለእውነተኛ ህብረት አስፈላጊ የሆነው እውነተኛ የግንኙነት ጥበብ ይጎድላቸዋል:: በመሆኑም እንዲህ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ከሌሎች ጋር እንዴት መቀራረብና መኖር እንደሚገባቸው መማር ይኖርባቸዋል:: ጥሩው ነገር፣ አዲስ ኪዳን ሕይ ወትን በመጋራት ለመኖር በሚቻልበት ትምህርት የተሞላ ነው:: ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጽፏል:- «*ይህንንም የምጽፍልህ፣ ብዘገይ እንኳ ሰዎች በእግ ዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንድታውቅ ነው:: ቤቱም የህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ... ነው*» 1ጢሞ. 3÷14-15::

እውነተኛ ያልሆነ ህብረት አባል መሆኑ ከሰለቸህ፣ ባለህበት አነስተኛ ህብ ረት፣ በሰንበት ትምህርት ክፍልና ቤተክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ ህብረትና ፍቅር እንዲኖር ከፈለግህ፣ ጠንካራ ምርጫ ማድረግና ጉዳት ሊያመጡ የሚ

ችሉ ነገሮችንም ለመቀበል መወሰን አለብህ::

**ህብረትን ማጉልበት እውነተኛነትን ይጠይቃል::** አንድን ችግር ሽፋፍኖ ማለፍ ወይም መተው የተሻለ ምርጫ በሚሆንበት ጊዜ እንኳን፣ እውነትን በፍቅር መናገር ይኖርብሃል:: በዙሪያችን ያሉ ሰዎች እራሳቸውን ወይም ሌሎችን ኃጢአታዊ በሆነ መንገድ ሲጎዱ በማየት ዝም ማለቱ በጣም ቀላል ቢሆንም፣ ድርጊቱ ግን የፍቅር አይደለም:: ብዙ ሰዎች እውነቱን እስከመንገር ድረስ (ነገሩ የማያስደስት ቢሆንም እንኳን)፣ የሚያፈ ቅራቸው ወዳጅ የላቸውም:: በመሆኑም ሕይወታቸውን አጥፊ በሆነ አካሄዳቸው ይገፉታል:: አንድን ሰው ምን ልንለው እንደሚገባ ብናውቅም፣ እንዳንናገር ፍርሃታችን ያግደናል:: ብዙ ህብረቶች በፍርሃት ተጎድተዋል:: የቡድኑ አባል የሆነ ሰው ሕይወት ሲፈራርስ እየተመለከተ እንኳን ለመናገር የሚደፍር አባል የለም::



መጽሐፍ ቅዱስ:- *«እውነትን በፍቅር እየተናገርን»* ኤፌ. 4÷15 ይላል:: ምክን ያቱም ያለ ግልጥነት ህብረት ሊኖረን አይችልም:: ሰሎሞን እንዲህ ብሏል:- *«እውነተኛ መልስ መስጠት ከንፈርን እንደመሳም ነው»* ምሳሌ 24÷26 :: የዚህ ቃል ትርጉም አንዳንድ ጊዜ፣ ኃጢአት በማድረግ ወይም ለማድረግ በመፈተን ላይ ያለን ሰው ፊት ለፊት በፍቅር ለመገሰጽ ጥረት ማድረግ ማለት ነው:: ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- *«ወንድሞች ሆይ፣ አንድ ሰው በኃጢአት ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት ይገባል»*

ገላ. 6÷1::

ብዙ የቤተክርስቲያን ህብረቶችና አነስተኛ ቡድኖች አለመግባባትን ስለሚ ፈሩ የይስሙላ ህብረቶች ሆነው ይኖራሉ:: አለመግባባትን ወይም ውጥረትን የሚያስነሳ ጉዳይ ብቅ ሲል፣ ሽፋፍኖ ለማለፍ ይሞከራል:: ይህ ድርጊት የሚፈጥረው የውሸት ሰላም ነው:: *«ሰላማችንን አታናጋው»*፣ የሚል አንድ ሰው ከመካከላቸው ይነሣና፣ በቁጣ ፀጉሩ የቆመውን ሰው ሁሉ ያቀዘቅዘዋል:: በዚ ህም ምክንያት ችግሩ ሳይፈታ፣ አባላቱ በውስጣቸው ቅሬታ እንደያዙ ይኖ ራሉ:: ስለ ችግሩ ሁሉም ያውቃሉ፤ ነገር ግን ማንም ደፍሮ በግልጥ አይና ገርም:: ድርጊቱ ታዲያ ሃሜት የሚስፋፋበትን ጤናማ ያልሆነ ምስጢራዊ ሁኔታ ይፈጥራል:: ጳውሎስ እንዲህ ላለው ሁኔታ የሰጠው መፍ ትሔ ቀጥተኛና እንዲህ የሚል ነበር:- *«ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀር ታችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ»* ኤፌ. 4÷25::

*አለመግባባቶች በተገቢው መንገድ መፍትሔ ሲያገኙ፣ እርስ በርሳችን ይበልጥ እንቀራረባለን::*

እውነተኛ ህብረት፣ በጋብቻ፣ በጓደኝነት ወይ በቤተክርስቲያን ቢሆን፣ የሚፀናው በግልጥነት ነው። እንደውም በማንኛውም ግንኙነት አለመግባባት የሚያመራው ወደ በለጠ ወዳጅነት ነው። ለግንኙነታችሁ መሰናክሎች የሆኑትን ነገሮች በግልጥ ተነጋግሮ ለመፍታት ግድ ብሏችሁ ጥረት ካላደረጋችሁ፣ ይበልጥ ለመቀራረብ አትችሉም። አለመግባባቶች በተገቢው መንገድ መፍትሔ ሲያገኙ፣ እርስ በርሳችን ይበልጥ እንቀራረባለን። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ሰውን የሚገስጽ ውሎ አድሮ ይወደዳል*» ምሳ. 28÷23።

ግልጥነት፣ የፈለከውን ነገር፣ በፈለከው ሥፍራና ጊዜ ያለ ሥርዓት እንድ ትናገር የሚፈቅድልህ ልዩ ፈቃድ አይደለም። ማንኛውንም ነገር የማድረጊያ ትክክለኛ ጊዜና መንገድ ያለ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፣ መክ. 8÷6። ያለ ጥንቃቄ የሚነገሩ ቃላት የማይሽር ቁስል ይፈጥራሉ። ቤተክርስቲያን ውስጥ እርስ በርሳችን እንደተፋቃሪ የቤተሰብ አባላት እንድንነጋገር እግዚአብሔር እንዲህ ብሎናል:- «*አረጋዊውን ሰው እንደ አባትህ ቆጥረህ ምከረው እንጂ በኃይለ ቃል አትናገረው። ወጣት ወዳጆችን እንደ ወንድሞች ተቀበላቸው፤ እንዲሁም አሮጊቶችን እንደ እናቶች፣ ወጣት ሴቶችን እንደ እህቶች በፍፁም ንጽሕና አስተናግዳቸው*» 1ጢሞ. 5÷1-2።

በሺህ ሚቆጠሩ ህብረቶች ከእውነተኛነት መታጣት የተነሣ ፈርሰዋል። የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ህብረታቸው ውስጥ ሥነ-ምግባር የጎደለው ድርጊት ሲፈፀም ተመልክተው ዝም በማለታቸው፣ ጳውሎስ ገስጿቸዋል። ችግሩን ፊት ለፊት ለመቃወም ድፍረት ያለው ሰው ባለመኖሩ፣ እንዲህ አላቸው:- «*በመካከላችሁ የዝሙት ርኩሰት እንዳለ ይወራል፤ እንዲህ ያለው ርኩሰት በአረማውያን ዘንድ እንኳ የማይታይ ነው፤ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው አለና። ደግሞም ታብያችኋል! ይልቅስ ሀዘን ተሰምቷችሁ፣ ይህን ድርጊት የፈፀመውን ሰው ከመካከላችሁ ልታስወግዱት አይገባምን? ምንም እንኳን እኔ በአካል አብሬያችሁ ባልሆንም፣ በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ልክ አብሬያችሁ እንዳለሁ ሆኜ፣ ይህን ባደረገው ሰው ላይ አሁኑኑ ፈርጄበታለሁ። በምትሰበሰቡበት ጊዜ እኔም በመንፈስ ከእናንተ ጋር ስለምሆን፣ በጌታችን በኢየሱስ ስምና በመካከላችሁ በሚገኘው በጌታችን በኢየሱስ ኃይል፣ ሥጋው ጠፍቶ መንፈሱ በጌታ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ዓይነቱ ለሰይጣን ይሰጥ። በመካከላችሁ መልካም አይደለም። ጥቂት እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካው አታውቁምን? አሁን ያለ እርሾ እንደሆናችሁ ሁሉ አዲስ ሊጥ እንድትሆኑ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ የፋሲካ በጋችን የሆነው ክርስቶስ ተሰውቶአልና። ስለዚህ በዓሉን ግፍና ክፋት በሞላበት እርሾ፣ በአሮጌው እርሾ ሳይሆን፣ እርሾ በሌለበት ቂጣ በቅንነትና በእውነት እናክብር። ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልዕክቴ ጽፌላችሁ ነበር። እንዲህም ስል በጠቅላላው ከዚህ ዓለም ሴሰኞች፣ ወይም ስግብግቦችና ቀማኞች ወይም ከጣዖት አምላ*

*ኪዎች ጋር እትተባበሩ ለማለት አይደለም፣ እንደዚያማ ቢሆን ከዚህ ዓለም ወጥቶ መለየት ያስፈልጋችሁ ነበር። ነገር ግን አሁን የጻፍሁላችሁ «ወንድም ነኝ» እያለ ከሚሰስን ወይም ከሚስገበገብ ወይም ጣዖትን ከሚያመልክ ወይም ከሚሳደብ ወይም ከሚሰክር ወይም ከሚቀማ ጋር እንዳትተባበሩ ነው። ከእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ጋር ምግብ እንኳ አትብሉ። ከቤተክርስቲያን ውጪ ባሉት ሰዎች ላይ ለመፍረድ እኔን ምን አገባኝ? በቤተክርስቲያን ባሉት ሰዎች ላይ እናንተ አትፈርዱምን?»* 1ቆሮ. 5÷1-12።

ህብረትን ማሳደግ፣ ትሁት መሆንን ይጠይቃል። እራስን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ ግብዝነት እና እብሪታዊ ኩራት፣ ከምንም በፈጠነ ሁኔታ ህብረትን ያፈርሳሉ። ኩራት ወይም ትዕቢት በሰዎች መካከል ግድግዳን ሲገነባ፣ ትህትና ደግሞ ድልድይ ይሠራል። ትህትና ግንኙነቶችን የሚያለሰልስና የሚያረጋጋ ዘይት ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ፡- *«እርስ በርስ በመከባበር ትሕትናን ልበሱ»* 1ጴጥ. 5÷5 የሚለው። የህብረትህ ትክክለኛ ልብስ ትሁት መንፈስ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው ቁጥር ቀሪ ንባብ እንዲህ ይላል፡- *«እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፣ ለትሁታን ግን ፀጋን ይሰጣል»።* ትሁት የምንሆንበት ሌላ ምክንያት ይህ ነው። ኩራት፣ ለእድገት፣ ለለውጥ፣ ለፈውስ እና ሌሎችን ለመርዳት እንድንችል ሊኖረን የሚገባንን የእግዚአብሔር ፀጋ ከሕይወታችን ያግደዋል። የእግዚአብሔርን ፀጋ የምንቀበለው፣ የሚያስፈልገን መሆኑን በትህትና ስንገልጥ ነው። ኩራት ባደረብን ጊዜ ሁሉ፣ አኗኗራችን እግዚአብሔርን *የሚቃወም* እንደሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጣል። ይህ ሞኝነት ያለበትና አደገኛ የሕይወት አቀጣጫ ነው።

ደካማነትህን በመቀበል፣ የሌሎችን ድካም በመታገስ፣ ለመታረም ዝግጁ በመሆን እና ለሌሎች ከበሬታን በመስጠት ትህትናን በቀላሉ ልታደብር ትችላለህ። ጳውሎስ እንዲህ በማለት ምክር ይለግሳል፡- *«እርስ በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ። ዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ እንጂ አትኩሩ፤ በራሳችሁም አትመኩ »* ሮሜ 12÷16። ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ ደግሞ እንዲህ ብሏል፡- *«በእራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ። እያንዳንዳችሁ ለሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ»* ፊልጵ. 2÷3-4።

> *ትህትና ራስን ትንሽ አድርጎ መመልከት ሳይሆን፣ ለሌሎች ይበልጥ ማሰብ ነው።*

ትህትና ራስን ትንሽ አድርጎ መመልከት ሳይሆን፣ ለሌሎች ይበልጥ ማሰብ ነው። ትሁት ሰዎች ትኩረታቸው ሌሎችን ማገልገል ነው፤ ስለ ራሳቸው

አያስቡም።

ህብረትን ማሳደግ መቻቻልን ይጠይቃል። ይህም ልዩነታችንን መቀበል፣ አንዱ ለሌላው ስሜት መጠንቀቅ እና የሚያናድዱንን ሰዎችንም መታገስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ለማነፅ፣ እርሱንም ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል»* ሮሜ 15፥2። ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡- *«እንዲሁም በማንም ላይ ክፉ እንዳይናገሩ፣ ሰላማውያን እንዲሆኑ፣ ለሰዎች ሁሉ ከልብ የመነጨ ትሕትና እንዲያሳዩ አስገንዝባቸው»* ቲቶ 3፥2።

አሥራ ዘጠነኛው ቀን

ህብረትን ማሳደግ

በየትኛውም ቤተ ክርስቲያንና በማንኛውም አነስተኛ ቡድን ውስጥ ቢያንስ አንድ «አስቸጋሪ» ሰው አለ፤ አብዛኛውን ጊዜ ከአንድ በላይ። እንዲህ ያሉ ሰዎች ምናልባት የተለዩ ስሜታዊ ፍላጎቶች፣ ጥልቅ ፍራቻ፣ የሚያናድድ ፀባይ ወይም ዝቅተኛ የመግባባት ችሎታ ያላቸው ይሆናሉ። «የበለጠ ፀጋ የሚያሻቸው ሰዎች» ልትላቸው ትችላለህ።

እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች በመካከላችን የሚያኖራቸው ለእነርሱም፣ ለኛም ጥቅም ነው። የእድገት መልካም ዕድሎችና የህብረት መፈተኛዎች ናቸው። እንደ ወንድምና እህቶቻችን እንወዳቸዋለን? እናከብራቸዋለን?

አንድ ቤተሰብ ውስጥ ተቀባይነትህ የሚወሰነው፣ በጉብዝናህ፣ በውበትህ ወይም ባለህ ተሰጥኦ ሳይሆን፣ አንዳችን የሌላችን በመሆናችን እውነት ላይ ተመሥርቶ ነው። ቤተሰብን እንከላከላለን፤ እንጠብቃለን። የቤተሰቡ አንድ አባል ሞኛሞኝ ይሆን ይሆናል፤ ግን ከእኛ አንዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እርስ በርሳችሁ በወንድማማች መዋደድ አጥብቃችሁ ተዋደዱ»* ሮሜ 12፥10።

እውነቱ፣ ሁላችንም ጥሩ ያልሆነና የሚያናድድ ባህርይ ያለን መሆናችን ነው። አንድ ህብረተሰብ ውስጥ መሆንና የሚስማማና የሚጣጣም ባህርይ ባለበት መሆን የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የህብረታችን መሠረቱ ከእግዚአብ ሔር ጋር ያለን ግንኙነት ነው፤ ቤተሰብ ነን።

የመግባባታችን አንዱ ቁልፍ፣ ሰዎች ከየት እንደሚመጡ መረዳቱ ነው፤ ታሪካቸውን እወቅ። የነበሩበትን ሁኔታ ስታውቅ፣ ይበልጥ የምትረዳቸው ሰው ትሆናለህ። ወደ ፊት ምን ያህል ይቀራቸዋል በማለት ፈንታ፣ ጉዳት እየደረሰባቸው ቢሆንም እንኳን እዚህ የደረሱት ምን ያህል ተጉዘው ነው ብለህ አስብ።

የመግባባትና የመከባበር ሌላ ጎኑ፣ የሌሎች ሰዎችን ጥርጣሬዎች አለማ ጣጣል ነው። አንተ የማትፈራውን ነገር ሌላ ሰው ቢፈራው፣ ፍርሃቱ አግባብ

የለውም ማለት አይደለም። እውነተኛ ህብረት ሊኖር የሚችለው፣ ሰዎች በሚ ናገሩት ነገር ሌሎች ይፈርዱብኛል የሚል ስጋት ሳያድርባቸው ጥርጣሬና ፍር ሃታቸውን ለመግለጥ የሚችሉ መሆናቸውን ሲረዱ ነው።

**ህብረትን ማሳደግ፣ ምስጢር መጠበቅን ይጠይቃል።** ሰዎች ግልጥ የሚ ሆኑት፣ እንዲሁም የተጎዱበትን ጥልቅ ነገር፣ ፍላጎታቸውን፣ ምስጢራቸው ንና ድካማቸውን ለሌሎች የሚያካፍሉት፣ የፍቅር አቀባበልና አስተማማኝ ምስጢር ጠባቂነት ያለበት ጤናማ ሁኔታ ሲያገኙ ነው። ምስጢር ጠባቂነት ሲባል፣ ወንድምህ ወይም እህትህ ኃጢአት ሲሠሩ አይተህ ዝም ማለት አለ ብህ ማለት አይደለም። ቡድኑ ውስጥ የተገለጠ ነገር እዚያው መቅረት አለ በት፤ ቡድኑም ጉዳዩን እራሱ ማየት እንጂ፣ በአሉባልታ መልክ ምስጢሩን ለሌ ሎች ማካፈል አይገባውም።

እግዚአብሔር ሐሜትን ይጠላል። በተለይ የሌላ ሰው ችግር «የጸሎት ጥያቄ» የሚያስመስለው ቀለም ተቀብቶ ሲቀርብ አይወድም። እንዲህ ይላል:- «*ጠማማ ሰው ጠብን ይዘራል፤ ሐሜተኛም የቅርብ ወዳጆችን ይለያያል*» መዝ. 16÷28። ሐሜት፣ ጉዳትና መከፋፈልን ያመጣል፤ ህብረትንም ያፈርሳል።

*ከገለሰብ ይልቅ የቤተ ክርስቲያኒቱ ህብረት ይበልጣል።*

በመሆኑም በክርስቲያኖች መካከል የመከፋፈል ምክንያት የሚሆኑ ሰዎችን ፊት ለፊት እንድንቋቋማ ቸው እግዚአብሔር በግልጥ ይናገራል ቲቶ 3÷10። እንዲህ ያሉ ሰዎች፣ የመከፋፈል ድርጊታቸውን ስትቋቋምባቸው ይናደዱና ህብረቱን ወይም ቤተ ክርስቲያኒቱን ትተው ይሄዱ ይሆናል፤ ቢሆንም ከግለሰብ ይልቅ የቤተክርስቲያኒቱ ህብረት ይበልጣል።

**ህብረትን ማጠናከር አዘውትሮ መገናኘትን ይጠይቃል።** እውነተኛ ህብረትን ለመገንባት፣ ከቡድንህ ጋር የማያቋርጥና ቋሚ ግንኙነት ሊኖርህ ይገባል። ህብረቶች ጊዜ ይወስዳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል:- «*አንዳንዶች ማድ ረጉን እንደተውት መሰብሰባችንን አንተው፤ ይልቁንም ቀኑ እየተቃረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችን እንበረታታ*» ዕብ. 10÷25። የመሰብሰብ ልማድን ማዳበር ይኖርብናል። ልማድ የምታዘወትረው እንጂ፣ አልፎ አልፎ የምታደርገው አይደለም። ጥልቅ ግንኙነት ለመመሥረት ከሰዎች ጋር *ብዙ ጊዜ* ማሳለፍ አለብህ። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ህብረት ሥር የማይሰደው በቂ የጋራ ጊዜ ስለማይኖረን ነው። የጋራ ጊዜ ቢኖረን እንኳን፣ የምናሳልፈው የአንድን ሰው ንግግር በማድመጥ ነው።

ህብረት («መሰብሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ሲሰማን እንሰበሰባለን») በማለት ምቹ ጊዜ ተፈልጎ የሚደረግ ሳይሆን፣ ለጤናማ መንፈሳዊነት ያስፈልገኛል በሚል

እምነት ላይ የሚመሠረት ነው። እውነተኛ ህብረትን ለማዳበር ከፈለግህ አስፈ ላጊ በማይመስልህ ጊዜ እንኳን ከአባላት ጋር መሰብሰብ አለብህ። ይህን የም ታደርገው፣ አስፈላጊ ነው ብለህ በማመንህ ነው። የመጀመሪያ ክርስቲያኖች በየቀኑ ይሰበሰቡ ነበር፡- «*በየዕለቱ በቤተ መቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸ ውም እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር* » የሐዋ. 2÷46።

የአንድ አነስተኛ ቡድን ወይም ክፍል አባል ከሆንክ፣ ዘጠኙን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ህብረት ባህርያት የሚያካትት የቡድን ቃል ኪዳን እንድታደርጉ አበ ረታታለሁ። እነርሱም፡- እውነተኛ ስሜቶቻችንን እንጋራለን (እውነተኛነት)፣ እርስ በርሳችን እንበረታታለን (የአብሮነት ስሜት)፣ እንረዳዳለን (ርህራኄ)፣ ይቅር እንባባላለን (ምህረት)፣ እውነትን በፍቅር እንናገራለን (ታማኝነት)፣ ድካ ማችንን እንቀባበላለን (ትህትና)፣ ልዩነታችንን እንቀበላለን (መከባበር)፣ ሐሜት አይኖርም (ምስጢር ጠባቂነት)፣ እና ለህብረቱ ቅድሚያ መስጠት (አዘውታሪ ነት) ናቸው።

የባህርያቱን ዝርዝር በምትመለከትበት ጊዜ፣ እውነተኛ ህብረት በብዛት የማይታይበት ምክንያት ግልጥ ይሆንልሃል። እውነተኛ ህብረት ማለት፣ ለእርስ በርስ መደጋገፍ ስንል እራስ ወዳድነትንና ነፃነታችንን መተው ማለት ነው። ሕይወትን የመጋራት ፋይዳ ከምንከፍለው ዋጋ እጅግ ይልቃል፣ ለመንግሥተ ሰማያትም ያዘጋጀናል።

## አሥራ ዘጠነኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ህብረት መስጠትን ይጠይቃል::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስሳልፎ ስለሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደሆነ በዚህ እናውቃለን፣ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል »* 1ዮሐ. 3፥16::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** አለሁበት ቡድንና ቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ የእውነተኛ ህብረት ባህርያት ያድጉ ዘንድ ለመርዳት የምችለው እንዴት ነው ?

20

# የፈረሰ ህብረትን ማደስ

*ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ በማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፣ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን።*

**2ቆሮ. 5÷18**

የሻከሩ ግንኙነቶች ሁል ጊዜ መታደስ ይገባቸዋል።

ሕይወት ማፍቀርን የምንማርበት በመሆኑ፣ ለግንኙነቶች ዋጋ እንድንሰጥና አንዳች መሽካከር፣ጉዳት ወይም ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ትተን ዞር ከማለት ይልቅ ጠብቀን ለመቆየት ማንኛውንም ጥረት እንድናደርግ እግዚአብሔር ይፈልጋል። እንደውም መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን፣ ግንኙነቶችን የማደስ አገልግሎት የተሰጠን መሆኑን ነው ኤፌ. 4÷3። በዚህም ምክንያት፣ የአዲስ ኪዳን ብዙ ክፍል፣ አንዳችን ከሌላችን ጋር የምንኖርበትን ሁኔታ ለማስተማሪያነት ውሏል። ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጽፏል፦ «*ከክርስቶስ ጋር ካላችሁ አንድነት የተነሣ የትኛውም መበረታታት፣ ከፍቅር የሆነ መጽናናት፣ የመንፈስ ህብረት፣ ምሕረትና ርኅራኄ ካላችሁ፣ በአንድ ፍቅር በአንድ መንፈስና በአንድ ዓላማ በመሆን ደስታዬን ፍፁም አድርጉልኝ*» ፊልጵ. 2÷1-2። ከሌሎች ጋር የመኖር ችሎታችን የመንፈሳዊ ብስለታችን ምልክት መሆኑን ጳውሎስ አስተምሮናል ሮሜ 15÷5።

ቤተሰቦቹ የሆንን እኛ እርስ በርሳችን ባለን ፍቅር እንድንታወቅ ክርስቶስ ስለሚፈልግ ዮሐ. 13÷35፣ የፈረሰ ህብረት በማያምኑ ሰዎች ዘንድ አሳፋሪ ምስክርነት ነው። ለዚህ ነበር ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት

በከፍተኛ ፀብ በመከፋፈል ላይ በሆኑና በፍርድ ቤት በተካሰሱ ጊዜ ቅር በመሰኘት እንዲህ በማለት የጻፈላቸው:- «ይህንንም የምለው ላሳፍራችሁ ብዬ ነው:: ለመሆኑ ከመካከላችሁ ወንድሞችን ለማስታረቅ የሚበቃ አስተዋይ ሰው የለምን? » 1ቆሮ. 6÷5:: የተፈጠረውን ችግር በሰላም ለመፍታት የሚችል ሰው ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አለመኖሩ አስደነገጠው:: በዚያው ደብዳቤ እንዲህ አለ:-«አንድ ልብ አንድ ሐሳብ እንዲኖራችሁ እንድትስማሙ እለምናችኋለሁ » 1ቆሮ. 1÷10::

የእግዚአብሔርን በረከት ከፈለግህና እንደ እርሱ ልጅነት ለመታወቅ ከፈለግህ አስታራቂነትን መማር አለብህ:: ኢየሱስ እንዲህ አለ:- «የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» ማቴ. 5÷9:: አስተውል፣ ኢየሱስ:- «ሰላም ወዳዶች ብፁዓን ናቸው » አላለም:: ምክንያቱም ሰው ሁሉ ሰላምን ይወዳል:: ወይም «ሰላማውያን ብፁዓን ናቸው» አላለም:: እንዲህ ያሉ ሰዎች በምንም ነገር ሰላማቸው አልተናጋም:: ኢየሱስ ያለው:- «ለሰላም የሚሠሩ ብፁዓን ናቸው» ነው:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ፀበኞችን ለማስታረቅ ተግተው ይሻሉ:: ማስታረቅ ከባድ ተግባር ስለሆነ፣ አስታራቂዎች ብርቅ ናቸው::

የተፈጠርከው፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ለመሆን ነው:: በመሆኑም በምድር ላይ የመኖርህ ሁለተኛ ዓላማ ከሌሎች ጋር መቀራረብንና መውደድን ለመማር ስለሆነ፣ ልታዳብራቸው ከሚገቡ ታላላቅ ክህሎቶች አንዱ ማስታረቅ ነው:: የሚያሳዝነው ነገር ግን፣ ግጭት ማስወገድን ብዙዎቻችን በፍጹም አልተማርንም::



ማስታረቅ ግጭትን መሸሽ አይደለም:: ከችግር መሸሽ፣ የሌለ ማስመሰል፣ ወይም ስለ ችግሩ ለመናገር አለመድፈር ፈሪነት ነው:: የሰላም ልዑል ኢየሱስ ግጭትን ፈጽሞ አልፈራም:: አንዳንድ ጊዜ ለሁሉም ይበጅ ዘንድ አለመግባባትን ቀስቅሷል:: አንዳንዴ ግጭትን ወይም አለመግባባትን ማስወገድ፣ አንዳንዴ ግጭትን መፍጠር፣ አንዳንዴ ደግሞ ማስታረቅ ያስፈልገናል:: ለዚህ ነው ለማያቋርጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጸለይ የሚኖርብን::

ሰላምን መፍጠር ላልተግባባነው ሰው የፈለገውን ማድረግ አይደለም:: ሁል ጊዜ ስለመሸነፍ፣ በር ላይ እንዳለ ምንጣፍ ስለ መረገጥ፣ እና ሰዎች ሁል ጊዜ እንደ ፈለጋቸው እንዲያደርጉብህ ስለ መፍቀድ አልነበረም ኢየሱስ የተናገረው:: እርሱም ብዙ ጉዳዮችን በዝምታ አላለፋቸውም፤ በክፉ ተቃውሞዎች ፊት በፅናት ቆመ እንጂ::

## ግንኙነትን የማደሻ መንገድ

በአማኝነታችን የተሰጠን አገልግሎት :- « *ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ ... የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን»* 2ቆሮ. 5÷18:: ህብረትን የማደሻ ሰባት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደረጃዎች ቀጥሎ ያሉት ናቸው::

**ሰውዬውን ከማናገርህ በፊት እግዚአብሔርን አናግር::** ችግሩን ለእግዚአ ብሔር አዋየው:: ለሌላ ወዳጅህ ከማማትህ በፊት ስለ ችግሩ ብትጸልይ፣ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ወይ ያንተን ልብ፤ ወይም ያለ አንተ እርዳታ ሰውዬውን ሲለውጠው ታያለህ:: ስለ ግንኙነቶችህ ብዙ ብትጸልይ፣ ግንኙነቶችህ ሁሉ ያለ ችግር ይቀጥላሉ::

*ህያኛ ቀን የፈረሰ ህብረትን ማደስ*

ዳዊት በመዝሙሮቹ እንዳደረገው ወደ ላይ ጸልይ:: ተስፋ ያስቆረጡህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ንገረው:: ወደ እርሱ ጩኽ :: በቁጣ፣ በጉዳት፣ በፍርሃት፣ እና በማና ቸውም ሌሎች ስሜቶችህ በፍጹም አይደነቅም፣ ወይም አይበሳጭም:: በመሆኑም የሚሰማህን በትክክል ንገረው::

ብዙዎቹ ግጭቶች ወይም አለመግባባቶች የሚበቅሉት፣ ባልተሟሉ ፍላጎቶች ምክንያት ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ፍላጎቶች የሚሟሉት በእግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ብቻ ሊያሟላው የሚቻለውን ፍላጎት፣ ባልንጀራህ፣ የትዳር ጓደኛህ፣ አለቃህ፣ ወይም ከቤተሰብህ አንዱ እንዲያሟላልህ የምትጠብቅ ከሆንህ እራስህን ለብስጭትና ለምሬት በማዘጋጀት ላይ ነህ:: ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያስፈልጉህን ነገሮች ሁሉ ለማሟላት የሚችል የለም::

ብዙዎቹ አለመግባባቶቻችን የሚፈጠሩት፣ ባለመጸለያችን መሆኑን ሐዋርያው ያዕቆብ ሲገልጥ እንዲህ ብሏል:- *«በእናንተ መካከል ያለው ጠብ ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚዋጉት ምኞቶቻችሁ አይደለምን? ትመኛላችሁ ነገር ግን አታገኙም»* ያዕ. 4÷1-2:: ወደ እግዚአብሔር በመመልከት ፈንታ፣ ደስተኞች ያደርጉን ዘንድ ወደ ሌሎች እንመለከትና፣ ሲተውን ወይም ሳይሳካላቸው ሲቀር እንናደዳለን:: *«ለምን መጀመሪያ ወደ እኔ አትመጣም?»* ይላል እግዚአ ብሔር::

**ሁል ጊዜ የመጀመሪያውን እርምጃ ውሰድ::** ጎዳም ሆንክ ተጎዳ፣ የመጀመሪያውን እርምጃ አንተ እንድትወስድ እግዚአብሔር ይፈልጋል:: ሌላ ሰው እንዲያደርግልህ አትጠብቅ:: ቀድመህ ወደ እነርሱ ሂድ:: የፈረሰ ግንኙነትን ማደስ በጣም ትልቅ ቁም ነገር ነው:: ድርጊቱ በጋራ ከማምለክ በፊት እንዲከናወን ኢየሱስ እንዲህ በማለት አዟል:- *«ስለዚህ መባህን*

*በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፥ መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤ በመጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ»* ማቴ. 5÷23-24::

ህብረት ሲቀዘቅዝ ወይም ሲፈርስ፣ ወዲያውኑ የሰላም ስብሰባ አቅድ:: ነገ ተነገወዲያ አትበል፤ ምክንያትም አትፍጠር ወይም «አንድ ቀን አደርገዋ ለሁ» እያልክ ቃል አትግባ:: በተቻለ ፍጥነት ፊት ለፊት ተገናኝተህ ለመነጋገር ቀጠሮ ያዝ:: መዘግየት ቁጣን አባብሶ ነገሮችን የከፉ ያደርጋ ቸዋል:: በግጭት ወይም አለመግባባት ወቅት ጊዜ የሚፈውሰው ነገር የለም:: ይልቁንም ጉዳቶች እንዲያመረቅዙ ያደርጋቸዋል::

በፍጥነት እርምጃ መውሰድ፣ የሚደርስብህን መንፈሳዊ ጉዳትም ይቀንስ ልሃል:: ኃጢአት፣ መፍትሄ ያላገኙ ግጭቶችን ጨምሮ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ህብረት የሚዘጋና ጸሎቶቻችንም እንዳይመለሱ የሚያደርግ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጣል 1ጴጥ. 3÷7፤ ምሳሌ 28÷9፤ ሕይወታች ንንም ያመሰቃቅለዋል:: የኢዮብ ወዳጆች እንዲህ በማለት አስታወሱት:- *«ሞኝን ሰው ብስጭት ይገድለዋል፤ ቂሉንም ቅናት ያጠፋዋል»* ኢዮብ 5÷2 ::

የመሰብሰቢያውን ትክክለኛ ጊዜና ሥፍራ መምረጥ ለሰላም ጉባኤ ውጤ ታማነት ወሳኝ ነው:: እንዳችሁ እንኳን ከደከማችሁ፣ በጥድፊያ ላይ ከሆናችሁ ወይም የምታቋርጡት ከሆነ ስብሰባውን አትጀምሩ:: ከሁሉም የሚሻለው ጊዜ ሁለታችሁም ሲመቻችሁ ነው::

**ስሜታቸውን በርህራሄ ተረዳላቸው ::** ከመናገር ይልቅ አድምጥ:: ለማን ኛውም አለመግባባት መፍትሄ ከመስጠትህ በፊት፣ ሰዎች ስሜታቸውን በሚ ገልጡበት ጊዜ አድምጣቸው:: ጳውሎስ እንዲህ በማለት ምክር ለግሷል:- *«እያንዳንዳችሁ ለሱችን የሚጠቅመው ንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ»* ፊልጵ. 2÷4:: *«አይመልከት»* የሚለው ቃል ስኮፓስ ከሚለው ግሪክኛ የተመለሰ ሲሆን፣ መመልከት ተብሏል:: *ቴሌስኮፕ* ወይም *ማይክሮስኮፕ* የሚለው እንግሊዝኛ ቃል የተወሰደውም ከዚሁ ነው:: የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም በትኩረት ተመልከት ማለት ይሆናል:: ለእውነቶቹ ሳይሆን፣ ለስሜታቸው ትኩረት ስጥ:: መፍትሄ በመስጠት ሳይሆን፣ በርህራሄ ጀምር::

> *የመጀመሪያውን እርምጃ አንተ እንድትወስድ እግዚአብሔር ይፈልጋል::*

ሰዎችን ስታነጋግር፣ መጀመሪያ ከሚሰማቸው ስሜት ልታወጣቸው አትሞክር:: አድምጣቸውና ስሜታቸውን ሳይደብቁ ዝርግፍ አድርገው እንዲያወጡት ፍቀድላቸው:: በሚሉት ነገር ባትስማማም የሚናገሩት የገባህ መሆኑን በሚታይ ምልክት ግለጥላቸው:: ስሜቶች ብዙ ጊዜ እውነት ወይም ተገቢ አይሆኑ ይሆናል:: እንደውም ቁጣ እንደሞኝ እንድናስብና እንድናደርግ ይገፋፋናል:: ዳዊት እንዲህ በማለት ያለበትን ጉድለት ገልጧል:- *«ስሜት የለሰውና ሰባዋቂ ሆንሁ፤ በፊትህም እንደ እንስሳ ሆንሁ»* መዝ. 72÷22:: ሁላችን ጉዳት በሚደርስብን ጊዜ እንደ አውሬ እንቆጣ ይሆናል::

በአንጻሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ሰውን ጠቢብ ሰእምርው ከቁጣ ያዘገዮዋል፤ ሰበደሰኛውም ይቅር ደል ዘንድ ክብር ይሆንሰታል*» ምሳሌ 19÷11:: ትዕግሥት ከጥበብ፣ ጥበብ ደግሞ የሌሎችን አሳብ ከማዳመጥ ይገኛሉ:: አንድን ሰው በምናደምጠው ጊዜ:- «ለአስተያየትህ ትልቅ ዋጋ እሰጠዋለሁ፤ ግንኙነታችንን እፈልገዋለሁ፣ ታስፈልገኛለህ» ማለታችን ነው:: «ሰዎች፣ ስለ እነርሱ ግድ እንደሚለን እስካላወቁ ድረስ፤ እኛ ስለምናውቀው ነገር ግድ አይኖራቸውም::» የሚለው የተለመደ አባባል እውነትነት አለው::

አንድነትን ስለማደስ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ሰማነጽ፤ እርሱንም ሰመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል* » ሮሜ 15÷2:: የሌሎችን ቁጣ በትእግሥት መቀበሉ፣ መስዋዕትነት ይጠይቃል፤ በተለይ ቁጣው መሠረት የሌለው ሲሆን:: ኢየሱስ ለአንተ ሲል የከፈለው ዋጋ ይህ መሆኑን አስታውስ:: አንተን ለማዳን ሲል መሠረት የሌ ለውና ተንኮል የተሞላበት ቁጣ በተሰነዘረበት ጊዜ በዝምታ ችሎታል:: «*ክርስቶስ ራሱን ደስ አሳሰኘምና፤ ነገር ግን አንተን የነቀፉበት ስድብ በእኔ ላይ ደረሰብኝ ተብሎ እንደተጻፈ ሆነበት*» ሮሜ 15÷3::

በአንተ በኩል ላለው ግጭት (አለመግባባት)፣ ንስሀ ግባ:: ግንኙነትን ለማደስ እርግጠኛ ፍላጎት ካለህ፣ የራስህን ስህተቶችና ኃጢአት በማመን



መጀመር አለብህ:: ድርጊቱ ነገሮችን አጥርቶ የመመልከቻ መንገድ መሆኑን ኢየሱስ እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «*አንተ ግብዝ፤ አስቀድመህ በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ፤ ከዚያም በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ሰማውጣት አጥርተህ ታያለህ*» ማቴ. 7÷5::

ሁላችንም ለኛ የማይታዩን ድካሞች አሉብን:: በመሆኑም፣ ግጭት ወይም አለመግባባት ከፈጠርክበት ሰው ጋር ከመገናኘትህ በፊት፣ ያንተን ድርጊቶች የሚመዝንልህ የሌላ ሦስተኛ ሰው እርዳታ መጠየቁ

ያስፈልግህ ይሆናል። በተጨማሪም ከችግሩ ምን ያህሉ የአንተ ጥፋት መሆኑን ያሳይህ ዘንድ እግዚአብሔርን ለምነው። «የችግሩ ፈጣሪ እኔ ነኝ? በተጨባጭ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረትኩ፣ ለሌላው ስሜት ግድ የሌለኝ፣ ወይም በጣም ስሜታዊ ነኝ?» በልና እራስህን ጠይቅ። በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም»* 1ዮሐ. 1÷8 ።

ንስሀ እርቅን የማምጫ ጠንካራ መሣሪያ ነው። ብዙ ጊዜ፣ ከዋናው ጉዳት ይልቅ ግጭቱን ለመፍታት የምንሞክርበት መንገድ የበለጠ ጉዳት ያስከትልብ ናል። ስህተትህን በትህትና መቀበል በምትጀምርበት ጊዜ፣ ድርጊትህ እራሱን በመከላከል አቋም ይቀርባል ብለው ይጠብቁህ የነበሩትን ሰዎች ቁጣ ያበርደውና አንተን ለማጥቂያነት ያዘጋጁትን መሣሪያ ያስጥላቸዋል። ለጥፋትህ ምክን ያት አትደርድር ወይም ከተጠያቂነት ለመሸሽ በሌላ አታሳብ። በግጭቱ ውስጥ ለተጫወትከው ሚና ጥፋተኛነትህን በታማኝነት ተቀበል። ለስህተትህ ኃላፊነትን ተቀበልና ይቅርታ ጠይቅ።

**ችግሩን እንጂ፣ ሰውዬውን አትቃወም።** ወቀሳን ወይም ተጠያቂነትን ለማስወገድ ብዙ ከደከምክ፣ ችግሩን ልትፈታ አትችልም። ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«የለዘበ መልስ ቁጣን ያበርዳል፤ ክፉ ቃል ግን ቁጣን ያጥራል»* ምሳሌ 15÷1። አሳብህን በፍፁም በቁጣ ለመግለጥ ስለማትችል፣ የምትጠቀምባቸውን ቃላት በመምረጡ ረገድ ብልህ ሁን። ከአሽሙር ንግግር ይልቅ፣ ለስላሳ መልስ ሁል ጊዜ ይሻላል።

ግጭትን በመፍታት ጊዜ፣ አንድን ነገር የምትገልጥበት ሁኔታ የምትገ ልጠውን ነገር ያህል ጠቃሚ ነው። በሚያስከፋ ሁኔታ ከገለጥከው፣ ተቀባዩ ወገን የሚቀበለው በተከላካይነት ነው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- *«ልባቸው ጠቢብ የሆነ አስተዋዮች ይባላሉ፤ ደስ የሚያሰኙ ቃላትም እውቀትን ያዳብራሉ»* ምሳሌ 16÷21። ጭቅጭቅ አይጠቅምም። ክፉ ተናጋሪ ከሆንክ፣ በፍጹም አሳማኝ ልትሆን አትችልም።

> *ግጭትን በመፍታት ጊዜ የምትገልጥበት ሁኔታ፣ ምትገልጠውን ነገር ያህል ጠቃሚ ነው።*

በኮሙኒስቱና በምዕራቡ መንግሥታት መካከል ቀዝቃዛው ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ጊዜ፣ አንዳንድ ጦር መሣሪያዎች በጣም አጥፊ ስለ ሆኑ፣ ፍጹም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሁለቱ ወገኖች ተስማምተው ነበር። ዛሬ ደግሞ ኬሚካላዊና ባዮሎጂካል መሣሪያዎች ታግደዋል። የተከማቹ የኑክሊየር መሣሪያዎችም በመቀነስና ከጥቅም ውጭ በመሆን ላይ ናቸው።

አንተም ለህብረት ስትል፣ የግንኙነት የኒውክሊየር የጦር መሣሪያዎችህ የሆኑትን ማለት ማውገዝን፣ ንቀትን፣ ማነፃፀርን፣ ስም ማጥፋትን፣ ስድብን፣መኩራራትን እና አሽሙረኛነትን ማጥፋት አለብህ። ጳውሎስ በዚህ አካኋን ያጠቃልለዋል:- *«ለሚሰሙት ፀጋን ይሰጥ ዘንድ፣ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ፣ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ »* ኤፌ. 4÷29።

**የተቻለህን ያህል ተባበር።** ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *«ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ»* ሮሜ 12÷18። ሰላም ሁልጊዜ ዋጋ ያስከፍላል። አንዳንድ ጊዜ ትምክህታችንን፣ ሁል ጊዜ ደግሞ እራስ ወዳድነታችንን እንድንተው ያስገድደናል። ለህብረት ስትል ለመደራደር፣ ከሌሎች ጋር ለመግባባት፣ እና ለፍላጎታቸው ቅድሚያ ለመስጠት የተቻለህን ሁሉ አድርግ፤ ሮሜ 12÷10፤ ፊልጵ. 2÷3። ከኢየሱስ የተራራ ላይ ስብከቶች አንዱ፣ ቀለል ባለ ሁኔታ ሲገለጥ እንዲህ የሚል መልእክት አለው:- *«ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና።»* ማቴ. 5÷9።

**ከውሳኔ ይልቅ ለእርቅ ትኩረት ስጥ።** ሰው ሁሉ በሁሉ ነገር ላይ ይስማማል ብሎ መጠበቅ ከእውነታ መራቅ ነው። እርቅ በግንኙነት ወይም በህብረት፣ ውሳኔ ግን በችግሩ ላይ ነው የሚያተኩሩት። በእርቅ ላይ በምናተኩርበት ጊዜ፣ የችግሩ ግዝፈት እየቀነሰ ይሄድና ብዙ ጊዜ ረብ የለሽ ይሆናል።

ልዩነቶችን ለማስወገድ ባንችል እንኳን፣ ግንኙነትን ልናድስ እንችላለን። ብዙ ጊዜ በክርስቲያኖች መሀል ተገቢና ትክክለኛ የሆኑ አለመስማማቶች፣ እንዲሁም የአሳብ መለያየቶች ይኖራሉ። አለመስማማታችን ግን ያለ ጥላቻ ሊሆን ይችላል። አንድ እንቁ ከተለያየ አቅጣጫ ሲታይ የተለየ ገጽታ አለው። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ተመሳሳይነትን ሳይሆን፣ አንድነትን ነው። በመሆኑም በእያንዳንዱ ጉዳይ በልዩነት ሳንፋጠጥ፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን ልንጓዝ እንችላለን።

ይህ ማለት ግን ችግሮችን ያለ መፍትሄ ተዋቸው ማለት አይደለም። ውይይቱን ወይም ክርክሩን መቀጠል ይኖርብህ ይሆናል። ግን በመግባባት መንፈስ አድርገው። እርቅ ማለት ማጥቂያውን መሣሪያ እንጂ፣ የግጭቱ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ቅበረው ማለት አይደለም።

ከዚህ ምዕራፍ በተረዳኸው አሳብ መሠረት ከማን ጋር ለመነጋገር ትፈልጋለህ? ከማን ጋር ነው ህብረትን ለማደስ የምትፈልገው? ይህን ለማድረግ ለሴላ አንድ ሰከንድ እንኳን አትዘግይ። አሳብህን ሰብስብ አድርግና ስለዚያ ሰው ለእግዚአብሔር ንገረው። ከዚያም ስልክ አንሳና ሂደቱን ጀምር።

እነዚህ ሰባት እርምጃዎች ለመረዳት ቀላል ቢሆኑም፣ አስቸጋሪዎች

*እርቅ በእውነተኛ ገን ኙነት ላይ ያተኩራል፤ ውሳኔ ግን በችግሩ ላይ ነው የሚያተኩረው።*

ናቸው። ግንኙነትን የማደስ ሂደት ብዙ ጥረትን ይጠይቃል። ለዚህ ነው ጴጥሮስ፦ «*ከክፉ ፈቀቅ ይበል፤ መልካምንም ያድርግ ዘንድ ሰላምን ይሻ፤ ይከተለውም*» 1ጴጥ. 3፥11 ያለው። ለሰላም በምትሠራበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ያደርገው የነበረውን ነገር በማከናወን ላይ ነህ። ለዚህ ነው እግዚአብሔር የሚያስተራርቁ ሰዎችን ልጆቼ የሚላቸው ማቴ. 5፥9።

ሀያኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፦** ግንኙነቶች ሁልጊዜ ሊታደሱ ይገባል።

**ላስታወሰው የሚገባ ጥቅስ፦** «*በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ*» ሮሜ 12፥18።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፦** የተቋረጠ ግንኙነቴን ዛሬ ማደስ የሚያስፈልገኝ ከማን ጋር ነው?

# 21

# ቤተ ክርስቲያንህን መጠበቅ

*በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት*
*ለመጠበቅ ትጉ ::*

**ኤፌ. 4÷3**

*በእነዚህም ሁሉ ላይ ሁሉን በፍጹም አንድነት የሚያስተ*
*ሳስረውን ፍቅርን ልበሱት ::*

**ቆላ. 3÷14**

የቤተ ክርስቲያንህን አንድነት መጠበቅ የአንተ ሥራ ነው::

የቤተክርስቲያን ውስጥ አንድነት በጣም ትልቅ ነገር በመሆኑ ነው፣ አዲስ ኪዳን ከመንግሥተ ሰማያት ወይም ከገሀነመ እሳት ይበልጥ ትኩረት የሰጠው:: እግዚአብሔር አንደ መሆንንና መስማማትን እርስ በርሳችን እንድን ለማመድ በጣም ይፈልጋል::

አንድነት የህብረት ዋና ነገር ነው:: አንድነትን ብታፈርስ፣ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያን፣ የህልውናዋን ዋና ነገር ታሳጣታለህ:: አንድነት፣ ቤተክርስቲያን ውስጥ በጋራ እንድንኖር እግዚአብሔር ላቀደልን ሕይወት መሠረታዊና ዋና ነገር ነው:: የህብረት ትልቁ ሞዴላችን ሥላሴ ነው:: አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም በሆነ ሁኔታ እንደ አንድ ተባብረዋል:: እግዚአብሔር እራሱ በመስዋዕታዊ ፍቅር፣ ሌሎችን በሚያስቀድም ትህትናና፣ ፍጹም በሆነ ህብረት ከሁሉ የሚበልጥ ምሳሌ ነው::

ሰማያዊው አባታችን እንደማንኛውም ወላጅ ፣ ልጆቹ በፍቅርና በህብረት ሲኖሩ በማየት፣ ደስ ይለዋል:: ኢየሱስ፣ በተልእኮው ፍጻሜ ወቅት፣ ከመታሰሩ ቀደም ብሎ ጥልቅ በሆነ ስሜት ለአንድነታችን ጸልይዋል ዮሐ. 17÷20-23:: በነዚያ የጣር ጊዜያት በአእምሮው የነበረ ከፍተኛ ነገር የህብረ

ታችን ጉዳይ ነበር። ጉዳዩ ታላቅ መሆኑን ከዚህ እንረዳለን።

በምድር ላይ ከቤተክርስቲያኑ ይበልጥ ለእግዚአብሔር ክቡር ነገር የለም። ከሁሉ የላቀ ዋጋ ከፍሎላታል። በመሆኑም በመከፋፈል ምክንያት ከሚመጣ መበታተን፣ ግጭት፣ እና መለያየት እንድትጠበቅ ይፈልጋል። የእግዚአ ብሔር ቤተ ሰብ አባል ከሆንክ፣ አባል የሆንክበትን ህብረት የመጠበቅ ኃላፊ ነት አለብህ። ህብረቱን ለመንከባከብ፣ ፍቅርን ለመጠበቅና ስምምነትን ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ፣ እንዲሁም በሚያ ምኑት መካከል ለማጎልበት የተቻለህን ሁሉ ታደርግ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ተሾመሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አን ድነት ለመጠበቅ ትጉ*» ኤፌ. 4÷3። እንዴት ነው ይህን የምናደርገው? መጽሐፍ ቅዱስ ተገቢውን ምክር ይሰጠናል።

*በምድር ላይ ከቤተክርስቲያኑ ይበልጥ ለእግዚአብሔር ክቡር የሆነ ነገር የለም።*

**በልዩነታችን ሳይሆን፣ አንድ በሚያደርጉን ነገሮች ላይ አትኩር ።** ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡- « *ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና፣ እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ*» ሮሜ 14÷19። በአማኝነታችን አንድ ጌታ፣ አንድ አካል፣ አንድ ዓላማ፣ አንድ አባት፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ ተስፋ፣ አንድ እምነት፣ አንዲት ጥምቀት፣ እና አንድ ፍቅር በጋራ አለን፤ ሮሜ 10÷12፤ 12÷4-5፤ 1ቆሮ. 1÷10፤ 8÷6፤ 12÷13፤ ኤፌ. 4÷4፤5÷5፤ ፊልጵ. 2÷2። አንድ ዓይነት ድነት፣ ሕይወት እና የወደፊት ሁኔታን፣ ማለት ከምንቆጥራቸው ልዩነታችን በጣም የሚበልጡና የምንጋራቸው ነገሮች አሉ። ከልዩነታችን ይልቅ ልናተኩርባቸው የሚገቡ እነዚህ ናቸው።

የተለያየ ማንነት፣ ልምምድ፣ ዘር፣ እና ምርጫ ሊሰጠን የወሰነ እግዚአብ ሔር መሆኑን ማስታወስ አለብን። እናም ልዩነቶቹን በመቻቻል ማለፍ ብቻ ሳይሆን፣ ዋጋ ልንሰጣቸውና በደስታ ልንቀበላቸው ይገባል። እግዚአብሔር ተመሳሳይነትን ሳይሆን፣ ህብረትን ነው የሚወደው። ነገር ግን፣ ለህብረትም ስንል ልዩነቶቻችን እንዲከፋፍሉን መፍቀድ የለብንም። በጣም አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች፣ ማለት ክርስቶስ እንደ ወደደን እርስ በርስ መዋደድን በመማር፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን እና ለቤተክርስቲያኑ ያቀዳቸውን አምስት ዓላማ ዎች በማከናወን ላይ ማተኮር ይኖርብናል።

ግጭት ወይም አለመግባባት፣ ብዙ ጊዜ፣ እምብዛም ወሳኝ ባልሆኑና «*አወዛጋቢ*»፣ ሮሜ 14÷1፤ 2ጢሞ. 2÷23፣ በሆኑ ነገሮች ላይ የማተኮራችን ምልክት ነው። ትኩረታችንን በሰዎች ማንነት፣ ምርጫ፣ ግንዛቤ፣ ሁኔታ

ወይም አደራረግ ላይ ስናሳርፍ፣ ሁልጊዜ መከፋፈል ይመጣል:: እርስ በርስ በመዋደድና የእግዚአብሔርን ዓላማ በማከናወን ላይ ብናተኩር ግን ውጤቱ መስማማት ይሆናል:: ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይማጠናል:- *«አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብ እንዲኖራችሁ፣ እርስ በርሳችሁም እንድትስማሙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ»* 1ቆሮ. 1፥10::

**ከሌሎች በምትጠብቀው ነገር ሚዛናዊ ሁን::** እግዚአብሔር የሚፈልገው እውነተኛ ህብረት ምን መሆኑን በትክክል ስትረዳ፣ ቤተክርስቲያንህ ውስጥ ባለው ሁኔታና እርሱ እንዲሆን በሚፈልገው ነገር መካከል ባለው ክፍተት ምክንያት በቀላሉ ተስፋ ትቆርጥ ይሆናል:: ቢሆንም፣ ምንም እንኳ ፍፁም ባትሆን፣ ቤተክርስቲያንን በከፍተኛ ስሜት ልንወዳት ይገባል:: ሊሆን የሚገባውን በመናፈቅ፣ በትክክል በመከናወን ላይ ያለውን መተቸት የብስለት ጉድለት ማረጋገጫ ነው:: በሌላም በኩል፣ የሚታየውን ጉድለት እንዳለ ተቀብሎ፣ ሊሆን የሚገባውን እውነተኛ ህብረት፣ ለማምጣት አለመትጋት ቸልተኝነት ነው:: ብስለት፣ በመሆን ላይ ባለውና ሊሆን በሚገባው መካከል መኖር ነው::

ሌሎች አማኞች ሊያሳዝኑህና እንደጠበቅካቸው ላይሆኑልህ ይችላሉ::

*ምንም እንኳን ፍፁም ባትሆን፣ ቤተክርስቶያንን በከፍተኛ ስሜት መውደድ አለብን::*

ይህ ድርጊታቸው ግን ከእነርሱ ጋር ያለህን ህብረት እንድታቋርጥ ምክንያት ሊሆን አይገባም:: እንደ ቤተሰብ አባል ባይሆኑል ህም ቤተሰቦችህ ስለሆኑ፣ በቀላሉ ልትለያ ቸው አትችልም:: በዚህ ድርጊት ፋንታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- *«ፍጹም ትሁታንና ገሮች ሁኑ፤ እርስ በርሳችሁም በፍቅር እየተቻቻላችሁ ትዕገሥተኞች ሁኑ»* ኤፌ. 4፥2::

ግልጥ በሆኑ ብዙ ምክንያቶች የተነሣ ሰዎች ስለ ቤተክርስቲያን ግራ የተጋባ አመለካከት ይኖራቸዋል:: ዝርዝሩ በጣም ብዙ ነው፤ ግጭት ወይም አለመግባባት፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች መጎዳት፣ ግብዝነት፣ ችላ መባል፣ ጠባብነት፣ ህግ አጥባቂነትና ሌሎች ኃጢአቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ያኔ ከመደ ንገጥና ከመደነቅ ይልቅ፣ ቤተክርስቲያን እኛን ጨምሮ የኃጢአተኞች ስብስብ መሆኗን ማስታወስ አለብን:: ኃጢአተኞች በመሆናችን፣ አንዳችን ሌላችንን እንጎዳለን፤ አንዳንዴ ሆን ብለን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሳናውቅ:: ቢሆንም ቤተ ክርስቲያኒቱን ትተን ከመሄድ፣ እዚያው ቆይተን ከተቻለ ለችግሩ መፍትሄ መፈለግ ነው ያለብን:: መሸሽ ሳይሆን፣ እርቅ ነው ወደ ብርቱ ባህርይ እና

ጥብቅ ህብረት የመሄጃው መንገድ።

አንድ የሚያሳዝን ወይም ግራ የሚያጋባ ነገር ሲከሰት ከቤተክርስቲያን መለየት በመንፈሳዊ ሕይወት ያለማደግ ምልክት ነው። እግዚአብሔር አንተ ንም ሆነ ሌሎቹን የሚያስተምራችሁ ነገሮች አሉት። ከዚሁ ጋር የሚሸሽባት ፍጹም ቤተክርስቲያን የለችም። እያንዳንዷ ቤተክርስቲያን የራሷ ችግርና ድካም አላት። በመሆኑም ሸሽተህ በሄድክበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ሌላ ቅሬታ ይገጥምሃል።

ግሮቾ ማርክስ የተባለ ሰው፣ አባላችን ሁን በሚለኝ ማናቸውም ክለብ ውስጥ አልገባም፣ በሚለው ንግግሩ ይታወቃል። አንድ ቤተክርስቲያን አንተን በሚያረካ ደረጃ ፍጹም ብትሆን፣ ያ ፍፁምነቷ አንተን አባል እንዳትሆን ያግድሃል። ምክያቱም፣ አንተ ፍፁም አይደለህም!

የናዚን አስተዳደር በመቃወሙ ሰማዕት የሆነው ጀርመናዊ ፓስተር፣ ደየትሪክ ቦንሆፈር፣ ህብረትን አስመልክቶ *የጋራ ሕይወት* በሚል ርዕስ በጣም ጥሩ መጽሐፍ ደርሷል። አለመግባባት፣ በቤተክርስቲያን የምናየው ነገር የሚ ፈጥርብንን ግራ መጋባትና ፍፁምነትን የመፈለግ የተሳሳተ አመለካከት ስለሚ ያጠፋ ጥሩ ነው ይላል፣ መጽሐፉ። ቤተክርስቲያንን እንድንወዳት ፍጹም ልትሆን ይገባታል የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት በመተውና ማስመሰላችንን በማስወገድ፣ ሁላችንም ፍጹምነት የሌለንና ፀጋ የሚያስፈልገን መሆናችንን እንመን። ይህ ነው የእውነተኛ ህብረት ጅማሬ።

ማንኛይቱም ቤተክርስቲያን እንዲህ የሚል ጽሑፍ ፊት ለፊት በርዋ ላይ ልታኖር ትችላለች፦ «ፍጹማን የሆኑ ሰዎች ለአባልነት ማመልከት አያስፈል ጋቸውም፤ ይህ፣ ኃጢአተኛነታቸውን ላመኑ፣ ፀጋ ለሚያስፈልጋቸውና ለማደግ ለሚሹ ሰዎች የተዘጋጀ ሥፍራ ነው »።

ቦንሆፈር እንዲህ ብሏል፦ «ከክርስቲያናዊ ህብረት ይልቅ ስለ ህብረት ያለ ውን ሕልም የሚወድ ሰው፣ ክርስቲያናዊውን ህብረት ያጠፋዋል ... ። ያለ ንበት ህብረት ታላቅ ልምምድና የሚጠቅም ነገር የማናገኝበት፣ በተቃራኒው ብዙ ድካም፣ ጥቂት እምነት፣ እንዲሁም ችግር ያለበት ይሆን ይሆናል። ቢሆንም በየዕለቱ ስለ ህብረታችን ከማመስገን ይልቅ፣ የማይጠቅምና የማይ ረባ ነው እያልን ሁልጊዜ ካጉረመረምን፣ እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንዳያ ሳድግ እንቅፋት እንሆንበታለን።

**ከመንቀፍ ይልቅ፣ ማበረታታትን ምረጥ።** ብተግባር ተሳትፎ የድርሻን ከማ በርከት ይልቅ፣ ዳር ቆሞ በቅንነት የሚያገለግሉ ሰዎችን መንቀፍ ሁል ጊዜ ቀላል ነው። እርስ በርሳችን እንዳንነቃቀፍ፣ እንዳንነፃፀር ወይም አንዳችን በሌ ላችን ላይ እንዳንፈርድ እግዚአብሔር በመደጋገም ያስጠነቅቀናል፣

ሮሜ14፥13፤ ያዕ. 4፥11፤ ኤፌ. 4፥29፤ ማቴ. 5፥9፤ ያዕ. 5፥9:: ሌላ አማኝ በእምነትና በቅንነት የሚያደርገውን በምትነቅፍበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ሥራ ጣልቃ በመግባት ላይ ነህ፣ *«ለባውን በሚያገለግል ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ? እርሱ ቢወድቅ ወይም ቢቆም ለጌታው ነው»* ሮሜ 14፥4::

ፈራጆች እንዳንሆን ወይም አመለካከታቸው ከእኛ የሚለዩ አማኞችን እንዳንንቅ ጳውሎስ እንዲህ በማለት በተጨማሪ ያስጠነቅቀናል:- *«ታድያ አንተ በወንድምህ ላይ ስለምን ትፈርዳለህ? ለምንስ ወንድምህን ትንቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር ወንበር ፊት እንቆማለንና»* ሮሜ 14፥10::

በሌላ አማኝ ላይ በምፈርድበት ጊዜ ሁሉ፣ አራት ነገሮች ወዲያውኑ ይሆናሉ:- ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን ህብረት አጣለሁ፤ ትዕቢተኛና ቅንነት የሌለኝ ሰው መሆኔን እገልጣለሁ፤ እራሴን ለእግዚአብሔር ፍርድ አዘጋጃለሁ፤ እና የቤተክርስቲያኔን አንድነት እጎዳለሁ::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን:- *«የወንድሞቻችን ከሳሽ»* ራዕይ 12፥10 ይለዋል:: ክስ፣ ማማረርና የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላትን መውቀስ የዲያብሎስ ሥራ ነው:: እነዚህን ነገሮች በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ፣ ተታልለን የሰይጣንን ሥራ በማከናወን ላይ ነን:: የቱንም ያህል ባትስማሙ እንኳን፣ ሌሎች ክርስቲያኖች ጠላቶችህ አለመሆናቸውን አስታውስ:: ሌሎች አማኞችን በማነፃፀር ወይም በመንቀፍ የምናባክነው ጊዜ ሁሉ የህብረታችንን አንድነት ለመገንባት የምናውለው ሊሆን በተገባ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ»* ሮሜ 14፥19::

*ሀያ አንደኛ ቀን*

**ቤት ክርስቲያንህን መጠበቅ**

**ለሀሜት ጆሮህን አትስጥ::** ሀሜት፣ የችግር ወይም የመፍትሔው አካል ያልሆነን ዜና ከአንዱ ወደ ሌላው የማስተላለፍ ተግባር ነው:: ሀሜትን ማሠራጨት ስህተት መሆኑን ታውቃለህ፤ ቤተ ክርስቲያንህን ለመጠበቅ ከፈለክ፣ ሀሜትን መስማትም የለብህም:: ሀሜትን ማድመጥ፣ የተሠረቀ ዕቃን እንደመቀበል ስለሚቆጠር፣ ወንጀሉን የሠራህ ያህል ጥፋተኛ ያደርግሃል::

አንድ ሰው መጥቶ ሀሜት ሲጀምርልህ:- «እባክህን አቁም:: እንዲህ ያለውን ነገር ለማወቅ አልፈልግም:: ሰውዬውን በቀጥታ አነጋግረኸዋል?»፣ የማለት ድፍረት ይኑርህ:: ሌሎችን ላንተ የሚያሙ ሰዎች አንተንም ለሌሎች ያማሉ፤ አይታመኑም:: ሀሜትን የምታደምጥ ከሆንክ፣ እግዚአብሔር ችግር ፈጣሪ ይልሃል፤ ምሳሌ 17፥4፤ 16፥28፤ 26፥20፤ 25፥9፤ 20፥19)::

*«እኩይ ሰው ክፉ ነገር ያደምጣል» ምሳሌ 17፥4፤ «እነዚህ ሰዎች በመካከላችሁ መለያየትን የሚፈጥሩ በደመነፍስ የሚነዱ መንፈስ የሌላቸው ናቸው» ይሁዳ 19።*

በእግዚአብሔር መንጋ መካከል፣ ትልቁ ማቁሰል የሚመጣው ብዙ ጊዜ ፣ ከተኩላዎች ሳይሆን የመንጋው አካል ከሆኑ በጎች መሆኑ ያሳዝናል። ጳውሎስ፣ *«እርስ በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ» ገላ. 5፥15* በማለት *«ሥጋውያን ክርስቲያኖችን»* አስጠንቅቋል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ እንዲህ ያሉት ችግር ፈጣሪዎች መወገድ አለባቸው ይላል፦ *«ሀሜተኛ ምስጢር ያባክናል፤ ስለዚህ ለፍላፊን ሰው አርቀው፣» ምሳሌ 20፥19።* ቤተክርስቲያን ውስጥ ወይም አነስተኛ ቡድን መሀል የሚነሣን ግጭት የማቆሚያ ፈጣኑ መንገድ፣ በሀሜት ተግባር የተሰማሩ ሰዎችን መቅረብና ድርጊታቸውን እንዲያቆሙ በጥብቅ ማስገንዘብ ነው። ሰሎሞን እንዲህ ይላል፦ *«እንጨት ከሌለ እሳት ይጠፋል፤ ሾክሻኪ ከሌለ፣ ጠብ ይበርዳል» ምሳሌ 26፥20።*

**ለግጭት መፍቻነት የእግዚአብሔርን ዘዴ ተጠቀምበት።** መጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ ከተጠቀሱት መርሆዎች በተጨማሪ፣ ኢየሱስም ሦስት ደረጃዎች ያሏቸው ቀላል አሠራሮችን ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል፦ *«ወንድምህም ቢበድልህ፣ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ክፋቱን ንገረው። ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ፤ ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ እንጋገረው» ማቴ. 18፥15-17።*

አንድ ግጭት በተፈጠረ ጊዜ፣ ወደ በደለህ ሰው በድፍረት በመሄድ እውነቱን በፍቅር ከመነጋገር ይልቅ፣ ቅሬታህን ለሌላ ሦስተኛ ሰው ለመግለጥ ትፈተናለህ። ይህ ነገሩን ስለሚያባብሰው፣ በቀጥታ ወደ አስከፋህ ሰው ሂድ።

ሁል ጊዜ የመጀመሪያው መሆን ያለበት እርምጃ፣ በግል ፊት ለፊት መነጋገር ስለሆነ፤ በፍጥነት ልታደርገው ይገባል። በዚህ አካኋን ችግሩን በሁለታችሁ መካከል ብቻ ልትፈታው ካልቻልክ፣ ሁለተኛው እርምጃ ፣ ችግሩን ለመፍታት የሚረዱና የሚያስታርቁ አንድ ወይም ሁለት ምስክሮችን ይዞ መሄድ ነው። ሰውዬው በግትርነቱ ከፀናስ ምን ታደርጋለህ? ወደ ቤተ ክርስቲያን ውሰደው ይላል ኢየሱስ። ከዚያ በኋላም ሰውዬው አልሰማም ካለ፣ እንደማያምን ሰው ተመልከተው ማቴ. 18፥17፤ 1ቆሮ. 5፥5።



**መጋቢህንና የቤተክርስቲያን መሪዎችህን ደግፋቸው።** ፍፁማን መሪዎች የሉም። ቢሆንም የቤተክርስቲያንን አንድነት ይጠብቁ ዘንድ ለነዚሁ ሰዎች እግዚአብሔር ኃላፊነትና ሥልጣንን ይሰጣቸዋል። መሪነት የእርስ በርስ ግጭት በሚነሣበት ጊዜ የማያስመሰግን ሥራ

ነው:: የቤተክርስቲያን መሪዎችና መጋቢያን ብዙ ጊዜ አንደኛው በሌላው ላይ በደል የፈፀሙ፣ የተጣሉ ወይም መንፈሳዊ ዕድገት የሌላቸው የቤተርስቲያን አባላትን በማስታረቅ አስቸጋሪ አገልግሎት ይጠመዳሉ:: ሰውን ሁሉ ለማስ ደሰት የመሞከር ሥራም ተሰጥቷቸዋል:: ይህ ደግሞ አስቸጋሪ ተግባር ነው፤ ኢየሱስ እንኳን ሊፈጽመው ያልቻለው!

ከሚያገለግሉን ሰዎች ጋር በምን ሁኔታ መገናኘት እንደሚኖርብን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጥ እንዲህ ይላል:- *«ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ ተገዙላቸውም:: ምክንያ ቱም እነርሱ በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር ስላለባቸው፤ ስለነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ:: ስለዚህ ሥራቸውን በሐዘን ሳይሆን፣ በደስታ ለማከናወን እንዲችሉ ታዘዟቸው:: ስለ ዚያ አይበጃችሁም»* ዕብ. 13÷17:: መሪዎችና መጋቢያን አንድ ቀን በእግዚ አብሔር ፊት በመቆም፣ ምን ያህል በመልካም ሁኔታ እንደጠበቁህ ያስረዳሉ:: *«በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር ስላለባቸው፣ ለነፍሳችሁ ይተጋሉ»* ዕብ. 13÷17:: አንተም ተጠያቂነት አለብህ:: ምን ያህል በመልካም ሁኔታ መሪዎችህን እንደተከተልክ ለእግዚአብሔር መልስ ትሰጣለህ::

*በመሪነት የሚያገለግሉንን ስናከብር፣ ህብረታችንን እንጠብቃለን::*

በህብረት ውስጥ የመከፋፈል አዝማሚያ ያላቸውን ሰዎች መሪው ወይም መጋቢው በምን ሁኔታ ሊይዛቸው እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ መመሪያ ይሰጣል:: እነርሱም፣ ውዝግብን ማስወገድ፣ የሚቃወሟቸው ሰዎች ድርጊታቸውን እንዲተው ከመጸለይ ጋር ማስተማር፣ ውዝግብ ፈጣሪዎችን ማስጠንቀቅ፣ ስምምነትና ህብረት ይኖር ዘንድ መማጠን፣ መሪዎ ቻቸውን የማያከብሩ ሰዎችን ከቤተክርስቲያን ማገድ፣ እና ክፍፍል ፈጣሪዎች በሁለት ማስጠንቀቂያዎች ካልተመለሱ እንዲሁ ከቤተክርስቲያን ማገድ፤ 2ጢሞ. 2÷14፤ 23-26፤ ፊልጵ. 4÷2፤ ቲቶ 2÷15- 3÷2-10 ናቸው::

በመሪነት የሚያገለግሉንን ስናከብር፣ ህብረታችንን እንጠብቃለን:: መጋቢያ ንና ሽማግሌዎች ጸሎታችንን፣ ማበረታታችንን፣ ምስጋና እና ፍቅራችንን ይፈ ልጋሉ:: እንዲህ ተብለን ታዘናል:- *«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ በእናንተ መካከል በትጋት የሚሠሩትን፣ በጌታም የበላዮቻችሁና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሯቸው እንለምናችኋለን»* 1ተሰ. 5÷12-13::

የቤተክርስቲያንን ህብረት የመጠበቅና የማስከበር ኃላፊነት እንድትቀበል አበ ረታታሃለሁ:: ያለ ኃይልህን ለቤተክርስቲያን አንድነት አውል፤ እግዚአብሔ ርም ደስ ይለዋል:: ነገሩ ሁል ጊዜ ቀላል አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ ለራስህ

ሳይሆን ለሌሎች ቅድሚያ በመስጠት፣ አካሉ ለሆነችው ቤተክርስቲያን መልካም የሆነ ነገር ማድረግ ይኖርብሃል። እግዚአብሔር የቤተክርስቲያን ቤተሰብ አካል የሚያደርገን አንዱ ምክንያት፣ እራስ ወዳድነታችንን መተው እንድንማር ነው። በህብረት ኑሮ ውስጥ «እኔ» በማለት ፋንታ «እኛ» እና «የኔ» በማለት ፋንታ «የኛ» ማለትን እንማራለን። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- *«እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ፣ የራሱን ብቻ አይፈልግ»* 1ቆሮ. 10÷24።

አንድነት ያላቸውን አብያተክርስቲያናት እግዚአብሔር ይባርካቸዋል። እኔ አባል በሆንኩባት ቤተክርስቲያን፣ እያንዳንዱ አባል የሚፈርመው ቃል ኪዳን አለ። ቃል ኪዳኑ የህብረታችንን አንድነት መጠበቅንም ያካትታል። በዚህ ምክንያት፣ ቤተክርስቲያኒቱ ህብረቷን የሚከፋፍል ግጭት ገጥሟት አያውቅም። ፍቅር ያለበትና የተባበረ ህብረት ስለሆነ፣ ብዙ ሰዎች የእኛ አባል ለመሆን *ይፈልጋሉ!* ባለፉት ሰባት ዓመታት ቤተክርስቲያኒቱ 9100 አዳዲስ አማኞችን አጥምቃለች። እግዚአብሔር አዳዲስ አማኞችን ሊያፈራ ሲሻ፣ አዲስ ለሚወለዱ አማኞች የምትመች ቤተክርስቲያን ይፈልጋል።

የቤተክርስቲያንህ ቤተሰብ ይበልጥ የተባበረና ፍቅር ያለው እንዲሆን ለማድረግ በግልህ ምን በማድረግ ላይ ነህ? በምትኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ ፍቅርና አባላት የሚሆኑበትን ህብረት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ። ማንኛውም ሰው መፈቀርን ይናፍቃል፣ ይፈልጋልም፤ ይህ ነው እውነቱ። በዚሁ መሠረት አባላቷ በእውነት የሚፋቀሩባት፣ እርስ በርሳቸው የሚንከባከቡባት ቤተክርስቲያን ሲያገኙ፣ ልታገለግላቸው ከሚቻላት በላይ ብዙ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያኒቱ የሚመጡ መሆናቸው መታወቅ አለበት።

ሀያ አንደኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ


**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፦** የቤተክርስቲያኔን ህብረት የመጠበቅ ኃላፊነት አለብኝ።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፦** *«ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና፣ እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ»*
ሮሜ 14÷19።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፦** የቤተክርስቲያኔን ቤተሰብ ህብረት ለመጠበቅ በአሁኑ ጊዜ በግሌ ምን በማድረግ ላይ ነኝ?

# ማስታወሻ

# ዓላማ ቁጥር 3



# ክርስቶስን ለመምሰል ነው የተፈጠርከው

*በእርሱ ተተክላችሁና ታንጻችሁ፣ እንደ ተማራችሁት*
*በእምነት ጸንታችሁ፣ የተትረፈረፈ ምሥጋና እያቀረባችሁ ኑሩ።*

ቆላ. 2፥7

# 22

# ክርስቶስን ለመምሰል ተፈጥረሃል

*እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው።*

ሮሜ 8፥29

*እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው ።*

ቆላ. 1፥15

ክርስቶስን ለመምሰል ነው የተፈጠርከው።

ከጅማሬው አንስቶ፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ፣ ልጁን ኢየሱስን እንድትመስል ማድረግ ነው። ይህ መድረሻ ግብህና ሦስተኛው የሕይወትህ ዓላማ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ይህን ዓላማውን እንዲህ በማለት ገለጠው።

*«እግዚአብሔርም ሰውን በመልካችን እንሥራ አለ » ዘፍ. 1፥26።*

ከፍጡራን ሁሉ «በእግዚአብሔር አምሳል» የተፈጠረ ሰው ብቻ ነው ። ይህ ትልቅ ዕድል ነው፤ ክብርም ይሰጠናል። «በእግዚአብሔር አምሳል» የሚለው ሐረግ የሚገልጠውን *ሁሉ* አናውቅም፤ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች እንደሚያካትት ግን እንረዳለን፦ እንደ እግዚአብሔር *መንፈሳዊ ህልውና* አለን፤ *መንፈሳችን* አይሞትም፤ ከምድራዊ አካላችን ባሻገር ዘላለማዊ ህልውና አለን። *አእምሮ* አለን፤ እናስባለን፤ እንመራመራለን፤ ችግሮችን እንፈታለን። እንደ እግዚአብሔር ከሌሎች *ጋር ለመቀራረብ* እንችላለን፤ እውነተኛ ፍቅር ለመስጠትና ለመቀበል እንችላለን። ህሊናዊ *ሥነ ምግባር* አለን፤ ትክክሉን ከስህተት እንለያለን። ይህ ነው በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ የሚያደርገን።

አማኞች ብቻ ሳይሆኑ፣ ሰው ሁሉ ከፊል የእግዚአብሔር አምሳያነት

እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ለዚህ ነው ማግደልና ጽንስ ማስወረድ ስህተት የሚሆነው ዘፍጥ. 6+9 ፤ መዝ. 139+13-16፤ ያዕ. 3+9:: ነገር ግን ይህ አምሳያነት፣ ሙሉ ያልሆነ፣ በኃጢአት ምክንያት የተበላሸና የተዛባ ሆኗል:: በመሆኑም ያጣነውን ሙሉ አምሳያነት ወደ ነበረበት የመመለስ ተልዕኮ ሰጥቶ እግዚአብሔር ኢየሱስን ላከው:: የእግዚአብሔር ሙሉ «መልክና አምሳያነት» ምን ይመስላል? ኢየሱስ ክርስቶስን ነው የሚመስለው! መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ:- *«የእግዚአብሔር ምሳሌ»፤ «የማይታይ አምላክ ምሳሌ »* እና *«የባሕርይ ምሳሌ»* 2ቆሮ. 4+4፤ ቆላ. 1+15፤ ዕብ. 1+3 ነው ይላል::

ሰዎች ቤተሰባዊ መመሳሰልን ለመግለጥ ብዙ ጊዜ፣ «አባቱን ይመስላል፣ እናቱን ይመስላል» የሚል ቃል ይጠቀማሉ:: ሰዎች የኔን ምስል ልጆቼ ውስጥ ማየታቸውን ስመለከት ደስ ይለኛል:: እግዚአብሔርም፣ ልጆቹ መልክና አምሳያውን እንዲይዙለት ይፈልጋል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እግዚአብሔርን እንደ ንመስል፣ የፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው»* ኤፌ. 4+24::

በጣም ግልጥ ልሁን፤ እግዚአብሔርን ወይም ከአማልክት አንዱን ልትሆን በፍፁም አትችልም:: እንዲያ ያለው በትዕቢት የተሞላ ውሸት ጥንታዊ



የሰይጣን ፈተና ነው:: ሰይጣን፣ አዳምና ሄዋንን ምክሬን ብትከተሉ:- *«እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑ ...»* ዘፍጥ. 3+4 በማለት ቃል ገባላቸው:: ብዙ ሃይማኖቶችና የአዲሱ ዘመን ፍልስፍናዎች፣ መለኮታዊ ናችሁ ወይም አምላክ ልትሆኑ ትችላላችሁ እያሉ አሁንም ይህንኑ አሮጌ ውሸት በማስፋፋት ላይ ናቸው::

ይህ አምላክ የመሆን ፍላጎት ያለንበትን ሁኔታ፣ የወደፊት ዕጣችንን፣ እና በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ለመቆጣጠር በምንሞክርበት ጊዜ ሁሉ ይከሰታል:: ነገር ግን ፍጡራን እንደመሆናችን በፍፁም ፈጣሪ ለመሆን አንችልም:: አምላክ እንድትሆን እግዚአብሔር አይፈልግም፤ *ፋይዳውን፣ ስነቡን፣ እና ባህርይውን* በመውረስ የእርሱ እንድትሆን ነው የሚፈልገው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ደግሞም በአእምሯችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው»* ኤፌ. 4+23-24::

እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሕይወትህ ያለው የመጨረሻ ዓላማ፣ ምቾት ሳይሆን፣ በባህርይ ማደግ ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወትህ አድገህ ኢየሱስን እንድትመስል ይፈልጋል:: ኢየሱስን መምሰል ማለት፣ ማንነትህን ማጣት

ወይም በሰው ሠራሽ ዘዴ የተዳቀለና አእምሮ አልባ ፍጡር መሆን ማለት አይደለም። ልዩ አድርጎ የፈጠረህ እግዚአብሔር ስለሆነ፣ ይህንን ሊያጠፋው አይፈልግም። ክርስቶስን መምሰል ማለት፣ አንተነትህን ሳይሆን፣ ባህርይህን መቀየር ማለት ነው።

እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ በተራራ ስብከቱ የጠቀሳቸውን ባህርያት፣ ማቴ. 5፥1-12፣ የመንፈስ ፍሬዎችን ገላ. 5፥22-23፣ ጳውሎስ ስለ ፍቅር በገለጠበት ትልቅ ምዕራፍ ውስጥ የጠቀሳ ቸውንና 1ቆሮ. 13፣ ጴጥሮስ ውጤታ ማና ፍሬ ያለው ሕይወት ባህርያ ትን አስመልክቶ የጠቀሳቸውን ዝር ዝሮች 2ጴጥ. 1፥5-8 እንድታዳብር ይፈልጋል። የባህርይ ዕድገት፣ እግዚ አብሔር ለሕይወትህ ካለው ዓላማዎች አንዱ መሆኑን በምትረሳበት ጊዜ ሁሉ፣ ባለህበት ሁኔታ ተስፋ የምትቆርጥ ትሆናለህ። «ለምንድነው ይህ የሚደርስብኝ? እንዲህ ባለው አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ የማልፈውስ ለምንድነው?» እያልክ ትጠይቃለህ። የዚህ አንዱ መልስ፣ ሕይወት እንዲህ ነው የሚል ይሆናል። ያ ነው እንድ ናድግ የሚረዳን። ምድር መንግሥተ ሰማይ አለመሆንዋን አስታውስ!

*እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሕይወትህ ያለው የመጨረሻ ዓላማ፣ ምቾት ሳይሆን፣ በባህርይ ማደግ ነው።*

ብዙ ክርስቲያኖች «ሕይወት ... እንዲበዛላቸው» ዮሐ. 10፥10 ፣ የሚለውን የኢየሱስ ተስፋ፣ ፍፁም ጤንነት፣ ምቹ ኑሮ፣ የማያቋርጥ ደስታ፣ የህልማ ቸው እውን መሆን፣ እንዲሁም በእምነትና በጸሎት ዓማካይነት ከችግር በፍጥነት መውጣት እንደሆነ አድርገው በተሣሣተ መንገድ ይተረጉሙታል። በአንድ ቃል፣ የክርስትና ሕይወት ቀላል እንዲሆን ይጠብቃሉ፤ መንግሥተ ሰማይን በምድር ይሻሉ።

በራስ ወዳድነት የተሞላው ይህ አመለካከት፣ እግዚአብሔርን የግል ፍላጎትህን ለማሟላት በምታደርገው ጥረት ሊረዳህ ብቻ የሚኖር መንፈስ እንደሆነ አድርጎ እንደመቁጠር ነው። እግዚአብሔር *አገልጋይህ* አይደለም። ሕይወት ቀላል ነው የሚለውን አሳብ የምትቀበል ከሆንክ፣ ወይ በጣም ግራ የተጋባ ሰው ትሆናለህ፣ ወይም እውነታን እየካድክ ትኖራለህ።

ሕይወት ስለ አንተ አለመሆኑን ፈጽሞ አትርሳ! የምትኖረው ለራስህ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ዓላማ ነው። እግዚአብሔር እውነተኛውን መንግሥተ ሰማያት በዘላለም ውስጥ አቅዶልህ ሳለ፣ መንግሥተ ሰማያትን በምድር ላይ የሚያቀርብልህ ለምንድነው? እርሱ በምድር ላይ ጊዜ የሚሰጠን፣ ለመንግሥተ

ለማየት የሚሆን ባህርያችንን እንድንገነባና እንድናጎለብትበት ነው።

## ውስጥህ የሚሠራ የእግዚአብሔር መንፈስ

የክርስቶስን የመሰለ ባህርይ ውስጥህ እንዲኖር ማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *«እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስታወት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው፣ መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው»* 2ቆሮ. 3፥18። ይበልጥ ኢየሱስን እንድንመስል የመለወጡ ይህ ሂደት መቀደስ የሚባል ሲሆን፣ የምድራዊ ሕይወትህ ሦስተኛ ዓላማ ነው።

በራስህ ብርታት የኢየሱስን ባህርይ ልታፈራ አትችልም። የአዲስ ዓመት ውሳኔዎች፣ ቆራጥነት እና በጣም ጥሩ ፍላጎቶች በቂ አይደሉም። እግዚአ ብሔር በሕይወታችን ሊያከናውን የሚፈልገውን ለውጥ ለመሥራት፣ ኃይል ያለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *«ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና፣ ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና»* ፊልጵ. 2፥13።

«የመንፈስ ቅዱስ ኃይል» ብለህ ስትጠቅስ፣ ብዙ ሰዎች የሚያስቡት፣ ስለ ተዓምራዊ ድርጊትና ኃይለኛ ስሜት ነው። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወትህ የሚገለጠው፣ በማታውቀው ወይም በማይሰማህ ሁኔታ ፀጥ ባለና ባልተጠበቁ መንገዶች ነው። ብዙ ጊዜ *«በትንሽ የዝምታ ድምፅ»* 1ነገ. 19፥12 ነው ጎንተል የሚያደርገን።

**ሀያ ሁለተኛ ቀን**

**ክርስቶስን ለመምሰል ተፈጥረሃል**

ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት፣ በመኖር እንጂ፣ በመቅዳት ወይም በመኮረጅ የምታፈራው አይደለም። ክርስቶስ በእኛ እንዲኖር እንፈቅዳለን። *«የዚህ ምስጢር ... በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ነው»* ቆላ. 1፥27። እንዴት ነው ይህ ነገር በሕይወታችን የሚከናወነው? በምርጫዎ ቻችን ዓማካይነት ነው። በሁኔታዎች ውስጥ ትክክለኛ ውን ነገር ለማድረግ እንመርጥና፤ ያን ለማድረግ የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል፣ ፍቅር፣ እምነት እና ጥበብ እንደሚሰጠንም እናምናለን። የእግዚአብ ሔር መንፈስ በውስጣችን ስለሚኖር፣ በጠየቅን ጊዜ ሁሉ እነዚህን ነገሮች እናገኛቸዋለን።

ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር መተባበር አለብን። በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጠቃሚ እውነት በተደጋጋሚ ተገልጦ እንመለከታለን። የእምነት እርምጃ በምትወስድበት *ቅጽበት*፣ መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ይልክልሃል። ኢያሱ

የማይታለፍ መሰናከል በገጠመው ጊዜ፣ መሪዎቹ በፍጥነት ይገሰግስ በነበረው ውሃ ውስጥ በታዛዥነትና በእምነት ከረገጡ *በኋላ* ነው የዮርዳኖስ ወንዝ *ያፈገፈገው* ኢያሱ 3፥13-17። ታዛዥነት የእግዚአብሔርን ኃይል የሚከፍት ቁልፍ ነው።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ በድርጊት የሚገለጥ ነገርህን ይጠባበቃል። ብር ታት ወይም የመተማመን ስሜት እስኪሰማህ አትጠብቅ። ፍርሃትና ሌሎች ስሜቶች ቢያድሩብህም፣ ትክክል የሆኑ ነገሮችን እየሠራህ በድካምህ ወደፊት ተራመድ። በዚህ አካኋን ነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምትተባበረውና ባህር ይህም የሚዳብረው።

መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ዕድገትን ከዘር፣ ከህንፃ፣ እና ከሚያድግ ህፃን ጋር ያነፃፅረዋል። እያንዳንዱ ዘይቤያዊ ገለጣ ተግባራዊ ተሳትፎን የሚጠይቅ መልእክት አለው። የዕፅዋት ዘር መተከልና እንክብካቤ ማግኘት አለበት፤ ህንፃ ዎች መገንባት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁ ብቅ አይሉም። ህፃናትም ለማደግ መመገብና አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ጥረት ለድነትህ የሚፈይደው ነገር ባይኖርም፣ ለመንፈሳዊ ዕድገትህ ግን ብዙ ጥቅም አለው። ኢየሱስን ለመምሰል በምናደርገው ዕድገት፣ *«የተቻለንን ሁሉ እንድናደርግ! እንድንተጋ»*፣ ቢያንስ ስምንት ጊዜ አዲስ ኪዳን ውስጥ ተነግ ሮናል። ቁጭ ብለህ፣ እራስ እንዲከናወን መጠበቅ የለብህም።

ክርስቶስን በመምሰል ሂደት፣ ያሉብንን ሦስት ኃላፊነቶች ጳውሎስ ኤፌሶን 4፥22-24 ውስጥ ገልጧቸዋል። በመጀመሪያ አሮጌ ድርጊቶቻችንን ለመተው መወሰን አለብን። *«ቀድሞ ስለነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞቱ የጉደ ፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ ተምራችኋል፤»* ኤፌ. 4፥22 ።

ሁለተኛ፣ የአስተሳሰብ ሁኔታችንን መለወጥ አለብን *«በአእምሯችሁም መንፈስ ታደሱ»* ኤፌ. 4፥24። በልባችን መታደስ «የተለወጥን» ሮሜ 12፥2፣ እንድ ንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ሮሜ 12፣ እና 2ቆሮ. 3፥18 ውስጥ አገል ግሎት ላይ የዋለውና «መለወጥ» የሚለው ቃል አቻ ግሪክኛ ትርጉም «*ሜታሞ ርፎሲስ*» የሚለው ነው። ይህ ዛሬ የአባጨጓሬን ወደ ቢራቢሮነት የመቀየር አስገራሚ የለውጥ ሂደት ለመግለጫነት አገልግሏል። እግዚአብሔር አሳባችንን እንዲመራ ስንፈቅድለት በመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚከናወነውን ሂደት ለመግለጫነት ይህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ከውስጥ የጀመረና በውጭም የሚታይ ለውጥ ይኖረናል። ተለውጠን፣ ይበልጥ ውብ እንሆናለን፤ እናም አዳዲስ ከፍታዎች ላይ እንድናንዣብብ ነፃ እንወጣለን።

ሦስተኛ፣ አዲስና መለኮታዊ ልማዶችን በማዳበር፣ የክርስቶስን ባህርይ

«መልበስ» አለብን:: ባህርይህ በመሠረቱ *የልማዶችህ (የተለምዶአዊ ድርጊትህ)* ድምር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «*እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው*» ኤፌ. 4÷24::

***ባህርይህ በመሠረቱ የልምዶችህ ድምር ነው::***

**እግዚአብሔር ሲቀርፀን በቃሉ፣ በሰዎችና በሁኔታዎች ይጠቀማል::** ሦስቱም ነገሮች ለባህርይ ዕድገት ምትክ የማይገኝላቸው አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: የእግዚአብሔር ቃል ለዕድገት የሚያስፈልገንን *እውነት* ያስጨብጠናል፤ የእግዚአብሔር ሰዎች ለዕድገት የሚያሻንን *እርዳታ* ያደርጉልናል፤ ሁኔታዎች ደግሞ ክርስቶስን መምሰልን የምንለማመድበት *አካባቢን* ይፈጥሩልናል:: የእግዚአብሔርን ቃል የምታጠናና በተግባር የምታውለው ከሆንክ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ዘወትር ከተገናኘህ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እያለህ በእግዚአብሔር መታመንን ከተማርክ፣ ይበልጥ ኢየሱስን እንደምትመስል አረጋግጥልሃለሁ:: እነዚህን የዕድገት መሠረታዊ ክፍሎች በቀሩን ምዕራፎች ውስጥ በዝርዝር እንመለከታቸዋለን::

ብዙ ሰዎች፣ ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናትና ፀሎት ብቻ ናቸው ብለው ያስባሉ:: ነገር ግን የሕይወት አንዳንድ ጉዳዮች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጸሎት ብቻ *በፍጹም* አይለወጡም:: እግዚአብሔር በሰዎች ይጠቀማል:: ህብረትን በመሻት አንዳችን በሌላችን ላይ ለመደገፍ ይቻለን ዘንድ ከተዓምራት ይልቅ፣ ብዙ ጊዜ በሰዎች ዓማካይነት መሥራትን ይመርጣል:: በህብረት እንድናድግ ነው የሚፈልገው::

በብዙ ሃይማኖቶች፣ በመንፈሳዊነት እጅግ ያድጉና ቅዱሳን የሚባሉት ከሌሎች ተለይተው፣ በሰዎች ባልተበከሉና ተራራ አናት ላይ በሚገኙ ገዳማት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው:: ይህ እጅግ የተሣሣተ ግንዛቤ ነው:: መንፈሳዊ ዕድገት፣ በግል ፍላጐትና ጥረት የሚመጣ አይደለም! ከሌሎች ተለይተህ ክርስቶስን ወደ መምሰል ልታድግ አትችልም:: ከሰዎች ጋር መቀላቀልና መስተጋብር መፍጠር አለብህ:: የአንድ ቤተክርስቲያን እና ህብረት አካል መሆን ያስፈልግሃል:: ለምን? ምክንያቱም እውነተኛ መንፈሳዊ ዕድገት እንደ ኢየሱስ መውደድን መማር ስለሆነና፣ ከሰዎች ጋር ግንኙነት ካላደረግህ ደግሞ ኢየሱስን መምሰልን ለመለማመድ ስለማትችል ነው:: ዋናው ነገር ፍቅር መሆኑን አስታውስ፤ እግዚአብሔርን ማፍቀር እንዲሁም፣ ሌሎች ሰዎችን ማፍቀር::

**ኢየሱስን መምሰል እረጅምና ዝግ ያለ የዕድገት ሂደት ነው::** መንፈሳዊ

ዕድገት ቅጽበታዊ ወይም አውቶማቲክ ክንውን አይደለም:: በቀሪው የሕይወት ዘመንህ ሁሉ የሚከናወንና ቀስ በቀስ የሚያድግ ሂደት ነው:: ጳውሎስ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:- *«በክርስቶስ ወዳለው ፍፁምነት ደረጃ እስክን ደርስ ነው»* ኤፌ. 4÷13::

በማደግ ላይ ያለ ሥራ ነህ:: የኢየሱስን ባሕርይ በሕይወትህ በማሳደግ የምታደርገው መንፈሳዊ ለውጥ፣ የቀሪው ዘመንህ ክንውን ነው:: ያም ቢሆን በምድር ላይ የሚያበቃ አይደለም:: የሚያበቃው፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስትሄድ ወይም ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ነው:: ባህርይህ ውስጥ ያልተጠና ቀቀ ነገር ሁሉ ያኔ ይከስማል:: በመጨረሻ ኢየሱስን ለማየት በምንችልበት ጊዜ፣ በፍፁም እሱን የምንመስል መሆናችንን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይነግረናል:- *«ወዳጆች ሆይ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ወደፊት ምን እንደም ንሆን ገና አልተገለጠም:: እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደንመስል እናውቃለን »* 1ዮሐ. 3÷2::

በክርስትና ሕይወትህ ብዙ ጊዜ ግራ መጋባት የሚደርስብህ፣ እግዚአብሔር ከምንም ይልቅ ባህርይህን ለማዳበር የሚፈልግ የመሆኑን እውነት ችላ ከማለ ትህ የተነሣ ነው:: «ምን ዓይነት ሥራ ልምረጥ?» የሚለውን የመሰለ የግል ጥያቄ አቅርበን እግዚአብሔር ፀጥ ያለ ሲመስለን እንጨነቃለን:: እውነቱ ግን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ለሕይወትህ የሚሆኑ *ብዙ* ልዩ ልዩ ሥራዎች ያሉ መሆኑ ነው:: እግዚአብሔር ከምንም ይልቅ የሚሻው፣ የምታደርገውን ነገር ሁሉ የክርስቶስን በመሰለ ሁኔታ እንድትፈፅመው ነው፣ 1ቆሮ. 10÷31፤ 16÷14፤ ቆላ. 3÷17፣23::

*እግዚአብሔር ከምንም ይበልጥ የሚፈልገው፣ የምታደርገውን ነገር ምንነት ሳይሆን፣ ማንነትህን ነው::*

እግዚአብሔር ከምንም ይልቅ የሚ ሻው፣ የምታደርገውን ነገር ምንነት ሳይሆን፣ ማንነትህን ነው:: ሰብዓዊ ፍጡራን እንጂ፣ ሰብዓዊ ድርጊቶች አይደ ለንም:: እግዚአብሔር በጣም የሚጨ ነቀው ከሥራህ ይልቅ ለባሕርይህ ነው:: ምክንያቱም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይዘህ የምትሄደው፣ ባህርይህን እንጂ ሥራህን አይደለም::

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል:- *« መልካም፣ ደስ የሚያ ሰኝና፣ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታወቁ ዘንድ፣ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» ሮሜ 12÷2::* ከባህል ጋር የሚቃረን ቢመስልም እንኳን ኢየሱስን በመምሰሉ ተግባር ላይ

ለማትከር ትችል ዘንድ፣ አንዳንድ ሁኔታዎችን በተመለከተ ቆራጥ ውሳኔ ማድ ረግ አለብህ። ያለዚያ ጓደኞች፣ ወላጆች፣ የሥራ ባልደረባዎች፣ እና ባህልን የመሳሰሉ ሌሎች ሁኔታዎች እነሱን ወደሚመስል ቅርፅ ሊለውጡህ ይሞክራሉ።

የሚያሳዝነው ነገር፣ ብዙ ተወዳጅ ክርስቲያናዊ መጻሕፍትን ስናገላብጥ የምንረዳው፣ አያሌ አማኞች ለታላቁ የእግዚአብሔር ዓላማ መኖራቸውን እየተዉ፣ ወደ ግል ኑሯቸው ስኬትና የስሜት እርካታ ማዘንበላቸውን ነው። ይህ እራስን ማምለክ እንጂ ደቀ መዝሙርነት አይደለም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ምቹና የተረጋጋ ሕይወት እንኖር ዘንድ ብቻ አይደለም። ዓላ ማው ከዚህ የጠለቀ ነው፤ ወደ ሰማይ ሳይወስደን በፊት እሱን የምንመስል ሊያደርገን ይፈልጋል። ይህ፣ ትልቁ እድላችን፣ የአሁን ኃላፊነታችንና የመጨ ረሻ ግባችን ነው።

ሀያ ሁለተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:- ክርስቶስን እንድመስል ነው የተፈጠርኩት።

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:- *«እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደመስታወት እያንፀባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን»* 2ቆሮ. 3÷18።

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:- ክርስቶስን ለመምሰል እንድችል፣ በየትኛው የሕይወቴ ክፍል ላይ ነው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ዛሬ መጠየቅ የሚያስፈልገኝ?

# እድገታችን

*ራስ ወደሆነው ወደ እርሱ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው፡፡*

*ኤፌ. 4÷15*

*ወዲህና ወዲያ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም፡፡*

*ኤፌ. 4÷14*

እንድታድግ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡

ሰማያዊው አባትህ ለአንተ ያለው ግብ፣ እንድታድግና የኢየሱስ ክርስቶስን ባህርያት እንድታዳብር ነው፡፡ የሚያሳዝነው ግን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች *ያረጃሉ እንጂ* በፍፁም *አያድጉም*፡፡ በመንፈሳዊ ሕፃንነት ቀርተዋል፤ ከመዳህ አላለፉም፡፡ የዚህ ምክንያቱ ለማደግ በፍፁም አስበው ስለማያውቁ ነው፡፡

*መንፈሳዊ ዕድገት* በራሱ የሚመጣ ነገር አይደለም፡፡ *መስጠትን* ይጠይቃል፡፡ ለማደግ *መፈለግ*፣ ለማደግ *መወሰን*፣ ለማደግ *ጥረት ማድ ረግ*፣ እና በማደግ *መቀጠል* አለብህ፡፡ ደቀ መዝሙርነት፣ ክርስቶስን የመምሰል ሂደትና ሁልጊዜ በውሳኔ የሚጀመር ተግባር ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ይጠራናል፡፡ እኛም ለጥሪው መልስ እንሰጣ ለን፡- «*ተከተለኝ አለው፣ ተነስቶም (ማቴዎስ) ተከተለው*» ማቴ. 9÷9፡፡

የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ኢየሱስን ለመከተል በመረጡ ጊዜ የውሣኔያቸው ውጤት ምን ሊሆን ይችል እንደነበር አላወቁም፡፡ የኢየሱ ስን ጥሪ በቀላሉ ተቀበሉ፡፡ አንተም ለመጀመር ማድረግ ያለብህ ይህንኑ ብቻ ነው፤ ደቀመዝሙር ለመሆን *ወስን፡፡*

ራስህን ከምትሰጣቸው ወይም ቃል ኪዳን ከምትገባባቸው ውሣኔዎች ይበልጥ ሕይወትህን የሚቀርፀው ነገር የለም፡፡ ራስህን የምትሰጥባቸው ውሣኔዎች ሊያሳድጉህ ወይም ሊያጠፉህ ይችላሉ፡፡ በዚያም ሆነ

በዚህ አንተነትህ ይገለጥባቸዋል:: ቃል ኪዳን የገባህባቸውን ወይም ራስህን የሰጠህባቸውን ነገሮች ንገረኝና፣ ከሀያ ዓመት በኋላ ምን እንደምትሆን እነግርሃለሁ:: የምንሆነው ራሳችንን የሰጠንለትን ነገር ነው ::

ብዙ ሰዎች፣ እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ያለውን ዓላማ የሚስቱት እዚህ ላይ ነው:: ብዙዎቹ ቃል ኪዳንን ወይም መሰጠትን ስለሚፈሩ፣ እንዲሁ በሕይወት ወንዝ ላይ ይንሳፈፋሉ:: ሌሎቹ ደግሞ አብረው ለመሄድ ለማይችሉ ለተለያዩ ፋይዳዎች (እሴቶች) በተከፋፈለ ልብ ራሳቸውን በመስጠት ተስፋ ወደ መቁረጥና ተራ ኑሮ ወደ መኖር ይደርሳሉ:: የቀሩት ደግሞ፣ ባለፀጋ ወይም ዝነኛ መሆንን ለመሳሰሉ ዓለማዊ ግቦች ራሳቸውን ይሰጡና ፍፃሜያቸው ብስጭትና መማረር ይሆናል:: ማንኛውም ምርጫ ዘላለማዊ ውጤት ስላለው፣ ምርጫህ በብልህት ይሁን:: ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል:- *«እንዲህ ሁሉም ነገር በዚህ ሁኔታ የሚጠፋ ከሆነ እናንተ እንዴት ዓይነት ሰዎች ልትሆኑ ይገባችኋል? እምን፣ በቅድስናና በእውነተኛ መንፈሳዊነት ልትኖሩ ይገባችኋል »* 2ጴጥ. 3÷11::

**የእግዚአብሔር ድርሻና የአንተ ድርሻ::** ክርስቶስን መምሰል፣ የክርስቶስን የመሰለ ምርጫ የማድረግ ውጤት እና፣ ምርጫህን ለማከናወን ይረዳህ ዘንድ በእርሱ መንፈስ መታመን ነው:: ክርስቶስን ለመምሰል ከቆረጥክና ከወሰንህ፣ በአዳዲስ መንገዶች መንቀሳቀስን መጀመር አለብህ:: አሮጌ ልምዶችን መተው እንዲሁም አዳዲስ ልምዶችን ማዳበርና አስተሳሰብህንም ሆን ብለህ መለወጥ ይኖርብሃል:: እነዚህን ለውጦች በማድረግ ጥረትህ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳህ እርግጠኛ ለመሆንም ትችላለህ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ:: ስለበጎ ፈቃዱ፣ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና»* ፊልጵ. 2÷12-13::

*የምንሆነው ራሳችንን*
*የሰጠንለትን ነገር ነው::*

ይህ ጥቅስ፣ *«ፈጽሙ»* እና *«የሚሠራ»* በሚሉት ቃላት የመንፈሳዊ ዕድገትን ሁለት ክፍሎች ያመለክታል:: *«ፈጽሙ»* የሚለው፣ የአንተን ኃላፊነት ሲያመለክት፣ *«የሚሠራ»* የሚለው ደግሞ የእግዚአብሔርን ድርሻ ይገልጣል:: መንፈሳዊ ዕድገት በአንተና በመንፈስ ቅዱስ የትብብር ጥረት የሚከናወን ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከእኛ ጋርም ይሠራል::

ለአማኞች የተጻፈው ይህ ምንባብ፣ የሚገልጠው፣ የድነትን መንገድ ሳይሆን፣ እንዴት ለማደግ እንደሚቻል ነው:: «ለ»ድነትህ ሥራ አይልም፣

ምክንያቱም ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ ላይ ምንም ልትጨምርበት አትችልም። «ፈጽሙ» የተባልነው ድነትን በሥራ ለማግኘት ሳይሆን፣ ያገኘነውን መንፈሳዊ ሕይወት እንድናሳድግ ነው።

ገበሬዎች በማሳቸው ላይ በመሥራት በእጃቸው ያለውን ማሳ ያለማሉ እንጂ ማሳውን አይሰሩትም። እግዚአብሔር አዲስ ሕይወትን ሰጥቶሃል፤ *«በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ»* ታሳድገው ዘንድ ኃላፊነት አለብህ። ይህ ማለት መንፈሳዊ እድገትህን በጥንቃቄ አዳብረው ማለት ነው! ሰዎች ስለ መንፈሳዊ እድገታቸው ግዴለሾች ሲሆኑ፣ ዘላለማዊ ጥቅሙን ያልተረዱ መሆናቸውን ያሳያል። (ምዕራፍ 4 እና 5 ውስጥ እንደተመለከትነው)

ሃያ ሰስተኛ ቀን
እድገታችን

**እስተሳሰብህንና አመለካከትህን መቀየር።** ሕይወትህን ለመለወጥ አስተ ሳሰብህን ልትለውጥ ይገባል። በምታደርገው በእያንዳንዱ ነገር በስተ ጀርባ አንድ አስተሳሰብ አለ። ማንኛውም ፀባይ በአንድ እምነት ዓማካይነት ይነሳሳል፤ ማንኛውም ድርጊት ደግሞ በአንድ ዓይነት አመለካከት ይገፋፋል። ይህን እውነት ሳይንቲስቶች ከመረዳታቸው ብዙ ሺህ ዓመታት በፊት እግዚአ ብሔር እንዲህ በማለት ገልጦታል፡- *«ከሁሉ በላይ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት ምንጭ ነውና»* ምሳሌ 4፥23 ።

እስቲ አውቶማቲክ (እራስ መር)፣ መቆጣጠሪያ ስለተገጠመለትና ወደ ምሥራቅ እንዲቀዝፍ ባህር ላይ ስለተለቀቀ አንድ ፈጣን የሞተር ጀልባ አስብ። ጀልባው አቅጣጫውን ለውጦ ወደ ምዕራብ እንዲቀዝፍ ለማድረግ ከወሰንክ፣ የጀልባውን አቅጣጫ ለመቀየር ሁለት አማራጮች አሉህ። አንደኛው አማ ራጭ፣ የጀልባውን ተሽከርካሪ መቅዘፊያ መያዝና ከታለመለት አቅጣጫ በተ ቃራኒው እንዲቀዝፍ በሰብዓዊ ብርታትህ ማስገደድ ነው። ያለ ነጂ የሚቀ ዝፈውን ጀልባ በብርቱ ትግል ትቋቋመው ይሆናል። በመጨረሻ ግን ከትግሉ ብርታት የተነሳ፣ እጆችህ ይዝሉና እራስ መሩን ተሽከርካሪ ትለቀዋለህ። ከዚ ያም ጀልባው እውስጡ በተስተካከለው እራስ መር ዕቅድ መሠረት ፊቱን ወደ ምሥራቅ ይመልስና ጉዞውን ይቀጥላል።

ሕይወትህን ቆራጥ ውሳኔ በማድረግ ለመለወጥ በምትሞክርበት ጊዜ፣ የሚ ሆነው ይህ ነው። «ምግብ ለመቀነስ እራሴን *አስገድደዋለሁ* ...፤ የተሻለ የአካል እንቅስቃሴ እሠራለሁ፤ ዝርክርክነትንና መዘግየትንም እተዋለሁ» ትላለህ። አዎ፣ ቆራጥነት የአጭር ጊዜ ለውጥ ያመጣል። ነገር ግን የችግሩን ሥር ስላልነቀልከው፣ የማያቋርጥ ውስጣዊ ጭንቀት ይፈጥርብሃል። የፈለከው ለውጥም በተገቢው አካኋን የመጣ ስለማይሆን፣ ታቆመውና ምግብ የመቀነስ ውሳኔህን ትተወዋለህ፤ የአካል እንቅስቃሴህንም ታቋርጥና ወዲያው ወደቀድሞ

አኗኗርህ ትመስሳለህ።

የተሻለና ቀላል መንገድ አለ፤ የእራስ መሩን መቆጣጠሪያ ማለትም አስተ ሳሰብህን መለወጥ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«የእግዚአብሔር ፈቃድ ... ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ ... »* ሮሜ 12፥2። በመንፈሳዊ ዕድገት የመጀመሪያው ደረጃ የአስተሳሰብ አቅጣጫህን ለመለወጥ መጀመር ነው። መለወጥ ሁል ጊዜ የሚጀምረው አእምሮህ ውስጥ ነው። አስተ ሳሰብህ የስሜትህን ሁኔታ ይወስነዋል፤ የስሜትህ ሁኔታ ደግሞ ድርጊትህን ያነሣሣዋል። ጳውሎስ እንዲህ ብሏል ፡- *«ደግሞም በአእምሯችሁ መንፈስ እንድትታደሱ»* ኤፌ. 4፥23።


ክርስቶስን ለመምሰል፣ የክርስቶስን አሳብ ማዳበር አለብህ። ይህን የአእምሮ ለውጥ አዲስ ኪዳን *ንስሐ* ይለዋል። በግሪክኛ ቀጥታ ትርጉም «አእምሮን መለወጥ» ማለት ነው። ንስሐ የምትገባው፣ አስተሳሰብህን ወደ እግዚአብ ሔር አሳብ በመቀየር፣ ስለ ራስህ፣ ስለ ኃጢአት፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ሌሎች ሰዎች፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ ወደፊት እድልህና ስለማናቸውም ነገሮች ሁሉ ስታስብ ነው። ይህን ስታደርግ የክርስቶስን አመለካከትና እይታ ትቀዳጃለህ።

*«በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ በእናንተም ዘንድ ይሁን»* ፊልጵ. 2፥5፣ ተብለን ታዘናል። ይህን ለማድረግ ሁለት ሂደቶች አሉ። የዚህ የአ እምሮ ለውጥ የመጀመሪያ ግማሽ፣ እራስ ወዳድና እራስ ተኮር የሆኑ ጨቅላ አስተሳሰቦችን መተው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«በአስተሳሰባችሁ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፉ ነገር ሕፃናት ሁኑ፤ በአስተሳሰባችሁ ግን ጉልማሶች ሁኑ »* 1ቆሮ. 14፥20። ሕፃናት በተፈጥሯቸው እራስ ወዳዶች ናቸው። ስለ ራሳቸ ውና ለሚያስፈልጓቸው ነገሮች ብቻ ነው የሚያስቡት። ለመቀበል እንጂ ለመስጠት አይችሉም። ይህ ጨቅላ አስተሳሰብ ነው። የሚያሳዝነው ግን ብዙ ሰዎች ፈጽሞ ይህን ከመሰለ አስተሳሰብ ያለፈ እድገት የሌላቸው መሆኑን ነው። እራስ ወዳድ የሆነ አስተሳሰብ የኃጢአታዊ ባህርይ ምንጭ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገል ጣል፡- *«እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸ ውን በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ»* ሮሜ 8፥5።

*አስተሳሰብህ ስሜትህን ይወስናል፤ ስሜትህ ደግሞ በድርጊትህ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል።*

እንደ ኢየሱስ ማሰብ የሆነው ሁለተኛ ክፍል፣ *በሳል* አስተሳሰብን *መጀመር* ነው።

ይህም በራስህ ሳይሆን በሌሎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በፍቅር ምንነት ላይ ባተኮረው በዚህ ትልቅ ምዕራፍ፣ ለሌሎች ማሰብ የመብሰል ወይም የማደግ ምልክት መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፡- «*ልጅ ሳለሁ፣ እንደ ልጅ እናገር ነበር፣ እንደ ልጅም አስብ ነበር። ከጐለመስሁ በኋላ ግን የልጅነትን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቻለሁ* » 1ቆሮ. 13+11።



ዛሬ ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ እድገት የሚለካው፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ ህና በምታውቀው አስተምህሮ ነው ብለው ያስባሉ። እውቀት የእድገት አንድ መለኪያ ቢሆንም፣ ነገሩ እዚያ ላይ አያበቃም። የክርስትና ሕይወት ከእምነት አንቀፅና ከእምነት አቋማችን በጣም ይልቃል፤ አኗኗርና ባህርይህንም ይጨምራል። ድርጊታችን ከእምነት አንቀጾቻችን ጋር መስማማት አለበት። እምነቶቻችንም የክርስቶስን በመሰለ ባሕርይ መታጀብ ይኖርባቸዋል።

ክርስትና፣ ሃይማኖት ወይም ፍልስፍና ሳይሆን፣ ግንኙነትና የሕይወት ዘይቤ ነው። የሕይወት ዘይቤ ዋና መሠረት፣ ኢየሱስ እንዳደረገው ከራሣችን ይልቅ ለሌሎች ማሰብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል* » ሮሜ 15+2-3።

ለሌሎች ማሰብ ክርስቶስን የመምሰል ዋናውና ማዕከላዊ ነገር ነው። ለክርስትና ሕይወት እድገት ማረጋገጫነቱም ከሁሉ የላቀ ማስረጃ ነው። እንዲህ ያለው አስተሳሰብ፣ በቀላሉ የማይመጣ፤ ያልተለመደ፣ ከባህል ጋር የማይጣጣምና አስቸጋሪ ነው። ደስ የሚያሰኘው ነገር እርዳታ ያለን መሆኑ ነው። «*ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ፣ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤ ይህም እግዚአብሔር በነፃ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው*» 1ቆሮ. 2+12። በሚቀጥሉት ጥቂት ምዕራፎች፣ በክርስትናችን እንድናድግ ይረዳን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች እንመለከታለን።

### ሀያ ሦስተኛ ቀን
### ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** በክርስትና ሕይወት ማደግን ምን ጊዜም ብንጀምረው ዘገየ አይባልም።

**ላስታወሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ፣ ይህን ዓለም አትምሰሉ»* ሮሜ 12፥2።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** በራሴ መንገድ ማሰቤን አቁሜ፣ በእግዚአብሔር መንገድ ላስብ የሚገባኝ በምን ጉዳይ ላይ ነው?

# 24

# በእውነት መለወጥ

*ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።*

*ማቴ. 4፥4*

*አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም ሊያንጻችሁና በቅዱሳን ሁሉ መካከል ርስት ሊያወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃል አደራ እሰጣችኋለሁ።*

*የሐዋ. 20፥32*

እውነት ይለውጠናል።

መንፈሳዊ እድገት ውሸትን በእውነት የመተካት ሂደት ነው። ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጸልይዋል፡- *«በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው»* ዮሐ. 17፥17። ቅድስና መገለጥን ይፈልጋል። የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የእግዚአብሔር ልጅን እንድንመስል የሚያደርገን በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ነው። ኢየሱስን እንመስል ዘንድ፣ ሕይወታችንን በቃሉ መሙላት አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናትና በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብ ሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው» 2ጢሞ. 3፥16-17።*

የእግዚአብሔር ቃል እንደሌላ ማንኛውም ቃል አይደለም። ሕያው ነው፣ ዕብ. 1፥12፤ የሐዋ. 7፥38፤ 1ጴጥ. 1፥23። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ *«እኔ የነገርኳችሁ ቃል፣ መንፈስም፣ ሕይወትም ነው» ዮሐ. 6፥63።* እግዚአ ብሔር ሲናገር ነገሮች ይለወጣሉ። በዙሪያህ ያለ ነገር፣ ተፈጥሮ ሁሉ ህያው የሆነው *«እግዚአብሔር ስለተናገረ»* ሲሆን፤ ወደ መኖር ያመጣቸውም

በቃሉ ነው፡፡ ያለ እግዚአብሔር ቃል ህያው ልትሆን አትችልም ነበር፡፡ ያዕ ቆብ እንዲህ ይላል፡- *«የፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን» ያዕ. 1÷18፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ*፣ ከአስተምህሮ *መጽሕፍት መመሪያነት* እጅግ የላቀ ነው፡፡

*የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የእግዚአ ብሔር ልጅን እንድንመስል የሚያደርገን በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ነው፡፡*

የእግዚአብሔር መጽሐፍ ሕይወት ይሰ ጣል፣ እምነትን ይፈጥራል፣ ለውጥ ያመ ጣል፣ ዲያብሎስን ያስፈራራል፣ ተዓምራት ያደርጋል፣ ደዌን ይፈውሳል፣ ባሕርይን ያንጻል፣ ሁኔታዎችን ይለውጣል፣ ደስታን ይሰጣል፣ መከራን ያሸንፋል፣ ፈተናን ድል ያደርጋል፣ ተስፋን ያድሳል፣ ኃይል ይሰ ጣል፣ አእምሯችንን ያነፃል፣ ነገሮችን ህያው ያደርጋል፣ ለወደፊት ዕድላችን ዘላለማዊ ዋስትናን ይሰጣል! ስለሆነም በቀላሉ አትመልከተው፡፡ የምግብን ያህል ለሕይወትህ አስፈላጊ ነገር አድርገህ ልትቆጥረው ይገባል፡፡ ኢዮብ እንዲህ ብሏል ፡- «*ከአፉ ከወጣው ትዕዛዝ አልራቅሁም፣ የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዣለሁ*» ኢዮብ 23÷12፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ዓላማህን ለማከናወን ትችል ዘንድ መመገብ የሚኖ ርብህ መንፈሳዊ ምግብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ወተት፣ እንጀራ፣ ጽኑ መብል፣ እና ጣፋጭ ምግብ ነው ተብሏል፤ 1ጴጥ. 2÷2፤ ማቴ. 4÷4፤ 1ቆሮ. 3÷2፤ መዝ. 119÷103፡፡ እነዚህ አራት ተከታታይ ምግቦች፣ ለመንፈሳዊ ጥንካሬና ዕድገት ይሆኑ ዘንድ፣ በመንፈስ ቅዱስ የምግብ ዝርዝር ላይ የቀረቡ ናቸው፡፡ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ይመክረናል፡- «*አዲስ እንደተወለዱ ሕፃናት ንጹሁን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ*» 1ጴጥ. 2÷2፡፡

## በእግዚአብሔር ቃል መኖር

ዛሬ፣ ከመቼውም ይልቅ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሶች በመታተም ላይ ናቸው፡፡ መደርደሪያ ላይ የሚቀመጥ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ጥቅም የለውም፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኞች በመንፈሳዊ ጠኔ ተይዘው፤ በመንፈሳዊ ምግብ እጥረት እስከ ሞት በመራብ ላይ ናቸው፡፡ ጤናማ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ትሆን ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር ቃል መመገብን ከማንኛውም ነገር ማስቀደም አለብህ፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- «*በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ*» ዮሐ. 8÷31፡፡ በዕለት ከዕለት ኑሮ በእግዚአብሔር ቃል መኖር ሦስት ክንውኖችን ይጠይቃል፡፡

**ሥልጣኑን መቀበል** አለብኝ:: መጽሐፍ ቅዱስ ለሕይወቴ ዋናው ባለሥል ጣን መሆን አለበት፤ የምተማመንበት የአቅጣጫ አመልካቼ፣ ተገቢ ውሣኔ ለመስጠት እችል ዘንድ የማዳምጠው አማካሪዬ፣ እና ማንኛውንም ነገር የምመ ዝንበት ማጣቀሻዬ ነው:: በሕይወቴ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ መሆን አለበት::

ብዙዎች ችግሮቻችን የሚመጡት፣ ምርጫዎቻችንን በማያስተማምኑ ነገሮች፣ ማለት፣ በባህል («ሰው ሁሉ ያደርገዋል»)፣ ልማድ («ሁልጊዜ እናደርገዋለን»)፣ ምክንያት («ተገቢ ነገር ይመስላል»)፣ ወይም ስሜት («ትክክል ይመስላል») በሚሉት ላይ ስለምንመሠርት ነው:: እነዚህ አራቱም ከወድቀት የመጡ ስህተቶች ናቸው:: የሚያስፈልገን፣ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የማይመራ ፍፁም መመሪያ ነው:: ለዚህ ፍላጎታችን መልስ ያለው የእግዚአ ብሔር ቃል ብቻ ነው:: ሰሎሞን እንዲህ በማለት ያስታውሰናል :- «*የእግዚአ ብሔር ቃል ሁሉ እንከን የለበትም*» ምሳሌ 30÷5:: ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ በማለት ይገልጣል:- «*ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናትና በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው» 2ጢሞ. 3÷16-17::*

ቢሊግርሃም የአገልግሎታቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት እና ስልጣን ይሰማቸው ከነበረ ጥርጣሬ ጋር የታገሉባቸው ጊዜዎች ነበሩ:: በጨረቃ በደመቀ አንድ ምሽት ለጸሎት ተንበረከኩና ይህንኑ ችግራቸውን ከእንባ ጋር ለእግዚአብሔር ነገሩት:: ከዚያ ዕለት አንስቶ የማይገባቸው የንባብ ክፍሎች ቢኖሩም እንኳን፣ መጽ ሐፍ ቅዱስን የሕይወታቸውና የአገልግሎታቸው ዋና ባለሥልጣን አድርገው እንደሚያምኑ ለእግዚአብሔር ቃል ገቡ:: ከዚያ ወዲህ የቢሊግርሃም ሕይወት ባልተለመደ ሁኔታ በኃይልና በውጤታማነት ተባረከ::



ዛሬ ልታደርገው የሚገባ ከሁሉ የሚልቅ ውሳኔ፣ የሕይወትህ ዋና ባለሥልጣን ምን መሆኑን መወሰን ነው:: በዙሪያህ ያለው ባህል፣ ልማድ፣ ምክንያቶች ወይም ስሜቶች ምንም ይሁኑ ምን፣ መጽሐፍ ቅዱስን የሕይወትህ የመጨረሻ ባለሥልጣን አድርግና ምረጥ:: ውሳኔ ስታደርግ፣ በመጀመሪያ «መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?» ብለህ ለመጠየቅ ወስን:: እግዚአብሔር አንድ ነገር አድርግ በሚልህ ጊዜ፣ ምንም እንኳን ነገሩ ባይገባህና ልታደርገውም የማይቻ

ልህ ቢመስልህ፣ ቃሉን ለማመንና የታዘዝከውን ለማድረግ ወስን። *«በሕጉ ያለውን፣ በነቢያትም የተጻፉትን ሁሉ አምኜ ...»* የሐዋ. 24፥14፣ የሚለውን የጳውሎስ ቃል የእምነትህ ማረጋገጫ አድርገህ ተጠቀምበት።

**እውነቱን ከሕይወቴ ማዋሀድ አለብኝ።** መጽሐፍ ቅዱስን ማመኑ ብቻ በቂ አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ በእውነቱ ዓማካይነት ይለውጠኝ ዘንድ አእምሮዬን በቃሉ መሙላት አለብኝ። ይህን የማድረጊያ አምስት መንገዶች አሉ፤ እነሱም ልትቀበለው፣ ልታነበው፣ ልትመረምረው፣ ልታስታውሰው፣ ልታሰላስለው ትችላለህ የሚሉት ናቸው።

አንደኛ:- የእግዚአብሔርን ቃል *የምትቀበለው* በተከፈተ፣ እንዲሁም ለመቀበል በተዘጋጀ ሁኔታ ስታደምጥና ስትረዳው ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውስጣችን ሥር ሰዶ ያፈራ ዘንድ፣ ቃሉን የመቀበላችን ሁኔታ ወሳኝ መሆኑን የዘሪው ምሳሌ በግልጥ ያስገነዝበናል። ኢየሱስ፣ ተቀባይነት የሌላቸውን ሦስት ሁኔታዎች ለይቶ አመልክቷል። እነሱም፣ ዝግ ልብ (የመንገድ ዳር አፈር)፣ አስመሳይ ልብ (አለታማ አፈር)፣ ያልተደላደለ ልብ (እሾህ የበቀለበት አፈር) ናቸው። ከዚያም እንዲህ አለ:- *«እንዴት እንደትሰሙ ተጠበቁ»* ሉቃስ 8፥18 ።

ከመልዕክት ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ምንም የማትማር መሆንህ በሚሰማህ ጊዜ ሁሉ፣ አስተሳሰብህን መርምር፤ በተለይ ኩራትህን። ምክንያቱም ትሁት ሆነህ ለመቀበል በተዘጋጀ ሁኔታ ውስጥ ከሆንክ፣ እግዚአብሔር በጣም አሰልቺ በሆነ አስተማሪም እንኳን ይናገራል። ያዕቆብ እንዲህ በማለት ይመክረናል:- *«ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን፣ በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በትህትና ተቀበሉ።»* ያዕ. 1፥21።

ሁለተኛ፣ በ2000 ዓመታት የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡት ካህናት ብቻ ነበሩ። ዛሬ ግን በቢሊዮን የምንቆጠር ሰዎች ዕድሉ አለን። ይህ ሆኖ ሳለ ግን ብዙ አማኞች ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ይልቅ፣ ዕለታዊ ጋዜጦችን ለማንበብ ይበልጥ ታማኞች ናቸው። አለማደጋችን አያስደንቅም። ለሦስት ሰዓት ቴሌቪዥን ስንመለከት ቆይተን ለሦስት ደቂቃ ያህል ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እናድጋለን ብለን ማሰብ የለብንም።

መጽሐፍ ቅዱስን ከዘፍጥረት እስከ ራእይ እናምነዋለን የሚሉ ብዙ ሰዎች፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ አንብበውት አያውቁም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች ብቻ ብታነብ፣ ሙሉውን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ውስጥ አጠናቅቀህ ታነበዋለህ። ከቴሌቪዥን የመመልከቻ ፕሮግራምህ ሰላሳ ደቂቃዎች ብትቀንስና ለመጽሐፍ ቅዱስ ማንበቢያነት ብታውለው፣ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በዓመት ሁለት ጊዜ ታነበዋለህ።

*መጽሐፍ ቅዱስን ከዘፍጥረት እስከ ራእይ እናምነዋለን የሚሉ ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ አንብበውት አያውቁም።*

መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ ማን በብ፣ የእግዚአብሔር ድምፅ በሚሰ ማበት እርቀት ላይ እንድትቆይ ያደር ግሃል። ለዚህ ነው ቃሉን አንድ ቅጂ ሁል ጊዜ ከአጠገባቸው እንዳይለዩ እግዚአብሔር የእስራኤልን ነገሥታት ያዘዛቸው፡- «*የዚህን ሕግ ቃል ሁሉና ይህን ሥርዓት በጥንቃቄ ይከተል ዘንድ፣ ከእርሱ ጋር ይሁን፤ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ያንብበው* » ዘዳግ. 17፥19። አጠገብህ ማኖር ብቻ አይደለም፤ ዘወትር አን ብበው። ይህን ለማድረግ የሚረዳ ቀላል ዘዴ፣ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበቢያ ዕለታዊ ዕቅድ ማውጣት ነው። የዕቅዱ መኖር መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዘፈ ቀደ በየሥፍራው ከመዝለልና ክፍሎቹን ባለማስተዋል ከማለፍ ይጠብቅሃል።

ሦስተኛ በቃሉ ለመኖር የሚረዳ ሌላ ተግባራዊ መንገድ፣ *መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር ወይም ማጥናት* ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና በማጥናት መካከል ያለው ልዩነት ሁለት ተጨማሪ ሥራዎችን ያካትታል። እነርሱም ስለ አነበብከው ክፍል ጥያቄን መጠየቅና የተረዳኸውን እውነት በጽሑፍ ማስፈር ናቸው። መረዳትህን በወረቀት ወይም በሌላ ነገር ላይ ካልመዘገብከው መጽሐፍ ቅዱስን አላጠናህም።

የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎችን ለመግለጥ ሥፍራ አይበ ቃኝም። ከሀያ ዓመት በፊት እኔ የጻፍኩትን ጨምሮ፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን የሚጠቅሙ ብዙ መጻሕፍት አሉ። ጥሩ መጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ምስጢር፣ ትክክለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅ ነው። ንባብህን ቆም አድርገህ ማን? ምን? መቼ? የት? ለምን? እና እንዴት? የሚሉትን ቀላል ጥያቄዎች ብትጠይቅ፣ የበለጠ ነገር ትረዳለህ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፍጹም ሕግ ተመልክቶ የሚጸና የሰማውን የሚያደርግና የማይ ረሳ ሰው በሥራው የተባረከ ይሆናል*» ያዕ. 1፥25።

በእግዚአብሔር ቃል የመኖሪያ አራተኛው መንገድ ያነበብከውን ቃል *ማስታ ወስ* ነው። የማስታወስ ችሎታህ ከእግዚአብሔር ነው የተሰጠህ። የማስታወስ ችሎታዬ ደካማ ነው ትል ይሆናል፣ እውነቱ ግን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አሳ ቦች፣ እውነቶች፣ እርግጥ የሆኑ ነገሮች፣ እና የምታስታውሳቸው አንዞች አሉህ። ለአንተ *ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን* ነው የምታስታውሰው። የእግዚአብ ሔር ቃል ጠቃሚህ ከሆነ፣ ጊዜ ሰጥተህ ታስተውሰዋለህ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማስታወስ የሚገኙ አያሌ ጥቅሞች አሉ።

ፈተናን ለመከላከል፣ ብልህነት የሞላበት ውሳኔ ለመስጠት፣ ጭንቀትን ለመቀ ነስ፣ በራስ መተማመንን ለማዳበር፣ መልካም ምክር ለመለገስ፣ እና እምነትህን ለሌሎች ለማካፈል ይረዳሃል፣ መዝ. 119፥11፤ 119፥105፤ 119፥49-50፤ ኤር. 15፥16፤ መዝ. 22፥18፤ 1ጴጥ. 3፥15።

የማስታወስ ችሎታችን እንደጡንቻ ነው። በተጠቀምክበት ቁጥር ይበልጥ ይጠነክራል። በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህን ማስታወሱ ቀላል ይሆ ንልሃል። እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል አሳብህን የነኩትን ትንሽ ካርድ ላይ በመመዝገብ ወደምትሄድበት ሁሉ ይዘሃ ቸው ልትሄድ ትችላለህ። እንዲህ ካደረግህ በኋላ በቃልህ ቀኑን ሙሉ ደጋ ግማቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን፣ ስትሠራ፣ የአካል እንቅስቃሴ ስታ ደርግ፣ ተሽከርካሪ ስትነዳ፣ ሰው ስትጠብቅ ወይም ተኝተህ ልታጠና ትችላለህ። መጽሐፍ ቅዱስን የማጥኛ ሦስት መንገዶች፣ ማጥናት፣ ማጥናት እና ማጥናት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑር ባችሁ»* ቈላስ. 3፥16።

በእግዚአብሔር ቃል የመኖሪያው አምስተኛ መንገድ፣ ቃሉን በጽሞና ማሰብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ማሰላሰል» ይለዋል። የማሰላሰል አሳብ ለብዙዎች ከእውነታ በመውጣት፣ አንድ ምትሃታዊ ቅርፅ በአእምሮ በመፍጠር ባልተ ጨበጠ አሳብ መንከራተት ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ማሰላሰል ወይም ማስተዋል ፍፁም ተቃራኒ ነው። ማሰላሰል አንድ ነገር ላይ *ያተኮረ ማሰብ* ነው። ከባድ ጥረትን ይጠይቃል። አንድ ጥቅስ መርጠህ ያንን በአእምሮህ ደጋግመህ ታሰላስለዋለህ።

ምዕራፍ 11 ውስጥ እንደጠቀስኩት፣ መጨነቅን ካወቅህ፣ ማሰላሰልንም ታውቃለህ ማለት ነው። ጭንቀት አሉታዊ በሆነ ነገር ላይ ያተኮረ ማሰላሰል ነው። ማሰላሰልም ተመሳሳይ ሆኖ፣ ከራስህ ችግር ይልቅ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ ማትኮር ነው።

**ሃያ አራተኛ ቀን በእውነት መለወጥ**

በየዕለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን ከማሰላሰል ይበልጥ ሕይወትህን የሚለውጥና፣ ይበልጥ ኢየሱስን እንድት መስል ሊያደርግህ የሚችል ሌላ ልማድ የለም። የክር ስቶስን ምሳሌ በመከተል፣ ጊዜ መድበን የእግዚአብሔርን እውነት ከልብ በምናሰላስልበት ጊዜ :- *«የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን»* 2ቆሮ. 3፥18።

እግዚአብሔር ስለ ማስተዋል ወይም ማሰላሰል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠውን ብዙ ጊዜ ብትመለከት፣ ጊዜ ሰጥተው ቃሉን ለሚያሰላስሉ ሁሉ

ተስፋ የገባላቸውን ጥቅሞች በመረዳት እጅግ ትደነቃለህ:: እግዚአብሔር ዳዊትን:- «*እንደልቤ የሆነ ሰው* » የሐዋ. 13÷22 ያለበት አንዱ ምክንያት፣ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተዋል በመውደዱ ነው:: እንዲህ ብሏል:- «*አቤቱ፣ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ! ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ* » መዝ. 119÷97:: የእግዚአብሔርን እውነት ከልብ ማሰላሰል፣ መልስ ለሚያገኙ ጸሎቶች ቁልፍ እና ስኬት ያለው ሕይወት መገኛ ምስጢርም ነው፣ ዮሐ. 15÷7፤ ኢያሱ 1÷8፤ መዝ. 1÷1-2::

***መመሪያዎቹን በተግባር መተርጎም*** አለብኝ:: ቃሉን በተግባር እስካልተረጎምን ድረስ መቀበል፣ ማንበብ፣ መመርመር፣ ማስታወስ፣ እና ማሰላሰል ፋይዳ የላቸውም:: «*ቃሉን አድራጊዎች*» ያዕ. 1÷22 መሆን አለብን:: ከሁሉም አስቸጋሪው እርምጃ ይህ ነው:: ምክንያቱም እዚህ ላይ ሰይጣን በጥብቅ ይዋጋናል:: በተማርከው መሠረት አንዳች ነገር የማታደርግ እስከሆንክ ድረስ፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሄድህ አያስጨንቀውም::

አንድን እውነት በመስማታችን፣ በማንበባችን ወይም በማጥናታችን ብቻ እውስጣችን ሰርፅዋል ብለን ካመንን፣ እራሳችንን እናታልላለን:: የተማርከውን በተግባር ለመተርጎም እስከማትችል ድረስ፣ ወደ ቀጣዩ ክፍለ ትምህርት፣ ሴሚናር፣ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈረንስ በመሄድ ሥራ የሚበዛብህ ሰው ትሆን ይሆናል:: ወደ ቀጣዩ ጥናትህ በምትሄድበት ጊዜ ያለፈውን ትምህርት ትረሳለህ:: በተግባር እስካልተተረጎሙ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶቻችን ሁሉ ዋጋ አይኖራቸውም:: ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- «*ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል፣ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራን ብልህ ሰው ይመስላል*» ማቴ. 7÷24:: ኢየሱስ በተጨማሪም የእግዚአብሔር በረከት የሚመጣው፣ እውነትን ከመታዘዝ እንጂ፣ ከማወቅ ብቻ አለመሆኑን እንዲህ በማለት ገልጧል፤ «*ይህን ብታውቁ፣ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ*» ዮሐ. 13÷17::

> ***እውነት ነፃ ያወጣሃል፤ በመጀመሪያ ግን፣ ብስጩ ወይም ሀዘንተኛ ያደርግህ ይሆናል::***

***መመሪያን በግል ሕይወታችን ከመተርጎም የምንሸሽበት ሌላ ምክንያት፣*** አስቸጋሪ፣ እንደውም ስቃይ ያለበት ሊሆን ስለሚችል ነው:: እውነት ነፃ ***ያወጣሃል***፤ *መጀመሪያ ግን* ሀዘንተኛ *ያደርግህ* ይሆናል! የእግዚአብሔር ቃል የልብ አሳባችንን ያጋልጣል፣ ስሕተቶቻችንን ለይቶ ያመለክታል፣ ኃጢአታችንን ይገልጣል፣ እናም እንድንለወጥ ይፈልጋል:: ለውጥን መቃወም ሰብዓዊ ተፈጥሮ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በሥራ መተርጎሙ ከባድ ሥራ ነው::

ለዚህ ነው የእግዚአብሔርን ቃል በግል ሕይወትህ መተርጎምህን በተመለከተ ከሌሎች ሰዎች ጋር መወያየትህ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው።

የአንድ አነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አባል መሆን እጅግ አስፈላጊ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። በራሳችን ጥረት ልንረዳ የማንችላቸውን እውነቶች ከሌሎች እንማራለን። ሌሎች ሰዎች ያላስተዋልካቸውን ነገሮች እንድታይና የእግዚአብሔርን እውነት በተግባር እንድትተረጉም ይረዱሃል። የቃሉ «አድራጊ» የመሆኛው ተመራጭ መንገድ፣ ባነበብከው፣ ባጠናኸው ወይም ባሰላሰልከው የእግዚአብሔር ቃል ግንዛቤ ላይ በመመሥረት፣ ልትወስድ የወሰንካቸውን የተግባር እርምጃዎች ሁል ጊዜ መጻፍ ነው። ልታደርግ ያሰብከውን የመጻፍ ልምድ አዳብር። ይህ ድርጊት፣ *ግላዊ* (አንተን የሚመለከት)፣ *ሊደረግ የሚቻል* (አንተ ልታደርገው የምትችለው)፣ እና *የሚረጋገጥ* (የከንውኑ ፍፃሜ ጊዜ *የተወሰነ*) መሆን አለበት። ማንኛውም ትግበራ፣ ከእግዚአብሔር፣ ከሌሎች ሰዎች ወይም ከግል ባሕርይህ ጋር የሚኖሩህን ግንኙነቶች ያካትታል።

የሚቀጥለውን ምዕራፍ ከማንበብህ በፊት፣ ይህን ጥያቄ በማሰላሰል ጥቂት ጊዜ አሳልፍ፤ ገና ማድረግ ያልጀመርከውና፣ እንድታደርገው እግዚአብሔር በቃሉ የነገረህ ነገር ምንድነው? በተረዳኸው መሠረት ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚረዱህ ጥቂት የድርጊት መግለጫዎችን ጻፍ። ድርጊቶቹን ማከናወን አለማከናወንህን ሊከታተል ለሚችል ጓደኛህ መንገር ያስፈልግህ ይሆናል። ዲ.ኤል.ሙዲ እንደሚለው፡- «መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠን እውቀት እንዲጨምርልን ሳይሆን፣ ሕይወታችንን እንዲለውጥ ነው።»

ሀያ አራተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** እውነት ይለውጠኛል፡፡

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል»* ዮሐ. 8፥31፡፡

**ልብ ልለው የሚገበ ጥያቄ ፡-** ገና ማድረግ ያልጀመርኩት፣ አደርገው ዘንድ እግዚአብሔር የነገረኝ ነገር ምንድነው?

# 25

# በችግር መለወጥ

*ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል።*

2ቆር. 4+17

*የእግዚአብሔር ሰው መሆንን እንደ ወርቅ አጥርቶ የሚያወጣው የመከራ እሳት ነው።*

ማዳም ጉዮን

ከእያንዳንዱ ችግር ጀርባ እግዚአብሔር አንድ ዓላማ አለው። ባህርያችንን ለመቅረጽ በሁኔታዎች ይጠቀማል። ኢየሱስን እንድን መስል የሚያደርገንም፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ይልቅ በሁኔታዎች ላይ በመመሥረት ነው። ምክንያቱ ግልጥ ነው፤ በቀን ውስጥ ሃያ አራት ሰዓት ከሁኔታዎች ጋር ትጋፈጣለህ።

በዓለም እስካለን ችግሮች የሚገጥሙን መሆኑን በመግለጥ ኢየሱስ አስጠንቅቆናል፣ ዮሐ. 16+33። በሽታ የማያጠቃው፣ መከራ የማይነካው ወይም ከችግር ነፃ በመሆን በሕይወት ጎዳና ላይ ስተት ብሎ የሚጓዝ ሰው የለም። ሕይወት የችግሮች ፍርርቆሽ ነው። አንደኛውን ችግር በተወጣኸው ቁጥር፣ ሌላው ለመተካት ይጠብቃል። ሁሉም ትልልቅ ችግሮች አይደሉም፤ አንተን በማሳደግ የእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ግን፣ ጠቃሚ ናቸው። ችግሮች ያሉ ወይም የተለመዱ መሆናቸውን ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ያረጋግጥልናል፡- «*እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደደረሰባችሁ በመቁጠር አትደነቁ*» 1ጴጥ. 4+12።

እግዚአብሔር ወደ ራሱ ሊያቀርብህ በችግሮች ይጠቀማል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፣ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል*» መዝ. 34+18። በጣም ትልል

ቆቹና ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ የአምልኮ ልምምዶችህ፣ ጭለማ በሆኑ ቀኖች ማለት፣ የልብ ስብራት በደረሰብህ፣ ብቻህን የሆንህ በመሰለህ፣ ምርጫ ባጣህበትና ሕመምህ በከፋ ጊዜ የምታደርጋቸው፣ ፊትህን ወደ እግዚአብሔር ብቻ የምትመልስባቸው ናቸው:: በመከራ ጊዜ ነው እውነተኛ፣ ከልብ የሆነና ማስመሰል የሌለበት ጸሎት መጸለይን የምንማረው:: በጭንቅ ጊዜ እንደ ነገሩ የሆነ ጸሎት የሚያስጸልይ ብርታት አይኖረንም::

ጆኒ ኤርክሰን ታዳ የተባሉ ሴት እንዲህ ብለዋል:- «ሕይወት ያማረ በሚሆንልን ጊዜ፣ ስለ ኢየሱስ በማወቅ፣ እርሱን በመምሰል፣ አባባሎቹን በመጥቀስና ስለ እርሱ በመናገር እንኖራለን:: እሱን የምናውቀው ግን በመከራ ጊዜ ነው::» ስለ እግዚአብሔር የምንማረው ከሌላ መንገድ ይልቅ በመከራ ነው::

እግዚአብሔር ዮሴፍን እሥር ቤት እንዳይገባ ዘፍጥ. 39፥20-22፣ ዳንኤል አንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንዳይጣል ዳን. 6፥16-23፣ ኤርምያስ ጠባብ ጉድጓድ ወስጥ እንዳይጣል፣ ጳውሎስ ሦስት የመርከብ አደጋዎች እንዳይደርሱበት 2ቆሮ. 11፥25፣ እና ሦስቱ ዕብራዊያን እቶን እሳት ውስጥ እንዳይጣሉ ዳን. 3፥1-26 ሊያደርግ ይችል ነበር፤ ግን አላደረገውም:: እነዚያ ችግሮች እንዲሆኑ ፈቀደ፤ በመከራዎቹ ውስጥ ያለፉት ሰዎችም ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ ቀረቡ::

*በጣም ትልልቆቹና ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ የአምልኮ ልምምዶችህ ጭለማ በሆኑ ቀኖችህ የምታከናውናቸው ናቸው*

ችግሮች ወደ እግዚአብሔር እንድንመለከትና ከራሳችን ይልቅ በእርሱ እንድንደገፍ ያስገድዱናል:: ይህን ጠቀሜታ አስመልክቶ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይመሰክራል:- «*በእርግጥ የሞት ፍርድ እንደተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው፣ ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው*» 2ቆሮ. 1፥9:: ያለህ እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ እስካልታየህ ድረስ፣ የሚያስፈልግህ እሱ ብቻ መሆኑን በፍፁም ልታውቅ አትችልም::

ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ከችግሮችህ የትኛውም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይደርስብህም:: የእግዚአብሔር ልጅ በሆነ ሰው ላይ የሚደርስ ማንኛውም ነገር *በአባት (በእግዚአብሔር) በኩል ያለፈ ስለሚሆን*፣ ሰይጣንና ሌሎቹም ለክፋ ቢያደርጉት እንኳን እሱ ለመልካም ይጠቀምበታል::

እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ስለሚቆጣጠር፣ አደጋዎች እርሱ ለአንተ ባለው ዕቅድ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮች ናቸው:: የሕይወትህ ማንኛውም ዕለት፣ ከመወለድህ በፊት በእግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ስለተጻፈ

መዝ. 139+16፣ *የሚደርስብህ ነገር ሁሉ መንፈሳዊ ጠቀሜታ አለው*፣ ሮሜ 8+28-29:: ይህ የሆነበትን ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጠዋል:- *«እግዚአብሔር ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚደረግላቸው እናውቃለን:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኩር እንዲሆን ነው»* ሮሜ 8+28-29::

*የሚደርስብህ ነገር ሁሉ መንፈሳዊ ትርጉም አለው ::*

## ሮሜ 8+28-29ን መረዳት

በጣም ብዙ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ከሚጠቀሱና የተሳሳተ ግንዛቤ ከተሰጣቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች አንዱ ይህ ነው:: ይህ ቃል «እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር እኔ በፈለግኩት መንገድ እንዲከናወን ያደርጋል» አይልም:: በግልጥ እንደሚታወቀው ይህ እውነት አይደለም:: በሌላም በኩል:- «እግዚአ ብሔር ማንኛውንም ነገራችንን በምድር ላይ አስደሳች ፍፃሜ እንዲኖረው ያደርጋል» አይልም:: ይህም እውነት አይደለም:: በምድር ላይ ብዙ የማያስ ደስቱ ፍጻሜዎች አሉ::

በወደቀ ዓለም ውስጥ ነው የምንኖረው:: በመንግሥተ ሰማያት ብቻ ነው ሁሉም ነገር እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት ፍፁም በሆነ መንገድ የሚከና ወነው:: ለዚህ ነው እንዲህ ብለን እንድንጸልይ የተነገረን:- «*ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣ እንዲሁም በምድር ትሁን* » ማቴ. 6+10:: ሮሜ 8+28-29ን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት፣ ቃሉን ሐረግ በሐረግ መመልከት አለብህ::

**«እናውቃለን»**፤ በአስቸጋሪ ጊዜ ተስፋችን የሚመሠረተው፣ ቀና ቀናውን በማሰብ፣ መልካም ምኞት ባለው አስተሳሰብ ወይም በተፈጥሯዊ ተስፋ ላይ አይደለም:: እግዚአብሔር የዓለማችን ፍፁም ተቆጣጣሪ፣ ገዥና የሚያፈቅረን በመሆኑ እውነት ላይ ነው::

**«እግዚአብሔር ... እንዲሠራ»**፤ ከማንኛውም ነገር ጀርባ ታላቅ ዕቅድ አውጪ አለ:: ሕይወትህ እንዲሁ የሆነ ዕድል፣ ዕጣ ወይም የመልካም አጋጣሚ ውጤት አይደለም:: ሁሉን ያቀፈ ትልቅ ዕቅድ አለ:: ታሪክህ *የእርሱ (የእግዚአብሔር ) ታሪክ*፣ አንቀሳቃሹም እርሱ ነው:: እኛ እንጂ እግዚአ ብሔር በፍፁም አይሳሳትም:: እርሱ ሊሳሳት አይችልም፤ ምክንያቱም እግዚ አብሔር ነው::

**«ነገር ሁሉ»**፤ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዕቅድ፣ የሚደርስብህን ነገር ሁሉ ማለት፣ ስሕተቶችህን፣ ኃጢአቶችህን እና የሚገጥሙህን ጉዳቶች

ሁሉ ያካትታል:: በሽታን፣ ዕዳን፣ አደጋን፣ የትዳር መፍረስን እና የምትወዳ ቸውን ሰዎች ሞትም ይጨምራል:: እግዚአብሔር እጅግ ከከፋ ነገር መልካ ምን ያወጣል:: ይህን ቀራንዮ ላይ አድርጎታል::

**«ተያይዞ ... እንዲሠራ»!** በተናጠል ወይም አንዱ ከሌላው ተለይቶ አይ ደለም:: በሕይወትህ የሚከናወኑ ነገሮች፣ በእግዚአብሔር *ዕቅድ* ውስጥ *ተያ ይዘው ይሠራሉ*:: የተነጣጠሉ ድርጊቶች ሳይሆኑ፣ ክርስቶስን እንድትመስል በሚከናወነው ሂደት ውስጥ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው:: ኬክ ለመጋገር ዱቄት፣ ጨው፣ ጥሬ እንቁላሎች፣ ስኳር እና ዘይት ያስፈልጉሃል:: እነዚህ ነገሮች በተናጠል ሲበሉ አይጥሙ ይሆናል:: አዋህደህ ስትጋግራቸው ግን ይጣፍጣሉ:: መራራ እና የማያስደስቱ ልምምዶችህን ለእግዚአብሔር ብታስ ረክበው ለበጎ ያዋህዳቸዋል::

**«ለበጎ»!** ይህ ቃል፣ በሕይወትህ ሁሉ ነገር በጎ ነው አይልም:: በዓለማችን ከሚከናወኑ ነገሮች ብዙዎቹ ክፉ እና መጥፎ ናቸው:: ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ ካለው ክፉ ውስጥ በጎ ነገርን በማውጣት የተካነ ነው:: በግልጥ በታ ወቀው የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ፣ ማቴ. 1÷1-16፣ አራት ሴቶች ተመዝግበዋል! እነሱም፣ ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት እና ቤርሳቤህ ናቸው:: ትዕ ማር የባሏን አባት አታላ የግብረሥጋ ግንኙነት በመፈፀም አረገዘች! ረዓብ ሴትኛ አዳሪ ነበረች! ሩት አይሁዳዊት ሳትሆን አይሁዳዊ ወንድ በማግባት የአ ይሁዳውያንን ሕግ ጣሰች! ቤርሳቤህ ከዳዊት ጋር አመነዘረች! ይህ ድርጊቷም የባሏን መገደል አስከተለ:: እነዚህ መልካም ስም ያላቸው አልነበሩም:: ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር በጎ አወጣና በእነርሱ የዘር ሐረግ በኩል ኢየ ሱስ መጣ:: የእግዚአብሔር ዓላማ፣ ከችግሮቻችን፣ ከስቃያችን እና ከኃጢአ ታችን እንኳን በላይ ነው::

**«ለሚወዱትና ... ለተጠሩት »!** ይህ ተስፋ የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑ አማኞች ብቻ ነው! ለማንኛውም ሰው አይደለም:: እግዚአብሔርን በመጻረር ለሚኖሩና በራሳቸው መንገድ ለሚፀኑ ነገር ሁሉ *ለክፉ* ይሆንባቸዋል::

**«እንደ ሐሳቡም»!** *ያ* አሳብ ምንድነው? **«የልጁን መልክ እንድንመስል»** ነው:: እግዚአብሔር በሕይወትህ ይከናወን ዘንድ የሚፈቅደው ነገር ሁሉ፣ ለዚህ ዓላማ ነው የተፈቀደው!

## ክርስቶስን የሚመስል ባሕርይ ማዳበር

እኛ በመከራ መሮና መዶሻ ተጠርበው እንደ ተሠሩ ጌጦች ነን:: ሻካራ ጠርዛችንን የጠራቢው መሮ ለመጥረብ ጥንካሬ የማይኖረው ከሆነ፣ እግዚአ

ብሑር በመራጃ ወይም በትልቅ መደሻ ይጠቀማል:: ግትሮች ከሆንን ደግሞ ከዚያም በገዘፈ መደሻ ይጠቀማል:: አስፈላጊ በሆነ መሣሪያ ሁሉ ይገለገላል::

ማንኛውም ችግር የባህርይ ማዳበሪያ መልካም አጋጣሚ ነው:: ችግሩ በከበደ መጠን ደግሞ፣ መንፈሳዊ ጡንቻን በማፈርጠምና ሞራልን በማጎልበት ረገድ የሚኖረው አቅም ከፍ ያለ ይሆናል:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «*በመከራችንም ሐሴት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን:: ትዕግሥት ፅናትን፣ ፅናት የተፈተነ ባህርይን፣ የተፈተነ ባህርይ ተስፋን*» ሮሜ 5+3-4:: በሕይወትህ ውጫዊ ክፍል የሚሆነው ነገር፣ *እውስጥህ የሚ*ሆነውን ያህል ጠቃሚ አይደለም:: ያለህበት ሁኔታ ጊዜያዊ ሲሆን፣ ባሕርይህ ግን ለዘላለም ይኖራል::

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ፈተናን፣ የብረትን አላስፈላጊ ነገር ከሚያስወግደው የብረት ማቅለጫ እሳት ጋር ያመሳስለዋል:: ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል:- «*በእሳት ተፈትና ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ*» 1ጴጥ. 1+7-8 :: አንድ አንጥረኛ፤ «የምታነጥረው ብር ንፁህ ሆኗል የምትለው መቼ ነው?» የሚል ጥያቄ ቀረበለት:: እርሱም:- «ምስሌን እውስጡ ስመለከት» ብሎ መለሰ:: ሕይወትህ በመከራ በሚጠራበት ጊዜ ሰዎች የኢየሱስን ምስል እውስጥህ ይመለከታሉ:: ያዕቆብ እንዲህ ብሏል:- «*የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ*» ያዕ. 1+3::

*በሕይወትህ ውጫዊ ክፍል የሚሆነው ነገር፣ እውስጥህ የሚሆነውን ያህል ጠቃሚ አይደለም::*

የእግዚአብሔር አሳብ፣ አንተን ኢየሱስን ማስመሰል ስለሆነ፣ ኢየሱስ ባለፈበት ተመሳሳይ ልምምድ ውስጥ ያሳልፍሃል:: ልምምዱም፣ ብቸኝነትን፣ ፈተናን፣ ጭንቀትን፣ ነቀፋን፣ ጥላቻን፣ እና ሌሎች ብዙ ችግሮችን ያካትታል:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ይላል:- «*ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ* » ዕብ. 5+8:: እግዚአብሔር፣ የገዛ ልጁ እንዲያልፍበት ከፈቀደው ልምምድ እኛን ለምን ነፃ ያደርገናል? ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- «*የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን*» ሮሜ 8+17::

## ለችግሮቻችን ኢየሱስ የሰጠውን ዓይነት ምላሽ መስጠት

ችግሮች ወዲያውኑ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር አያመጡም:: ብዙ ሰዎች የተሻሉ ከመሆን ይልቅ፣ ይበልጥ መራር ይሆናሉ፣ እናም በፍጹም

አያድጉም። ለችግሮችህ የምትሰጠው መልስ ኢየሱስ የሚሰጠው ዓይነት መሆን አለበት።


**የእግዚአብሔር ዕቅድ መልካም መሆኑን አስታውስ።** እግዚአብሔር ከሁሉ የሚሻልህን ነገር ያውቃል፣ የሚያስበውም ያንኑ ነው። ኤርምያስን እንዲህ ብሎታል:- «*ለእናንተ ያሰኝን እቅድ እኔ አውቃለሁ ... ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚሰጥ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም*» ኤር. 29÷11። ዮሴፍ ለባርነት የሸጡት ወንድሞቹን:- «*እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ... ለበጎ ነገር አዋለው*» ዘፍ. 50÷20፣ ባላቸው ጊዜ ይህን እውነት ተገንዝቦ ነበር። ሕዝቅያስም ለሞት የሚያበቃ ሕመም ባደረበት ጊዜ ተመሳሳይ ስሜት ነበር ያስተጋባው:- «*እነሆ በሥቃይ የተጨነቅሁት፣ ለጥቅሜ ሆነ*» ኢሳ. 38÷17። ከመከራ እንዲያወጣህ ወደ እግዚአብሔር ስትጮህ ምላሹ «እይሆንም» ከሆነ ይህንን አስታውስ:- «*አባቶቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር፤ እግዚአብሔር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለእኛ ጥቅም ይቀጣናል።*» ዕብ. 12÷10።

በስቃይህ ወይም በችግርህ ላይ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ በማት ኮር መጽናትህ ወሳኝ ነው። ኢየሱስ የመስቀሉን ሥቃይ የተቋቋመው እንዲህ ነው። እኛም የእርሱን ምሳሌ እንድንከተል እንዲህ በሚል ቃል እንበረታታ ለን:- «*የእምነታችን ጀማሪና ፍጻሜ አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታገሠ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል* » ዕብ. 12÷2። ኮሪ ቴን ቡም የተባሉና በናዚ የሞት እሥር ቤት ውስጥ የነበሩ ሴት የትኩረትን ኃይል እንዲህ ገልጠውታል:- «ወደ ዓለም ብትመለከት ተስፋ ትቆርጣለህ። ወደ ውስጥህ ብትመለከት በትካዜ ትዋ ጣለህ። ወደ ክርስቶስ ብትመለከት ግን እረፍትን ታገኛለህ!» ትኩረትህ ስሜት ህን ይወስነዋል።

**የጽናት ምስጢሩ፣ ሥቃይህ ጊዜያዊ፣ ዋጋህ ግን ዘላለማዊ መሆኑን ማስታ ወስ ነው።** ሙሴ በሕይወቱ ችግሮች በበዙበት ጊዜ ጸንቷል፤ ምክንያቱም:- «*ወደፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቶአልና*» ዕብ. 11÷26። ጳውሎስ በተመሳሳይ ሁኔታ በፈተና በመጽናት እንዲህ ብሏል:- «*ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል*» 2ቆሮ. 4÷17።

**ለአጭር ጊዜ አስተሳሰብ አትሸነፍ።** በመጨረሻው ውጤት ላይ አትኩር:- «*ልጆች ከሆንን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን*» » ሮሜ 8÷17።

**ደስ ይበልህ፣ አመስግንም።** መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ሳታቋርጡ*



*ፀልዩ፤ በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና» 1ተሰ. 5፥17-18 ::* ይህ እንዴት ይቻላል? እግዚአብሔር የነገረን፣ *«በሁሉ እንድናመሰግን»* እንጂ *«ስለሁሉ እንድናመሰግን»* ያለመሆኑን ልብ በል:: *ለክፋ፣ ለኃጢአት፣ ለመከራ* ወይም በዓለም ውስጥ ከነዚህ ለሚመነጨው *ሥቃይ ሰዘል* ውጤት ምሥጋና እንድታቀርብ እግዚአብሔር አይጠብቅም:: ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ችግርህን ለዓላማው መፈፀሚያ የሚጠቀም በት በመሆኑ እንድታመሰግነው ይፈልጋል::

*መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «ምን ጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ» ፊልጵ.* 4፥4:: «ስለ ስቃይህ ደስ ይበልህ» አላለም:: እንዲህ ያለው ሁኔታ በስቃይ የመርካት በሽታ ነው:: ደስ የሚልህ *«በጌታ»* ነው:: ምንም ይሁን ምን፣ በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ጥበቃ፣ ጥበብ፣ ኃይል እና ታማኝነት ደስ ይልሃል:: ኢየሱስ እንዲህ አለ:- *«እነሆ፣ ወርታችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና፣ በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ፣ ፈንድቁም»* ሉቃስ 6፥23::

እግዚአብሔር በስቃያችን ውስጥ አብሮን በማለፍ ላይ መሆኑን በማወቅም ደስ ሊለን ይችላል:: የምናገለግለው አምላክ እሩቅና ገለልተኛ ሆኖ ዳር በመቆም የተለመደውን ዓይነት የአይዟችሁ ማበረታቻ ቃል የሚወረውር አይደለም:: መከራችን ውስጥ ይገባል:: ኢየሱስ ሥጋ በመልበሱ ይህን አደረገ፤ የእርሱ መንፈስ ዛሬም በእኛ ውስጥ ይህን ያደርጋል:: እግዚአብሔር በፍፁም ለብቻችን አይተወንም::

ሃያ አምስተኛ ቀን

**በችግር መለወጥ**

**«አሁንስ በቃኝ» አትበል::** ትዕግስተኛና ቆራጥ ሁን:: *መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «መከራ ሲደርስባችሁ፣ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት:: ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ:: ምንም የማይጎድላችሁ ፍጹማንና ምሉዓን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈፅም» ያዕ.* 1፥2-4::

ባሕርይ የማሳደግ ሂደት ዝግ ያለ ነው:: የሕይወታችንን ችግር ለማስወገድ ወይም ከዚያ ለማምለጥ በሞከርን ቁጥር፣ ዑደቱን እናቋርጠዋለን፣ እድገታችንን እናዘገየዋለን፣ በመሆኑም ፍጻሜያችን የከፋ ስቃይ ይሆናል፤ የሽሽትና እውነታን የሚክድ፤ የማይረባ ሕይወት:: ስለ ባህርይ ዕድገት ዘላለማዊ ውጤት እርግጠኛ በምትሆንበት ጊዜ፣ *«አፅናኝ»*፣ *«መልካም ስሜት እንዲኖረኝ እርዳኝ»*፣ የሚለው ጸሎትህ ጥቂት እየሆነ፣ *«አስበጀኝ»*፣ «ይህን ተጠቅመህ

ይበልጥ አንተን የምመስል አድርገኝ» የሚለው ፀሎትህ ይበዛል::

የእግዚአብሔርን እጅ ባልተጠበቁ፣ ግራ በሚያጋቡና፣ ትርጉም የለሽ በሚመስሉ የሕይወትህ ሁኔታዎች ውስጥ ሲገለጥ በምታይበት ጊዜ፣ በማደግ ላይ መሆንህን ታወቃለህ::

አሁን በችግር ውስጥ ከሆንክ «ለምን እኔን?» ብለህ አትጠይቅ:: ከዚያ ይልቅ «ምን እንድማር ትፈልጋለህ?» በል:: ከዚያም በእግዚአብሔር ታመንና ትክክል የሆነን ነገር ማድረግህን ቀጥል:: *«የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ፣ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋል»* ዕብ. 10+36:: «አሁንስ በቃኝ» አትበል- ማደግህን ቀጥል::

ሃያ አምስተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:- ከእያንዳንዱ ችግር ጀርባ አንድ ዓላማ አለ::

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ :- *«እግዚአብሔርን ለሚወዱት፣ እንደሐሳቡም ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን»* ሮሜ 8+28::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ :-** በሕይወቴ ትልቁን እድገት ያመጣው ችግር ምንድነው?

# 26

# በፈተና ውስጥ ማደግ

*በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ የሕይወትን አክሊል ያገኛል፡፡*

*ያዕ. 1፥12*

*ፈተናዎች ሰ[illegible] መሰከት ውቀቱ ከፍተኛ ድገሪዎች ናቸው፡፡*

*ማርቲን ሉተር*

ማንኛውም ፈተና መልካም ነገር ለማድረግ ጥሩ አጋጣሚ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ዕድገት ጉዞህ ላይ፣ ፈተና ክፉ ነገር ለማድረግ አጋጣሚ እንደሚሆን ሁሉ፣ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግም ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን በምትረዳበት ጊዜ፣ ፈተና እንቅፋት ከመሆን ይልቅ እንደ መረማመጃ ይሆንልሃል፡፡ ፈተና የሚያቀርብልህ ምርጫን ነው፡፡ ሰይጣን አንተን ለማጥፋያነት የሚጠቀምበት ዋና መሣሪያው ፈተና ቢሆንም፣ እግዚአብሔር አንተን ለማሳደጊያነት ይፈልገዋል፡፡ ከኃጢአት ይልቅ መልካም ነገር ለማድረግ በምትመርጥበት ጊዜ ሁሉ የክርስቶስን ባህርይ በማዳበር ላይ ነህ፡፡

ይህን ለመረዳት፣ በመጀመሪያ የኢየሱስን ባህርያት ለይተህ ማወቅ አለብህ፤ የኢየሱስ ባህርያት ትክክለኛ መግለጫ ከሆኑት አንዱ፣ የመንፈስ ፍሬ ነው፡- *«የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው»* ገላ. 5+22፡፡

እነዚህ ዘጠኝ መስፈርቶች፣ ታላቁ ትዕዛዝ ሰፋ ብሎ የተገለጠባቸው ሲሆኑ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ባህርይ ውብ ክሆነ መንገድ ይገልጣሉ፡፡ ኢየሱስ፣ ፍፁም ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ እና ሌሎቹም የመንፈስ ፍሬዎች በአንድ አካል የተገለጡበት ነው፡፡ የመንፈስ ፍሬ

በውስጣችን አለ ማለት፣ ኢየሱስን መሰልን ማለት ነው።

እንዴት ነው ታዲያ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ዘጠኝ የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወትህ የሚያፈራቸው? በቅፅበት ነው የሚፈጥራቸው? አንድ ቀን ከእንቅልፍህ ስትነቃ ወዲያውኑ ባህርያቱን በዳበረ ሁኔታቸው ትሞላቸዋለህ? እንዲያ አይሆንም። ፍሬ ሁልጊዜ የሚያድገውና የሚበስለው *ቀስ በቀስ ነው።*

ቀጥሎ ያለው ዓረፍተ ነገር በሕይወትህ ከምትማራቸው እጅግ ጠቃሚ መንፈሳዊ እውነቶች አንዱን ይገልጣል። እግዚአብሔር፣ መንፈስ ቅዱስን በሕይወትህ የሚያሳድገው፣ ከሚጠበቅብህ ባሕርይ *ፍፁም ተቃራኒውን እንድታሳይ* በሚፈትኑህ ሁኔታዎች ውስጥ እንድታልፍ በመፍቀድ ነው። የባህርይ እድገት ሁል ጊዜ ምርጫን ያካትታል፤ ምርጫ እንዲኖር የሚያደርገው ደግሞ ፈተና ነው።


*እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በሕይወትህ የሚያሳድገው፣ ከሚጠበቅብህ ባሕርይ ፍፁም ተቃራኒ የሆነን ምላሽ እንድትሰጥ በሚፈትኑህ ሁኔታዎች ውስጥ እንድታልፍ በመፍቀድ ነው።*

ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር *ለመውደድ የሚያስቸግሩ* ሰዎችን በዙሪያችን በማኖር ፍቅርን ያስተምረናል። የሚወደዱና የሚወዱህን ሰዎች መውደዱ ያደገ ባሕርይን አይጠይቅም። ሀዘን ውስጥ ሆነን ወደ እርሱ ፊታችንን ስንመልስ፣ እግዚአብሔር እውነተኛ ደስታን ያስተምረናል። ጊዜያዊ *ደስታ* በውጫዊ ሁኔታዎች፣ እውነተኛ ደስታ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው።

እግዚአብሔር ነገሮች እኛ ባቀድነው መሠረት እንዲሄዱ በማድረግ ሳይሆን፣ የትርምስና ግራ የመጋባት ጊዜን በሕይወታችን እንዲመጣ በመፍቀድ እውነተኛ *ሰላምን* በውስጣችን ያዳብራል። አንድ ሰው ውብ የፀሐይ መጥለቅ ትዕይንትን በመመልከት ወይም በእረፍት ጊዜው በመዝናናት ሰላም ሊኖረው ይችላል። እውነተኛ ሰላምን ለመማር የምንችለው ግን፣ እንድንጨነቅ ወይም እንድንፈራ በሚያደርጉን ሁኔታዎች ውስጥ ሆነን በእግዚአብሔር ለመታመን በመምረጥ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ትዕግሥትን በሕይወታችን የምናዳብረው፣ እንድንጠብቅ በሚያስገድዱንና እንድንቆጣ ወይም እንድንበሳጭ በሚፈትኑን ሁኔታዎች ውስጥ ሆነን ነው።

እግዚአብሔር ምርጫን የሚፈቅድልን፣ እያንዳንዱን የመንፈስ ፍሬ በተቃራኒ ሁኔታ በመጠቀም ነው። መጥፎ ለመሆን ተፈትነህ የማታውቅ ከሆንክ፣ ጥሩ ሰው ነኝ ለማለት አትችልም። ታማኝነትህን በሚፈትን አጋጣሚ

ውስጥ ካላለፍክ፣ ታማኝ ነኝ ማለቱ ይሳንሃል:: ሀቀኝነት፣ እምነት የማጉደል ፈተናን በማሸነፍ ይገነባል፤ ትህትና የሚያድገው ደግሞ መታበይ አሻፈረኝ ሲባል ነው:: ጽናት የሚያድገው፣ ተስፋ ቆርጠህ እንድትተወው ሰሚገዳደርህ ፈተና የማትበገር በሆንህ ጊዜ ሁሉ ነው:: አንድን ፈተና ድል ባደረግህ ጊዜ ሁሉ ይበልጥ ኢየሱስን እየመሰልክ ትሄዳለህ::



## የፈተና አሠራር

የሰይጣን አሠራር በሙሉ ሊታወቅ የሚቻል መሆኑን መረዳቱ ይጠቅማል:: ሰይጣን ከፍጥረት መጀመሪያ አንስቶ በተመሳሳይ እስትራተጂና ተንኮሎች ነው ሚጠቀመው:: ፈተናዎቹ ሁሉ ተመሣሣይ አሠራሮችን ነው የሚከተሉት:: ለዚህ ነው ጳውሎስ:- «*የእርሱን ዕቅድ አንስተውምና*» 2ቆሮ. 2÷11 ያለው:: ሰይጣን፣ በአዳምና ሄዋን፣ እንዲሁም በኢየሱስ ላይ የተጠቀመባቸው አራት የፈተና ደረጃዎች መኖራቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን::

በአንደኛ ደረጃ፣ እውስጥህ ያለውን *ፍላጎት* ሰይጣን ያውቀዋል:: ኃጢአታዊ ፍላጎት ሊሆን ይችላል፤ የበቀል ወይም ከሌሎች የበላይ የመሆን:: ወይም ደግሞ ተገቢ የሆነ ፍላጎት ለምሳሌ፣ ለመፈቀር፣ ለመከበር፣ ወይም ለመደሰት መፈለግ:: ፈተና የሚጀምረው፣ ተገቢ ላልሆነ አንድ ፍላጎት እንድትሸነፍ ወይም ተገቢ የሆነን ፍላጎት በተሣሣተ መንገድ ወይም ጊዜ እንድትፈጽም ሰይጣን አሳብ በሚያቀርብልህ ጊዜ ነው:: በአቋራጭ መንገድ ላለመሄድ ሁልጊዜ ተጠንቀቅ:: አቋራጭ አካሄዶች ብዙ ጊዜ ፈተናዎች ናቸው:: ሰይጣን እንዲህ በማለት ያንሾካሹክልሃል:- «ለአንተ ነው የሚገባ! አሁኑኑ የራስህ ልታደርገው ይገባል! አስደሳች ... ምቹ... ይሆንልሃል፤ ወይም የተሻለ ስሜት እንዲኖርህ ያደርጋል::»

ፈተና በዙሪያችን ነው ያለው ብለን እናስባለን፤ እግዚአብሔር የሚነግረን ግን *እውስጣችን* የሚጀምር መሆኑን ነው:: ውስጣዊ ፍላጎት ከሌለህ፣ ፈተና ሊያጠቃህ አይችልም:: ፈተና ሁል ጊዜ የሚጀምረው በሁኔታዎች ሳይሆን፣ አእምሮህ ወስጥ ነው:: ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- «*ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጡት ክፉ ሐሳብ ምንዝር፣ ስርቆት፣ ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ መስገብገብ፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው፤ እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውንም ያረክሱታል*» ማር. 7÷21-23:: ያዕቆብ ደግሞ:- «*በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት*

*የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚዋጉት ምኞታችሁ አይደለምን?*» ያዕ. 4፥1 ይለናል፡፡

ሁለተኛ ደረጃ፣ *ፕርጣሬ ነው፡፡* ሰይጣን፣ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት የተናገ ረውን እንድንጠራጠርና እንዲህ እንድንል ሊያደርገን ይሞክራል፡- «በእውነት ይህ ስህተት ነውን? በእርግጥ እግዚአብሔር ይህን አታድርግ ብሏልን? እግዚአ ብሔር ይህን የከለከለው ሌላን ሰው፣ ወይም ሌላ ጊዜን አይደለምን? ደስ እንዲ ለኝ እግዚአብሔር አይፈልግምን?»፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ በማለት ያስ ጠነቅቀናል፡- «*ማንም ከሕያው እግዚአብሔር የሚያስኮበልል፣ ኃጢአትና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠንቀቁ*» ዕብ. 3፥12፡፡

*ፈተና በዙሪያችን ነው ያለው ብለን እናስባለን፤ እግዚአብሔር የሚነግረን ግን፣ እውስጣችን የሚጀምር መሆኑን ነው፡፡*

ሦስተኛ ደረጃ፣ *ማታለል*፡፡ ሰይጣን እውነት ለመናገር ስለማይችል፣ «*የሐሰ ትም አባት*» ዮሐ. 8፥44፣ ተብሏል፡፡ የሚነግርህ ነገር ሁሉ፣ ሐሰት ወይም ግማሽ እውነት ይሆናል፡፡ ሰይጣን፣ እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረውን ለመተካት ሲል፤ «አትሞትም፤ እንደ እግዚአብሔር አዋቂ ትሆናለህ፡፡ ምንም አይመጣብህም፤ በፍፁም ማንም አያውቅብህም፡፡ ችግርህን ያስወግድልሃል፤ ሁሉ የሚያደርገውና ትንሽ ኃጢአት እኮ ነው» በማለት ውሸቱን ይደረድራል፡፡ ይሁን እንጂ ትንሽ ኃጢአ ት እንደጽንስ ነው፤ ቀስ በቀስ እራሱን ይገልጣል፡፡

አራተኛ ደረጃ፣ *አለመታዘዝ ነው፡፡* አእምሮህ ውስጥ ስታጫውተው የቆየኸውን ኃጢአት በድርጊት ትገልጠዋለህ፡፡ እንደ አሳብ የተጀመረው ነገር፣ ፀባይ ሆኖ ይወለዳል፡፡ ትኩረትህን ለያዘው ነገር ሁሉ ትሸነፋለህ፡፡ የሰይጣንን ውሸት በማመን ያዕቆብ እንዲህ በማለት ከሚያስጠነቅቀን ወጥመድ ውስጥ እንዳትገባ ተጠንቀቅ፡- «*ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው፣ በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው፡፡ ምኞት ከፀነሰች በኋላ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፤ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ አትሳቱ*»

*ያዕ. 1፥14-16፡፡*

## ፈተናን ማሸነፍ

የፈተናን አሠራር መረዳቱ ይጠቅማል፡፡ ታሸንፈው ዘንድ ልትወስዳቸው የሚገቡ የተለዩ እርምጃዎችም እነሆ፡-

አትፍራ፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች፣ የሚፈትኑ አሳቦችን ለማሸነፍ ባለመቻ ላቸው የበደለኛነት ስሜት እየተሰማቸው፣ ከመፈተን «ያለፍኩ» አይደለሁም

ይላሉ፣ ተስፋም ይቆርጣሉ፣ በመፈተናቸው ያፍራሉ። ይህ በክርስትና ሕይወት መብሰልን በትክክል አለመረዳት ነው። *መቼም ቢሆን* ከፈተና ነፃ አትሆንም።

በአንድ በኩል ፈተናን እንደ በጐ ነገር ልንቆጥረው እንችላለን። ክፉ ፈቃዱን በመፈፀም ላይ ያሉ ሰዎች የራሱ ስለሆኑ ሰይጣን አይፈትናቸውም። ፈተና የድካም ወይም የዓለማዊነት ምልክት ሳይሆን፣ ሰይጣን የሚጠላህ የመሆኑ ምልክት ነው። ሰው በመሆናችንና በወደቀው ዓለም በመኖራችን የሚመጡብን ነገሮች ክፍልም ነው። በመሆኑም በፈተና አትደነቅ፣ አትደንግጥ ወይም ተስፋ አትቁረጥ። ፈተና አይቀሬ መሆኑንና ሙሉ በሙሉ ልታስወግደው የማትችል መሆንህን ተገንዘብ። መጽሐፍ ቅዱስ፡- «*ማንም ሲፈተን*» እንጂ፤ «*ከተፈተናችሁ*» አይልም። ጳውሎስ እንዲህ ይመክራል፡- «*ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም።» 1ቆሮ. 10፥13።*

*መፈተን* ኃጢአት አይደለም። ኢየሱስ በፍፁም ኃጢአት አልሠራም እንጂ ተፈትኖ ነበር፤ ዕብ. 4፥15። ፈተና ኃጢአት የሚሆነው፣ በተሸነፍክለት ጊዜ ብቻ ነው። ማርቲን ሉተር እንዲህ ብሏል፡- «አእዋፍ ከእራስህ በላይ እንዳይበሩ ልትከለክላቸው አትችልም፤ እራስህ ላይ ጎጆአቸውን እንዳይሠሩ ለማድረግ ግን ትችላለህ»። ሰይጣን አሳቦችን እንዳያቀርብልህ ልትከለክለው አትችልም። የሚያቀርብልህን አሳብ እምቢ ልትለው ግን ትችላለህ።

ለምሳሌ ብዙ ሰዎች በአካላዊ መስህብ እና በግብረሥጋዊ መነሣሣት መካከል ያለውን ልዩነት አያውቁም። ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። እግዚአብሔር ሁላችንንም ግብረሥጋዊ ተራክቦ የምንፈጽም ሰዎች አድርጎ ነው የፈጠረን። መልካም ነው። አካላዊ መስህብና ግብረሥጋዊ መነሣሣት፣ ተፈጥሯዊ፣ ድንገተኛና ለአካላዊ ውበት አፀፋነት ይውል ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠህ ሲሆን፣ *መመኘት* ግን ሆን ብሎ የሚፈፀም *ፈቃዳዊ ድርጊት ነው።*

*ፈተና ሰይጣን የሚጠላህ የመሆኑ እንጂ፣ የድካም ወይም የዓለማዊነት ምልክት አይደለም።*

ምኞት፣ በአካልህ ለማድረግ የምትፈልገውን ነገር፣ በአእምሮህ ለመፈጸም የምትመርጥበት ክንውን ነው። ኃጢአት የመሥራት ፍላጎት ሳይኖርህ፣ በተቃራኒ ፆታ ውበት የመሳብና የስሜት መነሣሣት ይገጥምህ ይሆናል። ብዙ ሰዎች፣ በተለይም ክርስቲያን ወንዶች፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ከሆነ ሰውነታቸው ያሉ ሆርሞኖች በመሥራታቸው በደለኛነት ይሰማቸዋል። እንዲት ውብ ሴት እንደተመለከቱ፣ የመመኘት ኃጢአት የፈፀሙ ያህል ስለሚቆጥሩት፣ ሃፍ

ረትና በደለኛነት ይሰማቸዋል:: ውብታዊ መስህብ በአካል ለማድረግ የምንፈልገውን ማሰላሰል እስካልሄደ ድረስ ኃጢአት አይደለም::

ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ በቀረብክ መጠን፣ ሰይጣንም ይበልጥ ሊፈትንህ ይሞክራል:: በእምነት የእግዚአብሔር ልጅ ስትሆን፣ ሰይጣን እንደተደራጀ የወንጀለኞች ቡድን መሪ ሊያጠፋህ «ኮንትራት» ይዋዋልብሃል:: ጠላቱ ነህ፤ ስለዚህም ለውድቀትህ በማሴር ላይ ነው::

አንዳንዴ፣ በመጸለይ ላይ እያለህ ሰይጣን አሳብህን ሊያዛባና ሊያሳፍርህ በማቀድ፣ ያልተለመደ ክፉ አሳብ ወደ አእምሮህ ያመጣል:: በድርጊቱ አትደናገጥ ወይም አትፈር፤ ሰይጣን ጸሎትህን ስለሚፈራው ሊያሰናክልህ የተቻለውን ሁሉ የሚያደርግ መሆኑን ግን ተገንዘብ:: «እንዲህ ያለውን ነገር እንዴት አሰባለሁ?» በማለት እራስህን ከመኮነን፣ ድርጊቱ የሰይጣን ጣልቃ ገብነት መሆኑን ተገንዘብና ትኩረትህን በፍጥነት በእግዚአብሔር ላይ አድርግ::

**የምትፈተንበትን ሁኔታ ለይተህ እወቅና ንቁ ሁን::** ከሌሎቹ ይልቅ ለፈተና ይበልጥ የሚያጋልጡህ አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ:: አንዳንዶቹ ወዲያውኑ እንድትወድቅ ሲያደርጉህ፣ ሌሎቹ ምንም አያስቸግሩህም:: እነዚህ ሁኔታዎች በተለይ በድካምህ ላይ የሚመጡ ስለሆኑ ለይተህ ልታውቃቸው ይገባል:: ምክንያቱም የሚያሰናክልህ ምን መሆኑን ሰይጣን *በትክክል* ስለሚያውቅ፣ ወደ ሁኔታዎቹ ሊወስድህ ያለማቋረጥ ይተጋል:: ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ያስጠነቀቀናል:- *«ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፣ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያና ወዲህ ይዞራል»* 1ጴጥ. 5+8::



«*መቼ ነው* በጣም የምፈተነው? ከሳምንቱ *በየትኛው ቀን?* ከቀኑ *በየትኛው ጊዜ? የት ነው* በጣም የምፈተነው? በሥራ ቦታ? ቤት? በጎረቤት? በእስፖርት ቦታ? ከከተማ ውጭ? አይሮፕላን ማረፍያ? ወይስ እንግዶች ማረፊያ ሆቴል ውስጥ?»

እንዲህ ብለህም ጠይቅ:- «በጣም በተፈተንኩ ጊዜ *አብሮኝ የነበረ ማነው?* ጓደኞቼ? የሥራ ባልደረባዎቼ? የማላውቃቸው ሰዎች? ወይስ ብቻዬን ነበርኩ?»:: ይህንንም ጠይቅ:- «በጣም በምፈተንበት ወቅት *ምንድነው የሚሰማኝ?*» የምትፈተነው በምትደክምበት፣ ብቻህን በምትሆንበት፣ በሚሰለችህ እና በተከፋህ ጊዜ ሊሆን ይችላል:: ጉዳት በደረሰብህ፣ በተቆጣህ፣ በተጨነቅህ፣ አንዳች ታላቅ ነገር በተከናወነልህ ወይም መንፈሳዊ ከፍታ በተሰማህ ጊዜም ይሆናል::

የምትፈተንባቸውን የተለዩ ሁኔታዎች ለይተህ ማወቅና በተቻለህ መጠን ከሁኔታዎቹ ለመራቅ የተዘጋጀህ መሆን አለብህ:: ፈተና ይመጣል ብለን

እንድንጠብቅና እንደ አመጣጡ ለመጋፈጥ እንድንዘጋጅ መጽሐፍ ቅዱስ በመደ
ጋገም ይነግረናል፣ ማቴ. 26+41፤ ኤፌ. 6+10-18፤ 1ተሰ. 5+6፣8፤
1ጴጥ. 1+13፤ 4+5፤ 5+8:: ጳውሎስ:- «*ለዲያብሎስም ሥፍራ አትስጡት*»
ኤፌ. 4+28፣ ብሏል:: በብልሀት ማቀድ ፈተናን ይቀንሳል:: መጽሐፈ ምሳሌ
ውስጥ እንዲህ የተባለውን ምክር ተከተል:- «*የእግርህን መንገድ አቅና፣ አካሄ
ድህም ሁሉ ይጽና:: ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል፤ እግርህን ከክፉ መልስ*»
ምሳሌ 4+26-27:: «*የቅኖች ጐዳና ከክፋት መራቅ ነው፤ መንገዱን የሚጠብቅ፣
ሕይወቱን ይጠብቃል*» ምሳሌ 16+17::

የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠይቅ:: እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜና ወቅት
አስቸኳይ ጥሪ የመቀበያ ልዩ መስመር አለው:: ፈተናን ለመቋቋም እርዳታ
ትጠይቀው ዘንድ ስለሚፈልግ እንዲህ ብሏል:- «*በመከራ ቀን ጥራኝ፣ አድንህ
ማለሁ፣ አንተም ታከብረኛለህ*» መዝ. 50+15::

ይህን ጸሎት እኔ «ፈጥኖ ደራሽ» እለዋለሁ:: ይህን የምልበት ምክንያት
ፈጣን ሆኖ እቅጩን የሚገልጥ በመሆኑ ነው:: ድረስ
ልኝ! አድነኝ! እርዳኝ! የሚለው ጸሎት:: ፈተና በድንገት
ሲያጠቃህ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ረጅም ውይይት የማድ
ረጊያ ጊዜ ስለማይኖርህ፣ የምታደርገው ነገር ቢኖር
መጮህ ብቻ ነው:: ዳዊት፣ ዳንኤል፣ ጴጥሮስ፣ ጳው
ሎስ፣ እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ችግር በገጠማ
ቸው ጊዜ እንዲህ ያለውን ፈጣን ጸሎት ጸልየዋል::



እግዚአብሔር የድረስልኝ ጩኸታችንን የሚሰማ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ
ዋስትና ይሰጠናል:: ይህ የሚሆነው ኢየሱስ ድካማችንን የሚረዳና የሚራራ
ልን በመሆኑ ነው:: የሚገጥሙን ፈተናዎች እሱንም ገጥመውታል::
«*በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ
በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን::*» ዕብ. 4+15::

እግዚአብሔር ፈተናን እንድናሸንፍ ሊረዳን በመጠባበቅ ላይ ከሆነ፣ ለምን
ድነው ፊታችንን ወደእርሱ የማንመልሰው? እውነቱን ለመናገር፣ አንዳንድ ጊዜ
እርዳታ *ለንሻም*! ስህተት መሆኑን ብናውቅም፣ በፈተና መሸነፍን *እንፈልጋ
ለን*:: ይህን የምናደርገው፣ እግዚአብሔር ለእኛ ከሚያውቀው ይልቅ፣ የሚሻ
ለንን እናውቃለን ብለን ስለምናስብ ነው::

ሌላ ጊዜ ደግሞ በተመሳሳይ ኃጢአት በተደጋጋሚ በመሸነፍ ላይ ስለምን
ገኝ፣ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለመጠየቅ እናፍራለን:: እግዚአብሔር ግን
ፍፁም አይታክትም፣ አይሰለችም ወይም በተደጋጋሚ ወደ እርሱ በመቅረባችን

ምክንያት ትዕግሥቱ አያልቅም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እንግዲህ፣ ምህረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ፣ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ »* ዕብ. 4+16።

የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው! ለትዕግሥቱም ፍጻሜ የለውም። አንድን ፈተና ለማሸነፍ የእግዚአብሔርን እርዳታ ፈልገህ በቀን ሁለት መቶ ጊዜ እንኳን ወደ እርሱ ብትጮህ፣ ይቅርታና ጸጋውን ሊሰጥህ ሳይሰለች በጉጉት ይጠብቅሃል። ስለዚህ በድፍረት ወደ እርሱ ቅረብ። ትክክለኛ ነገር ለማድረግ የሚያስችልህ ኃይል እንዲሰጥህ ጠይቀውና እንደሚሰጥህ በማመን ለመቀበል ጠብቅ።

ፈተናዎች በእግዚአብሔር እንድንታመን ያደርጉናል። አንድ ዛፍ ንፋስ በነፈሰበት ቁጥር ሥሮቹ እየበረቱ እንደሚሄዱ፣ ፈተናን በተቋቋምክ ጊዜ ሁሉ ይበልጥ ኢየሱስን ትመስላለህ። በምትሰናከልበት ጊዜ (ትሰናከላለህና)፣ እስከፊ ፍፃሜ ላይ ደረስክ ማለት አይደለም። ያኔ ከመሸነፍ ወይም ተስፋ ከመቁረጥ፣ ወደ እግዚአብሔር ተመልከት፣ እርዳታውን ጠብቅ፣ የኋላ ሽልማትህንም አስታውስ፡-! *«በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል»* ያዕ. 1+12።

ሀያ ስድስተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡- እያንዳንዱ ፈተና፣ መልካም ነገር የማድረጊያ አጋጣሚ ነው።

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡- *«በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል»* ያዕ. 1+12።

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡- የሚገጥመኝን በጣም የተለመደ ኃጢአት በማሸነፍ፣ የክርስቶስን ከሚመስሉ ባህርያት የትኛውን ለማዳበር እችላለሁ?

# 27

# ፈተናን ማሸነፍ

*ከወጣትነት ክፉ ምኞት ሽሽ፣ በንፁሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋርም ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርንና፣ ሰላምን ተከተል ።*

*2ጢሞ. 2፥22*

*በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።*

*1ቆሮ. 10፥13።*

ምን ጊዜም የማምለጫ መንገድ አለ።

አንዳንድ ጊዜ፣ ፈተና ልትሸከመው ከምትችለው በላይ የከበደ መስሎ ይሰማህ ይሆናል። ይህ ከሰይጣን የሚመጣ ውሸት ነው። እግዚአብሔር ፈተናን ትቋቋምበት ዘንድ እውስጥህ ካኖረው አቅም የበለጠ ፈተና እንዲደርስብህ እንደማይፈቅድ ቃል ገብቷል። የማታሸንፈው ማንኛውም ፈተና እንዲደርስብህ አይፈቅድም። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ አራት የፈተና ማሸነፊያ ቁልፍ እርምጃዎችን በመለማመድ የራስህን ድርሻ መወጣት አለብህ።

**ትኩረትህን በሌላ ነገር ላይ አድርግ።** መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *በየትኛውም* ስፍራ «ፈተናን ተቃወሙ» አለመባላችን ያስደንቅህ ይሆናል። «*ዲያብሎስን ተቃወሙት*» ነው የተባልነው። በኋላ እንደምገልጠው ይህ በጣም የተለየ ነገር ነው። የአሳባችንን ትኩረት እንድንቀይር ተመክረናል። ምክንያቱም አሳባችንን መቃወሙ የሚሠራ ነገር አይደለም። የማንፈልገውን አሳብ ላለማሰላሰል ስንሞክር፣ ይበልጥ በአሳቡ ላይ እንድናተኩርና

መስህብነቱን እንዲያጠናክርብን እናደርገዋለን:: ይህን አባባል ይበልጥ ሳብ ራራው:- አንድ አሳብ ወደ አእምሮህ እንዳይገባ ለመከላከል በሞከርህ ቁጥር፣ ይበልጥ ወደ ትውስታ ክፍልህ ታጠልቀዋለህ:: በመቃወም ይበልጥ ታበ ረታዋለህ:: የምትቃወመው ነገር ፈተና ከሆነ፣ ይህ ሁኔታ በእርግጥ ይገጥ ምሃል:: ከፈተና ከሚመጣ ስሜት ጋር በመዋጋት ልታሸንፈው አትችልም:: አንድን ስሜት ይበልጥ በተዋጋኸው ቁጥር ይበልጥ እያደከመ ይቆጣጠርሃል:: ባሰብከው ጊዜ ሁሉ ታጠነክረዋለህ::

*ከኃጢአት ጋር በምታደርገው ጦርነት መሸነፍም ሆነ ማሸነፍ የሚመጣው፣ አእምሮህ ውስጥ ነው:: ትኩረትህን የሳበው ነገር አንተንም ያሸንፍሃል::*

ፈተና ሁልጊዜ በአሳብ ነው የሚጀም ረው:: አሳብን በመማረክ የሚመጣን ፈተና የማስወገጃ ፈጣኑ መንገድ፣ ትኩ ረትህን ሌላ ነገር ላይ ማድረግ ነው:: አትዋጋው፤ የትኩረት አቅጣጫህን ወደ ሌላ ለውጥና በዚያ ላይ አነጣጥር:: ይህ ፈተናን የማሸነፊያ የመጀመሪያ እርምጃ ነው::

በቴሌቪዥን የሚተላለፍ የምግብ ማስታወቂያ ተመልክተህ ወደያውኑ ርሃብ ተሰምቶህ ያውቃል? አንድ ሰው ሲያስል ሰምተህ አንተም ጉሮሮህን የማጥ ራት አሳብ መጥቶብሃል? በጣም የሚያዛጋ ሰው እያየህ አንተም እንደ እርሱ የማዛጋት ፍላጎት አድሮብሃል? (ይህን ስታነብ ምናልባት በማዛጋት ላይ ነህ !):: አሳባችን ወደ አተኮረበት ነገር መሳባችን ብዙ ጊዜ የሚሆን ነገር ነው:: ስለ አንድ ነገር ይበልጥ ባሰብክ ቁጥር፣ ያ ነገር ይበልጥ አጥብቆ ይይዝሃል:: ከኃጢአት ጋር በምታደርገው ጦርነት መሸነፍም ሆነ ማሸነፍ የሚከናወነው አእምሮህ ውስጥ ነው:: ትኩረትህን የሳበው ነገር አንተንም ያሸንፍሃል:: ለዚህ ነው ኢዮብ እንዲህ ያለው :- «*ወደ ኮረዳይቱ ሳልመለከት፣ ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ* » ኢዮብ 31+1:: ዳዊትም እንዲህ ብሎ ነበር:- «*ከንቱ ነገር ከማየት ዓይኖቼን መልስ፣ በራስህ መንገድ እንደገና ሕያው አድርገኝ* » መዝ. 119+37::


ለዚህ ነው «ብዙ መመገብን መተው ይኖርብኛል ... ማጨስን ወይም መጎ ምጀትን ማቆም አለብኝ» ማለቱ እራስን ለተሸናፊነት የሚዳርግ እስትራቴጂ የሚሆነው:: በማትፈልገው ነገር ላይ እንድታተኩር ያደርግሃል:: «እናቴ ያደ ረገችውን ነገር ፈጽሞ አላደርገውም» እንደማለት ነው:: ያንኑ ነገር ለመድገም እራስህን በማዘጋጀት ላይ ነህ::

ውፍረትን ለመቀነስ የምትሞክራቸው ብዙ የምግብ መቀነስ ፕሮግራሞች፣ ሁል ጊዜ ስለ ምግብ እንድታስብና ርሃብ እንዲሰማህ ስለሚያደርጉ አይጠቅሙ

ህም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ንግግር ለማድረግ በመዘጋጀት ላይ ሳለች «አትፍሪ» እያለች በመደጋገም ለራሷ የምትናገር ሴት፣ እራሷን ለፍርሃት ታጋልጣለች! ማድረግ የሚኖርባት፣ ትኩረቷን ከስሜቷ ላይ በማንሣት በእግዚአብሔር፣ በንግግሯ ጠቃሚነት ወይም አድማጮቿ በሚፈልጉት ነገር ላይ ማድረግ ነው፡፡

ፈተና የሚጀምረው፣ ትኩረትህን በመማረክ ነው፡፡ ትኩረትህን የሚያገኝ ነገር ደግሞ ስሜቶችህን ያነሣሣቸዋል፡፡ ስሜቶችህ በተራቸው አመልህን ስለ ሚቀሰቅሱት የተሰማህን ነገር ታደርገዋለህ፡፡ «ይህን ለማድረግ አልፈልግም» በሚለው አሳብ ላይ ባተኮርክ ቁጥር፣ ጉልበቱን አጠንክሮ ወደ መረቡ ይስብሃል፡፡

ፈተናን ከመዋጋት ይልቅ፣ ችላ ማለቱ የበለጠ ውጤት አለው፡፡ የአሳብህ ትኩረት ሌላ ነገር ላይ ከሆነ፣ ፈተና በአንተ ላይ ጉልበት ያጣል፡፡ ስለዚህ፣ ፈተና ስልክ በሚደውልልህ ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር አትከራከር፤ ስልኩን ዝጋው !



አንዳንድ ጊዜ ፈተና ያለበትን ቦታ ትቶ መሄድን ይጠይቃል ማለት ነው፡፡ ትቶ መሸሽ ትክክል የሚሆነው እንዲህ ባለው ጊዜ ነው፡፡ ተነሳና ቴሌቪዥኑን ዝጋው፡፡ በሀሜት ተግባር ላይ ካሉ ሰዎች ተለይ፡፡ ሲኒማ በመመልከት ላይ ከሆንክ አቋርጥና ውጣ፡፡ እንዳትነደፍ ንቦች ካሉበት እራቅ፡፡ ትኩረትህን ወደ ሌላ ነገር ለመለወጥ የተቻለህን ሁሉ አድርግ፡፡

መንፈሳዊነትን በተመለከተ፣ አእምሮህ በጣም የተጋለጠ የአካልህ ክፍል ነው፡፡ ፈተናን ለመቀነስ አእምሮህን በእግዚአብሔር ቃልና በሌሎች ጥሩ አሳቦች ሙላው፡፡ መጥፎ አሳቦችን የምታሸንፋቸው፣ የተሻሉ ነገሮችን በማሰብ ነው፡፡ ይህ ነው የመተካት መርህ፡፡ ክፉን በመልካም ታሸንፈዋለህ፡- ሮሜ 12+21፡፡ አእምሮህ በሌላ ሥራ ከተጠመደ፣ ሰይጣን አሳብህን ሊያገኘውአይ ችልም፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በመደጋገም እንዲህ የሚለን፡- «*ኢየሱስን አስቡ*» ዕብ. 3+1፡፡ «*ኢየሱስ ክርስቶስን አስቡ*» 2ጢሞ. 2+8፡፡

«*እውነት የሆነውን ሁሉ፣ ክቡር የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል የሆነውን ሁሉ፣ ንጹህ የሆነውን ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆነውን ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ወይም ምሥጋና እንደነዚህ ስላሉት ነገሮች አስቡ* » ፊልጵ. 4+8፡፡

ፈተናን ድል የማድረግ ቁርጥ አሳብ ካለህ፣ አእምሮህን መቆጣጠርና ከመገናኛ ብዙሀን የምትወስዳቸውን ነገሮች መመርመር አለብህ፡፡ በምድር

ከኖሩ ሰዎች ሁሉ የላቀ ጥበብ የነበረው ሰው እንዲህ በማለት አስጠንቅቋል፡- *«ለፕብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና»* ምሳሌ 4+23:: የማይረቡ ነገሮችን እንዳሉ ወደ አእምሮህ አታግበስብስ:: የምታስባቸውን ነገሮች በጥንቃቄ ምረጥ:: የጳውሎስን ሞዴል ተከተል፡- *«ለክርስቶስ ለመታ ዘዝ አእምርን ሁሉ እንማርካለን»* 2ቆሮ. 10+5:: ይህ በሕይወታችን የምንለማ መደው ቢሆንም፣ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የአስተሳሰብ አቅጣጫህን ለመለወጥ ትችላለህ::

*ያለብህን ትግል ለበሰለ አማኝ ጓደኛህ ወይም ለሚረዳህ ቡድን ግለጥ::* የገጠመህን ትግል ለመላው ዓለም ማሠራጨት አይኖርብህም:: በታማኝነት የምታካፍለው ቢያንስ አንድ ሰው ግን ያስፈልግሃል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ለሥራቸው መልካም ውጤት ስለሚያገኙ፣ ከአንድ፣ ሁለት መሆን ይሻላል፣ አንዱ ቢወድቅ፣ ባልንጀራው ደገፍ ያነሣዋል»* መክ. 4+9-10::

ግልጥ ልሁን፤ ከማያቋርጥ መጥፎ ልማድ ማለት ከሱስና ፈተና ጋር በምታደርገው ውጊያ በመሸነፍ ላይ ከሆንክና፣ መልካም ነገር የማድረግ ፍላጎትህ አልሳካ እያለህ በተደጋጋሚ ውድቀትና የበደለኛ ነት ስሜት ውስጥ ገብተህ ከሆነ፣ በራስህ ጥረት ከችግሩ ለመላቀቅ አትችልም:: የሰዎች እርዳታ ያስፈልግሃል:: አንዳንድ ፈተናዎችን ልታሸንፋቸው የምትችለው፣ በሚጸልይልህ፣ በሚያበረታታህና በሚከታተልህ ጓደኛ እርዳታ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ለእድገትህና ለነፃነትህ ያለው ዕቅድ፣ ሌሎች ክርስቲያኖችንም ይጨምራል:: እውነተኛና ታማኝ ጓደኛነት፣ አልበገር ካሉ ኃጢአቶች ጋር ለብቻህ ለምታደርገው ትግል ማርከሻ ነው:: የምታመልጥበት ብቸኛ መንገድ ይህ ሆኑን እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ይገልጣል፡- *«ስለዚህ ኃጢያታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ጸልዩ»* ያዕ. 5+16::

ሀያ ሰባተኛ ቀን
ፈተናን ማሸነፍ

በተደጋጋሚ ከሚያሸንፍህ ፈተና ለመፈወስ በእርግጥ ትፈልጋለህ ? የእግ ዚአብሔር መፍትሔ ግልጥ ነው፤ በውስጥህ ልታፍነው አትሞክር፤ ተናዘ ዘው፣ አትሸሽገው፤ ግለጠው:: ስሜትህን መግለጡ የፈውስህ መጀመሪያ ይሆናል::

ጉዳትን መደበቅ ያባብሰዋል:: ችግሮች በጭለማ በመፈጠር እያደጉና፣ እየገዘፉ ይሄዳሉ:: ለእውነት ብርሃን ሲጋለጡ ግን ይኮማተራሉ:: ህመምህ የምስጢሮችህን ያህል ነው:: ስለዚህ ጭምብልህን አውልቅ፣ ፍፁም ነኝ የሚል ማስመሰልህን ተውና በነፃነት ተመላለስ::

እኔ በማመልክበት ቤተክርስቲያን የዚህን መርህ ጠንካራ ኃይል ተመልክተናል፡፡ የማገገም በዓል ብለን በጀመርነው በዚህ ኘሮግራም ዓማካይነት ሰዎች ተስፋ የለሽ ከሚመስሉ ሱሶች እና ተደጋጋሚ ፈተናዎች መዳፍ ነፃ ወጥተዋል፡፡ ፕሮግራሙ በተራራው ስብከት ላይ የተመሠረተና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሆኖ ስምንት ደረጃዎች ያሉት የማገገም ሂደት አለው፡፡ ሰዎችን በአነስተኛ ቡድኖች አዋቅሯል፡፡ ባለፉት አሥር ዓመታት፣ ቁጥራቸው ከ5000 የሚበልጥ ሰዎች ከልማዶች፣ ጉዳቶችና ሱሶች ነፃ ወጥተዋል፡፡ ዛሬ ኘሮግራሙ በሺህ በሚቆጠሩ አብያተክርስቲያን ውስጥ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ አንተም ይህን መርህ ቤተክርስቲያንህ ውስጥ እንድትጠቀምበት በከፍተኛ ሁኔታ አበረታታሃለሁ፡፡

> *እውነቱ፣ ልትገልጠው የማትችለው ነገር በሕይወትህ ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል ማለት ነው፡፡*

ሰይጣን፣ የኔ ኃጢአትና ፈተናዎች ከሌሎች የተለዩ ስለሆኑ፣ በምስጢር ልይዛቸው ይገባል ብለህ እንድታስብ ይፈልጋል፡፡ እውነቱ ግን ሁላችንም በአንድ ጀልባ የተሣፈርን መሆናችን ነው፡፡ ሁላችንም ከተመሳሳይ ፈተናዎች ጋር በመዋጋት ላይ ነን 1ቆሮ. 10+13፡፡ እና «*ሁላችንም ኃጢአት ሠርተናል*» ሮሜ 3+23፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አንተ የሚሰማህ ስሜት ተሰምቷቸዋል፤ አሁን የገጠመህ ዓይነት ትግልም ገጥሟቸዋል፡፡

ስህተታችንን እንድንደብቅ የሚያደርገን፣ ኩራት ነው፡፡ ሁሉን «በቁጥጥራችን ሥር» ያዋልን አድርገው ሰዎች እንዲያስቡ እንፈልጋለን፡፡ እውነቱ ግን፣ ልትገልጠው የማትችለው ነገር ምንም ይሁን ምን፣ በሕይወትህ ከቁጥጥርህ ውጭ የሆነ መሆኑ ነው፡፡ ይህም በገንዘብ ረገድ ያለብህ ችግር፣ በትዳር፣ በልጆች፣ በአስተሳሰቦች፣ ከተቃራኒ ፆታ ጋር ባለህ ግንኙነት፣ ድብቅ ልማዶችህና በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡ ችግሩን እራስህ የምትፈታው ቢሆን ኑሮ፣ እስካሁን ታደርገው ነበር፡፡ ግን አትችልም፡፡ ቁራጥነትና ግላዊ ውሳኔዎች በቂ አይደሉም፡፡

አንዳንድ ችግሮች ሥር የሰደዱ፣ ልማድ የሆኑ፣ ግዙፍ እና በራስህ ጥረት መፍትሔ ልታገኝላቸው የማይቻልህ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚያበረታታህ፣ የሚረዳህ፣ የሚጸልይልህ፣ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የሚወድህና በኃላፊነት የሚከታተልህ አንድ አነስተኛ ቡድን ወይም የቅርብ ጓደኛ ያስፈልግሃል፡፡ አንተም ለእነርሱ ተመሳሳዩን ልታደርግላቸው ትችላለህ፡፡

አንድ ሰው መጥቶ «ይህን እስከ ዛሬ ለማንም አልነገርኩም » በማለት

ምስጢሩን ሲገልጥልኝ ስለዚያ ሰው ደስ ይለኛል። ምክንያቱም እንዲህ የሚ ያደርጉ ሰዎች፣ ታላቅ እፎይታና ነፃነት መለማመድ እንደሚጀምሩ ስለማውቅ ነው። የታሠሩበት እግር ብረት ሊፈታና፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ለወደፊት ሕይ ወታቸው የተስፋ ጭላንጭል ሊመለከቱ ነው። እግዚአብሔር እንዳዘዘን፣ ያለብንን ችግር በክርስትና ሕይወቱ ለበሰለ ወዳጃችን ስንገልጥለት ሁል ጊዜ እንዲህ ይሆናል።

አንድ ብርቱ ጥያቄ ላቀርብልህ። በአንተ ዘንድ ያለ፣ ግን የሌለ ለማስመሰል የምትሞክረው ችግር ምንድነው? ስለምንድነው ልትገልጠው የምትፈራው? ችግሩን ብቻህን አትፈታውም። እርግጥ ነው ድካምን ለሌሎች ለመግለጥ ራስን ዝቅ ማድረግን ይጠይቃል። ራስን ዝቅ አለማድረግ ግን፣ ከችግርህ እንዳትላቀቅ ያደርግሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- « *እግዚአብሔር ትዕ ቢተኞችን ይቃወማል፣ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፤ ... ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ*» ያዕ. 4፥6-7።

**ዲያብሎስን ተቃወም**። እራሳችንን ዝቅ ካደረግንና ለእግዚአብሔር ከተገዛን በኋላ ዲያብሎስን እንድንቃወመው ተነግሮናል። የያዕቆብ 4፥7 ቀሪ ክፍል እንዲህ ይላል:- «*ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ፤ ከእናንተም ይሸሻል* »። የዲያብሎስን ጥቃት በዝምታ አንመለከትም፤ መዋጋት ይኖርብናል።

አዲስ ኪዳን፣ የክርስትና ሕይወት ከክፉ ኃይላት ጋር የሚደረግ መንፈሳዊ ውጊያ መሆኑን ለመግለጥ፣ ተዋጋ፣ ድል አድርግ፣ አሸንፍ፣ አስወግድ፣ በሚ ሉትና በመሳሰሉት የውጊያ ቃላት ይጠቀማል። ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ጠላት ግዛት ውስጥ ከሚሠሩ ወታደሮች ጋር ይነጻፀራሉ።

ዲያብሎስን ልንቃወመው የምንችለው እንዴት ነው? ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- «*የመዳንንም ራስ ቁር፣ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፣ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው*» ኤፌ. 6፥17። የመጀመሪያው እርምጃ የእግዚአብሔርን ማዳን መቀበል ነው። ለክርስቶስ እሺ ያልክ ካልሆንክ፣ ሰይጣንን እምቢ ልትለው አትችልም። ሰይጣንን መከላከያ ክርስቶስ ብቻ ነው። «በመዳን ራስ ቁር» ዓማካይነት አእምሯችን በእግዚአብሔር መከላከል ይደረግለታል። ይህን አትርሳ፤ አማኝ ከሆንክ፣ አንዳች ነገር እንድታደርግ ሰይጣን ሊያስገድድህ አይችልም። አሳብ ሊያቀርብልህ ብቻ ነው የሚችለው።

ሁለተኛ፣ ሰይጣንን ለመቃወሚያ የእግዚአብሔር ቃልን እንደመሣሪያ መጠቀም አለብህ። ኢየሱስ ምድረ በዳ ውስጥ በተፈተነ ጊዜ ይህን መንገድ ነው የተጠቀመበት። ሰይጣን ፈተና ባቀረበለት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ነው ክርስቶስ የተቃወመው። ያለውን ኃይል ለግላዊ ፍላጎቱ

ማርኪያነት እንዲጠቀምበት በተፈተነ ጊዜ፣ «አልራበኝም» አላለም:: በአእም ሮው ካለው የእግዚአብሔር ቃል ነው የጠቀሰው:: እኛም እንዲሁ ማድረግ ይኖርብናል:: እግዚአብሔር ቃል ውስጥ ኃይል ስላለ፣ ሰይጣን ይፈራዋል::

ምንጊዜም ከሰይጣን ጋር ክርክር ለመግጠም አትሞክር:: በሺህ ዓመታት የሚቆጠር ልምድ ስላለው በክርክር ከአንተ ይሻላል:: በጥሩ አመክንዮአዊ የአ ሳብ አቀራረብ ወይም በራስህ አስተሳሰብ ሰይጣንን ልትረታው አትችልም:: ነገር ግን በሚያርበደብደውና እውነት በሆነው የእግዚአብሔር ቃል ተጠቀም:: ለዚህ ነው ጥቅሶችን በቃል ማስታወሱ ፈተናን ለማሸነፊያ ፍፁም አስፈላጊ የሚሆነው:: በተፈተንክ ጊዜ ሁሉ በፍጥነት ትጠቀምበታለህ:: በኢየሱስ እን ደነበረው ለመታወስ ዝግጁ የሆነ የቃሉ እውነት ልብህ ውስጥ ተከማችቷል::

> *ምን ጊዜም ከሰይጣን ጋር ክርክር ለመግጠም አትሞክር :: በሺህ ዓመታት የሚቆጠር ልምድ ስላለው፣ በክርክር ከአንተ ይሻላል::*

በቃልህ ያጠናኸው ምንም የመጽ ሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከሌለህ፣ ጠመንጃህ ውስጥ ምንም ጥይት የለም! በቀሪው ሕይወትህ በሳምንት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንድታጠና አበረታታ ሃለሁ:: ይህን ብታደርግ ምን ያህል ብርቱ እንደምትሆን ገምት::

ደካማነትህን ተገንዘብ:: ትዕቢተኛና ትምክህተኞች እንዳንሆን እግዚአብሔር ያስጠነቅቀናል! እንዲህ ያለው ሁኔታ ወደ ጥፋት የሚወስድ ዝግጅት ነው:: ኤርምያስ እንዲህ ብሏል:- «*የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነው፤ ፈውስም የለውም*» ኤር. 17÷9:: የዚህ ትርጉሙ፣ እራሳችንን የማሞኘት ጥሩ ችሎታ አለን ማለት ነው:: አመቺ ሁኔታዎች ከተ ፈጠሩልን፣ ሁላችንም የትኛውንም ዓይነት ኃጢአት ለመሥራት እንችላለን:: ፈተና አይበግረንም በማለት መከላከያ መሣሪያችንን በፍጹም መጣል አይኖ ርብንም::

ፈታኝ ወደሆኑ ሥፍራዎች በግዴለሽነት አትሂድ፣ ሽሻቸው፣ ምሳሌ 14÷16:: ፈተና ውስጥ ገብቶ ለመውጣት ከሚደረግ ጥረት፣ አስቀድሞ መራቁ የሚቀል መሆኑን አስታውስ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ*» 1ቆሮ. 10÷12::

## ሀያ ሰባተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** ምን ጊዜም የማምለጫ መንገድ አለ።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** «*በሰዎች ሁሉ ላይ ከደርሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል* »

1ቆር. 10+13።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** አልላቀቅህ ያለኝን ፈተና ለማሸነፍ እንድችል መንፈሳዊ አጋሬ ሆኖ በጸሎት እንዲረዳኝ ማንን ልጠይቅ?

28

# ጊዜ ይወስዳል

*ሁሉም ነገር ጊዜ አለው፤ ከሰማይ በታች ለሚከናወነው ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው።*

መክ. 3፥1

*በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው፣ እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ።*

ፊልጵ. 1፥6

ወደ መብሰል (ዕድገት) የሚያደርስ አቋራጭ መንገድ የለም።

ሙሉ ሰው ወደመሆን ለማደግ ዓመታት ይወስድብናል። ፍሬ አድጎ ለመጎምራት አንድ ሙሉ ወቅት ይወስድበታል። የመንፈስ ፍሬም እንዲሁ ነው። ክርስቶስን የመምሰል ባህርይን በጥድፊያ ለማግኘት አይቻልም። መንፈሳዊ ዕድገት፣ እንደ አካላዊ ዕድገት ጊዜ ይወስዳል።

ፍሬ ቶሎ እንዲጎመራ ልታደርገው በምትሞክርበት ጊዜ ጣዕሙን ያጣል። አሜሪካን ውስጥ ቲማቲም ወደ መሸጫው ስፍራ በሚጓጓዝበት ጊዜ እንዳይ ፈርጥ ሲባል በጥሬው ነው የሚለቀመው። ከዚያም አረንጓዴ የነበረው ፍሬ ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት ወዲያውኑ የሚያቀላው ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ($CO_2$) የተባለ ጋዝ ይረጭበታል። በዚህ ሁኔታ የቀላው ቲማቲም ለምግ ብነት ዘግጁ ነው። ነገር ግን እግንዱ ላይ በቀስታ እንዲበስል የተደረገን ቲማቲም ያህል ጣዕም የለውም።

***በምን ያህል ፍጥነት*** እናድጋለን እያልን እኛ ስንጨነቅ፣ እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ግን ***ምን ያህል ብርቱ*** ሆነን ማደጋችን ነው። እግዚአብሔር ሕይወታችንን የሚመለከተው፣ ***ከዘላለም*** እና ***ለዘላለም*** ከሆነ ዓላማው አንፃር ስለሆነ፣ በፍጹም አይጣደፍም።

ላን አደምስ የተባለ ሰው፣ መንፈሳዊ ዕድገትን፣ የተባበሩት አገሮች ጦር ደቡብ ፓስፊክ ውስጥ የሚገኙትን ትንንሽ ደሴቶች፣ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ነፃ ለማውጣት ከተጠቀሙበት እስትራቴጂ ጋር አመሳስሎ ታል፡፡ ወታደሮቹ በመጀመሪያ ባሕር ውስጥ ካሉት መርከቦቻቸው ወደ ጠላት ይዞታ መድፍ በመተኮስ አንደኛይቱ ደሴት ላይ ያለውን የጠላት ኃይል «ያዳክሙታል»፡፡ ቀጥሎ አነስተኛ አባላት ያሉት የመርከበኛ ሠራዊት ደሴቲቱን ይወርር እና «መግቢያው» ላይ አነስተኛ በታ ይቆጣጠራል፡፡ ከዚህ በኋላ፣ ሠራዊቱ የደሴቲቱን ቀሪ ክፍል ነፃ የማውጣቱን ረጅም ሂደት፣ አንድ በአንድ ይጀምራል፡፡ በመጨረሻም ደሴቲቱ በሙሉ በሠራዊቱ ቁጥጥር ሥር ትሆናለች፤ ይህ የሚሆነው ግን ዋጋ ካስከፈሉ ጦርነቶች በኋላ ነው፡፡

*በምን ያህል ፍጥነት እናድጋለን እያልን እና ስንጨነቅ፣ እግዚአ ብሔርን የሚያሳስበው ግን የቱን ያህል ብርቱ ሆነን ማደጋችን ነው፡፡*

አደምስ ከሠራዊቱ ታሪክ ይህን ተመሳሳይነት አውጥቷል፡፡ ክርስቶስ በዳግም ልደታችን ወቅት ሕይወታችንን ከመቆጣጠሩ በፊት፣ አንዳንድ ጊዜ፣ የማንወጣቸው ችግሮች እንዲደርሱብን በመፍቀድ እኛን «ማዳከም» ይኖርበት ይሆናል፡፡ አንዳንዶች ክርስቶስ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ በራቸውን ሲያንኳኳ ይከፍቱለታል፣ ብዙዎቻችን ግን ለመክፈት እምቢተኞችና ተከላካዮች ነን፡፡ በእምነት ከመለወጣችን በፊት ባለው ልምምዳችን ኢየሱስ፡- *«እነሆ በደጅ ቆሜ በምብ እጥባለሁ»* የሚለን ነው የሚመስለን፡፡

አንተነትህን ለክርስቶስ እንደከፈትክለት እግዚአብሔር ወዲያውኑ የሕይወትህን «መግቢያ» ሥፍራ ይይዘዋል፡፡ ሕይወትህን *በሙሉ* ለእርሱ አስረክቤአለሁ ብለህ ታስብ ይሆናል፡፡ እውነቱ ግን አንተ እንኳን የማታውቀው ብዙ የሕይወትህ ክፍል ያለ መሆኑ ነው፡፡ የምታውቀውን ያህል ብቻ ነው በወቅቱ ለእግዚአብሔር ለመስጠት የምትችለው፡፡ ይህ ምንም አይደለም፡፡ ክርስቶስ የሕይወትህን መግቢያ በር አንዴ ከያዘ፣ ሙሉ ሕይወትህ የራሱ እስኪሆን ድረስ፣ የበለጠ ክልል የመያዝ ዘመቻውን ይጀምራል፡፡ ትግልና ጦርነቶች ቢኖሩም፣ ውጤቱ በፍጹም የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡ እግዚአብሔርም እንዲህ በማለት ተስፋ ሰጥቶናል፡- *«በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ»* ፊልጵ. 1፥6፡፡

ደቀ መዝሙርነት ክርስቶስን የመምሰል ሂደት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ፡- *«ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጽምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው»* ኤፌ. 4፥13፡፡ የመጨረሻ መድረሻህ ክርስቶስን መምሰል


ሲሆን፣ ጉዞህም እስከ ሕይወትህ ፍፃሜ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ይህ ጉዞ፣ *እምነትን* (በአምልኮ) ፣ *አካልነትን* (በህብረት)፣ እና *መሆንን* (በደቀ መዝሙርነት)፣ የሚያካትት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ እግዚአብሔር እርሱን በመምሰሉ ሂደት በየዕለቱ በትንሹ እየጨመርክ እንድታ ድግ ይፈልጋል፡- «*የፈጠረውን መልክ እንዲመስል፣ በእውቀት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል*» ቆላ. 3+10፡፡

ዛሬ አእምሯችን ፍጥነት በሚሹ ጉዳዮች ተሞልቷል፡፡ እግዚአብሔር የሚፈ ልገው፣ ከፍጥነት ይልቅ ብርታትና ፅናትን ሲሆን፣ እኛ የምንፈልገው ደግሞ፣ ቅፅበታዊ ጥገና፣ አቋራጭ መንገድ፣ ፈጣን መፍትሄ ነው፡፡ ስብከት፣ ሴሚናር ወይም ችግሮቻችንንና ፈተናዎችን በቅጽበት የሚያስወግድልንን፣ እንዲሁም በማደግ ላይ ካሉ ችግሮቻችን ሁሉ ወዲያውኑ የሚያላቅቀንን አንዳች ልምምድ እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን፣ የቱንም ያህል ብርቱና ስሜትን የሚነካ ቢሆን፣ እውነተኛ ዕድገት በፍፁም የነጠላ ልምምድ ውጤት አይሆንም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*የእርሱን መልክ እንደንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለ ወጣለን*» 2ቆሮ. 3+18፡፡

## ለምንድነው ረጅም ጊዜ የሚወስደው?

ምንም እንኳን እግዚአብሔር በቅጽበት ሊለውጠን የሚችል ቢሆን፣ በቀስታ ሊያሳድገን መርጧል፡፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በሚያሳድግበት ጊዜ ጥንቁቅ ነበር፡፡ እግዚአብሔር፣ እስራኤላውያን ከጠላቶቻቸው ብዛት የተነሣ እንዳ ይደነግጡ የተስፋይቱን ምድር «*ጥቂት በጥቂት*»፣ እንዲወርሱ እንዳደረገ ሁሉ፣ ዘዳግም 7+22፣ በእኛም ሕይወት እየጨመሩ በሚሄዱ ደረጃዎች መሥራትን ነው የሚመርጠው፡፡



ለምንድነው ለውጥና ዕድገት በጣም ረጅም ጊዜ የሚወ ስዱት? ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡

*ፈጣን ተማሪዎች አይደለንም*፡፡ ብዙ ጊዜ አንድን ነገር በትክክል ለመጨበጥ፣ አርባ ወይም አምሳ ጊዜ መማር ይኖርብናል፡፡ ችግሮች ይደጋገማሉ፣ እኛ ደግሞ «ሁለተኛ አላደርገውም! በዚህ ትምህርት አግኝቼበታለሁ» እንላለን፡፡ እግዚአብሔር ግን በፍጹም አዋቂ ነው፡፡ የሚሰጠንን ትምህርት በፍጥነት የምንዘነጋና፣ ቶሎ ወደ አሮጌው አኗኗራችን የምንመለስ መሆናችንን የእስራ ኤል ታሪክ ያረጋግጥልናል፡፡ ተደጋጋሚ ትምህርት ያስፈልገናል፡፡

ከአእምሯችን ልናስወጣቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ብዙ ሰዎች፣ ለዓመታት እውስጣቸው ያደገን፣ ወይም ከሌላ ሰው ጋር ያለባቸውን ችግር

ይዘው አንድ አማካሪ ዘንድ ይሄዱና፦ «ለችግሬ መፍትሔ እንድትሰጠኝ ፈልጋለሁ፤ ያለኝ ጊዜ አንድ ሰዓት ብቻ ነው» ይላሉ:: ረጅም ዕድሜ ያለውና ሥር የሰደደ ችግራቸው ቶሎ መፍትሔ እንዲያገኝ በገርነት ይጠብቃሉ:: ብዙዎቹ ችግሮቻችን እና መጥፎ ልማዶቻችን በአንድ ቀን ያደጉ ስላልሆኑ፣ ቶሎ ይወገዳሉ ብሎ መጠበቅ ከእውነታ መራቅ ነው:: የብዙ ዓመታት ጉዳትን በቅጽበት የሚፈውስ መድኃኒት፣ ጸሎት ወይም መርህ የለም:: የማስወገድና የመተካትን ከባድ ሥራ ይጠይቃል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይጠራዋል፦

«*አሮጌውን ሰው ማስወገድ*» እና «*አዲሱን መልበስ*» ሮሜ 13፥12፤

ኤፌ. 4፥22-25፤ ቆላ. 3፥7-10፣14:: ዳግም በተወለድክ ጊዜ አዲስ ፍጥረት መሆንን ብታገኝም፣ መወገድና መተካት የሚገባቸው አሮጌ ልማዶች፣ አኗኗርና ልምምዶች አሁንም አብረውህ አሉ::

**ስለ እኛ ያለውን ነባራዊ እውነት በትህትና ለመቀበል እንፈራለን::** እውነት በቅድሚያ ቢያሳዝነንም፣ በፍጻሜው ግን ነፃ የሚያወጣን መሆኑን ቀደም ብዬ ጠቁሜአለሁ:: የባሕርይ ጉድለታችንን በታማኝነት ብንቀበል ምን ይገጥመን ይሆን? የሚለው ፍርሃት ክህደት ወህኒ ውስጥ ያኖረናል:: እግዚአብሔር በበደላችን፣ በውድቀታችን እና በድካማችን ላይ የእውነቱን ብርሃን እንዲያበራባቸው ስንፈቅድለት ብቻ ነው ድካሞቻችንን ማስወገድ የምንጀምረው:: ለዚህ ነው ትሁት እና ለመማር የተዘጋጀ ልብ ከሌለህ ለማደግ የማትችለው::

> *ያለ ለውጥ ዕድገት የለም፤ ፍርሃት ወይም ማጣት የሌለበት ለውጥ የለም፤ ያለ ስቃይም መሸነፍ የለም::*

**ዕድገት ብዙ ጊዜ የሚያምና የሚያስፈራ ነው::** ያለ ለውጥ ዕድገት የለም፤ ፍርሃት፣ ማጣት፣ ሕመም (መጐዳት)፣ የሌለበት ለውጥም የለም:: ማንኛውም ለውጥ፣ አንድ ነገር ማጣትን ስለሚያስከትል፣ አዲሱን ለመለማመድ፣ አሮጌ አኗኗርህን መተው አለብህ:: ምንም እንኳን አሮጌዎቹ አኗኗሮቻችን የማይጠቅሙን ቢሆኑ፣ ቢያንስ እንደ አሮጌ ጫማ የሚመቹና የተለመዱ ስለሆኑ እነሱን ማጣቱ ያስፈራናል::

ሰዎች ብዙ ጊዜ ማንነታቸውን በጉድለታቸው ዙሪያ ይገነባሉ:: «የእኔ ባሕርይ ... ነው» እና «በቃ እኔ ባሕርዬ እንዲህ ነው» ይላሉ:: ስውር ሀሊናችን ውስጥ ያለው ስጋት፣ ልምዴን፣ መጎዳቴን፣ ወይም የሚወራልኝን ነገር ከተውኩ ምን ዓይነት ሰው እሆናለሁ? የሚል ነው:: ይህን የመሰለው ፍርሃት ዕድገትህን አዝጋሚ ያደርገዋል::

ልማዶች ለማደግ ጊዜ ይወስዳሉ:: ባህርይህ የልማዶችህ ድምር ውጤት መሆኑን አስታውስ:: ደግነትን *የማድረግ ልማድ* ከሌለህ፣ ደግ ነኝ ለማለት አትችልም:: ደግነትን የምታሳየው ደግ ልሁን ብለህ ሳታስብ ነው:: እውነተኛነት የሁል ጊዜ *ልማድህ* ካልሆነ፣ ቅን ነኝ ብለህ ለመናገር አትችልም:: *ለብዙኛው* ጊዜ ለሚስቱ ታማኝ የሆነ ባል፣ በፍጹም ታማኝ አይደለም! ልማዶችህ ባህርይህን ይገልጣሉ::

የክርስቶስን የሚመስሉ ባህርያትን ማዳበሪያ የሆነ አንድ መንገድ ብቻ አለ! ባህርያቱን *ተለማመዳቸው፣* ያ ደግሞ ጊዜ ይወስዳል! *ልማዶች በቅጽበት* አይመጡም:: ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጢሞቴዎስን ይመክረዋል:- «*ሰው ሁሉ ማደግህን ያይ ዘንድ በእነዚህ ነገሮች ላይ ትትጉ*» 1ጢሞ. 4+15::

*ሀያ ስምንተኛ ቀን*

**ጊዜ ይወስዳል**

አንድን ነገር ደጋግመህ ከተለማመድከው፣ በሚገባ ታውቀዋለህ:: መደጋገም የባህርይና የሞያ እናት ናት:: እንዲህ ያሉት የባህርይ ማዳበሪያ ልማዶች ብዙ ጊዜ፣ «*መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓቶች*» ተብለው ይጠራሉ:: እነዚህን የሚያስተምሩህ ብዙ ጥሩ ጥሩ መጻሕፍት አሉ::

## አትቸኩል

በመንፈሳዊ ሕይወት በምታድግበት ጊዜ፣ በሂደቱ ከእግዚአብሔር ጋር የምትተባበርባቸው ብዙ ሁኔታዎች አሉ::

እግዚአብሔር በሕይወትህ በመሥራት ላይ መሆኑ በማይሰማህ ጊዜ እንኳን በሥራ ላይ መሆኑን እመን:: መንፈሳዊ እድገት አንዳንድ ጊዜ አሠልቺና በአንድ ጊዜ አንድ ትንሽ እርምጃ የምትራመድበት ሥራ ይሆናል:: ቀስ በቀስ የሚመጣ መሻሻልን ጠብቅ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው፣ ከሰማይ በታች ለሚከናወነው ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው*» መክብብ 3+1:: መንፈሳዊ ሕይወትህ ውስጥም ወቅቶች አሉ:: አንዳንድ ጊዜ አጭርና ኃይለኛ ፍጥነት ያለው ዕድገት (የፀደይ ወራት)፣ ቀጥሎ ደግሞ ሥር የመስደድና የፈተና ወቅት (መከርና ክረምት)፣ ይኖሩሃል::

በተዓምር እንዲወገዱልህ የምትፈልጋቸው ችግሮች፣ ልማዶች እና ጉዳቶችስ? ለተዓምር መጸለዩ ጥሩ ነው፣ የጸሎትህ መልስ በዝግታ ለውጥ ዓማካይነት የሚመጣ ከሆነ ግን ቅር እንዳትሰኝ:: ሳያቋርጥ ዝግ ብሎ የሚፈስ የወንዝ ውሃ፣ በጊዜ ብዛት ቋጥኝ ይፈነቅላል፣ ግዙፉን ዓለትም ወደ ጠጠርነት ይለውጠዋል:: ትንሽ ችግኝ በጊዜ እርዝመት ግዙፍ ዛፍ ሊሆን

ይችላል።

በየጊዜው የምትቀስማቸውን ትምህርቶች የምትጽፍበት ማስታወሻ ደብተር አዘጋጅ። ይህ የምታከናውናቸው ነገሮች ማስታወሻ ሳይሆን፣ የምትቀስማቸውን ትምህርቶች የምትመዘግብበት ነው። እግዚአብሔር ስለ ራሱ፣ ስለ አንተ፣ ስለ ሕይወትህ፣ ስለ ግንኙነት፣ እና ስለ ማንኛውም ነገር ካስተማረህ ያገኘሃቸውን ግንዛቤዎችና የሕይወት ትምህርቶች መዝግባቸው። ሌላ ጊዜ እንብበህ ለማስታወስ፣ እንዲሁም ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ትችል ዘንድ መዝግባቸው፤ መዝ. 102፥18፤ 2ጢሞ. 3፥14። አንድን ትምህርት ደጋግመን የምንማርበት ምክንያት፣ ስለምንረሳ ነው። የጻፍካቸውን የመንፈሳዊ ጉዞ ማስታወሻዎች ዘወትር መከለሱ ከማያስፈልግ ስቃይና የልብ ስብራት ይጠብቅሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «*ስለዚህ ከሰማነው ነገር ስተን እንዳ ንወድቅ፣ ለሰማነው ነገር አብዝተን ልንጠነቀቅ ይገባናል* » ዕብ. 2፥1።

ከእግዚአብሔርም ሆነ ከራስህ ጋር ትዕግሥት ይኑርህ። በሕይወት ተስፋ ከሚያስቆርጡ ነገሮች አንዱ፣ የእግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ ከእኛው ጋር ብዙ የማይመሳሰል መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ዝግ ባለበት ጊዜ እኛ እንፈጥናለን። በሕይወት ያለህ ዕድገት አዝጋሚ በመምሰሉ ተስፋ መቁረጥ ይሰማህ ይሆናል። ያን ጊዜ እግዚአብሔር በፍፁም የማይጣደፍ፣ ነገር ግን፣ በጊዜው የሚደርስ መሆኑን አስታውስ። በዘላለም ውስጥ ላለህ ሥራ ሊያዘጋጅህ፣ ሕይወትህን በሙሉ ይጠቀምበታል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሰዎችን፣ በተለይም የመሪዎችን ባህርይ ለማዳበር በረጅም ሂደቶች የሚጠቀም መሆኑን በሚያስረዱ ምሳሌዎች የተሞላ ነው። ሙሴን ለማዘጋጀት፣ የምድረ በዳውን አርባ ዓመት ጨምሮ ሰማኒያ ዓመት ቆይቷል። ሙሴ «ጊዜው አልደረሰም? » እያለና እየጠየቀ ለ14,600 ቀን ጠብቋል። እግዚአብሔር ግን «ገና ነው» ይለው ነበር።

*እግዚአብሔር አይጣደፍም፤*
*ግን በጊዜው ይደርሳል።*

ተወዳጅ የሆኑ መጻሕፍት በአርዕስቶቻቸው የሚገልጡትን የመሰለና *ወደ ዕድገት የሚያደርስ ቀላል ጉዞ* ወይም *ቅጽበታዊ የቅድስና ምስጢር* የለም።

እግዚአብሔር እንጉዳይ ሲፈጥር በአንድ ሌሊት፣ ግዙፍ ግንድ ሲሠራ ግን በመቶ ዓመት፣ ያደርገዋል። ታላላቅ ሰዎች በትግል፣ በማዕበልና በመከራ ውስጥ ያድጋሉ። ሂደቱን በትእግሥት ተጠባበቅ። ያዕቆብ እንዲህ በማለት ይመክረናል፦ «*ምንም የማይጎድላችሁ ፍጹማንና ምሉዓን እንድትሆኑ ትዕግሥት*

*ሥራውን ይፈጽም»* ያዕ. 1+4::

ተስፋ አትቁረጥ:: እንባቆም፣ እግዚአብሔር ቶሎ አንድ ነገር ያላደረገ መስሎት ባዘነ ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንዲህ አለው:- *«ራእዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና፤ ስለመጨረሻውም ይናገራል፤ እርሱም አይዋሽም፣ የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤ በእርግጥ ይመጣል፣ ከቶም አይዘገይም»* ዕንባ. 2+3:: መዘግየት በእግዚ አብሔር ዘንድ ቃሉን መሻር አይደለም::

የቀረህን ብቻ ሳይሆን፣ እዚህ ለመድረስ የተጓዝከውን እርቀትም አስታውስ:: ለመገኘት እምትፈልግበት፣ ወይም እነበርህበት ሥፍራ አይደለህም:: ከዓመ ታት በፊት ሰዎች PBPGINFWMY የሚል ተወዳጅ መልእክት በምህፃረ ቃል የተጻፈበት አዝራር ያለው ልብስ ይለብሱ ነበር:: ሙሉ መልእክቱ ወደ አማርኛ ሲመለስ እንዲህ ይነበባል:- *«እባክህን ታገሥ፤ እግዚአብሔር በኔ የጀመረውን ገና አልጨረሰም »*:: እግዚአብሔር በአንተም የጀመረውን አልጨረሰምና ወደ ፊት መጓዝህን ግፋበት:: ቀንድ አውጣ እንኳን ያለ መታከት ተጉዞ ኖኅ መርከብ ዘንድ ደርሷል!

*ሀያ ስምንተኛ ቀን*

ስለዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ወደ መብሰል (ዕድገት) የሚያደርስ አቋራጭ መንገድ የለም::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመ ረው፣ እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ»* ፊልጵ. 1+6::

**ልብ ልለው የማገባ ጥያቄ:-** በየትኛው የመንፈሳዊ ዕድገት አቅጣጫ ነው ይበልጥ ታጋሽና ትጉህ መሆን የሚኖርብኝ?

29

# የተሰጠህን ሥራ መቀበል

*እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።*

*ኤፌ. 2÷10*

*የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርኩህ።*

*ዮሐ. 17+4*

በምድር ላይ የተፈጠርከው የድርሻህን ልታበረክት ነው።

በምድር ሀብት ልትጠቀም ማለትም ልትበላ፣ ልትጠጣና እንዲያው ቦታ ልትይዝ ብቻ አልተፈጠርክም። እግዚአብሔር የቀረጸህ በሕይወትህ አማካይነት ለውጥ የምታመጣ አድርጎ ነው። ምንም እንኳን ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው ብዙ መጻሕፍት ከሕይወት ምርጥ የሆነውን ነገር «ለማግኘት» የሚቻልበትን ምክር ቢለግሱ፣ እግዚአብሔር ግን የሠራህ ለዚህ አይደለም። የተፈጠርከው በምድር ባለው ሕይወት ላይ *ልትጨምር* እንጂ ልትወስድ ብቻ አይደለም። ይህ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለው አራተኛ ዓላማ ሲሆን፣ «አገልግሎት» ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝሮቹን ይሰጠናል።

**የተፈጠርከው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው።** መጽሐፍ ቅዱስ፡- *"እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ እየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።"* ኤፌ 2÷10 ይላል ። እነዚህ "መልካም ሥራዎች" አገልግሎቶችህ ናቸው። በማንኛውም መልኩ ሌሎችን ባገለገልክ ቁጥር፣ በእርግጥም እግዚአብሔርን በማገለገልና ቆላ. 3+23-24፣ ከዓላማዎችህ አንዱን በመፈጸም ላይ ነህ። እግዚአብሔር አንተን እንዴት ለዚህ ዓላማ *እንዳበጀህ* በሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ትመለከታለህ። እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው ለአንተም እውነት ነው፡- *"በማህፀን ሳልሠራህ አውቅሁህ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ።"* ኤር.1+5። በዚህች ምድር ላይ የተፈጠርከው፣ ልዩ ለሆነ

ሥራ ነው::

ድነት የተሰጠህ እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *"እኛ ስላደረግነው ስንዳች ነገር ሳይሆን፣ ከዕቅዱና ከጸጋው የተነሣ ያዳነን፣ ወደ ቅዱስ ሕይወትም የጠራን እርሱ ነው::"* ጢሞ. 1+9:: እግዚአብሔር ያዳነህ «ቅዱስ ሥራውን» ለማከናወን እንድትችል ነው:: የዳንከው በማገልገልህ ሳይሆን፣ እንድታገለግል ነው:: በእግዚአብሔር መንግሥት፣ ቦታ፣ ዓላማ፣ ሚናና የምትፈጽመው ተግባር አለህ:: ይህ ለሕይወትህ ታላቅ ጠቀሜታና ዋጋ ያጐናጽፈዋል::

ላንተ ድነት ኢየሱስ የገዛ ሕይወቱን ከፍሏል:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *"በዋጋ ተገዝታችኋልና ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ"* 1ቆሮ. 6+20 በማለት ያሳስበናል:: እግዚአብሔርን የምናገለግለው፣ ከጥፋተኝነት ስሜት፣ ከፍርሃት ወይም ከግዴታ ሳይሆን፣ ከደስታና ስላደረገልን ነገር ከልብ ከመነጨ ምስጋና የተነሣ ነው:: ለእግዚአብሔር የነፍሳችን ባለ ዕዳዎች ነን:: በእርሱ የማዳን ሥራ ያለፈ ኃጢአታችን ይቅር ተብሎልናል፤ የአሁን ሕይወታችን ትርጉም ያለው ሆኗል፤ ለመጪው ዘመናችን ደግሞ ዋስትና አግኝተናል:: ጳውሎስ እነዚህን ሁሉ አስደናቂ ጥቅሞች አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:- *"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ::"* ሮሜ 12+1::

**ህያ ዘጠነኛ ቀን የተሰጠህን ሥራ መቀበል**

ሐዋርያው ዮሐንስ ለሌሎች የምናደርገው የፍቅር አገልግሎት በእውነት መዳናችንን ያሳያል በማለት ሲያስተምር:- *"ወንድሞቻችንን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ በሞት ይኖራል"* ዮሐ. 3+14 ብሏል:: ለሌሎች ፍቅር ከሌለኝ፣ እነሱን ለማገልገል ምንም ፍላጐቱ ከሌለኝና ለራሴ ብቻ የማስብ ከሆንሁ፣ በርግጥ ክርስቶስ በሕይወቴ አለ ወይ? ብዬ መጠየቅ ይኖርብኛል:: ድነት ያገኘ ልብ ለማገልገል ይፈልጋል::

እግዚአብሔርን ስለማገልገል ብዙ ሰዎች በትክክል የማይረዱት ቃል «*አገልጋይ*» የሚለው ነው:: ብዙዎች «አገልጋይ» የሚለውን ቃል ሲሰሙ፣ ፈጥነው የሚያስቡት ስለ መጋቢዎች፣ ቄሶች እና የሙሉ ጊዜ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ነው:: እግዚአብሔር ግን የእርሱ ቤተሰብ የሆነ ሰው ሁሉ አገልጋይ መሆኑን ነው የሚናገረው:: ስለዚህ ክርስቲያን ከሆንክ፣ አገልጋይ ነህ፤ ስታገለግል ደግሞ አገልግሎትህን ፈጸምክ ማለት ነው::

ሀመምተኛይቱ የጴጥሮስ አማት ኢየሱስ በፈወሳት ጊዜ፣ በተሰጣት አዲስ ጤንነት በመጠቀም፡ *"ተነስታም አገለገለቻቸው"* ማቴ. 8+15:: ይህን ነው ማድረግ ያለብን:: የተፈወስነው ሌሎችን ለመርዳት፣ የተባረክነውም በረከት ለመሆን ነው:: የዳንነው ልናገለግል እንጂ፣ ዝም ብለን በመቀመጥ መን ግሥተ ሰማያትን ልንጠባበቅ አይ ደለም::

*ለሌሎች ፍቅር ከሌለኝ፣ እነርሱን ለማገልገል ፍላጐቱ ከሌለኝና ስለራሴ ብቻ የማስብ ከሆንኩ፣ በእርግጥ ክርስቶስ በሕይወቴ አለወይ? ብዬ መጠየቅ ይኖርብኛል::*

ጸጋውን በተቀበልንበት ቅጽበት እግዚአብሔር ለምን ወዲያውኑ መንግሥተ ሰማያት አይወስደንም በማለት ጠይቀህ ታውቃለህ? በዚህ በረከሰ ዓለም ውስጥ ስለምን ተወን? የተወንማ ዓላማዎቹን እንድንፈጽም ነው:: አንዴ ከዳንህ በኋላ እግዚአብሔር ለራሱ ዓላማ ሊጠቀምብህ ይፈልጋል:: በቤቱ ውስጥ *አገልግሎት*፣ በዓለም ደግሞ *ተልዕኮ ለአንተ* አለው::

የተጠራኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው:: በክርስትና ሕይወት በማ ደግ ላይ እያለህ፣ በእግዚአብሔር «የተጠሩ» ሰዎች ሚሲዮናውያን፣ መጋቢ ዎች፣ ደናግሎችና «የሙሉ ጊዜ» የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው ብለህ አስበህ ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን ለአገልግሎት፣ የተጠራ መሆኑን ይነግረናል:: ኤፌ. 4+14 ፤ ሮሜ 1+6-7:: ለድነት መጠራ ትህ፣ ለአገልግሎት መጠራትህንም ያካትታል:: ሁለቱም አንድ ናቸው:: የምት ሠራው ምንም ሆነ ምን፣ የተጠራኸው *ለሙሉ ጊዜ* የክርስትና አገልግሎት ነው:: "የማያገለግል ክርስቲያን" የሚለው አባባል እርስ በእርሱ ይቃረናል::

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *"እኛ ስላደረግነው አንዳች ነገር ሳይሆን፣ ከዕ ቅዱና ከጸጋው የተነሣ ያዳነን ወደ ቅዱስ ሕይወትም የጠራን እርሱ ነው:: ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን"* 2ጢሞ. 1+9:: ሐዋርያው ጴጥሮስም:- *"እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአ ብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ::"* 1ጴጥ. 2÷9 በማለት ያክልበታል:: እግዚአ ብሔር በሰጠህ ችሎታ ሌሎችን በረዳህበት ቁጥር ጥሪህን በመፈጸም ላይ ነህ::

መጽሐፍ ቅዱስ:- *"... ይህም ከሙታን ለተነሣው ለእርሱ፣ ለሌላው ሆናችሁ ለእ ግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ ነው::"* ሮሜ 7÷4 ይላል:: እግዚአብሔርን ለማገል ገል ምን ያህል ጠቃሚ ሆነሃል? በቻይና ባሉ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያን፣ አዳዲስ ሰዎች ወደ ጌታ ሲመጡ፣ ሌሎቹ አማኞች:- "አሁን ኢየሱስ የሚመ

ለከትባቸው ጥንድ ዓይኖች፣ የሚያደጥምባቸው አዳዲስ ጆሮዎች፣ ሌሎችን የሚረዳባቸው አዳዲስ እጆች፣ እንዲሁም ሌሎችን የሚያፈቅርበት አዲስ ልብ አገኘ» በማለት ይቀበሏቸዋል፡፡

የአንድ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ አባል መሆን የሚኖርብህ ዋና ምክንያት፣ ሌሎች አማኞችን በሚገባ በማገልገል ጥሪህን እንድትፈጽም ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *"እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ብልቶች ናችሁ፡፡"* 1ቆሮ. 12+27፡፡ አገልግሎትህ በክርስቶስ አካል ውስጥ በእጅጉ ይፈለጋል፤ በመሆኑም በአቅራቢያህ ባለ ማንኛውም አጥቢያ ለማገልገል ጠይቅ፡፡ እያንዳንዳችን የምንጫወተው ሚና አለ፤ ሚናችን ደግሞ አስፈላጊ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ትንሽ የሚባል አገልግሎት የለም፤ ሁሉም ያስ ፈልጋል፡፡

እንደዚሁም ቤተክርስቲያን ውስጥ የማይጠቅም አገልግሎት የለም፡፡ አንዳን ዶቹ የሚታዩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከጀርባ የሚሠሩና የተደበቁ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ ቢሆኑም ሁሉም ዋጋ አላቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ታናሽ የሚመስሉ ወይም የተደበቁ አገልግሎቶች ታላቅ ለውጥ ያመጣሉ፡፡ ቤቴ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆነው መብራት በመመገቢያ ክፍል ያለውና ባለጌጡ ሳይሆን፣ ሌሊት በምነ ሳበት ጊዜ የእግር ጣቶቼን ከእንቅፋትና ከመቁሰል የምትጠብቅልኝ ትንሽ የሌ ሊት አምፑል ናት፡፡ በመጠንና በጠቃሚነት መካከል ምንም ዓይነት ቁርኝት የለም፡፡ ተግባራችንን ለመወጣት አንዳችን በሌላችን ላይ ስለምንደጋገፍ፣ እያን ዳንዱ አገልግሎት ይጠቅማል፡፡

ከአካልህ ብልቶች አንዱ ሥራውን ማከናወን ቢያቅተው፣ ምን ይፈጠራል?



ትታመማለህ፤ ሌሎች የአካል ክፍሎችህም ይሰቃያሉ፡፡ ጉበትህ ለብቻው ለመኖር ቢወስን ምን እንደሚፈጠር እስቲ አስብ፡፡ እናም ጉበት "እኔ ደክሞኛል! ከእንግዲህ ይህንን አካል ለማገልገል አልፈልግም! ለማረፍ እፈልጋለሁ፣ የሚጠቅመኝን ነገር መሥራት ይኖርብኛል! ሌሎች ደግሞ በተራቸው እኔን ተክተው ይሥሩ፡፡" ቢል ምን ይፈጠራል? አካልህ ይሞታል፡፡ ባሁኑ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ አብያተክርስ ቲያን የሚሞቱት፣ ለማገልገል በማይፈልጉ ክርስቲያኖች ምክንያት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እንደ ተመልካች ተቀምጠው እያዩ አካሉ ይሰቃያል፡፡

እግዚአብሔርን እንድታገለግል ታዝሃል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ ምሳሌውን እንዲከተሉ ቀጥሎ ያለውን በግልጥ ነግሯቸዋል፡- *"የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች በዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና"* ማቴ. 20+28፡፡ አገልግሎት፣ ለክርስቲያኖች ስንፈልግና አንዳንዴ

ትርፍ ጊዜ ሲኖረን በጊዜ ስሌዳችን ጣልቃ የምናስገባው ነገር አይደለም:: የክርስቲያን ሕይወት ዋና ነገር ነው:: ጌታ ኢየሱስ የመጣው "ለማገልገል" እና "ለመስጠት" ነው:: እነዚህ ሁለት የድርጊት ቃላት የአንተንም ምድራዊ ሕይወት ሊገልጡ ይገባል:: ማገልገልና መስጠት እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን አራተኛ ዓላማ ያጠቃልሉታል:: ማዘር ቴሬዛ፣ በአንድ ወቅት "ቅዱስ ኑሮ የእግዚአብሔርን ሥራ በፈገግታ በመሥራት ውስጥ ይገኛል::" በማለት ተናግረዋል::

በመንፈሳዊ ሕይወት መብሰል በራሱ የመጨረሻ ነገር አለመሆኑን ኢየሱስ አስተምሯል:: ብስለት ለአገልግሎት፣ የምናድገውም ለመስጠት ነው! በትምህርት ላይ ትምህርት እየጨመርን መቀጠሉ በቂ አይደለም:: በምናውቀው መሥራት፣ እናምንበታለን የምንለውን ደግሞ በተግባር ማዋል ይኖርብናል:: የተረዳነውን ነገር በተግባር አለማዋላችን ጭንቀትን ይፈጥራል:: አገልግሎት ያልታከለበት ትምህርት ወደ መንፈሳዊ ድርቀት ይመራል:: በገሊላ ባህር እና በሙት ባህር መካከል የነበረው ንጽጽር አሁንም እውነት ነው:: ገሊላ በሕይወት የተሞላ ባህር ነው:: ምክንያቱም ወደ ውስጡ ሌላ ውሃ ያስገባል፣ መልሶም ይሰጣል:: በተቃራኒው ፣ ሙት ባህር ውስጥ ምንም ዓይነት ሕይወት አይገኝም፣ ወደ ውጭ የሚያወጣው ነገርም የለም:: እንቅስቃሴ የሌለበት ባህር ነው::

> ***በመንፈሳዊ ሕይወትህ መብሰል በራሱ የመጨረሻ ነገር አይደለም፣ ብስለት ለአገልግሎት ነው::***

በአሁኑ ጊዜ ብዙ አማኞች የሚያስፈልጋቸው ነገር፣ ወደ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሄድ አይደለም:: ምክንያቱም በተግባር ላይ ከሚያውሏቸው በእጅጉ የሚበልጡ ነገሮች አውቀዋል:: የሚያስፈልጓቸው ነገሮች፣ መንፈሳዊ ጡንቻቸውን የሚያዳብሩባቸው ***የአገልግሎት*** ልምምዶች ናቸው::

አገልግሎት ከአዳማዊው ባህርያችን ጋር ይቃረናል:: አብዛኛውን ጊዜ ***ከማገልገል*** ይልቅ "***መገልገልን***" እንፈልጋለን:: እናም "ፍላጐቴን የሚያሟላልኝና የምባረክበትን ቤተ ክርስቲያን እፈልጋለሁ"ስንል እንጂ "የማገለግልበትን፣ ለበረከት የምሆንበትን ቤተክርስቲያን እና ቦታ እፈልጋለሁ" ስንል አንደመጥም:: ሌሎች እንዲያገለግሉን እንጠብቃለን እንጂ ተቃራኒውን አናስብም:: በክርስትና ሕይወት በበሰልን ጊዜ ግን የሕይወታችን ዋና ትኩረት ሌሎችን ወደማገልገል እየተቀየረ ሊመጣ ይገባል:: የበሰለ የክርስቶስ ተከታይ፣ "***ፍላጐቴን የሚያሟላ***ልኝ ማነው?" የሚለውን ጥያቄ ያቆማል:: በዚያ ፈንታ "የማንን ፍላጐቶች ላሟላ እችላለሁ?" እያለ መጠየቅ ይጀምራል:: አንተስ ይህን ትጠይቃለህን?

## ለዘላለም ሕይወት መዘጋጀት

የምድር ሕይወትህ ሲያበቃ፣ እግዚአብሔር ፊት ትቆምና በሕይወትህ ሌሎችን ምን ያህል በሚገባ እንዳገለገልክ ትመዘናለህ። መጽሐፍ ቅዱስ፡- *"ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን"* ሮሜ 14÷12 ይላል። ይህ ምን እንደሚያመለክት አስተውል። አንድ ቀን እግዚአብሔር ለራሳችን ያጠፋነውን ጉልበትና ጊዜ፣ ሌሎችን ለማገልገል ካጠፋነው ጋር ያወዳድረዋል። ራስ ወዳድነታችንን ለመሸፈን የምናቀርባቸው ምክንያቶች ሁሉ ዋጋ ቢስ ይሆናሉ።

"በጣም ሥራ ይበዛብኝ ነበር" ወይም " የራሴ እቅዶች ነበሩኝ" አሊያም "በሥራ ወይም በመዝናናት ተጠምጄ ነበር፤ ወይም ለጡረታ ዘመኔ በመዘጋጀት ላይ ነበርኩ" ለሚሉት ፋይዳ ቢስ ምክንያቶች ሁሉ እግዚአብሔር፣ "አዝናለሁ ይህ የማይሆን መልስ ነው። እኔ የፈጠርኳችሁ፣ ያዳንኳችሁ እና የጠራኋችሁ፣ እንዲሁም ያዘዝኳችሁ፣ በማገልገል እንድትኖሩ ነው። ከዚህ ሁሉ ያልተረዳችሁት የትኛውን ክፍል ነው?" በማለት ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱስ የማያምኑ ሰዎችን፡- *"ነገር ግን ራስ ወዳዶች፣ እውነትን ትተው ክፋትን በሚከተሉ ፍርድና ቁጣ ይደርስባቸዋል።"* ሮሜ 2÷8 በማለት ያስጠነቅቃል። ክርስቲያኖችን በተመለከተ ግን ቅጣቱ የዘላለም ሽልማትን ማጣት ነው።

ሙሉ በሙሉ ኖርን የምንለው፣ ሌሎችን ስንረዳ ነው። ጌታ እየሱስ፡- *"ነፍሱን ለማዳን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፣ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋት ሁሉ ግን ያድናታል።"* ብሏል፣ ማር. 8÷35፤ ማቴ. 10÷39 እና 16÷25፣ እንዲሁም ሉቃስ 9÷24 እና 17÷33ን ተመልከት። ይህ እውነት እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ፣ ወንጌላት ውስጥ አምስት ጊዜ ተጠቅሷል። በማገልገል ላይ ካልሆንህ፣ በምድር የምትኖረው እንዲሁ፤ ወይም ያለ ዓላማ ይሆናል። ምክንያቱም ሕይወትህ ትርጉም የሚኖረው ስታገለግል ነው። እግዚአብሔር ከራስ ወዳድነት ተላቀህ ሌሎችን ማፍቀርንና ማገልገልን እንድትማር ይፈልጋል።

## አገልግሎትና ጠቃሚነት

ሕይወትህን ለአንድ ነገር መስጠትህ አይቀርም። ለምን ይሆን? ለሥራ፣ ለስፖርት፣ ለዝንባሌህ፣ ለዝና ወይስ ለሀብት? ከእነዚህ አንዱም ዘላቂ ጥቅም የለውም። አገልግሎት ወደ እውነተኛ ጠቃሚነት የሚወስደን ጉዳና ሲሆን፣ የሕይወታችንን ትርጉም የምናገኘውም በማገልገል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፡- *"እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እያንዳንዳችንም*

*አገልግሎት ወደ ትክክለኛ ጠቃሚነት የሚወስደን ጎዳና ነው::*

*የሰላው ብልት ነን"* ሮሜ 12÷5 ይላል:: ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋር በአንድነት ስናገለግል ሕይወታችን ዘላለማዊ አስፈላጊነ ትን ይጐናጸፋል:: ሐዋርያው ጳውሎስ:- *"አካል የተሠራው ከብዙ ብልቶች እንጂ ከአንድ ብልት አይደለም::"* 1ቆሮ. 12÷14 ይላል:: እንዲሁም ቁ. 19 ላይ *"ሁሉም አንድ ብልት ቢሆን ኖሮ አካል ከየት ይገኝ ነበር?"* ይላል::

የራሱ በሆነው በዚህ ዓለም ላይ ለውጥ እንድታመጣ እግዚአብሔር ይፈል ጋል:: እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ምድራዊው የሕይወት ዘመንህ *እርዝመት* አይደ ለም፤ በሕይወትህ ለሌሎች *ያደረግከው* እንጂ:: *ምን ያህል ዘመን ኖርክ* ሳይ ሆን፤ *እንዴት ኖርክ*፣ የሚለው ነው ቁም ነገሩ::

በማንኛውም አገልግሎት ውስጥ የማትሳተፍ ከሆንክ፣ ምን ዓይነት ምክን ያት በማቅረብ ላይ ትሆን? አብርሃም ሽማግሌ፣ ያዕቆብ ተቅበዝባዥ፣ ሊያ ደም ግባት የሌላት፣ ዮሴፍ የተገፋ፣ ሙሴ ኮልታፋ ፣ ጌድዮን ድሃ፣ ሳምሶን ጥገኛ፣ ረዓብ ምግባረ ብልሹ፣ ዳዊት ለትዳሩ ታማኝ ያልነበረና ብዙ የቤተሰብ ችግር የነበረበት፣ ኤልያስ ሞትን የተመኘ፣ ኤርምያስ ትካዜ ያበዛ የነበረ፣ ዮናስ ላለመታዘዝ ያንገራገረ፣ ኑኃሚን ባሏ የሞተባት ሴት፣ መጥምቁ ዮሐንስ ፀባዩ ከሰው የማይገጥም፣ ጴጥሮስ ስሜታዊ እና ችኩል፣ ማርታ ጭንቀታም፣ ሳምራዊቷ ሴት ብዙ ያልተሳኩ ጋብቻዎች የነበሩዋት፣ ዘኪዮስ በሕዝብ የማ ይወደድ፣ ቶማስ ተጠራጣሪ፣ ጳውሎስ ጤናው የተቃወሰ፣ ጢሞቴዎስ ዓይ ናፋርና ፈሪ ነበሩ:: እነዚህ የተለያዩ ጉድለቶች ናቸው:: ይሁንና እግዚአብሔር ሁሉንም ለአገልግሎት ተጠቅሞባቸዋል:: ምክንያት መደርደርን እስካቆምክ ድረስ በአንተም ይጠቀማል::

## ሀያ ዘጠነኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:- አገልግሎት አማራጭ አይደለም።

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:- *«ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።»* ኤፌ 2÷10።

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:- አገለግለው ዘንድ እግዚአብሔር ያቀረበልኝን ጥሪ እንዳልቀበል ወደ ኋላ የያዘኝ ነገር ምንድነው?

30

# የተበጀኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው

*እጅህ አበጀችኝ፤ ሠራችኝም፣ ... ::*

ኢዮብ 10÷3

*ለራሴ ያበጀሁት ሕዝብ ምስጋናዬን ያውራ ዘንድ ይህን አደርጋለሁ::*

ኢሳ 43÷21

የተበጀኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው::

እግዚአብሔር በዚች ምድር ላይ እያንዳንዱን ፍጡር ሲሠራው ከአንድ ልዩ ችሎታ ጋር ነው:: አንዳንድ እንስሳት ይሮጣሉ፣ ሌሎች ይዘላሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ይዋኛሉ፣ ጥቂቶች ጉድጓድ ይቆፍራሉ፣ ሌሎች ደግሞ በክንፍ ይበርራሉ:: እግዚአብሔር ባበጃቸው መሠረት እያንዳንዳቸው የሚጫወቱት አንድ የተለየ ሚና አለ:: የሰው ልጆችን በተመለከተም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: እያንዳንዳችን አንድ ነገር ለማከናወን ልዩ ሆነን ተቀርጸናል፣ ወይም *ተበጅተናል*::

የሕንፃ *ሥራ* ባለሙያዎች (አርክቴክቶች) የአንድን ህንጻ ዲዛይን ከመ *ሥራ*ታቸው በፊት "ህንጻው ለምን አገልግሎት የሚውል ነው? እንዴትስ ጥቅም ላይ ይውላል?" ብለው ይጠይቃሉ:: የታለመለት ዓላማ ሁልጊዜ የህንጻውን ዓይነት ይወስነዋል:: እግዚአብሔርም አንተን ከመፍጠሩ በፊት በዚች ምድር ላይ እንድትጫወት የሚፈልገውን ሚና ወስኗል:: ልታገለግ ለው የሚፈልግበትን ትክክለኛ መንገድም አቅዷል:: እናም ለነዚያ ተግባራት እንደምትሆን አድርጎ አበጅቶሃል:: አንተ የሆንከውን የሆንክበት ምክንያት፣ ለተለየ አገልግሎት በመሠራትህ ነው::

*መጽሐፍ ቅዱስ*:- *«ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራ ዎች ነን::»* ኤፌ 2÷10 ይላል:: አንተ የእግዚአብሔር የእጅ *ሥራ*ው ጥበብ

ውጤት ነህ፡፡ ያለ አሳብ በገፍ የሚመረት የፋብርካ ምርት ዓይነት አይደለ ህም፡፡ ይልቁንም ልዩ፣ ተመሳሳይ የሌለህና በዓላማ የተቀረጽክ ፍጡር ነህ፡፡

እግዚአብሔር ሆን ብሎ አገልግሎትህን የተለየ በሚያደርገው መልኩ እንድታገለግለው አበጅቶሃል፡፡ አንተን ለመፍጠር የተጠቀመበትን ንጥረ ነገር (DNA)፣ የቀላቀለው በጥንቃቄ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ነገር ያለውን እጅግ አስደናቂ አትኩሮት ዳዊት እንዲህ በማለት አመስግኗል፡- *"አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና በእናቴም ማህፀን ውስጥ አበጃጅተህ ሠራኸኝ፡፡ ገረምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥ ረአለሁና አመሰግንሃለሁ፡፡"* መዝ 139÷14፡፡

*እግዚአብሔር የሚያባክነው አንድም ነገር የለም፡፡*

ኤቴል ዋተርስ የተባለ ሰው እንደተናገረው ደግሞ፣ "እግዚአብሔር የሚጣል ነገር ወይም እክት አይሠራም"፡፡

እግዚአብሔር ከመወለድህ በፊት አንተን ማበጀቱ ብቻ ሳይሆን፣ የማበጃጀቱን ሂደት ለማገዝ የሕይወትህን እያንዳንዱን ቀን አቅዶአል፡፡ ዳዊት እንዲህ ብሏል፡- *"ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን አዩ፣ ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ በመጽሐፍ ተመዘገቡ"* መዝ. 139÷16 ብሏል፡፡ ይህ ማለት በሕይወትህ ከሚያከናውነው ነገር አንድም የማይጠቅም ነገር የለም ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር *እያንዳንዱን ክስተት* ሌሎችን ለማገ ልገል እንድትበቃ ሊቀርጽህ፣ እንዲሁም እርሱን እንድታገለግለው ሊያበጃጅህ ይጠቀምበታል፡፡

እርሱ የሚያባክነው አንድም ነገር የለም፡፡ ለክብሩ ሊጠቀምበት ባይፈ ልግ ኖሮ፣ ችሎታን፣ ፍላጐትን፣ ልዩ ጥበብን፣ ስጦታን፣ ማንነትን እና የሕይወት ልምድን አይሰጥህም ነበር፡፡ እነዚህን ለይተህ በማወቅና በመረዳት እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ፈቃድ ለመገንዘብ ትችላለህ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፡- «*ገረምና ድንቅ*» ነህ ይላል፡፡ የተለያዩ ነገሮች (Factors) ውህደት ነህ፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች አምስቱን ለማስታወስ ይረዳህ ዘንድ ቀላል ምህፃረ መጠሪያ ፈጥሬ **መ-ል-ክ-ስ-ል** ብዬዋለሁ፡፡ መንፈሳዊ ስጦታህ፣ ልብህ፣ ክህሎትህ፣ ስብእናህና የሕይወት ልምምድህ (ተሞክሮህ) ናቸው፡፡ ልብ ልትላቸው ይገባል፡፡ በዚህና በሚቀጥለው ምዕራፍ እነዚህን አምስት ነገሮች (Factors) እንመለከታለን፡፡ በመቀጠልም **መልክስልህን** እንዴት እንደምታገኝና እንደምትጠቀምበት እገልጣለሁ፡፡

## እግዚአብሔር ለአገልግሎትህ እንድትስማማ አድርጎ

## አንተን የሚቀርጽበት ሁኔታ

እግዚአብሔር አንድ ሥራ በሚሰጠን ጊዜ ሁሉ ያን ተግባር ለመፈጸም የሚያስፈልገንን ነገር በሙሉ ያስታጥቀናል። ይህ የችሎታዎች ድብልቅ ያንተ መልክስል ይባላል። ሲዘረዘርም ቀጥሎ ያለውን ይመስላል፤

መንፈሳዊ ስጦታዎች

ልብ

ክህሎት ወይም ችሎታ

ስብእና ወይም ማንነት

ልምድ

## መልክስል:- *መንፈሳዊ ስጦታዎችህን መግለጥ*

እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ በአገልግሎቱ የሚጠቀምባቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች ይሰጣል፣ ሮሜ 12÷4-8፤ 1ቆሮ. 12፤ ኤፌ. 4÷8-15፤1ቆሮ. 7÷7። እነዚህ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል እንዲችሉ ለአማኞች ብቻ የተሰጡና የተለዩ ችሎታዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ:- *"መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፣ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፣ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊረዳው አይችልም።"* 1ቆሮ. 2÷14 ይላል።

መንፈሳዊ ስጦታዎችህ፣ በጥረትህ ወይም የሚገቡህ ስለሆኑ የምታገኛቸው አይደሉም። ለዚህ ነው *ስጦታዎች* የተባሉት! ከእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታዎች አንድ መገለጫ ናቸው:- *"ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል።"* ኤፌ 4÷7። እንዲኖርህ የምትፈልገውን ስጦታ ለመምረጥ አትችልም። ያን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *"እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል።"* 1ቆሮ 12÷11።

እግዚአብሔር የተለያየ ዓይነትን ስለሚወድና፣ ልዩ እንድንሆን ስለሚፈልግ፣ ለሁላችንም አንድ ዓይነት ስጦታ አልሰጠንም፤ 1ቆሮ. 12÷29-30። በተጨማሪም የትኛውም ሰው *ሁሉንም* ስጦታዎች በአንድ ላይ አይቀበልም። ሁሉም ቢኖርህ ኖሮ ብማንም ስጦታ ለመገልገል አትፈልግም ነበር። ይህ ደግሞ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ፣ እንዲሁም እንድንደጋገፍ የሚያዘውንና ከእግዚአብሔር ዓላማዎች አንዱ የሆነውን ዋና ነገር ያጠፋዋል።

መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡህ ለራስህ ሳይሆን፣ *ለሌሎች* ጥቅም ነው። እንዲሁም ለሌሎች መንፈሳዊ ስጦታ የተሰጣቸው፣ ለአንተ ጥቅም ነው።

**ሠላሳኛ ቀን**

## የተበጀኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው

መጽሐፍ ቅዱስ:- *"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መገለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው::"* 1ቆሮ 12÷7 ይላል:: እግዚአብሔር በዚህ መልኩ ያቀደው እርስ በርሳችን እንድንፈላለግ ነው:: ስጦታችንን በሕብረት ስንገለገልበት፣ ሁላችንም እንጠቀማለን:: ሌሎች ስጦታዎቻቸውን ካልተጠቀሙባቸው፣ ተገቢህ የሆነን ነገር ታጣለህ፤ አንተም በስጦታዎችህ ካልተገለገልክባቸው፣ ሰዎች ከአንተ ሊያገኙዋቸው የተገባቸውን ነገሮች ታሳጣቸዋለህ:: ለዚህ ነው መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን ለይተን እንድናውቃቸውና እንድናሳድጋቸው የታዘዝነው:: ለመሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎችህን ለመረዳት ሞክረህ ታውቃለህ? እንደተጠቀለለ የተቀመጠ ስጦታ ዋጋ የለውም::

እነዚህን ስለ መንፈሳዊ ስጦታ የተገለጡ እውነቶች በረሳን ቁጥር፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ይፈጠራል:: የተለመዱ ሁለት ችግሮች *"በስጦታ መቀናናት"* እና *"ስጦታን ለገዘፎ ማየት"* ናቸው:: የመጀመሪያው የሚከሰተው፣ ስጦታችንን ከሌሎች ሰዎች ስጦታዎች ጋር ማወዳደር ስንጀምር፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ለኛ በሰጠው ስጦታ ሳንረካ ስንቀርና፣ የሌሎች ሰዎችን በስጦታዎች አጠቃቀም ተመልክተን ስንቀና ነው:: ሁለተኛው ችግር የሚፈጠረው፣ ሰዎች ሁሉ የኛን የመሰለ መንፈሳዊ ስጦታ ይኖራቸዋል ብለን ስንጠብቅ እና፣ እኛ የተጠራንበትን ሥራ እነርሱ እንዲሠሩት እንዲሁም ለሥራው እኛ የሚሰማን ዓይነት ልዩ ፍቅርና ሸክም ይኖራቸዋል ብለን ስናስብ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *"አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው::"* 1ቆሮ 12÷5 ይላል::

> *ተከፍቶ ያልታየ ስጦታ ዋጋ የለውም::*

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አንተን ለአገልግሎት ለመቅረጽ የሚጠቀምባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች እስከትረሳ ድረስ፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ ከመጠን በላይ ታተኩራለህ:: ስጦታዎችህ እግዚአብሔር ለአገልግሎትህ ያለውን ፈቃድ የምታውቅበትን አንድ ቁልፍ ይገልጡልሃል:: ይሁንና መንፈሳዊ ስጦታዎችህ አጠቃላይ ምስል አይደሉም:: እግዚአብሔር በሌሎች አራት ነገሮች (Factors) ጭምር አበጅቶሃል::

## መልክስል:- ልብህን ማድመጥ

መጽሐፍ ቅዱስ *ልብ* የሚለውን ቃል የሚጠቀምበት እውስጥህ ያለውን ጥቅል ምኞት፣ ተስፋ፣ ፍላጐት፣ ጉጉት፣ ህልም እና ፍቅር ለመግለጥ ነው::

ልብህ፣ ውስጥህ ያለውን ማንኛውንም የመነሳሳት ምንጭ የሚወክል ሲሆን፣ ልታደርግ የምትወደውንና በጣም የምታስብለትን ነገር ያጠቃልላል:: ዛሬም እንኳን፣ *«በሙሉ ልቤ እፈቅርሃለሁ»* በምንልበት ጊዜ ይህን ቃል እንጠቀም በታለን::

*መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- "ውሃ ፊትን እንደሚያሳይ፣ የሰውም ልብ ማንነቱን ገልጦ ያሳያል::"* ምሳሌ 27÷19:: ልብህ *እውነተኛ* ማንነትህን ይገልጣል:: ማን እንደሆንክ ሰዎች *የማያስቡትን*፣ ወይም ሁኔታዎች አስገድደውህ የሆንከውን ሳይሆን፣ እውነተኛ ማንነትህን ነው ልብህ የሚገልጠው:: የተናገርከውን ለምን እንደተናገርህ፣ የተሰማህ ስሜት ለምን እንደተሰማህ፣ ያደረግከውን ለምን እንዳደረግህ የሚወሰነው ልብህ ነው፣ ማቴ. 12÷34፤ መዝ 34÷7፤ ምሳሌ 4÷23ን ተመልከት::

በተፈጥሮ እያንዳንዳችን ልዩ የልብ ምት አለን:: ልዩ የጣት አሻራ፣ የዓይን ውሃ፣ እና ድምጽ እንዳለን ሁሉ፣ የልባችን ምትም እጅግ መጠነኛ ልዩነት አለው:: በምድር ላይ እስከ ዛሬ ከኖሩት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦች መካከል አንድም ሰው ያንተን የሚመስል የልብ ምት የሌለው መሆኑ እጅግ አስደናቂ ነው::

በተመሳሳይም እያንዳንዳችን አሳባችንን ስለሚማርኩ ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎች በምናሰላስልበት ጊዜ ልዩና የኛ ብቻ የሆነ *ስሜታዊ* «የልብ ምት» እግዚአብሔር ሰጥቶናል:: ለአንዳንድ ነገሮች በደመነፍስ እንጨነቃለን፣ ስለሌሎቹ ደግሞ ግድ የለንም:: እነዚህ ሁኔታዎች የት ማገልገል እንደሚኖርብህ የሚጠቁሙ ፍንጮች ናቸው::

ሌላኛው የልብ መጠሪያ ቃል ጥልቅ ስሜት (Passion) ነው:: ጥልቅ ስሜት የሚያሳድሩብህ አንዳንድ ጉዳዮች አሉ:: ለሌሎቹ ደግሞ ግድ አይኖርህም:: አንዳንድ ሁኔታዎች በጣም ያነቃቁህና ትኩረትህን ይቆጣጠሩታል፤ ሌሎቹ ደግሞ ስሜትህን የሚጐዱና የሚያስለቅሱህ ይሆናሉ:: እነዚህ ሁኔታዎች የልብህን አፈጣጠር ነው የሚያመለክቱት::

በልጅነትህ እጅግ የሚያስደስቱህ ነገሮች፣ ምናልባት ከቤተሰቦችህ ማንም ከቁም ነገር የማይቆጥራቸው መሆናቸውን አጢነህ ይሆናል:: እነዚህ ዝንባሌዎች ከየት መጡ? ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: እግዚአብሔር እነዚህን ተፈጥሯዊ ዝንባሌዎች ሲሰጥህ አንድ ዓላማ ነበረው:: የልብ ምትህ ለአገልግሎት የተበጀህበትን መልክስል ለመረዳት ሁለተኛው ቁልፍ ነው:: ዝንባሌዎችህን ችላ አትበላቸው:: ይልቁንም ለእግዚአብሔር ክብር የሚውሉበትን ሁኔታ አስብ:: እነዚህን ነገሮች ለመሥራት የምትወድበት ምክንያት አለ::

መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ እንዲህ ይላል፣ «*በፍጹም ልባችሁ አምላካችሁን አገልግሉ*» ዘዳ. 11÷13፤ 1ሳሙ. 12÷20፤ ሮሜ 1÷9፤ ኤፌ. 6÷6 ። እግዚአብሔር በፍቅር እንጂ በግዳጅ እንድታገለግለው አይፈልግም። ሰዎች ዝንባሌና ጉጉት በማያሳድርባቸው ሥራ ላይ ቢሠማሩ የሚያመጡት ውጤት እምብዛም ነው። እርሱንና ሰዎችን ለማገልገል ተፈጥሯዊ ዝንባሌህን እንድትጠቀም፣ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ውስጥህ የሚጮኸው ፍላጐት ብታደምጠው እግዚአብሔር ለአንተ ያሰበው አገልግሎት የቱ መሆኑን ይጠቁምሃል።



እግዚአብሔርን ከልብህ ማገልገልህን የምታውቀው እንዴት ነው? የመጀመሪያው ጠቋሚ ነገር *ፍላጎት ወይም መነሣሣት* ነው። *የምትወደውን ነገር* ስትሠራ ማንም ሊያነሣሣህ አያስፈልግም፤ ሊያደፋፍርህ ወይም ሊቆጣጠርህም አይችልም። የምታደርገው ፍጹምና ንጹህ በሆነ ደስታ ነው። ክፍያ፣ ሙገሳና አፀፋ አትፈልግም። ምክንያቱም በዚህ መንገድ ማገልገልህን ትወደዋለህ። ተቃራኒውም እውነት ነው። ከልብህ ሳትፈልግ የምትሠራውን ስታከናውን በቀላሉ ተስፋ ትቆርጣለህ።

እግዚአብሔርን ከልብ የማገልገልህ ሁለተኛ መግለጫ *ውጤታማነት* ነው። *እንደትወደው* አድርጐ እግዚአብሔር እውስጥህ ያስቀመጠውን ሥራ ስትሠራ ውጤታማ ትሆናለህ። *ጽኑ የውስጥ ፍላጐት* ጥሩ ሥራ ያሠራል። አንድን ሥራ የምትሠራው ያለ ፍላጎትህ ከሆነ፣ በሥራው ውጤታማ ልትሆን አትችልም። በየትኛውም የሥራ መስክ በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ የሆኑ ሰዎች፣ ትርፍ ለማግኘት ወይም በግዴታ ሳይሆን፣ በጽኑ ፍላጐት የሠሩ ናቸው።

*የምትወደውን ነገር ስትሠራ ማንም ሊያነሣሣህ አያስፈልግም።*

ሰዎች "የማልወደውን ሥራ የምሠራው ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ስል ነው። አንድ ቀን ግን ይህን ትቼ የምወደውን እሠራለሁ።" ሲሉ ሰምተናል። ይህ ትልቅ ስህተት ነው። የልብህን መሻት በማይገልጥ ሥራ ላይ በመሠማራት ሕይወትህን አታባክነው። የሕይወት ታላላቅ ነገሮች ቁሳቁሶች አለመሆናቸውን አስታውስ። የሕይወት ትርጉም በብዙ እጥፍ ከገንዘብ ይልቃል። በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌለው ባለፀጋ የነበረ ሰው አንድ ጊዜ ሲናገር፦ "*እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር፣ ሁከት ካለበት ትልቅ ሀብት ይበልጣል*" ምሳሌ 15÷16 ብሏል።

"ለጥሩ ኑሮ" ብለህ አንድ ነገር ላይ አትደላደል፤ ምክንያቱም ጥሩ ኑሮ

በራሱ ጥሩ አይደለም። በመጨረሻ አያረካህም። የምትኖርበት ብዙ ሀብት ሊኖርህና እንዳችም የምትኖርበት ምክንያት አይኖርህ ይሆናል። ይልቅ "ለተሻለ ህይወት" አልም። ይህ የሚሆነው የልብህን በሚገልጥ መንገድ እግዚአብሔርን ስታገለግለው ነው። ደስ የሚያሰኝህን፤ እንድትሠራ እግዚአብሔር በልብህ ያኖረውን ሥራ ለይና እወቅ። ከዚያም ለእግዚአብሔር ክብር ፈጽመው።

ሠላሳኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:- የተበጀሁት እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው።

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:- *"አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው።"* 1ቆሮ 12÷6።

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:- ሌሎችን በጥልቅ ፍቅር በማገልገልና ሥራውንም በመውደድ ረገድ በምን ሁኔታ ነው እራሴን ለማየት የምችለው?

31

# መልክስልህን (ቅርጽህን) መረዳት

*አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፣ በእናቴ ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ ሰራኸኝ።*

መዝ. 139÷13

አንተን መሆን የምትችለው አንተው ብቻ ነህ።

እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን የቀረጸን፣ በዓለም ተመሳሳይ ቅጂያችን እንዳይኖር አድርጎ ነው። አንተን ልዩ ያደረጉህን ነገሮች የመሰለ ውሁድ ያለው ማንም የለም። አንተ እንዲኖርህ እግዚአብሔር ያሰበው ሚና በምድር ላይ ሌላ ሰው ሊኖረው አይችልም ማለት ነው። ለክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያን)፣ ልታበረክተው የሚገባህን ልዩ ሥራ ካላከናወንህ፣ ሥራው ሳይሠራ ይቀራል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *"ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራ ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው።"* 1ቆሮ 12÷4-6 ። ባለፈው ምዕራፍ ከነዚህ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን፣ ማለት ስለ ስጦታዎችህና ልብህ ተመልክተናል። አሁን ቀሪውን እና እግዚአብሔርን የማገልገል **መልክስልህን** እንመለከታለን።

## መልክስል: *በክህሎቶችህ መጠቀም*

ችሎታዎችህ አብረውህ የተወለዱ የተፈጥሮ ጥበቦች ናቸው። አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮ የቃላት ችሎታ አላቸው። ከእናታቸው ማህፀን የወጡት እየተናገሩ ነው! አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮ የአካል ቅልጥፍና ችሎታ የታደሉ ይሆኑና በአካል ብቃት ከሌሎች የተሻሉ ይሆናሉ። ሌሎቹ ደግሞ የሂሳብ፣ የሙዚቃ ጥበብ ወይም የመካኒክነት ልዩ ችሎታ ይኖ

ራቸዋል፡፡

እግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን እና ሌሎች የማምለኪያ መገልገያዎችን ለማዘጋጀት ሲፈልግ፣ ለሥራው የሚሆኑ የእጅ ጥበብ ባለ ሙያዎችን አዘጋ ጅቷል፡፡ እነሱም፡- *«በሁሉም ዓይነት የእጅ ጥበብ ሥራ፣ ብልሃት ችሎታና ዕውቀት»* ዘፀ. 31÷3-5 ያላቸው ሆነው ነበር የተቀረጹት፡፡ ዛሬም እግዚአብሔር ሰዎች ያገለግሉት ዘንድ እነዚህንና በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች ችሎታዎችን ይሰጣቸዋል፡፡

**ችሎታዎቻችን ሁሉ የመጡት ከእግዚአብሔር ነው፡፡** ለኃጢአት ሥራ የምናውላቸው ችሎታዎቻችን እንኳን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡን፣ ነገር ግን ያለ አግባብ የተጠቀምንባቸው ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *"እንደተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን"* ሮሜ 12÷6፡፡ የተፈጥሮ ችሎታዎችህ ከእግዚአብሔር የተሰጡህ በመሆናቸው፣ ከመንፈሳዊ ስጦታዎችህ እኩል አስፈላጊ እና «መንፈሳዊ» ናቸው፡፡ ልዩ የሚያደርጋቸው፣ የተፈጥሮ ስጦታዎችህ ስትወለድ አብረውህ የመጡ መሆናቸው ብቻ ነው፡፡

ሰዎች ላለማገልገል ከሚሰጡዋቸው እጅግ የተለመዱ ምክንያቶች አንዱ፣ «የምሰጠው ወይም የማገለግልበት ምንም ችሎታ የለኝም» የሚል ነው፡፡ ይህ ማላገጥ ይሆናል፡፡ ውስጥህ የቀበርካቸው፣ በደርዘን፣ ምናልባትም በመቶዎች፣ የሚቆጠሩ፣ ያልተነኩ፣ ያላስተዋልካቸውና ያልተጠቀምክባቸው ችሎታዎች አሉህ፡፡ መካከለኛ የዕውቀት ደረጃ አለው የሚባል አንድ ሰው ከ500 እስከ 700 የሚደርሱ የተለያዩ ችሎታዎች ያሉት መሆኑን ብዙ ጥናቶች ይገልጣሉ፡፡ ይህም ከምትገነዘበው በላይ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ አንጎልህ 100 ትሪሊየን ክስተቶችና ዕውቀቶችን ለመያዝ ይችላል፡፡ አዕምሮህ በሰከንድ 15,000 ውሳኔዎችን ለመስጠት ይችላል፤ እውስጥህ በሚካሄደው የምግብ መፍጨትና የመዋሃድ ሂደት እንደሚሆነው ማለት ነው፡፡ አፍንጫህ 10,000 የሚያህሉ የተለያዩ ሽታዎችን ለማሽተት ይችላል፡፡ እጅህ 1/25000ኛ የሆነ ነገርን በዳሰሳ ለመለየት ይችላል፡፡ ምላስህ ሁለት ሚሊዮን እጅ ውሃ ውስጥ ያለን የአንድ ኪኒን ክፋይ ውሁድ በቅምሻ ሊለይ ይችላል፡፡ የታጨቁ ድንቅ ችሎታዎች ባለቤት እና ዕጹብ ድንቅ የሆንክ የእግዚአብሔር ሥራ ነህ፡፡ የቤተ ክርስቲያን አንዱ ኃላፊነት የታመቁ ችሎታዎችህን ለይቶ ማውጣትና ለእግዚአብሔር ሥራ አገልግሎት እንድታውለው ማድረግ ነው፡፡

**ማንኛውም ችሎታ ለእግዚአብሔር ክብር ሊውል ይችላል፡፡** ጳውሎስ፡- *« ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት፡»* 1ቆሮ. 10÷31 ብሏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለክብሩ በተጠቀመባቸው

የችሎታ ምሳሌዎች የተሞላ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከተጠቀሱት ችሎታዎች ጥቂቶቹ፣ የሥነ-ጥበብ ችሎታ፣ የሥነ-ህንፃ ችሎታ፣ የአስተዳደር ችሎታ፣ የምግብ ማብሰል፣ የጀልባ ሥራ፣ የከረሜላ ሥራ፣ የመከራከር፣ የዲዛይን ሥራ፣ አስከሬን በማድኃኒት የማድረቅ ጥበብ፣ የጥልፍ ሥራ፣ የቅርጻ ቅርጽ ሥራ፣ የግብርና ሥራ፣ የዓሣ ማጥመድ፣ የአትክልተኛነት፣ የመሪነት፣ የግንባታ ዕቃዎች ሥራ፣ የሙዚቃ ሥራ፣ የጦር መሣሪያ ሥራ፣ በመርፌ የመስፋት ጥበብ፣ የስዕል ጥበብ፣ የተከላ ሥራ፣ ፍልስፍና፣ የማሽን ሥራ፣ የፈጠራ ሥራ፣ የአናጺነት ሥራ፣ ጀልባ ቀዘፋ፣ የሽያጭ ሥራ፣ ወታደርነት፣ የስፌት ሥራ፣ አስተማሪነት፣ የሥነ-ጽሑፍና የግጥም ሥራ እና የመሳሰሉት ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *"አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው::"* 1ቆሮ. 12÷6 ይላል:: እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ልዩ ችሎታህ የሚንጸባረቅበትና ለውጥ የምታመጣበት ቦታ አለው:: ያን ቦታ ፈልጎ ማግኘት ያንተ ፈንታ ነው::

እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎች ብዙ ገንዘብ ለማግኘት የሚችሉበትን ችሎታ ሰጥቷቸዋል:: ሙሴ እስራኤላውያንን:- *«ነገር ግን ሀብት እንድታፈራ ችሎታ የሰጠሁ... እርሱ ስለሆነ፣ አምላክህን እግዚአብሔርን አስበው»* ዘዳ. 8+18 በማለት አሳስቧቸዋል:: ይህ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ንግድን በማቋቋም፣ በግብይት ጊዜ ውሳኔ በመስጠትና ጥሩ ትርፍ በማግኘት ጉበዞች ናቸው:: ይህ የንግድ ችሎታ ካለህ፣ ለእግዚአብሔር ክብር ልትጠቀምበት ይገባል:: እንዴት? በመጀመሪያ ይህ ችሎታ ከእግዚአብሔር የሚመጣ መሆኑን እወቅና የሚገባውን ክብር ስጠው:: ሁለተኛ የሌሎችን ፍላጐት ለማገልገያና፣ ላላመኑ ሰዎች ስለ እምነትህ መናገሪያነት ተጠቀምበት:: ሦስተኛ ከትርፍህ ቢያንስ ከመቶ አሥሩን ለእግዚአብሔር በመስጠት አምልኮህን ፈጽም ዘዳ. 14÷ 22-27:: በመጨረሻም ዋና ግብህ *ሀብትን ማካበት* ሳይሆን፣ *የእግዚአብሔርን መንግሥት መገንባት* ይሁን:: ይህን ጉዳይ ምዕራፍ 34 ውስጥ እገልጠዋለሁ::

***ለመሥራት የምችለውን*** **እንዳደርግ ነው እግዚአብሔር** ***የሚፈልገው***:: በምድር ላይ ያንተ በሆኑት ችሎታዎች ለመጠቀም የምትችለው አንተ ብቻ ነህ:: እግዚአብሔር ለአንተ ብቻ የሰጠህን የሚመስል **መልክስል** ያለውና ሚናህንም ሊጫወት የሚችል ሰው የለም:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መልካም ነገር የሚያስታጥቅህ መሆኑን እንዲህ በማለት ይገልጣል:- *"ፈቃዱን እንድታደርጉ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታጥቃችሁ፣ ደስ የሚያሰኘውንም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ያድርግ፣ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፣ አሜን"*
ዕብ 13+21:: እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ፈቃድ እንድታውቅ ይረዳህ

ዘንድ፣ ምን ለመሥራት ጥሩ ችሎታ እንዳለህና በምን ደካማ እንደሆንህ በጥብቅ መርምረህ እወቅ::

*ለመሥራት የምችለውን እንዳደርግ ነው እግዚአብ ሔር የሚፈልገው::*

እግዚአብሔር የሙዚቃን ድምፅ ጠብቀህ የመዘመር ችሎታን ካልሰጠህ፣ የግል ዘማሪ እንድትሆን አይጠብቅም:: ዘመንህን ሁሉ ልዩ ክህሎት በሌለህ ሥራ እንድ ታሳልፍም አይጠይቅህም:: በሌላ በኩል ግን፣ ያሉህ ችሎታዎች እግዚአብሔር በዘመንህ ሁሉ እንድትሠራ የሚፈልገውን ሥራ የሚያሳዩ ብርቱ ጠቋሚዎች ናቸው:: ላንተ ያለውን ፈቃድ እንድታውቅ የሚረዱ አመልካቾችም ናቸው:: ዲዛይን በማውጣት፣ በስዕል፣ ወይም በማደራጀት ሥራ ጥሩ ችሎታ ካለህ፣ እግዚአብሔር በሕይወትህ ያለው ፈቃድ እነዚህን ክህሎቶች ያካተተ መሆኑን በሚገባ ለመገመት ትችላለህ:: እርሱ ጥሪያችንን ከችሎታዎቻችን ጋር ያቀራኛ ል እንጂ፣ ችሎታዎቻችንን አያባክንም ::

ችሎታዎችህ ለአገልግሎት እንድትጠቀምባቸው እንጂ፣ ለኑሮ የሚያስፈልግ ህን ገንዘብ (እንጀራ) ለማግኛ ብቻ አይደለም ከእግዚአብሔር የተሰጡህ:: ጴጥ ሮስ:- "*እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሰባውን ያገልግል*፦" 1ጴጥ 4፥10 ብሏል::

ሠላሳ አንደኛ ቀን

**መልክስልህን መረዳት**

ይህ ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ እንኳን አሜሪካ በሚገኘውና ሳድልባክ በሚባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ 7,000 ሰዎች ችሎታዎቻቸውን ለተለያዩ የቤተክ ርስቲያኒቱ አገልግሎቶች በማዋል ላይ ናቸው:: ለተቸ ገሩ ሰዎች የተለገሱ አሮጌ መኪናዎችን በማደስ፣ ቤተ ክርስቲያን በምታካሂዳቸው ልዩ ልዩ ግዢዎች እየተደራደሩ እጅግ ቅናሽ የሆነ ዋጋ በማስገኘት፣ በቅየሳ ሥራዎች፣ ፋይሎችን በሚገባ በማደራጀት፣ አካባቢን በማሳመር፣ በሥነ ጥበብ ሥራ፣ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና የህንጻዎችን ዲዛይን መሥራት፣ የጤና አገልግሎት በመስጠት፣ ምግብ በማዘጋጀት፣ መዝ ሙር በመድረስ፣ ሙዚቃ በማስተማር፣ የዕርዳታ መጠየቂያ እቅዶችን በመ ጻፍ፣ ቡድኖችን በመምራት፣ በአምልኳዊ ሥርአቶች ላይ ያተኮረ ጥናት በማካ ሄድ፣ ጥናቶችን በመተርጐም እና በመቶዎች በሚቆጠሩ ሌሎች ሞያዊ ተግባ ራት ይሳተፋሉ:: ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሚመጡ አዳዲስ አባላት፣ "ባለህ ሞያ ቤተክርስቲያንህን ልታገለግል ይገባል::"እየተባለ ይነገራቸዋል::

## መልክስል: *በማንነትህ መጠቀም*

እያንዳንዳችን ምን ያህል ልዩ እና ተመሳሳይ የሌለን መሆናችንን እናስተ ውልም:: የDNA ሞሊኩይሎች ወሰን በሌላቸው መንገዶች ይደባለቃሉ:: የድብልቁ ቁጥር ሲቀመር $10^{2.400.000.000.000}$ ነው:: ይህ ቁጥር የሚያሳየው፣ አንተን መሳይ ሰው ለማግኘት የማይታሰብ መሆኑን ነው:: ከዚህ ቁጥር እያን ዳንዱን 0 አንድ ኢንች ስፋት እንዲኖረው አድርገህ ልትጽፈው ብትሞክር፣ 37,000 ማይልስ እርዝመት ያለው ወረቀት ያስፈልግሃል::

ይህን ነገር ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ በማሰብ አንዳንድ ሳይንቲስቶች አጥ ናፊ ዓለሙ ውስጥ ያሉት እያንዳንዱ ቅንጣቶች ቢቆጠሩ፣ ከኋላው 76 ዜሮ ዎችን ባስከተለ 10 ቁጥር ያንሱ ይሆናል በማለት ገምተዋል:: ይህ መጠን ያንተ DNA ሊሆን ከሚችለው መጠን በጣም ያነሰ ነው:: ያንተ ልዩ መሆን ሳይንሳዊ የሕይወት እውነት ነው:: እግዚአብሔር አንተን ከሠራ በኋላ ቅርጽ ማውጫውን ሰብሮታል:: እናም አንተን የመሰለ ሰው ቀድሞ አልነበረም፤ ወደ ፊትም አይኖርም::

እግዚአብሔር የተለያየ ዓይነትን የሚወድ መሆኑ ግልጥ ነው፤ ዙሪያህን በመመልከት ብቻ ይህን ለማረጋገጥ ትችላለህ:: እያንዳንዳችንን የብቻችን በሆነ ልዩ ልዩ ማንነት ፈጥሮናል:: *በይናፋሮችንና ደፋሮችንም ፈጥሯል::* የተለመደ ነገር የሚወዱ እንዲሁም *ልዩ ልዩ የሆኑ* ነገሮችን የሚወዱ ሰዎችንም ፈጥ ሯል:: አንዳንዶችን *«አስተዋዮች»* አንዳንዶችን *«ለሚታዩዎች»* አድርጎ አበጅቷ ቸዋል:: አንዳንዶች በግል፣ ሌሎች ደግሞ በቡድን ሲሠሩ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ:: *መጽሐፍ ቅዱስ «አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው ::»* 1ቆሮ. 12፥6 ይላል::

እግዚአብሔር በሁሉም ዓይነት ማንነት የሚጠቀም ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማረጋገጫዎች ይሰጠናል:: ጴጥሮስ ደፋር፣ ጳውሎስ ቁጡ፣ ኤር ሚያስ ተካዥ ወይም ሐዘንተኛ ነበሩ:: በአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መካከል የነበረውን የማንነት ወይም የባሕርይ ልዩነት ስትመለከት ለምን አንዳንዴ እርስ በርስ ይጋጩ እንደ ነበረ በቀላሉ ትረዳለህ::



ለአገልግሎት «ትክክል» ወይም «ስህተት» የሚባል የሰው ማንነት የለም:: ቤተክርስቲያን ሚዛናዊና አስደሳች እንድትሆን፣ ሁሉም ዓይነት ማንነት ያስፈልጋታል:: ሁላችንም አንድ አይነት ብንሆን ኖሮ ዓለም እጅግ አሰልቺ ትሆን ነበር:: ጥሩነቱ ግን የሰው ልጆች ልዩ ልዩ በሆኑ ማንነቶች ተገል ጠዋል::

*መንፈሳዊ ስጦታዎችህን፣ እንዲሁም ችሎታዎችህን እንዴትና የት*

ልትጠቀምባቸው እንደሚገባ ማንነትህ ይወስነዋል፡፡ ለምሳሌ ሁለት ሰዎች ተመሳሳይ የወንጌላዊነት ስጦታ ቢኖራቸውና አንደኛው አይናፋር፣ ሌላው ደግሞ ደፋር ቢሆኑ፣ ስጦታዎቻቸውን የሚገልጡበት መንገድ የተለያየ ይሆናል፡፡

አናጢዎች እንጨትን ከተፈጥሮአዊ መስመሩ በተቃራኒ ከመቁረጥ ይልቅ መስመሩን ተከትሎ መቁረጡ የሚቀል መሆኑን ያውቃሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ «ከማንነትህ ውጭ» በሆነ መንገድ እንድታገለግል ስትገደድ፣ መጨነቅና አለመቻቻት ይፈጠርብሃል፤ ሥራው ተጨማሪ ልፋትና ኃይል ይጠይቃል፤ እናም ውጤቱ አናሣ ይሆናል፡፡ ለዚህ ነው የሌላን ሰው አገልግሎት አስመስሎ መሥራቱ በፍጹም የማይቻለው፡፡ አንተ *የእነርሱ* ማንነት የለህም፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረህ ራስህን እንድትሆን ነው! ከሌሎች ምሳሌነት ልትማር ትችላለህ፤ ነገር ግን፣ የተማርከውን ነገር በራስህ **መልክስል** ልታጠራው ይገባል፡፡ ዛሬ ማንነትህን እንድትረዳ የሚያግዙህ ብዙ መጻሕፍት እና መሣሪያዎች አሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ማንነትህን ለእግዚአብሔር ሥራ ልትጠቀምበት የምትችልበትን መንገድ ልትወስን ትችላለህ፡፡

የተለያዩ ማንነቶቻችን ልዩ ቀለም እንደተቀባ መስታወት የእግዚአብሔርን ብርሃን በተለያዩ ቀለማትና ቅርጽ ያንጸባርቃሉ፡፡ ሁኔታው የእግዚአብሔርን ቤተ ሰብ በጥልቀትና በልዩ ልዩ መልኩ ይባርካል፡፡ እኛንም በግል ይባርከናል፡፡ እግዚአብሔር ያቀደልህን መሥራቱ ደስ *ያሰኝሃል*፡፡ በሰጠህ ማንነት ስታገለግል ስኬት፣ እርካታና ፍሬያማነት ያንተ ይሆናሉ፡፡

> *እግዚአብሔር ሲፈጥርህ ያቀደልህን ሥራ መሥራቱ ደስ ያሰኝሃል፡፡*

## መልክስል፡ በልምዶችህ መጠቀም

በአብዛኛው ከቁጥጥርህ ውጭ በሆኑ የሕይወት ልምዶች ተቀርጸሃል፡፡ እግዚአብሔር እነዚህ ልምምዶች በሕይወትህ እንዲኖሩ የፈቀደው፣ ሊቀርጽህ ባለው ዓላማ ምክንያት ነው፣ 2ቆሮ 1÷4፡፡ እርሱን ለማገልገያነት የተበጀህበትን ሁኔታ ለማወቅ ካለፈው ሕይወትህ ቢያንስ ስድስት ዓይነት ልምዶችን መመርመር ይኖርብሃል፡-

- *በተሰባዊ* ልምምዶች፣ ቤተሰብህ መሀል በማደግ ላይ ሳለህ ምን ተምረሃል?
- *ትምህርታዊ* ልምምዶች፣ ትምህርት ቤት ሳለህ የምትወዳቸው

የትምህርት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

- *ሙያዊ* ልምምዶች፣ በጣም የምትወዳቸውና ስትሠራቸውም ይበልጥ ውጤታማ የሆንክባቸው የሥራ መስኮች ምን ነበሩ?
- *መንፈሳዊ* ልምምዶች፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያሳለፍካቸው በጣም ትርጉም ያላቸው ጊዜያት የተኞቹ ነበሩ?
- *የአገልግሎት* ልምምዶች፣ እግዚአብሔርን እንዴት ታገለግለው ነበር?
- *አስቸጋሪ* ልምምዶች፣ ከምን ዓይነት ችግሮች፣ ጉዳቶች፣ ሀዘኖችና ፈተናዎች ተምረሃል?

እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ሲያዘጋጅህ ይበልጥ የሚጠቀመው፣ በመጨረሻ ዎቹ ወይም አስቸጋሪዎቹ የሕይወት ልምምዶችህ ነው። ***እግዚአብሔር ጉዳትን በፍጹም ያለጥቅም አያባክንም።*** እንደውም ከሁሉ የሚበልጠው አገልግሎትህ ብዙ ጊዜ የሚወጣው በጣም ከተጐዳህበት ነገር ነው። በአእምሮ ዝግመት በሽታ የሚጠቃ ልጅ ያላቸውን ወላጆች ለማገልገል፣ ተመሳሳይ በሽታ ያለበት ልጅ ካላቸው ወላጆች የተሻለ ማን አለ? ከአልኮል ሱሶች ለመላቀቅ የሚታገል ሰውን ለመርዳት፣ እንዲህ ዓይነቱን ክፉ ቁራኛ ተዋግቶ ነፃነትን ካገኘ ሰው የተሻለ ማን ይኖራል? ባሏ ሌላ ሴት አፍቅሮ የሄደባትን ሴት በዚሁ ስቃይ ውስጥ ካለፈች ሴት ይበልጥ ማን ሊያጽናናት ይችላል?

እግዚአብሔር ሌሎችን ለምትረዳበት አገልግሎት ሊያዘጋጅህና ሊያስታጥቅህ ሲፈልግ ሆን ብሎ በተለያዩ መከራዎች ውስጥ ያሳልፍሃል። መጽሐፍ ቅዱስ፡- *"እኛ ራሳችን ከእግዚአብሔር በተቀበልነው መጽናናት፣ በመከራ ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣ እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናል።"* 2ቆሮ 1÷14 ይላል።

እግዚአብሔር እንዲጠቀምብህ ከልብህ ከፈለግህ፣ አንድ ታላቅ እውነት ልት ረዳ *ይገባል*። ከምንም በላይ የምትጠላቸው ወይም የሚጸጽቱህ፣ እናም ልትደ ብቃቸውና ልትረሳቸው የምትፈልጋቸው የሕይወት ልምዶችህ፣ እግዚአብሔር ሌሎችን ለመጥቀሚያነት ሊገለገልባቸው የሚፈልጋቸው አገልግሎቶችህ ናቸው!

እግዚአብሔር በተጐዳህባቸው የሕይወት ልምዶች ለመጠቀም ይችል ዘንድ፣ ለሰዎች ልትነግራቸው ፈቃደኛ መሆን አለብህ። መደበቁን ትተህ፣ ስህተትህን፣ ውድቀትህንና ፍርሃትህን አምነህ ልትቀበል ይገባል። ይህ ምናልባት ከሁሉ የሚበልጥ ውጤታማ አገልግሎትህ ሊሆን ይችላል። ሰዎችን ይበልጥ ልናበ ረታታቸው የምንችለው፣ ጥንካሬያችንን አንድ ባንድ እየዘረዘርን ስንመጻደ ቅባቸው ሳይሆን፣ በተለያዩ ድክመቶቻችን የእግዚአብሔር ጸጋ ምን ያህል እንደ ረዳን ስንነግራቸው ነው።

ጳውሎስ ይህን እውነት ስለተረዳ ከሀዘን ጋር የነበረውን ትግል እንዲህ በማለት ሳይደብቅ ተናግሯል፡- *«ወንድሞች ሆይ በእስያ ስለ ደረሰብን መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፣ በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስክምንቆርጥ ድረስ ከአቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር፡፡ በእርግጥም የሞት ፍርድ እንደተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው*

*እግዚአብሔር በተገዳሀባቸው የሕይወት ልምዶችህ ለመጠቀም ይችል ዘንድ ለሰዎች ልትነገራቸው ፈቃደኛ መሆን አለብህ፡፡*

*ሙታንን በሚያስነሣው በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው፡፡ እርሱ እንዲህ ካለው የሞት አደጋ አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ወደ ፊትም ደግሞ እንደሚያድነን ተስፋችንን በእርሱ ላይ ጥለናል፡፡»* 2ቆሮ. 1÷8-10፡፡

ጳውሎስ የገጠመውን የተስፋ መቁረጥና የመጠራጠር ልምድ ምስጢር አድርጐ ቢያስቀረው ኖሮ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከልምዱ በመማር አይጠቀሙም ነበር፡፡ የተገለጡ የሕይወት ልምምዶች ብቻ ናቸው ሌሎችን ለመርዳት የሚችሉት፡፡ አዶልፍ ኽክስሊይ የተባለ አንድ ሰው፡- "የሕይወት ልምድህ የተከሰተብህ ሁኔታ ሳይሆን፣ በተከሰተብህ ሁኔታ የተነሣ የምትፈጽመው ነው» ብሏል፡፡ ባለፍክባቸው ሁኔታዎች ምን ትሠራባቸዋለህ? ያለፈ ጉዳትህን በከንቱ አታባክነው፡፡ ይልቁንስ ሌሎችን ለመርዳትነት ተጠቀምበት፡፡

ለአገልግሎት የተበጀህባቸውን አምስት መንገዶች እስካሁን ስንመለከት፣ እግዚአብሔር ታገለግለው ዘንድ ላዘጋጀህ ዓላማ በምን ሁኔታ እንዳዘጋጀህ ግልጥ የሆነ መረዳት እንዳገኘህና፣ ይህንንም በማድረጉ፣ ለሉዓላዊነቱ ከልብ የመነጨ አድናቆት እንዳደረብህ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ለአገልግሎትህ ፍሬያማነትም ሆነ ስኬት ዋናው ምስጢር፣ በተበጀህበት መልክስል መጠቀሙ ነው፡፡ የልብህ መሻት ባለበት፣ ማንነትህንና የሕይወት ልምድህን በሚገልጥ መንገድ፣ በመንፈሳዊ ስጦታዎችህና ችሎታዎችህ ተጠቅመህ ስትሠራ እጅግ ውጤታማ ትሆናለህ፡፡ እነዚህ በትክክል ሲከናወኑ ይበልጥ ይሳካልሃል፡፡

ሠላሳ አንደኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ማንም እኔን ሊሆን አይችልም።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *"እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ፀጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የፀጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል"* 1ጴጥ. 4÷10።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** እግዚአብሔር ከሰጠኝ ችሎታ ወይም የግል ልምድ፣ ለቤተክርስቲያኔ ላበረክተው የምችለው ምን አለ?

# 32

# እግዚአብሔር በሰጠህ መጠቀም

*እንግዲህ እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፡፡*
*እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን፡፡*
ሮሜ 12÷5

*አንተነትህ ከእግዚአብሔር የተሰጠህ ሲሆን፣ በአንተነትህ የምታከናውነው ሥራ [illegible]ም [illegible]እግዚአብ[illegible]ጠው ነው፡፡*
የዳኒ[illegible]

እግዚአብሔር ከአንተነትህ ምርጥ የሆነው ነገር ይገባዋል፡፡ የፈጠረህ ለዓላማ በመሆኑ፣ በተሰጠህ ነገር የተቻለህን ሁሉ እንድትሠራበት ይጠብቃል፡፡ ስለሌሉህ ችሎታዎች እንድትጨነቅ ወይም ቢኖረኝ እያልክ እንድትመኝ አይፈልግም፡፡ ይልቁንም እንድትጠቀምባቸው በሰጠህ ልዩ ተሰጥኦዎች ላይ እንድታተኩር ነው የሚሻው፡፡


ለአገልግሎት ባልተቀረጽህባቸው መንገዶች እግዚአብሔርን ለማገልገል በምትሞክርበት ጊዜ፣ ድርጊትህ አራት ማዕዘን የሆነ ብሎንን ክብ ቀዳዳ ውስጥ ለመክተት እንደመታገል ይቆጠራል፡፡ ይህን የመሰለውን ሙከራ ተስፋ የሚያስቆርጥ ከመሆኑም በላይ፣ ውጤቱ ውሱን ነው፡፡ ጊዜህን፣ ተሰጥኦህን እና ጉልበትህን ያባክናል፡፡ ሕይወትህን በተመራጭ ሁኔታ መጠቀም ማለት፣ እግዚአብሔርን በተሠራህበት ሁኔታ፣ ማገልገል ማለት ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ፣ **መልክስልህን** ማወቅ፣ ተቀብለህ በእርሱ ደስተኛ መሆን እና ሙሉ ጠቀሜታው እስኪገለጥ ድረስ ማሳደግ ይኖርብሃል፡፡

## መልክስልህን ተረዳ

*መጽሐፍ ቅዱስ፡- "ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ፡፡"* ኤፌ. 5÷17 ይላል፡፡ ሌላ ቀን ሳታሳልፍ አሁኑኑ እግዚአ

ብሔር ያቀደው ምን እንድትሆንና እንድትሠራ መሆኑን አጥርተህ ለመረዳት ሞክር።

ስጦታና ችሎታዎችህን በመመርመር ጀምር። ችሎታ ያለህ በየትኞቹ ነገሮች ላይ እንደሆነና፣ የሚያቅቱህ የትኞቹ መሆናቸውን ጊዜ በመውሰድና በታማኝነት መርምር። ጳውሎስ፡- *“እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን ራሳችሁን በአግባቡ መዝኑ እንጂ፣ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን እመክራለሁ።”* ሮሜ 12÷3 ብሏል። ዝርዝር አዘጋጅ። ቅን አስተያየታቸውን እንዲሰጡህ ሰዎችን ጠይቅ። እውነቱን ለማወቅ እንጂ፣ ሙገሳ ፍለጋ በመሯሯጥ ላይ አለመሆንህን ንገራቸው። መንፈሳዊ ስጦታዎችና የተፈጥሮ ችሎታዎች ሁል ጊዜ የሚረጋገጡት በሌሎች ነው። የአስተማሪነት ወይም የዘማሪነት ስጦታ እንዳለህ ብታስብና፣ በዚህ የሚስማማ ሌላ ሰው ባይኖር ምን እንደሚፈጠር ገምት። የመሪነት ስጦታ እንዳለህ ለማወቅ ከፈለግህ፣ ዞር በልና ከጀርባህ ተመልከት! የሚከተልህ ሰው ከሌለ መሪ አይደለህም።



እንዲህ በልና ጠይቅ። ሌሎች ያረጋገጡትና በሕይወቴ ያየሁት ፍሬ የትኛው ነው? ውጤታማ የሆንኩት በምንድነው? መንፈሳዊ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን ለመመርመር የተዘጋጁ መጠይቆች መጠነኛ ፋይዳ ሊኖራቸው ይችላል፤ ጠቀሜታቸው ግን ውሱን ነው። በመጀመሪያ እነዚህ ለሁሉም ሰው የተዘጋጁ ወጥ መመዘኛዎች ስለሆኑ፣ ያንተን ማንነት በሚገባ ያገናዘቡ አይሆኑም። ሁለተኛ፣ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተሰጠም፤ በመሆኑም ማንኛውም ትርጉም ጽኑ መሠረት የሌለውና፣ ቤተ እምነታዊ አመለካከት የሚንፀባረቅበት ነው። ሌላው ችግር፣ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ይበልጥ ባደግህ ቁጥር፣ ብዙ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ባሕርያት የሚታዩብህ ትሆናለህ። መንፈሳዊ ስጦታህ ስለሆነ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ብስለት ምክንያት ልታገለግል፣ ልታስተምር ወይም በደግነት ልትለግስ ትችላለህ።

መንፈሳዊ ስጦታዎችህንና ችሎታዎችህን ለይተህ ለማወቅ ከሁሉ የተሻለው መንገድ በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ መሞከር ነው። ወጣት በነበርኩ ጊዜ፣ መቶ የሚሆኑ ስጦታዎችና ችሎታዎችን ለመለየት የሚረዱ መጠይቆችን ሞክሬ ቢሆንም፣ አንድም ቀን አስተምሬ ስለማላውቅ፣ የማስተማር ስጦታ ያለኝ መሆኑን በፍጹም አልገነዘብም ነበር! የመናገር ወይም የማስተማር ዕድሎችን ተቀብዬ ማገልገል ከጀመርኩ በኋላ ነው ውጤቱን ያየሁት። ከሰዎች ማረጋገጫዎችን ያገኘሁት እና «ይህን እንዳደርግ ነው

እግዚአብሔር ስጦታን የሰጠኝ» ለማለት የቻልኩት።

ብዙ መጻሕፍት፣ ስጦታን የማወቅ ሂደትን ወደኋላ ያስኬዱታል። «መንፈሳዊ ስጦታህን እወቅ፤ ከዚያም አገልግሎትህ ምን ሊሆን እንደሚገባ ትረዳለህ» ይላሉ። ትክክለኛው አሠራር ግን ተቃራኒው ነው። በተለያዩ አገልግሎቶች እየተሣተፍህ አገልግሎትህን ጀምር፣ ከዚያ በኋላ ስጦታህን ታውቃለህ። በአገልግሎት መሳተፍ እስክትጀምር ድረስ ውጤታማነትህ በምን መሆኑን ለማወቅ አትችልም።

በተግባር ስላልሞከርካቸው፣ እንዳሉህ እንኳን ያላወቅሃቸው ብዙ ችሎታዎችና ስጦታዎች ውስጥህ ተደብቀዋል። ስለሆነም ከዚህ ቀደም ያልሠራህባቸውን ነገሮች እንድትሞክር አበረታታሃለሁ። ዕድሜህ የቱንም ያህል የገፋ ይሁን፣ መሞከርህን በፍፁም እንዳታቋርጥ አበረታታሃለሁ። የተደበቁ ችሎታዎችን በሰባና ሰማኒያ ዓመት ዕድሜያቸው ያገኙ ብዙ ሰዎች ገጥመውኛል። በዘጠና ዓመት ዕድሜዋ በአሥር ኪሎ ሜትር እሩጫ እየተወዳደረች የምታሸንፍ አንዲት ሴት አውቃለሁ። ይህን በሩጫ ደስተኛ የመሆን ችሎታዋን ሰባ ስምንት ዓመት እስኪሆናት ድረስ አላወቀችውም ነበር።

*እስካልሞከርከው ድረስ፣ ውጤት የምታመጣበት አገልግሎት የትኛው መሆኑን በፍጹም ለማወቅ አትችልም።*

አንድ አገልግሎት ውስጥ በፈቃደኝነት ከመሣተፍህ በፊት፣ ስጦታዎችህን ለማወቅ አትሞክር። ማገልገል ጀምር። በአገልግሎት በመሳተፍ ነው ስጦታዎችህን የምታውቃቸው። ለማስተማር፣ ለመምራት፣ ለማደራጀት፣ የሙዚቃ መሣሪያ ለመጫወት ወይም ከወጣቶች ጋር ለመሥራት ሞክር። እስካልሞከርከው ድረስ ውጤት የምታመጣበት አገልግሎት የትኛው መሆኑን ለማወቅ በፍፁም አትችልም። ውጤት ካጣህበት፣ «ሙከራ» እንጂ ውድቀት አትበለው። ውጤታማ የምትሆነው በየትኛው የአገልግሎት መስክ መሆኑን በመጨረሻ ትረዳለህ።

**ልብህንና ማንነትህን መርምር**። ጳውሎስ እንዲህ በማለት ምክር ለግሷል፦ *«እያንዳንዱ የራሱን ተግባር ይመርምር፤ ከዚያም በኋላ ከሌላ ሰው ጋር እራሱን ሳያወዳድር እራሱ የሚመካበትን ያገኛል»* ገላ. 6፥4። በጣም ከሚቀርቡህ ሰዎች አስተያየት ማግኘቱ ይጠቅማል። እንዲህ በልና እራስህን ጠይቅ፣ ስሠራው ከሁሉ በላይ የሚያስደስተኝ ነገር ምንድነው? በሕይወቴ ሙሉነት የሚሰማኝ መቼ ነው? ምን በማድረግ ላይ ስሆን ነው የጊዜው መሄድ እንኳን የማይታወቀኝ? የምወደው የተለመዱ ነገሮችን ነው ወይስ አዳዲሶችን? በቡድን ማገልገልን ነው የምመርጠው ወይስ ብቻዬን? ከሰዎች ጋር መሆንን ነው

ይበልጥ የምመርጠው ወይስ ብቻዬን? በአእምሮዬ ይበልጥ የምጠቀም ነኝ ወይስ በስሜቴ? ከመፎካከርና ከመተባበር የቱን ነው ይበልጥ የምወደው?

**ልምዶችህን መርምርና ከእነርሱ ውስጥ ያገኘሃቸውን ትምህርቶች ለይተህ አውጣ::** ሕይወትህን በመመርመር ልምምዶችህ እንዴት እንደቀረፁህ አስተውል:: ሙሴ እስራኤላውያንን እንዲህ አላቸው:- *«የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ተግሣጽ፣ ደሄውም ግርማውን፣ብርቱ እጁንና የተዘረጋች ክንዱን ያዩትና የተለማመዱት ልጆቻችሁ ሳይሆኑ እናንተ እንደሆናችሁ ዛሬ አስታውሱ»* ዘዳ 11÷2:: የተረሱ የሕይወት ልምዶች ጥቅም የላቸውም:: ለዚህ ነው የመንፈሳዊ ሕይወታችንን የየዕለት ዘገባ መያዝ የሚኖርብን:: ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ያለፉበትን መከራ ይረሳሉ ብሎ በመጨነቅ እንዲህ አላቸው :-*«በእርግጥ ለከንቱ ከሆነ፣ ይህን ያህል መከራ የተቀበላችሁት እንዲያው ነውን?»* ገላ. 3÷4::

በመከራ፣ በውድቀት ወይም ሀፍረት ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መልካም ዓላማ ብዙ ጊዜ አይታየንም:: ኢየሱስ የጴጥሮስን እግር ባጠበ ጊዜ እንዲህ አለ:- *«የማደርገውን አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስታውሳለህ»* ዮሐ. 13÷7:: እግዚአብሔር አንድን ችግር ለመልካም ያቀደው መሆኑን የምንገነዘበው፣ ችግሩ ካለፈ በኋላ ዘግይቶ ነው::

ከልምምዶች ውስጥ ትምህርት የሆኑትን ለይቶ ማውጣቱ ጊዜ ይወስዳል:: እግዚአብሔር በሕይወትህ የተለያዩ ጊዜያት የሠራቸውን ነገሮች ረጋ ብልና መርምር:: እነዚያን የሕይወት ትምህርቶች በምን ሁኔታ ሌሎችን ለመርዳትነት ሊገለገልባቸው እንደሚፈልግም እወቅ:: ይህን ለማድረግ በሳምንቱ መጨረሻ የእረፍት ቀንህ ወደ አንድ ገለልተኛ የእረፍት ሥፍራ በመሄድ፣ ***የሕይወት መገምገሚያ ጊዜ እንድታሳልፍ*** አሳብ አቀርብልሃለሁ:: ይህን ለማድረግ የሚረዱህ መረጃዎች አሉ:: በኢንተርኔት የመረጃ መረብ www.purposedrivenlife.Com. ውስጥ ተመልከት::

## መልክስልህን ተቀበለው፤ ደስም ተሰኝበት::

እግዚአብሔር የሚሻልህን ስለሚያውቅ፣ እርሱ አንተን የሚቀርጽበትን መንገድ በምሥጋና ተቀበል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ነገር ግን ለእግዚአብሔር መልስ የምትሰጥ አንተ ማነህ? ሥራ ሠሪውን፣ ለምን እንዲህ ሠራኸኝ? ይለዋልን? ሸክላ ሠሪ፣ ከሚሠራው ጭቃ፣ አንዱን ሸክላ ለክብር፣ ሌላውን ደግሞ ለተራ አገልግሎት የማድረግ መብት የለውምን?* » ሮሜ 9÷20-21::

አንተነትህ እግዚአብሔር በሉዓላዊ ዓላማው የሠራው ስለሆነ፤ ቅር ልትሰኝበት ወይም አልቀበልም ልትለው አይገባም:: እራስህን እንደ ሌላ ሰው ለመቅ

ሪጽ ከመሞከር ይልቅ፣ እግዚአብሔር ለአንተ ብቻ በሰጠህ አንተነት ደስተኛ መሆን አለብህ:- *«ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን ለእያንዳንዳችን ፀጋ ተሰጥ ቶናል» ኤፌ. 4÷7::*

**መልክስልህን** የመቀበል አንዱ ክፍል፣ ጉድለቶችህን መገንዘብ ነው:: በሁሉም ብቁ የሆነ ሰው የለም፤ ሁሉን እንዲሆን የተጠራም የለም:: ሁላች ንም ግልጥ የሆነ የአገልግሎት ድርሻ አለን:: ጳውሎስ ጥሪው ሁሉን ለመ ሥራት ወይም ሁሉን ለማስደሰት ሳይሆን፣ እንዲሠራው አስቦ እግዚአብ ሔር እሱን በቀረጸበት አገልግሎት ላይ ብቻ ማትኮር መሆኑን ተገንዝቦ ነበር፤ ገላ. 2÷7-8:: እንዲህ ብሏል:- *«እኛ ግን ከመጠን በላይ አንመካም፤ የምንመካው እግዚአብሔር በመደበልንና እስከ እናንተም እንኳ በሚደርሰው አገልግሎታችን ወሰን ነው»* 2ቆሮ. 10÷13::

*ወሰን* የሚለው ቃል፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን አንድ የአገልግሎት መስክ ወይም ክልል የሚሰጠን መሆኑን ያመለክታል:: **መልክስልህ** ልዩ ሞያህን ይወስነዋል:: ለሥራው ወስኖ እግዚአብሔር ከቀረጸን በላይ አገልግሎታችንን ልናሰፋው እንጨነቃለን:: አንድ ሯጭ የተሰመረ የመሮጫ ክልል እንደሚሰጠው ሁሉ፣ በግላችን:- *«በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ»* ዕብ. 12÷1:: ካንተ ለጥቆ አለው መሥመር ውስጥ ባለው እሯጭ አትቅና፤ እሩጫህን በመፈፀሙ ላይ ብቻ አትኩር::

በሰጠህ **መልክስል** በመጠቀም ደስተኛ እንድትሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እያንዳንዱ የራሱን ተግባር ይመርምር፣ ከዚያም በኋላ ከሌላ ሰው ጋር ራሱን ሳያወዳድር ስለ ራሱ የሚመካበትን ያገኛል»* ገላ. 6÷4:: ከማገልገልህ የተነሣ የምታገኘውን ደስታ ሰይጣን በሁለት ሁኔታዎች ሊሠርቅህ ይሞክራል:: እነሱም አገልግሎትህን ከሌሎች አገልግሎት ጋር እንድታወዳድር መፈተን እና፣ አገልግሎትህን ሰዎች ከሚጠብቁት ነገር ጋር እንድታስማማ መፈተን ናቸው:: ሁለቱም እግዚአብሔር ባቀደልህ መንገድ እንዳታገለግል አቅጣጫህን የሚያስቱና ለጉዳት የሚዳርጉ የጥፋት ወጥመዶች ናቸው:: በአ ገልግሎትህ ደስተኛ በማትሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ ምክንያቱን ለማወቅ ከነዚህ ፈተና ዎች አንዱ ይሆናል ብለህ በመመርመር ጀምር::

እራሳችንን በፍፁም ከሌሎች ጋር እንዳናነፃፅር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል:- *«እያንዳንዱ የራሱን ተግባር ይመርምር፤ ከዚያም በኋላ ከሌላ ሰው ጋር ራሱን ሳያወዳድር ስለራሱ የሚመካበትን ያገኛል»* ገላ. 6÷4:: **መልክስልህን**፣ አገልግሎትህን ወይም የአገልግሎትህን ውጤቶች ከማንም ጋር ማነፃፀር የማይኖርብህ ሁለት ምክንያቶች አሉ:: የመጀመሪያው፣ ሁልጊዜ

ከአንተ የተሻለ የሚሠራ የሚመስል ሰው ስለሚገጥምህ ተስፋ ትቆርጣለህ። ወይም ሁልጊዜ እንደ አንተ ውጤታማ የማይ መስል ሰው ስለሚገጥምህ በትዕቢት ትሞላለህ። ከእነዚህ አንዱ ከአገልግሎት ሊያወጣህና ደስታህን ሊሠርቅህ ይችላል።

*በስጦህ መልክስል በመጠቀም ደስተኛ እንድትሆን እግዚአ ብሔር ይፈልጋል።*

እራሳችንን ከሌሎች ጋር ማነፃፀሩ ሞኝነት መሆኑን ጳውሎስ እንዲህ በማለት ገልጧል:- «*እራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋር እራሳችንን ልንመድብ ወይም ልናነፃፅር አንደፍርም*» 2ቆሮ. 10÷12። መልእክቱ በአጭሩ ሲገለጥ:- «*በዚህ ሁሉ ማነፃፀር፣ ደረጃ መስጠትና ውድድር ዋናውን ነገር ይስታሉ*» 2ቆሮ. 10÷12 የሚል ነው።

ሠላሳ ሁለተኛ ቀን እግዚአብሔር በሰጠህ መጠቀም

የአገልግሎት መልክስልህን ባለመረዳታቸው የሚነቅፉህና ልትሠራው ይገባል ብለው ከሚያስቡት ነገር ጋር የምትስማማ ሊያደርጉህ የሚሞክሩ ሰዎች ይገጥሙሃል። ፊት አትስጣቸው። ጳውሎስ አገልግሎቱን ካልተረዱና ከሚነቅፉት ሰዎች ጋር ይጋጭ ነበር። ለነቃፊዎቹ ይሰጥ የነበረው አጸፋ ሁል ጊዜ ተመሳሳይ ነው፤ ማነፃፀርን አስወግድ፣ ማጋነንን ተቃወም፣ የእግዚአብሔ ርን ብድራት ፈልግ የሚል ነበር፣ 1ቆሮ. 10÷12-18።

ጳውሎስ እግዚአብሔር እንዲያ በታላቅ ሁኔታ የሚጠቀምበት ሰው ከሆነበት ምክንያቶች አንዱ፣ በነቀፋ፣ የራሱን ከሌላ ሰው አገልግሎት ጋር በማነፃፀር ወይም ፍሬ አልባ በሆነ ክርክር ውስጥ በመግባት አገልግሎቱ እንዲሰናከል ባለመፍቀዱ ነው። ጆን ባንያን የተባለ መንፈሳዊ ጸሐፊ እንዲህ ብሏል:- «ሕይወቴ ፍሬ አልባ ሆኖ፣ ማንም ቢያመሰግነኝ ግድ የለኝም፤ እንዲሁም ሕይወቴ ፍሬ አፍርቶ ማንም ቢነቅፈኝ ግድ የለኝም »።

## መልክስልህን ማሳደጉን ግፋበት

ኢየሱስ ስለ መክሊቶች የተናገረው ምሳሌ የሚያስገነዝበን፣ የተቻለንን ሁሉ እንድንሠራ እግዚአብሔር የሚጠብቅ መሆኑን ነው። ስጦታና እውቀታችንን፣ የልብ መነሣሣታችንን፣ የባሕርይ እድገታችንን እና ስብእናችንን ማሳደግ፣ እንዲሁም በአገልግሎታችን ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን ልምዳችንን ማስፋት ይኖርብናል። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ሰዎች እንዲህ ብሏቸዋል:- «*ፍቅራችሁ በጥልቅ እውቀትና በማስተዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ እጸልያለሁ*» ፊልጵ. 1÷9።

ጢሞቴዎስንም እንዲህ በማለት አስታውሶታል:- «*ስለዚህ በእጆቼ መጫን የተቀበልከውን፣ በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታቀጣጥል አሳስብሃለሁ*» 2ጢሞ. 1÷6::

ጡንቻዎችህን በእንቅስቃሴ ካላለማመድካቸው፣ ይደክሙና ይመነምናሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር የሰጠህን ችሎታና ሞያ በሥራ ላይ ካላዋልካቸው፣ ታጣቸዋለህ:: ይህን እውነት ለማጉላት ኢየሱስ የመክሊቶቹን ምሳሌ አስተማረ:: በተሰጠው አንድ መክሊት ያልሠራውን አገልጋይ አስመልክቶ ጌታው እንዲህ አለ:- «*በሉ እንግዲህ ታላንቱን ወስዳችሁ ዐሥር ታላንት ላለው ስጡ*» ማቴ. 25÷28:: በተሰጠህ ካልተጠቀምክበት ታጣዋለህ:: ባለህ ስጦታ ከተጠቀምክበት ግን እግዚአብሔር ይጨምርበታል:: ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲህ ብሎታል:- «*ሽማግሌዎች እጃቸውን በአንተ ላይ ሲጭኑ በትንቢት የተሰጠህን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል:: ... በትጋትም ፈጽማቸው*» 1ጢሞ. 4÷14-15::

ስጦታዎችህ ሁሉ በልምምድ ዓማካይነት ይሰፋሉ፣ ያድጋሉም:: ለምሳሌ ሙሉ በሙሉ ያደገ የማስተማር ስጦታን ማንም አያገኝም:: ነገር ግን በጥናት፣ በአስተያየት፣ እና ልምምድ «ጥሩ»፣ የተሻለ፣ ቀስ በቀስም የተዋጣለት አስተማሪ ወደመሆን ያድጋል:: በከፊል ባደገ ስጦታ አትቁም:: መርምርና የምትችለውን ሁሉ ተማር:: «*እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ፣ እራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ*» *2ጢሞ. 2÷15::* መልክስልህን ለማሳደግና የአገልግሎት ሞያህን የሰላ ለማድረግ በማናቸውም የሥልጠና ዕድል ተጠቀም::

መንግሥተ ሰማያት ውስጥ እግዚአብሔርን ለዘላለም እናገለግለዋለን:: በምድር ላይ በማገልገልም ለዘላለማዊው አገልግሎት ልንዘጋጅ እንችላለን:: ለኦሎምፒክ ውድድር እንደሚዘጋጅ አትሌት፣ ለታላቁ ቀን ልምምዳችንን እንቀጥላለን:: «*ለውድድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን ይገዛል:: እነርሱ አላፊ ጠፊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ይደክማሉ፤ እኛ ግን ለዘላለም የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንደክማለን::*» 1ቆሮ. 9÷25:: ለዘላለማዊ ኃላፊነቶችና ሽልማቶች በመዘጋጀት ላይ ነን::



# 33

# የእውነተኛ አገልጋዮች ፍሬ

*ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ*
*ሁሉ አገልጋይ ይሁን።*
ማር 10+43

*ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።*
ማቴ 7+16

እግዚአብሔርን የምናገለግለው ሌሎችን በማገልገል ነው።

ዓለም ታላቅነትን የምትገልጠው በኃይል፣ በሀብት፣ በክብርና በሥልጣን ነው። ሌሎች እንዲያገለግሉህ ለማዘዝ ከቻልክ ወደ ታላቅነት ደርሰሃል። "በመጀመሪያ እኔ" በሚል አስተሳሰብ በተሞላ እራስን የማገልገል ባህል ውስጥ አገልጋይ ሆኖ መታየቱ፣ ተወዳጅ አስተሳሰብ አይደለም።

ጌታ ኢየሱስ ግን፣ ታላቅነትን የሚለካው፣ በአገልግሎት እንጂ በኑሮ ደረጃ አይደለም። እግዚአብሔር ታላቅነትህን የሚለካው ምን ያህል ሰዎችን ታገለግላለህ በሚል እንጂ፣ ምን ያህል ሰዎች ያገለግሉሃል በሚል መለኪያ አይደለም። ይህ ከዓለም የታላቅነት መለኪያ ጋር በጣም የሚቃረን ከመሆኑ የተነሳ ለመረዳት፣ ይበልጡንም ደግሞ እውነቱን ለመለማመድ እጅግ አስቸጋሪ ይሆንብናል። ከሁሉ የላቀው ሥፍራ ከመካከላቸው ለማን መሰጠት አለበት በሚለው ጉዳይ ደቀ መዛሙርት ተከራክረው ነበር። አሁንም ከ2000 ዓመታት በኋላ፣ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን፣ በቤተ እምነቶችና በቤተክርስቲያን አጋዥ ድርጅቶች ውስጥ በላይኛው የአገልግሎት ሥልጣን ላይ ለመሆን ይሻኮታሉ።

በመሪነት ጉዳይ በሺ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ተጽፈዋል። በአገልጋይነት ላይ የተጻፉት ግን ጥቂት ናቸው። ሰው ሁሉ መሪነትን ይፈልጋል። ማንም ግን አገልጋይ ለመሆን አይሻም። ተራ ወታደር ከመሆን ይልቅ ጄነራል ለመሆን እንፈልጋለን። ክርስቲያኖች እንኳን *"አገልጋይ-መሪዎች"*

ለመሆን እንጂ፣ አገልጋዮች ብቻ ለመሆን አይፈልጉም:: እርሱን መምሰል ማለት ግን አገልጋይ መሆን ማለት ነው:: እርሱም እራሱን የጠራው አገልጋይ ብሎ ነው::

እግዚአብሔርን ለማገልገል መልክስልህን ማወቁ አስፈላጊ ነው፤ የአገልጋይ ልብ ያለህ መሆኑ ደግሞ ይበልጥ ያስፈልግሃል:: እግዚአብሔር የቀረጸህ ለአ ገልግሎት እንጂ፣ ለራስ ወዳድነት ያለ መሆኑን አስታውስ:: የአገልጋይ ልብ ከሌለህ፣ የተበጀህበትን ቅርጽ ለራስህ ጥቅም ያለ አግባብ ለማዋል ትፈተናለህ:: አንዳንድ ሥራዎችን ላለመፈጸም እንደ ምክንያት ትጠቀምበትም ይሆናል::

እግዚአብሔር አንዳንዴ *ባልተቀረጽንበት* መንገድ እንድናገለግለው በመጠየቅ ልባችንን ይፈትነዋል:: አንድ ሰው ጉድጓድ ውስጥ ወድቆ ብትመለከት፣ ሰውየውን እንድትረዳው እንጂ:- «ሰዎችን የመርዳትና ቸርነትን የማድረግ ስጦታ የለኝም» እንድትል እግዚአ ብሔር አይጠብቅም:: የአንድ ነገር ስጦታ ባይኖርህም፣ ያን ለመሥራት የተጠራው ሰው በአካባቢው ከሌለ፣ አንተ እንድትሠራው ተጠርተህ ይሆናል:: ቀዳሚው አገልግሎትህ በተቀ ረጽህበት አካባቢ ነው፤ ሁለተኛው አገልግሎትህ ግን በተፈለግህበት ጊዜና ቦታ የምታከናውነው ነው::

*መልክስልህ አገልግሎትህን፣ አገልጋይ ልብህ ግን እድገትህን ይገልጣል::*

**መልክስልህ** አገልግሎትህን፣ የአገልጋይ ልብህ ግን እድገትህን ይገልጣሉ:: አንድ ስብሰባ ሲያበቃ ወደ ኋላ ቀረት ብሎ፣ ቆሻሻ መልቀም እና ወንበሮችን ማስተካከል የተለየ ችሎታን አይጠይቅም:: በዚህ ጉዳይ ማንም አገልጋይ ሊሆን ይችላል:: የሚጠይቀው ቀና ባሕርይን ብቻ ነው::

አገልጋይ ሳይሆኑ፣ የሕይወት ዘመንን በሙሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ይቻላል:: የአገልጋይ ልብ ሲኖርህ ግን ይገባል:: አገልጋይ ልብ እንዳለህ በምን ታውቃለህ? ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- «*ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ቀፕቋጦ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?*» ማቴ 7÷16::

እውነተኛ አገልጋዮች እራሳቸውን ለአገልግሎት ያቀርባሉ:: አገልጋዮች አገልግሎታቸውን ውሱን በሚያደርጉ ነገሮች አያጨናንቁም:: በተጠሩ ጊዜ ወደ አገልግሎት ዘለው ለመግባት የተዘጋጁ ለመሆን ይፈልጋሉ:: አገልጋይ፣ ልክ እንደ ወታደር ለግዳጅ ዝግጁ ሆኖ መጠባበቅ ይኖርበታል:: «*በውትድርና የሚያገለግል ሰው አዛዡን ለማስደሰት ይጥራል እንጂ፣ በሌላ ሥራ ራሱን አያጠላልፍም::*» 2ኛ ጢሞ. 2÷4:: ነገሮች ሲመቻቹልህ ብቻ የምታገለግል ከሆንህ

እውነተኛ አገልጋይ አይደለህም፡፡ እውነተኛ አገልጋዮች በማይመች ሁኔታ ውስጥ እንኳን ተፈላጊውን ነገር ያደርጋሉ፡፡

እግዚአብሔር በሚፈልግህ ጊዜ ሁሉ ትገኛለህ? ያቀድከውን ነገር ቢያመሰቃቅልብህ አትበሳጭም? አገልጋይ እንደመሆንህ የምታገለግልበትን ጊዜና ቦታ ለመምረጥ አትችልም፡፡ አገልጋይ መሆን ማለት፣ እግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳህን እንዲቆጣጠረው ሙሉ መብት መስጠትና፣ በፈለገ ጊዜ ጣልቃ እንዲገባ መፍቀድ ማለት ነው፡፡

በየዕለቱ መጀመሪያ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆንህን ለራስህ ከነገርከው፣ ጣልቃ ገብ ነገሮች በጣም አያበሳጩህም፡፡ ምክንያቱም፣ ያንተ አጀንዳ እግዚአብሔር የሚያመጣውን ማንኛውንም ነገር መፈጸም ይሆናል፡፡ አገልጋዮች በየመሃሉ የሚመጡ ሥራዎች ሲገጥሟቸው፣ ከእግዚአብሔር የተሰጡ የአገልግሎት እድሎች እንደሆኑ በመቁጠር፣ አገልግሎቱን በመለማመድ ባገኙት ዕድል ለመጠቀም ደስተኞች ናቸው፡፡

**እውነተኛ አገልጋዮች ለሌሎች ፍላጐት ትኩረት ይሰጣሉ፡፡** አገልጋዮች ሁልጊዜ ሌሎችን የሚረዱበትን መንገድ ይፈልጋሉ፡፡ አገልግሎታቸውን የሚፈልግ ነገር ሲገጥማቸው፣ በማገልገል በእድሉ ይጠቀማሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡- *"ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ፡፡"* ገላ 3÷28፣ እንደሚለው ማድረግ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድን የተቸገረ ሰው ወደ አንተ ሲያመጣ፣ በአገልጋይነት አንድታድግ ዕድል መስጠቱ ነው፡፡ አስተውል፣ እርሱ የሚፈልገው፣ የቤተ ክርስቲያንህ አባላት ፍላጐት ቅድሚያ እንዲሰጠው እንጂ፣ «በምታከናውነው ሥራ ዝርዝር» መጨረሻ ላይ እንዲጻፍ አይደለም፡፡

ንቁ ስሜትና ዝግጁነት ስለሌለን፣ የምናገለግልባቸው አጋጣሚዎች ያመልጡናል፡፡ ትልልቅ የማገልገል ዕድሎች ብዙ አይቆዩም፡፡ በፍጥነት ያልፋሉ፤ እንዳንዴ ያን ሰው ልታገለግለው የምትችልበት ዕድል ሁለተኛ የማይገኝና አንድ ብቻ ሊሆን ስለሚችል በዕድሉ ተጠቀምበት፤ *"አሁን ልትረዳው ስትችል ነገ ተመለስ አትበለው"* ምሳሌ 3÷28፡፡



ጆን ዌስሊ እጅግ አስደናቂ የሆነ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር፡፡ የእርሱ መርህ፣ «በምትችለው ነገር ሁሉ፣ በምትችለው መንገድ ሁሉ፣ በምትችለው ቦታ ሁሉ፣ በምትችለው ጊዜ ሁሉ፣ ልታደርግላቸው ለሚቻልህ ሰዎች ሁሉ፣ የሚቻልህን መልካም ነገር ሁሉ አድርግ» የሚል ነበር፡፡ ይህ ነው ታላቅነት፡፡ ማንም ሊሠራ የማይፈልጋቸውን ትንንሽ ነገሮች በመሥራት ልትጀምር ትችላለህ፡፡ እነዚህን ትንንሽ

ነገሮች ልክ እንደታሳቅ ሥራ አከናውናቸው፤ እግዚአብሔር ይመለከታልና።

**እውነተኛ አገልጋዮች ባላቸው ነገር የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ።** አገልጋዮች ምክንያቶችን አይደረድሩም፤ ነገ ከነገ ወደያ አይሉም፣ ወይም የተሻለ ሁኔታ እስኪመጣ አይጠብቁም። መሥራት የሚገባቸውን በሙሉ ይሠራሉ እንጂ፣ "ከነዚህ ቀናት ባንዱ" ወይም "ጊዜው ሲስተካከል" አይሉም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ ***«ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም፤ ደመናትንም የሚያይ አያጭድም»*** መክ. 11፥4። እግዚአብሔር፣ የምትችለውን፣ ባለህ ነገር፣ ባለህበት ቦታ ሁሉ እንድትሠራ ይጠብቅብሃል። ተግባራዊ ካልሆነ እጅግ ድንቅ መጠነኛ አሳብ ይልቅ፣ በሥራ የሚገለጥ አገልግሎት ይሻላል።

ብዙ ሰዎች ከማያገለግሉበት ምክንያት አንዱ፣ ለአገልግሎት አንበቃም ብለው መፍራታቸው ነው። እግዚአብሔርን ማገልገል የሚገባቸው ታዋቂ ሰዎች ብቻ ናቸው የሚለውን ውሸት አምነዋል። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያን «ፍፁምነት» የተባለን ነገር እንደ ጣዖት አድርገው ማቅረባቸው፣ መካከለኛ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ወደ አገልግሎት ከመግባት እንዲያመነቱ ያደርጋቸዋል።

«እጅግ የተዋጣለት ሆኖ የማይሠራ ከሆነ፣ አትሥራው» ሲባል፣ ምናልባት ሰምተህ ይሆናል። ኢየሱስ ግን እንዲያ አላለም! የምንሠራው ነገር ሁሉ ስንጀምረው በጥሩ ሁኔታ አይሠራም፤ ይበላሽ ይሆናል። እንዲህ እንዲህ እያልን ነው የምንማረው። እኔ በማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን "ጥሩ" የሚል መርህ አለን። አንድ ነገር እግዚአብሔር እንዲጠቀምበትና እንዲባርከው ሲባል ፍጹም መሆን የለበትም። በጥቂት ምሁራን የሚመራና ፍጹም የሆነ ቤተክርስቲያን ከሚኖረን ይልቅ፣ በሺ የሚቆጠሩ ተራ ሰዎችን በአገልግሎት ብናሳትፋቸው ይሻላል።

**እውነተኛ አገልጋዮች ሥራቸውን ሁሉ እኩል በሆነ መሰጠት ያከናውናሉ።** አገልጋዮች የሚሠሩትን ሁሉ፣ « *በሙሉ ልባችሁ አድርጉት!*» ቆላ 3፥23 ተብለዋል። ከዚህ ጋር የተዛመደው፣ ዋና ቁም ነገር፣ የሥራው ትልቅነት ሳይሆን፣ ሥራው መሠራት አለበት ወይ? የሚለው ነው።

እጅግ ከፍተኛና ጠቃሚ ሰው ከሚያደርግህ የሕይወት ደረጃ ላይ ትደርስ ይሆናል፤ እንዲያ መሆኑ ግን ዝቅተኛ የሆነን ሥራ ከመሥራት በፍፁም አያግድህም። እግዚአብሔር ከተራ ሥራ ፈጽሞ ነፃ አያረግህም። ይህም ባህርይህን ማስተካከያ በሆነው ትምህርት ውስጥ ዋናው ክፍል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *"አንድ ሰው ምንም ሳይሆን ትልቅ የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላል።"* ገላ 6፥3። ክርስቶስን ወደ መምሰል የምናድገው፣ እንዲህ ባሉ

ታናናሽ አገልግሎቶች ዓማካይነት ነው።

ኢየሱስ ትኩረት የሰጠው፣ ሰዎች ለማይፈልጓቸው ሥራዎች ነበር፤ እግር ማጠብ፣ ልጆችን መርዳት፣ ቁርስ ማዘጋጀት፣ አካል ጉዳተኞችን ማገልገል ለመሳሰሉት። የመጣው ለማገልገል በመሆኑ፣ ለእርሱ ዝቅተኛ የሆነ ነገር አልነበረም። ይህን ያደረገው፣ ታላቅነቱን በመተው ሳይሆን፣ በታላቅነቱ ምክንያት ነው። በመሆኑም የእርሱን ፈለግ እንድንከተል ይጠበቅብናል፤ ዮሐ 13፥15።

ዝቅተኛ ሥራዎችን መሥራት ብዙውን ጊዜ የልብ ትልቅነትን ያመለክታል። አገልጋይ ልብህ ሌሎች ያላሰቡትን ታናሽ ሥራ በመሥራት ይገለጣል። ታንኳቸው ተሰባብሮ ከባህር ውስጥ ሲወጡ፣ ጳውሎስ የማገዶ እንጨት ሰብስቦ ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች እሳት እንዲሞቁ እንዳደረገው ማለት ነው፤ የሐ ሥራ 28፥3። እሱም ልክ እንደ ሌሎቹ ሰውነቱ እስኪዝል ቢደክምም፣ ለሁሉም አስፈላጊ የሆነ ነገርን አደረገ። አገልጋይ ልብ ሲኖርህ የትኛውም ሥራ ላንተ የተናቀ አይሆንም።

ታላላቅ ዕድሎች ብዙ ጊዜ ታናናሽ ሥራዎች ውስጥ ይደበቃሉ። በሕይወት ውስጥ ትልልቆቹን ነገሮች የሚወስኑት ትንንሽ ነገሮች ናቸው። ለእግዚአብሔር ትልልቅ ሥራዎችን ለመሥራት አትፈልግ። እምብዛም ታላቅ ያልሆኑ ሥራዎችን ሥራ። እግዚአብሔርም እንድትሠራ ለሚፈልገው ሥራ ይሾምሃል። በመሆኑም ታላቅ የሆነን ሥራ ለመሥራት ከመሞከርህ በፊት ተራ በሆነው ሥራ አገልግል፤ ሉቃስ 16፥10-12።

ለእግዚአብሔር ትንንሽ ነገሮችን ከመሥራት ይልቅ፣ ታላላቅ ነገሮችን መሥራት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ።

> *ታላላቅ ዕድሎች ብዙ ጊዜ ታናናሽ ሥራዎች ውስጥ ይደበቃሉ።*


መሪ ለመሆን የሚደረገው ፉክክር የተጨናነቀ ነው። አገልጋዮች ለመሆን ለሚፈልጉ ግን ሜዳው በሰፊው ተንጣሏል። አንዳንድ ጊዜ ወደ ላይ ባለሥልጣናትን ታገለግላለህ። አንዳንዴ ደግሞ ወደ ታች ችግረኞችን ታገለግላለህ። በየትኛውም አቅጣጫ ይሁን፣ የሚፈለገውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ ስትሆን የአገልጋይ ልብ ታዳብራለህ።

እውነተኛ አገልጋዮች ለአገልግሎታቸው ታማኞች ናቸው። አገልጋዮች ተግባራቸውን ያከናውናሉ፣ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፣ ቃል ኪዳናቸውን ይጠብቃሉ፣ እናም የገቡትን ቃል ይፈጽማሉ። አንድን ሥራ በግማሹ አያቆሙትም፤ ተስፋ በቆረጡ ጊዜም ሥራቸውን አያቋርጡም። ሌሎች የሚተ

ማመኑባቸውና የሚመኩባቸው ናቸው።

ታማኝነት ብዙም የማይገኝ ነገር ነው! መዝ. 12÷1። ብዙ ሰዎች እራስን ለአገልግሎት የመስጠትን ትርጉም አያውቁትም። ድንገት ቃል ይገቡና በማይ ረባ ምክንያት ያለ ምንም ማመንታት፣ ጸጸት ወይም ይቅርታ ቃላቸውን ያጥ ፋሉ። በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ ሰዎች ዝግጁዎች ካለመሆናቸው የተነሣ፣ ወይም ደውለው እንኳን መቅረታቸውን ባለመናገራቸው ሳቢያ ቤተክርስቲያንና ሌሎች ድርጅቶችም፣ በየሳምንቱ የሚፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ማስተካ ከያ ማድረግ ግድ ይሆንባቸዋል።

ሌሎች የሚተማመኑብህ ለመሆን ትችላለህን? ልትጠብቃቸው የሚገቡ ቃል ኪዳኖች፣ መፈጸም የሚኖርብህ ስዕለቶች፣ ወይም ልታከብራቸው የሚገቡ ግዴታዎች አሉ? ይህ ፈተና ነው። እግዚአብሔር ታማኝነትህን በመፈተን ላይ ነው። ይህን ፈተና ካለፍክ፣ ጥሩ ቡድን ውስጥ ነው ያለኸው። አ



ብርሃም፣ ሙሴ፣ ሳሙኤል፣ ዳዊት፣ ዳንኤል፣ ጢሞቴዎስ እና ጳውሎስ ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ተብለዋል። ከዚህም ይልቅ እግዚአብሔር ለታማኝነትህ በዘላለም መንግሥቱ ሊሸልምህ ቃል ገብቷል። አንድ ቀን ጌታ:- *"ደግ አድርገሃል፣ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፣ በትንሽ ነገር ላይ ታማኝ ስለሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፣ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ ።"* ማቴ. 25÷23 ቢልህ ምን እንደሚሰማህ አስቲ ገምት።

በነገራችን ላይ ታማኝ አገልጋዮች በፍጹም ጡረታአይወጡም። በሕይወት እስካሉ ድረስ በታማኝነት ያገለግላሉ። ከሥራህ ጡረታ ልትወጣ ትችላለህ። እግዚአብሔርን ከማገልገል ግን በፍጹም ጡረታ አትወጣም።

እውነተኛ አገልጋዮች የሰዎችን ትኩረት አይፈልጉም። አገልጋዮች እራሳ ቸውን አያስተዋውቁም፣ ወይም እዩኝ እዩኝ አይሉም። ሰዎችን ለመሳብ ከመጣርና የስኬታማነት ሸማ ለብሶ ከመታየት ይልቅ *"ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትህትናን ልበሱ"* 1ጴጥ 5÷5፣ በሚለው የሕይወት መርህ ይመላለሳሉ። በአገልግሎታቸው ምክንያት ዕውቅና ቢያገኙ በትህትና ይቀበሉታል። መጥፎ ዝና ከሥራቸው እንዲያደናቅፋቸው ግን አይፈቅዱም።

ጳውሎስ መንፈሳዊ የሚመስል፣ ነገር ግን ማስመሰል የነበረ፣ የታይታ የሆነና ትኩረትን ለመሳብ የተደረገን አንድ አገልግሎት አጋልጧል። እርሱም የታይታ አገልግሎት ብሎታል ኤፌ 6÷6 ። እንዲህ ያለው ድርጊት መንፈ ሳዊነታችንን በማሳየት የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ የምንሰጠው አገልግሎት ነው። ይህ ነበር የፈሪሳውያን ኃጢአት። ሌሎችን መርዳትን፣ ስጦታን፣

እንዲሁም ጸሎትን እንኳ ሳይቀር በሌሎች ሰዎች ለመታየት ሲባል ወደሚከናወን ተግባርነት ለወጡት:: ኢየሱስ ይህን አስተሳሰብ ስለጠላው እንዲህ በማለት አስጠንቅቋል:- *"ሰዎች እንዲያዩአችሁ፣ መልካም ሥራችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠንቀቁ፤ እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ አባታችሁ ዋጋ አታገኙም"* ማቴ. 6÷1::

ራስን ከፍ ከፍ ማድረግና አገልጋይነት አይጣመሩም:: እውነተኛ አገልጋዮች ለሌሎች አድናቆት ወይም ሙገሳ ሲሉ አያገለግሉም:: የሚኖሩት ለአንዱ ተመልካች ለእግዚአብሔር ነው:: ጳውሎስ:- *"ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የምጥር ብሆን ኖሮ፣ የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንሁ ነበር"* ገላ. 1÷10 ብሏል::

ብዙ እውነተኛ አገልጋዮችን ደማቅ ብርሃን ባለው መድረክ ላይ አታገኟቸውም፤ በተቻላቸው መጠን ይርቁታል:: ሰዋራ ስፍራ በፀጥታ በማገልገል ነው የሚረኩት:: ዮሴፍ ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ነው:: የሰዎችን ትኩረት ወደ ራሱ ሳይስብ በዝምታ ጲጥፋራን፣ የአሠሩትን ሰዎች፣ የፈርኦንን ምግብና ወይን ቀማሾች በዝምታ አገለገለ:: እግዚአብሔርም ያን አስተሳሰብ ባረከው:: ፈርኦን ታላቅ ሹመት በሾመው ጊዜም የአገልጋይ ልብ ነበረው፤ ለሸጡት ወንድሞቹ እንኳን ይህ ልብ ነበረው::

የሚያሳዝነው ነገር፣ ዛሬ ብዙ መሪዎች እንደአገልጋይ ይጀምሩና ባለ ዝና ይሆናሉ:: ያኔ ታዲያ ኃይለኛ የመድረክ መብራት ፊት መሆን ለእውርነት የሚዳርጋቸው መሆኑን ባለመረዳት፣ ትኩረት የመሳብ ሱስ ያድርባቸዋል::

ታዋቂ ወይም ተደናቂ ሳትሆን፣ ድንግዝግዝ ባለ ትንሽ ሥፍራ በማገልገል ላይ ትሆን ይሆናል:: አድምጠኝ! እግዚአብሔር ነው ባለህበት ቦታ ለአንድ ዓላማ ያስቀመጠህ! የራስህን ፀጉሮች በሙሉ ቆጥሯቸዋል፤ በመሆኑም ያለህበትን ያውቀዋል:: ካለህበት ሊያዛውርህ እስኪመርጥ ድረስ እዚያው ብትቆይ ይሻልሃል:: ለሌላ ቦታ ሲፈልግህ ይህንኑ እንድታውቀው ያደርጋል:: አገልግሎትህ ለእግዚአብሔር መንግሥት አስፈላጊ ነው:: *"ሕይወታችሁ የሆነው ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እናንተም በዚያን ጊዜ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ"* ቆላ 3÷4::

ሠላሳ ሦስተኛ ቀን

የእውነተኛ አገልጋዮች ፍሬ

አሜሪካ ውስጥ ከ750 የሚበልጡ «የዝና አዳራሾች» እና ከ450 የሚበልጡና «እነማን ነበሩ?» የሚሉ ህትመቶች አሉ:: ነገር ግን ብዙ እውነተኛ አገልጋዮችን በነዚህ ቦታዎች አታገኙአቸውም:: የስማቸው መጠራትና አለመጠራት ለእውነተኛ አገልጋዮች ምናቸውም አይደለም፤ ምክንያቱም በጠቃሚነትና በታዋቂነት መካከል ያለውን ልዩነት ያውቁታል:: ባይኖሩ ምንም የማይጐዱህ፣ ግን ጎልተው የሚታዩ የአካልህ ክፍሎች አሉህ:: ምትክ የሌላቸው

የአካል ክፍሎችህ ግን ድብቆቹ ናቸው:: የክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያን) ውስጥም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: እጅግ ጠቃሚው አገልግሎት በአብዛኛው የማይታየው ነው 1ቆሮ 12÷22-24::

እግዚአብሔር በምድር አገልግሎታቸው በፍጹም ያልታዩና ያልታወቁትን በመንግሥተ ሰማያት ወደ ፊት ይሸልማል:: እነዚህም ሰዎች ስለ እነርሱ በምድር ምንም ያልተሰማ፣ የአእምሮ ህመምተኛ ህፃናትን ያስተማሩ፤ በዕድሜ እጅግ የገፉ አዛውንትና ባልቴቶችን ሲንከባከቡ የኖሩ፣ የኤድስ በሽተኞችን ያስታመሙ፣ እንዲሁም በማይታዩና በሺዎች በሚቆጠሩ ሌሎች መንገዶች ያገለገሉ ናቸው::

ይህን በመረዳት፣ አገልግሎትህ ልብ ባይባል ወይም ጠቃሚ ሆኖ ባይቆጠር ተስፋ አትቁረጥ:: እግዚአብሔርን በማገልገሉ ተግባር ግፋበት! *«ስለዚህ የተወደ ዳችሁ ወንድሞች ሆይ፣ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በምንም ነገር አትናወጡ:: ስጌታ ሥራ ዘወ ትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ስጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላ ችሁ::» 1ቆሮ.* 15÷58:: ከሁሉ ታናሽ የሆነውን አገልግሎት እንኳን እግዚአብ ሔር ይመለከታል፣ ይሸልማልም:: ይህን የጌታ ኢየሱስ ቃል አስታውስ:- *"ስለዚህ እውነት እላችኋለሁ፣ ማንም ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች ለአንዱ ደቀ መዝሙረ በመሆኑ አንድ ጽዋ ቀዝቃዛ ውሃ ቢሰጠው ዋጋውን አያጣም::"* ማቴ. 10÷42::

ሠላሳ ሦስተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** ሌሎችን በማገልገል እግዚአብሔርን አገለግላለሁ::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *"ስለዚህ እውነት እላችኋለሁ፣ ማንም ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች ለአንዱ ደቀ መዝሙረ በመሆኑ አንድ ጽዋ ቀዝቃዛ ውሃ ቢሰጠው ዋጋውን አያጣም::"* ማቴ. 10÷42::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** የእውነተኛ አገልጋዮች ባህርያት ተብለው ከተጠቀሱት ስድስት ነገሮች ትልቅ ተግዳሮት የሆነብኝ የትኛው ነው?

# 34

# እንደ አገልጋይ ማሰብ

*አገልጋዩ ካሌብ ግን የተለየ መንፈስ ስላለውና በፍጹም ልቡ*
*የተከተለኝ በመሆኑ ሄዶባት ወደ ነበረችው ምድር*
*አስገባዋለሁ ዘሮቹም ይወርሷታል::*

**ዘኁ. 14÷24**

*በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ*
*በእናንተም ዘንድ ይሁን::*

**ፊልጵ 2÷5**

አገልግሎት የሚጀምረው አእምሮህ ውስጥ ነው::

አገልጋይ መሆን የአእምሮ፣ ማለትም የአመለካከት ለውጥን ይጠይቃል:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይበልጥ የሚያተኩረው፣ በምንሠራው ነገር ምንነት ላይ ሳይሆን፣ ሥራውን በምንሠራበት ምክንያት ላይ ነው:: አስተሳሰቦች ከውጤቶች ይበልጥ ዋጋ አላቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ንጉሥ አሜሲያስ የእግዚአሔርን ሞገስ ያጣበትን ምክንያት ሲገልጥ:- *«እርሱም በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነገር አደረገ፤ ነገር ግን በፍጹም ልቡ አልነበረም::»* 2ዜና. 25÷2 ይላልዕዕ እውነተኛ አገልጋዮች አምስት የአስተሳሰብ አቅጣጫዎች ባሉት የአእምሮ ዝግጅት እግዚአብሔርን ያገለግሉታል::

አገልጋዮች ከራሳቸው ይልቅ ስለ ሌሎች ያስባሉ:: የአገልጋዮች ትኩረት እራሳቸው ላይ ሳይሆን፣ ሌሎች ላይ ነው:: እውነተኛ ትህትና ማለት ራስን ዝቅ አድርጐ መመልከት ሳይሆን፣ ስለ ራሳችን ብዙ አለማሰብ ነው:: እንዲህ ያሉ አገልጋዮች እራሳቸውን የሚረሱ ናቸው:: ጳውሎስ *"እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ::"* ብሏል ፊልጵ. 2÷4:: ይህ ነው «ሕይወትን አሳልፎ መስጠት» ማለት! ሌሎችን ለማገልገል እራስህን መርሳት:: በፍላጐቶቻችን ላይ ማትኮራችንን ስናቆም፣ በዙሪያችን ያሉ ፍላጐቶችን የምንገነዘብ እንሆናለን::

ኢየሱስ:- «... የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም ምሳሌ ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደ ረገ::» ፊልጵ. 2+7:: ለሌላ ሰው ጥቅም ስትል እራስህን ባዶ ያደረግክበት የመጨረሻ ጊዜ መቼ ነበር? በአንተነትህ የተሞላህ ከሆንክ አገልጋይ ለመሆን አትችልም:: እራሳችንን ስንረሳ ብቻ ነው፤ ሊታወሱ የሚገባቸው ተግባራትን የምናከናውነው::

ምን ያደርጋል ታዲያ፣ ብዙዎቹ አገልግሎቶቻችን እራስን ማገልገል ናቸው:: የምናገለግለው፣ ሰዎች እንዲወዱን፣ ለመደነቅ፣ ወይም ዓላማችንን ለማሳካት ነው:: ይህ መደለል ወይም ማታለል እንጂ፣ አገልግሎት አይደ ለም:: እንዲህ የምናደርግ ከሆንን፣ ሁልጊዜ የምናስበው የቱን ያህል ታዋ ቂና ተደናቂ መሆናችንን ነው:: አንዳንድ ሰዎች አገልግሎትን ከእግዚአብሔር ጋር እንደመደራደሪያ መሣሪያነት ሊጠቀሙበት በመሞከር:- «እግዚአብሔር ሆይ! አንድ ነገር ካደረክልኝ ይህን አደርግልሃለሁ» ይላሉ:: እውነተኛ አገልጋዮች እግዚአብሔርን ለራሳቸው ዓላማ ሊጠቀሙበት አይሞክሩም:: እርሱ *ለዓላማው* እንዲገለገልባቸው ይፈቅዳሉ::

እራስን የመርሳት ብቃት እንደ ታማኝነት ሁሉ እጅግ ብርቅ ነገር ነው:: ጳውሎስ ከሚያውቃቸው ሰዎች ሁሉ እንደ መልካም ምሳሌ ሊያመለክተው የቻ ለው፣ ጢሞቴዎስን ብቻ ነበር፣ ፊልጵ. 2+20:: የሕይወቴን መሠረታዊ ችግር ስለሚገዳደረው፣ እራሴን እንደ አገልጋይ አድርጌ ማሰቡ ያስቸግረኛል፤ ምክንያቱም በተፈጥሮዬ እራስ ወዳድ ነኝ:: በጣም የማስበው ስለራሴ ነው:: ለዚህ ነው፣ ትህትና ዕለታዊ ትግሌና በተደጋጋሚ ልማ ረው የሚገባ ትምህርት የሚሆንብኝ:: የራሴን ወይም የሌሎችን ፍላጎት የማገል ገሉ ምርጫ በተሰጠኝ ጊዜ ሁሉ፤ አገልጋይ የመሆን ዕድል በየዕለቱ በተደጋጋሚ እፊቴ ይደቀናል:: እራስን መካድ የአገልጋይነት ዋና ነገር ነው::

*እውነተኛ አገልጋዮች እግዚአ ብሔርን ለራሳቸው ዓላማ ሊጠቀሙበት አይሞክሩም:: እርሱ ለዓላማው እንዲገለ ገልባቸው ይፈቅዳሉ::*

አገልጋይ ልባችንን ለመለካት የምንችለው፣ ሰዎች እንደ አገልጋይ በሚቆጥ ሩን ጊዜ በምናሳየው አፀፋ ነው:: ችላ ስትባል፣ ሁሉ አዛዥህ ሲሆን ወይም እንደ ዝቅተኛ ሰው ስትቆጠር፣ ምንድነው የምታደርገው? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«አንድ ሰው አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል የሚያህል ርቀት እንድትሄድ ቢያስገድድህ አጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ»* ማቴ. 5+41::

አገልጋዮች እንደ ባለ አደራ እንጂ፣ እንደ ባለቤት አያስቡም:: የሁሉም

ነገር ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን አገልጋዮች ያስታውሳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጠው ባለአደራ፣ ንብረት እንዲያስተዳድር የተሰጠው አገልጋይ ነው። ዮሴፍ ግብጽ ውስጥ እስረኛ በነበረ ጊዜ እንዲህ ያለ አገልጋይ ነበር። ጲጥፋራ ቤቱን በሙሉ በአደራ ሰጠው። ከዚያም የወኅኒ ቤቱ ኃላፊ ወኅኒውን ሰጠው። በመጨረሻም ፈርኦን አገሩን በሙሉ ሰጠው። በሁሉም ታማኞች እንድንሆን እግዚአብሔር ስለሚፈልግ፣ አገልጋይነትና ባለአደራነት 1ቆሮ. 4÷1፣ አይነጣጠሉም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ባለአደራዎች ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው*» 1ቆሮ. 4÷2። እግዚአብሔር የሰጠህን ሀብት እንዴት ነው የምታስተዳድረው?

እውነተኛ አገልጋይ ለመሆን፣ ገንዘብ ከሕይወትህ ጋር ባለው የግንኙነት ጉዳይ ላይ መወሰን ይኖርብሃል። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- «*በአንድ ጊዜ ሁለት ጌቶችን ማገልገል የሚችል ማንም ባሪያ የለም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፣ ወይም አንዱን ይጠጋል፣ ሌላውን ይንቃል። የእግዚአብሔርም የገንዘብም ባሪያ መሆን አትችሉም*» ሉቃስ 16÷13። «*የለብህም*» ሳይሆን «*አትችልም*» ነው ያለው። የማይቻል ነገር ነው። ለአገልግሎት መኖርና ለገንዘብ መኖር የተለያዩና የማይገናኙ ግቦች ናቸው። የትኛውን ነው የምትመርጠው? የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንክ፣ የራስህ ለመሆን አትችልም። ጊዜህ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ሙሉውን እንጂ፣ የትርፍ ጊዜ ታማኝነትን አይደለም እግዚአብሔር የሚፈልገው።

ገንዘብ በሕይወትህ እግዚአብሔርን የመተካት ከፍተኛ ኃይል አለው። ብዙ ሰዎች፣ ከአገልግሎት መንገድ የሚወጡት ከሌላ ነገር ይልቅ በቁሳቁስ ወይም በገንዘብ ምክንያት ነው። «ገንዘብ የማጠራቀም ዓላማዬን ካሳካሁ በኋላ እግዚአብሔርን አገለግለዋለሁ » ይላሉ። ይህ ለዘላለም የሚፀፀቱበትና ጥበብ የጎደለው ውሣኔ ነው። ኢየሱስ ጌታህ ሲሆን፣ ገንዘብ ያገለግልሃል፤ ገንዘብ ጌታህ ከሆነ ግን፣ ባሪያው ትሆናለህ። ብልጽግና ኃጢአት አይደለም። ብልጽግናን ለእግዚአብሔር ክብር አለማዋል ግን ኃጢአት ነው። የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ይበልጥና ሁል ጊዜ የሚያሳስባቸው ከገንዘብ ይልቅ አገልግሎት ነው።

እግዚአብሔር ገንዘብን የአገልጋይን ታማኝነት ለመፈተኛነት የሚጠቀምበት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያስገነዝባል። ለዚህ ነው ኢየሱስ ከመንግሥተ ሰማያትና ከሲኦል ይበልጥ ስለ ገንዘብ የተናገረው። እንዲህ ብሏል:- «*እንግዲህ በዓለም ሀብት ካልታመናችሁ፣ እውነተኛውንማ ሀብት ማን አደራ ብሎ ይሰጣችኋል?*» ሉቃስ 16÷11። ገንዘብህን የምታስተዳድርበት ሁኔታ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን የበረከት መጠን ይወስነዋል።

ምዕራፍ 31 ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎችን፣ ማለት የእግዚአብሔርን መን ግሥት ገንቢዎችንና ሀብት ገንቢዎችን ጠቅሻለሁ:: ሁለቱም አንድን ሥራ የማሳደግ፤ የመዋዋል ወይም የመሸጥ፣ እንዲሁም የማትረፍ ስጦታ አላቸው:: ሀብት ገንቢዎች የቱንም ያህል ያጠራቅሙ፣ ሀብት ማግበስበሱን ይገፉበታል:: የእግዚአብሔርን መንግሥት ገንቢዎች ግን ተቃራኒውን ነው የሚያደርጉት:: ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ይጥራሉ:: ያን የሚያደርጉት ግን፣ ለሌሎች ለመስጠት ነው:: ሀብታቸውን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያንና በዓለም ውስጥ ያላትን ተልእኮ ለመርዳት ያውሉታል::

ሳድል ባክ በተባለችው አጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ውስጥ፣ ካሉት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ሥራ የአቅማቸውን ለመስጠት ይችሉ ዘንድ፣ በተቻላቸው መጠን ብዙ ሀብት ለማፍራት የሚጥሩ ባለ ሀብ ቶች አሉ:: ከቤተክርስቲያንህ መሪዎችና ከመጋቢህ ጋር በመወያየት ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ገንቢ ቡድን ማቋቋም እንድ ትጀምር አበረታታሃለሁ::

**አገልጋዮች ስለ ራሳቸው ሥራ እንጂ ስለ ሌሎች ሥራ አያስቡም::** ከሌ ሎች አገልጋዮች ወይም አገልግሎቶች ጋር ራሳቸውን አያነፃፅሩም፣ አይነቅፉም ወይም አይወዳደሩም:: እግዚአብሔር በሰጣቸው ሥራ በጣም ስለሚረኩ ለነ ዚህ ነገሮች ጊዜ የላቸውም::

**ሰላሳ ሦስተኛ ቀን**
**እንደ**
**አገልጋይ**
**ማሰብ**

በእግዚአብሔር አገልጋዮች መካከል የሚደረግ ፉክ ክር በብዙ ምክንያት ተገቢ አይደለም:: ሁላችንም አንድ አገልግሎት ውስጥ ነን፣ ዓላማችን የራሳችንን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን መልካምነት ማሳየት ነው:: የተለያዩ አገልግሎቶች ተሰጥተውናል፤ ሁላችንም በልዩ ሁኔታ ተቀርፀናል:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «*እርስ በርሳችን እየተነነታተልንና እየተቀናናን በከንቱ ውዳሴ አንመካ*» ገላ. 5÷26::

የማይረባ ምቀኝነት በአገልጋዮች መካከል ሥፍራ የለውም:: በአገልግሎት ስትጠመድ፣ ነቃፊ ለመሆን ጊዜ አይኖርህም:: ሌሎችን ለመንቀፊያነት የሚጠፋ ጊዜ ሁሉ ለማገልገያነት ሊውል ይችል የነበረ ነው:: ማርታ፣ ማርያም ሥራ እንደማታግዛት ለኢየሱስ በወቀሰቻት ጊዜ የአገልጋይ ልቧ ተለይቷት ነበር:: እውነተኛ አገልጋዮች ትክክል ባልሆነ ነገር ምክንያት አይማ ረሩም፣ የአዛኝ ቅቤ አንጓች አይነት ባህርይ የላቸውም፣ በማያገለግሉ ሰዎችም አይቆጡም:: እግዚአብሔርን በመተማመን ዝም ብለው አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ::


ሌላውን የጌታ አገልጋይ መመዘኑ የኛ ሥራ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ

እንዲህ ይላል፡- «*ሌላውን በሚያገለግል ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ? እርሱ ቢወድቅ ወይም ቢቆም ለጌታው ነው፤ ጌታ ሊያቆመው ስለሚችልም ይቆማል*» ሮሜ 14÷4:: ለሌሎች ነቀፋና፣ ለራሳችን ጥብቅና መቆሙም የኛ ሥራ አይደለም:: ለጌታህ ተወው:: ተቃውሞ በገጠመው ጊዜ እውነተኛ ትህትና ያሳየው ሙሴን እና፣ ለተቃዋሚዎቹ፡- «*እኔም ታላቅ ሥራ እየሠራሁ ስለሆነ፣ ወዳላችሁበት ሥፍራ መውረድ አልችልም:: ትቼው ወደ እናንተ ወርጄ ሥራው ለምን ይቆማል?*» ነህ. 6÷32፣ በማለት የመለሰውን የነህምያን ምሳሌ ተከተል::

እንደ ኢየሱስ የምታገለግል ከሆንክ፣ የነቀፋን አይቀሬነት ጠብቅ:: ዓለም፣ የቤተክርስቲያን አብዛኛው ሕዝብ እንኳን ሳይቀር፣ እግዚአብሔር ዋጋ የሚሰጠው ነገር ምን መሆኑ አይገባቸውም:: ለኢየሱስ የተገለጠውና ከፍቅር መልካም ሥራዎች አንዱ የሆነው ድርጊት፣ በደቀ መዛሙርት ተነቅፏል:: ማርያም ያላትን እጅግ ብዙ ዋጋ የሚያወጣ ውድ ሽቶ ይዛ በመሄድ ኢየሱስ ላይ አፈሰሰችው:: ይህ ውድ የሆነ አገልግሎቷ በደቀመዛሙርቱ «ጥፋት» ተብሏል:: ኢየሱስ ግን ድርጊቷን «መልካም» አለው፤ ያ ነው ዋናው ነገር:: ሌሎች ምንም ይበሉ ምን፣ ለኢየሱስ የምትሰጠው አገልግሎት በፍጹም አይባክንም::

**አገልጋዮች ማንነታቸውን ኢየሱስ ላይ ይመሠርታሉ::** የተወደዱትና ተቀባይነትን ያገኙት በፀጋ መሆኑን ስለሚያስታውሱ፣ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ ማረጋገጥ አይኖርባቸውም:: ሰዎች «አይመጥነንም» የሚሉትን ሥራ ለመቀበል ፈቃደኞች ናቸው:: የራስን ማንነት በሚገባ በማወቅ ከተከናወኑ ታላላቅ አገልግሎቶች አንዱ፣ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠቡ ነው:: እግር ማጠብ ፣ ዝቅ ያለ ደረጃ ከሚሰጠው ጫማ መወልወል ጋር እኩል ነው:: ኢየሱስ ግን ማንነቱን ያውቅ ስለ ነበር እግር ማጠቡ ስለራሱ የነበረውን አመለካከት አላዛባውም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*ኢየሱስም፣ አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሔር እንደተላከና፣ ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ አውቆ፣ ከእራት ተነሣ፣ መጎናፀፊያውን አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ » ዮሐ. 13÷3-4::*

አገልጋይ ከሆንክ፣ ማንነትህን በክርስቶስ ላይ መሥርት:: በማንነታቸው እርግጠኞች የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ለማገልገል የሚችሉት:: ስለማንነታቸው እርግጠኛ ያልሆኑ ሰዎች፣ «ሌሎች ስለ እኔ ምን ይላሉ?» በማለት ሁል ጊዜ ይጨነቃሉ:: ድካማችን ይጋለጥብናል ብለው ስለሚፈሩ፣ እራስን በመከላከል ኩራትና ማስመሰል ጀርባ ይደበቃሉ:: በራስ መተማመንን ባጣህ ቁጥር፣ ሰዎች እንዲያገለግሉህና ይሁንታቸውንም እንዲሰጡህ ይበልጥ ትፈልጋለህ::



ሄኔሪ ኖዌን የተባለ ሰው እንዲህ ብሏል:- «ሌሎችን ለማገልገል እንድንችል፣ ለእነርሱ መሞት አለብን፤ ማለት አስተሳሰባችንንና ፋይዳችንን በሌሎች መሥፈርት መለካታችንን መተው አለብን:: ይህንን ስናደርግ ነፃ ሆነን ለሌሎች ርህራሄ ለማሳየት እንችላለን:: ብቃትህንና ማንነትህን ከኢየሱስ ጋር ባለህ ግንኙነት ላይ በም ትመሠርትበት ጊዜ፣ ሌሎች ስለ አንተ ስለሚያስቡት ነገር ከመጨነቅ ነፃ ትሆናለህ:: በእውነትና በበለጠ ሁኔታ እንድታገለግላቸው የሚያስችልህ እንዲህ ያለው ነገር ነው::

አገልጋዮች የሥራቸውን ፋይዳ ለማረጋገጥ፣ ግድግዳቸውን በትምህርት ማስረጃ፣ በምልክቶችና በሽልማቶች መሸፈን አያስፈልጋቸውም:: በማዕረግ ስም እንጠራ አይሉም፤ የትልቅነት ሽማም አይከናነቡም:: የማዕረግ ምልክ ቶች አስፈላጊነት አይታያቸውም:: ማንነትና ጠቃሚነታቸውንም በሥራቸው አይመዝኑም:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «...*ጌታ ራሱ የሚያመሰግነው እንጂ፣ ራሱን በራሱ የሚያመሰግን ተቀባይነት አይኖረውም*» 2ቆሮ.10+18::

ግንኙነትንና ዝናን አስመልክቶ በሕይወቱ ሙሉ ማንነቱን በመኩራራት የመናገር ዕድል የነበረው ሰው ቢኖር፣ የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ ነበር:: እንደ ወንድምነቱ ከኢየሱስ ጋር ለማደጉ ማስረጃ የነበረው ሰው ነው:: ይሁን እንጂ ደብዳቤው መግቢያ ላይ ስለ ራሱ ሲናገር:- «*የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ*» ያዕ. 1+1 ብሏል:: ወደ ኢየሱስ ይበልጥ በቀረብክ ቁጥር፤ እራስህን የማስተዋወቅ ፍላጎትህ ያንሳል::

አገልጋዮች አገልግሎትን እንደ ግዴታ ሳይሆን፣ እንደ ዕድል ነው የሚቆጥ ሩት:: ሰውን መርዳት፣ በችግራቸው መድረስ፣ እና ማገልገል ደስ ያሰኛ ቸዋል:: እግዚአብሔርን በደስታ ያገለግሉታል:: ለምንድነው የሚያገለግሉት? ጌታን ስለሚወዱት፣ የፀጋው ውለታ ስላለባቸው፣ አገልግሎት ታላቅ የሕይወት ጥቅም መሆኑን ስለሚያውቁ እና እግዚአብሔር የአገልግሎት ዋጋን ለመክፈል ቃል መግባቱን ስለተረዱ ነው:: ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቃል ገብቷል:- «*የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፣ እኔም ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል፣ የሚያገ ለግለኝንም አባቴ ያከብረዋል*» ዮሐ. 12+26:: ጳውሎስም:- «*እግዚአብሔር አመፀኛ አይደለም፣ እርሱ ሥራችሁን፣ እንዲሁም በፊትም ሆነ አሁን ቅዱሳንን በመርዳት ለስሙ ያሳያችሁትን ፍቅር አይረሣም*» ዕብ. 6+10 ብሏል::

*ወደ ኢየሱስ ይበልጥ በቀረብክ ቁጥር፣ እራስህን የማስተዋወቅ አስፈላጊነት ያነሰ ይሆናል::*

በዓለም ካሉት ክርስቲያኖች ከመቶ

አሥሩ እጅ የእውነተኛ አገልጋይነት ተግባራቸውን በትጋት ቢያከናውኑ ኑሮ ሊሠራ ይችል የነበረውን መልካም ነገር ሁሉ ገምት:: እንደዚያ ካሉት ሰዎች እንደ አንዱ ለመሆን ፈቃደኛ ነህ? የዕድሜህ ጉዳይ ምንም አይደለም፤ እንደ አ ገልጋይ መሥራትና ማሰብ ከጀመርክ እግዚአብሔር ይጠቀምብሃል:: አልበርት ሼውዘር የተባለ ሰው እንዲህ ብሏል:- *«በእውነት ደስተኞች የሆኑ ሰዎች እንዴት ማገልገል እንደሚቻል የተማሩት ብቻ ናቸው»*

ሠላሳ አራተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** አገልጋይ ለመሆን የግድ እንደ አገልጋይ ማሰብ ይኖርብኛል::

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** *«በክርስቶስ እየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ በእናንተም ዘንድ ይሁን»* ፊልጵ. 2÷5::

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** ብዙውን ጊዜ ግድ የሚለኝ በሌሎች የመገልገሌ ጉዳይ ነው ወይስ ሌሎችን ለማገልገል የምችልባቸውን መንገዶች መፈለጌ?

# 35

# የእግዚአብሔር ኃይል በድካምህ ውስጥ

*እኛም በእርሱ ደካሞች ብንሆንም፣ እናንተን ለማገልገል ግን በእግዚአብሔር ኃይል ከእርሱ ጋር ሕያዋን ሆነን እንኖራለን፡፡*

2ቆሮ. 13፥4

*ጸጋዬ ይበቃሃል፣ ኃይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና አለኝ፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ፡፡*

2ቆር. 12፥9

እግዚአብሔር በደካሞች መጠቀምን ይወዳል፡፡

ሰው ሁሉ ድካሞች አሉበት፡፡ አንተም ብዙ አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አስተ ሳሰባዊ እና መንፈሳዊ ጉድለቶች አሉብህ፡፡ የገንዘብ እጥረት እንዲሁም የግንኙነት ጉድለት የመሳሰሉ እና ከቁጥጥርህ ውጭ የሆኑ ድካሞች ይኖ ሩብህ ይሆናል፡፡ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ያደክሙሃል፡፡ ዋናው ነገር ሁኔታ ዎቹ ሲገጥሙህ ምን ታደርጋለህ? የሚለው ነው፡፡ በአብዛኛው የምና ደርገው፣ ደካማነታችንን አንቀበልም፤ እናስተባብላለን፤ ምክንያት እንሰ ጣለን፤ እንሸሽጋቸዋለን፣ ስለእነርሱ ስናስብ እናዝናለን፡፡ ይህ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር በድካማችን ተጠቅሞ ሊፈጽም ያሰበውን እንዳያከናውን ያደርገዋል፡፡

እግዚአብሔር ድካምህን የሚመለከተው በተለየ ሁኔታ ነው፡፡ እንዲህ ይላል፡- «*ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ፣ መንገዴ ከመንገዳችሁ፣ ሐሳቤም ከሐ ሳባችሁ እንዲሁ ከፍ ያለ ነው*» ኢሳ. 55፥9፡፡ በመሆኑም ብዙ ጊዜ እኛ ከምንጠ ብቀው በተቃራኒ ነው የሚሠራው፡፡ ሊጠቀም የሚፈልገው፣ በብርታታችን ብቻ ነው ብለን እናስባለን፤ እርሱ ግን ድካማችንንም ለክብሩ ሊያውለው ይፈልጋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- « *ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔር ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ*» 1ቆሮ. 1፥27:: ድካሞችህ አጋጣሚዎች አይደሉም:: እግዚአብሔር ድካሞቹ በሕይወትህ እንዲኖሩ የፈቀደ ኃይሉን በአንተ በኩል ለመግለጥ ባለው ዓላማ መሠረት ሆነ ብሎ ነው ::

የሰዎች ጥንካሬ ወይም ብቃት እግዚአብሔርን ማርኮት አያውቅም:: ከዚያ ይልቅ ደካሞች ወደ ሆኑና፣ ያንንም ወደሚቀበሉ ሰዎች ነው የሚቀርበው:: ይህን ድካማችንን የመገንዘብ ባሕርይ ኢየሱስ:- «*በመንፈስ ድሆች*» ማቴ. 5፥3 እንደመሆን አድርጐ ቆጥሮታል:: ይህን የመሰለውን ሕይወት ጌታ በዋናነት ይባርከዋል::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ፍፁም ባልሆኑና ተራ በሆኑ ሰዎች ዓማካይነት ያልተለመዱና አስደናቂ ሥራዎች ማከናወንን የሚወድ መሆኑን የሚገልጡ ምሳሌዎች የሞሉበት ነው:: እግዚአብሔር በፍፁማን ሰዎች ብቻ ቢገለገል ኑሮ፣ ምንም ባልተሠራ ነበር:: ምክንያቱም ማንኛችንም ጉድለት አልባዎች አይደለንም:: እርሱ ፍፁማን ባልሆኑ ሰዎች የሚገለገል መሆኑ ሁላችንንም የሚያበረታታ ዜና ነው::

ድካም፣ ወይም ጳውሎስ እንደሚለው፣ «*መውጊያ*» 2ቆሮ. 12፥7፣ ኃጢአት አይደለም:: እንደ መጥፎ ምግባር ወይም የጸባይ ጉድለት ልትለውጠው የሚቻልህም አይደለም:: እንደ አብዝቶ መመገብና ትእግሥት ማጣት በቀላሉ አትቀይረውም:: የወረስከው ወይም ልትለውጠው የማይቻልህ ማንኛውም ጉድለት ነው:: *አካላዊ ጉድለት፤* ለምሳሌ አካል ጉዳተኛነት፣ የማይድን በሽታ፣ የአቅም ማነስ ሊሆን ይችላል:: *የስሜት ጉድለት፤* ለምሳሌ ባለፈ ሕይወታችን በደረሰ አጋጣሚ ምክንያት የሚመጣ መጥፎ ትዝታ፣ እንግዳ ልማድ፣ ወይም በዘር የሚተላለፍ ፀባይ ሊሆን ይችላል:: ፍፁም የተሰጥኦ ወይም የእውቀት ጉድለት ሊሆንም ይችላል:: ፍጹም ብሩህ አእምሮ ወይም ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ተሰጥኦ ማንኛችንም የለንም::

በሕይወትህ ያለውን ጉድለት ስታስብ፣ «እግዚአብሔር በፍጹም አይጠቀምብኝም» ወደሚለው ድምዳሜ ለመድረስ ትፈተን ይሆናል:: ነገር ግን በእኛ አለመብቃት እርሱ በፍጹም አይወሰንም:: እንደውም ታላቅ ኃይሉን ተራ ዕቃ ውስጥ ማኖሩ ደስ ያሰኘዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ነገር ግን ይሀ እጅግ ታላቅ ኃይል ከእግዚብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን ለማሳየት፣ ይሀ*

> *እግዚአብሔር በፍፁማን ሰዎች ቢገለገል ኑሮ ምንም ባልተሠራ ነበር::*

የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን» 2ቆሮ. 4፥7:: እንደማንኛውም ሸክላ ጥን ካሬ የሌለን፣ ጉድለት ያለን እና በቀላሉ የምንሰበር ነን:: በድካማችን ዓማካ ይነት እንዲሠራ ብንፈቅድለት ግን እግዚአብሔር ይጠቀምብናል:: ይህ ይፈ ፀም ዘንድ ጳውሎስን እንደሞዴል ልንከተለው ይገባል::

ድክመቶችህን ተቀበል:: ጉድለትህን እመን:: ፍፁም ለመምሰል መሞከርህን ተውና ለራስህ እውነተኛ ሁን:: በማስተባበል ወይም ምክንያት በመስጠት ከመኖር ይልቅ፣ ድካሞችህን ለይተህ ለማወቅ አሰላስል:: በዝርዝር ልትጽፋቸ ውም ትችላለህ::

ለጤናማ ኑሮ የሚያስፈልጉንን ነገሮች የሚገልጡ ሁለት ምስክርነቶች አዲስ ኪዳን ወስጥ ይገኛሉ:: የመጀመሪያው ጴጥሮስ ለኢየሱስ የተናገረው ነው:- *«አንተ ክርስቶስ የህያው እግዘአብሔር ልጅ ነህ»* ማቴ. 16፥16:: ሁለኛው፣ ጳውሎስ አንድ ሥፍራ ለተሰበሰቡ ጣኦት አምላኪዎች:- *«እኛም እኮ ሰንደናን ተው ሰዎች ነን»* የሐዋ. 14፥15 በማለት የተናገረው ነው:: እግዚአብሔር እንዲጠቀምብህ ከፈለክ፣ የእርሱን ማንነትና የራስህን ማንነት ማወቅ አለብህ:: ብዙ ክርስቲያኖች በተለይም መሪዎች፣ ሁለተኛውን እውነት ማለት ሰዎች ነን! ማለትን ይዘነጉታል:: ይህን መቀበሉ የሚያስቸግርህ ከሆነ፣ ድካምህን እንድ ትገነዘብ የሚያደርግህ ችግር እንዲደርስብህ ከመፍቀድ እግዚአብሔር አያመነ ታም:: ይህን የሚያደርገው ስለሚወድህ ነው::

በድካምህ ደስተኛ ሁን:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል :- «*እርሱ ግን <ፀጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና> አለኝ:: ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ*» 2ቆሮ. 12፥8-9:: በመጀመሪያ ሲታሰብ ይህ የሚቻል ነገር አይመስልም:: ምክንያቱም ከድካ‐ማችን ነፃ እንድንወጣ እንጂ፣ በዚያ ደስ እንድንሰኝ አይደለም የም ንፈልገው! ይሁን እንጂ፣ ድካማችንን መቀበላችን በእግዚአብሔር መልካምነት የመታመናችን መግለጫ ነው:: «እግዚአብሔር ሆይ! እንደምትወደኝና የሚሻለኝን ነገር እንደምታውቅ አምናለሁ» ማለትም ይሆናል::

ጳውሎስ የተፈጥሮ ድካማችንን ተቀብለን ልንኖር የተገባ የመሆኑን ብዙ ምክንያቶች ይገልጥልናል:: የመጀመሪያው፣ ድካሞቻችን በእግዚአብሔር እንድ ንታመን ያደርጉናል:: ጳውሎስ እግዚአብሔር ሊያስወግድለት ያልፈቀደውን የራሱን ድካም በመጥቀስ እንዲህ ብሏል:- *«ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭንቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያንጊዜ ብርቱ ነኝና»* 2ቆሮ. 12፥10:: ደካማ መሆንህ በተሰማህ ቁጥር፣ በእርሱ እንድትታመን እግዚአብሔር እያስታወሰህ መሆኑን ተረዳ::

ድካሞቻችን ትዕቢትን ይከላከሉልናል፣ ትሁትም ያደርጉናል:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «*ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፣ እርሱም የሚያሰቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ*» 2ቆሮ. 12÷7:: እግዚአብሔር በራስ መተማመናችንን ለመቆጣጠር ዋና ድካምን ከዋና ብርታት ጋር ያያይዘ ዋል:: ድካማችን እንደ ተቆጣጣሪ በመሆን ከእግዚአብሔር እየቀደምን ከመሮጥ ይጠብቀናል::

ጌዴዎን ከምድያማውያን ጋር ለመዋጋት 32,000 ተዋጊዎችን ባዘጋጀ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ወደ 300 ዝቅ አደረገበት:: ይህ ቁጥር ብዛቱ 135,000 ከነበረው የጠላት ሠራዊት ጋር ሲነፃፀር 1 የጌዴዎን ወታደር ከ 450 ሰው ጋር እንዲ ዋጋ ሆነ:: ነገሩ ሲታሰብ የጌዴዎንን ሠራዊት ለእልቂት መዳረግ ይመስላል:: እግዚአብሔር ይህን ያደረገው፣ እስራኤላውያን ከጠላታቸው የዳኑት፣ በራሣ ቸው ብርታት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን እንዲገነዘቡ ነው::

ድካማችን በአማኞች መካከል ያለውን ህብረት ያበረታታል:: ብርቱነት በራስ መተማመንን («ሌላ ሰው አያስ ፈልገኝም»)፣ ማለትን የሚያስከትል ሲሆን፣ ድካማችን ግን አንዳችን ለሌላችን የቱን ያህል የምናስፈልግ መሆናችንን ያስገነዝበናል:: የሕይወት ድካማችንን ክሮች በአንድ ላይ ስንገምዳቸው ብርቱ የጥንካሬ ገመድ ይወጣቸዋል:: ቨንስ ሀቨነር የተባለ ጸሐፊ እንዲህ ብሏል:- «ክርስቲያኖች እንደበረዶ ብናኝ (በአንዳንድ የዓለም አካባቢዎች እንደሚዘን በው)፣ አቅመ ቢሶች ናቸው:: በአንድ ላይ ተጣብቀው ሲረጉ ግን፣ በጎዳና ላይ ከሆነ፣ የተሽከሪካሪዎችን እንቅስቃሴ የሚገታ ግዙፍ ኃይል ይሆናሉ»::

*ውጤታማ አገልግሎትህ ከጥልቅ ጉዳቶችህ ይወጣል::*

ከሁሉም ይልቅ፣ ድካሞቻችን ርህራሄንና የአገልግሎት ብርታት ይጨም ሩልናል:: የሌሎችን ድካሞች ይበልጥ የምንረዳና የምናዝንላቸውም እንሆና ለን:: እግዚአብሔር በምድር ላይ የክርስቶስን የመሰለ አገልግሎት እንዲኖርህ ይፈልጋል:: ይህ ሲሆን፣ በአንተ ቁስል ሌሎች ፈውስ ያገኛሉ ማለት ነው:: የሕይወትህ ትልቅ መልዕክቶችና እጅግ ውጤታማ አገልግሎትህ ከጥልቅ ጉዳ ቶችህ ይወጣሉ:: ያስፈሩህ፣ በጣም ያፈርክባቸው፣ እና ለሌሎች ለማካፈል ያልፈለካቸው ነገሮች፣ እግዚአብሔር ሌሎችን ለመፈወሻነት የሚጠቀምባቸው ዋና መሣሪያዎች ናቸው::

ታላቁ ሚሲዮናዊ ኸድሰን ቴይለር እንዲህ ብሏል:- «ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ደካሞች ነበሩ»:: የሙሴ ድካም ግልፍተኛነቱ ነበር:: ይህ ፀባዩ

አንድ ግብፃዊ እንዲገድል፣ ተናገረው የተባለውን ቋጥኝ እንዲመታ፣ እና አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፉበትን ጽላት እንዲሰብር አድርጎታል። እግዚአብሔር ግን:- *«በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሁት ሰው»* ዘኁ. 12+2 አድርጎ ሰወጠው።

የጌዴዎን ድካም እራሱን ዝቅ አድርጎ ማየትና ከባድ ፍርሃት ነበር፤ እግዚአብሔር ግን *«ኃያል ጦረኛ»* መሳ. 6+12፣ አደረገው። የአብርሃም ድካም ፍርሃት ነበር። እራሱን ከጉዳት ለማዳን ሲል፣ ከአንዴም ሁለቴ ሚስቱን እህቴ ናት አለ። እግዚአብሔር ግን አብርሃምን *«ለሚያምኑ ... ሁሉ አባት»* ሮሜ 4+11 በማድረግ ለወጠው። ችኩሉንና ደካማ አስተሳሰብ የነበረው ጴጥሮስን *«ዓለት»* ማቴ. 16+18፣ ዘማዊው ዳዊትን:- *«እንደ ልቤ የሆነ»* የሐዋ. 13+22 ወደ መባል፣ ከአብሪተኞቹ *«የመብረቅ ልጆች»* አንዱ የሆነውን ዮሐንስን *«የፍቅር ደቀ መዝሙር»* ወደ መባል ለውጧቸዋል።


ዝርዝሩ ሊቀጥል ይችል ነበር:- *«እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ልበል? ስለ ጌዴዎን፣ ስለ ባርቅ፣ ስለ ሳምሶን፣ ስለ ዮፍታሔም፣ ስለዳዊት፣ ስለ ሳሙኤል እንዲሁም ስለ ነቢያት እንዳልተርክ ጊዜ የለኝም ... በድካማቸው በረቱ »* ዕብ. 11+32-34። እግዚአብሔር ድካሞችን ወደ ብርታቶች መለወጥን ያውቅበታል። ትልቁን ድካምህን ወስዶ ሊለውጠው ይፈልጋል።

ድካምህን በታማኝነት ለሌሎች ንገር። አገልግሎት የሚጀመረው፣ ድካምህን በመግለጥ ነው። እራስህን መከላከልህን በተውከ፣ ጭንብልህን ባወለቅህ እና ያለብህን ትግል ለሌሎች በገለጥህ ቁጥር፣ ሌሎችን በማገልገል ረገድ እግዚአብሔር ይበልጥ ይጠቀምብሃል። ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ ሁሉ ድካሙን በመግለጥ ጥሩ ምሳሌ ሆኗል። በዚሁ መሠረት የሚከተሉትን በታማኝነት ገልጧል:-

- ውድቀቶቹን:- *«የማደርገው፣ ላደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም፣ ዳሩ ግን ለማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር ነው»* ሮሜ 7+19።
- ስሜቶቹን:- *«የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፣ ሁሉን በግልጽ ነገርናችኋል፤ ልባችንንም ወለል አድረገን ከፍተንላችኋል»* 2ቆሮ. 6+11።
- ተስፋ መቁረጡን :- *«ወንድሞች ሆይ፣ በእስያ ስለደረሰብን መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቆርጥ ድረስ ከአቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር»* 2ቆሮ. 1+8።
- ፍርሃቱን:- *«ወደ እናንተ የመጣሁት በድካምና በፍርሃት፣ እንዲሁም በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር»* 1ቆሮ. 2+3።

እርግጥ ግልጥነት አደጋ አለው። መከላከያህን አስወግደህ ሕይወትህን ለሌ

ሉች መግለጡ ያስፈራ ይሆናል:: ውድቀቶችህን፣ ስሜትህን፣ ተስፋ መቁረጥህንና ፍርሃትህን በምትገልጥበት ጊዜ በሰዎች መገለል ይደርስብሃል:: ከዚህ የምታገኛቸው ጥቅሞች ግን ከጉዳቱ ይበልጣሉ:: ግልጥነት የስሜት ነፃነት ነው:: ከጭንቀት ይገላግላል፤ ፍርሃትህንም ያስወግድልሃል:: ወደ ነፃነት



በሚደረግ ጉዞ የመጀመሪያው እርምጃ ነው::

እግዚአብሔር *«ለትሁታን ፀጋን የሚሰጥ»* መሆኑን ተመልክተናል:: ብዙዎች ግን ትህትናን በተሳሳተ ሁኔታ ነው የሚረዱት:: ትህትና እራስህን ማዋረድ፣ ወይም ብርታትህን መካድ ሳይሆን፣ ድካሞችህን ማመን ነው:: ይበልጥ እውነተኛ ስትሆን፣ የእግዚአብሔር ፀጋ ይበልጥ ይበዛልሃል:: በሌሎች ዘንድም ሞገስን ታገኛለህ:: ግልጥነት ማራኪ ባሕርይ ነው:: በተፈጥሯችን ትሁት ወደ ሆኑ ሰዎች መቅረብን እንወዳለን:: አስመሳይነት ያርቃል፣ ሀቀኝነት ይማርካል፣ ግልጥነት ደግሞ ወደ ጠበቀ ወዳጅነት የሚያደርስ መንገድ ነው::

ለዚህ ነው እግዚአብሔር በብርታትህ ብቻ ሳይሆን፣ በድካምህም ለመጠቀም የሚፈልገው:: ሰዎች ብርታትህን ሲያዩ ተስፋ ይቆርጡና:- «መልካም ሆኖለታል ወይም ሆኖላታል፤ እኔ ግን በፍፁም ላደርገው አልችልም» ይላሉ:: ነገር ግን ደካማ ብትሆንም እንኳን እግዚአብሔር ሲጠቀምብህ ሲያዩ:- «እግዚአብሔር ምናልባት በእኔም እንደ እርሱ ይጠቀምብኝ ይሆናል!» ብለው እንዲያስቡ ያበረታታቸዋል:: ብርታታችን ውድድርን፣ ድካማችን ግን ህብረትን ይፈጥራል::

ሰላሳ አምስተኛ ቀን

**የእግዚአብሔር ኃይል በድካምህ ውስጥ**

በሕይወትህ አንድ ወቅት ቆም ብለህ ፍላጎትህ ሰዎችን በድርጊትህ ማስደነቅ ወይስ በጎ ተጽዕኖ ማሳደር መሆኑን መወሰን አለብህ:: ሰዎችን ከሩቅ ለማስደነቅ ትችላለህ፤ ተጽዕኖ ልታሳድርባቸው ከፈለክ ግን ልትቀርባቸው ይገባል:: እንዲህ በምታደርግበት ጊዜ ድካምህ ይታያቸው ይሆናል:: ጥሩ ነው:: ለመሪነት እጅግ አስፈላጊ የሆነው ባህርይ፣ ፍጹምነት ሳይሆን ታማኝነት ነው:: ሰዎች ሊያምኑህ ይገባል፤ ካልሆነ አይከተሉህም:: ታማኝነትን የምታዳብረው፣ ፍጹም በመምሰል ሳይሆን፣ እውነተኛና ግልጥ በመሆን ነው::

በድካምህ ተመካ:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *«እንዲህ ስላለው ሰው እመካለሁ፣ ስለ ራሴ ግን ከድካማነቴ በስተቀር አልመካም»* 2ቆሮ. 12÷5:: በራስህ የምትተማመንና የማትበገር ሰው ከመምሰል ይልቅ፣ እራስህን የፀጋ ታላቅ ውጤት አድርገህ ቁጠር:: ሰይጣን ድካሞችህን ሲያመለክትህ ተስማማና:-

«በድካማችን የሚራራልንን» ዕብ. 4፥15፣ ኢየሱስና፦ «የሚማልድልንን» ሮሜ 8፥26 መንፈስ ቅዱስን፣ በማመስገን ልብህን ሙላው።

ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ይበልጥ ሊጠቀምብን በማሰብ አንዳንድ ጊዜ ብርታታችንን ወደ ድካም ይለውጠዋል። ያዕቆብ አታላይ ነበር። ሕይወቱን ያሳለፈው፣ ሲያቅድና ዕቅዱ ካመጣበት መዘዝ ሲሸሽ ነው። አንድ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር በመታገል እንዲህ አለ፦ «ካልባረከኝ አልለቅህም»። እግዚአብሔርም «እሺ» ካለ በኋላ ጭኑን ከመጋጠሚያው ላይ አናጋበት። ይህን ያደረገው ለምን ዓላማ ነው?

እግዚአብሔር የያዕቆብን ብርታት ነካና (የጭን ጡንቻ ጠንካራ የአካል ክፍል ነው)፣ ደካማ አደረገው። ከዚያ በኋላ ያዕቆብ ለመሸሽ የማይችል አንካሳ ሆነ። ወደደም ጠላ በእግዚአብሔር እንዲደገፍ ተገደደ። እግዚአብሔር እንዲባርክህና በታላቅ ሁኔታ እንዲጠቀምብህ ከፈለግህ፣ ቀሪ የሕይወት ዘመንህን እያነከስክ ለመሄድ ፈቃደኛ መሆን አለብህ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደካማ ሰዎች ነው የሚጠቀመው።

ሠላሳ አምስተኛ ቀን


ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፦ ደካማነቴን አምኜ ስቀበል፣ እግዚአብሔር ይበልጥ ይሠራብኛል።

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፦ «ፀጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሉ ፍጹም የሚሆነው፣ በድካም ጊዜ ነው» 2ቆሮ. 19፥9።

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፦ ድካሜን ለመደበቅ በመሞከር የእግዚአብሔርን ኃይል ውስጥ በማድረግ ላይ ነኝን? ሌሎችን ለመርዳት እችል ዘንድ፣ በምንድነው ግልጥና እውነተኛ ልሆን የሚገባኝ?

## ዓላማ ቁጥር 5



# የተሠራኸው ለተልዕኮ ነው

*የጻድቅ ፍሬ የሕይወት ዛፍ ናት፤ ነፍሳትን*
*የሚማርክም ጠቢብ ነው።*

**ምሳሌ 11፥30**

# 36

# የተሠራኸው ለተልዕኮ ነው

*አንተ ወደ ዓለም እንደላክኸኝ እኔም ወደ ዓለም ልከአቸዋለሁ።*

*ዮሐ. 17፥18*

*ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔርን የፀጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቆጠር እንደ ከንቱ ነገር ናት ።*

*የሐዋ. 20፥24*

የተሠራኸው ለተልዕኮ ነው።

እግዚአብሔር በዓለም በሥራ ላይ ስለሆነ፣ አብረኸው እንድትሠራ ይፈልጋል። ሥራው ተልዕኮህ በመባል ይታወቃል። እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት፣ በዓለም ደግሞ ተልዕኮ እንዲኖርህ ይፈልጋል። አገልግሎት ለአማኞች የምታበረክተው ሲሆን፣ ቆላ. 1፥25፣ ተልዕኮ ደግሞ ላላመኑት የምትሰጠው አገልግሎት ነው። ተልዕኮህን መፈፀም፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለው አምስተኛ ዓላማ ነው።

የሕይወት ተልዕኮህ ከሌሎች ጋር የምትጋራው እና የብቻ ነው። የተልዕኮህ አንድ ክፍል ከክርስቲያኖች ሁሉ ጋር የምትካፈለው ኃላፊነት ሲሆን፣ ሌላው ለአንተ ብቻ የተሰጠ ልዩ ሥራ ነው። ሁለቱንም ከፊታችን ባሉት ምዕራፎች እንመለከታቸዋለን።

ሚሽን የሚለው እንግሊዝኛ ቃል «መላክ» ተብሎ ከሚተረጐመው የላቲን ቃል የተወሰደ ነው። ክርስቲያን መሆን፣ የክርስቶስ ወኪል በመሆን ወደ ዓለም መላክን ይጨምራል። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል ፦ «*አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ*» ዮሐ. 20፥21።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የሕይወት ተልዕኮውን በግልጥ ተረድቶ ነበር:: በአሥራ ሁለት ዓመቱ እንዲህ አለ:- *«ለምን ፈለጋችሁኝ? ለባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?»* ሉቃስ 2÷49:: ከሀያ አንድ ዓመት በኋላ በመስቀል ላይ በሚሞትበት ጊዜ ደግሞ *«ተፈጸመ»* ዮሐ. 19÷30 ብሏል:: ልክ መጻሕፍትን ከግራና ከቀኝ እንደሚይዝ መደገፊያ፣ እነዚህ ሁለት አባባሎች በሚገባ የተኖረን ወይም በዓላማ የሚመራ ሕይወትን ጅማሬና ፍጻሜ ያሳያሉ:: ኢየሱስ ከአባቱ የተቀበለውን ተልዕኮ ፈጸመው::

እርሱ በምድር ላይ የነበረው ተልዕኮ፣ አሁን የእኛ ተልዕኮ ሆኗል:: ምክንያቱም እኛ አካሉ ነን:: በሥጋዊ አካሉ ያደረገውን፣ እኛ እንደ መንፈሳዊ አካል (ቤተ ክርስቲያን)፣ ልንቀጥለው ይገባል:: ምን ነበር ያ ተልዕኮ? ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ማገናኘት! መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እርሱ በክርስቶስ ዓማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን»* 2ቆሮ. 5÷18::

እግዚአብሔር ሰዎችን ከሰይጣን ነፃ በማውጣት ከራሱ ጋር ሊያስታርቃቸው ይፈልጋል:: ይህን የሚያደርገው፣ እንሠራቸው ዘንድ የተፈጠርንላቸውን አምስት ዓላማዎች እንድናከናውን ነው:: እነርሱም፣ እንድንወደው፣ የቤተሰቡ አካል እንድንሆን፣ እርሱን እንድንመስል፣ እንድናገለግለው፣ ስለእርሱ ለሌሎች እንድንነግር ናቸው:: እንዴ የእርሱ ከሆንን፣ ወደ ሌሎች ለመድረሻነት ይገለገልብናል:: ያድነንና ከዚያ ይልከናል:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *«ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤ እግዚአብሔርም በእኛ ዓማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን»* 2ቆሮ. 5÷20:: እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን ፍቅርና ዓላማ የምንናገር መልእክተኞች ነን::

## የተልዕኮህ ጠቃሚነት

ምድራዊ የሕይወት ተልዕኮህን መፈጸም፣ ለእግዚአብሔር ክብር የመኖርህ አስፈላጊ ክፍል ነው:: ተልዕኳችን በጣም አስፈላጊ የሆነባቸውን ብዙ ምክንያቶች መጽሐፍ ቅዱስ ይዘረዝራቸዋል::

**ተልዕኮህ፣ ኢየሱስ በምድር የነበረው ተልዕኮ ቀጣይ ነው::** ተከታዮቹ እንደ መሆናችን መጠን እርሱ የጀመረውን መቀጠል አለብን:: ኢየሱስ የሚጠራን ወደ እርሱ እንድንመጣ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ሌሎች እንድንሄድለትም ነው:: ተልዕኮህ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣ ኢየሱስ አምስት ጊዜ ፤ በተለያዩ አምስት መንገዶች፣ አምስት ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ ደጋግሞ ጠቅሶታል፣ ማቴ. 28÷19-20፤ ማር. 16÷15፤ ሉቃ. 24÷47፤ ዮሐ. 20÷21፤ የሐዋ. 1÷8:: «ይህን

> ሠላሳ ስድስተኛ ቀን
> የተሠራኸው
> ለተልዕኮ
> ነው

*በእርግጥ እንድትረዳ በጥብቅ እፈልጋለሁ*» የሚል ይመስላል:: እነዚህን አምስት የኢየሱስ ተልዕኮዎች ፣ ስታጠና የተልዕኮህን መቼ፣ የት፣ ለምን እና እንዴት መሆን በዝርዝር ትረዳለህ::

ኢየሱስ በታላቁ ተልዕኮ ትእዛዙ ውስጥ እንዲህ ብሏል:- «*ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እነሆም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ* » ማቴ. 28÷19-20:: ይህ ተልዕኮ ለመጋቢያንንና ሚስዮናውያን ብቻ ሳይሆን፣ ለእያንዳንዱ የኢየሱስ ተከታይም የተሰጠ ነው::

*ኢየሱስ የሚጠራን ወደ እርሱ እንድንመጣ ብቻ ሳይሆን ፣ ወደ ሌሎች እንድንሄድለትም ነው::*

ይህ ከኢየሱስ የተሰጠህ ተልዕኮ ስለሆነ፣ ከፈለግህ ብቻ የምታደርገው አይደለም:: እነዚህ የኢየሱስ ቃላት ታላቅ ተልእኮ እንጂ፤ *ታላቅ ማሳሰቢያዎች* አይደሉም:: የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ከሆንክ ተልእኮህ ግዴታ ነው:: ይህን ችላ ማለት አለመታዘዝ ይሆናል::

በዙሪያህ ስላሉት የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሔር በኃላፊነት የሚጠይቅህ መሆኑን አላወቅህ ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*እኔ ኃጢአተኛውን ሰው በእርግጥ ትሞታለህ ባልኩት ጊዜ ፣ አንተ ባታስጠነቅቀው ፣ ነፍሱንም ያድን ዘንድ ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ባትነግረው ፣ ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፤ አንተንም ስለ ደሙ በኃላፊነት እጠይቅሃለሁ*» ሕዝ. 3÷18:: አንዳንድ ሰዎች የሚያውቁህ ክርስቲያን አንተ ብቻ ስለምትሆን፣ ተልዕኮህ ስለ ኢየሱስ ለእነርሱ መንገር ነው::

**ተልዕኮህ አስደናቂ ዕድል ነው::** ታላቅ ኃላፊነት ቢሆንም፣ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው መሆን ታላቅ ክብር ነው:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- « *ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ ዓማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን* » 2ቆሮ. 5÷18:: ተልዕኮ ፣ *ለእግዚአብሔር ጋር* መሥራትንና እርሱን መወከልን የመሳሰሉ ሁለት ታላላቅ ዕድሎች አሉት:: መንግሥቱን በመገንባት ተግባር ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን እንሠራለን:: ጳውሎስ:- «*ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ» 2ቆሮ. 6÷1 ነን ይለናል::*

ኢየሱስ ድነታችንን አስገኘልን፣ የቤተሰቡ አባል አደረገን፣ መንፈሱን ሰጠን፣ ከዚያም በዓለም ወኪሎቹ አደረገን:: እንዴት ያለ ዕድል ነው! መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን ፣ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን*» 2ቆሮ. 5÷20::

**የዘላለም ሕይወት የሚያገኙበትን መንገድ ለሰዎች መንገር፣ ልታደርግላቸው ከሚቻልህ ነገሮች ሁሉ ትልቁ ነው።** ጎረቤትህ የካንሰር ወይም የኤች አይ ቪ በሽታ ቢኖርበትና አንተ መድኃኒቱን አውቀህ፤ ነፍስ አድን የሆነውን የፈውስ ዜና ባትገልጥለት፣ ድርጊትህ ወንጀል ይሆናል። ከዚህ የሚከፋው ድርጊት ግን ይቅርታ፣ ዓላማ፣ ሰላም እና ዘላለማዊ ሕይወት የሚገኝበትን መንገድ ምስጢር አድርጎ መያዙ ነው። ዓለም ካላት ሁሉ የሚልቅ የምሥራች ዜና አለን። ይህን የምሥራች ለሌሎች ማካፈል፣ ልታደርግላቸው የሚቻልህና ከሁሉ የሚበልጥ መልካምነት ነው።

በክርስትና ብዙ የቆዩ ሰዎች ካሉባቸው ችግሮች አንዱ፣ ያለ ክርስቶስ መኖር ምንኛ ተስፋ ቢስነት መሆኑን መርሳታቸው ነው። ሰዎች የቱንም ያህል የተሳካላቸው ቢመስሉ፣ ያለ ክርስቶስ ተስፋ በሌለው ሁኔታ የጠፉና ከእግዚአብሔር ለዘላለም ወደ መለየት አቅጣጫ በማምራት ላይ መሆናቸውን ማስታወስ ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «*ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና*» የሐዋ. 4፥12። እያንዳንዱ ሰው ኢየሱስ ያስፈልገዋል።

**ተልዕኮህ ዘላለማዊ ጠቀሜታ አለው።** በሰዎች ዘላለማዊ ዕጣ ላይም ተፅዕኖ ይኖረዋል። በመሆኑም በምድራዊው ሕይወትህ ወቅት ከምትደርስበት ማንኛውም ሥራ፣ ግኝት፣ ወይም ግብ ይበልጥ ጠቃሚ ነው። የተልዕኮህ ውጤት ለዘላለም ይኖራል፤ የሥራህ ውጤት ግን አይኖርም። ከምትሠራው ነገር ሁሉ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት እንዲመሠርቱ በመርዳት የምታከናውነውን ያህል ቁም ነገር ያለው የለም። ለዚህ ነው ለተልዕኳችን መጣደፍ የሚኖርብን። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል ፡- «*ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ፤ ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣል*» ዮሐ. 9፥4። የሕይወት ተልዕኮህን በተመለከተ ሰዓቱ ወደ ፍፃሜው በመሽከርከር ላይ ስለሆነ፣ ለሌላ አንድ ተጨማሪ ቀን አትዘግይ። መልካሙን የድነት የምሥራች ለሌሎች የማድረስ ተልዕኮህን አሁኑኑ ጀምር! ወደ ኢየሱስ ካመጣናቸው ሰዎች ጋር ለመደሰት ዘላለም በሙሉ አለን፤ መልካሙን የምሥራች ወደ ሰዎቹ ለማድረሻ ያለን ጊዜ ግን፣ የሕይወት ዘመናችን ብቻ ነው።

> *ታላቁ ተልዕኮ*
> *የኢየሱስ ተከታይ ለሆነ*
> *ሁሉ ተሰጥቷል።*

እንዲህ ሲባል የሙሉ ጊዜ ወንጌላዊ ለመሆን ሥራህን መተው አለብህ ማለት አይደለም። ባለህበት ሆነህ መልካሙን የምሥራች ለሌሎች እንድትነግር እግዚአብሔር ይፈልጋል። እንደ ተማሪ፣ እናት፣ የአፀደ ሕፃናት

መምህር፣ ነጋዴ፣ ሥራ አስኪያጅ ... ፣ ሥራህ ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔር በመንገድህ ላይ የሚያኖራቸውንና ወንጌል ልታካፍላቸው የሚገባ ሰዎችን ያለማቋረጥ ፈልግ።

**ተልዕኮህ ለሕይወትህ ትርጉም ይሰጠዋል።** ዊልያም ጀምስ የተባለ ሰው እንዲህ ብሏል:- «በምድራዊ ሕይወት በሚገባ ለመጠቀም የሚቻለው፣ ዘላለማዊነት ባለው ነገር ላይ በማዋል ነው»። እውነቱ ታዲያ፣ ዘላለም የሚኖረው የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ መሆኑ ነው። ሌላው ሁሉ በመጨረሻ ይጠፋል። ለዚህ ነው በዓላማ የሚመራ ሕይወት በመኖር ማለትም፣ አምልኮ፣ ህብረት፣ መንፈሳዊ ዕድገት፣ አገልግሎት ያለው ሕይወት መኖርና ምድራዊ ተልዕኳችንን መወጣት የሚኖርብን። የነዚህ ድርጊቶች ውጤቶች ዘላለም ይኖራሉ።

እግዚአብሔር የሰጠህን ምድራዊ ተልዕኮ ካልተወጣህ፣ ከእርሱ የተሰጠህን ሕይወት በከንቱ ታባክነዋለህ። ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «*ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔርን የፀጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቱን ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቆጠር እንደከንቱ ነገር ናት*» የሐዋ. 20÷24። ከምትኖርበት ሥፍራና እግዚአብሔር ከሰጠህ ማንነት የተነሣ፣ አንተ ብቻ መልካሙን የድነት የምሥራች ልትነግራቸው የሚቻልህ ሰዎች በዚህች ምድር ላይ አሉ። ከአንተ የተነሣ አንድ ሰው እንኳን መንግሥተ ሰማያት ቢገባ፣ ሕይወትህ ዘላለማዊ ለውጥ አመጣ ማለት ነው። በዙሪያህ ያለውን የተልዕኮህን መስክ ቃኝና እንዲህ በማለት ጸልይ። «እግዚአብሔር ሆይ! ስለ ኢየሱስ እንድነግረው በሕይወቴ ያስቀመጥከው ሰው ማነው?»

**እግዚአብሔር ለታሪክ ድምዳሜ ያዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ፣ ከተልዕኳችን መፈፀም ጋር የተቆራኘ ነው።** ዛሬ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓትና ስለ ዓለም ፍጻሜ ለማወቅ ያለው ፍላጎት በማደግ ላይ ነው። መቼ ይሆን ይህ የሚሆነው? ወደ ሰማይ ሊያርግ ሲል ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን የጠየቁት ይህንኑ ነበር። የእርሱም መልስ በጣም ግልጥ ነው:- «*አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት ማወቅ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ*» የሐዋ. 1÷7-8 አላቸው።

ደቀ መዛሙርቱ ስለ ትንቢት ለመነጋገር በሚፈልጉ ጊዜ፣ ኢየሱስ ቶሎ ብሎ ውይይቱን ወደ ወንጌል ሥርጭት ቀየረው። በዓለም ባላቸው ተልዕኮ ላይ እንዲያተኩሩ ሊያደርጋቸው ፈለገ። የንግግሩ ቁም ነገር:- «የመመለሴ ዝርዝር ነገር፣ የናንተ ጉዳይ አይደለም። ጉዳያችሁ የሰጠኋችሁ ተልዕኮ ነው፤ እዚያ ላይ አትኩሩ! » የሚል ነው።

የኢየሱስን መመለሻ ትክክለኛ ጊዜ መገመቱ ፍሬ ቢስ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ እንዲህ ብሏል ፡- «*ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር ማንም አያው ቅም*» ማቴ. 24÷36። ኢየሱስ ቀኑን ወይም ሰዓቱን አላውቅም ካለ፣ ለምንድ ነው አንተ ለማወቅ የምትሞክረው? በእርግጥ የምናውቀው ነገር፣ መልካ ሙን የድነት የምሥራች እንዲሰሙ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ ቃሉን እስኪሰሙ ድረስ ኢየሱስ

*ሰይጣን፣ እምነትህን ከማካ ፈል ሌላ ማንኛውንም ነገር እንድትሠራ ስለሚያደርግህ ተልዕኮህ በቀላሉ ይደናቀፋል።*

የማይመለስ መሆኑን ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- «*ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል*» ማቴ. 24÷14። ኢየሱስ በቶሎ እንዲመለስ የምትፈልግ ከሆንክ፣ የመምጣቱን ትንቢት በመመራመር ሳይሆን፣ ተልዕኮህን በማከናወኑ ላይ አትኩር።

እምነትህን ከማካፈል ይልቅ ሌላ ማንኛውንም ነገር እንድትሠራ ሰይጣን ስለሚፈልግ፣ ተልዕኮህ በቀላሉ ይደናቀፋል። አንድ ሰው አብሮህ ወደ መንግ ሥተ ሰማያት እንዲሄድ የምታደርግ እስካልሆንክ ድረስ፣ ማንኛውንም መል ካም ተግባር ብትሠራ አይቃወምህም። በተልዕኮህ መሠረት በጥብቅ መሥራት ስትጀምር ግን፣ ዲያብሎስ ማናቸውንም ማሰናከያ እንደሚወረውርብህ ጠብቅ። እንዲያ በሚሆንብህ ጊዜ ቀጥሎ ያሉትን የኢየሱስ ቃላት አስታውስ፡- «*እርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም*» ሉቃስ 9÷62።

# ተልዕኮህን ለመፈፀም የምትከፍለው ዋጋ

ተልዕኮህን ለመፈፀም ይቻል ዘንድ፣ የራስህን አጀንዳ በመተው፣ እግዚአ ብሔር ለሕይወትህ ያለውን አጀንዳ መቀበል ይኖርብሃል። በሕይወትህ ልታከናውናቸው ከምትፈልጋቸው ሌሎች ነገሮች ጋር ልታዳብለው አትች ልም። አንተም እንደ ኢየሱስ፡- «*አባት ሆይ ... የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈፀም*» ሉቃስ 22÷42 ልትል ይገባል። መብቶችህን፣ ፍላጎቶችህን፣ ህልሞ ችህን፣ ዕቅዶችህን፣ እና ምኞቶችህን ለእርሱ አሳልፍና ስጥ። «ላደርገው የምፈልገውን ባርክልኝ» የሚለውን የመሰለ የእራስ ወዳድነት ጸሎት በመተ ው፡- «እግዚአብሔር ሆይ የምትባርከውን ነገር እንድሠራ እርዳኝ» በልና ጸልይ። ከግርጌው ፊርማህ የተደረገበትን ባዶ ወረቀት አዘጋጅና ሌላውን ዝርዝር ነገር እርሱ እንዲያስፍርበት በመንገር ለእግዚአብሔር ስጠው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ብልቶቻችሁን የክፋት መሣሪያ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፤ ይልቁንስ ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገሩ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ*» ሮሜ 6÷13::

የቱንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍልህ፣ የሕይወት ተልዕኮህን ለመወጣት ቆርጠህ ከተነሣህ፣ ጥቂት ሰዎች ብቻ ሊለማመዱት በሚችሉት ሁኔታ የእግዚአብሔርን በረከት ትለማመዳለህ:: መንግሥቱን ለማገልገል ቆርጠው ለተነሡ ወንድና ሴት አገልጋዮቹ እግዚአብሔር የማያደርግላቸው ነገር የለም:: ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቃል ገብቷል:- «*ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል*» ማቴ. 6÷33::

## ለኢየሱስ አንድ ተጨማሪ ሰው

አባቴ ከአምሳ ዓመት ለበለጠ ጊዜ፣ በአብዛኛው ገጠር ባሉ ትንንሽ አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ሲያገለግል ኖሯል:: ተራ ሰባኪ ቢሆንም፣ ተልዕኮ ያለው ሰው ነበር:: በጣም ይወደው የነበረ ሥራ፣ ፈቃደኛ ሰዎች ያሉበትን ቡድን ይዞ ወደ ሌሎች አገሮች በመሄድ ለአነስተኛ አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ መሥራት ነበር:: በሕይወት ዘመኑ በዓለም ዙሪያ ለ150 አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ሠርቷል::

በ1999 (እ.ኤ.አ) በካንሰር በሽታ ሞተ:: በሕይወቱ የመጨረሻ ሳምንት በግማሽ ስመመን ውስጥ ነበር:: በሚያልምበት ጊዜ በህልሙ ስለሚያየው፣ ወይም ስለሚያደርገው ነገር ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገራል:: አልጋው አጠገብ ቁጭ ብዬ ህልሙን በማድመጥ ስለ አባቴ ብዙ ተረዳሁ:: ስለ ቤተክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ ሥራዎቹ እያፈራረቀ ይናገር ነበር::



የሕይወቱ ፍፃሜ በተቃረበ ጊዜ፣ አንድ ምሽት፣ ባለቤቴ፣ የአክስቴ ልጅና እኔ አጠገቡ ተቀምጠን ሳለ፣ በድንገት በረታና ከመኝታው ለመነሣት ይሞክር ጀመር:: አቅም አልነበረውም፤ ባለቤቴ እንዲተኛ አስገደደችው:: እርሱ ግን ካልተነሣሁ ብሎ አስቸገረን:: በመጨረሻም ባለቤቴ :- «ጂሚ፣ ምን ልታደርግ ነው የምትሞክረው?» አለችና ጠየቀችው:: «ለኢየሱስ አንድ ተጨማሪ ሰው ማዳን አለብኝ! አንድ ሌላ ሰው ለኢየሱስ ማዳን አለብኝ!» እያለ ይናገር ጀመር::

ከዚያ በኋላ ለአንድ ሰዓት ያህል «ለኢየሱስ አንድ ተጨማሪ ሰው ማዳን አለብኝ» የሚለውን አረፍተ ነገር ለመቶ ጊዜ ያህል ጋግሞታል:: እንባዬ በጉንጮቼ እየወረደ፣ ስለ አባቴ እምነት እግዚአብሔርን ለማመስገን አቀረቀርኩ::

ያኔ አባቴ ከሲታ እጁን እራሴ ላይ አሳረፈና እንዲህ አለኝ ፡- «አንድ ተጨማሪ ሰው ለኢየሱስ አድን! አንድ ተጨማሪ ሰው ለኢየሱስ አድን!»።

አባቴ የተናገረው ነገር የቀሪው ሕይወቴ መልእክት እንዲሆን ወሰንኩ። አንተም የሕይወትህ ትኩረት አድርገህ እንድትወስደው እጠይቃለሁ። ምክን ያቱም ከዚህ ይልቅ በዘላለም ውስጥ ትልቅ ልዩነት የሚያመጣ ነገር የለም። እግዚአብሔር እንዲጠቀምብህ ከፈለግህ፣ እርሱን የሚያሳስበው ነገር ሊያሳስብህ ይገባል። ከሁሉም ይልቅ እግዚአብሔርን የሚያሳስበው፣ የፈጠራቸው ሰዎች ነፃ መውጣት ነው። የጠፉ ልጆቹ እንዲገኙለት ይፈልጋል! ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ነገር የሌለ መሆኑን መስቀሉ ያረጋግጥልናል። አንድ ቀን እግዚአብሔር ፊት በመቆም፡- «ተልዕኮዬ ተከናውኗል» ለማለት ትችል ዘንድ «አንድ ተጨማሪ ሰው ለኢየሱስ የማዳን » ፍለጋህን እንድትቀ ጥል እጸልይልሃለሁ።

ሠላሳ ስድስተኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡ - የተበጀሁት ለተልዕኮ ነው።

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡- *«ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው። እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ»* ማቴ. 28፥19-20።

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር የሰጠኝን ተልዕኮ እንዳልፈጽም ያገዱኝ ፍርሃቶች ምንድናቸው? መልካሙን የምሥራች ለሌሎች እንዳ ልነግር የሚያደርገኝስ ምንድነው?

# 37

# የሕይወት መልእክትህን ማካፈል

*በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለው።*

*1ዮሐ. 5፥10*

*... የጌታ ቃል ከእናንተ ወጥቶ በመቄዶንያና በአካይያ መሰማቱ ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ያላችሁ እምነት በሁሉ ቦታ ታውቆአል፤ ስለዚህ እኛ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም መናገር አያስፈልገንም።*

1ተሰ. 1፥8

ልታካፍለው የሚገባ የሕይወት መልእክት እግዚአብሔር ሰጥቶሃል። አማኝ በሆንህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክተኛም ሆነሃል። እግዚአብ ሔር በአንተ በኩል ለዓለም ለመናገር ይፈልጋል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡- «*ከእግዚአብሔር እንደተላኩ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን*» 2ቆሮ. 2፥17። የምታካፍለው ምንም እንደሌለህ ታስብ ይሆ ናል። ይህ ግን ሰይጣን ዝም ሊያሰኝህ የሚያደርገው ሙከራ ነው። እግዚአብሔር ሌሎችን ወደ ራሱ ቤተሰብነት ለማምጫነት ሊጠቀምባቸው የሚፈልጋቸው ብዙ የሕይወት ልምምዶች አሉህ። መጽሐፍ ቅዱስ እን ዲህ ይላል፡- «*በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለው*» 1ዮሐ. 5፥10። የሕይወት መልእክትህ አራት ክፍሎች አሉት፡

- የሕይወት *ምስክርነትህ*፡- ከኢየሱስ ጋር የሕይወት ግንኙነት የጀመርህበት ታሪክ
- ከሕይወት *ያገኘሃቸው ትምህርቶች*፡- እግዚአብሔር ያስተማረህ ወሳኝ ትምህርቶች
- *መንፈሳዊ ቅናትህ*፡- ይበልጥ ግድ እንድትሰኝበት እግዚአብሔር አንተን የቀረፀበት ጉዳይ

• *የምሥራቹ ቃል፡- የድነት መልእክት*

**የሕይወት መልእክትህ ምስክርነትህንም ያካትታል፡፡** ምስክርነትህ ክርስቶስ በሕይወትህ ያመጣውን ለውጥ የሚተርክ ነው፡- «*እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣ ለራሱ የተ ለያችሁ ሕዝብ ናችሁ*» 1ጴጥ. 2÷9፡፡ የምስክርነት ፍሬ ነገር ይህ ነው፤ ጌታን በሚመለከት በግል የተለማመድከውን ማካፈል፡፡ ፍርድ ቤት ውስጥ የሚመሰክር ሰው ስለ ጉዳዩ እንዲከራከር፣ እውነቱን እንዲያረጋግጥ፣ የብያኔ ግፊት እንዲያደርግ አይጠበቅበትም፤ ይህ ሁሉ የጠበቃ ሥራ ነው፡፡ ምስክ ሮች የሚጠበቅባቸው፣ የደረሰባቸውን ወይም ያዩትን መናገር ብቻ ነው፡፡

*የምትመሰክራቸው ታሪኮች ኢየሱስ ክርስቶስ ከአንተ ልብ ወደ ሌሎች የሚሸጋገርበትን ድልድይ ይሠራሉ፡፡*

ኢየሱስ «*ምስክሮቼ ትሆናላችሁ*» የሐዋ. 1÷8 አለ እንጂ፣ «ጠበቃዎቼ ትሆናላችሁ» አላለም፡፡ ታሪክህን ለሌሎች እንድታካፍል ይፈልጋል፡፡ የምታካፍለው ምስክርነት፣ ልዩ ከመሆኑም በላይ፣ የምድራዊ ተልዕኮህ ጠቃሚ ክፍል ነው፡፡ የአንተን የሚመስል ሌላ ታሪክ የለም፤ በመሆኑም ልታካፍለው የምትችለው አንተ ብቻ ነህ ፡፡ ካላካፈልከው ለዘላለም ጠፍቶ ይቀራል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር ባትሆንም እንኳን ስለ ሕይወትህ ሙሉ እውቀት አለህ፤ በሕይወት ልምድ ላይ ክርክር መክፈትም አስቸጋሪ ነው፡፡ የሕይወት ምስክርነትህ ከስብከት ይበልጣል፡፡ ምክንያቱም ያላመኑ ሰዎች ፖስተሮችን (መጋቢዎች) እንደ የሽያጭ ባለሙያዎች፣ አንተን ደግሞ በተሰጠው አገልግሎት «እንደረካ ደንበኛ» ስለሚቆጥሯችሁ፣ ይበልጥ ያምኑሃል፡፡

ከመመሪያዎች ይልቅ የሕይወት ታሪክን መረዳት ይቀላል፣ ሰዎችም የግል ታሪኮችን መስማትን ይወዳሉ፡፡ የግል ታሪኮች ትኩረታችንን ይስባሉ፣ ለረጅም ጊዜም እናስታውሳቸዋለን፡፡ ሥነ-መለኮታውያን የሆኑ ሰዎችን እየጠቀስክ በምትናገርበት ጊዜ፣ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች የመስማት ፍላጎታቸው ይቀዘቅዝ ይሆናል፤ ስለማያውቁት ልምምድ የመስማት ተፈጥሯዊ ጉጉት ግን አላቸው፡፡ የምትመሰክራቸው ታሪኮች፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአንተ ልብ ወደ ሌሎች የሚሸ ጋገርበትን ድልድይ ይሠራሉ፡፡

ግላዊ ምስክርነትህን የመናገርህ ሌላ ጥቅም፣ በአእምሮ የሚሠሩ የሙግት መከላከያዎችን ገለል የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን የማይቀበሉ ብዙ ሰዎች፣ ትሁት የሆነ ግለ ታሪክን ያደምጣሉ፡፡ ለዚህ ነው

ጳውሎስ በስድስት የተለያዩ አጋጣሚዎች ወንጌልን ለማ ካፈል ከመጽሐፍ ቅዱስ ከመጥቀስ ይልቅ በግላዊ ምስክርነቱ የተጠቀመው የሐዋ. 22÷26::

**ሠላሳ ሰባተኛ ቀን**

**የሕይወት መልእክትህን ማካፈል**

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያት ስለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁል ጊዜ የተ ዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን፣ ይህን ሁሉ በትህትናና በአክብሮት አድርጉት»* 1ጴጥ. 3+15:: «የተዘጋጀን» ለመሆን ተመራጩ መንገድ፣ ምስክርነቶችህን መጻፍና ዋና ዋናዎቹን ነጥቦች ማጥናት ነው:: ቀጥሎ ባለው ሁኔታ በአራት ክፈለው:-

1. ኢየሱስን ከማግኘቴ በፊት ሕይወቴ ምን ይመስል እንደነበር
2. ኢየሱስ የሚያስፈልገኝ መሆኑን እንዴት እንደተረዳሁ
3. ሕይወቴን ለኢየሱስ እንዴት እንደሰጠሁት
4. ኢየሱስ በሕይወቴ ያመጣው ለውጥ

እርግጥ ከድነት ታሪክህ በተጓዳኝ ሌሎች ብዙ ምስክርነቶች አሉህ:: እግዚአብሔር ለረዳህ ለእያንዳንዱ ልምድ አንድ ታሪክ አለህ:: እግዚአብሔር ያሳለፈህን ችግሮች፣ ሁኔታዎችና ውጣ ውረዶች ሁሉ በዝርዝር መያዝ አለብህ:: ከዚያም ሁኔታዎችን በጥንቃቄ እያጠናህ አማኝ ያልሆነ ወዳጅህ ከሕይወቱ ጋር በሚያዛምድበት ሁኔታ ታሪኮቹን ተጠቀምባቸው:: የተለያዩ ሁኔታዎች የተለያዩ ምስክርነቶችን ይፈልጋሉ::

**የሕይወት መልእክትህ ከሕይወትህ ያገኘሃቸውን ትምህርቶች ያካትታል::** የሕይወት መልእክቶችህ ሁለተኛ ክፍል፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ባደ ረግኸው ጉዞ ያስተማረህ ልምምዶች ናቸው:: እነዚህም ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ግንኙነቶች፣ ችግሮች፣ ፈተናዎችና ልዩ ልዩ የሕይወት ሁኔታዎች ያገኘ ሃቸው ትምህርቶችና መረዳቶች ናቸው:: ዳዊት እንዲህ በማለት ጸለየ:- *«የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ፤ እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ »* መዝ. 119÷39:: የሚያሳዝነው ነገር፣ በሕይወታችን ከሚደርሱ ነገሮች ብዙም የማንማር መሆናችን ነው:: ስለ እስራኤላውያን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«እርሱ ብዙ ጊዜ ታደጋቸው፤ እነርሱ ግን አመፃን ሙጥኝ አሉ፣ በኃጢአ ታቸውም ተዋረዱ»* መዝ. 106+43:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ገጥመውህ ይሆናል::

ከራስህ ሕይወት ተሞክሮ መማር አዋቂነት ሲሆን፣ ከሌሎች የሕይወት ተሞክሮ መማሩ ደግሞ የበለጠ አዋቂነት ነው:: ሁሉንም ነገር ከመከራና ስሕተት የምንማርበት በቂ የሕይወት ዘመን የለንም:: መጽሐፍ ቅዱስ:- *«የጠቢብ ሰው ዘለፋ ለሚሰማ ጆሮ እንደ ወርቅ ጉትቻ ወይም ጥሩ የወርቅ ጌጥ*

*ክራስህ የሕይወት ተሞክሮ መማር ስዋቂነት ሲሆን፣ ከሌሎች የሕይወት ተሞክሮ መማሩ ደግሞ የበለጠ ስዋቂነት ነው::*

ነው » ምሳሌ 25÷12 ይለናል:: ዋና ዋና የሕይወት ትምህርቶቹ ናቸው የምትላቸውን ለሌሎች ለማካፈል ትችል ዘንድ ጻፋቸው:: ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ስላደረገልን ሊደነቅ ይገባል:: የሕይወት ትምህ ርቶቹን ከመጻፉ የተነሣ ይሄው መጽሐፈ ምሳሌንና መክብብን ለማግኘትቻልን፤ መጻሕፍቱ ተግባራዊ የሕይወት ተመክሮዎች የሞሉባቸው ናቸው:: እያንዳን ዳችን ከሌሎቻችን ለመማር ብንችል ኖሮ፣ ስንት ተስፋ መቁረጦች ወይም ሀዘኖች ይወገዱ እንደ ነበር ለመገመት ትችላለህ::

በሳል ሰዎች ከእያንዳንዱ የሕይወት ልምምዳቸው ትምህርትን የመቅሰም ልምድ ያዳብራሉ:: እኔም ከሕይወትህ ያገኘሃቸውን ትምህርቶች በዝርዝር እንድትጽፋቸው አበረታታሃለሁ:: በዝርዝር ካልጻፍካቸው በቀጡ አላሰባሰብ ካቸውም ማለት ነው:: በሕይወት ትውስታህ ውስጥ ለመንደርደርና ለመነሻነት የሚረዱህ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና ጥያቄዎች እነሆ፣ መዝ. 51፤ ፊልጵ. 4÷11-13፤ 2ቆሮ. 1÷4-10፤ መዝ. 119+71፤ ዘፍ. 50÷20::

- ከውድቀቴ እግዚአብሔር ያስተማረኝ ምንድነው?
- ገንዘብ ከማጣቴ እግዚአብሔር ያስተማረኝ ምንድነው?
- እግዚአብሔር ከሀዘን፣ ከስቃይና ከተጎዳ ስሜት ያስተማረኝ ምንድነው?
- እርሱን በመጠበቅ አማካይነት እግዚአብሔር ምን አስተማረኝ?
- በሕመሜ አማካይነት እግዚአብሔር ምን አስተማረኝ
- ከቅሬታ እግዚአብሔር ምን አስተማረኝ?
- ከቤተሰቤ፣ ከቤተ ክርስቲያኔ፣ ከሰዎች ጋር ካለኝ ግንኙነት፣ ከትንንሽ ቡድኖች እንዲሁም ከሚተቹኝ ሰዎች ምን ተማርሁ?

**የሕይወት መልእክትህ ከእግዚአብሔር ያገኘኸውን መንፈሳዊ ቅንዓት ማካፈልንም ያካትታል::** እግዚአብሔር በጣም ጥልቅ ስሜት ያለው አምላክ ነው:: አንዳንድ ነገሮችን በጣም ይወዳቸዋል፣ ሌሎችን ደግሞ በጣም ይጠላ ቸዋል:: ወደ እርሱ በቀረብክ ቁጥር፣ በዓለም ላይ የእርሱ ወካይና ተናጋሪ ትሆን ዘንድ፣ በጥልቅ ስለሚወዳቸው ወይም ስለሚፈልጋቸው ነገሮች የጋለ ስሜት እንዲያድርብህ ያደርጋል:: ይህም ጥልቅ ስሜት ስለ አንተ ችግር፣ ዓላማ፣ መርህ ወይም ስለ ተወሰኑ ሰዎች ሊሆን ይችላል:: ምንም ይሁን ምን ስለዚያ ነገር ለመናገርና ለውጥ ይመጣ ዘንድ የምትችለውን ሁሉ እንድታደርግ

ግድ ይልሃል።

በጣም ስለምትወደው ወይም ግድ ስለሚልህ ነገር ከመናገር ልትቆጠብ አትችልም። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- *«በልብ ውስጥ የሞላውን እንደበት ይናገረዋል»* ማቴ. 12÷34። ሌሎች ሁለት ምሳሌዎችም አሉ። ዳዊት እንዲህ ይላል:- *«የቤትህ ቅናት በላችኝ፣ የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ለልፎለል»* መዝ. 69÷9። ኤርሚያስ ደግሞ:- *«ከእንግዲህ የእርሱን ስም አላነሣም፣ በስሙም አልናገርም ብል፣ ቃሉ በልበ እንደ እሳት በአጥንቴም ውስጥ እንደረመጥ ሆነብኝ »* ኤር. 20÷9 ብሏል።

አንዳንድ ሰዎች አንድን በጐ ዓላማ እንዲያራምዱ እግዚአብሔር ልዩ መንፈሳዊ ቅንዓት ይሰጣቸዋል። ይህም ሰዎቹ በግላቸው ካለፉበት ትግል፣ ለምሳሌ በሰዎች መጠቃት፣ ሱስ፣ መካንነት፣ ሀዘን ወይም በሽታ የመሳሰለ ችግር ይሆን ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር፣ ስለ ራሳቸው ለመናገር የማይችሉ ሰዎችን ወክለው ይናገሩ ዘንድ፣ በሰዎች ላይ ፍላጎትን ያሳድራል። ገና ላልተወለዱ፣ መከራ ለሚደርስባቸው ሰዎች፣ ለድሆች፣ ለእሥረኞች፣ ግፍ ለሚደርስባቸው፣ ላልታደሉ፣ እና ፍትህ ላጡ ሰዎች እንዲሟገቱ ያደርጋቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ደካሞችን መከላከል የሚገባ መሆኑን በሚያስገነዝቡ ትእዛዛት የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋፋት ጥልቅ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች ይጠቀማል። አዳዲስ አብያተ ክርስቲያን ለመመሥረት፣ ቤተሰብን ለማጠናከር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራዎችን ለማገዝ ወይም የቤተክርስቲያን መሪዎችን ለማሰልጠን የጋለ መሻት ይሰጥህ ይሆናል። የተለያዩ ሰዎችን፣ ማለት ነጋዴዎችን፣ ወጣቶችን፣ ለትምህርት የመጡ የውጭ ተማሪዎችን፣ ወጣት እናቶችን፣ ስፖርተኞችን ወይም ትርፍ ጊዜያቸውን በአንድ ጉዳይ ላይ የሚያሳልፉ ሰዎችን እንድታገለግል ሸክም ይሰጥህ ይሆናል። እግዚአብሔርን ብትጠይቀው፣ ጠንካራ ክርስቲያናዊ ምስክርነት የሚያስፈልገውን አንድ አገር ወይም ብሔረሰብ የማገልገል ሸክም ይሰጥሃል።

> *እግዚአብሔር በዓለም እንዲፈጸም የሚፈልገው ነገር ሁሉ ይከናወን ዘንድ የተለየ የአገልግሎት ሸክምን ይሰጠናል።*

እግዚአብሔር በዓለም እንዲፈጸም የሚፈልገው ነገር ሁሉ ይከናወን ዘንድ የተለየ የአገልግሎት ሸክምን ይሰጠናል። ሰው ሁሉ አንተ የሚሰማህ ሸክም ይሰማዋል ብለህ መጠበቅ አይገባህም። ከዚያ ይልቅ አንድ ሰው የሚኖረው ነገር ሌላው ስለማይኖረው፣ እንዳችን የሌላችንን የሕይ

ወት መልእክት ልናደምጥና ዋጋ ልንሰጠው ይገባል። ለሌላ ሰው ከእግዚአ ብሔር የተሰጠውን ሽክም በፍጹም ዝቅ አድርገህ አትመልከት። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«ለበገ እስከሆነ ደረስ ተቀርቋሪ መሆን መልካም ነው»* ገላ. 4፥18።

የሕይወት መልእክትህ የምሥራቹን ቃል (ወንጌልን)፣ ያካትታል። የምሥራቹ ቃል ምንድነው? *«በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፣ ጽድቁም ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በእምነት የሆነ ነው»* ሮሜ 1፥17። *«እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቆጥ ርባቸውም ነበር፣ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን» 2ቆሮ. 5፥19።* የምሥ ራቹ ቃል፣ ለእኛ መዳን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠንን ጸጋ በም ናምንበት ጊዜ፣ ኃጢአታችንን ይቅር ተባልን፣ ለሕይወታችን ዓላማ አገኘን፣ በሰማይ የመኖር ተስፋም ተሰጠን የሚለው ነው።

የምሥራቹን ቃል የማካፈል ዘዴን የሚያስረዱ ብዙ መጻሕፍት አሉ። ነገር ግን ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ የተገለጡትን ስምንት አሳቦች ከራስህ ጋር እስካላዋሀድካቸው ድረስ፣ በዓለም ያሉ ሥልጠናዎች ሁሉ እንኳን ስለ ክርስቶስ እንድትመሰክር ሊያነሣሱህ አይችሉም። ከሁሉም ይልቅ፣ እግዚአብሔር እንደ ወደዳቸው ኃጢአተኞችን መውደድን ተማር።

እግዚአብሔር የማይወደውን ሰው ፈጥሮ አያውቅም። ማንኛውም ሰው ለእርሱ ክቡር ነው። ኢየሱስ እጆቹን በመስቀል ላይ ግራና ቀኝ በዘረጋቸው ጊዜ፡- «ይህን ያህል እወድሃለሁ» ማለቱ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-*«የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል፣ ምክንያቱም፣ አንዱ ስለ ሁሉ እንደሞተ እርገጠኞች ሆነናል ...»* 2ቆሮ. 5፥14። በዚህ ዓለም ስላለህ ተልዕኮ ሽክም አልሰማህ ባለ ቁጥር፣ ኢየሱስ ስለ አንተ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ሥራ በማሰብ ጥቂት ጊዜ አሳልፍ።

እግዚአብሔር ላላመኑ ሰዎች ግድ ስለሚለው፣ እኛም ስለ እነርሱ ግድ ሊለን ይገባል። ፍቅር በመምረጥ አይሆንም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«በፍቅር ፍርሃት የለም፣ ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል»* 1ዮሐ. 4፥18። ወላጆች የልጆቻቸውን ሕይወት ለማዳን በመቃጠል ላይ ወደ አለ ህንፃ እሮጠው ይገ ባሉ። ይህን የሚያደርጉት፣ ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ከፍርሃታቸው ስለሚበልጥ ነው። በዙሪያህ ላሉ ሰዎች መልካሙን የምሥራች ቃል ለማካፈል የምትፈራ ከሆንክ፣ ለነሱ ባለው ፍቅሩ ይሞላህ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይቀው።



መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*ማንም እንዳይጠፋ፥ ሁሉ ለንስሐ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሣል*» 2ጴጥ. 3÷9:: ክርስቶስን የማያውቅ አንድ ሰው የምታውቅ ከሆነ፣ በፍቅር እያገለገልከውና መልካሙን የምሥራች እያካፈልከው ሳታቋርጥ ልትጸልይለት ይገባል:: የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ያልሆነ አንድ ሰው እንኳን በማህበረሰብህ ውስጥ ካለ፣ ቤተክርስቲያንህ መልካሙን የምስራች በማድረስ ረገድ ሳታቋርጥ መሥራት አለባት:: ለማደግ የማትፈልግ ቤተክርስቲያን ዓለምን ምን ቸገረኝ:- «ወደ ሲኦል ግቢ» በማለት ላይ ናት::

የምታውቃቸው ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ዘንድ ምን ለማድረግ ፈቃደኛ ነህ? ወደ ቤተክርስቲያንህ ትጋብዛቸዋለህ? ታሪክህን ትነግራቸዋለህ? ይህን መጽሐፍ ትሰጣቸዋለህ? ምሳ ትጋብዛቸዋለህ? ድነትን እስኪያገኙ ድረስ ትጸልይላቸዋለህ? የተልዕኮህ ሜዳ በዙሪያህ ነው ያለው:: እግዚአብሔር የሚሰጥህ ዕድል አያምልጥህ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «*በውጭ ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ ተመላለሱ፤ በተገኘውም ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ*» ቆላ. 4÷5::

ባንተ ምክንያት መንግሥተ ሰማያት የሚገባ ሰው አለን? መንግሥተ ሰማያት ከሚገቡ ሰዎች መካከል:- «ላመሰግንህ እፈልጋለሁ:: ስለ ወደድከኝና መልካሙን የምሥራች ስለ አካፈልከኝ ነው እዚህ የተገኘሁት» የሚልህ ሰው ይኖር ይሆን? መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ የረዳሃቸውን ሰዎች እዚያ ስታገኛቸው የሚጠብቅህን ደስታ ገምት:: የአንድ ሰው ዘላለማዊ ድነት በሕይወት ዘመንህ ልታከናውን ከምትችለው ሌላ ነገር ሁሉ የላቀ ፋይዳ አለው:: ዘላለም የሚኖሩ ሰዎች ብቻ ናቸው::

እግዚአብሔር ለምድራዊው ሕይወትህ ያለውን አምስት ዓላማዎች በዚህ መጽሐፍ ተምረሃል:: የቤተሰቡ አባል፣ የባሕርዩ ሞዴል፣ የክብሩ መገለጫ፣ የፀጋው አገልጋይ፣ እና የእርሱን መልካም የምሥራች ለሌሎች የምታደርስ መልእክተኛ እንድትሆን ፈጥሮሃል:: ከነዚህ ዓላማዎች በምድር ላይ ብቻ የሚከናወነው አምስተኛው ነው:: የቀሩት አራቱ በአንዳንድ ሁኔታዎች በዘላለም ውስጥ ይቀጥላሉ:: ለዚህ ነው መልካሙን የምሥራች ማሠራጨቱ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው:: የሕይወት መልእክትህን ለማካፈያና ተልዕኮህን ለመፈፀሚያ ያለህ ጊዜ አጭር ነው::

## ሠላሳ ሰባተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ላስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:-** እግዚአብሔር በኔ ዓማካይነት ለዓለም አንድ ነገር ለመናገር ይፈልጋል።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:-** «*እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁል ጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን ይህን ሁሉ በትህትናና በአክብሮት አድርጉት*» 1ጴጥ. 3+15-16።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:-** መለስ ብዬ ያለፈ ታሪኬን ሳስብ ለማን ነው ያን እንዳካፍል እግዚአብሔር የሚፈልገው?

38

# ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን መሆን

*ኢየሱስ ተከታዮቹን እንዲህ አላቸው፣ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።»*

ማር. 16፥15

*መንገድህ በምድር ላይ፣ ማዳንህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል ይታወቅ ዘንድ።*

መዝ. 67፥2

ታላቁ ተልዕኮ ያንተ ተልዕኮ ነው።

አንድ ምርጫም አለህ። ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን ወይም ዓለማዊ ክርስቲያን መሆን።

ዓለማውያን ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የሚፈልጉት የግል ኑሯቸውን ለማሳካት ነው። አማኞች ቢሆኑም እራስ፣ ወዳዶች ናቸው። በመዝሙር ዝግጅቶችና በችሎታ ማዳበሪያ ሴሚናሮች ላይ መገኘትን ይወዳሉ። በሚስዮናዊ ሥራ ሴሚናሮች ላይ ግን በፍፁም አታገኛቸውም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለ ነገር አይወዱም። ጸሎቶቻቸው የሚያተኩሩት በፍላጎቶቻቸው፣ በበረከቶቻቸውና ደስታቸው ላይ ነው። «ቅድሚያ እኔ»፣ እንዴት ነው እግዚአብሔር ሕይወቴን ይበልጥ ምቹ የሚያደርገው የሚል ነው እምነታቸው። የእግዚአብሔር ዓላማ መገልገያ ከመሆን ይልቅ፣ እርሱን ለዓላማቸው ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ።

በተነፃፃሪው ደግሞ፣ ለዓለም ጠቃሚ የሆኑ ክርስቲያኖች ድነትን ያገኙትና የተሠሩት ለአገልግሎት፣ እንዲሁም ለተልዕኮ መሆኑን ያውቃሉ። የግል ተልዕኮ ለመቀበል ይጓጓሉ፤ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው ሰዎች የመሆን ዕድል ሲያገኙም ደስተኞች ናቸው። በምድር ላይ ሙሉ ህያውነት ያላቸው ሰዎች ለዓለም ጠቃሚ የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው። ለውጥ እንደሚያመጡ ስለሚያውቁ ደስታቸውን፣ ልበ ሙሉነታቸውንና

ትጋታቸውን ወደ ሌሎች ያስተላልፋሉ። ይህን የሚያደርጉት እነዚህ ባህሪያት ለውጥ የሚያመጡ መሆናቸውን ስለሚያውቁ ነው። በየማለዳው የሚነቁትም በዕለቱ እግዚአብሔር በአዲስ መንገድ የሚጠቀምባቸው መሆኑን በመጠበቅ ነው። የትኛውን ዓይነት ክርስቲያን ነው ለመሆን የምትፈልገው?

እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከሁሉ ትልቁ፣ ሰፊው፣ ባለ ብዙ ፈርጅና በጣም ጠቃሚ በሆነ ዓላማው፣ ማለት በመንግሥቱ ሥራ፣ እንድትካፈል ይጋብዝሃል። ታሪክ የእርሱ ሥራ ነው። ዘላለማዊ የሆነ ቤተሰቡን በመገንባት ላይ ነው። ከእግዚአብሔር መንግሥት ይበልጥ ዋጋ ያለውና ዘላለማዊ ነገር የለም። ዓለም አቀፉ የእግዚአብሔር ተልዕኮ የሚፈጸም መሆኑን ከራዕይ መጽሐፍ እንረዳለን። አንድ ቀን ታላቁ ተልዕኮ ታላቅ ፍጻሜ ያገኛል። አንድ ቀን *«ከቋንቋ ሁሉ ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ»* ራዕይ 5፥9፣ የሆኑ ብዙ ሕዝቦች፣ በመንግሥተ ሰማያት ለኢየሱስ ለመስገድ እፊቱ ይቆማሉ። ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን በመሆን የምታደርገው ተሳትፎ፣ የመንግሥተ ሰማያትን ምንነት በቅድሚያ በጥቂቱ የመለማመድ ዕድል ይሰጥሃል።



ኢየሱስ፣ ተከታዮቹን *«በዓለም ዙሪያ ሁሉ ሄደው መልካሙን የምሥራች ለሰዎች እንዲያውቁ»* በነገራቸው ጊዜ፣ እነዚያ ጥቂትና ድሀ የመካከለኛው ምሥራቅ ደቀ መዛሙርት ግራ ተጋብተው ነበር። በእግራቸው ሊጓዙ ነው፣ ወይስ በእንስሳት ጀርባ? የነበራቸው መጓጓዣ ያ ብቻ ነበር። ውቂያኖስ የሚያቋርጡ መርከቦች አልነበሩም። በመሆኑም ወደ ዓለም ሁሉ ለመሄድ የአቅም ችግር ነበረባቸው።

ዛሬ አይሮፕላኖች፣ መርከቦች፣ ባቡሮች፣ አውቶቡሶችና አውቶሞቢሎች አሉን። ዓለማችን ሥልጣኔ ካፈራቻቸው መገናኛዎች የተነሣ አንሳለች፣ በየቀኑም በማነስ ላይ ናት። አስፈላጊ ከሆነ፣ በሰዓታት በሚቆጠር ጊዜ ውቅያኖስን በበረራ አቋርጠህ ከተጓዝህ በኋላ በሚቀጥለው ዕለት ወደ ቤትህ ለመመለስ ትችላለህ። ባለንበት ጊዜ፣ በማንኛውም የአጭር ጊዜ ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ተልዕኮ (ሚሽን) ውስጥ ለመሳተፍ ያለው ዕድል ፍፁም ገደብ የለሽ ነው። የጉዞ ወኪሎችን ብቻ ጠይቅ፤ የትኛውም የዓለም ማዕዘን ቅርብህ ነው። መልካሙን የምሥራች ላለማሠራጨት የምናቀርበው ምንም ምክንያት የለንም።

የመረጃ መረብ (ኢንተርኔት)፣ በተግባር ላይ በዋለበት በአሁኑ ጊዜ ዓለም ከመቼውም ይልቅ አንሳለች። ከስልክና ፋክስ በተጨማሪ፣ ኢንተርኔት መረብ ውስጥ የመግባት እድል ያላቸው ክርስቲያኖች በዓለም ባሉ አገሮች ከሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ። በዓለም አካባቢ ካሉ ሰዎች ጋር ለመገና

ኘት የምትችልበት ዕድል እጅህ ውስጥ ሆኗል።

እሩቅ ያሉ ብዙ መንደሮች እንኳን በኢሜይል የሚተላለፉ መልእክቶችን ይቀበላሉ። በመሆኑም ከቤትህ ሳትወጣ በሌላው የዓለም ክፍል ካለ ሰው ጋር *ስለ ወንጌል ለመነጋገር* ትችላለህ! ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ተልዕኮን ለመወጣት ቀላል የሆነበት ጊዜ እንደ አሁኑ በታሪክ አልነበረም። ትላልቆቹ ችግሮች የርቀት፣ የገንዘብ ወይም የመጓጓዣ አይደሉም። ብቸኛው ችግር *አስተሳሰባችን ነው።* ለዓለም የምትጠቅም ክርስቲያን ለመሆን ትችል ዘንድ፣ አንዳንድ የአስተሳሰብ ለውጦች ማድረግ ይኖርብሃል። አተያይና ዝንባሌህ መለወጥ አለባቸው።

## ለዓለም ጠቃሚ እንደሆነ ክርስቲያን ለማሰብ የሚቻለው እንዴት ነው?

አስተሳሰብህን ራስህ ላይ ያማከለ ከማድረግ፣ ሌላ ላይ ያማከለ አድርገህ ለውጠው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «*ወንድሞች ሆይ በአስተሳሰባችሁ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፋ ነገር ሕፃናት ሁኑ፤ በአስተሳሰባችሁ ግን ጉልማሶች ሁኑ*» 1ቆሮ. 14፥20። ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን ለመሆን ይህ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ሕፃናት ለራሳቸው ብቻ ነው የሚያስቡት፤ ጉልማሶች ግን ስለሌሎች ያስባሉ። እግዚአብሔር እንዲህ በማለት አዟል፦ «*እያንዳንዳችሁ ለሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ እራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ*» ፊልጵ. 2፥4።

> *ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ተልዕኮን ለመወጣት፣ ቀላል የሆነበት ጊዜ እንደ አሁኑ በታሪክ አልነበረም።*

እርግጥ፣ እንዲህ ያለው የአስተሳሰብ ለውጥ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም፣ በተፈጥሯችን ለራሳችን የምናደላ ነን። ሰዎች በማስታወቂያዎች የሚያበረታቱንም ስለ ራሳችን እንድናስብ ነው። እንዲህ ያለውን አካሄድ በመተው፣ ፍፁም የአቅጣጫ ለውጥ ለማድረግ የምንችለው፣ ያለ ማቋረጥ በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ብቻ ነው። እርሱ ብቻችንን እንድንታገል አይተወንም፦ «*ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ፣ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤ ይህም እግዚአብሔር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው*» 1ቆሮ 2፥12።

ካላመኑ ሰዎች ጋር በምትወያይበት ጊዜ ሁሉ፣ ስለ መንፈሳዊ ፍላጎታቸው ለማሰብ ይረዳህ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ጠይቅ። ለሚገጥሙህ ሰዎች በጸጥታ የመጸለይ ልምድ ልታዳብር ትችላለህ። «አባት ሆይ ይህ ሰው አንተን እንዳያ

ውቅ የሚከለክለው ነገር ምን መሆኑን እንዲረዳ አደርገው ዘንድ እርዳኝ» በል::

ዋና አሳብህ፣ ሌሎች በመንፈሳዊ ጉዟቸው የደረሱበትን መረዳትና፣ ክርስቶስን ወደ ማወቅ አንድ እርምጃ እንዲቀርቡ የሚያደርጋቸውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ነው:: ይህን የምታከናውንበትን ዘዴ ከጳውሎስ አስተሳሰብ ልትማርና ልታዳብር ትችላለህ:: እንዲህ ብሏል ጳውሎስ:- *«እኔ ሰውን ሁሉ በማንኛውም ረገድ ለማስደሰት እንደምጥር፣ እናንተም እንዲሁ አድርጉ:: ብዙዎች ይድኑ ዘንድ፣ ለራሴ የሚጠቅመውን ሳይሆን ለእነርሱ የሚጠቅመውን እሻለሁና»* 1ቆሮ. 10+33::

አስተሳሰብህን ከአጥቢያዊ ወደ ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ ለውጥ:: እግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ አምላክ ነው:: ሁልጊዜ ለመላው ዓለም ያስባል:: *«... ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና»* ዮሐ. 3+16:: እግዚአብሔር ከመጀመሪያ አንስቶ ከፈጠረው ሕዝብ ሁሉ የቤተሰብ አባላት የሚያደርጋቸውን ሰዎች ይፈልግ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውንም ልክና የመኖሪያ ሥፍራቸውንም ዳርቻ ወሰነላቸው:: ይኸውም ሰዎች እግዚአብሔርን ፈልገው ተመራምረው ምናልባት ያገኙት እንደሆነ ብሎ ነው፤ ይህም ቢሆን፣ እርሱ ከእያንዳንዳችን የራቀ ሆኖ አይደለም»* የሐዋ. 17+26-27::

አብዛኛው የዓለም ክፍል ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ አለው:: ግዙፎቹ የመገናኛ ብዙሃንና የንግድ ድርጅቶች ሁሉ የተለያዩ አገሮች የጋራ ሀብቶች ናቸው:: አለባበሶችን፣ መዝናኛዎችን፣ ሙዚቃን፣ እስፖርቶችንና በፍጥነት የሚዘጋጁ ምግቦችን እንኳን ሳይቀር በምንጋራበት ጊዜ፣ ይህን አብረናቸው ከምናደርግባቸው አገሮች ጋር ሕይወታችን ይበልጥ እየተጣመረ ይሄዳል:: ከምትለብሳቸው ልብሶችና ከምትመገባቸው ምግቦች ብዙዎቹ ምናልባት በሌላ አገር የተፈበረኩ ናቸው:: ከምንገነዘበው በላይ ተያይዘናል::

> ሠላሳ ስምንተኛ ቀን
> ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን መሆን

እንዲህ ባለው ጊዜ በሕይወት መኖራችን ደስ ያሰኛል:: ከቀደሙት ዘመናት ይልቅ ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች በምድር ላይ አሉ:: ጳውሎስ እንዲህ ማለቱ ትክክል ነበር :- *«ይህም ወደ እናንተ ደርሶአል:: ይህንም ወንጌል ከሰማችሁበትና የእግዚአብሔርን ፀጋ እውነት ከተረዳችሁበት ቀን ጀምሮ በዓለም ዙሪያ እየሠራ እንዳለ ሁሉ በእናንተም ዘንድ ፍሬ እያፈራና እያደገ ነው»* ቆላስ. 1÷6::

ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብን የምትጀምሪው፣ ለተወሰኑ አገሮች በመጸለይ ነው:: ለዓለም ጠቃሚ የሆኑ ክርስቲያኖች ለዓለም ይጸልያሉ:: አንድ ሉል ወይም የዓለም ካርታ ያዝና ስማቸውን እየጠቀስክ ለአገሮች ጸልይ:: መጽሐፍ

ቅዱስ እንዲህ ይላል:- *«ለምነኝ፤ መንግሥታትን ርስት አደርገ የምድርንም ዳርቻ ግዛት እንዲሆንህ እሰጥሃለሁ»* መዝ. 2+8::

ጸሎት፣ በዓለም ላለህ አገልግሎት እጅግ ጠቃሚ መሣሪያ ነው:: ሰዎች ፍቅራችንን አይቀበሉ፣ መልእክታችንንም እምቢ ይሉ ይሆናል:: ጸሎታችን ለሚያሳድርባቸው ተጽእኖ ግን ምንም መከላከያ የላቸውም:: ከምትፀልይለት ሰው ያለህ እርቀት ሁለት ሜትር ቅርብ ወይም በአሥር ሺህ ማይሎች የሚ ርቅ ቢሆንም፣ ጸሎትህን እንደ አህጉር አቋራጭ ሚሳይል ሰውዬው ልብ ላይ ልታነጣፅር ትችላለህ::

ስለምን መጸለይ ይኖርብናል? የመመስከር ዕድል ስለምናገኝባቸው ሁኔታ ዎች፣ ቈላስያስ 4+3፤ ሮሜ 1+10፤ የመናገር ድፍረት እንዲኖረን፣ ኤፌ. 6+19፤ የሚያምኑ ሰዎች እንዲገጥሙን፣ ዮሐ. 17+20፣ መልእክቱ በፍጥነት እንዲሠራጭ፣ 2ተሰ. 3+1፤ እና ስለ ሠራተኞች እንድንጸልይ መጽሐፍ ቅዱስ ያሳስበናል፣ ማቴ. 9+38:: ጸሎት በዓለም ዙሪያ ያሉ አገልጋዮች ማህበርተኛ ያደርግሃል::

በዓለም አቀፉ የመከር ሥራ ለተሠማሩ ሚሲዮናውያንና ሌሎች ሰዎችም መጸለይ አለብህ:: ጳውሎስ የጸሎት አጋሮቹን እንዲህ ብሏቸዋል:- *«እናንተ በጸሎታችሁ ደግፉኝ»* 2ቆሮ. 1+11::

*ሰዎች ፍቅራችንን አይቀበሉ፣ መልእክታችንንም እምቢ ይሉ ይሆናል፤ ጸሎታችን ለሚያሳድርባቸው ተጽዕኖ ግን ምንም መከላከያ የላቸውም::*

ዓለም አቀፍ አስተሳሰብን የማዳበሪያ ሌላው መንገድ፣ ዜናዎችን *«በታላቁ ተልዕኮ ዓይን»* ማንበብና መመልከት ነው:: ለውጥ ወይም ግጭት በሚኖርበት ጊዜ፣ እግዚአ ብሔር ሰዎችን ወደ ራሱ ለማምጫነት የሚጠቀምበት ስለመሆኑ እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ:: ሰዎች ውጥረት ሲገጥማቸው ወይም ከአንድ ነገር ወደ ሌላው በሽግግር ላይ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ከመቼውም ይልቅ ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ:: የዓለማችን የለውጥ ፍጥነት በመጨመር ላይ በመሆኑ፣ ሰዎች ከምን ጊዜም ይልቅ መልካሙን የምሥራች ለማድመጥ ዝግጁ ናቸው::

ወደ ዓለም አቀፍ አስተሳሰብ የመሸጋገሪያው ተመራጭ መንገድ፣ ለአጭር ጊዜ የሚሲዮናዊ አገልግሎት ወደ ሌላ አገር መሄድ ነው! ከግንዛቤ አኳያ ሌላ ባህል ውስጥ የሚገኝን እውነተኛ የሕይወት ልምድ የሚተካ ነገር የለም:: ስለ ተልዕኮህ ማጥናትና መወያየቱን አቁምና ወደ ድርጊት ተሸጋገር! ወደ ሥራው ጠልቀህ እንድትገባ አደፋፍርሃለሁ:: በአገልግሎቱ የምንሳተፍበትን ሁኔታ በተ መለከተ ኢየሱስ ሐዋ. 1+8 ውስጥ አንድ ምሳሌ ሰጥቷል:- *«በኢየሩሳሌም፣*

*በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»*:: ተከታዮቹ ለራሳቸው ሕዝብ (ኢየሩሳሌም)፣ ለአገራቸው (ይሁዳ)፣ ሌላ ባሕል ላላቸው ሕዝቦች (ሰማርያ)፣ እና ለሌሎች ሕዝቦች (በመላው ዓለም)፣ መልካሙን የምሥራች ማድረስ ነበረባቸው:: ተልዕኳችን በቅደም ተከተል ሳይሆን፣ አንድ ላይ የሚከናወን መሆኑን ልብ በል:: ሚሲዮናዊ ስጦታ ያለው፣ ሰው ሁሉ ባይሆንም፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከላይ ከተጠቀሱት አራት ሚሲዮናዊ ቡድኖች በአንድ ወይም በሌላ ሁኔታ እንዲሳተፍ ተጠርቷል:: የሐዋ. 1+8 ክርስቲያን ነህን?

በነዚህ አራት አቅጣጫዎች የተልዕኮ ተሳትፎ ለማድረግ ግብ ቅረፅ:: ወደ ሌላ አገር በሚደረግ አጭር ሚሲዮናዊ ጉዞ ለመሳተፍ በአስቸኳይ ገንዘብ ማጠራቀምና አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ እንድትጀምር አበረታታሃለሁ:: አብዛኛዎቹ ሚስዮናዊ ድርጅቶች ይህን እንድታደርግ ይረዱሃል:: በዚህ ሁኔታ መሳተፉ ልብህንና እይታህን ያሰፋዋል:: እምነትህን ያሳድገዋል፣ ርህራሄህን ጥልቅ ያደርገዋል፣ ከዚህ ቀደም በማታውቀው ደስታም ይሞላሃል:: በሕይወትህ የአቅጣጫ ለውጥ የሚመጣበት አጋጣሚም ሊሆን ይችላል::

«እዚህና አሁን» የሚል አስተሳሰብህን ወደ ዘላለማዊ አስተሳሰብ ለውጠው:: በምድር ባለህ ጊዜ በሚገባ ለመጠቀም፣ ዘላለማዊውን የአስተሳሰብ አቅጣጫ መከተል ይኖርብሃል:: እንዲህ ማድረግ፣ ለጥቃቅን ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት ከመስጠት ይጠብቅሃል:: አጣዳፊና ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅም ይጠቅምሃል:: ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- *«ዐይናችን የሚያተኩረው፣ በሚታየው ነገር ሳይሆን፣ በማይታየው ላይ ነው:: የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፣ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው»* 2ቆሮ. 4+18::

ዛሬ ጉልበታችንን የምናፈስባቸው ብዙዎቹ ነገሮች በዘላለማዊው ሕይወት ከሚገኘው ጠቀሜታ ጋር ሲነጻጸሩ፣ የአንድ ዓመት ፋይዳን ያህል እንኳ ጠቀሜታ የላቸውም:: ሕይወትህን በጊዜያዊ ነገር አታባክነው:: ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:- *«እርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም»* ሉቃስ 9+62:: ጳውሎስም እንዲህ የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል:- *«በዚህ ዓለም ነገር የሚጠቀሙም እንደማይጠቀሙበት ይሁኑ፤ የዚህ ዓለም መልክ አላፊ ነውና»* 1ቆሮ. 7+31:: በተልዕኮ መንገድህ ላይ እንቅፋት ሆኖ እንዲቆም የምትፈቅድለት ነገር ምንድነው? ለዓለም ጠቃሚ ክርስቲያን ከመሆን የሚያግድህ ምን ይሆን? ምንም ይሁን ምን አስወግደው:: «... *ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ»* ዕብ. 12+1:: ኢየሱስ:- *«በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ»*

*«ይዘኸው ልትሄድ አትችልም»*
*መጽሐፍ ቅዱስ ግን፣ ወደዚያ በሚሄዱ ሰዎች ላይ ገንዘብህን በማዋል፣ አስቀድመህ ልትልከው ትችላለህ ይላል::*

ማቴ. 6÷20፣ ብሏል:: ይህን እንዴት ለማድረግ እችላለን? ኢየሱስ፣ ብዙዎች በተሳሳተ ሁኔታ ከተረዷቸው ንግግሮቹ በአንደኛው እንዲህ ብሏል:- *«ስለዚህ እላችኋለሁ፣ የዚህ ዓለም ገንዘብ ባለቀ ጊዜ በዘላለም ቤት ተቀባይነት እንዲኖራችሁ በዚሁ ገንዘብ ወዳጆችን ለራሣችሁ አፍሩበት»* ሉቃስ 16÷9::

ለራስህ ወዳጆች «ግዛበት» ማለቱ አይደለም፣ ኢየሱስ:: እግዚአብሔር የሚሰጥህን ገንዘብ፣ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጫነት ተጠቀምበት ማለቱ ነው:: እነዚህ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማያት በምትሄድበት ጊዜ የሚቀበሉህ ዘላለማዊ ወዳጆች ይሆናሉ:: ይህን የመሰለው ሁኔታ መቼም ልታደርገው ከምትችለው የሚበልጥ ድንቅ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት ነው::

*«ይዘኸው ልትሄድ አትችልም»* የሚል አነጋገር ሰምተህ ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን፣ ወደዚያ በሚሄዱ ሰዎች ላይ ገንዘብህን በማዋል አስቀድመህ ልትልከው ትችላለህ ይላል! በተጨማሪም እንዲህ ይላል፣ *«በዚህ ዓይነት፣ እውነተኛ የሆነውን ሕይወት ያገኙ ዘንድ፣ ለሚመጣው ዘመን ጽኑ መሠረት የሚሆን ሀብት ለራሳቸው ያከማቻሉ»* 1ጢሞ. 6+19::

ከማመካኘት ይልቅ ተልዕኮህን ለመወጣት የሚያስችልህን፣ ዘዴ ለመፍጠር አስብ:: ፈቃደኛ ከሆንክ፣ ምንጊዜም የማድረጊያው መንገድ አለ፤ ሊረዱህ የሚችሉ ድርጅቶችም አሉ:: ተልዕኮን በተመለከተ ከሚቀርቡ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ቀጥሎ ያሉት ናቸው::

- *«የቋንቋ ችግር አለብኝ::»* ባለንበት ጊዜ ቋንቋዎችን ለመማር የሚረዱ ብዙ ዘዴዎችና ምቹ ሁኔታዎች አሉ::
- *«የምሰጠው ምንም የለኝም::»* አለህ እንጂ፤ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ በመልክህልህ ውስጥ ያሉ ችሎታዎችና ልምዶች በጥቅም ላይ የሚውሉበት ቦታ ይኖራል::
- *«በጣም አርጅቻለሁ፤(ወይም ልጅ ነኝ)::»* ብዙ የተልዕኮ ድርጅቶች ለዕድሜ የሚመጥኑ ፕሮግራሞች አሏቸው::

ሣራ አርጅቻለሁ ብትል፤ ኤርምያስም ገና ልጅ ነኝ ብሎ ቢያመካኝም፤ እግዚአብሔር ምክንያታቸውን አልተቀበለውም፤ *«ወደምልክህ ሁሉ ሄደህ ያዘዝሁህን ሁሉ ትናገራለህ፤ እኔ ስድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ»* ኤር. 1+7-8፣ ብሏል::

ምናልባት ከእግዚአብሔር ልዩ «ጥሪ» ያስፈልገኛል ብለህ በማመን አንዳች ልዕለ ተፈጥሯዊ ስሜት ወይም ልምምድ በመጠባበቅ ላይ ትገኝ ይሆናለህ። እግዚአብሔር ግን ጥሪውን አስቀድሞ በተደጋጋሚ ገልጧል። እርሱ ለሕይ ወታችን ያለውን አምስት ዓላማዎች ለመፈፀም ማለት፤ ልናመልከው፤ ህብረት ልንፈጥር፣ ክርስቶስን እንድንመስል፣ እንድናገለግልና ለዚህ ዓለም ተልዕኳችን ከእርሱ ጋር እንድንሠማራ ተጠርተናል። እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው የሚ ፈልገው፣ ከሕዝቡ በጥቂቶቹ ሳይሆን፣ በሁሉም ነው። ሁላችንም ለእግዚአ ብሔር ተልዕኮ እንድንሠማራ ተጠርተናል። የቤተክርስቲያኑ አካል የሆኑ አማኞች ሁሉ፣ የወንጌሉን የምሥራች ሁሉ፣ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲወስዱ ይፈልጋል፣ (ከሉዛን ቃል ኪዳን፣ 1974 የተወሰደ)።

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ያለውን ዓላማ ስተው ታል። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ወደ አንድ ሥፍራ ሄደው እንዲያገለግሉት ይፈልግ እንደሆነ እግዚአብሔርን በፍፁም አለመጠየቃቸው ነው። ብዙዎች ከፍርሃት ወይም ከእውቀት ማጣት የተነሣ፣ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም ባሕል በሚስዮናዊነት አገልግሎት የመሰማራቱን ነገር ከአእምሯቸው አውጥተው ታል። አንተም ተልዕኮን አሻፈረኝ ለማለት የምትፈተን ከሆንክ፣ ተልዕኮህ እውን ሊሆኑ የሚችልባቸውን የተለያዩ መንገዶች ለማጣራት ሞክር፣ (በሚገ ጥሙህ ነገሮች ትደነቃለህ)። በሚመጡት ዓመታት እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምን መሆኑን ለማወቅ መጸለይ ይኖርብሃል። ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የተልዕኮ በሮች በተከፈቱበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት፣ በሺህ የሚቆጠሩ ቋሚ ሚስዮናውያን እጅግ ይፈለጋሉ።

ኢየሱስን ለመምሰል ከፈለክ፣ ለመላው ዓለም የፍቅር ልብ ሊኖርህ ይገባል። ቤተሰቦችህና ወዳጆችህ ብቻ ወደ ክርስቶስ በመምጣታቸው ልትረካ አትችልም። በዓለማችን ከስድስት ቢሊዩን የሚልቁ ሰዎች አሉ፣ ኢየሱስም የጠፉ ልጆቹ ሁሉ እንዲገኙለት ይፈልጋል። እንዲህ ብሏል:- «*ነፍሱን ለማዳን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፣ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋት ሁሉ ግን ያድናታል*» ማር. 8፥35። ታላቁ ተልዕኮ፣ ተልዕኮህ፤ ድርሻህን መወጣቱ ደግሞ ጠቃሚ ሕይወ ትን የመኖሪያ ምስጢር ነው።

## ሠላሳ ስምንተኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ:- ታላቁ ተልዕኮ ተልዕኮዬ ነው::

ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ:- «*መንገድህ በምድር ላይ፤ ማዳንህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል ይታወቅ ዘንድ* » መዝ. 67÷2::

ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ:- በሚቀጥለው ዓመት ለአጭር ጊዜ የሚስዮናዊነት አገልግሎት ለመጓዝ እንድችል አሁን ምን ዝግጅት ላድርግ?

# 39

# የሕይወትህን ሚዛን መጠበቅ

*እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች*
*እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ ::*

**ኤፌ. 5+15**

*... ጸንታችሁ ከቆማችሁበት መሠረት በዓመፀኞች ስሕተት ተስባችሁ*
*እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ::*

**2ጴጥ. 3+17**

ሚዛናቸውን የጠበቁ የተባረኩ ናቸው፤ ከሁሉ ይልቅ ይዘልቃሉና።

ከበጋ የኦሎምፒክ ጨዋታዎች አንዱ ፔንታትሎን (አምስትዮሽ ፉክክር) ተብሎ የሚጠራው ነው። ይህ ጨዋታ ራሳቸውን የቻሉ አምስት ፉክክራዊ ተግባራት አሉት፡- ሽጉጥ ተኩስ፣ አጥር ዝላይ፣ የፈረስ ግልቢያ፣ ሩጫና የውሃ ዋና ሲሆኑ፣ የፔንታ አትሌቶች ግብ ከእነዚህ አንዱን ወይም ሁለቱን ሳይሆን፣ አምስቱንም ማሸነፍ ነው።

ሕይወትህም በሚዛን የምትጠብቃቸው አምስት ዓላማዎች ያሉት ፔንታ ትሎን ነው። እነዚህም ዓላማዎች፣ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የተኖሩ፣ ኤፌሶን 4 ውስጥ በጳውሎስ የተብ ራሩ፣ ዮሐንስ 17 ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት የታዩ፣ በእርሱም ታላቅ ትዕዛዝና ተልዕኮ ማጠቃለያ የተሰጠባቸው ናቸው። እንግዲህ እግዚአ ብሔር ለሕይወትህ ያሉትን አምስት ዓላማዎች የገለጠበትን የዚህን መጽ ሐፍ መልእክት እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ያጠቃልሉታል፡-

1. **«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ ውደድ»፡-** ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ስለሆንህ ዓላማህ እግዚአብሔርን *በአምልኮ* መውደድ ነው።
2. **«ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ»፡-** እግዚአብሔር አንተን ያበጀህ ለአ ገልግሎት ስለሆነ፣ ዓላማህ *በአገልግሎት* ዓማካይነት ለሌሎች ፍቅርን ማሳየት ነው።

3. «እንግዲህ ሂዱና ሕዝቦችን ... ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው »:- ለተል ዕኮ ተፈጥረሃልና ዓላማህ፣ የእግዚአብሔርን መልእክት *በወንጌል ስርጭት* ዓማካይነት ለሌሎች ማካፈል ነው።

4. «እያጠመቃችኋቸው ...»:- ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተሠርተሃልና ዓላማህ *ሕብረት* በማድረግ የቤተክርስቲያኑ አካል መሆን ነው።

5. «ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው...»:- የተ ፈጠርከው ኢየሱስ ክርስቶስን እንድትመስል ስለሆነ፣ ዓላማህ *በደቀ መዝሙርነት* ወደ ብስለት ማደግ ነው።

ለታላቁ ትእዛዝና ለታላቁ ተልዕኮ የምታሳየው ታላቅ ታማኝነት፣ ታላቅ ክርስቲያን ያደርግሃል።

እነዚህ አምስት ዓላማዎች ሚዛናቸውን እንዲጠበቁ ማድረጉ ቀላል አይደለም። ልባችን ወደሚግልበት በማድላት ሌሎቹን የሕይወት ዓላማዎች የመዘንጋት አዝማሚያ ይታይብናል። አብያተክርስቲያንም ቢሆኑ እንዲሁ ነው የሚያደርጉት። ነገር ግን ጥብቅ ህብረት ባለው አነስተኛ ቡድን ውስጥ በመሳተፍ፣ መንፈሳዊ ጤንነትህን በየ ጊዜው በመመዘን፣ የየዕለት የሕይወት ልምምድህን በመመዝገብና ያገኘሃቸውን ትምህርቶች ለሌሎች በማካፈል የሕይ ወት ዓላማዎችህ ሚዛን ጠብቀው እንዲሄዱ ለማድረግ ትችላለህ። እነዚህ በዓላማ ለሚመራ ሕይወት እጅግ የሚያስፈልጉ አራት ተግባራት ናቸው። ወዲያና ወዲህ ሳትል በዓላማህ እንድትጸና ከፈለግህ እነዚህን እንደ ልማድ ማዳበር ይኖርብሃል።

*ለታላቁ ትእዛዝና ለታላቁ ተልእኮ የምታሳየው ታላቅ ታማኝነት፣ ታላቅ ክርስቲያን ያደርግሃል።*

**ከመንፈሳዊ አጋር ወይም አነስተኛ ቡድን ጋር በሚገባ ተነጋገርበት።** እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን መርሆች ከራስ ጋር የማዋሃጃው ዓይነተኛ መንገድ፣ መርሆዎቹን በአነስተኛ ቡድን ደረጃ መወያየት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «*ብረ ትን ብረት እንደሚስል፣ ሰውም ሰባውን ሰው እንዲሁ ይስለዋል*» ምሳሌ 27፥17 ይላል። የተሻለ ትምህርት የምናገኘው በማህበረሰብ ደረጃ ነው። አእምሮአችን የሰላ የሚሆነውና እምነታችንም ሥር የሚሰደው፣ ከሌሎች ጋር በምናደር ጋቸው ውይይቶች ነው።

በዓላማ የሚመራ ሕይወት ያለው አነስተኛ የንባብ ቡድን እንድታሰባስብና እነዚህን ምዕራፎች በየሳምንቱ እንድትቃኛቸው አበክሬ አሳስብሃለሁ። የእያንዳ ንዱን ምዕራፍ የሕይወት ተዛምዶዎችና እንደምታዎች ተወያዩበት። ይህን

ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህስ ለእኔ፣ ለቤተሰቤ እና ለቤተክርስቲያናችን ምን ማለት ነው? እኔ ስለዚህ ጉዳይ ማድረግ ያለብኝ ምንድነው? ሐዋርያው ጳውሎስ:- «*ከእኔ የተማራችሁትን ወይም የተቀበላችሁትን፣ የሰማችሁትን ወይም የያዛችሁትን ማናቸውንም ነገር አድርጉ*» ፊልጵ. 4፥9 ይላል::



አንድ መጽሐፍ ለብቻ ቢነበብ ከሚሰጠው ይልቅ በአነስተኛ ቡድን በጋራ ቢጠና ጠቀሜታ አለው:: ስላነበብከው ነገር ያለህን አሳብ ለሌሎች ለማካፈልና የእነርሱን አሳብ ለማዳመጥም ትችላለህ:: ስለ እውነተኛ የሕይወት ምሳሌዎች ለመወያየትም ትችላለህ:: እነዚህን የሕይወት ዓላማዎች ወደ ሕይወት ለመተርጎም ከቡድንህ ጋር በምታደርጉት ጥረት እርስ በርስ ልትበረታቱ፣ አንዱ ለሌላው ሊፀልይና ልትረዳዱ ትችላላችሁ:: ልብ በል፣ ዕድገታችን ሊሆን የሚገባው ለየብቻ ሳይሆን፣ አንድ ላይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ:- «*ስለዚህ በእርግጥ አሁን እንደምታደርጉት ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ፤ አንዱም ሌላውን ያንጽ*» 1ተሰ. 5፥11 ይላል::

የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ እንዲኖርህም አበረታታሃለሁ:: እዚህ መጽሐፍ ውስጥ በየዐውዳቸው የተጠቀሱና ከሺህ የሚልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሉ:: ነገር ግን የመጻሕፍቱ ምዕራፎች እንዳይሰፉ በማሰብ የተጠቀምኩባቸውን ጥቅሶች በሰፊው ከማብራራት ተቆጥቤአለሁ:: መጽሐፍ ቅዱስ የታቀደው አንቀጽ በአንቀጽ፣ ምዕራፍ በምዕራፍ፣ እንዲሁም ከመላ መጻሕፍቱ አንፃር እንዲጠና ነው:: እንዲህ ዓይነቱን ጥናት ለማካሄድ የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎችን የሚያስተምር መጽሐፍ ጥሩ ጥቆማ ያደርጋል::

**መንፈሳዊ ጤንነትህን በየጊዜው ፈትሽ::** የአምስቱን ዓላማዎች ሚዛን የመጠበቂያው ዓይነተኛ መንገድ፣ ሕይወትህን በየጊዜው መመዘን ነው:: *ራሳችንን ለመመዘን* ልማዳችን እግዚአብሔር ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣል:: ቢያንስ አምስት ጊዜ መንፈሳዊ ሕይወታችንን እንድንፈትንና እንድንመዝን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተነግሮናል፣ ሰቆ. 3፥40፤ 1ቆሮ. 11፥28-31፤ 13፥5፤ ገላ. 6፥4:: «*በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ:*» 2ቆሮ. 13፥5::

አካላዊ ጤንነትህ ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን፣ የደም ግፊትህን፣ የሰውነት ሙቀትህን፣ ክብደትህንና የመሳሰሉትን በየጊዜው መቆጣጠር ይኖርብሃል:: እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሕይወት ጤንነት ወሳኝ የሆኑትን የአምልኮ፣ የህብረት፣ የባሕርይ ዕድገት፣ የአገልግሎትና የተልዕኮ ጤንነትህን በየጊዜው መመዘን ይኖርብሃል:: ነቢዩ ኤርምያስ እንዲህ በማለት ይመክረናል:- «*መንገዳችንን*

*እንመርምርና፣ እንፈትን፣ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ።»* ሰቆ. 3+40።

## ሰላሣ ዘጠነኛ ቀን
## የሕይወትህን ሚዛን መጠበቅ

ሳድልባክ በምትባለው ቤተ ክርስቲያናችን በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በዓላማ ለመጽናት የተጠቀሙባቸውን የግል ሕይወት መመዘኛ መንገዶች አዘጋጅተናል። ሐዋርያው ጳውሎስ:- *«አሁንም የጀመራችሁትን ተግባር በዓቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድርሱት ...»* 2ቆሮ. 8+11 ይለናል።

**የየዕለት የሕይወት እንቅስቃሴህን ማስታወሻ ላይ መዝግብ።** እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ከማሟላት አንፃር ያለህበትን ደረጃ ለማጠናከር በጣም ጥሩ የሆነው መንገድ፣ የየዕለት የሕይወት ልምምድህን መመዝገብ ነው። ይህ የዕለት ተግባርህን ሁሉ ሳይሆን፣ ልትረሳ የማትፈልጋቸውን የሕይወት ትምህርቶች የምትመዘግብበት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ:- *«ከሰማነው ነገር ስተን እንዳንወድቅ፣ ለሰማነው ነገር አብልጠን ልንጠነቀቅ ይገባናል»* *ዕብ. 2÷1* ይላል። የተመዘገበ ነገር ምን ጊዜም ቢሆን ይታወሳል።

ጽፎ ማስቀመጥ እግዚአብሔር በሕይወትህ በማከናወን ላይ ያለውን ነገር ግልጥ ያደርግልሃል። ዳውሰን ትሮትማን የተባለ ሰው እንዲህ ይል ነበር:- «አሳቦች በእጃችን በያዝነው ብዕር ውስጥ ሲያልፉ ውስብስብነታቸው ይፈታል»። መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር ሰዎች ስለ መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲመዘግቡ የተናገራቸውን ብዙ ምሳሌዎች ይሰጠናል:- *«ሙሴም በጉዞአቸው ላይ ሳሉ የሰፈሩባቸውን ቦታዎች በእግዚአብሔር ትእዛዝ መዘገበ»* ዘኁል. 33÷2። ሙሴ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመስማት ጉዞአቸውን መመዝገቡ ደስ አያሰኘህም? ሙሴ በመስነፍ የታዘዘውን ባያደርግ ኖሮ ከግብጽ የመውጣታቸውን ኃያል የሕይወት ትምህርት አናገኘውም ነበር።

የሕይወት ታሪክህ የሙሴን ያህል ስፋት ያለው ባይሆንም፣ አስፈላጊነቱ ግን አያጠራጥርም። ሕይወት ጉዞህ ነው፤ ጉዞ ደግሞ ሊመዘገብ ይገባል። በዓላማ የሚመራ ሕይወት ስትኖር፣ የምትደርስባቸውን የመንፈሳዊ ጉዞ ደረጃዎች ትጽፋቸዋለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

እየመረጥህ መልካም የሆነውን ገጽታ ብቻ አትጻፍ፤ ልክ ንጉሥ ዳዊት እንዳደረገው ጥርጣሬዎችህን፣ ፍርሃቶችህን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረግኸውን ትግል ሁሉ መዝግብ። ታላላቅ የሕይወት ትምህርቶቻችን የሚመጡት ካለፍናቸው መከራዎች ነው። እግዚአብሔር እንባዎቻችንን እንደሚመዘግብ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:- *«ሰቆቃዬን መዝግብ፤ እንባዬንም በሰቃህ አጠራቅም ሁሉስ በመዝገብህ የተያዘ አይደለምን?»* መዝ. 56÷8። ችግሮች በገጠሙህ ጊዜ

ሁሉ እግዚአብሔር የሕይወትህን አምስት ዓላማዎች ግብ ለመምቻነት የሚጠቀምባቸው መሆኑን ልብ በል። ችግሮች ወደ እግዚአብሔር እንድታተኩር ያስገድዱሃል፤ በህብረት ወደ ሌሎች እንድትጠጋ ይገፋሃል፤ ኢየሱስ ክርስቶስን በምትመስልበት ባሕርይ ይቀርጹሃል፤ ምስክርነትም ይሰጡሃል፤ እያንዳንዱ ችግር በዓላማ የሚመራ ነው።

መዝሙረኛው ዳዊት በብዙ ስቃይ ውስጥ ሆኖ እንዲህ አለ፡- «*ወደ ፊት የሚፈጠር ሕዝብ እግዚአብሔርን ይወድስ ዘንድ፣ ይህ ለመጪው ትውልድ እንዲህ ተብሎ ይጻፍ*» መዝ. 102፥18። እግዚአብሔር ዓላማዎቹን በምድር ላይ እንድትፈጽም እንዴት አድርጎ እንደረዳህ ለመጪው ትወልድ ልታስተላልፍ ይገባል። ምክንያቱም አንተ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከገባህ በኋላ እንኳን ይህ የሚቀጥልና የሚነገር ምስክርነት ነው።

**የምታውቀውን ለሌሎች አስተላልፍ።** ማደግህ እንዲቀጥል ከፈለግህ እጅግ የተሻለው መንገድ፣ ያገኘሃቸውን ትምህርቶች ለሌሎች ማስተላለፍ ነው። መጽሐፈ ምሳሌም፡- « ... *ሌሎችን የሚያረካም ራሱ ይረካል*» ምሳሌ 11፥25 ይላል። ከሕይወት የተገኙ ትምህርቶችን ለሌሎች የሚያስተላልፍ ሰው፣ የበለጠ ነገር ከእግዚአብሔር ያገኛል።

እንግዲህ የሕይወትን ዓላማ ተገንዝበ ሃልና ይህንኑ ለሌሎች የማስተላለፍ ኃላፊነት አለብህ። እግዚአብሔር መልዕ ክተኛው እንድትሆን ይጠራሃል። ሐዋር ያው ጳውሎስ 2ጢሞ. 2፥2 ውስጥ እንዲህ ብሏል፡- «... *ከእኔ የሰማኸውን ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች በደራ ለተ* »። እኔ ከሌሎች የተማርኩትን በዚህ መጽሐፍ ዓማካይነት ለአ ንተ አስተላልፌአለሁ። ይህን ለሌሎች ማስተላለፍ ደግሞ የአንተ ግዴታ ነው።

> *እግዚአብሔር ዓላማዎችን በምድር ላይ እንድትፈጽም እንዴት አድርጎ እንደረዳህ ለመጪው ትውልድ ልታስተላልፍ ይገባል።*

ምናልባት የሕይወትን ዓላማ ያልተገነዘቡና በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ታውቅ ይሆናል። እነዚህን እውነቶች ለልጆችህ፣ ለወዳጆችህ፣ ለጎረቤቶችህና አብረውህ ለሚሠሩ ሰዎች አካፍላቸው። ይህን መጽሐፍ ለአንዱ ወዳጅህ የምት ስጠው ከሆነም፣ በመታሰቢያው ገጽ ላይ የግል ማስታወሻህን ጨምርበት።

ብዙ ባወቅህ ቁጥር ይህንኑ እውቀት ሌሎችን ለመርዳት እንድትጠቀምበት እግዚአብሔር ይጠብቃል። ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡- «*እንግዲህ መል ካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት እያወቀ የማያደርግ ሰው ኃጢአት ያደርጋል*» ያዕ. 4፥17። እውቀት ኃላፊነትን ይጨምራል። የሕይወትን ዓላማ ለሌሎች

ማስተላለፍ ከግዴታ ያለፈ ሲሆን፣ በሕይወቱ ከሚያጋጥሙ ታላላቅ ዕድሎች አንዱ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ ቢያውቅ ኖሮ ዓለም እንዴት የተለየች ቦታ ትሆን እንደነበር ለመገመት ትችላለህ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፡- *«ይህንን ትእዛዝ ለወንድሞች ብታሳስብ በእምነት ቃልና በተቀበልኸው መልካም ትምህርት ታንጸህ የክርስቶስ ኢየሱስ በጎ አገልጋይ ትሆናለህ»* 1ጢሞ. 4÷6 ብሏል፡፡

## ሁሉም ለእግዚአብሔር ክብር ነው

የተማርነውን ሁሉ ለሌሎች የምናስተላልፍበት ምክንያት፣ ለእግዚአብሔር ክብርና ለመንግሥቱ ዕድገት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ባለው ምሽት ለአባቱ እንዲህ አለ፡- *«የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ»* ዮሐ. 17÷4፡፡ እነዚህን ቃላት ሲጸልይ ገና ለኃጢአታችን አልሞተም ነበር፡፡ ታዲያ የትኛውን «ሥራ» ነው የፈጸመው? በዚህ ሁኔታ ከሥርየት ሥራው ስለተለየ ነገር ነበር የሚናገረው፡፡ የዚህ መልስ የሚገኘው በዚሁ



ጸሎቱ ቀጣይ ሃያ ቁጥሮች ውስጥ ነው፤ ዮሐ. 17÷6-26፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፉት ሦስት ዓመታት ደቀ መዛሙርቱ ለእግዚአብሔር ዓላማ እንዲኖሩ በማዘጋጀት ላይ እንደነበር ለአባቱ ነገረ፡፡ እግዚአብሔርን እንዲያውቁና እንዲወዱት ረዳቸው (አምልኮ)፣ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ አስተማራቸው (ህብረት)፣ ወደ ብስለት ያድጉ ዘንድም ቃሉን ሰጣቸው (ደቀ መዝሙርነት)፣ እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው አሳያቸው (አገልገሎት)፣ ለሌሎችም ይናገሩ ዘንድ ላካቸው (ተልዕኮ)፡፡ ይህን በማድረግ በዓላማ የሚመራ ሕይወትን በምሳሌነት አሳየ፡፡ እንዴት መኖር እንዳለባቸውም ለሌሎች አስተማረ፡፡ ይህ ሥራ ነው ክብርን ለእግዚአብሔር ያመጣ፡፡

ዛሬም እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ለተመሳሳይ ሥራ ይጠራናል፡፡ እነዚህን ዓላማዎች እንድንኖራቸው መፈለግ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎችም ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ እንድንረዳቸው ይፈልጋል፡፡ ሰዎችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንድናስተዋውቃቸው ይሻል፣ ወደ እርሱም ህብረት እንድናመጣቸው፣ በመንፈሳዊ ሕይወት አድገው የአገልግሎት ሥፍራቸውን እንዲያውቁና በተራቸው ለሌሎች እንዲነግሩ እናደርግ ዘንድ ይፈልጋል፡፡

ዓላማ መራሽ ሕይወት ማለት ይህ ነው፡፡ በየትኛውም የዕድሜ እርከን ላይ ብትሆን፣ ቀሪ ሕይወትህ ከመቼውም የተሻለ ይሆናል፡፡ በዓላማ መኖርን ዛሬ ልትጀምር ትችላለህ፡፡

ሠላሳ ዘጠነኛ ቀን

ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ፡-** ሚዛናቸውን የጠበቁ የተባረኩ ናቸው።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ፡-** *«እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ»* ኤፌ. 5፥15።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር ለሕይወቴ ያቀዳቸውን አምስት ዓላማዎች ሚዛናዊ ለማድረግና፣ ትክክለኛ መንገዴን ጠብቄ ለመጓዝ እንድችል ከአራቱ ተግባራት የትኛውን ልጀምር?

# 40

# በዓላማ መኖር

*በሰው ልብ ብዙ ሐሳብ አለ፣ የሚፈጸመው ግን*
*የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው።*

**ምሳሌ 19፥21**

*ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካገለገለ*
*በኋላ አንቀላፋ።*

**የሐዋ 13፥36**

የእርግጠኛ ኑሮ ብቸኛው መንገድ፣ በዓላማ መኖር ነው። ከዚህ ውጭ ኑሮ ዝም ብሎ ይሆናል።

ብዙ ሰዎች ከሦስት መሠረታዊ የሕይወት ጉዳዮች ጋር ይታገላሉ። የመጀመሪያው የማንነት ጉዳይ ነው፤ «እኔ ማን ነኝ ?»፤ ሁለተኛው ጠቃሚ ወይም ተፈላጊ የመሆን ጉዳይ ነው «ፋይዳ ያለኝ ሰው ነኝን?»፤ ሦስተኛው የተጽዕኖ ጉዳይ ነው «በሕይወት ውስጥ ያለኝ ድርሻ ምንድ ነው?»። የእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልስ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ባለው አምስት ዓላማዎች ውስጥ ይገኛል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የተሠማራበትን አገልግሎት በጨረሰባት የመጨረሻ ዕለት ምሳሌ ይሆናቸው ዘንድ እግራቸውን አጠበና፦ *«እንግዲህ እነዚህን ነገሮች ስውቃችሁ ብትፈጽሙ ትባረካላችሁ»*፣ ዮሐ. 13፥17 አላቸው። እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚፈልገውን ነገር አንዴ ካወቅህ፣ በረከቱ የሚመጣው ያወቅኸውን ስታደርግ ነው። እንግዲህ አብረን ያደረግነውን ይህን የአርባ ቀን ጉዞ ወደ መጨረሱስንቃረብ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማዎች አውቀሃልና በተግባር ላይ ካዋልካቸው ትባረካለህ።

ይህ ምናልባት አሁን የምታደርጋቸውን አንዳንድ ነገሮች ማቆም ይኖርብሃል ማለት ሊሆን ይችላል። በሕይወትህ ልታደርግ የምትችላቸው

ብዙ «ጥሩ» ነገሮች ይኖራሉ። አምስቱን የእግዚአብሔር ወሳኝ ዓላማዎች ግን የግድ ልታደርጋቸው ይገባል። ክፋቱ በሕይወታችን ወሳኝ የሆነውን ነገር በቀላሉ መርሳታችንና መንገድ መሳታችን ነው። እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ለመ ከላከል የሕይወትህን ዓላማ የሚገልጥ ዐረፍተ ነገር በማዘጋጀት፣ ደጋግመህ ልትቃኘው ይገባል።

## የሕይወት ዓላማ መግለጫ ምንድነው ?

**እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ባጭሩ የሚገልጥ ዐረፍተ ነገር** ነው። እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን አምስት ዓላማዎች ለመፈጸም ቃል መግባትህን በራስህ ቃላት የምታረጋግጥበት ነው። የዓላማ መግለጫ፣ የግቦች ዝርዝር አይደለም። ግቦች ጊዜያዊ ሲሆኑ፣ ዓላማዎች ግን ዘላለማዊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *«የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል፤ የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው።»* መዝ. 33፥11።

**የሕይወትህን አቅጣጫ የሚጠቁም አረፍተ ነገር ነው።** ዓላማዎችህን በወ ረቀት ላይ ማስፈር በተለይ ስለ ሕይወትህ አቅጣጫ እንድታስብ ያስገድድሃል። መጽሐፍ ቅዱስ፦ *«የእግርህን ጎዳና አስተካክል፤ የጸናውን መንገድ ብቻ ያዝ»* ምሳሌ 4፥26 ይላል። የሕይወት ዓላማ መግለጫ በገንዘብህ፣ በሕይወትህና፣ በጊዜህ ምን እንደምታደርግ መጠቆም ብቻ ሳይሆን፣ ምን ማድረግ እንደማይ ገባህም ያመለክትሃል። መጽሐፈ ምሳሌ እንዲህ ይላል፦ *«አስተዋይ ሰው ጥበብን ከፊቱ አይለያትም፣ የተላሉች ዓይኖች ግን እስከ ምድር ዳርቻ ይንከራተታሉ»* ምሳሌ 17፥24።

**«ስኬት» ማለት ለአንተ ምን ማለት መሆኑን የሚገልጥ ዐረፍተ ነገር ነው።** ይህ ዐረፍተ ነገር፣ ዓለም ዋነኛ ነገር ነው ያለውን ሳይሆን፣ አንተ ዋነኛ ነገር ነው የምትለውን ይገልጣል። ለሕይወት የምትሰጠውን ፋይዳ የሚያብራራ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ፦ *«ከሁሉ የሚሻለውን ለይታችሁ እንድታውቁ ...»* ፊሊጵ. 1፥10 ብሏል።

**ሚናህን ግልጥ የሚያደርግልህ ዐረፍተ ነገር ነው።** በሕይወትህ በየደረጃው የተለያዩ ድርሻዎች ቢኖሩህም ዓላማዎችህ ግን የማይቀየሩ ናቸው። ከሚኖርህ ማንኛውም ዓይነት ሚና (ድርሻ) ሁሉ ይበልጣሉ።



**የተፈጠርህበትን መልክስል (ቅርጽ) የሚገልጥ ዓረፍተ ነገር ነው።** ታገለግለው ዘንድ እግዚአብ ሔር አንተን የፈጠረበትን በልዩ ሁኔታዎች ያንፀባርቃል።

የሕይወት ዓላማ መግለጫህን ለመጻፍያ ጊዜ ውሰድ። በመጀመሪያው ሙከራህ በአንዴ ቁጭ ብለህ ያለቀለት ነገር በመጻፍ ለመጨረስ አትሞክር። የመጣልህን አሳብ ወዲያው ጻፈው። ምን ጊዜም ቢሆን አዲስ ከመጻፍ፣ የተጻፈውን ማረም ይቀላል። የሕይወት ዓላማ መግለጫህን ስታዘጋጅ ልብ ልትላቸው የሚገቡ አምስት ጥያቄዎች እነሆ!

## አምስቱ የሕይወት ታላላቅ ጥያቄዎች

**የሕይወቴ ማዕከል ሊሆን የሚገባው ምንድነው?** ይህ *አምልኮን* የሚመለከት ጥያቄ ነው። የምትኖረው ለማን ነው? ሕይወትህን ልትገነባ የተዘጋጀኸው ለምን ዓላማ ነው? የመተዳደሪያ ሙያህን፣ ቤተሰብህን፣ ስፖርትን ወይም ሌላ የመዝናኛ ልማድን፣ ገንዘብን፣ ጨዋታንና ሌሎች ተግባራትን የሕይወትህ ማዕከላት ልታደርጋቸው ትችላለህ። እነዚህ ሁሉ ግን የሕይወት ነውጥ በገጠመህ ጊዜ አንተን ደግፎ የሚያቆይ ጥንካሬ የላቸውም። አንድ የማይናወጥ ማዕከል ያስፈልግሃል።

ንጉሥ አሳ፣ *«የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ ሕጉንና ትእዛዙንም እንዲፈጽሙ የይሁዳን ሕዝብ አዘዘ»* 2ዜና 14፥4። በመሠረቱ የሕይወትህ ማዕከል የሆነ ነገር ሁሉ አምላክህ ነው። ሕይወትህን ለክርስቶስ በሰጠህ ጊዜ እርሱ የሕይወትህ ማዕከል ሆኗል። በመሆኑም በአምልኮ ዓማካይነት በሥፍራው እንዲቆይ ማድረግ ይኖርብሃል። ሐዋርያው ጳውሎስ፦ *«ይኸውም እምነት ክርስቶስ በልባችሁ እንዲያድር ነው።»* ኤፌ. 3፥17 ይላል።

*እግዚአብሔር የሕይወትህ ማዕከል ሲሆን ታመልከዋለህ። ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ትጨነቃለህ።*

እግዚአብሔር የሕይወትህ ማዕከል መሆኑን እንዴት ታውቃለህ? እግዚአብሔር የሕይወትህ ማዕከል ሲሆን ታመልከዋለህ። ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ትጨነቃለህ። ጭንቀት፣ እግዚአብሔር በሕይወትህ ወደ ጥግ ገፋ የተደረገ መሆኑን የሚያስጠነቅቅ ምልክት ነው። መልሰህ የሕይወትህ ማዕከል ስታደርገው ግን ወዲያው በሰላም ትሞላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ፦ *«ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል»* ፊልጵ. 4፥7 ይላል።

**የሕይወቴ *ባሕርይ* ምን መሆን ይኖርበታል?** ይህ ደግሞ ደቀ መዝሙርነትን የሚመለከት ጥያቄ ነው። ምን ዓይነት ሰው ነው የምትሆነው? እግዚአብሔርን የሚገደው፣ ከምታደርገው ነገር ይልቅ *የምትሆነው* ነው። ልብ በል፤

ለዘላለም አብሮህ የሚቆየው ባሕርይህ እንጂ፣ የመኖሪያ ሙያህ አይደለም። ልታዳብር የምትፈልጋቸውን በጎ ባሕርያት ዝርዝር ያዝና ለሕይወትህ ማሳደጊያነት ተለማመዳቸው። ከመንፈስ ፍሬዎች ገላ. 5፥22 ወይም ከተ ራራው ስብከት ለመጀመር ትችላለህ ማቴ. 5፥7።

ሐዋርያው ጴጥሮስ:- «*በዚህ ምክንያት በሙሉ ትጋት በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር ጣሩ፤ በበጎነት ላይ ዕውቀትን፣ በዕውቀት ላይ ራስን መግዛት፣ ራስን በመግዛት ላይ መጽናትን፣ በመጽናት ላይ እውነተኛ መንፈሳዊነትን፣ በእውነተኛ መንፈሳዊነት ላይ ወንድማዊ መተሳሰብን፣ በወንድማዊ መተሳሰብ ላይ ፍቅርን ጨምሩ*» 2ጴጥ. 1፥5-7 ብሏል። እልሆንልህ በሚልህ ጊዜ ተስፋ ቆርጠህ አትተወው። የክርስቶስን የመሰለ ባሕርይ ለማዳበር የሚደረገው ጥረት የዕድሜ ልክ ጉዳይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት እንዲህ ብሏል:- «*ለሕይወትህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ ራስህንና የሚሰሙህን ታድናለህ*» 1ጢሞ. 4፥16 ።

**አርባኛ ቀን በዓላማ መኖር**

**ከሕይወቴ የሚጠብቀው ድርሻ ምን ሊሆን ይገባል?** ይህ ለማያምኑ ሰዎች የሚኖርህን አገልግሎት የሚመለከት ጥያቄ ነው። ክርስቶስ አካል (ቤተ ክር ስቲያን) ውስጥ፣ አገልግሎትህ ምን ሊሆን ይገባል? **መልክስልህን** (መንፈሳዊ ስጦታህን፣ ልብህን፣ ክህሎትህን፣ ሰብእናህንና ልምምድህን) ካወቅህ ዘንድ፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ከአንተ የሚጠበቀው የተሻለ ድርሻ የቱ ነው? ልዩነት ለማምጣት የምትችለው እንዴት ነው? አገለግላቸው ዘንድ የተበጀሁ ላቸው፣ ልዩ ቡድኖች በክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያን) ውስጥ ይኖሩ ይሆን? የተፈጠርህበትን አገልግሎት ስታሟላ ስለሚኖሩህ ሁለት ጥቅሞች ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «*ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳንን ጉድለት የሚያ ሟላ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ነው*» 2ቆሮ. 9፥12 ።

የተቀረጽከው ሌሎችን ለማገልገል ነው። ቢሆንም ኢየሱስ እንኳን በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የሁሉንም ፍላጎት አላሟላም። በመልክስልህ መሠረት ማንን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል እንደምትችል መምረጥ ይኖርብሃል። «ማንን ነው ይበልጥ የመርዳቱ መሻት ያለኝ?» ብለህ መጠየቅ ይኖርብሃል። ኢየሱስ:- «*እንድትሄዱና ፍሬ እንድታፈሩ ፍሬአችሁም እንዲኖር ሾምኋችሁ*» ዮሐ. 15፥16 ብሏል። እያንዳንዳችን የምናፈራው የተለያየ ፍሬ ነው።

**ሕይወቴ ሊያስተላልፈው የሚገባ መልእክት ምንድነው?** ይህ የሚያመ ለክተው፣ ለማያምኑ ሰዎች የሚኖርህን የተልዕኮ ጥያቄ ነው። የተልዕኮህ

መግለጫ፣ የሕይወት ዓላማህ መግለጫ አንድ ክፍል ነው። የሕይወት ምስክርነትህንና የምሥራቹን ቃል ለሌሎች ለማካፈል ቃል የገባህ መሆንህን ያካትታል። ከሕይወት ያገኘሃቸውን ትምህርቶችና እግዚአብሔር በዓለም ላሉ ሰዎች ታካፍለው ዘንድ በልብህ ያቀጣጠለውን ፍቅር ዘርዝርና ጻፍ። በክርስቶስ ኢየሱስ እያደግህ በሄድህ ቁጥር፣ እግዚአብሔር ወንጌልን ልታደርስላቸው የሚገባህንና የምታተኩርባቸው ሰዎችን ይሰጥሃል። ይህን በዓላማ መግለጫህ ውስጥ ስለማካተትህ እርግጠኛ ሁን።

የልጆች አባት ከሆንክ፣ የተልዕኮህ አንድ ክፍል፣ ልጆችህ ክርስቶስን እንዲያውቁ ማሳደግ፣ እርሱ ለሕይወታቸው ያለውን ዓላማ እንዲገነዘቡ መርዳትና በዓለም ውስጥ ወደ አላቸው ተልዕኮ ማሰማራት ነው። የኢያሱን የዓላማ መግለጫ፣ መግለጫህ ውስጥ ለማካተት ትችላለህ፡- *«እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን»* ኢያ. 24÷15 ።

ሕይወትና ኑሯችን የምናስተላልፈውን መልእክት መደገፍና ማረጋገጥ አለበት። አማኝ ያልሆኑ ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነት ከመቀበላቸው በፊት፣ የሕይወታችንን ተአማኒነት ለማወቅ ይፈልጋሉ። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ *«... ብቻ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ...»* ፊልጵ. 1+27 የሚለን።

**በሕይወቴ ልቀላቀለው የሚገባ ማህበረሰብ የቱ ነው?** ይህ ደግሞ *ህብረትን ይመለከታል*። ለሌሎች አማኞችና ለእግዚአብሔር ቤተሰቦች ያለህን ቃል ኪዳንና ግንኙነት እንዴት ትገልጠዋለህ? «እርስ በእርሳችሁ» የሚለውን ትእዛዝ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የምትለማመደው የት ነው? ተሳታፊ አባል የሆንክበት የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ የቱ ነው? በመንፈሳዊ ሕይወት ባደግህ ቁጥር የክርስቶስን አካል (ቤተክርስቲያንን) እየወደድህና መስዋዕት ልትሆንላትም እየፈለግህ ትመጣለህ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-*«ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ስለ እርሷም ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ»* ኤፌ. 5÷25። ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ያለህን ፍቅር የሚገልጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ዓላማ መግለጫህ ውስጥ መጨመር አለብህ።

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ በማፈላለግ ላይ እያለህ ስለ እያንዳንዱ ዓላማ የሚገልጡልህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አካት። እዚህ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት አሉ። የሕይወት ዓላማ መግለጫህን በምትፈልገው ሁኔታ ለመቅረጽ ሳምንታት ወይም ወራት ሊፈጅብህ ይችላል። ጸልይ፣ አሰላስልበት፣ ከቅርብ ወዳጆችህ ጋር ተነጋገርበት፣ መጽሐፍ ቅዱስንም በጥሞና አንብብ። የተሟላ የዓላማ መግለጫህን ከመጻፍህ በፊት፣ መላልሰህ መጻፍ ይኖርብህ ይሆናል።

*ለማኝ ያልሆኑ ብዙ ሰዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ከመቀበላቸው በፊት፣ የሕይወታችንን ተዓማኒነት ለማወቅ ይፈልጋሉ::*

እንዲያም ሆኖ እንኳን እግዚአብሔር ስለ መልክስልህ የተሻለ መረዳት በሰጠህ ቁጥር ጥቃቅን ለውጥ ማድረግ ያስፈል ግህ ይሆናል::

ከዝርዝር የዓላማ መግለጫህ በተ ጨማሪ በሚታወስና በሚያነቃቃ መልኩ አምስቱን የሕይወት ዓላማዎች በአጭሩ የሚገልጥልህ መፈክር መሰል ዐረፍተ ነገር ቢኖርህ ይጠቅማል:: ዓላማህን በየዕለቱ ታስብበታለህ:: ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል:- «*በልብህ ስትጠብቃቸው፣ ሁሉም በከንፈሮችህ ላይ የተዘጋጁ ሲሆኑ ደስ ይላልና* » ምሳሌ 22፥18:: ጥቂት ምሳሌዎች እነሆ:-

- «የሕይወቴ ዓላማ በልቤ ክርስቶስን ማምለክ፣ በተፈጠርሁበት መልክስል እርሱን ማገልገል፣ ከእርሱ ቤተሰብ ጋር ህብረት ማድረግ፣ ወደ እርሱ ባሕርይ ማደግና ለክብሩ በዓለም ውስጥ ተልዕኮውን ማሟላት::»
- «የሕይወቴ ዓላማ የክርስቶስ ቤተሰብ አባል መሆን፣ የባሕርይው ሞዴል፣ የፀጋው አገልጋይ፣ የቃሉ መልእክተኛና የክብሩ አጉልቶ አሳይ መሆን ነው::»
- «የሕይወቴ ዓላማ ክርስቶስን መውደድ፣ በክርስቶስ ማደግ፣ ስለ እርሱ ለሌሎች መንገር፣ በቤተክርስቲያኑ በኩል እርሱን ማገልገልና ቤተሰ ቤም ሆነ ሌሎች ይህንኑ እንዲያደርጉ መምራት ነው»
- «የሕይወቴ ዓላማ ለታላቁ ትእዛዝና ለታላቁ ተልዕኮ በታላቅ መሰጠት መኖር ነው::»
- «ግቤ ክርስቶስን መምሰል ነው፤ ቤተሰቤም ቤተክርስቲያን ናት፣ አገልግሎቴ ——— ፣ ተልእኮዬም ——— ነው፣ ለዚህ የሚያነሳ ሳኝም የእግዚአብሔር ክብር ነው»::

ምናልባት «እግዚአብሔር ለሥራዬ ፣ለትዳሬ፣ ለምኖርበትና ለምማርበት ቦታ ያለው ፈቃድስ ምንድነው?» ብለህ ታስብ ይሆናል:: እውነቱን ለመናገር እነዚህ ሁሉ በሕይወትህ፣ ሁለተኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ናቸው:: ለአንተ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድና የተለያዩ አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ:: የትም ኖርክ፣ ምንም ሥራህ ወይም ማንንም አገባህ ማንን፣ ከሁሉ የሚበልጠው የእግዚአ ብሔርን የዘላለም አሳብ መፈጸምህ ነው:: እንዲህ ያሉት ውሳኔዎች ዓላማህን ሊደግፉት ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስ:- «*በሰው ልብ ብዙ አሳብ አለ የሚፈጸመው*

*ገን የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው»* ምሳ 19÷21 ይላል:: ለዘላለም የሚዘልቀው እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለው ዓላማ ስለሆነ በራስህ ሳይሆን፣ በእርሱ ዕቅድ ላይ አትኩር::

የሕይወት ዓላማህን ሌሎች በቀብርህ ሥነ ሥርዓት ላይ እንዲናገሩ ከምትፈልገው ንግግር አንጻር ቅረጽ፣ የሚል አመለካከት ከዚህ ቀደም ሰምቼአለሁ:: የተዋጣለት የመታሰቢያ ንግግር አስብና የሕይወት ዓላማ መግለጫህን በዚያ ላይ መሥርት:: እውነቱን ለመናገር ይህ መጥፎ ዕቅድ ነው:: በሕይወትህ መጨረሻ ሰዎች ስለ አንተ የሚሉት ነገር ምንም አይፈይድም:: ትልቁ ቁም ነገር እግዚአብሔር ስለ አንተ የሚለው ነገር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ፦ *«... ልባችንን የሚመረምረውን እግዚአብሔርን እንጂ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብለን አይደለም»* 1ተሰ. 2÷4 ይላል::

አንድ ቀን እግዚአብሔር ለእነዚህ የሕይወት ጥያቄዎች የሰጠሃቸውን መልሶች ይመለከታል:: ኢየሱስን የሕይወትህ ማዕከል አድርገኸዋል? ባህርይውን አዳብረሃል? ሌሎችን ለማገልገል ሕይወትህን ሰጥተሃል? መልእክቱን በማስተላለፍ ተልዕኮውን ተወጥተሃል? ቤተሰቡን በመውደድ እውስጡ ተሳትፎ አድርገሃል? መጨረሻ ላይ ወሳኞቹ ነገሮች እነዚህ ብቻ ናቸው:: *«የእኛ መመካት ገን ዳር ድንበር ስላለው ከዚያ አይወጣም:: ይህም እግዚአብሔር በሰጠን የአገልግሎት በር ክልል የተወሰነ ነው»* 2ቆሮ. 10÷13::

# እግዚአብሔር ሊጠቀምብህ ይፈልጋል

የዛሬ ሠላሳ ዓመት ገደማ የሕይወቴን አቅጣጫ ለዘላለም ያስለወጠኝን አንድ ሐረግ፣ የሐዋ. 13÷36 ውስጥ ልብ አልኩ:: ቃላቱ ስምንት ብቻ ቢሆኑም «ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካገለገለ በኋላ አንቀላፍቶአል» የሚለው ሐረግ በጋለ ብረት እንደታተመ ጸሑፍ በሕይወቴ ታትሞ ቀረ:: እግዚአብሔር ዳዊትን፦ *«እንደ ልቤ የሆነና እኔ የምሻውን ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ»* ያለበት ምክንያት አሁን ገብቶኛል የሐዋ. 13÷22:: ዳዊት ምድራዊ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ዓላማ ማከናወኛነት አሳልፎ የሰጠ ሰው ነው::

ከዚህ የሚበልጥ ታላቅ የመታሰቢያ ጽሑፍ የለም:: እስቲ አንተም ባለህበት ትውልድ ዘመን የእግዚአብሔርን ዓላማ ያገለገልክ መሆንህን የሚገልጥ ጽሑፍ በመቃብርህ ሐውልት ላይ በማይጠፋ ሁኔታ የተጻፈበት መሆኑን አስብ:: ጸሎቴ እኔ ከሞትኩ በኋላ ሰዎች እንዲያ ብለው እንዲጽፉልኝ ነው:: ለአንተም እንዲያ እንዲሉልህ እጸልያለሁ:: ለዚህ ነው ይህን መጽሐፍ የጻፍ

ኩልህ።

ይህ ሐረግ በሚገባ የተኖረን ሕይወት ፍጻሜ የሚያስገነዝብ ትልቅ መግለጫ ነው። አንተ ዘላለማዊውንና ጊዜ የማይሽረውን (የእግዚአብሔርን ዓላማ)፣ በዚህ በአሁን ጊዜና በተወሰነ ሁኔታ (በዘመንህ) ታከናውናለህ። በዓላማ የሚመራ ሕይወት ማለት ይህ ነው። በዚህ ዘመን ያለውን የእግዚአብሔር ዓላማ፣ ያለፈውም ሆነ መጪው ትውልድ ሊያከናውነው አይችልም። ይህን ልናደርግ የምንችል እኛ ብቻ ነን፤ ልክ እንደ ንግሥት አስቴር እግዚአብሔር፣ *«... ለዚህ ጊዜ»* ፈጥሮሃል ፣ አስቴር 4፥14።



አሁንም ቢሆን፣ እግዚአብሔር፣ የሚጠቀምባቸውን ሰዎች ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ:- *«በፍጹም ልባቸው የሚታመኑበትን ለማበረታታት የእግዚአብሔር ዓይኖች በምድር ሁሉ ላይ ይመለከታሉና»* 2ዜና 16፥9 ይላል። እግዚአብሔር ለዓላማው የሚጠቀምበት ሰው ትሆናለህን? በዘመንህ የእግዚአብሔርን ዓላማ ታገለግላለህን?

ሐዋርያው ጳውሎስ በዓላማ የሚመራ ሕይወት ነው የኖረው። እንዲህ ብሏል:- *«ስለዚህ እኔ ግብ እንደሌለው ሰው በከንቱ አልሮጥም»* 1ቆሮ. 9፥26። የመኖሩ ብቸኛ ምክንያት እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ዓላማዎች ለመፈጸም ነበር። ደግሞም እንዲህ አለ:- *«ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ ነው»* ፊልጵ. 1፥21። ሞትንም ሆነ ኑሮን አልፈራም። በሁለቱም መንገድ የእግዚአብሔር ዓላማ ይፈጽማል፤ በፍጹም አይከስርም!

ታሪክ አንድ ቀን ያከትማል፤ ዘላለም ግን ይቀጥላል። ዊልያም ኬሪ የተባለ ስመጥር የወንጌል መልእክተኛ:- «ወደ ፊት የሚገለጠው ነገር የእግዚአብሔርን ተስፋ ያህል ብሩህ ነው» ብሏል። ዓላማዎችህን ማከናወኑ አስቸጋሪ በሚመስልበት ጊዜ በፍጹም ተስፋ አትቁረጥ። ለዘላለም የሚኖር ሽልማትህን አስታውስ። መጽሐፍ ቅዱስ:- *«... ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልና»* 2ቆሮ. 4፥17 ይላል።

*በዓላማ መኖርን ዛሬ ልትጀምር ትችላለህ።*

አንድ ቀን ሁላችንም እግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቆመን ጥልቅ በሆነ ምሥጋና ሕይወታችንን ለክርስቶስ ስናቀርብ እስቲ በዓይነ ህሊናህ አስብ። ሁላችንም በአንድ ላይ እንዲህ እንላለን።

*«ጌታችንና አምላካችን ሆይ፣ ክብርና ሞገስ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፣ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፣ ሆነዋልም።»* ራዕይ 4፥11። ስለ ዕቅዱ እናመሰግነዋለን፤ ለዓላማውም ለዘላለም እንኖራለን።

## አርባኛ ቀን

## ስለ ዓላማዬ ሳስብ

**ላሰላስለው የሚገባ ጉዳይ :-** የእርግጠኛ ኑሮ ብቸኛው መንገድ፣ በዓላማ መኖር ነው።

**ላስታውሰው የሚገባ ጥቅስ :-** «*ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካገለገለ በኋላ አንቀላፍቶአል*» የሐዋ. 13÷36።

**ልብ ልለው የሚገባ ጥያቄ :-** ለሕይወት አምስት ታላላቅ ጥያቄዎች ያሉኝን መልሶች እና ዓላማዬን ወረቀት ላይ የማስፍረው መቼ ነው?

ተቀጥላ

# የመወያያ ጥያቄዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ካሉት ጥያቄዎች በተጨማሪነት፣ ቀጥሎ ያሉትን የመወያያ ጥያቄዎች በአነስተኛ ቡድንህ ወይም በእሁድ ትምህርት ክፍል ውስጥ ልትገለገልባቸው ትችላለህ::

## ለምንድነው የተፈጠርኩት ?

- የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር የሆነውና «ስለአንተ አይደለም» የሚለው ቃል እንደምታ ምንድነው?
- የብዙ ሰዎች ሕይወት በምን ይመራል ብለህ ታስባለህ? ሕይወትህን የሚመራው ኃይል ምንድነው ?
- እስካሁን ሕይወትህን በተሻለ ሁኔታ የገለጠው የትኛው ምስል ወይም ተምሳሌት ነው ? እስፖርታዊ ውድድር፣ ሰርከስ፣ ወይስ ሌላ ነገር?
- ምድራዊ ሕይወታችን ለዘላለማዊው ሕይወት የመዘጋጃ ጊዜ መሆኑን ሁላችንም ብንረዳ ኑሮ፣ ከተለመደው አኗኗራችን የተለየ ምን እናደርግ ነበር ?
- በምድር ላይ ከሰዎች ጋር የተያያዘና ለእግዚአብሔር ዓላማ እንዳይኖሩ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው ?
- ለእግዚአብሔር ዓላማ እንዳትኖር የሚከለክልህና የተቀራኘህ ነገር ምንድነው?

## ለእግዚአብሔር ደስታ የታቀድህ ነህ

- «ሕይወትህን በሙሉ ለእግዚአብሔር ደስታ መኖር» ፣ ሰዎች «አምልኮን» ከሚረዱበት ሁኔታ እንዴት ነው የሚለየው ?
- ከእግዚአብሔር ጋር መወዳጀት፣ካማንኛውም ወዳጅነት ጋር እንዴት ነው የሚመሳሰለው፣ በምንስ ይለያል ?

- እግዚአብሔር ከአንተ የራቀ በመሰለህ ጊዜ ካገኘኸው ትምህርት ለሌሎች አካፍል።
- የቱነው የሚቀልህ፣ በግል ወይስ በጉባዔ ማምለኩ? በየትኛው የአምልኮ ጊዜ ነው ወደ እግዚአብሔር እንደቀረብክ የሚሰማህ ?
- ቁጣን ለእግዚአብሔር ለመግለጥ ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው ?
- ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ለማስገዛት በምታስብበት ጊዜ የሚያስፈራህ ነገር ምንድነው ?

## ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተሠርተሃል

- «ለኢየሱስ ቃል እንደምንገባ ሁሉ፣ እርስ በርሳችን ቃል መገባባታችን» ሰዎች «ህብረትን» ከሚረዱበት ሁኔታ እንዴት ነው የሚለየው?
- ሌሎች አማኞችን እንዳንወዳቸውና እንዳንጠነቀቅላቸው የሚያግዱን ነገሮች ምንድናቸው ?
- ፍላጎቶችህን፣ መጎዳትህን፣ ፍርሃትህንና ተስፋዎችህን ለሌሎች እንድታካፍል ነገሮችን ቀላል የሚያደርግልህ ምንድነው?
- ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይመጡ የሚያቀርቧቸው የተለመዱ ምክንያቶች ምንድናቸው፣ ለምክንያቶቹ ማስተባበያነት የምትሰጣቸው መልሶችስ ምንድናቸው?
- ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን ህብረት ለመከላከልና ለማሳደግ ቡድናችን ምን ሊያደርግ ይችላል?
- ወደ ነበራችሁ ህብረት ልትመልሰው የምትፈልገው ሰው አለ? ለዚህ ጉዳይ እንድንጸልይልህ ትፈልጋህ?

## ክርስቶስን ለመምሰል ነው የተፈጠርከው

- «ክርስቶስን መምሰል» ብዙ ሰዎች ከሚያስቡት «ደቀመዝሙርነት» የሚለየው እንዴት ነው?
- አማኝ ከሆንክ ወዲህ በሕይወትህ ላይ ያየሃቸው አንዳንድ ለውጦች ምንድናቸው? ሌሎች ሰዎችስ ምን ለውጥ አሳዩህ?
- እስከ ዛሬ ዓመት ድረስ እንዴት ነው ይበልጥ ክርስቶስን ለመምሰል የምትፈልገው? ወደምትፈልገው ግብ ለመድረስ ዛሬ ምን ልታደርግ

ትችላለህ?

- በመንፈሳዊ እድገትህ ውስጥ ዕድገቱ አዝጋሚ ከመምሰሉ የተነሣ በትዕግሥት መጠበቅ የሚኖርብህ የቱን ነው?
- እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሕይወትህ እንድታድግ ሊረዳህ እንዴት ነው በበሽታ ወይም በችግር የተጠቀመው?
- ምን ጊዜ ነው ለፈተና በጣም የምትጋለጠው? ፈተናን ለማሸነፍ ይበልጥ የጠቀሙህ የትኞዎቹ እርምጃዎች ናቸው?

## የተበጀኸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው

- «በመልክስልህ መጠቀም» ብዙ ሰዎች ከሚያስቡት አገልግሎት የሚለየው እንዴት ነው?
- በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሌሎችን ለማገልገያነት ልትጠቀምበት የምትወደው ምንድነው?
- ስለአሳለፍከውና በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎችን ለመርጃነት እግዚአብሔር ስለተጠቀመበት አስከፊ ልምምድ አስብ::
- እራሳችንን ከሌሎች ጋር ማነፃፀሩ፣ ልዩ የሆነ መልክስላችንን ሙሉ በሙሉ ከማዳበር የሚያግደን እንዴት ነው?
- ድካም በተሰማህ ጊዜ፣ እንዴት ነው የእግዚአብሔር ኃይል በአንተ ሲገለጥ ያየኸው?
- የትንሹ ቡድናችን ወይም ክፍል እያንዳንዱ አባል የአገልግሎት ሥፍራ እንዲያገኝ እንዴት ነው የምንረዳው? የቤተክርስቲያናችንን ቤተሰብ ለመርዳት ቡድናችን ምን ሊያደርግ ይችላል?

## የተሠራኸው ለተልዕኮ ነው

- ሰዎች «የወንጌል አገልግሎት» የሚለውን ቃል ሲሰሙ የሚያሳዩዋቸው ወይም ከሌሎች የሚተላለፋባቸው ፍርሃቶች ምንድናቸው? መልካሙን የምሥራች ቃል ለሌሎች እንዳታካፍል የሚከለክልህ ምንድነው?
- ከዓለም ጋር እንድትካፈለው እግዚአብሔር የሰጠህ የሕይወት መልእክት ክፍል ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
- የቡድንህ አባላት ሊጸልዩለት የሚገባን አንድ የማያምን ወዳጅህን ስም

ነገራቸው፡፡

- ታላቁን ተልዕኮ ለመፈጸም ቡድናችን በጋራ ምን ሊያደርግ ይችላል?
- ይህን መጽሐፍ በጋራ ማንበብህ እንዴት ነው የሕይወትህን ዓላማ ትክክለኛ አቅጣጫ ያስያዘው? በጣም የረዱህ አስተውሎቶች ምንድናቸው?
- ሕይወት ለዋጭ የሆነውን የዚህን መጽሐፍ መልዕክት ታካፍለው ዘንድ እግዚአብሔር ወደ አእምሮህ የሚያመጣው ሰው ማነው?